# አላህን ፈለግሁት ኢየሱስን አገኘሁት

ዶ/ር ነቢል ቁሬሺ

ወርሃ ሕዳር 2009 ዓ.ም.

ይህ መጽሐፍ "Seeking Allah Finding Jesus: A Devout Muslim Encounters Christianity"በሚል ርዕስ ከተጻፈው መጽሐፍ ላይ በደራሲው ፈቃድ የተተረጎመ ነው፡፡

# አስተዋፅዎ

**መቅድም በሊእስትሮቤል ....................................................... 6**

**መግቢያ ............................................................................. 8**

**መንደርደርያ ፡ አላህን መፈለግ................................................... 9**

## ክፍል አንድ ፡ ወደ ጸሎት ተጠሩሁ

1. የአባቶቼ ጸሎት ..................................................................... 21
2. የእናት እምነት....................................................................... 25
3. የአራት ሰዎች ማሕበር................................................................ 29
4. ፍፁም የሆነው መጽሐፍ ............................................................. 32
5. የነቢዩ ታሪኮች ...................................................................... 37
6. በጸሎት ሥርኣት የሚገኝ ፅድቅ ...................................................... 47
7. በእስልምና ውስጥ የሚገኝ ክፍፍል ................................................... 52
8. ፍኖተ ሸሪኣ .......................................................................... 59
9. የታማኝ ሰው ህልሞች ................................................................ 65
10. የበረከት ወር ......................................................................... 71

## ክፍል ሁለት ፡ የእስልምና አምባሳደር

11. ሦስተኛው ባሕል ..................................................................... 78
12. በምዕራብ የሚኖሩ ሙስሊሞች.......................................................... 83
13. ራስን መሳት እናመተካካት............................................................ 89
14. አብ ከኢየሱስ ይበልጣል.............................................................. 96
15. የሰማይ ደጆችና የገሃነም ነበልባሎች.................................................. 102
16. አንጡራ ትውፊት ..................................................................... 108
17. በሰማይ ውስጥ የሚታዩ ምልክቶች.................................................. 113
18. ክብርና ሥልጣን....................................................................... 118

19. የሰላም ሃይማኖት......................................................................125

## ክፍልሦስት ፡አዲስ ኪዳን ሲፈተሽ

20. ወንድማማች መሆን..................................................................132
21. ዓይኖቼ ተከፈቱ.......................................................................137
22. የጽሑፎች ዝግመተ ለውጥ ..........................................................144
23. ተዓማኒነትን እንደገና መፈተሽ ......................................................151

## ክፍል አራት ፡ ዋናው ነገር

24. የሊትመስ ወረቀት ፈተና ..............................................................159
25. ራስን የመሳት መላምት በመስቀል ሲጠረቅ .........................................166
26. በቤተክርስቲያን የተገኘ ሙስሊም....................................................176
27. ሙግት ስለክርስቶስ ትንሣኤ ...........................................................185

## ክፍል አምስት ፡ ኢየሱስ ሟች መሲህ ወይንስ መለኮታዊ ወልደ እግዚአብሔር?

28. ዘረመልና ኢየሱስ......................................................................195
29. ኢየሱስ የአናፂዎች ፈጣሪ ............................................................200
30. መለኮታዊ የሰው ልጅ ...............................................................207
31. አስተምህሮተ ጳውሎስና ቀዳሚው ኢየሱስ ..........................................214

## ክፍል ስድስት ፡ ስለ ወንጌል የቀረበ ሙግት

32. ሥላሴ ....................................................................................221
33. ሥላሴን ማሰላሰል.......................................................................224
34. ደህንነት በሚዛን ላይ ..................................................................229
35. ወንጌል ሲፈተሽ.........................................................................237

## ክፍል ሰባት ፡ ስለ መሐመድ እውነተኛው ነገር

36. መሐመድን በአጉሊ መነፅር............................................................242

37. እንከን አልባው ነቢይ ............ 251
38. ከመጋረጃው በስተጀርባ የሚገኝ ሽብር ............ 256
39. መሐመድ ረሱል አላህ? ............ 262

## ክፍል ስምንት ፡ የቁርአን ቅድስና

40. የቁርአን ሙግት ............ 266
41. ቁርአን፣ሳይንስና አስተምህሮተ ቡካይሌ ............ 270
42. ሐዲስ እና የቁርአን ታሪክ ............ 275
43. ቀኝ እጆቻቸው የያዙትን ሁሉ ............ 282

## ክፍል ዘጠኝ፡ እምነት በጥርጣሬ ሲተካ

44. አመክንዮና መገለጥ ............ 288
45. መስቀሉን መከተል የሚያስከፍለው ዋጋ ............ 291
46. እኔ ቅርብ ነኝ፤ ፈልጉ ታገኛላችሁ ............ 295
47. በመስቀሎች የተሞላው መስክ ............ 297

## ክፍል አሥር፡ በእግዚአብሔር እጅ መመራት

48. ህልሞችን መተርጎም ............ 302
49. ጠባቡ በር ............ 311
50. ከመስጊድ የሚያስወጣው ቀጥተኛ መንገድ ............ 315
51. የኀዘን ጊዜ ............ 318
52. ቃሉ ይናገራል ............ 322
53. ኢየሱስን ማግኘት ............ 325
የነገሩ ፍፃሜ ............ 330
ማስታወሻዎች ............ 334

# መቅድም

እኔና የአገልግሎት ባልደረባዬ ማርክ ሚተልበርግ ስለ ሙስሊሞች እምነት ክርስቲያኖችን ለማሰልጠን *እስልምናን መረዳት* የሚል ብሔራዊ የሥልጠና መርሃ ግብር ባዘጋጀንበት ወቅት እንድንጋብዘው ወደ አእምሯችን የመጣው የመጀመርያው ሊቅ ነቢል ቁሬሺ ነበር፡፡

በኅክምና፣ በመንፈሳዊ ጉዳዮችና በዓቀበተ እምነት ዲግሪዎች ያሉት ከእስልምና ወደ ክርስትና የመጣው ይህ ወጣት የጠለቀ እውቀትና ጥሩ የንግግር ክህሎት እንዳለው እናውቅ ነበር፡፡ በሥልጠናው ወቅትም እስልምናን በሰፊው የሚያስቃኙ ትምህርቶችን ከመስጠት በተጓዳኝ ከእስልምና ወደ ክርስትና ያደረገውን አስቻጋሪ ጉዞ መስክሯል፡፡

ከሁሉም በላይ መደመምን የፈጠረብኝ ደግሞ ከሥልጠናው በኋላ የተከሰተው ነገር ነው፡፡ ነቢልና ሌሎች ተሳታፊዎች ጥያቄዎችን ለመመለስ ወደ ቤተ ክርስቲያን አውደ ምህረት ሄደው ነበር፡፡ አንዲት እንስት ወደ ማይክሮፎኑ ተጠግታ "እንደ አንድ ሙስሊም ስለ መሐመድ ማወቅ የሚገባኝ ነገር ምንድነው?" የሚል ጥያቄ አቀረበች፡፡ በሥልጠናው ወቅት የሰማችው ነገር በውስጧ ግጭትን የፈጠረ ይመስለኛል፡፡

ነቢል ከዚያ ቀደም ከማውቀው በተለየ ሁኔታ እጅግ የጠለቁ ሐሳቦችን ማንሸራሸር ጀመረ፡፡ እጅግ ጥልቅ ከሆነ ግንዛቤና ልምድ የመነጩ ሐሳቦችን በመተንተን ሃይማኖቱን በሚገባ ያጠና ጠንካራ ሙስሊም ብቻ ሊገነዘባቸው የሚችላቸውን ጉዳዮች ይናገር ነበር፡፡ እርሱና ሌሎች ምሑራን ስለዚያች ሴት አጥብቀው ይጸልዩ በነበረበት ሰዓት ሲታይበት የነበረው የርህራሄ መንፈስ ልቤን በእጅጉ ነካው፡፡እርሱ ራሱ እስልምናን መጠራጠር ሲጀምር ያሳለፈውን ትግል አስታውሶ ይመስለኛል፡፡

ነቢልን የተዋወቅሁት በጓደኞቼ በኩል ነበር፡፡ በዚያን ምሽት ከዚያ ቀደም ለነቢል የነበረኝ አክብሮትና አድናቆት በእጅጉ ጨመረ፡፡ በቀጣዮቹ ገፆች ውስጥ ነቢል እውነትን

በቅን ልቦና ሲፈልግ ሳለ ያገኛቸውን አዳዲስ መረጃዎችና ልዕለ ተፈጥሯዊ ጉዳዮች ይተርክላችኋል፡፡ እኔ እንዳወቅሁት ሁሉ እናንተም ታውቁት ዘንድ ጉጉት አድሮብኛል፡፡

በእስልምና ባሕል ውስጥ ስር ሰዶ ያደገ ሰው የእግዚአብሔርን እውነተኛ ማንነት ለማወቅ ጥረት በሚያደርግበት ወቅት ምን ያህል ዋጋ እንደሚከፍል ትገነዘባላችሁ፡፡ ይህ መጽሐፍ ቤተሰብ፣ ጓደኞችና ሃይማኖት የተጋመዱበት ግለ ታሪክ ሲሆን ስለ እስልምና ያላችሁን ዕውቀት በማሳደግ የሙስሊሙን ዓለም በተለየ መንገድ እንድታውቁት የሚያስችላችሁን ግንዛቤ ያስጨብጣችኋል፡፡

ክርስቲያን ከሆናችሁ ሙስሊሞችን ለመውደድና በወንጌል ለመድረስ የሚያስችላችሁን አዲስ አስተሳሰብ ያጎናፅፋችኋል፡፡

ሙስሊም ከሆናችሁ ደግሞ ቅድመ ማስጠንቀቂያ ልሰጣችሁ እፈልጋለሁ፡፡ አንኳር የሆኑት የእምነታችሁ አዕማዳት ጥልቅ በሆኑ ታሪካዊ እውነታዎችና ምክንያታዊ አስተሳሰቦች ይፈተሻሉ፡፡ ነገር ግን በተከፈተ ልብ የምታነቧቸው ከሆነ ነቢል የተማረውን ነገር ለናንተ በማካፈል መንፈሳዊ ጉዟችሁን ሊደግፍ የተነሳ ወዳጃችሁ መሆኑን እንደምትረዱ ጥርጥር የለኝም፡፡

እግዚአብሔር ነቢልን በዚህ ጎዳና እንዲጓዝ ያደረገው ላልተጨበጠ ዓላማ ሳይሆን እርሱንና የታሪኩን አንባቢያን በእጅጉ ስለወደደ እንደሆነ በሚገባ ተረድቻለሁ፡፡ የእውነትን የከበረ ዋጋ የተረዱና እግዚአብሔርን በግል የማወቅ ጥማት ያላቸው ወገኖች ሁሉ ይህንን መጽሐፍ ትኩረት ሰጥተው ሊያነቡት ይገባል፡፡

አንብቡትና እግዚአብሔር የነቢልን ታሪክ ተጠቅሞ የገዛ ሕይወታችሁን እንዴት እንደሚቀርፀው ዕዩት፡፡

\- ሊ እስትሮቤል

*The Case for Christ* እና*The Case for Faith*መጻሕፍት ደራሲ

# መግቢያ

ውድ ወዳጆቼ ሰላም ለናንተ ይሁን!

በተከታዮቹ ገፆችውስጥ የግል ሐሳቤና ከኀሊና የማይጠፉ ትውስታዎቼ ሰፍረዋል፡፡ ልቤ ቀለም ሆኖ በወረቀት ላይ ፈስሶ ትመለከታላችሁ፡፡ ይህንን መጽሐፍ ስታነቡ ሳላችሁ የቤተሰቤ አባልና ጓደኞቼ ትሆናላችሁ፡፡ ወጣት ሆኜ በእስልምና ውስጥ ባሳለፍኳቸው ጣፋጭ ጊዜያት እንዲሁም ትውልደ አሜሪካዊ ሙስሊም በመሆኔ ምክንያት በተፈጠረብኝ የባሕል ግጭት ውስጥ አብራችሁኝ በመግባት ትካፈላላችሁ፡፡ ክርስትና በሙስሊም ዕይታ ምን ያህል አሰናካይ እንደሆነ፤ ከወንጌል ታሪካዊ እውነታዎች ጋር ያደረግሁትን ትግልና ቀስ በቀስ የእስልምናን ድብቅ እውነታዎች በመረዳቴ ምክንያት የቆምኩበት መሠረትሲናጋ በኔ ቦታ ሆናችሁ ትመለከታላችሁ፡፡ የግል ማስታወሻዎቼን ስታነቡ ሳላችሁ የሰማዩ አባታችን በራዕዮችና በህልሞች እንዲሁም በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ውስጤን በመለወጥ ወደ ልጁ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት እንደመራኝ ታስተውላላችሁ፡፡ይህንን ምስክርነት በማንበብ በሕይወት መንገድ ላይ ከእኔ ጋር በመጓዝ በጥልቀት ታውቁኛላችሁ፤ እውነተኛ ጓደኞሞችም እንሆናለን፡፡

## የመጽሐፉ ዓላማ

ነገር ግን ይህ መጽሐፍ ከግል ምስክርነቴ ያለፈ ነው፡፡ ሦስት ዓላማዎችን ታሳቢ አድርጎ የተዘጋጀ ነው፡፡

1. ግድግዳዎችን በማፍረስ ሙስሊም ያልሆነ ሰው የሙስሊሞችን ልብና አእምሮ በመረዳት የውስጥ ዕይታ እንዲኖረው ማድረግ፡፡
   የቢሊዮኖችን አእምሮ ሰቅዞ የያዘውን የእስልምናን ምትሃታዊ ውበት ነባራዊ እውነታዎችን ብቻ በማካፈል ማስረዳት ያዳግታል፡፡ ነገር ግን እኔ ወዳለሁበት

ዓለም ዘልቃችሁ በመግባት የሙስሊም ባልንጀራችሁን ውስጠት ተረድታችሁት እንደራሳችሁ አድርጋችሁ ትወዱት ዘንድ ጸሎቴ ነው፡፡ የመጽሐፉ የመጀመርያዎቹ ሁለት ክፍሎች ለዚሁ ዓላማ ተብለው የተዘጋጁ በመሆናቸው ምክንያት ለእስልምና የሚወግኑ መስለው ከታዩዋችሁ ለቀደመው እምነቴ በወቅቱ የነበረኝን ፍቅር ለማሳየት ብቻ የታለሙ መሆናቸውን ተረዱልኝ፡፡

2. የወንጌል ማስረጃ ከእስልምና ማስረጃ ጋር ሲስተያይ ምን ያህል የላቀ እንደሆነ በሚያሳዩ እውነታዎችና እውቀት እናንተን ማስታጠቅ፡፡

   ታሪክ ለወንጌል መሠረታዊ አዕማድ፤ ማለትም ኢየሱስ በመስቀል ላይ ስለመሞቱ፣ ከሞት ስለመነሳቱና አምላክ መሆኑን ስለመናገሩ ፅኑ ምስክርነት ይሰጣል፡፡ በዚህ ሁኔታ ታሪክ በእስልምና መሠረታዊ አዕማድ ማለትም በቁርአን መለኮታዊነትና በመሐመድ ነቢይነት ላይ የተመሠረተውን የእኔን እስላማዊ ነገረ መለኮት ተገዳድሯል፡፡ እስልምናን በጥንቃቄ ካጠናሁ በኋላ የደረስኩበት እውነታ የኔን ዓለም ከስር መሠረቱ አናውጦታል፡፡ቁርአንም ሆነ መሐመድ ስለ እግዚአብሔር እውነተኛውን ነገር ስለማስተማራቸው ለማመን የሚያስችል ምንም ዓይነት የረባ ምክንያት የለም፡፡ ይህ መጽሐፍ በዓመታት መካከል የተማርኳቸውን እውነታዎችና የመከራከርያ ነጥቦች ሁሉ ለመዘርዘር በእጅጉ የማይበቃ ቢሆንም ከክፍል ሦስት ጀምሮ እስከ ክፍል ስምንት ድረስ የሚገኙት ገፆች የተማርኳቸውን ነገሮችና እንዴት ከእስልምና ወደ ኢየሱስ እንደመሩኝ በመጠኑ ያሳያሉ፡፡

3. ከወንጌል ጋር ትንቅንቅ ውስጥ የገቡ ሙስሊሞች የሚከፍሉትን ዋጋና ጥርጣሬያቸውን ጨምሮ በውስጣቸው የሚካሄደውን ትግል መግለጥ፡፡

   በክፍል ዘጠኝና አስር ውስጥ እንደምትመለከቱት በዚህ ትግል መካከል ነው እግዚአብሔር ሰዎችን በራዕዮችና በህልሞች የሚያገኘው፡፡

## ***ይህ መጽሐፍ እንዲህ ይነበብ***

***መንደርደርያ፡፡*** ከመጀመራችሁ በፊት ይህንን ማንበባችሁን እርግጠኞች ሁኑ!

***የቃላት መፍቻ፡፡*** ይህንን መጽሐፍ ባነበባችሁ ቁጥር የሚገጥሟችሁ ብዙ እስላማዊ ቃላት ይኖራሉ፡፡ በጽሑፉ ውስጥ መጀመርያ በተጠቀሱ ጊዜ ፍቺያቸውን ሰጥቻለሁ፡፡

***የሊቃውንት አስተዋፅዖዎች፡፡***በእውነቱ ከሆነ እነዚህ የመጽሐፉ ስውር ዕንቁዎች ናቸው፡፡ በየክፍሉ መጨረሻ ላይ ወደ ሊቅ አስተዋፅዖ የሚወስድ አስፈንጣሪ ይገኛል፡፡ ዕውቅ ከሆኑ ወንጌላውያን ጀምሮ ምጡቅ የቁርአን ሊቃውንት እስከሆኑት ድረስ የሚገኙ ሙስሊሞችን ከልባቸው የሚወዱና የወንጌል ሸክም ያላቸው የተማሩ ሰዎች ልሒቃዊ እውቅናቸውን እንዲሁም ከልምድ የመነጨ አስተያየታቸውን በመለገስ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የራሳቸውን ድምፅ አክለዋል፡፡ በእርግጥ ከነዚህ ሊቃውንት መካከል ሦስቱ ወደ ኢየሱስ ባደረግሁት ጉዞዬ ውስጥ የግል አስተዋፅዖ ነበራቸው፡፡ ተያያዥ ከሆነው ክፍል በማስከተል በቀጥታ እያንዳንዱን አስተዋፅዖ ታነቡ ዘንድ አበረታታችኋለሁ፡፡ የአበርካቾቹ ዝርዝር የሚከተለው ነው፡

- አብዱ ሙሬይ፡- የሕግ አዋቂ፣ ዓቃቤ እምነትና ሺኣ ሙስሊም የነበሩ
- ማርክ ሚተልበርግ፡- እውቅ ደራሲና ዓለም አቀፍ ወንጌላዊ
- ዶ/ር ዳንኤል ቢ. ዋላስ፡- የአዲስ ኪዳን ጥናቶች እጅግ ዕውቅ ፕሮፌሰር
- ዶ/ር ማይክ ሊኮና፡- የነገረ መለኮት ተባባሪ ፕሮፌሰርና የታሪክ ሊቅ
- ጄ. ኤድ ኮሞዜውስኪ፡- የመጽሐፍ ቅዱስና የነገረ መለኮት ጥናቶች ፕሮፌሰር
- ሮበርት ኤም. ቦውማን ጁንየር፡-ተመራማሪና ደራሲ
- ዶ/ር ዴቪድ ውድ፡- ፈላስፋና የአክትስ 17 ዓቀበተ እምነት አገልግሎት ዳይሬክተር

- ዶ/ር ኪዝ ስሞል፡- የቁርአን እጅ ጽሑፎች ሊቅና በኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ አማካሪ
- ዶ/ር ጌሪ ሀበርማስ፡- በሊበርቲ ዩኒቨርሲቲ የፍልስፍናናየሥነ መለኮት ትምህርት ክፍሎች ሊቀ መንበር እንዲሁም የታሪክ ሊቅ
- ጆሽ ማክዱዌል፡- ዓለም አቀፍ ወንጌላዊና ዓቃቤ እምነት

***ማስታወሻ ስለ ትረካዊ ግለ ታሪክ፡፡*** ዘመነ አጎዝ ላይ በመገኘታችን ምክንያት ሰዎች ትረካዊ ግለ ታሪክ ፍፅምና እንዲኖረው ይጠብቃሉ፡፡ ነገር ግን ይህ በእጅጉ የተሳሳተ ነው፡፡ ትረካዊ ግለ ታሪክ የሚያካፍላቸውን ታሪኮች በተመለከተ በባሕርዩ የተወሰነ ነፃነት ሊኖረው ያስፈልጋል፡፡ እባካችሁን ልክ እንደ ካሜራ ያለ ፍፅምናን አትጠብቁ! የዚህ መጽሐፍ አካሄድ እንደዚያ አይደለም፡፡ ያንን መስፈርት ለማሟላት ሃያ ሁለት ዓመታት ያህል የሚረዝም ቪድዮ መሆን ይኖርበታል፡፡ ይህ ደግሞ እናቴን እንኳ አሰልችቷት ሊያስነባት ይችላል፡፡

በትዕምርተ ጥቅስ ያስቀመጥኳቸው ቃላት ግርድፍ ቅርርብ ናቸው፡፡ ጥቂቶቹ እንዲያውም በተለያዩ ጊዜያት የተደረጉ ምልልሶችን በመጭመቅ የሚወክሉ ናቸው፡፡ አንዳንዴም ትርክቶች ከርዕሶች ጋር አብረው ይሄዱ ዘንድ የጊዜ ቅደም ተከተላቸው ተዛብቶ እንዲቀመጡ ተደርጓል፡፡ አልፎ አልፎ ደግሞ በምልልሱ ወቅት የነበሩ ሰዎች ለግልፅነት ሲባል በትረካው ውስጥ ሳይካተቱ ቀርተዋል፡፡ እነዚህ ሁሉ ስልቶች በትረካዊ ግለ ታሪኮች ውስጥ የተለመዱ ናቸው፡፡ ለሰው ልጅ የትውስታ ዘዴም እንግዳ አይደሉም፡፡ እባካችሁን ይህንን መጽሐፍና በውስጡ የሚገኘውን ግለ ታሪክ በዚ መረዳት አንብቡልኝ፡፡

## ጸሎት

ይህንን መጽሐፍ ስታነቡ ብቻ ሳይሆን የተማራችሁትን ነገር ስትተገብሩ እንዲሁም ጌታንና ሕዝቡን ስታገለግሉ ሳላችሁም ጭምር ባርኮቱ እንዲበዛላችሁ ጸሎቴ ነው፡፡ ከምንጠይቀውና ከምንጠብቀው በላይ እጅግ አብዝቶ ማድረግ የሚችለው ጌታ አምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ ለሚያምኑትና እርሱን ለሚከተሉት ሰዎች የተሰጠ የዘለዓለም ሕይወት የሆነውን አስደናቂ እውነት ለማስፋፋት በውስጣችሁ ይሥራ፡፡ ቤተሰቤንና ጓደኞቼን ጨምሮ የጠፉትንና እርሱ የሚያሻቸውን መድረስ ትችሉ ዘንድ እናንተን ተጠቅሞ መላውን ዓለም ይንካ፡፡ ማንነታችንን በየጊዜው የፀጋና የእውነት ምንጭ ወደሆነው እርሱን ወደመምሰል በመለወጥና ተዓምራዊ የሆነውን መንፈሱን በማፍሰስ ይህንን ይፈፅም፡፡ በኢየሱስ ስም እጸልያለሁ፣ አሜን፡፡

# መንደርደርያ

## አላህን መፈለግ

በተሰበረ ልብ ሆኜ ሰፊ በሆነው የሙስሊሞች የጸሎት አዳራሽ ውስጥ በአምላኬ ፊት ተደፋሁ፡፡ ባለፉት ጥቂት ዓመታት የኔ ንፅረተ ዓለም፣ የማውቀው ነገር ሁሉ ቀስ በቀስ ተፈረካከሷል፡፡ ይህ ዕለት ደግሞ የኔ ዓለም ሙሉ በሙሉ የተደረመሰበት ዕለት ነው፡፡ በፍርስራሹ ውስጥ ተቀምጬ አላህን ፈለግሁት፡፡

እርጥበታማ የሆነው የዝናባማው ወቅት ምሽት ቦታውን እየተረከበ በነበረበት ሰዓት እየራቁ የሚሄዱ ኮቴዎች በመስጊዱ አዳራሽ ውስጥ ይስተጋባሉ፡፡ ሌሎች ጸላዮች ወደየቤቶቻቸውና ቤተሰቦቻቸው እየተመለሱ ነበር፤ ነገር ግን እኔ በሐሳብ ማዕበል እየናወዝኩ ነው፡፡ እያንዳንዱ የአካል ክፍሌ እርስ በርሱ እየተፋጨ ነው፡፡ በግንባሬ ወለሉ ላይ ተደፍቼ ልቤም የደረቴን አጥንቶች አልፋ ልትወጣ እየታገለች ከንፈሮቼ በፀጉራማው ምንጣፍ ላይ የሚያንሾኳሹኳቸውን ቃላት አእምሮዬ ያውጠነጥን ነበር፡፡

እነዚህ አዲስ ቃላት አልነበሩም፡፡ እነዚህን የአረብኛ ቃላት በቀን 132 ጊዜያት እንዳነበንብ የተማርኩት ስሜን እንኳ ከማወቄ በፊት ነበር፡፡ *ሰጅዳ* ወይም ሙስሊሞች አላህን እያወደሱ በፊቱ የሚሰግዱበትን *ሥርአት* እየተገበርኩ ነበር፡፡ ከዚህ ቀደም ቃላቱን ቀለል አድርጌ ብናገራቸውም ዛሬ ግን እንደርሱ አልሆነም፡፡ ከንፈሮቼ የሸመደድኳቸውን ቃላት ቢናገሩም አእምሮዬ ስለ ፈጣሪዬ እንደማውቃቸው የማስባቸውን ነገሮች ሁሉ መጠራጠር ተያይዟል፡፡

*ሱብሃነ ረቢ አል-ዐላ፡፡*

*ታላቁ ጌታዬ የተመሰገነ ይሁን፡፡*

“ጌታዬ የተመሰገነ ይሁን… ጌታዬ ማነው? ጌታ ሆይ አንተ ማነህ? የአባቶቼ አምላክ አላህ ነህን? ሳመልክህ የኖርኩት አምላክ ነህን? አባቴ ሲያመልክህ የኖረው አምላክ ነህን? በእውነት መሐመድን[1] ﷺ እንደ መጨረሻ ነቢይና ቁርአንን እንደመመርያ የላከኸው አንተ ነህን? አንተ የእስልምና አምላክ አላህ ነህ፣ አይደለም እንዴ? ወይም አንተ…”ከአንደበቴ አፈትልኮ ሊወጣ የነበረውን ክህደት በመታገል ገታሁት፡፡ ነገር ግን ክህደት ነው ያልኩት ነገር እውነት ቢሆንስ?

“ወይም አንተ ኢየሱስ ነህን?”

የገሃነም መውረጃ መንገድ መጀመሬን አእምሮዬ ስለነገረኝ ልቤ ምቷንያቆመች መሰለኝ፡፡ “አላህ ሆይ ሰው ካንተ እኩል ሆኗል ብዬ በፍፁም አልናገርም! እባክህን እንደርሱ ተናግሬ ከሆነ ይቅር በለኝ፤ ምክንያቱም እንደርሱ ለማለት ፈልጌ አይደለምና፡፡ ማንም ሰው ካንተ እኩል ሊሆን አይችልም፡፡ አንተ ከፍጥረት እጅግ የላቅህ ነህ፡፡ አላህ *ሱብሃነ ወታዓላ*[2]ሁሉም ላንተ ይሰግዳል፡፡”

“ለማለት የፈለግሁት አላህ ሆይ አንተ ከሃሊ ኩሉ ስለሆንክ ብትፈልግ የፍጥረትን ባሕርይ ተላብሰህ መምጣት ትችላለህ፡፡ ወደዚህ ዓለም ገብተሃልን? ሰው ሆነሃልን? ያ ሰው ደግሞ ኢየሱስ ይሆንን?

አላህ ሆይ መጽሐፍ ቅዱስ ትክክል ሊሆን አይችልም፣ ይችላል እንዴ?”

በሰጅዳ ከንፈሮቼ እየጸለዩ ባለበት በዚያው ጊዜ አእምሮዬ ያለ እረፍት ይሟገተኝ ነበር፡፡ ሰጅዳው ከመጠናቀቁ በፊት የአረብኛው ሐረግ ሁለቴ መደገም ይኖርበታል፡፡

*ሱብሃነ ረቢ አል-ዐላ፡፡*

ታላቁ ጌታዬ የተመሰገነ ይሁን፡፡

“ነገር ግን እጅግ ታላቅ የሆነው አላህ ወደ ዓለም ገብቷል ብሎ መናገር እንዴት ይቻላል? ይህ ዓለም ቆሻሻና በኃጢአት የተሞላ ነው፡፡ ክብርና ምስጋና ሁሉ ለሚገባው ለእርሱ

የሚመጥን ቦታ የለም፡፡ ታላቅና እጅግ የከበረው ፈጣሪ አምላክ በሴት ማህፀን አልፎ ወደዚህ ዓለም መጥቷል ብዬ እንዴት ማሰብ እንኳ እችላለሁ? *አዑዙ ቢላህ!*[3] ይህ አስፀያፊ ነው! መብላት፣ መድከም፣ ማላብ፣ መድማትና በመጨረሻም በመስቀል ላይ መቸንከር፡፡ ይህንን ማመን አልችልም፡፡ አምላክ ከዚህ ጋር ሊነፃፀር የማይችል ክብር ነው የሚገባው፡፡ ግርማው ከዚህ እጅግ የላቀ ነው፡፡"

"ነገር ግን ግርማው የልጆቹን ያህል ለእርሱ አስፈላጊ ባይሆንስ?"

*ሱብሃነ ረቢ አል-ዐላ፡፡*

ታላቁ ጌታዬ የተመሰገነ ይሁን፡፡

"በእርግጥ ለእርሱ አስፈላጊዎች ብንሆንም አላህ እኛን ይቅር ለማለት መሞት አያስፈልገውም፡፡ አላህ ሁሉን ቻይ ስለሆነ ከፈለገ በቀላሉ ይቅር ሊለን ይችላል፡፡ እርሱ *አል-ገፉር* እና *አል-ረሂም* ነው![4]ይቅርታው ከማንነቱ ይመነጫል፡፡ ወደዚህ ዓለም በመምጣት በመስቀል ላይ መሞት ከኔ ኃጢአት ጋር በምን ይገናኛል? እርሱ ሞቶ ከነበረ ዓለምን ይገዛ የነበረው ማን ነበር? *ሱብሃነ አላህ!*እርሱ ኢ-ሟቲ ነው! ይህ የክብሩ አካል ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት ስላቆች አያስፈልጉም፡፡ ዙፋኑ ላይ ተቀምጦ ይቅር ሊል ይችላል፡፡

ነገር ግን አላህ ዝም ብሎ በግብታዊነት ይቅር የሚል ከሆነ እንዴት ፍትሃዊ ሊሆን ይችላል? አምላክ ግብታዊ አይደለም፡፡ እርሱ ፍፁም ፃድቅ ነው፡፡ በግብታዊነት ይቅር የሚል ከሆነ እንዴት ፍትሃዊ ሊሆን ይችላል? ‹ከፈለገ ዝም ብሎ ይቅር ሊለን› አይችልም፡፡ የኃጢአቴ ቅጣቱ መከፈል ይኖርበታል፡፡"

ከወለሉ ቀና ብዬ ተረከዜ ላይ በመቀመጥ *ተክቢር* አልኩኝ፡፡

*አላሁ አክበር፡፡*

አላህ ታላቅ ነው፡፡

“አምላኬ ሆይ አንተ በእውነት ታላቅ መሆንህን አውቃለሁ ነገር ግን ቅዱስ ቁርኣን የሚያስተምራቸው አንዳንድ ነገሮች ከታላቅነት የራቁ ናቸው፡፡ አላህ ሆይ ይህንን ጉዳይ መረዳት ተስኖኛል፡፡ እባክህን እዘንልኝ፡፡ አንተን ለመጠራጠር ፈልጌ አይደለም፡፡ ስላለማወቄና መረዳት ስላለመቻሌ ይቅር በለኝ፡፡ አላህ ሆይ እባክህን ይህ ሁሉ ጥርጣሬ እንዳያስቆጣህ እለምንሃለሁ፡፡ የሆነ ያልተረዳሁት ነገር መኖር አለበት፤ ነገር ግን አንተ መልካምና አፍቃሪ ሆነህ ሳለህ በቁርአን ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ ትዕዛዛትን የምትሰጥበት መንገድ ሊኖር አይችልም፡፡ ቃልህ በመሆኑ ምክንያት በየዕለቱ ሳነበውና ስወደው በኖርኩት መጽሐፍ ገፆች ውስጥ ብዙ ሁከትና ጥላቻን አግኝቼበታለሁ፡፡

ምናልባት ቁርአን ቃልህ አለመሆኑን እያሳየኸኝ ይሆንን? ስለ እርሱ የተነገሩኝ ብዙ ነገሮች ሀሰት ሆነው አግኝቼአቸዋለሁ፡፡ ፍፁም እንዳልተለወጠ ተምሬያለሁ ነገር ግን ሐዲስ እና ታሪክ መለወጡን ያሳያሉ፡፡ ስለ ሳይንስና ስለ መፃዒው ጊዜ በሚናገሩ ልዕለ ተፈጥሯዊ እውቀቶች የተሞላ መሆኑን ተምሬያለሁ፤ ነገር ግን በገዛ ዓይኖቼ እንድመለከት በጠየቅሁህ ጊዜ ምንም ላገኝ አልቻልኩም፡፡ ስለ ቁርአንእንደማውቃቸው ያሰብኳቸው ነገሮች ብዙዎቹ እውነት አይደሉም፡፡ እውን ያንተ መጽሐፍ ነውን? እባክህን አላህ እዘንልኝ፡፡

“አንተ ማነህ?”

> *አት-ቲየቱ ሊላሂ፣ ዋስ-ሰላዋቱ ወት-ተዪበቱ፡፡ አሰላሙ ዐለይከ አዩሃ ን-ነቢዩ ወ ራመቱላሂ ወ በረከቱሁ፡፡ አስ ሰላሙ ዐለይነ ወዐላ ዒባዲ ላሂ ሳሊሂን፡፡*
>
> ጥራት፣ ጸሎትና መልካም ነገሮች ሁሉ ለአላህ የተገቡ ናቸው፡፡ የአላህ ነቢይ ሆይ የአላህ ሰላም፣ እዝነትና በረከት ባንተ ላይ ይሁን፡፡ ሰላም በኛና በአላህ አገልጋዮች ላይ ይሁን፡፡

“አላህ ሆይ አመሰግንሃለሁ፡፡ መገዛት ሁሉ ለአንተ ነው፡፡ ነገር ግን ያልተረዳሁት ብዙ ነገር አለ፡፡ በጸሎቴ ሰዓት ለመሐመድﷺ የምናገረው ለምንድነው? ሊሰማኝ አይችልም፡፡

ሞቷል! ነቢዩ ቢሆን እንኳ ወደ ማንኛውም ሰው መጸለይ የለብኝም፡፡ ሰላምን በእርሱ ላይ የምመኘው ለምንድነው? እኔ የእርሱ አማላጅ አይደለሁም፡፡ እነዚህ ቃላት እርሱ በሕይወት በነበረ ጊዜ ሲነገሩ እንደነበር አውቃለሁ፡፡ ነገር ግን ያንተ ታላቅ ነቢይ ማንኛውም ሰው ስለ ሰላም እንዲጸልይለት የሚያስፈልገው ለምንድነው? ዋስትናና ሰላምን ልትሰጠው አትችልም ነበርን? ነቢይ እንደመሆኑ መጠን ሰላምና ዋስትና ከሌለው እኔስ ያለኝ ተስፋ ምንድነው?"

በነቢዩ ትውፊቶችና ቤተሰቦቼ ባስተማሩኝ መሠረት ጣቴን ወደሰማይ በመቀሰር የእምነት መግለጫውን ደገምኩት፡

*አሽሃዱ አላ ኢላ ሀኢለላ ወአሽሃዱ አነ መሐመደን አብዱሁ ወ-ረሱሉሁ፡፡*

ከአላህ በስተቀር ሊመለክ የሚገባው እንደሌለና መሐመድም ባርያውና መልእክተኛው መሆኑን እመሰክራለሁ፡፡

"አላህ ሆይ እባክህን ይቅር በለኝ፡፡ መሐመድ ﷺ ያንተ መልእክተኛ መሆኑን ልመሰክር የምችለው እንዴት ነው? ይህንን ማድረግ ቀላል ነበር! መሐመድ ﷺ በምድር ላይ ከኖሩት ሰዎች መካከል እጅግ የላቀ በመሆኑና የሚስተካከለው ስለሌለ እንድወደው እናቴአስተምራኛለች፡፡ ቸርነቱ የተትረፈረፈ፣ ምህረቱ ወደር የሌለውና ለሰው ልጆች ያለው ፍቅር የማይለካ መሆኑን አስተምራኛለች፡፡ *ኡማ* እስካልተጠቃ ድረስ ጦርነትን እንደማያውጅና የሴቶችን እንዲሁም የሌሎች ጭቁኖችን መብት ለማስከበር እንደተዋጋ ተምሬያለሁ፡፡ እርሱ ፍፁም የሆነ ወታደራዊ መሪ፣ ዋና ተናጋሪና ምሳሌያዊ የሆነ የአላህ ተከታይ ነበር፡፡ እርሱ *አል-ኢንሳን አል-ከሚል፣* ፍፁም የሆነ ሰው ነበር፡፡*ራህመቱ-ሊል ዓለሚን* ለዓለም ሁሉ የተሰጠ የተሠገወ የአላህ ምህረት ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት ሰው *ረሱል አላህ፣* የአላህ መልእክተኛ መሆኑን መመስከር ቀላል ነበር፡፡"

"ነገር ግን አሁን ደርሼ ስለ እርሱ እውነቱን አውቄያለሁ፡፡ ተለባብሶ የሚታለፍ ብዙ ነገር አለ፡፡ ስለመጀመርያው መገለጡ፣ በሲራራ ነጋዴዎች ላይ ስለፈፀመው ጥቃት፣ በዕድሜ ጨቅላ ስለነበረችው ሚስቱ፣ ከዘይነብ ጋር ስለፈፀመው ጋብቻ፣ በእርሱ ላይ

ስለተሠራው አስማት፣ ስለመመረዙ፣ ስለፈፀማቸው ግድያዎች፣ ሰዎችን ስለማሰቃየቱ፣ እና ...”

በቸልታ ላልፈው የማልችለው አንድ ነገር ጋር ስደርስ ሀሳቤ ዝግ አለ፡፡ “የኔ ተወዳጅ ነቢይ የሆነው መሐመድ እንዴት ﷺ ይህ እንዲደረግ ... ሊፈቅድ ቻለ?”

ያ ግፍ በተፈፀመባቸው ሰዎች ቦታ የመሆን ስሜት ተሰምቶኝ አእምሮዬ ከጸሎቱ ሐሳብ ተንሸራተተ፡፡ ቁርአንን ስመረምር ካገኘሁት ነገር ጋር እየታገልኩ ነበር፡፡ እንዴት ይህንን ሊያደርግ ይችላል? በተጠቂዎቹ ቦታ በመሆን ያንን ሰቆቃ አሰብኩት፡፡ ይህ በገዛ ቤተሰቤ ላይ ደርሶ ቢሆን ኖሮስ? የተወራለት የነቢዩ ደግነት ወዴት አለ?

ይህ በሚሆንበት ሰዓት ነህስ በመሰለው የበረሃ ሰማይ ስር ቆሜ ራሴን ተመለከትኩት፡፡ የህዝቤን ሰቆቃ ሳስብ ውስጤ በቁጣ ነደደ፡፡ የደም ጎርፍና ሞት፡፡ ጥቂት ወጣቶች እየተስገበገቡ በሬሳዎች ላይ እየተረማመዱ ወደ መሐመድ ﷺ መጡ፡፡ አረመኔያዊ የሆነውን መሻታቸውን በመናገር መሐመድ ምሪትን እንዲሰጣቸው ጠየቁት፡፡ የመሐመድ ፊት ፈካ ብሎ በላብ ችፍፍ ሲል ታየኝ፡፡ ከአላህ ዘንድ መገለጥን እየተቀበለነበር፡፡[7] ይህንንም ለወታደሮቹ ባሳወቀ ጊዜ በክፉት የተለወሰ ፈገግታ ፊታቸው ላይ ታየ፡፡ በስሜት እየነደዱ ወደየድንኳኖቻቸው ተጣደፉ፡፡ አላህ ተግባራቸውን አፅድቋል፡፡ ለተወሰነ ጊዜ ሁሉም ድምፃቸውን አጥፍተውአደፈጡ፡፡

ድንገት የማልቋቋመው ጩኸት የበረሃውን ሰማይና ነፍሴን ሲተረትር ተሰማኝ፡፡ ጯኺዋ እናቴ ነበረች፡፡

ብንን ብዬ ወደ እውኑ ዓለም ስመለስ ዓይኖቼ ቦግ ብለው ተከፈቱ፡፡ አሁንም በመስጊዱ ውስጥ *የሰላት* ጸሎትእየጸለይኩ ነበር፡፡ በመሐመድ ﷺ ላይ ያደረብኝ የጥላቻ ስሜት ኩነኔን በመፍራት ስሜት ተቀለበሰ፡፡ አላህን የተዳፈርኩት መስሎ ተሰማኝ፡፡ አሁንም ድረስ መሐመድ የእኔ ነቢይ ነው፡፡ አሁንም ለእርሱ ያለኝን ታማኝነት አላጎደልኩም፡፡ ነገር ግን ከልክ አልፌ ሄጃለሁ፡፡

*እንዲህ ሆኜ የምቀጥለው እስከ መቼ ድረስ ነው? አስቶጉፍሩላህ፡፡*[8]

እራሴን ወደ ቀኝ ወደ ግራ ዘንበል ዘንበል በማድረግ የጸሎት ሥርኣቱን ፈጥኜ አጠናቀቅሁኝ፡፡

*አሰላሙ አለይኩም ወራሙቱላህ፡፡*

የአላህ ሰላምና እዝነት በናንተ ላይ ይሁን፡፡

ከአፍታ በኋላ ፊቴን እጆቼ ላይ ድፍት አደረኩት፡፡ዓይኖቼ እምባ አቅርረው ዕይታዬ ተጋረደ፡፡ የተለመደው ጸሎት ተጠናቋል አሁን ደግሞ የልቤን ጸሎትየምጸልይበት ጊዜ ነው፡፡

"አምላኬ ሆይ ሰላምህን እሻለሁ፡፡ እባክህን እዘንልኝና አንተን በማወቅ የሚገኘውን ሰላም ስጠኝ፡፡ አንተ ማን እንደሆንክ አላውቅም ነገር ግን አንተን ሳያውቁ መኖር ትርጉም እንደሌለው ገብቶኛል፡፡ አንተ ይህንን ዓለም ፈጥረሃል፡፡ ትርጉም የምትሰጠውም አንተ ነህ፡፡ አንተ በዓላማ ሰርተኸው ባይሆን ኖሮ ትርጉም የለሽ በሆነ ነበር፡፡

"እባክህን ሁሉን ቻዩ አምላክ ሆይ ማን እንደሆንክ ንገረኝ! አንተንና አንተን ብቻ እሻለሁ፡፡ ልትታደገኝ የምትችለው አንተ ብቻ ነህ፡፡ የተማርኳቸውን ነገሮች ሁሉ በእግሮችህ ስር አስቀምጣለሁ፡፡ ሕይወቴንም በሞላ ላንተ እሰጣለሁ፡፡ፍቃድህ ከሆነ ደስታዬን፣ ጓደኞቼን፣ ቤተሰቤን ወይም ደግሞ ሕይወቴን እንኳ ቢሆን ውሰዳቸው፡፡ ነገር ግን እባክህን አምላኬ ሆይ አንተን ላግኝህ፡፡

የምሄድበትን ጎዳና አብራልኝ፡፡ ምንም ያህል እንቅፋቶች በፊቴ ቢኖሩ፣ ምንም ያህል ጉድጓዶችን መዝለል ቢኖርብኝ ወይም ገብቼ መውጣት ቢኖርብኝ፣ በምንም ዓይነት እሾኽና አሜኬላ መካከል ማለፍ ቢኖርብኝ ግድ የለኝም፡፡ በቀናው ጎዳና ላይ ምራኝ፡፡ እስልምና ከሆነ እንዴት እውነት ሊሆን እንደሚችል አሳየኝ! ክርስትና ከሆነ ማየት እችል

ዘንድ ዓይኖቼን ክፈትልኝ! ውዱ አምላኬ ሆይ እኼድበት ዘንድ መንገድህ የትኛው እንደሆነ አመልክተኝ፡፡”

ለኔ ባይታወቀኝም ከልቤ ስፈልገው የነበረው የእግዚአብሔር ሰላምና ምህረት ሊያገኘኝ ጥቂት ጊዜ ብቻ ቀርቶ ነበር፡፡ ልቤንና የሕይወት መንገዴን እስከወዲያኛው ሊለውጡ የሚችሉ ልዕለ ተፈጥሯዊ የሆኑ ህልሞችና ራዕዮችን ሊሰጠኝ ቀርቦ ነበር፡፡

ክፍል ፩

# ወደ ጸሎተ ተጠራሁ

*የኔ ንፅረተ ዓለም፣ የማውቀው ነገር ሁሉ ...*

# የአባቶቼ ጸሎት

ንጋት አካባቢ በመላው የእስልምና ዓለም ከፍ ያሉ ድምፆች ከአድማሱ ጥግ ብቅ የምትለዋን ፀሐይ ይቀበሏታል፡፡ ከየጣሪያዎቹና ማማዎቹ ላይ *በተክቢር* የሚጀምሩ የሙስሊሞች ዋና እምነቶች በተደጋጋሚ ይታወጃሉ፡፡

*አላሁ አክበር!*

*አሻዱ አን-ላ ኢላሃ ኢል-አላህ!*

*አሻዱ አነ መሐመድ ኡር-ረሱል አላህ!*

አላህ ታላቅ ነው!

ከአላህ በስተቀር አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ!

መሐመድ የአላህ መልእክተኛ መሆኑን እመሰክራለሁ!

**አዛን፡** የሙስሊሞች የፀሎት ጥሪ

ይህ ወደ ጸሎት የሚደረግ ጥሪ፣ **የአዛን** መጀመርያ ነው፡፡ ጥሪው ሙስሊሞች ገና ከእንቅልፍ ከመነሳታቸው ሕይወታቸውን ለአላህ እንዲሰጡ ያስታውሳቸዋል፡፡ በቃል ከተሸመደዱ አልፎ አልፎ ከሚደረጉ ጸሎቶች ጀምሮ ጊዜ ተወስዶ እስከሚደረጉ ሥርኣታዊ ጸሎቶች ድረስ የሚገኙትን በመፈፀም እውነተኛ ሙስሊሞች አላህን ያስታውሱታል፤ እስላማዊ ትውፊቶችንም ይከውናሉ፡፡ አዛን ሙስሊሞችን ወደ አንድነት ይጠራል፣ ልባቸውን አንድ ያደርጋል፣ ከየአቅጣጫው እንዲተምሙ፣ በአላህ ፊትም በአንድነት እንዲሰግዱ ያደርጋቸዋል፡፡

ከውጪ ሆኖ ለሚመለከት ሰው አዛን የሌሊቱን ሰማይ ለሁለት የሚሰነጥቅ፣ ጨለማውን ከቀን የሚለይ፣ በሙስሊሞች ምድርና ማሕበረሰብ ውስጥ ሕይወትን የሚዘራ ነገር መስሎ ሊታየው ይችላል፡፡

ስለዚህ ሙስሊሞች አዛንን ለየዕለት እንቅስቃሴ አንዳቸው ሌላቸውን ለማንቃት ብቻ ሳይሆን ሕይወትንም ለመኖር ጭምር አንዳቸው ሌላቸውን ለማንቃት ቢጠቀሙ አያስገርምም፡፡ እያንዳንዱ የሙስሊም ልጅ በሚወለድበት ጊዜ አስቀድሞ አዛን መስማት እንዳለበት የሚናገር**ሐዲስ**፣ የነቢዩ መሐመድ ﷺ ትውፊት አለ፡፡ እኔ በተወለድኩበት እለት አባቴ የገዛ አባቱ ከ28 ዓመታት በፊት በጆሮው ላይ የተናገረውን በመድገም ዝግ ባለ ድምፅ አዛን በጆሮዬ ላይ ብሎ ነበር፡፡ በትውፊት መሠረት በጆሮዬ ላይ የተነገሩ የመጀመርያዎቹ ቃላት እነዚህ ነበሩ ማለት ነው፡፡

ቤተሰቦቼ ሐዲስን ለመከተል ልዩ ትኩረት ይሰጡ ነበር፡፡ከሁሉ በላይ እኛ ቁሬሾች ነን፡፡ ቁሬሾች ደግሞ የመሐመድ ጎሣዎች ናቸው፡፡ እድሜዬ ከፍ ሲል የስማችንን ልዩ ደረጃ ተረድቼ ነበር፡፡ ከነቢዩ ወርሰነው እንደሆነ አባቴን ጠየቅሁት፡፡

"አባዬ እኛ እንደ መሐመድ ﷺ ሁሉ ትክክለኛ ቁሬሾች ነን እንዴ?"

**በኡርዱ** ቋንቋ እንዲህ በማለት መለሰልኝ "ጂ ሜራ ቤይታ"፡፡ "አዎ ልጄ" ማለቱ ነበር፡፡ "መሐመድ እድሜያቸው ከልጅነት ያለፈ ወንድ ልጆች አልነበሩትም፡፡ እኛ የሀዝራት ዑመር ልጆች ነን፡፡" ዑመር ሱኒዎች በፈጣሪ የተመሩ የመሐመድ ﷺ ተተኪዎች እንደሆኑ ከሚያምኗቸው አራት **ኸሊፋዎች** መካከል አንዱ ነበር፡፡የዘር ግንዳችን በእርግጥም የተከበረ ነው፡፡ ቤተሰቦቼ በውርሶቻቸው መኩራታቸው አያስገርምም፡፡

**ሐዲስ፡** በትውፊት የተመዘገቡ የመሐመድ ቃላት እና ድርጊቶች

**ኡርዱ፡** የፓኪስታን ቋንቋ

**ኸሊፋ፡** ዋና መሪ በሙስሊሞች ላይ ያለው ከፍ ያለ ሥልጣን፡፡ ብዙ ጊዜ ይህ መጠርያ የመሐመድን አራቱን ተተኪዎች ለማመልከት ያገለግላል፡፡

አባቴ በ1970ዎቹ ውስጥ ፓኪስታንን ለቆ እንዲወጣ ያስገደደው ለቤተሰቡና ለውርሶቹ የነበረው ፍቅር ነበር፡፡ ወላጆቹና ዘመዶቹ የተሻለ ኑሮ እንዲኖሩ የማድረግ ህልም ነበረው፡፡ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ከመጣ በኋላ በታላቅ ወንድሙ ምክር የባህር ኃይልን ተቀላቀለ፡፡ በባህር ላይ ይሠራ በነበረበት ጊዜ ምንም እንኳ ብቸኛ ገቢው እርሱ ቢሆንም ይከፈለው ከነበረው ገንዘብ ለቤተሰቦቹ ይልክ ነበር፡፡ ከጥቂት ዓመታት በኋላ ከእናቴ ጋር ጋብቻው ስለተመቻቸለት ለአጭር ጊዜ ወደ ፓኪስታን ተመልሶ ነበር፡፡

*እማ፣* እናቴ ለቤተሰቧና ለሃይማኖቷ የተሰጠ ሕይወት ትኖር ነበር፡፡ የሙስሊም ሚስዮናዊ ልጅም ነበረች፡፡ *ትልቁ አባዬ* ብዬ የምጠራው አባቷ ከእናቷ፣*ከትልቋ እማ* ጋር በተጋቡ በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ኢንዶኔዥያ በመሄድ ሰዎችን ወደ እስልምና ይጋብዝ ነበር፡፡ ትልቋ እማ ቤተሰቡን ለማኖር ሥራ ትሠራ ስለነበርና ትልቁ አባዬ ደግሞ ብዙ ጊዜ የሚስዮናዊነት አገልግሎቱን ይከውን ስለነበር እናቴ ታናናሾቿን በማሳደግና የእስልምናን መንገድ በማስተማር ትልቅ ሚና ትወጣ ነበር፡፡

እድሜዋ አሥር ዓመት ሲሆን እማ ከታናናሾቿና ከትልቋ እማ ጋር በመሆን ወደ አገረ ፓኪስታን ተመለሰች፡፡ የሚስዮናዊነት አገልግሎታቸውን በጥንቃቄ በመወጣታቸውም ምክንያት ማሕበረሰቡ ለቤተሰቧ ሞቅ ያለ አቀባበል አደረገ፡፡ትልቁ አባዬ ግን በኢንዶኔዥያ ውስጥ ሚስዮናዊ ሆኖ በመቆየት ለእረፍት ብቻ ወደ ፓኪስታን ይመለስ ነበር፡፡እማ በቤት ውስጥ ያላት ኀላፊነት ከፍ እያለ መጣ፡፡ አምስት ታናናሾችዋን የማሳደግ ኀላፊነት ትከሻዋ ላይ ስለወደቀ ሁለተኛ ዲግሪዋን በከፍተኛ ማዕረግ አጠናቃ ሕክምና የማጥናት ዕድል ብታገኝም አልተቀበለችም፡፡ትልቋ እማ በአካባቢው **ጆማት** ውስጥ በፍቃደኝነት በጸሐፊነት ታገለግል ስለነበር በቤት እገዛ ያስፈልጋት ነበር፡፡

**ጆማት፡** በአረብኛ ቋንቋ ስብሰባን የሚያመለክት ሲሆን ብዙ ጊዜ “ቡድን” ወይም “ስብስብ” ተብሎ ይተረጎማል፡፡

ትልቋ እማ ሕይወቷን ከሞላ ጎደል ለእስልምና መስዋዕት በማድረግ ትኖር ነበር፡፡ የሚስዮናዊ ሚስት ብቻ ሳትሆን እንደ እማ ሁሉ የሚስዮናዊ ልጅም ነበረች፡፡ አባቷ በሕክምና እያገለገለ ሰዎችን ወደ እስልምና ይጋብዝ በነበረበት በዩጋንዳ

ውስጥ ነበር የተወለደችው፡፡ የሚስዮናዊ ልጅ ሆና ያደገች፣ የሚስዮናዊ ሚስት ለመሆን የሰለጠነችና የመጨረሻ የሥራ ዘመኗን በጀማት ውስጥ በማገልገል ያሳለፈች በመሆኗ ምክንያት በማሕበረሰቡ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ ከበሬታና ተቀባይነትን አትርፋለች፡፡ትልቋ እማየእናቴ ዋና ሞዴል ነበረች፡፡ እናቴ ደግሞ ይህንን ቅርስ በራሷ ቤተሰብ ውስጥ ከማስቀጠል የላቀ ሌላ ምኞት አልነበራትም፡፡

በወቅቱ ለኔ ባይታወቀኝም አዛንን በለሆሳስ በጆሮዬ ላይ የተናገረው ሰው ቁረሺ የሚለውን የከበረ ስም የተሸከመ ራሱን ለሌሎች ሰውቶ የሚኖር አፍቃሪ ሰው ነበር፡፡ እንክብካቤ ያደረገችልኝ ደግሞ የሚስዮናውያን ልጅ፣ ልምድ ያላት ተንከባካቢና እስልምናን የማገልገል ፅኑ መሻት የነበራት ሴት ነበረች፡፡ ሁለተኛ ልጃቸውና የመጀመርያ ተባዕት ልጃቸው ነበርኩኝ፡፡ ወደ ጸሎትእየተጠራሁ ነው፡፡

# የእናት እምነት

በአካል፣ በስሜትና ማሕበራዊ በሆኑ ጉዳዮች ረገድ ይህ ቀረ በማይባል ሁኔታ እንክብካቤ እየተደረገልኝ ነበር የልጅነት ሕይወቴን ያሳለፍኩት፡፡ሲደረግልኝ የነበረውን ጥንቃቄ ሳስብ እስከ ዛሬ ድረስ እደመማለሁ፡፡ በሰውነቴ ላይ የሚታዩት ጠባሳዎች አነስተኛ በሆኑ ጉዳቶች የመጡ ምልክቶች ብቻ ሲሆኑ የትላንት ያህል ትዝ ይሉኛል፡፡ ትልቁ ጠባሳ - ይታያችሁ ከሁለት ኢንች አይበልጥም - የሦስት ዓመት ልጅ እያለሁ ሰባራ መስኮት እጄ ላይ በመውደቅ ባደረሰብኝ ጉዳት የመጣ ነበር፡፡ ያ ዕለት በአእምሮዬ ውስጥ ተቀርፆ የቀረው ስለ እናቴ እምነት ካወቅሁት ነገር የተነሳ ነው፡፡

በወቅቱ አባቴ በኖርፎልክ፣ ቨርጂንያ ውስጥ ተመድቦ ይሠራ ነበር፡፡ ባሕር ኃይልን ከተቀላቀለ አስራ አንደኛ ዓመቱን የያዘ ሲሆን ባለፉት ጥቂት ሳምንታት ቀን ቀን እየሠራ ማታ ማታ ደግሞ ሁለተኛ ዲግሪውን ያጠና ነበር፡፡ ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ ከተራ አባልነት ከፍ በማለት የደረጃ ሁለት ሌውትናንት ማዕረግ አግኝቶ ነበር፡፡ በእርግጥ በወቅቱ ብዙም የማውቀው ነገር አልነበረኝም፡፡ የማውቀው ብቸኛ ነገር ቢኖር አባዬ ስለ እኛ በትጋት መሥራቱን ነው፡፡ ከዚህ የተነሳ ፍቅር ባይጓደልብኝም ነገር ግን ብዙ ጊዜ አላየውም ነበር፡፡

እማ ዘወትር የማትለየን ተንከባካቢያችንና በሕይወታችን ውስጥ የጎላ ተፅዕኖ የነበራት አሳዳጊያችን ነበረች፡፡ ዘወትር ሁሉንም ነገር ማድረግ የምትችል ትመስል ነበር፡፡ምግባችንን ከማዘጋጀት ጀምሮ፣ ልብሳችንን በንፅህና

**አቂዳ፡** ጥልቅ የሆኑ እስላማዊ እምነቶች

እስከመጠበቅ ከዚያም **አቂዳ** እስከማስተማር ድረስ የሚገኙትን ጉዳዮች ስትከውን የድካም ስሜት የሚሰማትም አይመስልም ነበር፡፡ አንድም ቀን ስትማረር አይቻት አላውቅም፡፡ነገር ግን አእምሮዋን እንዳትስት በጣም ጠንካራና የማይለዋወጡ ሁለት ሕግጋት ብቻ ነበሯት፤ ማታ ከሦስት ሰዓት በኋላ ምንም ዓይነት መነጫነጭ የለም እንዲሁም ብዙ ጊዜ እንደምታደርገው ሻይ በምትጠጣበት ጊዜ መረበሽ አይቻልም የሚሉት ነበሩ፡፡

እንግዶቻችንን ተቀብሎ ማስተናገድ ክብር ነው የሚል እምነት ስለነበራት እንግዶች በሚመጡበት ጊዜ ከፍተኛ የሆነ ደግነት ታሳይ ነበር፡፡እንግዶቹ መብላት ከሚችሉት በላይ ምግብ ይዘጋጃል፣ ቤቱ ከተሰራበት ቀን ይልቅ ይፀዳል፣ ሽክ ብለን እንለብሳለን፣ መርሃ ግብራችን በዚያን ዕለት ነፃ ይሆናል፣ ምናልባት እንግዳው መቆየት የሚፈልግ ከሆነ ተብሎም አንድ ተጨማሪ ቀን ነፃ ይደረጋል፡፡ እንዲህም ሆኖ ምግብ ባለመኖሩና እኛም ደግሞ በጥሩ ሁኔታ ባለመልበሳችን እንግዳውን አብዝታ ይቅርታ መጠየቅ የመስተንግዶው አካል ስለነበር ለምደነዋል፡፡ እንግዶቹም መልሰው እንዲህ ዓይነት እጅ የሚያስቆረጥም ምግብ ከበሉ ዓመታት ማለፉን፣ እንዲህ የፀዳ ቤት በሰማይ እንኳ መኖሩን እንደሚጠራጠሩና እኛ ልጆቿም ለልጆቻቸው ጥሩ ምሳሌ የምንሆን መሆናችንን ይነግሯት ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ሁሉም ሰው የኩራት ስሜት ይሰማዋል፤ እንግዶቹ ከበሬታን በማግኘታቸው፣ እማ በመወደሷና እኛ ህፃናት ደግሞ በአዋቂዎች ንግግር መካከል ስማችን በመጠቀሱ፡፡

አንዳንዴ እንግዶቹ ለወራት ያህል ከእኛ ጋር የሚቆዩ ቢሆኑም የእማ ደግነት ግን ፈፅሞ አይነጥፍም፡፡ በቤታችን ረጅሙን ጊዜ ከሚያሳልፉት እንግዶች መካከል ትልቋ እማና *እማማ* ብለን የምንጠራት እህቷ ይጠቀሳሉ፡፡ እማማ ልበ ሰፊ፣ በጣም ሳቂታና ትንሽ ሰውነት የነበራት ፍልቅልቅ ሴት ነበረች፡፡ከኔ ጋር የገበታ ጫወታዎችን ለመጫወት ምን ጊዜም ዝግጁ ስትሆን ለሦስት ዓመት ልጅ የሚያስፈልገውን ታጋሽነት አታጎድልም

ነበር፡፡ እኔ ሳጭበረብር ደግሞ አውቃ ማዶ ማዶ እየተመለከተች ያላየች ታስመስል ነበር፡፡

የመቁሰል አደጋው በደረሰብኝ ዕለት እማማ እቤታችን ነበረች፡፡ እርሷና እማ የላይኛው ክፍል ውስጥ የነበሩ ሲሆን እኔ ደግሞ እማ በገበያ አዳራሾች ውስጥ እንዳልረብሻት ለማባበያ በገዛችልኝ መንሸራተቻዎችና ትንንሽ የመጫወቻ መኪኖች እየተጫወትኩ ነበር፡፡ ታላቅ እህቴ ባጂእና እኔ ጥሩ መግባባት ነበረን፡፡ በእርሷ ትንንሽ ፈረሶች የምጫወት ከሆነ እርሷ ደግሞ ከእኔ ጋር ሆና በኔ መንሸራተቻዎች ትጫወታለች፡፡የምትፈልገውን መኪና መርጣ ትወስዳለች እኔም ደግሞ የምፈልገውን ፈረስ መርጬ እወስዳለሁ፡፡ አሻንጉሊት ፈረሶቿን በኩራት ሄጄ በመውሰድ የተሻለውን መርጬ መውሰዴን ተከራክሬ አሳምናታለሁ፡፡ ብዙ ጊዜ አንድ ዓይነት መኪና መርጣ የምትወስድ ሲሆን እርሷ ያልወሰደችው በእጄ የሚገኘው መኪና የተሻለ መሆኑን ተከራክሬ አሳምናታለሁ፡፡

ባጂ በመንሸራተቻዬ ተጫውታ ስልችቷት ፈረሶቿን ለመውሰድ ሄዳለች፤ እኔ ደግሞ መኪናዬ ላይ ተቀምጬ ወለሉ ላይ በአግዳሚ ወንበሮች መካከል እየበረርኩ መጫወቴን ቀጥያለሁ፡፡ በከፊል የተከፈተውን መስኮት ቀና ብዬ ተመለከትኩት፣ ከዚያም መኪናውን ለማጋጨት ጊዜው እንደሆነ አሰብኩኝ፡፡ መኪናውን ወደ መስኮቱ እያበረርኩኝ በመውሰድ ከመስታወቱ ጋር አጋጨሁት፡፡

እስከ ዛሬ ድረስ የመስኮቱ አወዳደቅ ትዝ አይለኝም፡፡ የማስታውሰው ነገር ቢኖር ሰቅጣጭ የሆነውን ህመም፣ የማያቋርጠውን ደምና የእምባ ዶፍ እያዘነብኩኝ እማን ጮኬ መጣራቴን ነው፡፡

እማ ከደረጃው ላይ በጥድፊያ ወርዳ በመምጣት አደጋውን በተመለከተች ጊዜ ለማልቀስ ምንም አልቀራትም ነበር ነገር ግን ወዲያውኑ ስሜቷን ተቆጣጠረች፡፡ የባሕር ኃይል መኮንን ሚስት እንደመሆኗ መጠን

**ዱዓ፡** በተወሰኑ ጊዜያት የሚደገሙ የሙስሊም ፀሎቶች ሲሆኑ ከሰላት የተለዩ ናቸው፡፡ የተሸመደዱ ወይም በራስ አባባል የሚፀለዩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

የእናትነትንም፣የአባትነትንም ሚና መጫወት ታውቅበታለች፡፡ አሁን ደግሞ ጊዜው የማልቀስ አይደለም፡፡ ነገር ግን ማድረግ የሚገባትን በብልሃት እያደረገች ፍርሃቷን ለአላህ ሰጠችው፡፡

መስኮቱን ካነሳች በኋላ እጇን በፋሻ በመጠቅለል *ቡርቃዋን* በጥድፊያ ሸብ አድርጋ ባጇን ለእማማ አደራ ብላት ወደ ክሊኒክ ልትወስደኝ ተሸክማኝ ወደ መኪናዋ ተጣደፈች፡፡ እዚያ እስክትደርስ ድረስ **ዱዓ** ታነበንብ ነበር፡፡ ዱዓውን ከቁርአን ክፍል፣ ከሸመደደችው የሐዲስ ክፍልና የራሷን ጸሎት በማከል ትፈፅም ነበር፡፡ በአላህ ሉኣላዊ ጥበቃ ላይ የነበራት መተማመን ብርታትን ሰጥቷታል፣ ውሳኔዋን አፅንቷል፣ ፍርሃቷንም አርግቦላታል፡፡

ክሊኒክ ከደረስን በኋላ መሰፋት ነበረብኝ፡፡ ዶክተሩ እማ እንዳትመለከት ሊያስወጣት ቢሞክርም እኔ ግን የሙጥኝ ብዬ ያዝኳት፡፡ እጄ እየተሰፋ ሳለ የዶክተሩንና የነርሶቹን የአግራሞት ዕይታ ችላ በማለት ድምጿ እየተሰማ ትጸልይ ነበር፡፡ በዚያን ዘመን ሙሉ ቡርቃ የለበሰች በአረብኛና በኡርዱ የምትጸልይ የባህር ኃይል ሚስት ትቅርና አሜሪካውያን ሙስሊሞች እንኳ እምብዛም አይታወቁም ነበር፡፡

ህፃን ልጇ እያለቀሰና በአርምሞ የሚመለከቷት ዓይኖች እያሉ ስትፈፅማቸው የነበሩት ከልብ የመነጩ ዱዓዎቿና በአላህ ላይ የነበራት ጠንካራ መተማመን ልረሳው የማልችለው የእምነቷ ምስክሮች ነበሩ፡፡ በልጅነቴ ወራት ከቁርአንና ከሐዲስ ብዙ ዱዓዎችን አስተምራኛለች፤ እኔም ደግሞ ኃይላቸውን ስላወቅሁኝ በልቤ ውስጥ አኑሬያቸዋለሁ፡፡ በፍርሃትና በጭንቀት ሰዓት ሲያበረቷትም አይቻለሁ፤ ይህ ደግሞ ከየትኛውም አካላዊ ጠባሳ ይልቅ ጎልቶ የሚታይ ምልክት በማንነቴ ላይ አኑሮ አልፏል፡፡

# የአራት ሰዎች ማሕበር

እድሜዬ ከፍ እያለ በመጣ ቁጥር እኔና ቤተሰቤ በአካባቢያችን ከሚገኙት ሰዎች ጋር መግባባት እንደማንችል ይሰማኝ ጀመር፡፡ ይህንን ባሰብኩ ቁጥር ልቤ ይተክዛል፡፡ ከእስላማዊ ባሕል ባሻገር ሕይወቴ የ1980ዎቹ ካርቱኖች፣ የፕላስቲክ መጫወቻዎችና የእልከኝነት ስሜት ቅይጥ ነበር፡፡ ከእድሜ እኩዮቼ ጋር መግባባት ያን ያህል ባይቸግረኝም ነገር ግን ሰዎች የማያውቁትን ነገር ስለሚፈሩ የእስልምና እምነቴ ብዙ ጓደኞቼና ቤተሰቦቻቸው በጥርጣሬ እንዲመለከቱኝ አድርጓል፡፡ በጣም ብቸኛ ነበርኩኝ፡፡

ነገሩን የከፋ የሚያደርገው ደግሞ የባሕር ኃይል ቤተሰቤን በየጊዜው ከቦታ ቦታ ማዛወሩ ነበር፡፡ ስር ለመስደድ የሚያስችለን በቂ ጊዜ አልነበረንም፡፡ ቀደምት ትውስታዎቼ ከቤት ለቆ የመውጣት፣ ወደ አዲስ ቤት የመግባትና አዲሱን ቦታ "እቤታችን" ብሎ የመጥራት ምስሎች ናቸው፡፡ ነገር ግን እነዚህ ትዝታዎች አሁንም ድረስ ጣፋጭ ትዝታዎቼሆነው እንደቀጠሉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ያህል ቨርጂንያን ለቀን የወጣንባት ዕለት እስከ ዛሬ ድረስ አትረሳኝም፡፡

የማላውቃቸው ሰዎች የቤት ቁሳቁሶቻችንን ሲወስዱ የበሩ መጋረጃ ስር ሸጉጥ ብዬ አለቅስ ነበር፡፡ እነዚህ ሰዎች ማን እንደሆኑና ምን ስላጠፋሁ ይህ እጣ እንደደረሰብኝ እያሰብኩኝ ሆድ ብሶኝስነፋረቅ እማ ታፅናናኝ ነበር፡፡ በሁኔታዬ ተገርማ መሳቋም እውነት ነው፡፡ በተለይም የምወዳት ወንበር በማላውቀው ሰው ስትወሰድ በቀልድ እንደጎነተለችኝ አስታውሳለሁ፡፡ ነገር ግን ደግሞ የማባበል እቅፏና የማፅናናት ድምጿም ከትዝታዬ ማህደር አልተፋቀም፡፡

ፊቴን በእጆቿ በመያዝ ወደ እቅፏ አስጠግታ *"ክያ ባት ሃይ?"* በማለት ጠየቀችኝ፡፡ *"ክያ ባት ሃይ፣ ሜረ ቤይታ?"* "ልጄ ምን ሆንክብኝ?"

"ባለ እንጆሪዋን ወንበር ወሰዷት!"

*"ታድያ ወንበሯ ከእናትህ ትበልጥብሃለች እንዴ? እኔ አለሁልህ እኮ፡፡ አባና ባጂም እዚሁ ናቸው፡፡ አላህ ሁሉንም ነገር ሰጥቶሃል! ሌላ ምን ትፈልጋለህ ቢሉ?" ቢሉ* ወላጆቹ ብቻ እኔን የሚጠሩበት ቅፅል ስም ነበር፡፡ በተለይም ፍቅራቸውን ለመግለፅ ሲፈልጉ እንደዚያ ይጠሩኛል፡፡ በቀጥታ "እወድሃለሁ" የሚሉት አልፎ አልፎ ብቻ ነበር፡፡ ለባሕላዊው ፓኪስታናዊ ያ ብዙም የተለመደ አይደለም፡፡ ፍቅር በውስጠ አዋቂነት የሚገለፅ ነው፡፡ ወላጆች አስፈላጊ የሆነውን ነገር በማቅረብና ልጆች ደግሞ ታዛዥ በመሆን ነው ፍቅራቸውን የሚገልፁት፡፡

በእስልምና ባሕል ውስጥ ለወላጆች መታዘዝ ትልቅ ትኩረት የሚሰጠው ፍቅር በተግባር የሚገለፅ ነው የሚል እምነት ስላለ ነው፡፡ ዕድሜዬ በአስራዎቹ ውስጥ በነበረ ጊዜ እማ "እኔ የምልህን ካላደረግህ እንደምትወደኝ ብትነግረኝ ምን ዋጋ አለው?" በማለት ብዙ ጊዜ ታዛዥነትን ታስታውሰኝ ነበር፡፡ ኋላ ላይም ጌታ ኢየሱስን ለመከተል ሳስብ ትልቅ አለመታዘዝ የሆነውን ውሳኔ ልወስን እንደሆነ ስለተሰማኝ ውስጤ ተረብሾ ነበር፡፡ ቤተሰቦቼ እንደተከዱ ብቻ አይደለም የሚሰማቸው፤ ነገር ግን ልባቸው ሊጠገን በማይችል ሁኔታ ይሰበራል፡፡

ነገር ግን የአራት ዓመት ልጅ እያለሁ ስለ ልብ ስብራትና ቤተሰቦቼን ስለማሳዘን ማሰብ አልችልም፡፡ ባለ እንጆሪዋ ወንበሬ እንድትመለስልኝ ብቻ ነበር ፍላጎቴ፡፡

ሁሉም ነገር ተሸክኖ ለጉዞ ዝግጁዎች ከሆንን በኋላ አባዬ ቤተሰቡን በመሰብሰብ "እስቲ እንጸልይ" አለ፡፡ እማና አባዬ እንደሚያደርጉት ሁሉ መዳፎቼን ቆልመም በማድረግ ወገቤ አካባቢ ከፍ አደረኳቸው፡፡ ሁላችንም በዝምታ ጉዟችን መልካምና የቀና እንዲሆን አላህን ለመንነው፡፡

ወደ አባዬ አዲሱ የምድብ ቦታ ስንደርስ በዱኑን፣ ስኮትላንድ ውስጥ ራሳችንን አገኘን፡፡ አሁን ዞር ብዬ ሳየው ዱኑን የመጀመርያው ትክክለኛ ቤቴ እንደነበር ይሰማኛል፡፡ በትምህርት ቤት ብዙ ጓደኞችን ስላፈራሁ ወይም ብዙ የጎረቤት ልጆችን ስለተዋወቅሁኝ አልነበረም፡፡ ባለ እንጆሪዋ ወንበር እንኳ ተወስዳብኛለች፡፡ ነገር ግን በነዚያ ዓመታት ከቤተሰቤ ጋር በጥብቅ ስለተቆራኘሁና እምነቴን በጥልቀት ስላወቅሁ ነው፡፡ እናቴ፣ አባቴና እህቴ ነበሩኝ፡፡ ከእነርሱ ውጪ ሌላ አያሻኝም ነበር፡፡

ምዕራፍ አራት

# ፍፁም የሆነው መጽሐፍ

ስኮትላንድ በደረስኩ ጊዜ እንግሊዘኛን በሚገባ አልተማርኩም ነበር፡፡ በቤት ውስጥ የምንነጋገረው በኡርዱ ብቻ ሲሆን የምንማራቸው ፊደላት ደግሞ የአረብኛ ብቻ ነበሩ፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ግልፅ ነው፤ቁርአን በአረብኛ ስለተጻፈ እኔና ባጂ ለማነብነብ መማር ግድ ስለሆነብን ነበር፡፡

ሙስሊሞች እያንዳንዱ የቁርአን ቃል ከአላህ ዘንድ በመልአኩ ገብርኤል አማካይነት ለመሐመድﷺ ቃል በቃል እንደተነገረው ነው የሚያምኑት፡፡ ስለዚህ ቁርአን በትርጉም ደረጃ ብቻ ሳይሆን ቃላቱ እንኳ በቀጥታ ከሰማይ የመጡ መገለጦች ናቸው፡፡ ከዚህ የተነሳ ሙስሊሞች ቁርአን ሊተረጎም እንደሚችል አያምኑም፡፡ ከአረብኛ ውጪ ባለ በሌላ በየትኛውም ቋንቋ ቢጻፍ ቁርአን ሳይሆን የቁርአን ፍቺ ነው የሚሆነው፡፡ መጽሐፉ እውነተኛ ቁርአን የሚሆነው በአረብኛ ሲጻፍ ብቻ ነው፡፡

ለዚህ ነው ቁርአን ቃል በቃል ነቁጥ በነቁጥ ሳይለዋወጥ እንደቆየ ማመን ለሙስሊሞች አስፈላጊ የሆነው፡፡ ኢማሞችና አስተማሪዎች ብዙ ጊዜ መሐመድ ከገብርኤል ከሰማበትና ለጸሐፍቱ ካነበነበበት ጊዜ ጀምሮሳይለዋወጥ በትክክል ተጠብቆ መቆየቱን ይናገራሉ፡፡ በእርግጥ መሐመድ ﷺ ቁርአንን በማቀናበር ረገድ ምንም ያደረገው ነገር አልነበረም፤ እርሱ መገለጡን ለሰው ልጆች የሚያደርስ ማስተላለፍያ ብቻ ነበር፡፡ ትክክለኛ መልኩንም ኀላፊነት በተሞላበት ሁኔታ ጠብቋል፡፡ ይህንን ባያደርግና ቃላቱ

ትንሽ እንኳ ቢለወጡ ኖሮ ቁርአን ዳግመኛ ሊገኝ በማይችልበት ሁኔታ በጠፉ ነበር፡፡ ነገር ግን ቃላቱ ተለዋውጠዋል ብሎ ማሰብ የማይቻል ነው፡፡ ቁርአን እንከን የለሽ በሆነ ሁኔታ መተላለፉን የሚጠራጠር ማንም የለም፡፡ ስለዚህ የቃላቱ እንከን አልባ መሆን ጥርጥር የለውም፡፡

በእርግጥ ቃላቱ ላይ ትኩረት በማድረጋቸው ምክንያት ብዙ ሰዎች የቃላቱን ትርጉም ችላ ብለዋል፡፡ ቁርአንን በየጊዜው የሚያነበንቡ ሰዎች ብፁዓን ተደርገው የሚቆጠሩ ሲሆን በቁርአን ትርጉም ላይ ብቻ የሚያተኩሩ ሰዎች ደግሞ ምሑራን ተደርገው ይታሰባሉ፡፡ ብፅዕና ትልቅ ክብር በመሆኑ ምክንያት እኔ የማውቃቸው ብዙ ሰዎች የቁርአንን ብዙ ክፍሎች በቃላቸው ሸምድደው ቢይዙም ነገር ግን የአንቀፆቹን አውድ ወይም ትርጉም እምብዛም ማብራራት አይችሉም፡፡

እማ የቁርአንን መነባንብና ፍቺ ታስተምረን ነበር፤ ነገር ግን ማነብነቡን ታስቀድም ነበር፡፡ በየዕለቱ ባሕላዊውን የሙስሊም ኮፍያ እራሴ ላይ በመድፋት ከአጠገቧ አስቀምጣ አረብኛ ታስጠናኝ ነበር፡፡*አል-ቃኢዳ* “መመርያ” በሚል መጽሐፍ ነበር የጀመርነው፡፡ የአረብኛን ፊደሎች የተለያዩ መልኮች ከነድምፆቻቸው ተምረንበታል፡፡ ልክ ስኮትላንድ ከመድረሳችን “ተመርቄ” ከቃኢዳ ወደ ቁርአን ተሻገርኩኝ፡፡

ያቺ ዕለት በጣም ትዝ ትለኛለች ምክንያቱም በሕይወቴ በጣም ከደነገጥኩባቸው ቀናት መካከል አንዷ ነበረችና፡፡ የመጨረሻውን የቃኢዳ ገፅ አጥንቼ ስጨርስ እማ በአጠገቧ የተቀመጠውን ቁርአን አንስታ በስጦታ መልክ አበረከተችልኝ፡፡ ይህ ቁርአን እንደ ስጦታ የተቀበልኩት የመጀመርያው መጽሐፍ ነበር፡፡

እየፈነደቅሁኝ ለባጂ ላሳያት በርሬ ሄድኩኝ፡፡ ባጂ በአባና እማ ክፍል ጎን ወለል ላይ ትጫወት ስለነበር አጠገቧ ቁጭ ብዬ ቁርአኑን ላሳያት መሬት ላይ አስቀመጥኩት፡፡

ከመቅፅበት እማ ጆሮን የሚበጥስ ጩኸት እያሰማች ወደኔ አቅጣጫ እየተደነቃቀፈች መጣች፡፡ “ነቢል!” ብላ አምባረቀች፡፡ ድርቅ ብዬ ቀረሁ፡፡ እንደዚያ ስትጮኽም ሆነ ስትጣደፍ አይቻት አላውቅም ነበር፡፡ “ቁርአንን መሬት ላይ አታስቀምጥ!”

“እሺ”

“ሁል ጊዜ ከፍ አድርገህ ያዘው፡፡ ከፍ ባለ ቦታ ላይ አስቀምጠው፣ ከመንካትህ በፊት እጅህን ታጠብ፣ በቀኝ እጅህ ብቻ ያዘው፡፡ ይህ እንደማንኛውም መጽሐፍ አይደለም፣ የአላህ ቃል ነው፡፡ ተገቢ የሆነውን ክብር ስጠው!”

“እሺ”

“*ጀአ፣ ሂድ*” በጣም ተበሳጭታ ስለነበር ሳላቅማማ ሱልል ብዬ ሄድኩኝ፡፡ ከዚያን ዕለት ጀምሮ ቁርአንን ከፍ አድርጌ መያዝ ጀመርኩኝ፡፡ ባጂም ከኔ ስህተት ተምራ ስለነበር በሚቀጥለው ጊዜ እማ ቁርአኖቻችንን አምጥተን እንድናነብ ስትነግረን እጆቻችንን የቻልነውን ያህል ወደ ላይ በመወጠር ከራሶቻችን በላይ ከፍ አድርገን በመያዝ መጣን፡፡ እማ ፈገግ አለች፡፡ ለማለት የፈለገችው እንደርሱ ባይሆንም ነገር ግን ደስተኛ ነበረች፡፡

ባጂ ታላቅ እንደመሆኗ መጠን ቀደመች፡፡ እማ ባጂ የምታነባቸውን ቃላት በጣቷ እየጠቆመች በገፁ ላይ በቀስታ ከግራ ወደ ቀኝ ታንቀሳቅስ ነበር፡፡ ባጂ ቃላቱን በዜማ ስትላቸው ስለነበር በፍጥነት አታነብም ነበር፡፡ ቁርአንን በዜማ እንድናነብ ነበር የተማርነው፡፡ ድምፁንም የተቻለንን ያህል ለማስዋብ ጥረት እናደርግ ነበር፡፡ አንዳንድ ሰዎች ቅኝታቸውን፣ ምታቸውን፣ የድምፅ አወጣጣቸውንና ዜማቸውን በማስተካከል ለዚህ ልምምድ ሕይወታቸውን ይሰጣሉ፡፡

ነገር ግን እኔና ባጂ እንደዚያ አልነበርንም፡፡ ጥቂት ዓመታትን ከኔ ቀደም ብላ የጀመረች ስትሆን በመጠኑ ቁርአንን ማነብነብ ተምራለች፡፡ እኔ ከዚያ ቀደም ቁርአንን አንብቤ ስለማላውቅ በጣም ጓጉቼ ነበር፡፡

“ቢሉ ከሁሉ አስቀድመን የምናነበንበው ምንድነው?”

*“ቢስሚላሂ ረህማን አረሂም፡፡”*

“ምን ማለት ነው?”

"በአላህ ስም በጣም ርህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው፡፡"

"ይህንን ጸሎትየምንጸልየው ለምንድነው?"

"ሁሉም ነገር የአላህ መሆኑን ለማስታወስና መልካም ነገሮችን ብቻ ማድረግ እንድንችል፡፡"

"ሻባሽ፣ በጣም ጥሩ፡፡ ይህ ጸሎት ከየት እንደመጣ ታውቃለህ?"

"አላውቅም፡፡"

"በቁርአን ውስጥ በሚገኙት በሁሉም **ሱራዎች** መጀመርያ ላይ ይገኛል፡፡"

"በሁሉም ሱራዎች?"

"ከአንዱ በስተቀር በሁሉም ሱራዎች ላይ፡፡"

"እማ አላህ ለምንድነው አንዱን ሱራ የተወው?"

"ቤይታ አላህ በዚያ ሱራ ላይ በሰዎች በጣም በመቆጣቱ የተነሳ የቢስሚላን ባርኮት ሳይሰጠን ቀረ፡፡ ነገር ግን በጣም ስለሚወደን በሌላ ሱራ ላይ ተጨማሪ አስቀምጦልናል፡፡ ስንት ሱራዎች አሉ?"

**ሱራ፡** የቁርአን ምዕራፍ

"114"

"ሻባሽ፡፡ ኢንሻ አላህ ሁሉንም በቅርቡ ታነባቸዋለህ፡፡ ባጂ ሰባት ዓመት ሲሆናት ነው ቁርአንን አንብባ የጨረሰችው፣ አንተ ግን ስድስት ዓመት ሲሆንህ እንድትጨርስ ነው የምፈልገው፡፡ እሺ እንቀጥል፡፡"

ቀናት በሄዱ ቁጥር ከቁርአን ጋር መላመድ ጀመርኩኝ፡፡ ቁርአን በሁለት መንገድ መከፈሉን ተረዳሁኝ፤ አንደኛው በ 114 ሱራዎች ሲሆን ሌላኛው ደግሞ በ30 ክፍሎች ነው፡፡ ሁለተኛው መንገድ በሰላሳዎቹ **የረመዳን** ወር ቀናት ውስጥ በቀላሉ ተነቦ ማለቅ እንዲችል በማለምቁርአን ከተሰበሰበ ከረጅም ዓመታት በኋላ

**ረመዳን፡** የሙስሊሞች ቅዱስ ወር

ሙስሊሞች የፈጠሩት የአከፋፈል ስልት ነው፡፡ ነገር ግን ሰላሳዎቹ ክፍሎች በሌላ ምክንያት ለኔ አስፈላጊዎች ነበሩ፤ አንዱን ስጨርስ እማ የእንኳን ደስ ያለህ ስጦታ ትገዛልኝ ነበር፡፡ ከተገዙልኝ ስጦታዎች መካከል የማሪዮ ብራዘርስ ቅርጫት ለኔ በጣም አስደሳቹ ነበር፡፡

ደህና ሊባል የሚችል ዙር ላይ ስደርስ እማና እኔ የራሳችንን ምት ፈጠርን፡፡ ቁርአኔን ይዘን እንቀመጥና ያነበብነው የመጨረሻው ገፅ ተከፍቶ እማ የቀኑን የመጨረሻ የጥናት ገፅ ትወስናለች፡፡ ምክንያቱ ባይገባኝም እኔ ግን ሁል ጊዜ ለማነብነብ የምመርጠው አስራ ስምንት ቁጥሮችን ነበር፡፡ እማ ለዕለቱ ከዚያ በላይ የምትወስን ከሆነ እነጫነጫለሁ፤ ከዚያ በታች ከሆነ ግን እርሷን ለማስደሰት ተጨማሪ አንብቤ አስራ ስምንቷን እሞላለሁ፡፡

እንዲህ እያሉ ቀናት ነጎዱ፡፡ እማን እጅግ ባስደሰተ ሁኔታ ስድስት ዓመት ሊሆነኝ ትንሽ ሲቀር ቁርአንን አጠናቀቅሁኝ፡፡ በዘወትር ጸሎት ውስጥ በየዕለቱ ማነብነብ እንድችል እማ የመጨረሻዎቹን ሰባት ሱራዎች እንድሸመድድ እረዳችኝ፡፡ ምዕራፍ 112 ላይ የሚገኘው ሱረት አል ኢኽላስ አጭር፣ በቀላሉ የሚታወስና ዜማው የሚጥም ስለሆነ እወደው ነበር፡፡ በተጨማሪም ለመጀመርያ ጊዜ በቃል የሸመደድኩት ሱራ ሲሆን በሰላት ጊዜ ደጋግሜ ብዬዋለሁ፡፡ እማም ይህንን ምዕራፍ ትወደዋለች ነገር ግን በተለየ ምክንያት ነው፡፡ በሐዲስ መሠረት ይህ ሱራ ክብደት ያለውና አስፈላጊ ከመሆኑ የተነሳ እርሱን ማነብነብ የቁርአንን አንድ ሦስተኛ እንደ ማነብነብ እንደሚቆጠር መሐመድ ተናገሯል፡፡

መሐመድ በጣም አስፈላጊ እንደሆነ የተናገረው መልእክት ምን እንደሆነ እስኪ ገምቱ? አምላክ አባት አይደለም ልጅም የለውም የሚል ነው፡፡

ምዕራፍ አምስት

# የነቢዩ ታሪኮች

“አርፍደናል፣ እንሂድ!”

ዕለቱ ቅዳሜ ጠዋት ሲሆን አባዬ በር ላይ ቆሞ ይጠብቀን ነበር፡፡ በየሳምንቱ ቅዳሜ ቤተሰቡ በሙሉ ከዱኑን ወደ ግላስጎው ጀማት **መስጊድ** ይጓዛል፡፡ ሁሉም ሊባል በሚቻልበት ሁኔታ ከፓኪስታን የመጡ ሙስሊሞች ሲሆኑ ከእነርሱ ጋር የምናሳልፈው ጊዜ ለሁላችንም አስደሳች ነበር፡፡ እንደ እኛ ሁሉ እነርሱም ባይተዋሮች ስለነበሩ በአንድነት ስንሆን ጥሩ ስብጥር እንፈጥር ነበር፡፡ እማ ከቤት ውጪ ስትሆን ፀጉሯን የማትሸፈንበት ብቸኛ ቦታ እዚያ በመሆኑ ምክንያት ያችን ቀን በጉጉት የምትጠባበቅ ነው የምትመስለው፡፡ ሙስሊም ሴቶች አንድ ላይ ሲሆኑ መሸፈኛዎቻቸውን ይገልጣሉ፡፡ በእንዲህ ዓይነት አጋጣሚዎች ደግሞ ለፋሽን ትኩረት ይሰጣሉ፡፡

> **መስጊድ፡** የሙስሊሞች የማምለኪያ ቦታ፡፡ መስጊድ ወይም መስጂድ ተብሎ ሊጠራ ይችላል፡፡

እማ ዝግጅት ስታደርግ ሳለች ማርፈዷ የተለመደ ነበር፡፡ ሁሌ ነው የምታረፍደው፡፡ በፓኪስታን ባህል ሰዓት ማክበር በምዕራባውያን ዘንድ እንደሆነው ያን ያህል ጥብቅ ጉዳይ አይደለም፡፡ ማህበራዊ ኩነቶች ቅድሚያ ይሰጣቸዋል፡፡ ሰዓት ማክበር ትክክል መሆኑ የሚታመን ቢሆንም ነገር ግን ለግብዣ በተጠሩበት ቤት ልክ በሰዓቱ መገኘት በተወሰነ ደረጃ ከጨዋነት አይቆጠርም፡፡ ለመምጣታችሁ የመጨረሻዋን ደቂቃ ዝግጅት እያደረጉ ቢሆንስ? ከመዘጋጀታቸው በፊት መድረስ እንግዳ ተቀባይነታቸውን ያደበዝዛል፡፡ አስራ አምስት ወይም ሰላሳ ደቂቃ ማርፈድ ጥሩ ነው፡፡

በሌላ ወገን ደግሞ አባዬ ይህንን ልማድ በወታደር ማሰልጠኛ ጣብያ በነበረበት ጊዜ ጥሎታል፡፡ ወታደር እንደመሆኑ መጠን የኛ ጎታታነት ትእግስቱን ይፈታተናል፡፡ ብዙ ቢሞክርም ነገር ግን የእማን ሁኔታ መለወጥ አልቻለም፡፡ ሁል ጊዜ ለእርሷ ትክክል መስሎ የታያትን ብቻ የምታደርግ ስትሆን አባዬ ግን የቤቱ ዋና እርሱ መሆኑን ሳያስታውሳት አያልፍም ነበር፡፡ እንዲህ ሲሆን ለተወሰኑ ደቂቃዎች ከሰማቸው በኋላ በቀስታ በማባበል ታበርደዋለች፡፡ ይህ የፍቅረኛሞች ሽኩቻ በቅዳሜ ጠዋት የቀን መቁጠርያ ላይ የሰፈረ ይመስላል፡፡ነገር ግን ይህኛው ቅዳሜ በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ነው የሚመጣው፡፡ የኛ ጀማት *ሲራት አን-ነቢ፣* የነቢዩን ሕይወት የሚዘክርበት ቀን ነው፡፡ የመሐመድ የልደት ቀን ሳይሆን ማሕበረሰቡ ተሰብስቦ የመሐመድን ታሪክ ለማውራት የመረጠው ቀን ነው፡፡

ሙስሊሞች የመሐመድን ሕይወት እንደ ተምሳሌታዊ ሕይወት የሚቆጥሩት ሲሆን ጠንካራ ሙስሊሞች ደግሞ እርሱን ለመምሰል ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ይህንንም ለማድረግ የሕይወት ታሪኮቹን **ከሲራ** መጻሕፍትና ከሐዲሳት ይማራሉ፡፡ ከሞላ ጎደል ታሪኮቹን እራሳቸው አያነቧቸውም፡፡ ይልቁኑ መስጊድ በመሄድ በስብከቶች መልክ ይሰማሉ፡፡ ሐዲሳትን በደንብ ማወቅና በትክክለኛ አውዳቸው ውስጥ ማንበብ እንዲሁም መጥቀስ ልቅናን ይጠይቃል፡፡ ከዚህ የተነሳ ወደ መስጊድ መሄድ ከመንፈሳዊና ከማሕበራዊ ሁኔታዎች አኳያ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ነገር ግን አርፍደናል፡፡

**ሲራ፡** የመሐመድ ግለ ታሪክ

*“ቻሎ! ኑ!”*

ማለዳው ለእማ፣ ለባጂና ለእኔ በጣም ጥድፍያ የሞላበት ነበር፡፡ከመኝታችን ተነስተን የጠዋት ጸሎታችንን ካደረስን በኋላ፣ እማ እኔና ባጂን አለበሰችን፣ መገበችን ከዚያም የፊት መዋቢያዎቿን መቀባባት ጀመረች፡፡ የፊት ዱቄትና የከንፈር ቀለም ከመቀባቷ በፊት ድምጿን ከፍ አድርጋ *“ተዘጋጅቻለሁ!”* ማለቷ የተለመደ ነበር፡፡ በዚህኛው ቅዳሜ

ግንየከንፈር ቀለሟን ወደ መኪናው ይዛ መጥታለች፡፡ ከአፍታ በኋላ ወደ ግላስጎው ጉዞ እንጀምራለን፡፡

ከዱኑን ግላስጎው ለመድረስ ሆሊ ሎችን ማቋረጥ ይኖርብናል፡፡ሆሊ ሎች በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት የአሜሪካ የኒኩለር ባሕር ኃይል መመላለሻ ነበር፡፡ አባዬ የጥገና መርከብ ላይ ይሠራ የነበረ ሲሆን የደህንነትና የአካባቢ ጥበቃ ኃላፊ ነበር፡፡ እኔ ግን በወቅቱ ምንም የማውቀው ነገር አልነበረም፡፡ የማውቀው ነገር ቢኖር የባህር ሰርጡን የሚያሻግሩን ሁለት ጀልባዎች መኖራቸውን ነው፡፡ አንዷ አነስ ያለ መጠን ያላት ባለ ቀይ ቀለም ስትሆን ተለቅ ያለ መጠን ያላት ደግሞ ጥቁር ነበረች፡፡ ባለ ጥቁር ቀለሟ አይብና ሳንዱች የምንበላበት የመመገቢያ ቦታ ነበራት፡፡ ጀልባ ላይ በምንሆንባቸው ጊዜያት እማና አባ ብዙ ጊዜ በእንቶ ፈንቶ ጉዳዮች በመከራከር ነበር የሚያሳልፉት፡፡ ዛሬ ግን በመኪና ውስጥ በመቆየት ለሲራት አን-ነቢ መርሃ ግብር እኛን ለማዘጋጀት ወስነዋል፡፡

እማ ጥያቄዎችን ትጠይቀን ነበር፡፡ ከኔና ከባጂ መልሱን ያወቀ ቀድሞ ይመልስ ነበር፡፡ “*ባተኣ፣* ንገሩኝ መሐመድ መቼና የት ነበር የተወለደው?”

“በ570 ዓ.ም. በመካ ነበር፡፡”

“ሻበሽ፣ በጣም ጥሩ! *ሑብ ባተኣ፣* አሁን ደግሞ አባቱ ማን እንደሚሰኝ ንገሩኝ?”

“ስሙ አብደላህ ይባላል፣ ነገር ግን መሐመድ ከመወለዱ በፊት ነበር የሞተው፡፡”

“እናቱስ?”

“ስሟ አሚና ነበር፤ እርሱ እድሜው ስድስት በሆነ ጊዜ ነበር የሞተችው፡፡”

“ስለዚህ እርሷ ከሞተች በኋላ መሐመድን ማን ነበር ሲንከባከበው የነበረው?”

“አያቱ አብዱል ሙጠሊብ ነበር፡፡ ነገር ግን ከሁለት ዓመት በኋላ እርሱም ሞቷል፡፡”

“ከዚያስ?”

“አጎቱ አቡ ጣሊብ ነበር፡፡ ብዙ ዓመት ኖሮ ነበር የሞተው፡፡”

እነዚህ የሙስሊም ልጆች ሁሉ የሚማሩት የመደበኛ ትምህርት አካል ሲሆኑ በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ናቸው፡፡ ሙስሊም ወላጆች ብዙ ጊዜ ልጆቻቸው ስለ እስልምና ባላቸው ዕውቀት የሚኮሩ ሲሆኑ እማና አባም ከዚያ የተለዩ አልነበሩም፡፡

"መልካም፣ ይኸኛው ደግሞ ትንሽ አስቸጋሪ ነው፡፡ እናቱ ከመሞቷ በፊት መሐመድ ምን እንደደረሰበት እስኪ ንገሩኝ፡፡"

**ጂን፡** ጋኔን ማለት ሲሆን መንፈሳዊያን ፍጥረታት ናቸው፡፡

ባጂ እንዲህ በማለት መለሰች፡ "አንድ ቀን መሐመድ ከዕድሜ እኩዮቹ ጋር እየተጫወተ ሳለ ሁለት መላእክት ወደ እርሱ በመምጣት ደረቱን ከፈቱ፡፡ ሌሎች ህፃናት ግን በመፍራት መላእክቱ **ጂን** መስለዋቸው ነበር፡፡ ስለዚህ ሮጠው ተሸሹ፡፡ መላእክቱ የመሐመድን ልብ በማውጣት እስኪያብለለጭ ድረስ አፀዱት፡፡ ከዚያም ደረቱ ውስጥ መልሰው በማስቀመጥ ሄዱ፡፡"[9]

"ሻበሽ፣ *ጉርያ!"* ይህ እማ ባጂን የምትጠራበት የቅፅል ስም ሲሆን "አሻንጉሊቷ" እንደማለት ነው፡፡ "አንቺ ይህንን ስለመለስሽ አሁን ደግሞ ነቢል ባተኦ፤ የመሐመድ የመጀመርያዋ ሚስት ማን ትባል ነበር፣ እንዴት ነበር የተጋቡት?"

ይኸኛው ቀላል ነው፡፡ "የመሐመድ የመጀመርያዋ ሚስት ከዲጃ ትሰኛለች፡፡ ኃብታም መበለት የነበረች ስትሆን መሐመድ ነጋዴ በመሆን ተቀጥሮ ይሰራላት ነበር፡፡ ንግድ ላይ ጎበዝ መሆኑንና በገንዘብም ታማኝ መሆኑን ባየች ጊዜ እንዲያገባት ጠየቀችው፡፡"

"እድሜያቸው ምን ያህል ነበር?"

"መሐመድ ሃያ አምስት ሲሆን ከዲጃ ደግሞ አርባ አመቷ ነበር፡፡"

"ጥሩ ነው ግን ይህ ብዙም የሚከብድ ላይሆን ይችላል፡፡ ኡብ ባተኦ፣ ቢሉ፣ መሐመድ ነቢይ መሆኑን እንዴት ነበር ማወቅ የቻለው?"

"በዋሻ ውስጥ ሲጸልይ ሳለ አንድ ቀን..."

አባዬ ጣልቃ ገባ፣ "የዋሻው ስም ምን ነበር?"

"የሒራ ዋሻ፡፡ሲጸልይ ሳለ መልአክ ወደ እርሱ በመምጣት አንብብ አለው፡፡ ነገር ግን መሐመድ ማንበብ አይችልም ነበር ስለዚህ መልአኩ እንዲያነብ ሦስት ጊዜ አዘዘው፡፡ ከዚያም መልአኩ ለመሐመድ የመጀመርያዎቹን የቁርአን ጥቅሶች ሰጠው፡፡"

እማዬ ቀጠለች፣ "ሸበሽ፣ ያ ሱራ ምን ነበር?"

እኔም ሆንኩ ባጂ የዚህን ጥያቄ መልስ አናውቅም ነበር፡፡ ቁርአን በጊዜ ቅደም ተከተል መሠረት ስላልተቀመጠ ይህንን ማወቅ ከበድ ይላል፡፡ በምናነበው መጽሐፍ ውስጥ ተለይቶ ስላልተቀመጠ ብዙም ትኩረት አልሰጠነውም ነበር፡፡

"ችግር የለውም አትጨነቁ፡፡ ዛሬ ምናልባት የሆነ ሰው የሚጠይቃችሁ ከሆነ *ሱራ አል-አለቅ* መሆኑን አስታውሱ፡፡"

"*ጃኒጃትኛው* ሱራ እንደሆነ ማንም አይጠይቃቸውም፡፡ አስፈላጊ የሆነውን ጥያቄ ጠይቂያቸው፡፡" ጃን ወይም ጃኒ የኡርዱ የቁልምጫ አጠራር ሲሆን "የኔ ሕይወት" ማለት ነው፡፡ተወዳጅ ለሆነ ሰው የሚሰጥ መጠርያ ሲሆን አባዬ የተጠቀመበት አጠቃቀም "የኔ ውድ" በሚል ነበር፡፡እማ ግን ደስ አላላትም ነበር፡፡ "ከሱራ ስም ይልቅ አስፈላጊው የዋሻ ስም ነው አይደል? እሺ ጥሩ ነው፡፡ እንግዲያውስ የቤቱ ጌታ ጥያቄዎቹን ይጠይቅ!"

"መልካም፣እጠይቃለሁ፡፡ ቻሎ ባተአ፤ መሐመድን እንደ ነቢይ የተቀበለው የመጀመርያው ሰው ማን ነበር?"

"ሚስቱ ከዲጃ ናት፡፡"

"ከወንዶች መካከልስ?"

"ምርጥ ጓደኛው አቡበከር፡፡"

**ሺአ፡** የእስልምና ሁለቱ ዋና ቡድኖች ከሚባሉት መካከል አንዱ የሆነው የሺአዊነት ተከታዮች፡፡

"አቡበከርን ለየት የሚያደርገው ነገር ምንድነው?"

"መሐመድ ከሞተ በኋላ የመጀመርያው ኸሊፍ ሆነ፡፡" ይህ **ሺአዎች** የማይቀበሉት ወሳኝ ጉዳይ ቢሆንም እኔና ባጂ ግን ስለ ጉዳዩ የምናውቀው ነገር አልነበረም፡፡

“ከልጆች መካከል እስልምናን የተቀበለው ማን ነበር?”

“የመሐመድ የአጎት ልጅ አሊ፡፡”

“አሊን ለየት የሚያደርገው ምን ነበር?”

“አራተኛው ኸሊፍ ሆነ፡፡”

“አብዛኞቹ የመካ ነዋሪዎች እንዴት ነበር እስልምናን የተቀበሉት?”

“ሙስሊሞችን በመስደብና ጉዳት በማድረስ ለረጅም ዘመናት ያሳድዷቸው ነበር፡፡”

“ከዚያስ ምን ሆነ?”

“መሐመድ ወደ መዲና መሰደድ ነበረበት፡፡”

አባዬ ዝም አለ፡፡ መርከቢቱ ወደቡ አካባቢ ስትቆም የባሕር ሞገድ በቀስታ ጎኗን ሲታከክ ይታያል፡፡ ተከታታይ ከነበረው የጥያቄ እሩምታ በማስከተል የተፈጠረው ዝምታ የአካባቢውን እርጋታ አጉልቶታል፡፡ አባዬ ምን እያሰበ ይሆን?

ድምፁ የፀጥታውን ድባብ መልሶ ገፈፈው፡፡ አጠያየቁ ከበፊቱ ጠንከር ባለ ሁኔታ ነበር፡፡ “ቢሉ ባተአ፣ መሐመድ የተዋጋው የመጀመርያው ጦርነት ምን ነበር? በዝርዝር ንገረኝ፡፡”

“የበድር ጦርነት ነበር፡፡ መካውያን ሙስሊሞችን ለማጥቃትና ለማጥፋት ወደ መዲና መጡ፡፡ አንድ ሺህ ወታደሮችና ብዙ ፈረሶችን ይዘው መጡ፡፡ ሙስሊሞች ግን 313 ወንዶች፣ በጣም ጥቂት ትጥቅና ጥቂት ፈረሶች ብቻ ነበሯቸው፡፡”

“ማን አሸነፈ?”

“ያሸነፍነው በርግጥ እኛ ነበርን፡፡”

“ለምን?”

“ምክንያቱም እኛ የተሻልን ስለነበርን፡፡”

"አይደለም ቤይታ፡፡ በሁሉም ረገድ እነርሱ የተሻሉ ነበሩ፡፡ አላህ ስለረዳን ነው እኛ ያሸነፍነው፡፡ ይህ ጦርነት በተለመደው መልኩ ቢጠናቀቅ ኖሮ እኛ ተሸንፈን መሐመድ ይሞት ነበር፤ አኡዙ ቢለህ፡፡ አምላክ እኛ ሙስሊሞችን ይረዳናል፡፡ ምክንያቱም የርሱ ሕዝቦች ነንና፡፡ እሺ *ቤይቴ፣* አሁን ደግሞ ያንቺ ተራ ነው፡፡ በመዲና የተደረጉት ሌሎች ጦርነቶች የትኞቹ ነበሩ?"

"የኡሁድ ጦርነትና የምሽግ ጦርነት፡፡" ባጂ ደስ እያላት ትመልስ ነበር፡፡

"ሙስሊሞች እነዚህን ጦርነቶች መዋጋት ለምን ነበር ያስፈለጋቸው? ጥቃት ፈፃሚዎቹ እኛ ነበርን?"

"አይደለም አባ፡፡ ሙስሊሞች ራሳቸውን ለመከላከል ብቻ ነው የሚዋጉት፡፡ መካውያን ሙስሊሞችን ሲያጠቋቸው ነበር፡፡"

"ስለዚህ ሙስሊሞች መካውያንን ለማስቆም ምን አደረጉ?"

"መካን ወረሩ፡፡"

"ይህ የተተነበየው የት ነበር?"

እኔ ጣልቃ በመግባት፣ "በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነው፣ በአሪት ዘዳግም" አልኩኝ፡፡[10] "መሐመድ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ" የሚል እስላማዊ ዓቀበተ እምነት አለ፡፡ የኛ መጻሕፍት ስለ መሐመድ በተተነበዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተሞሉ ናቸው፡፡እመሰጥባቸው ነበር፡፡ በተጨማሪም ትርጉሙ ባይገባኝም ዝም ብዬ ብቻ "አሪት ዘዳግም!" ማለት ያስደስተኝ ነበር፡፡

"እሺ የመጨረሻ ጥያቄ፡፡ መሐመድ መካን ባሸነፈ ጊዜ ምን ነበር ያደረገው?"

"መካውያንን በሙሉ ይቅር አላቸው!"

"አዎ..." አባዬ በስሜት ተዋጠ፡፡ በዚህ ጊዜ በተመስጦ ሆኖ ሊናገር እንደሆነ ገባኝ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ለእስልምና ያለው ፍቅር ስለሚያሰክረው ሊሰማው የሚችል ማንም

ሰውእንኳ ባይኖር ዝም ብሎ ለነፋስ ይናገራል፡፡ ብዙ ጊዜ እንደርሱ አይሆንም ነገር ግን እንደርሱ ሲሆን የደስታ ስሜት ይሰማኛል፡፡ የሚናገረውን በተመስጦ አዳምጣለሁ፡፡

"አዎ፣ ሁሉንም ይቅር አላቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች የመሐመድን አጎት የገደሉ፣ ለከዲጃ ሞት ተጠያቂዎች የሆኑ፣ ሙስሊሞችን ለብዙ ዘመናት ያሳደዱና ኢጋዥ በሌለው ማሕበረሰብ ላይ ብዙ የጦርነት ዘመቻዎችን ያደረጉ ሰዎች ነበሩ፡፡ በመጨረሻም መሐመድ እነርሱን የማጥፋት ዕድል ሲያገኝ የሚገባቸው ባይሆንም ሁላቸውንም ይቅር አላቸው፡፡ መሐመድ *ራህመቱላህ፣* የአላህ ምህረት ተብሎ መጠራቱ ያስደንቃልን?"

የአባዬ ዓይኖች ቡዝዝ ብለው የአድማሱ ጥግ ላይ አተኮሩ፡፡ ለነቢያችን ያለን አክብሮትና ተከታዮቹ በመሆናችን ምክንያት የሚሰማን የኩራት ስሜት እያየለ የሚናገረውን እያንዳንዱን ቃል ልቅም አድርገን እንሰማ ነበር፡፡

"ብዙ መካውያን በዚያን እለት የመሐመድን ምህረት በመመልከት የእስልምናን ውበት መሰከሩ፡፡ በአረብያ ይኖሩ የነበሩት ሕዝቦች ሁሉ በመሐመድ በመደነቅ እስልምናን ተቀበሉ፡፡ መልእክተኛውና መልእክቱ እጅግ ድንቅ ስለነበሩ የእስልምና ግዛተ መንግሥት በአጭር ጊዜ ውስጥ ከእስፔን እስከ ሕንድ ተስፋፋ፡፡ በዓለም ታሪክ ከተፈጠሩት ታላላቅ ስልጣኔዎች መካከል ግንባር ቀደም ነበር፡፡ ምዕራባውያን በጨለማ ዘመን ውስጥ በሚኳትኑበት ወቅት እስልምና ወርቃማውን ዘመን ያጣጥም ነበር፡፡የምዕራባውያን ሥልጣኔ የእስላም ባለ ዕዳ ነው፡፡ ሳይንስ፣ መድኃኒት ቅመማ፣ ሒሳብ፣ ፍልስፍና ... በእነዚህ ሁሉ መስኮች ሙስሊሞች የገዘፈ ተፅዕኖ ነበራቸው፡፡ ለዚህ ነው እስከ ዛሬ ድረስ አልጀብራና አልኬሚ የሚሉትን የመሳሰሉ የአረብኛ ቃላት በውስጣቸው የምናገኘው፡፡ የሚያሳዝነው ነገር የምዕራባውያን ስልጣኔ ድል በነሳ ጊዜ ሁሉንም ደመሰሱት፡፡ ሙስሊም ሊቃውንት ተገደሉ፣ ቤተ መጻሕፍት ተቃጠሉ፣ ከተሞች ፈራረሱ፡፡ የእስፔን ወረራ ክርስቲያኖች በሙስሊሞች ላይ ለፈፀሙት ነገር አንዱ ማሳያ ነው፡፡"

“ነገር ግን ክርስቲያኖች ለምንድነው በሙስሊሞች ላይ እንዲህ ዓይነቱን ነገር የሚፈፅሙት?” ከፍ ባለ ድምፅ ጠየቅሁኝ፡፡ “**ሐዝራት** ዒሳን ይከተሉት የለም እንዴ?”

**ሐዝራት፡** “የተከበረ” የሚል ትርጉም ያለው የክብር መጠርያ፡፡
**ዒሳ፡** በአረብኛ ኢየሱስ

“ቤይታ፣ የሐዝራት ዒሳ ተከታዮች አልነበሩም፡፡ እርሱን መከተል ካቆሙ ዘመናት ተቆጥረዋል፡፡ ኢየሱስን ወደ አምላክነት በመቀየር አቀለሉት፤ በአላህ ላይም ክህደት ፈፀሙ! ለዚህ ነው አላህ መሐመድን እንደ መጨረሻው ነቢይና እስልምናን እንደ መጨረሻው መልእክት ለዓለም የላከው፡፡ አላህ በነቢያቱ በኩል የላካቸውን መልእክቶች ሁሉ የያዘ ነው፤ አዳም፣ ኖኅ፣ አብረሃም፣ እስማኤል፣ ይስሐቅ፣ ሙሴ፣ ዳዊት፣ ኤልያስ … ሁላቸውም ለሕዝቦቻቸው ከአላህ ዘንድ መልእክቶችን ያመጡ ሲሆን ሕዝቦቻቸው መጀመርያ ላይ ተቀብለዋቸዋል፡፡ ነገር ግን የኋለኞቹ ትውልዶች ሁላቸውንም በርዘዋቸዋል፡፡ ከምንጫቸው በራቅን ቁጥር ብርሃናቸው እየደበዘዘ ይሄዳል! ለዚህ ነው ዛሬ የሚገኘውን መጽሐፍ ቅዱስ ማመን የማንችለው፤ ተበርዟል፡፡ ትክክለኛው ቁርአን ብቻ ነው፡፡ እስልምና ብቻ ነው መበረዝ የማይችለው፡፡ መልእክቱ እስኪሰራጭና መላው ዓለም ሙስሊም እስኪሆን ድረስ አላህ ይጠብቀዋል፡፡ ያ የፍርድ ቀን የሚመጣበት ነው፡፡ ያ እስልምና ድል ነሺ የሚሆንበት ዕለት ነው፡፡”

አባዬ ለእምነቱ ባለው ፍቅር ሁላችንም ደስተኞች ነበርን፡፡ ለመጪው ዓለም አቀፋዊ እስላማዊ የበላይነት ያለውንም ራዕይ ተቀብለናል፡፡ ይህንን ድል ነውጠኛ የሚያደርገው ምንም ነገር የለም፡፡ ይህ የሚያማልል ዓይነት አፈፃፀም ነው፡፡

እንዲህ እንዲህ እያልን ለጥቂት ጊዜ በምናብ ከተንሳፈፍን በኋላ እማ ወደ ምድር መለሰችን፡፡ “ቻሎ፣ ይህ በቂ ነው፡፡ ከአፍታ በኋላ መስጊድ እንደርሳለን፡፡ እንዘጋጅ፡፡” ትክክል ነበረች፡፡ ወደ መስጊድ እየቀረብን ነበር፡፡ ጊዜ ራሱ የቆመ ስለመሰለኝ ከመርከቢቱ ላይ ስንወርድ እንኳ አልታወቀኝም ነበር፡፡ ስለ ሃይማኖት መወያየት በጣም ያስደስተኛል፡፡ ቁርአን፣ አላህ፣ መሐመድ፣ ቀናት፣ ስሞች፣ ቦታዎች … ሁላቸውም ቀልቤን ይስቡት ነበር፡፡ ስለ መጽሐፍ ቅዱስና ስለ ኢየሱስ ማውራት እንኳ ያስደስተኝ

ነበር፡፡ በኔ ዕይታ ይህ ሁሉ አላህ ለሰው ልጆች ያቀደውና በምድር ላይ ከኖሩት መካከል ታላቁ ሰው በሆነው በመሐመድ በኩል እውን የሆነ እቅድ እንደሆነ ይሰማኝ ነበር፡፡ ልባችንን ለእርሱ ሰጥተናል፣ ከእርሱም ጋር ቃልኪዳን አድርገናል፡፡

ምዕራፍ ስድስት

# በጸሎት ሥርአት የሚገኝ ፅድቅ

ልጅ ሳለሁ የግላስጎው መስጊድ ከምወዳቸው ቦታዎች መካከል አንዱ ነበር፡፡ ከአውራ ጎዳናው ትንሽ ፈንጠር ብሎ ባልተለመደ አቀማመጥ በክሊድ ወንዝ አጠገብ ይገኛል፡፡ በቀይ ድንጋዮች የተሰራና አረንጓዴ ጣርያ እንደ ኮፍያ የደፋ ሲሆን በስርአት ያልተደረደሩ መወጣጫዎች ያሏቸው ብዙ ወለሎች፣ በሮችና መተላለፍያዎች ነበሩት፡፡ ከሌሎች ሙስሊም ልጆች ጋር አኩኩሉ ለመጫወት አመቺ ቦታ ነበር፡፡

ከልጆች ጫወታ በተጨማሪ ብዙ የምዕመናን ክንዋኔዎች በመስጊዱ ውስጥ ይታዩ ነበር፡፡ ለዓመት በኣላት፣ ለክብረ በኣላት፣ ለቀብር ሥርአቶች፣ ለሠርግ፣ ለሽርሽር፣ ለመዝናናትና ለሌሎችም ብዙ ጉዳዮች እንደ ማሕበረሰብ እንሰበሰብ ነበር፡፡ መስጊድ ለሙስሊሞች በተለይም ደግሞ ከአገር ቤት ርቀው ለሚኖሩ ሕብረት ለናፈቃቸው ሙስሊሞች በጣም የተወደደ ቦታ ነው፡፡ ነገር ግን ከነዚህ መካከል አንዱ እንኳ የመስጊድ ዋነኛ ዓላማ አይደለም፡፡

**ሰላት፡** የሙስሊሞች ሥርአታዊ ጸሎት

የመስጊድ ዋና ዓላማ የጋራ ጸሎት፣ **ሰላት** ነው፡፡ እነዚህ በቀን አምስት ጊዜ በሙስሊሞች የሚፈፀሙ የግዴታ ጸሎቶች ናቸው፡፡ መጀመርያ እንቆማለን፣ ከዚያ እናጎነብሳለን፣ ከዚያ ለአጭር ጊዜ በግንባራችን መሬት ላይ እንደፋለን፣ ከዚያ ቀና በማለት ተረከዛችን ላይ እንቀመጣለን፣ በአረብኛ የተሸመደዱ ጸሎቶችንም ወደ አላህ እንጸልያለን፡፡

እያንዳንዳቸው አምስቱ የዘወትር ጸሎቶችየየራሳቸው ስም አላቸው፡ *ፈጅር፣ ዙህር፣ መግህሪብ እና ኢሻ፡፡* ቃላትና አሰጋገዶች ለሁሉም አንድ ቢሆኑም ነገር ግን የድግግሞሽ ልዩነት አላቸው፡፡ እያንዳንዱ ድግግሞሽ **ረካት** በመባል ይታወቃል፡፡ አንድ ሙስሊም በቀን አስራ ሰባት ረካት መጸለይ ይጠበቅበታል፤ አማራጭ ጸሎቶችም ጎን ለጎን ይደረጋሉ፡፡ በኛ ጀማት ከተቻላ በየዕለቱ ሠላሳ አንድ ረካት እንድንጸልይ ተምረናል፡፡

የጸሎት ሰዓታት ለሙስሊሞች የየዕለት የሰዓት አከፋፈል በመሆን ያገለግላሉ፡፡ አዛን ለፈጅር ያነቃናል፣ ለዙሁር ከረፋዱ ሥራችን አረፍ እንላለን፣ ከአስር በኋላ ወደ ቤታችን እንሄዳለን፣ ከመግህሪብ በኋላ እራት እንበላለን፣ ከኢሻ በኋላ ደግሞ ለመኝታ እንዘጋጃለን፡፡ ልክ አዛን እንደተሰማ እነዚህን ጸሎቶች ከመፈፀማቸው በፊት ሙስሊሞች **ውዱ**በመባል የሚታወቅ የትጥበትሥርኣት ይፈፅማሉ፡፡ ይህም ሥርኣታዊ የእጅ፣ የፊትና የእግር ትጥበት ነው፡፡ ውዱ በሚፈፅሙባቸው ጊዜያት የተሸመደዱ ዱኣዎችን ይጸልያሉ፡፡ ከዚያም በጥድፊያ ወደ ጸሎት ስብሰባው ይሄዳሉ፡፡

> ***ረካት፡*** *በመቆም፣ ማጎንበስ፣ መስገድ እና መቀመጥ የጠከፋለ የሰላት ክፍልፋይ፡፡*
>
> ***ውዱ፡*** *ከሰላት በፊት የሚደረግ የመታጠብ ሥርኣት፡፡*
>
> ***ኢማም፡*** *ብዙ ጊዜ በመስጊድ ፀሎትን የሚመራ የሙስሊሞች መሪ*

በመላው ዓለም የሚገኙት ሙስሊሞች ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ በሆነ ሁኔታ ይጸልያሉ፡፡ በርግጥ ለጸሎት በሚቆሙበት ሰዓት ሁላቸውም ጥቁር አራት ጎን ወደሚመስለው ከዕባ ወደተባለው የሙስሊሞች የተቀደሰ ቦታ ፊታቸውን በማዞር ነው፡፡ በሙስሞች አፈታሪክ መሠረት ካዕባን የሰሩት አብርሃምና ልጁ እስማኤል ነበሩ፡፡ መሐመድ ወደ መዲና ከተሰደደ በኋላ ሙስሊሞች ሁሉ በሰላት ሰዓት ወደ ካዕባ እንዲዞሩ አዟቸዋል፡፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ካዕባን በከበበው ዋናው መስጊድ ውስጥ ሲቆሙ ክብ በመስራት እንዲሁም በመላው ዓለም በረድፍ በመቆም ስግደታቸውን ይፈፅማሉ፡፡ በምዕራብ የሚኖሩ ሙስሊሞች ትክክለኛውን አቅጣጫ ለማወቅ ኮምፓስ

ሲጠቀሙ ሳታዩ አትቀሩም፡፡ ኮምፓስ የተገጠመላቸው የጸሎት ክፍሎችን እንኳ አይቻለሁ፡፡

ጸሎቱ **ኢማም** በተባለ አንድ ሰው ይመራል፡፡ ሴቶችና ወንዶች በተለያዩ ክፍሎች ውስጥየሚጸልዩ ቢሆኑም ነገር ግን የኢማሙን ድምፅ መስማት በሚችሉበት ርቀት ላይ ይሆናሉ፡፡ ኢማሙ ሲመራ የተወሰኑ የጸሎቱ ክፍሎች በዝምታና በግል ይጸለያሉ፣ ሌሎቹን ደግሞ ኢማሙ ድምፁን ከፍ በማድረግ ይናገራቸዋል፡፡ እያንዳንዱ የጸሎቱ ክፍል በቁርአን ንባብ የታጀበ ሲሆን ኢማሙ ሁልጊዜ እነዚህን በቃል ያነበንባቸዋል፡፡

በጸሎት ሰዓት ቁርአንን ማነብነብ በሰባተኛው ክፍለ ዘመን ይኖር በነበረው በአብዛኛው ፊደል ባልቆጠረው ማሕበረሰብ መካከል ቁርአንን ለማስተማር የተዋጣለት መንገድ የነበረ ሲሆን ይህ ዘዴ ዛሬም ድረስ ይሠራል፡፡ ለዚህ ነው አንድ ሰው ኢማም ለመሆን የሚያስፈልገው ብቸኛ መመዘኛ ቁርአንን ማወቅና አብዛኛውን ክፍል በቃል ማነብነብ የሆነው፡፡ አልፎ አልፎ ኢማሙ ሲያነበንብ ሳለ ስህተቶችን ሊሰራ ይችላል፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ ማስተካከያ መስጠት ከፊት የሚቆሙት ሰዎች ኃላፊነት ነው የሚሆነው፡፡ ከዚህ የተነሳም በሰላት ሰዓት ከፊት የሚቆሙት ሰዎች በእድሜ ጠና ያሉ፣ የተከበሩ ሙስሊሞች ሆነው ይታያሉ፡፡

ከዚህ አነስተኛ ሁኔታ በተረፈ ሙስሊሞች በሰላት ጊዜ በሚኖረው እኩልነት ኩራት ይሰማቸዋል፡፡ ከባለጠጎች ጀምሮ እስከድሆች፣ ከመሪዎች እስከ ተራ ሰራተኞች ድረስ ሁሉም ሰው ጎን ለጎን ቆሞ በአንድነት ይጸልያል፡፡ ማንም የማይናገርበት፣ በጸላዮች ፊት የማያቋርጥበት፣ ማንም ጣልቃ የማይገባበት ክቡር ሥርኣት ነው፡፡

በእርግጥ ከአምስት አመት ቀዥቃዣ አሜሪካዊ ህፃን በስተቀር ይህንን ለማድረግ የሚደፍር ማንም የለም፡፡ በሰላት ሰዓት በጸላዮቹ መካከል ስሽሎከሎክ ከድርጊቴ እንድታቀብ የሆነ ሰው በስሱ ኩርኩም ያቀምሰኝ ነበር፡፡ ወላጆቼ በዚህቅሬታ አይገባቸውም ነበር፤ አንድን ህፃን ማሳደግ የመስጊዱ ሁሉ ኃላፊነት እንደሆነ ስለሚታመን የኛ ጀማት አባላት ጥልቅ የሆነ መተማመን ነበራቸው፡፡

ከዕለታት በአንዱ ቀን እንደ ልማዴ በሰላት ሰዓት ያለ እረፍትስሯሯጥ አንድ እጅ ከበስተጀርባዬ ቸብ ሲያደርገኝ ተሰማኝ፡፡ ማን እንደመታኝ ለማየት ዘወር ብል ማንንም ማየት አልቻልኩኝም፡፡ በቅርብ ርቀት ላይ የነበረው አጎቴ ስለነበር እርሱ እንደመታኝ በማሰብ የሰላት ሰዓቱ ሲያበቃ እምባ እያዘራሁከሰስኩት፡፡ ፊቱ ላይ ምንም ምልክት ሳያሳይ ጣቱን ወደ ሰማይ በመቀሰር "አላህ ነው የመታህ" አለኝ፡፡ ከዚያም በመገረም "ወይኔ፣ በፍጥነት ዘወር ብዬ ቢሆን ኖሮ የአላህን እጅ ለጥቂት አይቼ ነበር!" ብዬ አሰብኩኝ፡፡ ከዚያን ቀን ጀምሮ በሰላት ሰዓት አደብ ገዝቼ መቆም ጀመርኩኝ፡፡ ከሃያ ዓመታት በኋላ አጎቴ እንደመታኝ ቢናዘዝም እስከዚያችዕለት ድረስ ግን በአላህ በራሱ እጅ በመመታቴ ኩራት ይሰማኝ ነበር፡፡

ቃላቱና አቋቋሙ ሁሉ የተሸመደዱ ስለሆኑ" ሰላትን ግላዊ የሚያደርገው ምንም ነገር የለም፡፡ ለአብዛኞቹ ሙስሊሞች የግዴታ ተግባር እንጂ ግላዊና ልባዊ አይደለም፡፡

አንድ ሰው የሚያነበንባቸውን ቃላት ትርጉም እያሰበ በመጸለይ ግላዊ ሊያደርገው ቢችልም ነገር ግን በየዕለቱ አስራ ሰባቱንም ረካቶች በዚያ መልኩ የሚተገብር ሙስሊም አይኖርም፡፡ ቃላቱ ራሳቸው በባዕድ ቋንቋ በመሆናቸው ምክንያት አነብናቢው ሊያሰላስላቸው አይችልም፡፡ ይህ ለአረብኛ ተናጋሪዎች እንኳ እውነት የሆነ ጉዳይ ነው፡፡ አረቦች ከቦታ ቦታ የሚለያዩ የተለያዩ ዘዬዎች ያለውን አረብኛ ነው የሚናገሩት፡፡ የጥንቱን አረብኛ የሚማሩት በትምህርት ቤት ነው፡፡ የዘወትር ጸሎት ቋንቋ የማንም አይደለም፡፡

እውነቱ ይህ ሆኖ ሳለ ሙስሊሞች ለምን በቀን አምስቴ እንደሚጸልዩ በማሰብ ግራ የሚገባው ሰው ሊኖር ይችላል፡፡ ለግላችን ምንም ትርጉም የማይሰጡን ከሆነ ተመሳሳይ ቃላትን በቀን አምስቴ ማነብነቡ ትርጉሙ ምንድነው? ወጣት እያለሁ እኔ ራሴ ግራ ይገባኝ ስለነበር አባቴን ጠይቄው ነበር፡፡ እርሱም ሲመልስ እንዲህ በማለት ነበር፡- "ነቢል በአላህ ፊት ሁላችንም የቆሸሽን ስለሆንን የእርሱ ማንፃት ያስፈልገናል፡፡ እስኪ

**ጁማ፡** የሙስሊሞች ሰንበት ስም

በቀን አምስት ጊዜ ብትታጠብ ምን ያህል ንፁህ ልትሆን እንደምትችል አስብ! ሰላት ሁልጊዜ ንፁህ እንድንሆን አላህ የሰጠን መንፈሳዊ ባኞ ነው፡፡ ለዚህ ነው በቀን አምስት ጊዜ የምንፀልየው፡፡”

በጸሎቱ ውስጥ ጥቂት ልዩነቶች ይታያሉ፡፡ በሙስሊሞች ሰንበት ቀን ማለትም አርብ አርብ ኢማም ስብከቱን ካቀረበ በኋላ ሙስሊሞች **ጁማ** የተባለ የተለየ የዙህር ጸሎትይጸልያሉ፡፡*ጁማ* የሚለው ቃል “ስብስብ” የሚል ትርጉም አለው፡፡ ይህ ጸሎት የሚጸለየው ሦስት ሰዎችና ከዚያ በላይ ሲኖሩ ነው፡፡ የአርብ ጸሎት አስፈላጊ ከመሆኑ የተነሳ የአርብ ቀን በአረብኛና በኡርዱ ከእርሱ ስያሜውን አግኝቷል፡፡ ሦስት አርብ ጸሎቶችን በተከታታይ ከገደፍን ፈፅሞ የማይጠፋ ጥቁር ጠባሳ በልባችን ላይ እንደሚፈጠር እናትና አባታችን አስተምረውናል፡፡

እንዳለመታደል ሆኖ መስጊድ ከቤታችን ካለው ርቀትና በአባዬ መርሃ ግብር ምክንያት አርብ አርብ ወደ መስጊድ መሄድ አንችልም ነበር፡፡ ለአምስቱ የዘወትር ጸሎቶችም መሄድ አንችልም ነበር፡፡ የአርብና የዘወትር ጸሎቶችን እንደ ቤተሰብ በቤታችን እንጸልይ ነበር፡፡ አባዬ ወደ ሌላ ቦታ ቢሄድና በቤት ውስጥ ሌላ ወንድ ዘመድ ባይኖር እማና ባጂን በጸሎት የምመራቸው እኔ ነበርኩኝ፡፡ እማዬ ለዚያ መብቃቴን በማረጋገጧ ምክንያት ይህንን ማድረግ የጀመርኩት ገና ልጅ ሳለሁ ነበር፡፡

ጸሎት መምራት ቢያስደስተኝም እንዲሁም በመስጊድ የሚገኙት አንዳንድ ኢማሞች ደስ የሚል ዜማና ግርማ ሞገስ ቢኖራቸውም አባዬ ግን ተወዳጁ ልዩ ኢማም ነበር፡፡ የምት አጠባበቁ፣ ድምፁ፣ ዜማውና በቤተሰባችን ፊት ሲቆም የሚታይበት ግርማ ሞገስ ፍፁም ሆኖ ይታየኝ ነበር፡፡ አሁን እንኳ ዓይኔን ብጨፍን ረጃጅም የቁርአን ክፍሎችን ሲያነበንብ ድምፁ በምናብ ጆሮዬ ይንቆረቆራል፡፡ እነዚህን ክፍሎች የያዝኩበት ምክንያት አባዬ በተደጋጋሚ ስለሚያነበንባቸው ነበር፡፡ ሰላት አባቴ መንፈሳዊ መሪዬ መሆኑን እንዳምንና ቁርአን በልቤ ላይ እንዲታተም አድርጓል፡፡ የሰላት ኃይል የዚያን ያህል ነው፡፡

# በእስልምና ውስጥ የሚገኝ ክፍፍል

1989 ዓ.ም. ለኛ ጀማት ወሳኝ ነበር፡፡ ቤተ እምነታችን፣ ማለትም የአሕመዲያ ቤተ እምነት ምስረታ መቶኛ ዓመት ሲሆን ይህንን ክብረ በዓል ለመካፈል ሰዎች ከመላው ዓለም በእንግሊዝ አገር ተሰብስበው ነበር፡፡ ይህ ጊዜ እኛ በእንግሊዝ አገር ከነበርንበት ጊዜ ጋር በመገጣጠሙ ምክንያት የኔ ቤተሰብ ይህንን ዕድል እንደ ትልቅ በረከት ነበር የቆጠረው፡፡ ይህንን ክብረ በዓል ከተካፈሉት በአስር ሺህዎች ከሚቆጠሩት ሰዎች መካከል ለመቆጠር ታድለናል፡፡

ክብረ በዓሉ የተደረገው በእንግሊዝ ውስጥ በሚገኝ ቲልፎርድ በተሰኘ ገጠራማ አካባቢ ሲሆን  ትልልቅ ዳሶች እንደ ስብሰባ አዳራሾችና የታጨዱ ሳሮች ደግሞ እንደ መንገድ ሆነው ነበር፡፡የሚጸለይባቸው፣ ምግብ የሚሸጥባቸው፣ የሳተላይት ስርጭት የሚከናወንባቸውና በራሪ ወረቀቶች የሚሸጡባቸው ድንኳኖች ነበሩ፡፡ ዝግጅቱን ለመታደም ከመላው ዓለም የተጋበዙ ዲፕሎማቶችና ባለስልጣናት የነበሩ ሲሆን ብዙዎቹ የመቻቻልና የሕብረ ባሕል መልዕክቶችን ነበር ይዘው የመጡት፡፡

ወንዶች በሚቀመጡበት በኩል እንዲቀመጡ የተፈቀደላቸው ሴት ዲፕሎማቶች ብቻ ነበሩ፡፡ ሴቶች የተቀመጡበት ረድፍ ከወንዶቹ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ለብቻው የተለየ ነበር፡፡ ገና ልጅ ስለነበርኩኝ ወደ ሴቶች ክፍል ብገባ የሚደነግጥ አልነበረም፡፡በተደጋጋሚም እገባ ነበር፡፡ ከወንዶቹ ረድፍ ይልቅ የተነቃቃ ነበር፡፡ ሴቶቹ በቀለም ያጌጡ ልብሶችን ለብሰዋል፡፡ ድምፃቸውን ከፍ በማድረግም ይስቁ ነበር፡፡ ከወንዶች ረድፍ በቴሌቪዥን የሚተላለፈውንም ንግግር ችላ በማለት ወሬ ይሰልቁ

ነበር፡፡ የወንዶቹ ረድፍ ድባብ ቀዝቀዝ ያለ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለስድስት ዓመት ልጅ አሰልቺ ነው፡፡ ከዋና ክፍለ ጊዜያት በአንዱ ከሴቶች ክፍል ወጥቼ በልዩ ሁኔታ የተዘጋጁ ባጆች ይሸጡበት ወደነበረው ወደ ወንዶች ባዛር አቀናሁ፡፡ እየሄድኩኝ ሳለሁ በመካከል አንድ ዕድሜው ጠና ያለ ሰው ትከሻዬን አፈፍ አድርጎ ያዘኝ፡፡ጠምዝዞ በማዞር ይዞ ወደ ወንዶች ክፍል መራኝ፡፡ ከፊት ለፊት ወደ ራሱ አስጠግቶ አስቀመጠኝ፡፡ በአንደበቱ ባይናገረኝም ነገር ግን ኮስተር ያለው አስተያየቱ "አርፈህ ቁጭ በልና ንግግሩን ስማ" የሚል መልዕክት ነበረው፡፡ እስከ ዛሬ ድረስ የዚያን ሰው ማንነት ባላውቅም ነገር ግን በጀማት ቦታ ትልቅ ሰው አለመታዘዝ ነውር መሆኑን ስለተገነዘብኩኝ ንግግሩን መስማት ጀመርኩኝ፡፡

ተናጋሪው ከፓኪስታን የመጣ ሚስዮናዊ በመሆኑ ቅላፄው ለመስማት ያዳግታል፡፡ የመጀመርያ ቋንቋው ከኡርዱ ጋር ቅርርብ ያለው ፐንጃቢ የተሰኘ ቋንቋ ሲሆን በፓኪስታን ገጠራማ አካባቢዎች የሚነገር ነው፡፡ እንግሊዘኛውን በፐንጃቢኛ ቅላፄ ሲዳምጠው ጆሮን ይፍቃል፡፡ መልእክቱ ትልልቅ ሰዎች በሚገኙበት ጀማት የሚነገረውን የሚመጥን ሲሆን በተደጋጋሚ ሰምቼዋለሁ፡፡

እኛ ሙስሊሞች የመሆናችንን እውነታ እያስረዳ ነበር፡፡

"ሌሎች ሙስሊሞች እኛ ሙስሊሞች እንዳልሆንን ነው የሚናገሩት ነገር ግን እኛን ከእስልምና ለማስወጣት እነርሱ ማናቸው? አነስ ኢብን ማሊክ እንዳስተላለፈው መሐመድ እንዲህ ብሏል '**ሸሃዳን** የሚያውጅ ማንኛውም ሰው ሙስሊም ነው፡፡' ሸሃዳ ደግሞ ግልፅ ነው፡ 'ከአላህ በስተቀር አምላክ የለም መሐመድም መልእክተኛው ነው፡፡' ዛሬ እንኳ ማድረግ የሚኖርባችሁ ነገር ቢኖር ሸሃዳን ማወጅ ነው፤ ከዚያ በእስልምና ውስጥ ትጠቃለላላችሁ፡፡"

**ሸሃዳ፡**'ከአላህ በስተቀር አምላክ የለም መሐመድም መልእክተኛው ነው' የሚለው የሙስሊሞች ዋነኛ የእምነት መግለጫ፡፡

ይህንን በቀጥታ እያለ ያለው እንደ እየተቆራጠጡ ለሚሰሙት ዲፕሎማቶች ይመስላል፡፡

“ሙስሊም ለመሆን እያንዳንዱ ሰው ሸሃዳን ማነብነብ ይኖርበታል፡፡ በዚህ ውብ የሆነ የነቢያችን የመሐመድ ﷺ ሐዲስ መሠረት ሙስሊም ለመሆን ያንን ማድረግ ብቻ ይበቃዋል፡፡”

በዚህ ጊዜ ሚስዮናዊው የበለጠ እየጋለ መጣ፡፡ ከዓመታት በኋላ የእርሱ የቅርብ ሰዎች በሌሎች ሙስሊሞች እጅ አሰቃቂ ስደት እንደደረሰባቸው ሰምቻለሁ፡፡ ከእርሱ ሕብረት አባላት መካከል አንዳንዶቹ እንዲያውም ተገድለዋል፡፡

“ሸሃዳን አለመቀበል ሙስሊም እንዳትሆኑ ያደርጋችኋል፤ ሸሃዳን ማወጅ ሙስሊም እንድትሆኑ ያደርጋችኋል፤ እኛ ደግሞ ሸሃዳን እናውጃለን፡፡ በቃ ይኸው ነው፡፡ እኛ ሙስሊሞች ነን! ነገር ግን በእስልምና ድንበር ላይ እየኳተንን ያለን ይመስል ለምንድነው ይህንን ግልፅ ማድረግ ያስፈለገኝ? ከእስልምና ግዴታዎቻችን መካከል ችላ ያልነው ይኖር ይሆን? በፍፁም!”

**አምስቱ የእስልምና አዕማዶች፡** ከሙስሊሞች ሁሉ የሚጠበቁ መሰረታዊ የእስልምና ልምምዶች
**ዘካት፡** ግዴታ ምፅዋት
**ሐጅ፡** በየዓመቱ ወደ መካ የሚደረግ ሃይማኖታዊ ጉዞ
**ስድስቱ የእምነት አቋሞች፡** መሰረታዊ የሙስሊም እምነቶች

ፈጠን በማለት የሙስሊሞች ሁሉ ግዴታ የሆኑትን አምስቱን የእስልምና መሠረታዊ ልምምዶች ዘረዘረ፡፡ እነዚህም **አምስቱ የእስልምና አዕማዶች** በመባል ይታወቃሉ፡፡

“ሸሃዳን እናውጃለን፤ ሰላት እንሰግዳለን፤ **ዘካት** ለምንዱባን እንሰጣለን፤ በረመዳን ወር እንፆማለን፤ **ሐጅ** ለመፈፀም ወደ ካዕባ እንሄዳለን! እነዚህ እንድንፈፅማቸው በአላህ በቁርአን ውስጥ የታዘዝናቸው ነገሮች ናቸው፡፡ ሁላቸውንም ደግሞ እንፈፅማለን፡፡ ታድያ ሙስሊሞች መሆናችንን ሊክድ የሚችል ማነው?

ይህንን ከቁርአንና ከሐዲስ ስናብራራላቸው ሌላ ዘዴ በመፈለግ ተቃውሚቸውን ይቀይራሉ! ‘በተግባር ሙስሊሞች ለመምሰል ትሞክራላችሁ ነገር ግን መሐመድ

ያስተማረውን አታምኑም!' ይሉናል፡፡ እርሱ ያስተማረው እኛ የማናምነው ምን እንደሆነ እስኪ ንገሩኝ?"

ሚስዮናዊው ከመሠረታዊ ልምምዶች**ስድስቱ የእምነት አቋሞች** ወደሚባሉት መሠረታዊ እምነቶች ዘለለ፡፡

"አንድ አምላክ በሆነው በአላህ እናምናለን፤ በማይታዩት መንፈሳዊያን ፍጥረታት እናምናለን፤ አላህ ነቢያትን ወደዚህ መላኩን እናምናለን፤ ለነቢያቱ ቅዱሳት መጻሕፍትን መስጠቱን እናምናለን፤ የፍርድ ቀን እንዳለ እናምናለን፤ የአላህ ቅድመ ውሳኔ በአፅናፈ ዓለም ላይ ሉኣላዊ መሆኑን እናምናለን! ታድያ የቀረ የማናምነው ምንድነው?

እኛ የማናምነው ውሸትን ነው! እንደ ሺኣዎች አላህ አቡበከርን ኸሊፋ በማድረጉ ምክንያት ስህተት መስራቱን አናምንም! ሱኒዎች ደግሞ እንደሚያደርጉት በአላህ ስም ሙስሊሞችን መግደል ይቅርና ማንንም ሰው በመግደል አናምንም! እነዚህን መጥፎ እምነቶች ብንቀበል ኖሮ ሙስሊሞች አይደላችሁም መባላችን ትክክል በሆነ ነበር!"

የአሕመዲ ሚስዮናውያን አስቸጋሪ የሆኑትን ጉዳዮች በጥንቃቄ የመያዝ ሁኔታ አይታይባቸውም፡፡ የቃላት አመራረጡ ግርድፍ ቢሆንም በንግግሩ ውስጥ ግን የተወሰነ እውነታ አለበት፡፡ በሺኣና በሱኒ መካከል የሚገኘውን ዋና የሆነውን የሙስሊሞች ክፍፍል እየተናገረ ነበር፡፡ ሦስት ዋና የሆኑ የሺኣ እስልምና ክፍሎች ያሉ ሲሆን ሺኣዎች በአጠቃላይ ከዓለም ሙስሊሞች 10-15 በመቶ ያህል ይሆናሉ፡፡ በእስልምና የመጀመርያዎቹ ዘመናት ሥልጣን የሚተላለፈው በመሐመድ የዘር ሐረግ እንደሆነ ያምናሉ፡፡ ስለዚህ መሐመድ ከሞተ በኋላ ለመሐመድ ቅርብ የሆነ ወንድ ተወላጅ ሥልጣን መያዝ ነበረበት ይላሉ፡፡ ያ ደግሞ አሊ ነበር፡፡ ነገር ግን መሐመድ በሞተ ጊዜ የተሾመ ተተኪ አልነበረም፡፡ ሙስሊሞች አቡበከርን የመጀመርያው ኸሊፋ አድርገው መረጡ፡፡ በአመዛኙ የአቡበከርን ኸሊፋነት የተቀበሉ ሙስሊሞች ከአራቱ የሱኒ መደቦች መካከል አንዱን የሚከተሉ ሲሆኑ ከዓለም ሙስሊሞች መካከል 80 በመቶ የሚሆነውን ይይዛሉ፡፡

የተቀሩት 5-10 ከመቶ የሚሆኑት ደግሞ ከነዚህ ጎራዎች መካከል የማይመደቡ ናቸው፡፡ እኛ በዚህ ውስጥ እንጠቃለላለን፡፡

“መሐመድ ሸሃዳን የምናነበንብ ከሆነ ሙስሊሞች መሆናችንን አውጇል፡፡ ያንን እናደርጋለን፡፡ አምስቱን አዕማዶች መፈፀም እንዳለብን ቁርአን ይነግረናል፡፡ ያንን እናደርጋለን፡፡ አምስቱን የእምነት አንቀፆች እንድናምን እስልምና ያስተምረናል፡፡ ይህንንም እናደርጋለን! ታድያ ለምንድነው **ካፊር** በማለት የሚጠሩን?”

**ካፊር፡**ከሃዲ፤ ሙስሊም ያልሆነ ሰው

“በቁርአን ውስጥ የሚገኙትን ሁለት ቃላት እነርሱ በሚተረጉሙት መንገድ ባለመተርጎማችን በድፍረት ካፊር ይሉናል፡፡ ሁለት ቃላት ብቻ! *‘ኸተም አን-ነቢዩን፣* የነቢያት መደምደምያ፡፡’ በነዚህ ነውጠኞችና መሃይማን ሙስሊሞች አስተሳሰብ መሠረት በነዚህ ቃላት ላይ ልዩነትን ማሳየት ሙስሊም ወንድሞቻቸውን መግደልን ያፀድቃል፣ አስቶጉፍሩላህ!”

ኢማሙ የኛ ቤተ እምነት መስራች የሆነው ሚርዛ ጉለም አሕመድ በመሐመድ ስር ነቢይ ነኝ በማለት ስለ ራሱ የተናገረውን አከራካሪ ንግር እየጠቀሰ ነበር፡፡ ብዙ ሙስሊሞች ሱራ 33፡40 ከመሐመድ በኋላ ሌላ ነቢይ ሊኖር እንደማይችል እንደሚናገር ስለሚያምኑ ሚርዛ ጉለም አሕመድ ሀሰተኛ ነቢይ እንደሆነና ተከታዮቹም ሙስሊሞች እንዳልሆኑ ይናገራሉ፡፡ ከዚህ የተነሳ ፓኪስታንና ኢንዶኔዥያን በመሳሰሉት አገራት በሺህዎች የሚቆጠሩ አሕመዲዎች በሙስሊም ወገኖቻቸው እጅ ተገድለዋል፡፡

“የሰላም ሃይማኖት የሆነውን የደም እና የሽብር ሃይማኖት ወደመሆን ለውጠውታል፡፡ ነገር ግን **ኢንሻ አላህ፣** አላህ በአሕመዲያዎች በኩል እስልምናን ያድሰዋል፡፡ የዘመናችንን ኢማም፣ ተስፋ የተገባለትን መሲህ ልኮታል፡፡ ተተኪዎቹም ደግሞ መለኮታዊ ሹመት ያላቸው ኸሊፎች ናቸው፡፡”

**ኢንሻ አላህ፡**አላህ ከፈቀደ ማለት ሲሆን የተለመደ የሙስሊሞች አባባል ነው

አሕመድ ስለራሱ ከተናገራቸው ነገሮች መካከል አስደንጋጩ ይህኛው ነው፡፡ ነቢይ መሆኑን ተናግሮ *ኸተም አን-ነቢዪን* ከሚለው ቃል ጋር ከተላተመ በኋላ አዲስ ነቢይ አለመሆኑን ለማስረዳት በመሞከር ራሱን ይከላከላል፡፡ የብዙ እምነት ተከታዮች የነቢያቶቻቸውን ተመልሶ መምጣት እንደሚጠባበቁ ይናገራል፡፡ አይሁዶች ኤልያስን ይጠብቁታል፣ ሒንዱዎች ክሪሽናን ይጠብቁታል፣ ቡዲስቶች ቡደሃን ይጠብቁታል፣ ክርስቲያኖች ደግሞ ክርስቶስን ይጠብቁታል፡፡ አሕመድ እነዚህ ሁሉ ሰዎች በአንድነት እንደሚጠቃለሉ ይናገራል፡፡ ከዚህም በላይ ተከታዮቹ አዲስ ካሊፌት መመስረታቸውን ይናገራሉ፡፡ ይህ ደግሞ የመጨረሻውን ካሊፌት የሚጠብቁትን በመላው ዓለም የሚገኙትን ሙስሊሞች ሁሉ የሚያስቆጣ ነው፡፡

“አላህን ማሸነፍ የሚችል ማነው? እርሱ ሴራ ከሚሸርቡት ሁሉ በላጭ ነው፡፡ ዓለምን በእስላምና በአሕመዲያ ያጥለቀልቃታል! ይህንን ሰይጣን እንኳ ማሰናከል አይቻለውም!”

ሚስዮናዊው ይህንን በተናገረ ጊዜ ቅፅበታዊ ጩኸቶች ከሕዝቡ መካከል ተዥጎደጎዱ፡፡ ሁሉም አንድ ነገር ነበር የሚሉት፡ “ተክቢር!” በድንኳኑ ውስጥ የተሰበሰቡት በሺህዎች የሚቆጠሩት ሰዎች በአንድ ድምፅ ምላሽ ሰጡ “አላሁ አክበር!” ጠንከር ያለው ድምፅ በድጋሚ አሸንፎ ወጣ “ተክቢር!”የተሰበሰቡት ወንዶች ሁሉ በጋለ ስሜት መልስ ሰጡ “አላሁ አክበር!”አሕመዲዎች መስማማታቸውን ለመግለፅ ብዙ ጊዜ አያጨበጭቡም ነገር ግን አላህን ለማመስገን ና በረከቱን ለመለማመን አንዳቸው ሌላቸውን ይቀሰቅሳሉ፡፡

“ተክቢር!” በማለት የጮኸው ሰውዬ አሁንም “እስላም!” በማለት ጩኸቱን ቀጠለ፣ መልሱም *“ዚንዳባድ”* (ለዘላለም ይኑር) የሚል ነበር፡፡ “እስላም!” “ዚንዳባድ!” “አሕመዲያ!” “ዚንዳባድ!” ተለይተው የማይታወቁ ድምፆች በሙብረቅ ጩኸት የሙስሊሙን ሰራዊት አላህን እንዲያወድሱ ሲመሩለተመለከተ ሰው ጊዜ ራሱ የቆመ መስሎ ሊታየው ይችላል፡፡ በርግጥ ከዳር ሆኖ ለሚመለከት ሰው ሰራዊቱ ከሰላማዊ ሙስሊሞች የተዋቀረ መሆኑ ሊገባው አይችልም፡፡በሺዎች የሚቆጠሩት ሰዎች ማጓራት እጅግ አስደንጋጭ ነበር፡፡

ምንም ነገር ሳይጨምር ሚስዮናዊው ጉባኤውን በማመስገን ንግግሩን ቋጨ፡፡ ዛሬ ላይ ደርሼ የትክክለኛነትና የስህተት ትምህርት ተከታይነት ብዙ ገፅታዎች ያሉትና ውስብስብ መሆኑን ተረድቻለሁ፡፡ በዚህ ዘመን ከጥቃቅን ነጥቦች በመነሳት ብዙ ሙስሊሞች አንዳቸው ሌላቸውን ሙስሊም እንዳልሆኑ መናገራቸው እውነት ነው፡፡ እዚህ ግቡ በማይባሉ አለመስማማቶች ሳብያ ከሃዲ ተባብሎ መፈራረጅ የተለመደ ነው፡፡ ከእነዚህ ሁሉ የእስልምና አንጃዎች መካከል የከሃዲነት ታርጋ ያልተለጠፈበት አንድ ቡድን እንኳ መኖሩን እጠራጠራለሁ፡፡

ይህ እንዳለ ሆኖ የአሕመዲያዎች መስራች ብዙ ወገኖችን ሊያስቆጡ የሚችሉ ነገሮችን ስለ ራሱ ብሏል፡፡ እርሱ የኢየሱስ ዳግመኛ ምፅዓት መሆኑን መናገሩ ክርስቲያኖችንም ሆነ ሙስሊሞችን ማስቆጣቱ እሙን ነው፡፡ ለነቢያት የሚገባውን ክብር መጠየቁ በሙስሊሞች ዘንድ በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ ትክክለኛ ሙስሊሞች የሚባሉቱ አሕመዲያን እንደ ምንፍቅና መቁጠራቸው ለምን እንደሆነ ማየት አያዳግትም፡፡

ነገር ግን ለእኔ አሕመዲያዎች ሙስሊሞች እንደሆኑ እንዳምን የሚያደርጉኝ ብዙ ምክንያቶች አሉ፡፡ ሚስዮናዊው እንደተናገረው አሕመዲያዎች ዋና ዋና የሚባሉትን የእስልምና አስተምህሮዎችና ልምምዶች ሁሉ ይተገብራሉ፡፡ የየዕለት ኑሯቸውና በተግባር የሚገለፀው እምነታቸው ሲታይ አሕመዲያዎች ከሞላ ጎደል ከሱኒ ሙስሊሞች የተለዩ አይደሉም፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ እኔ ራሴ አሕመዲ በነበርኩበት ዘመን ሙስሊም መሆኔ እንጂ አሕመዲ መሆኔ ብዙም አይሰማኝም ነበር፡፡ ነገር ግን ከዚህ በላይ መሐመድ እራሱ አሕመዲዎችን እንደ ሙስሊም ይቆጥራቸዋል፡-“ከአላህ በስተቀር አምላክ አለመኖሩን የሚያውጀውን ሰው ከማሕበር አታግልሉት”[12] ብሏል፡፡

ከዚህ መማር ያለብን ነገር ቢኖር በእስልምና ውስጥ ብዙ ክፍፍል መኖሩን ነው፡፡ አንድ ሰው ሙስሊም መሆኑን ለማወቅ እንደ መመዘኛ የሚጠቅመው አላህ አምላክ መሆኑንና መሐመድም መልእክተኛው መሆኑን ማወጁ ነው፡፡ ከዚህ ነጥብ ባሻገር ባሉት ጉዳዮች ላይ በእስልምና ውስጥ ብዙ መከፋፈል አለ፡፡

# ፍኖተ ሽሪአ

ሽሪአ ሲነሳ በእስልምና ውስጥ ከሚገኘው ብዝሃነት ጋር የተያያዙ ብዙ አመለካከቶችን እናገኛለን፡፡ ሽሪአ አብዛኞቹ ሙስሊሞች በጥልቀት የሚያውቁት ዘርፍ አይደለም፡፡ ይህንን ቃል ለመጀመርያ ጊዜ የሰማሁት የኛ ጀማት በዓመት አንድ ጊዜ በሚያዘጋጀው *ኢጅተማ* ወይም የውድድር መርሃ ግብር ላይ ነበር፡፡

ውድድሮቹ መንፈሳዊና እስፖርታዊ ገፅታዎችነበሯቸው፡፡ መንፈሳዊ ገፅታዎቹ የቁርአን ሽምደዳ፣ ቁርአንን ማነብነብ፣ የአዛን ክህሎት፣ እስላማዊ ግጥሞችን ማነብነብ፣ የንግግር ውድድር፣ የሐዲስ ሽምደዳ እና ጠቅላላ የሃይማኖታዊ እውቀት ፈታናዎችን ያጠቃልላል፡፡ እማ በመንፈሳውያኑ፣ በተለይም ደግሞ የንግግር ውድድር ላይ እንዳተኩር ታደርግ ስለነበር እስፖርታዊ ውድድሮቹ ምን ምን እንደሚያጠቃልሉ የማውቀው ነገር የለኝም፡፡

እማ ለንግግር እንድዘጋጅ በጥብቅ ታሰለጥነኝ ነበር፡፡ ንግግሩን በሙሉ ከመጻፍ አልፋ እንዴት ማቅረብ እንዳለብኝ አሰልጥናኛለች፡፡

ከውድድሩ ቀደም ብለው በነበሩት ምሽቶች ከኢሻ ሰላት በኋላ ቆሜ እንድለማመድ ታደርግ ነበር፡፡ ከበስተጀርባዬ በመቆም በንግግር መሃል የአፅንዖት የእጅ ምልክቶችን እንዳደርግ ልክ እንደ አሻንጉሊት እጆቼን ታንቀሳቅስ ነበር፡፡ ንግግሩ ጉልበት እንዲኖረው የት ማቆም እንዳለብኝ፣ ጭንቅላቴን እንዴት ማንቀሳቀስ እንዳለብኝ እንዲሁም ፍጥነትና ድምፅ እንዴት መጨመር እንዳለብኝ ታስተምረኝ ነበር፡፡ ፓኪስታን በነበረች ጊዜ

የክርክር ቡድን መሪ እንደነበረች ኋላ ላይ  ለመገንዘብ ችያለሁ፡፡ ይህ ደግሞ ከአባዬ ጋር የምታደርገውን ንግግር ለተመለከተ ሰው እውነታነቱ ይገባዋል፡፡

በዕለተ ኢጅተማ ዕድሜያቸው ከስድስት እስከ ስምንት በሆኑት ሕፃናት ቡድን ውስጥ ነበር የተወዳደርኩት፡፡ የንግግሩ ርዕስ ደግሞ “ውጤቱ ምንም ይሁን ምን ምን ጊዜም እውነትን ብቻ ተናገር” የሚል ነበር፡፡ ላደረኩት ንግግር ሽልማት ተበርክቶልኛል፡፡ በሌሎች ዘርፎችም የተወሰኑ ሽልማቶችን አግኝቼ ነበር፡፡እማና አባዬም ተወዳድረው ነበር ነገር ግን የአዋቂዎቹ ውድድር የወጣቶቹን ያህል ሞቅ ያለ አልነበረም፡፡ ውድድሩ ባጠቃላይ እስልምናን በአዲሱ ትውልድ ዘንድ በማስረፅ ላይ ያተኮረ ይመስላል፡፡ ወጣት ተሳታፊዎች እንዲካፈሉ በሚል የአዋቂዎቹ ውድድር ከወጣቶቹ በኋላ ነበር የተደረገው፡፡

ቅድመ ዝግጅ የተደረገበት የማይመስለውን የወንዶቹን የንግግር ውድድር እስከ መጨረሻው ድረስ ለመከታተል ወስኜ ቁጭ አልኩኝ፡፡ በዚህ ውድድር ላይ የተነሱት ርዕሰ ጉዳዮች ብዙ ነበሩ፡፡ “የአሕመዲ ጀማትን ታሪክ በቅደም ተከል ተናገር”፣ “ልጆቻችንን በእስልምና መንገድ ለማሳደግ ምን ማድረግ አለብን?” እና “ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ አለመሆኑን የምናውቀው እንዴት ነው?” የሚሉት ርዕሶች ከብዙዎቹ ጥቂቶቹ ነበሩ፡፡

አጎት ፈይዛን ብዬ የምጠራው ሰው “የሸሪኣን ምንጮችና አተገባበር አብራሩ”በሚል ርዕሰ ጉዳይ ላይ ንግግር ያደርግ ነበር፡፡ ይህ ሰው ዕድሜው በአርባዎቹ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን እንግሊዘኛን ጥርት አድርጎ ይናገር ነበር፡፡ ተነስቶ በመቆም ታዳሚዎቹን በተለመደ ሰላምታ አሰጣጥ ሰላም ካለ በኋላ ንግግሩን ጀመረ፡፡

“የተከበሩ ኢማም፣ የተከበራችሁ ታላላቆች፣ የተከበራችሁ እንግዶችና ውድ ወንድሞች፣ **አሰላሙ አለይኩም ወ ራሙቱላሂ ወበረካቱ፡፡**”

ክፍሉን የሞሉት ተሰብሳቢዎች *“ወአለይኩም አሰላም”* በማለት በአንድ ድምፅ መለሱለት፡፡

አጎት ፈይዛን ማስታወሻውን አየት በማድረግ ጀመረ፡፡ "ዛሬ የተሰጠኝ ርዕሰ ጉዳይ ሽሪኣ የሚል ነው፡፡ ሽሪኣ እስላማዊ ሕግ ነው፡፡ *ሽሪኣ* የሚለው ቃል ትርጉም ‹መንገድ› የሚል ነው፡፡ ይህም ማለት እንደ አላህ ፈቃድ የምንጓዝበት ትክክለኛ መንገድ ማለት ነው፡፡"

በዕለቱ ለዳኝነት የተሰየሙት ሽማግሌዎች የመደመም ዓይነት ስሜት ፊታቸው ላይ ታየ፡፡ አረብ ያልሆኑ ሙስሊሞች የአረብኛቃላትን በትክክል ከተረጎሙ በውድድርም ሆነ በሌላ በማንኛውም ንግግር ወቅት ተጨማሪ ነጥብ ያስገኝላቸዋል፡፡

ዳኞቹ በሰጡት ምላሽ የበለጠ ድፍረት በማግኘት ንግግሩን ቀጠለ፡፡ "የሽሪኣ መጽሐፍ የለም፡፡ ***ፊቅህ*** የተሰኘ የሕግ አካሄድ በመጠቀም ከተለያዩ ምንጮች በየደረጃው መሰብሰብ ይኖርብናል፡፡ ዋናውና ትልቁ ምንጭ ቁርአን ነው፡፡ የአላህ ቃል በመሆኑ ምክንያት ከቁርአን የላቀ ምንም ነገር የለም፡፡ ነገር ግን ቁርአን ሁሉን ነገር በውስጡ ያቀፈ አይደለም፡፡ እንደ ሙስሊሞች ቁርአን ውስጥ የማይገኙ ልናደርጋቸውና ልናምናቸው የሚገቡ ብዙ ነገሮች አሉ፡፡ በዚህም ሳቢያ ሁለተኛ ምንጭ ወደሆነው ወደ ሐዲስ መሄድ ያስፈልገናል፡፡"

> **አሰላሙ አለይኩም ወ ራመቱላሂ ወበረካቱ፡** የተለመደ የሙስሊሞች ሰላምታ ሲሆን "የአላህ ሰላም፣ እዝነት እና በረከት በእናንት ላይ ይሁን" ማለት ነው፡፡
>
> **ፊቅህ፡** የእስልምና የሕግ ሂደት

ቁርአን በቂ አይደለም በሚለው ንግግር ምክንያት በጉባኤው ውስጥ የነበሩ የተወሰኑ ሰዎች መደናገጥ ውስጥ ገቡ፡፡ ነገሩ ትክክል ቢሆንም በዚህ መልኩ በግርድፍ መነገር አልነበረበትም፡፡ ቁርአን መሆን ከነበረበት ደረጃ በታች እንደሆነ ስለሚያስመስል አሸማቃቂ ነው፡፡ ነገር ግን የአጎት ፈይዛን ዓይኖች በሽማግሌዎቹ ላይ አነጣጠሩ፡፡ በንግግሩ ምንም የተለየ ስሜት ስላላንፀባረቁ ቀጠለ፡፡

"ሐዲሳት በቁርአን ውስጥ የሚገኙትን ነገሮች ያብራራሉ እንዲሁም ግልፅ ያደርጋሉ ነገር ግን አይጣረሱም፡፡ በእስልምና ውስጥ ተቃርኖ የለም፡፡ ሐዲስ በማንኛውም መንገድ ከቁርአን ጋር የሚጣረስ ከሆነ ተኣማኒ ስላልሆነ ተቀባይነት ማግኘት የለበትም፡፡ አንድን

ጉዳይ ግልፅ የሚያደርግ ሐዲስ ካልተገኘ ወደ ሦስተኛው የሸሪኣ ምንጭ መሄድ ይኖርብናል፡፡ ይኸውም **ኢጅማ** ሲሆን በእስልምና የሰለጠኑ የአስተዋይ ሙስሊም ሊቃውንት ስብስብ ነው፡፡” አጎት ፈይዛን በኩራት ወደ እርሱ ሲመለከት የነበረውን ኢማም ገርመም በማድረግ ፈገግ አለ፡፡

“እነዚህ የሸሪኣ ምንጮች ናቸው ነገር ግን የት ነው የምናየው?በየትኛውም ጥሩ ሙስሊም ሕይወት ውስጥ እናየዋለን፡፡ እንዴት እንደምንጸልይ፣ መች እንደምንፆም፣ ማንን እንደምናገባ፣ የትኞቹን ምግቦች መብላት እንደሌለብን ይደነግጋል፡፡ ዋና የሆኑት ጉዳዮች ሁሉ በሸሪኣ ውስጥ ይጠቀለላሉ፡፡ በቤታችን ውስጥ ከሚገኙት ውድ እቃዎች ዘካት መክፈልን የመሳሰሉ ጥቃቅን ነገሮችንም ጭምር በጥልቀት ይተነትናል፡፡” ሽማግሌዎቹ በመጠኑ ሳቅ በማለት አጎት ፈይዛን እንዲያጠቃልል ምልክት ሰጡት፡፡

“የሸሪኣን ምንጮችና አተገባበር የተመለከተ አጭር ማብራርያ ይህንን ይመስላል፡፡ ሹክሪያ፣ አመሰግናለሁ፡፡” ይህንን በማለት ተመልሶ ወለሉ ላይ ተቀመጠ፤ ሽማግሌዎችም ጭንቅላታቸውን በመነቅነቅ አድናቆታቸውን ገለፁ፡፡

ኋላ ላይ መገንዘብ እንደቻልኩት ቢያንስ ከአሕመዲ ዕይታ አንፃር ለጥያቄው ጥሩ ምላሽ ተሰጥቷል፡፡ አሕመዲዎች ጥብቅ የሆነ የሥልጣን ተዋረድ ስላላቸው ጠባብ የምርጫ ዕድል ነው ያላቸው፡፡ የጀማት መሪዎች የሸሪኣን ሕግ ከመተርጎም አኳያ ሙሉ ሥልጣን አላቸው፡፡ እነዚህ መሪዎች የተናገሩት ነው የሚተገበረው፡፡ ለአብዛኞቹ ሙስሊሞች ግን እንደርሱ አይደለም፡፡

ሌሎች ሙስሊሞች ምርጫ አላቸው፡፡ ለምሳሌ ያህል ሱኒ ሙስሊም ሴት ፍቺ መፈጸም ብትፈልግ ከባለ ሥልጣን ይሁንታ መግኘት ይኖርባታል፡፡ ይህ ቢያንስ **ከሙፍቲ** መሆን ይኖርበታል፡፡ ሙፍቲ በመሠረታዊ የሸሪኣ ሕግ የሰለጠነ ሰው ነው፡፡ በሙፍቲ ፊት ጉዳይዋን ካቀረበች በኋላ**ፈትዋ** የተሰኘ ውሳኔውን ይሰጣታል፡፡ የእርሱ ፈትዋ ካልተመቻት

> **ፈትዋ:** በሙስሊም ባለሥልጣን የሚደረግ ድንጋጌ

ወደ ሌላ ሙፍቲ በመሄድ የተሻለ ፈትዋ መፈለግ ትችላለች፡፡

ከተለያዩ የአስተሳሰብ ጎራዎች የሆኑ ሙፍቲዎች የተለያዩ አመለካከቶች ስለሚኖራቸው የተለያዩ ፈትዋዎችን ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ ያህል አንዳንድ የሱኒ ጎራዎች አንዲት ሴት ለጋብቻ ከመስጠቷ በፊት ውሳኔዋ መጠየቅ እንዳለበት አፅንዖት ይሰጣሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ ሴት ልጅ በቤተሰቦቿ ውሳኔ ብቻ መመራት እንዳለባት ይደነግጋሉ፡፡ማንም ሰው በየትኛውም የአስተሳሰብ ጎራ የታሰረ ስላልሆነ አንዳንድ ሴቶች በሚመርጡት ፈትዋ ላይ ተመስርተው የአስተሳሰብ ጎራቸውን ይመርጣሉ፡፡ ይህ ዓይነቱ "የፈትዋ ግብይት" በሱኒ ሙስሊሞች የማይበረታታ ቢሆንም አሕመዲዎች በጣም ጥብቅ ከሆነው የሥልጣን ተዋረዳቸው የተነሳ ማድረግ ለማይችሏቸው ነገሮች እንደ ጥሩ ምሳሌ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

ውስብስብ ሁኔታውን የሚገልፅ ሌላ ፅንፍም አለ፤ሁሉም ቤተ እምነቶች የትኛው ሐዲስ ትክክል ነው በሚለው ጥያቄ ላይ የተለያየ አቋም አላቸው፡፡ ሐዲሳት ሁለተኛ የሸሪኣ ምንጮች እንደመሆናቸው መጠን እነዚህ የአቋም ልዩነቶች በጉልህ የሚታይ ተፅዕኖ አላቸው፡፡ ሱኒና ሺኣዎች እስልምናን በተለያዩ መንገዶች እንዲለማመዱ ያደረገው ይህ ጉዳይ ነው፡፡ የሐዲስ መጻሕፍታቸው አንኳር ልዩነቶች ይታዩባቸዋል፡፡ እነዚህ ልዩነቶች ኢማሞች ያሏቸውን ሥልጣን በተመለከተ ሺኣዎች ከሚያራምዱት አቋም ጋር ተደምረው ስለ ሸሪኣ ያሉትአመለካከቶች በእጅጉ የተራራቁ እንዲሆኑ አድርገዋል፡፡

ነገር ግን ዋና ዋና የሆኑት የእስልምና ቤተ እምነቶች የሚግባቡባቸው ነገሮች ከግምት ውስጥ ሲገቡ እነዚህ ልዩነቶች አንሰው ይታያሉ፡፡ ለምሳሌ ያህል አራቱም ዋና ዋና የሱኒ የአስተሳሰብ ጎራዎችና ሦስቱም ዋና ዋና የሺኣ የአስተሳሰብ ጎራዎች ከእስልምና የሚወጡ ሰዎች መገደል እንዳለባቸው ያስተምራሉ፡፡ ልዩነቶች የሚታዩት ዝርዝር በሆኑት ለዚያ በሚያበቁ ጉዳዮችና የአፈፃፀም ሂደት ላይ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ዕድሜ ጠገብ ከሆነው ተግባር ጋር የማይስማሙት ጥግ ላይ ያሉት ለዘብተኛ ሙስሊሞችና አሕመዲያን የመሳሰሉትአናሳ ቡድኖች ብቻ ናቸው፡፡

እነዚህን ነገሮች የተማርኩት በኢጅተማ ውስጥ አይደለም፡፡ እዚያ መማርም አያሻኝም፡፡ በርግጥ አብዛኞቹ ሙስሊሞች ስለ እነዚህ ጉዳዮች ዕውቀት የላቸውም፡፡ እስልምናን የሚያውቁት በሚለማመዱት ልክ ነው፡፡ ነገር ግን እነዚህ ጉዳዮች የሊቃውንት ብቻ ናቸው፡፡ ከምንም በላይ ኢጅተማና ሌሎች መሰል ስብሰባዎችለእስልምና ጥልቅ ፍቅር እንዲኖረንና እርስ በርሳችን የጠበቀ ሕብረት እንዲኖረን አድርገውናል፡፡ እኛ መልሶቻቸውን ለማናውቃቸው ጥያቄዎች መልስ ያላቸው የሃይማኖት መሪዎች እንዳሉን ማረጋገጫ ሰጥተውናል፡፡ በየጊዜው በመሰብሰብና ስለ እምነታችን ጉዳዮች በመወያየት ጠንካራ ማሕበረሰብ ሆነናል፡፡

# የታማኝ ሰው ህልሞች

አንድ ምሽት ከተመሳሳይ ስብሰባ በኋላ ከግላስጎው ወደ ዱኑን በመኪናችን እየተጓዝን ሳለን አባና እማ ስለ አንድ ጉዳይ መጨነቃቸው በግልፅ ይታይ ነበር፡፡ በማርፈዳችን ምክንያት ሆሊ ሎች ላይ ይመላለሱ የነበሩት ጀልባዎች ሥራቸውን ጨርሰው መልህቃቸውን ጥለዋል፡፡ ቤታችን ለመድረስ ለሁለት ሰዓት ተኩል ያህል የባሕር ሰርጡን መዞር ያስፈልገን ነበር፡፡

ነገር ግን መሰል ሁኔታዎች ከዚህ ቀደም ቢያጋጥሙንም እማና አባ ሐሳብ ገብቷቸው አያውቅም ነበር፡፡ ቀጣዩ ቀን እሑድ በመሆኑ ምክንያት አባ ከሥራ ልቀር እችላለሁ የሚል ስጋት ሊገባው አይችልም፡፡ ሁለቱም ከፊት የተቀመጡ ሲሆን እኛ ልንሰማው በማንችለው ሁኔታ ዝግ ባለ ድምፅ ይነጋገሩ ነበር፤ ነገር ግን እኔና ባጂ ንግግራቸው ከረር ያለ መሆኑንና የሥጋት ጥላ በመካከላቸው ማጥላቱን ማስተዋል አልከበደንም ነበር፡፡ የሆነ ችግር ተፈጥሯል ማለት ነው፡፡

ባጂ አስቀድማ ጠየቀች፡፡ “አባዬ ችግር አለ እንዴ?”

“የለም ቤይቲ፡፡ ቀበቷችሁን አጥብቁ፣ በሩ በትክክል መዘጋቱን አረጋግጡ ከዚያ ተኙ፡፡ የእንቅልፍ ሰዓታችሁ አልፏል፡፡ ኢንሻ አላህ ከአፍታ በኋላ ቤታችን እንደርሳለን፡፡” እማ ገርመም አደረገችው፡፡ ዝምታ ሰፈነ፡፡

ከቆይታ በኋላ አባነንኳቸው፡፡ “ምንድነው እየሆነ ያለው እማዬ?”

“አባዬ ሰማኸኝ? መልሱልኝ እንጂ፡፡” ምንም ያህል ብንጎተጉታቸው አባና እማ ጉዳዩን ሊነግሩን የፈለጉ አይመስልም፡፡ ከዚህ በኋላ በምንም ዓይነት ተዓምር እንቅልፍ ሊወስደን አይችልም፡፡ ነገር ግን እንዲቆጡን ስለማንፈልግ የተኛን አስመሰልን፡፡

ፀጥታ ከነገሰባቸው የተወሰኑ ደቂቃዎች በኋላ እማ ተነፈሰች፡፡ ወደ አባ በመዞር “አሁንም አንድ መስሎ ይታይሃል?” በማለት ጠየቀችው፡፡

“አዎ፣ ያው ይመስላል፡፡ እንዲያውም የበለጠ ይመስላል፡፡”

“በቃ አዙረን እንመለስ! ወደ መጣንበት እንመለስ! ቻሎ፣ ይበቃናል!”

አባዬ ሐሳቡን የወደደው ይመስላል፡፡ ሳያቅማማ መኪናውን በማዞር ወደ ግላስጎው አቀና፡፡ እኔና ባጂ ምንም ዓይነት ጥያቄ ማቅረብ እንደሌለብን ገብቶናል፡፡ ጭንቀቱ እየረገበ ቢሆንም ነገር ግን ድባቡ አልተሻሻለም፡፡

“ሆቴል ልፈልግ?” አባ ጠየቀ፡፡

“አይ፣ የማሊክ ቤት ማረፍ እንችላለን፡፡ የሆነውን ይረዱልናል፡፡”

እማ የተናገረችው ነገር ፍርሃቴን ወደ ደስታ ለወጠልኝ፡፡ የማሊክ ቤተሰቦች ከመስጊድ አባላት ሁሉ የበለጠ የምንቀርባቸው ነበሩ፡፡ ማሊክና ባለቤቱን ‹አጎቴ› እና ‹አክስቴ› በማለት ነበር የምጠራቸው፡፡ ይህ አጠራር በፓኪስታን ባሕል የተለመደ ስለሆነ ብቻ አይደለም ነገር ግን እንደ ሁለተኛ ወላጆቼ ስለምቆጥራቸውም ጭምር ነው፡፡ባጠፋም ባለማም ሞቅ ባለ ፍቅር ነበር የሚቀበሉኝ፡፡

አጎቴና አክስቴ ጥሩ ጓደኞቻችን የሆኑ አምስት ልጆች ነበሯቸው፡፡ የቤተሰቡ ታላቅ ልጅ አስራ ሦስት ዓመቱ ነበር፡፡ በልጅነቴ እንደ ጥሩ ምሳሌ የምቆጥረው እርሱን ነበር፡፡ ከእርሱ ጋር የማሳልፈው ጊዜ እጅግ አስደሳች ነበር፡፡ ለጊዜውም ቢሆን ያልተለመደው የጎዞ መስተጓጎል ተረስቷል፡፡

ይህንን ያልታሰበ መስተጓጎል የበለጠ አጓጊ የሚያደርገው ደግሞ በጓደኞቼ ቤት ውስጥ ለመጀመርያ ጊዜ ማደሬ ነው፡፡ ቤተሰቦቻችንን ለመጎብኘት ወይም በሌላ ምክንያት ጉዞ ላይ ካልሆንን በስተቀር ከቤት ውጪ አድረን አናውቅም፡፡ አብሮን የሚያድር ጓደኛ ባለመኖሩ ምክንያት ብቻ ሳይሆን እማ ከእርሷ ዕይታ መራቃችን ስለማያስደስታት ከቤተሰብ ተነጥሎ መተኛት የማይታሰብ ነው፡፡

የገበታ ጫወታዎችን እየተጫወትንና ፊልም እያየን ሌሊቱን አጋመስን፡፡ ወላጆቻችን ከተኙ በኋላ ጓደኞቼ *ፕሬዴተር* የተሰኘ ርዕስ ያለው አስፈሪ ፊልም በቪድዮ ማጫወቻው ውስጥ ጨመሩ፡፡

የቤተሰብ ቁጥጥር ተለይቶኝ ስለማያውቅ እንደዚያ ዓይነት ፊልም አይቼ አላውቅም ነበር፡፡ ፊልሙ ከጀመረ ከአፍታ በኋላ ከፍተኛ ፍርሃት ውስጥ ገባሁ፡፡ የጓደኞቼ ማባበል እንኳ ቴሌቪዥኑን እንዳይ አላደረገኝም፡፡ ወደ መኝታዬ በመሄድ ለመተኛት ሞከርኩኝ፡፡ በዚያን ሌሊት የሰዎች አደን፣ የደም ነጠብጣቦችና አስፈሪ የሆኑየአስትሪያውያን ቅላፄዎች በህልሜ እየተፈራረቁስቃዥ ጎህ ቀደደ፡፡ ወደ መኝታ ከሄድኩበት ጊዜ ይልቅ አካሌ ዝሎ ከአልጋ ላይ ወረድኩ፡፡

በበነጋው ለንጉሣዊ ቤተሰብ የተዘጋጀ የሚመስለውን የፓኪስታንና የስኮትላንድ ምግቦች ድብልቅ የሆነውን ቁርስ ከበላን በኋላ እማ አክስቴን አመስግና ወደ በሩ ተጠግታ በመቆም ከአጎቴ ጋር ሲያወጋ የነበረውን አባን መጠበቅ ጀመረች፡፡ እማ በቂ እንቅልፍ አለመተኛቴን ስላወቀች ሁሌም ሲደክመኝ እንደማደርገው እርሷን ደገፍ ብዬ መቆሜን አልተቃወመችም፡፡

አክስቴ መንገዱን እየተመለከተች መናገር ጀመረች፡፡ "አሁን ቀን ስለሆነ ያየውን ልትነግሪኝ ትችያለሽ፡፡"

"በቀን እንኳ ለሰው የማትናገሪው ዓይነት ህልም እኮ ነው፡፡"

የእንቆቅልሹ መልስ ይህ ነበር፡፡ አባ ህልም አልሟል፡፡ በኛ ባሕል ህልም እንደ ዋዛ አይታይም፡፡ አንድ ተኣማኒ ሐዲስ እንደሚናገረው “የታማኝ ሰው ህልም ትንቢታዊ ነው፡፡”[13] እኔ እስከማውቀው ድረስ አብዛኞቹ ሙስሊሞች በቀጥታ ከፈጣሪያቸው ዘንድ መልእክት የሚጠብቁት በህልም በኩል ብቻ ነው፡፡

ለዚህ ደግሞ ጥሩ ምክንያት አለ፤ህልሞች ብዙ ጊዜ ይፈፀማሉ፡፡ አባ ብዙ ትንቢታዊ ህልሞችን አይቷል፡፡ እንደ ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል የሆነ ወቅት ላይ ለማዕረግ ዕድገት የውድድር ፈተና ወስዶ ነበር፡፡ በፈተናው ዕለት እርሱና አምስት ጓደኞቹ ከባድ ተኩስ በበዛበት የጦር ሜዳ ውስጥ ሲዋጉ ህልም አየ፡፡ ከአደጋ ለማምለጥ አንድ በርቀት የሚታይ አጥር መዝለል ነበረባቸው፡፡ ስድስቱም መሮጥ ጀመሩ፡፡ አባ መጀመርያ አጥሩን ዘለለ፡፡ እርሱን ተከትሎ ደግሞ ሌላው ጓደኛው ዘለለ፡፡ የተቀሩት አራቱ መዝለል አልቻሉም፡፡

ከጥቂት ሳምንታት በኋላ የፈተና ውጤት ሲመጣ በህልሙ ያያቸው አምስቱም ጓደኞቹ ፈተናውን የወሰዱ ሲሆን ማለፍ የቻሉት ግን ልክ በህልሙ እንዳየው እርሱና አንዱ ጓደኛው ብቻ ነበሩ፡፡

ትልቋ እማ አንድ ጊዜ አባቷ ከሞተና ከተቀበረ ከቀናት በኋላ ህልም አልማ ነበር፡፡ ሙሉ በሙሉ በዝናብ በሰብሶ በር ላይ በመቆም እያንኳኳ እርዳታዋን ይጠይቅ ነበር፡፡ ለሦስት ተከታታይ ቀናት ተመሳሳይ ህልም ካለመች በኋላ መቃብሩን ሄዳ ለማየት ወሰነች፡፡ እዚያ ስትደርስ አውሬ ጉድጓዱን ቆፍሮት ጎርፍ ገብቶበት ተመለከተች፡፡

የቤተሰቤ አባላት ስለ ህመም፣ የፅንስ መጨንገፍ፣ ልደት፣ ሞትና ስለ ብዙ ጉዳዮች ቀጥተኛ ህልሞችን አልመዋል፡፡ ህልም በተለይ ሊታለፍ የሚችልን አደጋን የሚያስጠነቅቅ ከሆነ እንደዋዛ አናየውም፡፡

**ሰደቃ፡** ብዙ ጊዜ ክፉ አጋጣሚዎችን ለማስወገድ የሚሰጥ በበጎ ፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ስጦታ፡፡
**አልሀምዱሊላህ፡** “ምስጋና ሁሉ ለአላህ ይሁን” የሚል ትርጉም ያለው የሙስሊሞች የተለመደ አባባል፡፡ ሃሌሉያ ከሚለው ጋር የሚመሳሰል እስላማዊ የምስጋና ቃል ነው፡፡

አክስቴ እማ ህልሙን ለሆነ ሰው መንገር እንደሚያስፈልጋት ስለተገነዘበች ደግማ ጠየቀቻት፡፡ “**ሰደቃ** በመስጠት ልጸልይላችሁ ስለምፈልግ ያየውን ንገሪኝ፡፡”

እማ ትንሽ አቅማማች፡፡ “እሺ እነግርሻለሁ ነገር ግን ትርጉሙ ምን እንደሆነ አላውቅም፡፡ ለሌላ ሰው ደግሞ መንገር የለብሽም፡፡ ህልሙን ያየው ከሁለት ቀናት በፊት ነበር፡፡ ሁላችንም መኪናችን ውስጥ ሆነን በጨለማ መንገድ ላይ እናሽከረክር ነበር፡፡ መንገዱ ጠባብ ሲሆን ከዳርና ዳር እሳት ነበር፡፡ እሳቱ ራሱ ጨለማዊ ሲሆን ምንም ብርሃን አልነበረውም፡፡ ምንም ነገር አይታየውም ነበር፡፡ ባጂና ነቢልን ዞር ብሎ ሲያያቸው ጠፍተዋል፡፡”

እማ ንግግሯን በመግታት መኪናው አጠገብ ቆመው የነበሩትን አባንና አጎቴን በዝምታ ተመለከተቻቸው፡፡ አክስቴ “ትርጉሙ ምን ይመስልሻል?” በማለት ጠየቀቻት፡፡

የእማ መልስ “አስቶጉፉሩላህ፣ ስለዚያ ማሰብ አልፈልግም!” የሚል ነበር፡፡

“ከዚያስ ትላንት ማታ መንገዱ ላይ ምን ተከሰተ?”

እማ አሁንም ከመናገሯ በፊት አቅማማች፡፡ “ወደ ዱኑን የሚወስደው ረጅሙ መንገድ በቀን እንኳ አስቸጋሪ ነው፡፡ እቤታችን ለመድረስ መንገዱን ካጋመስን በኋላ መብራት እስከጠፋበት ጊዜ ድረስ ስለ ጉዳዩ በጭራሽ አላሰብንም ነበር፡፡ ጨለማው ከህልሙ ጋር በጣም ይመሳሰል ነበር፡፡ ከዚያ ለመመለስ ወሰንን፡፡ የህልሙ ትርጉም ምንም ይሁን ምን አላህ እንዳተረፈን አስባለሁ፡፡”

በመጨረሻም አክስቴ ፈገግ ብላ ወደ እማ በመዞር “**አልሀምዱሊላህ፡፡** አላህን እናመስግነው፡፡ ከመሄዳችሁ በፊት ዱአ አድርጉ፣ ሰደቃ ስጡ፣ ስለዚህ ጉዳይም ደግማችሁ አታስቡ፡፡ ቤት እንደደረሳችሁ ደውልሉኝና ሁላችሁም ሰላም መሆናችሁን ልወቅ፡፡” በምላሹ እማ ፈገግ በማለት አቀፈቻት፡፡ አክስቴ እውነተኛ ወዳጅ ናት፡፡

ሁለቱም ቤተሰቦች በመኪናው አጠገብ አንድ ላይ ሰብሰብ ብለን በሰላም ወደ ቤታችን መመለስ እንድንችል በዝምታ ጸለይን፡፡ ይህ የተለመደ ተግባር ቢሆንም በዚያ ማለዳ ግን ተጨማሪ ትርጉም ነበረው፡፡

በመኪናችን ውስጥ ሆነን ከከተማ ከወጣን በኋላ አባ መጥፎ ህልም አልሞ እንደሆን ጠየቅሁት፡፡ እማን አየት አደረጋት ነገር ግን ምንም አላለችውም፡፡

“አዎ ቤይታ፡፡”

“እኔም ማታ መጥፎ ህልም አልሜ ነበር አባዬ ጃን፡፡ ምንም ማለት አይደለም፡፡” አባዬ ሳቅ አለ፡፡ “ቢሉ የተለያዩ ዓይነት ህልሞች አሉ፡፡”

“ምንድነው የሚለያቸው?”

“ከፈጣሪ የሆነውን ስታይ ይታወቅሃል፡፡”

“አላህ ብዙ ጊዜ ህልም ያሳይሃል?”

“አዎ ቤይታ፣ በጣም ብዙ፡፡” ይህን ብለን ጨረስን፡፡ ከጥቂት ቀናት በኋላ አባዬ ትንቢታዊ ህልሞችን ማየቱን እንዲያቆም ወደ አላህ ለመጸለይ ወሰነ፡፡

አባትንቢታዊ ህልሞችን በብዛት ማለም ካቆመ ከሃያ ዓመት በላይ ሆኖታል፡፡ በሌላ ወገን እኔ ደግሞ አላህ በህልሞች በኩል እንዲመራኝ ለረጅም ጊዜያት በመደፋት የምጸልይበት ጊዜ ከፊት ለፊት ይጠብቀኝ ነበር፡፡ ያ ጊዜ ሲደርስ አባ የተናገረው ትክክል መሆኑን አረጋገጥኩኝ፡፡ አንድ ሲያሳየኝ ከእርሱ መሆኑን ተረዳሁኝ፡፡

ምዕራፍ አሥር

# የበረከት ወር

በስኮትላንድ ያሳለፍኳቸው ዓመታት እጅግ አስደሳች ነበሩ፡፡ ልቤ በምድሪቱና በሕዝቡ ውበት ተማርኳል፡፡ ቤታችን በቀዝቃዛ ማለዳዎች ከሩቅ የሚሰሙ የጡሩንባ ድምፆችን በሚያስተጋባ ኮረብታ ስር ነበር የሚገኘው፡፡ በዱኑን አካባቢ የሚገኙ ተራሮች ለዚያ ዓላማ የተሰሩ ነው የሚመስሉት፡፡ የእንጆሪ ሰንሰሎች በግቢያችን አካባቢ ይታያሉ፡፡ ፍየሎች ደርሰው እንዳይበሏቸው በሽቦ ታጥረዋል፡፡ መደበኛ ትምህርቴን የጀመርኩት በአቅራቢያችን በሚገኝ ሳንድባንክ የመጀመርያ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆን በመስጊድም ጥቂት ጓደኞችን አፍርቼ ነበር፡፡ ሕዝቡ ደግ ነው፡፡ የትራፊክ መብራት አስቁሞን ሳለ አንድ ሁለት ጊዜ ከማናውቃቸው ሰዎች የእራት ግብዣ ቀርቦልናል፡፡ ስኮትላንድን በጣም ነው የወደድኳት፡፡ ለአገሪቱ ያለኝ ፅኑ ፍቅር በወረስኩት ጠንካራ የስኮቲሽ ቅላፄ ይንፀባረቃል፡፡

ቀዝቃዛው ጦርነት እየተቀዛቀዘ ነበር፡፡ ይህ ማለት የኒውክለር ባህር ኃይል ጣብያ ከዚህ በኋላ አያስፈልግም ማለት ነው፡፡ እነሆ እንደተለመደው ወደ ሌላ ቦታ የምንንቀሳቀስበት ጊዜ መጣ፡፡ ስኮትላንድን ለመልቀቅ የሚታየኝ አዎንታዊ ነገር አንድ ብቻ ነበር፤ ረመዳን በእጅጉ ቀላል ይሆንልኛል፡፡

ረመዳን የሙስሊሞች ቅዱስ ወር ነው፡፡ ለሠላሳ ቀናት ያህል ሙስሊሞች ፀሐይ ወጥታ እስከትጠልቅ ድረስ ይፆማሉ፡፡ ምግብም ሆነ ውኃ በአፋቸው እንዲነኩ አይፈቀድላቸውም፡፡ ይህ ልማድ አራተኛው የእስልምና አምድ ሲሆን አቅም ባላቸው

ሙስሊሞች ሁሉ ላይ የተደነገገ ነው፡፡ በሠላሳዎቹ ቀናት መጨረሻ ላይ ሙስሊሞች ከሁለቱ ዋና ዋና በአላታቸው መካከል አንዱ የሆነውን **ኢድ አል-ፈጥር**ን ያከብራሉ፡፡

**ኢድ አል-ፈጥር፡** ከሁለቱ ዋና ዋና የሙስሊሞች በኣላት መካከል አንዱ ሲሆን የረመዳንን ፍፃሜ ያመለክታል፡፡

ረመዳን ከቀኑ ርዝመት የተነሳ በስኮትላንድ ውስጥ በጣም አድካሚ ነው፡፡ ስኮትላንድ በሰሜናዊ ንፍቀ ክበብ ጥግ ላይ ከአይስላንድ በታች ትገኛለች፡፡ በበጋ ወቅት ፀሐይ ከማለዳው አሥር ሰዓት ተኩል አካባቢ በመውጣት ከምሽቱ አራት ሰዓት አካባቢ ትጠልቃለች፡፡ ረመዳን እኛ እዚያ በነበርንባቸው ዓመታት እንደሆነው በበጋ ወራት ውስጥ የሚሆን ከሆነ ሙስሊሞች በቀን ለአሥራ ስምንት ሰዓታት ያህል መፆም ይጠበቅባቸዋል፡፡ ያንን ሁሉ ሰዓት አለመብላት ከባድ ቢሆንም ውኃ መከልከሉ ግን ይበልጥ አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ ለሠላሳ ቀናት ያህል ያንን መታገሱ ጥንካሬና እምነትን ይፈትናል፡፡

ነገር ግን እስልምና በአመዛኙ ብዙዎች እንደሚያስቡት ግትር አይደለም፡፡ ለምሳሌ ያህል ፆምን በተመለከተ ልዩ ሁኔታዎች አሉ፡፡ ሙስሊም ከታመመ፣ መንገደኛ ከሆነ ወይም በሆነው ምክንያት መፆም ካልቻለ ምርጫዎች አሉት፡፡ ከነዚህ መካከል አንዱ ለድኾች ምግብን በመስጠት ግዴታውን መወጣትና የገደፋቸውን የፆም ቀናት በሌላ ጊዜ ማካካስ ነው፡፡

ፆም አስፈላጊ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የረመዳን ወቅት ሲነሳ ስለፆም ብቻ ማሰብ ነገሩን በትክክል አለመረዳት ነው፡፡ ለሙስሊሞች ቅዱሱ ወር ከዚያ የላቀ ትርጉም አለው፡፡ ማህበረሰብ የሚገነባበት፣ የተበላሹ ሕብረቶች የሚታደሱበት፣ ውስጥን ለማንፃት ትግል የሚደረግበት፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ የአንድ ሰው እምነት የሚጠነክርበት ወር ነው፡፡ ዘመዶች ይጠራሉ፣ ስጦታዎች ይገዛሉ፣ ድግሶች ይዘጋጃሉ፡፡ የገና በዓል በምዕራባውያን ዘንድ ወሩን በሙሉ እንደሚከበረው ሁሉ የረመዳን ወርም በዓለም ዙርያ በሚገኙት ሙስሊሞች ዘንድ በደስታ ይከበራል፡፡

እስላማዊው የቀን መቁጠርያ በጨረቃ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ረመዳን መቼ እንደሚጀምር ትክክለኛውን ቀን መገመት ይከብዳል፡፡ ብዙ ጊዜ እርግጠኛ የማይኮንበት ሌሊት አለ፡፡ በየዓመቱ ከአባ ጋር ውጪ በመቆም ሰማዩ ጠርቶ ጨረቃዋን ለማየት በጉጉት አንጋጥጬ እመለከት ነበር፡፡ አዲስ ጨረቃ ከታየች ራሶቻችንን ዝቅ በማድረግ የተሸመደደ ዱኣ እናነበንባለን፡፡ ከዚያ አባ ወደ ኩሺና ይሄድና ውሳኔውን ለእማ ይነግራታል፡፡ ሁሌ የሚቀጥለውን ቀን ምግብ በማዘጋጀት ሥራ ስለምትጠመድ ከእኛ ጋር ውጪ በመቆም የተጠባበቀችበትን ጊዜ አላስታውስም፡፡ ምግብ በገፍ ነው የሚዘጋጀው፡፡

በተለመደ ሁኔታ ፀሐይ ከመውጣቷ ከአንድ ሰዓት በፊት ቀደም ብለን እንነሳለን፡፡ ውዱ ከፈፀምን በኋላ ቁጭ ብለን ምግብ ከመብላታችን በፊት በምርጫ የሚደረግ ጸሎት ስምንት ረካት እንጸልያለን፡፡ ከፀሐይ መውጫ በፊት የሚበላ ምግብ **ሴህሪ** በመባል ይታወቃል፡፡ ቀኑን የምንውልበትን ጉልበት የመስጠትና ሕብረት እንድናደርግ የመርዳት ጣምራ ዓላማዎችን ያነገበ ነው፡፡ እማ ቁርስ ስታዘጋጅ ብዙ ጊዜ ለአላህ ወይም ለመሐመድ የምስጋና መዝሙሮችን ታንጎራጉራለች፡፡ የኩሽና ሥራዋን ከጨረሰች በኋላ ጠረጴዛውን በምግብ ትሞዋለች፡፡ እርጎና እንቁላል የሴህሪ ዋና ምግቦች ሲሆኑ አኩሪ አተር፣ ቦሎቄ፣ የዶሮ ጥብስ፣ ከስንዴ የሚሰሩ ምግቦች፣ ወተት፣ ጭማቂዎችና እማ ለጠዋት አስፈላጊ እንደሆኑ ያመነችባቸው የምግብ ዓይነቶች ሁሉ ይቀርባሉ፡፡

> **ሴህሪ፡** ሙስሊሞች ከፆም በፊት የሚቆርሱት ገበታ፡፡

ወደ ኩሽና ስንገባ *ሮቲ* እና *ፐራታ* የተሰኙ የፓኪስታን ቂጣዎችን ማዘጋጀት ትጀምራለች፡፡ ቂጣዎቻችንን በትኩሱ መመገብ እንዳለብንም ትነግረናለች፡፡ እማ ብዙ ጊዜ ለሰዎች ምግብ ማቅረብ ያስደስታታል፡፡ ሴህሪ ለቤተሰቧ ስታቀርብ ደግሞ ደስታዋ የበለጠውን ይጨምራል፡፡እኛ እስክንጠግብ ድረስ አትቀመጥም፤ ደግሞም በቂ ትኩስ ዳቦ ለሁሉም ማዘጋጀትን አትረሳም፡፡

ሴህሪ ስንበላ ዓይኖቻችንን ከሰዓቱ ላይ አንነቅልም፡፡ ፀሐይ የምትወጣበትን ትክክለኛ ሰዓት የሚነግረን መቁጠርያ በፍሪጃችን ላይ ስለንምናስቀምጥ መቼ ምግብ ማላመጥ ማቆም እንዳለብን እናውቃለን፡፡ ከፀሐይ መውጫ በፊት ወደ መጸለያ ቦታ በመሄድ የአዛን ጥሪ አደርጋለሁ፡፡ አዛን እስኪጠናቀቅ ድረስ የኛ ቤተሰብ መብላትና መጠጣቱን ይቀጥላል፡፡

አንድ ቀን ማለዳ የአዛን ጥሪ ሰዓት ሲደርስ እማ በቀልድ መልክ "ቢሉ ዛሬ የአዛን ጥሪ ስታደርግ ጎተት አድርገው፤ ለመብላት ተጨማሪ ጊዜ ያስፈልገኛል!" ማለቷ አይረሳኝም፡፡ በአዛን መቀለድ ባይቻልም ነገር ግን የእማ በሳቅ የታጀበ ልመና እያስደሰተኝ አዛኑን በፍጥነት ጀምሬ ጨረስኩት፡፡ እማ የጎረሰችውን ምግብ በፍጥነት አላምጣ ለመዋጥ እየሞከረች "ነቢል! በገዛ እናትህ ላይ ይህንን በመፈፀምህ ማፈር አለብህ!" አለችኝ፡፡

እኔና ባጂ ቀኑን ሙሉ ትምህርት ቤት እንውላለን፡፡ እማ ፆም በትምህርታችን ላይ ተፅዕኖ እንደሚኖረው ስለምታስብ ቀኑን ሙሉ እንድንፆም አትፈቅድልንም ነበር፡፡ ሙስሊም ጓደኞቻችን እንደሚፆሙ ስንነግራት "እኔ እናታቸው ነኝ እንዴ? እስኪታድጉ ድረስ መፆም የለባችሁም፡፡ አሁን ልምምድ ላይ ናችሁ፡፡ ምናልባት የእነርሱ እናቶች አድገዋል ብለው ስለሚያስቡ ሊሆን ይችላል፡፡ ከሌሎች ህፃናት ጋር ራሳችሁን ማወዳደር የለባችሁም፡፡" የሚል መልስ ትሰጠን ነበር፡፡ የተቆጣች ለመምሰል ብትሞክርም ነገር ግን የኛ ለመፆም መጓጓት እንደማያስቆጣት እናውቃለን፡፡

እንደ አብዛኞቹ ሙስሊሞች እናታችንም በረመዳን ወር ደስተኛ ለመሆን የተቻላትን ታደርጋለች፡፡ ቁርአንን በማነብነብና በጸሎት የምታሳልፍ ሲሆን ከምንም በላይ ደስታን የሚያጎናፅፋት ይመስላል፡፡ በረመዳን ወቅት ብዙ ጊዜ ቁርአንን ሁለት ዙር አንብባ ትጨርሳለች፡፡

> **ኢፍጣር፡** ሙስሊሞች ብዙ ጊዜ በጋራ በመሰባሰብ ከፆም በኋላ የሚቆርሱትገበታ
>
> **ተረዊህ፡** በረመዳን ወቅት ሌሊት በፈቃደኝነት የሚጸለይ ጸሎት
>
> **ሐፊዝ፡** ቁርአንን በሙሉ በቃሉ የሸመደደ ሰው

ይህ ማለት በየዕለቱ የሰላሳዎቹን ክፍሎች ሁለት ሁለት ክፍሎች ማለት ነው፡፡

ብዙ ጊዜ ማታ ቤተሰባችን **ለኢፍጣር** ራት የመስጊዳችን አባላት ወደሆኑት ሰዎች ቤት ይሄድ ነበር፡፡ ኢፍጣር የዕለት ፆም መፍቻ ሲሆን አጠቃላዩ ማሕበረሰብ አንድ ላይ በመሰባሰብ የሚደሰትበት ጊዜ ነው፡፡ በሐዲስ መሠረት መሐመድ ፆም ሲፈታ የሚበላው የመጀመርያው ነገር ቴምር እንደሆነ ስለተነገረ በዓለም ዙርያ የሚገኙት ሙስሊሞች ይህንኑ ያደርጋሉ፡፡ ብዙ ጊዜ ኢፍጣር ለመታደም አርፍደን ስለምንነሳ ቴምራችንን መኪና ውስጥ ነበር የምንበላው፡፡

ፆሙ በቴምር ብቻ ከተፈታ በኋላ ሙሉ ገበታ ከመቅረቡ በፊት ማሕበረሰቡ የመግህሪብጸሎትይጸልያል፡፡ ትንሽ እየተጫወትን ከቆየን በኋላ የኢሻ ጸሎት አዛን ይሰማል፡፡ በረመዳን ወቅት የሚጸለዩ **ተረዊህ** የተሰኙ አማራጭ ጸሎቶችም አሉ፡፡ በመስጊድ ውስጥ የሚደረጉት ኢፍጣሮች የሚመሩት ቁርአንን በሙሉ በቃሉ በሸመደደ **ሐፊዝ** ኢማም ነው፡፡ ኢማሙ ቁርአንን ስለሚያነበንብ እነዚህ የተረዊህ ጸሎቶች በየምሽቱ ከአንድ እስከ ሁለት ሰዓት ያህል ሊፈጁ ይችላሉ፡፡አምላኪዎቹ አብዛኛውን ጊዜ የሚያሳልፉት እጃቸውን አጣምረው ቆመው የሚነበበውን ቁርአን በመስማት ነው፡፡ ተረዊህ ከተጠናቀቀ በኋላ ሁሉም ሰው ከጥቂት ሰዓታት በኋላ ከመኝታው መነሳት እንዳለበት እያስታወሰ ወደየቤቱ ይሄዳል፡፡

በብዙ አካባቢዎች ሙስሊሞች የረመዳን ምሽቶችን የሚያሳልፉት በሌሎች ሰዎች ቤት በመሆኑ ምግብ ማዘጋጀት የአስተናጋጁ ኀላፊነት ነው የሚሆነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ከሚያስፈልገው በላይ ብዙ ምግብ ይዘጋጃል ማለት ነው፡፡ ጿሚዎች በየማለዳውና በየምሽቱ ከመደበኛ አመጋገባቸው የበለጠ ስለሚመገቡ ረመዳን አብዛኛው ሰው ክብደት የሚጨምርበት ወር ነው፡፡

ረመዳንን በመደበኛነት እንድፆም የተፈቀደልኝ ስኮትላንድን ለቀን ከወጣን በኋላ ነበር፡፡ ስኮትላንድን የለቀቅነው በ1990 ሲሆን በቀጥታ የተጓዝነው ኮኔክቲከት ወደሚገኘው የግሮተን ባሕር ኃይል ጣብያ ነበር፡፡ በግሮተን የማሕበረሰብ መስጊድ ካለመኖሩ የተነሳ

ቤቴ ሆኖ አይሰማኝም ነበር፡፡ ጥሩ ጓደኞችን ካለማፍራቴም በላይ የወረስኩትን የስኮቲሽ ቅላፄ ረሳሁት፡፡ ስኮትላንድ ሙስሊም የመሆንን ትርጉም የተማርኩባትና ከእስልምናዬ ጋር ፅኑ ፍቅር ውስጥ የገባሁባት ነበረች፡፡

ከሦስት ዓመታት በኋላ ወደ ቨርጂንያ እንደገና ተንቀሳቀስን፡፡ አባ የሌውትናንት ኮማንደርነትን ማዕረግ በማግኘቱ ምክንያት ከእንግዲህ ወዲያ በመከላከያ ከቦታ ወደ ቦታ እንዲዛወር አይደረግም፡፡ የቨርጂንያ የባሕር ዳርቻ ዘላቂ ጓደኝነትን ያፈራሁበት፣ በዕድሜ የበሰልኩበት፣ እንዲሁም የወደፊት ሕይወቴን አቅጣጫ የወሰንኩበት ነበር፡፡ እስላማዊው ባሕሌ ከአሜሪካ አውድ ጋር ሲጋጭ ለመጀመርያ ጊዜ የተሰማኝም እዚያ ነበር፡፡ በመጨረሻም እስልምናንና የተማርኩትን ሁሉ ለመተው የወሰንኩበት ቦታ ነው፡፡

*በአሜሪካ ውስጥ ሙስሊም ሆኖ ስለማደግ*

*የሚያወሳውን የሊቅ አስተዋፅዖ ለማየት ሺኣ ሙስሊም የነበሩትን፤*

*የሕግ ባለ ሙያና ዓቃቤ እምነት የሆኑትን የአብዱ ሙሬይ*

*ጽሑፍ ተከታዩን ድረ-ገፅ በመክፈት ያንብቡ contributions.NabeelQureshi.com*

## ክፍል ፪

# የእስልምና አምባሳደር

*በእውነት መሐመድን እንደ መጨረሻ ነቢይ እና ቁርአንን እንደመመርያ የላክኸው አንተ ነህ…*

ምዕራፍ አሥራ አንድ

# ሦስተኛው ባሕል

የሰባተኛ ክፍል ተማሪ ሳለሁ ዘላቂ ጓደኞችን አፈራሁ፡፡ ዴቪድ፣ ቤንና ሪክ ልክ እንደ ወንድሞቼ ነበሩ፡፡ ሁሉንም ነገር ደግሞ እናደርግ የነበረው በጋራ ነበር፡፡ እማ ባይዋጥላትም ማደጌ እየገባት ስለመጣ ከቤት ውጪ እንዳሳልፍ ትፈቅድልኝ ጀመር፡፡ ከመደበኛ የትምህርት ጊዜ ውጪ ለሚከወኑ ተግባራዊ ልምምዶች ከቤት ውጪ አሳልፋለሁ፡፡ አንዳንዴ ደግሞ የተወሰኑ ሰዓታትን በጓደኞቼ ቤት እንዳሳልፍ ትፈቅድልኛለች፡፡

ዕድሜዬ አሥራዎቹ ውስጥ ከመግባቱ በፊት ከእማ ጋር ኮምጠጥ ያለ ንግግር አድርገን ነበር፡፡ አንድ ቀን ምሽት ቤተሰባችን የኢሻ ሰላት ከውኖ ካበቃ በኋላ ከጸሎትክፍሉ ልወጣ ስል እማ አስቆመችኝ፡፡ “ነቢል ለጥቂት ጊዜ እስኪ እዚህ ቆይ፡፡”

ይህ የተለመደው ዓይነት ምልልስ እንደማይሆን ገባኝ፡፡ “እማ ምን ተፈጠረ?”

“ቤይታ የተወሰኑ ሙስሊም ልጆች በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ ቢኖሩና እስልምናን ስትወክል ብቸኛ ባትሆን እንዴት ደስ ባለኝ፡፡ ነገር ግን ያ የአላህ ፈቃድ አልሆነም፡፡ ሁል ጊዜ ይህንን አስታውስ፤ የትም ብትሆን ወይም ምንም ነገር ብታደርግ የእስልምና አምባሳደር ነህ፡፡ ሁል ጊዜም ቢሆን የእስልምና አምባሳደር ሆነህ ትቀጥላለህ፡፡”

በቅንነቷ እና ማስተዋልን በተሞላው አነጋገሯ ተመስጬ አዳምጣት ነበር፡፡ “ሰዎች ፊትህን ሲመለከቱ ‹ሙስሊም ነው!› ብለው ያስባሉ፡፡ ምንም ብታደርግ እንደርሱ

ማሰባቸው አይቀርም፡፡ ጎበዝ ተማሪ ሆነህ ለንግግር ብትጋበዝ ‹ንግግር እያደረገ ያለው ጎበዙ ሙስሊም ተማሪ ነው!› ብለው ያስባሉ፡፡ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ልትሆን ትችላለህ፡፡ ‹ሙስሊሙን ፕሬዚዳንት ተመልከቱት!› ይላሉ፡፡ በምዕራብ እስልምና ለሕዝቡ ባዕድ ነው፤ ብዙዎችም ይቃወሙታል፡፡ ስለ አንተ ምንም ከማሰባቸው ወይም ከመናገራቸው በፊት ሙስሊም መሆንህ ነው የሚታያቸው፡፡ ይህ ያንተ መለያ በመሆኑ ልትቀበለው ይገባል፡፡"

እማ ብዙ ጊዜ እንደዚህ አትናገርም፡፡ የተናገረቻቸው ቃላት የኀላፊነት ስሜት እንዲሰማኝ አደረጉ፡፡ ቅንድቤን ፊታ ኮስተር እያደረኩኝ የተናገረቻቸውን ቃላት ልቅም አድርጌ ሰማኋቸው፡፡ጠበቅ አድርጋ በእናትነት ፍቅር አቀፈችኝ፡፡ "ቢሉ አትጨነቅ! ይህ መልካም ነገር ነው፡፡ እስልምናን መወከል እና ሰዎችም ውበቱን እንዲረዱት ማድረግ መባረክ ነው፡፡ ጎበዝ ተማሪ ሆነህ ሰዎች ‹እስልምና ጎበዝ ተማሪዎችን ያፈራል!› እንዲሉ ማድረግ አለብህ፡፡ ፕሬዚዳንት ሆነህ ‹እስልምና ጥሩ መሪዎችን ያፈራል!› እንዲሉ ማድረግ አለብህ፡፡ ነገር ግን ደግሞ የፅዳት ሰራተኛ እንኳ ብትሆን የተሻለ ሆነህ ተገኝ፡፡"

የፅዳት ሰራተኛ ብሆን ደስተኛ መሆኗ ቢያጠራጥረኝም በአዎንታ ጭንቅላቴን ነቀነቅሁኝ፡፡

"ሻባሽ ቤይታ፡፡ ምንም ነገር ብታደርግ ሰዎች እስልምናን እንዲያመሰግኑ በጣም አክባሪ፣ ቅንና ታማኝ ሁን፡፡ አስተማሪዎችህን እጅግ አድርገህ አክብራቸው! ልክ እኔን እንደምታከብረው አክብራቸው፡፡ እኔ መጥቼ ስጎበኛቸው በክፍል ውስጥ ከሚገኙት ተማሪዎች ሁሉ እጅግ አክባሪያቸው እንደሆንክ እንዲነግሩኝ እፈልጋለሁ፡፡ መጠጥ በእስልምና የተከለከለ ነው፡፡ መሳደብም ሆነ ከሴቶች ጋር ለብቻ ማሳለፍ የለብህም፡፡ ማንም ሰው የወቀሳ ጣቱን ሊቀስርብህ እስከማይችል ድረስ ንፁህ ሰው ሁን፡፡ አንተ ክቡር በመሆንህ በልባቸው ውስጥ ያመሰግኑሃል ወይንም ደግሞ ራሳቸውን ስለሚጠሉ ይጠሉሃል፡፡ በዚህም ሆነ በዚያ መልካም ሰው ያደረገህ እስልምና መሆኑን ይገነዘባሉ፡፡"

ያደረግሁትም ያንኑ ነበር፡፡ በትምህርት ቤት ሊሰሙኝ ፍቃደኛ ከሆኑ ሰዎች ጋር ስለ እስልምና እነጋገር ነበር፤ ላመንኩበት ነገር እቆም ነበር፤ በሥነ ምግባር የተመሰገነ ለመሆን በትጋት ሠርቻለሁ፡፡ የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ብንሆንም ነገር ግን የሚጠጡ፣ አደንዛዥ ዕፅ የሚወስዱና ፆታዊ ግንኙነት የሚፈፅሙ ልጆችን አውቅ ነበር፡፡ ደስ የሚለው ነገር ከጓደኞቼ መካከል አንዳቸውም በእንዲህ ዓይነት ተግባራት ውስጥ የሚሳተፉ ስላልነበሩ እስከ መጨረሻው ድረስ እስልምናን በጥሩ ሁኔታ ለመወከል አልከበደኝም ነበር፡፡

ነገር ግን ሁኔታዎች እየተለወጡ ነበር፡፡

የአፍላነት ዕድሜ ለሁሉም ሰው ከባድ ነው፡፡ ዕድሜያቸው በአስራዎቹ ውስጥ የገባ ልጆች ወላጆቻቸው ከቀረፁላቸው ስብዕና በመውጣት የራሳቸውን ስብዕና ይገነባሉ፡፡ እያንዳንዱ ሁኔታ የየራሱ ተግዳሮቶች አሉት፡፡ ለእኔም ሆነ ለባጂ ተግዳሮት የሆነብን ነገር የስብዕና ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የአስተሳሰብ አቅጣጫም ጭምር ነበር፡፡ እግሮቻችን በየትኛውም ባሕል ውስጥ ሳይተከሉ በሚዋዥቅ መሠረት ላይ የቆምን ሆነናል፡፡

የመጀመርያውን ለውጥ ያስተዋልኩት በቤተሰብ ስብሰባ ወቅት ነበር፡፡ ሁሉም የእማ ዘመዶች ይኖሩ የነበሩት በሰሜን ምስራቅ በመሆኑ ምክንያት በዓመት ብዙ ጊዜ እንገናኝ ነበር፡፡ ዕድሜዬ አስራዎቹ ውስጥ ሲገባ ወላጆቼ፣ አክስቶቼና አጎቶቼ ጥሩ የፓኪስታን ወጣት እንድሆንላቸው ነበር የሚፈልጉት፡፡ የእኔም ፍላጎት ከዚያ የተለየ አልነበረም፡፡ ችግሩ ግን በጣም የምቀርበው አንድም ጥሩ ፓኪስታናዊ ጓደኛ ስላልነበረኝ እንዴት መሆን እንዳለብኝ አለማወቁ ነበር፡፡ እማ ያንን ልታስተምረኝ አትችልም፡፡

በዕድሜ ጠና ያለውን የአጎቴን ልጅና በዕድሜ ከእኔ የሚያንሰውን አጎቴን በአነጋገር ለመምሰል ጥረት አደርግ ነበር ሆኖም በፓኪስታን ባሕልመሠረት ጨዋ በመሆንና ባለመሆን መካከል ያለውን ልዩነት አውቄ የምኖርበት መረዳት አልነበረኝም፡፡

በአሜሪካ ባሕልመሠረት በጣም ጨዋ የምባል ዓይነት ልጅ ብሆንም ነገር ግን የፓኪስታንን ባሕል ባለማወቄ ዘመዶቻችንን ጎብኝተን ስንመለስ አክብሮት አላሳየህም

በሚል ዘወትር ከወላጆቼ ወቀሳ ይሰነዘርብኝ ነበር፡፡በተጨማሪም ዘመዶቼ ትዕግስታቸው እስኪያልቅ ድረስ ብዙ ጥያቄዎችን እጠይቅ እንደነበር አስተውያለሁ፡፡ በባሕላችን ለታላላቆች ያለምንም ጥያቄ መታዘዝ ያስፈልጋል፡፡ መታዘዝ ምን ያህል እንደምናከብራቸውና በአንዳንድ አውዶች ምን ያህል እንደምንወዳቸው የሚያሳይ ተግባር ነው፡፡ ጥያቄ ብዙ ጊዜ ሥልጣናቸውን እንዳለመቀበል ይቆጠራል፡፡ ነገር ግን በትምህርት ቤት መምህራኖቻችን በጥልቀት ማሰብን ያስተምሩናል፤ ጥያቄዎችንም መጠየቅ መልካም መሆኑን ይነግሩናል፡፡

አእምሮዬ በጥልቀት እንዲያስብ ተደርጎ መቀረጹ ከባሕላችን ጋር የሚሄድ አልሆነም፡፡

ይህ ማለት እኔ የባሕርይ ችግር አልነበረብኝም ማለት አይደለም፤ የተወሰነ ችግር ነበረብኝ፡፡ ኩራተኛና ራስ ወዳድ ወጣት ነበርኩኝ፤ ያ ደግሞ ለብዙ ችግሮች ዳርጎኛል፡፡ የኔ ወላጆች እንዳደረጉት ሁሉ መልካም ወላጆች መሰል ችግሮችን በመታገስ ልጆቻቸው በመልካም ሁኔታ እንዲያድጉ ይቀርጿቸዋል፡፡ ሆኖም ወላጆቼ እንደ ችግር ያዩዋቸው አንዳንድ ነገሮች የባሕል ግጭቶች ብቻ ነበሩ፡፡ የእኔ ሥሪት ከእነርሱ በጣም የተለየ ነበር፡፡ እነርሱ የሚያስቡት እኔ ጥሩ የፓኪስታን ሐር መሆኔን ነበር ነገር ግን የኤስያ ሐርና የአሜሪካ ጥጥ ድብልቅ መሆኔን አልተረዱም፡፡

በትምህርት ቤትም ተመሳሳይ ነገር ገጥሞኛል፡፡ አሜሪካውያን ጓደኞቼ ደረቅ ፓኪስታናዊ እንደሆንኩ ስለሚያስቡ መግባባት ይቸግረኝ ነበር፡፡ምንም ያህል ብንቀራረብ ሁል ጊዜ በመካከላችን ድንበር ነበረ፡፡ በአንድ ወቅት የዓመቱ ትምህርት መዝጊያ ሳምንት በሚከበርበት ሰሞን የገጠመኝን እስከ ዛሬ አልረሳውም፡፡ ስለችሎታችን አስተያየቶችን የምንቀበልበት ዕለት ነበር፡፡ "ይህ ልጅ ወደፊት የኪስ ኮምፒውተር ይፈጥራል ነገር ግን ልብስ በሚታጠብበት ዕለት በቁምጣው ኪስ ውስጥ ይረሳዋል" የሚል አስተያየት ነበር የተሰጠኝ፡፡ ሆኖም የፎቶግራፍ መነሻ ሰዓት እስኪደርስ ድረስ ምሽቱ አስደሳች ነበር፡፡ ጓደኛዬ ቤን ከምርጥ ጓደኞቹ ጋር ፎቶግራፍ ለመነሳት እንደሚፈልግ አስታውቆ እኔን በማግለል ዴቪድና ሪክን ብቻ መረጣ፡፡ ከበረዶ የቀዘቀዘ ቢለዋ ልቤን የወጋኝ ያህል ነበር

የተሰማኝ፡፡ ስለዚያ ክስተት ሳስብ እስከ ዛሬ ድረስ ውስጤ ያዝናል፤ ነገር ግን ችግሩ የእርሱ አልነበረም፡፡ በትክክል የምገጥምበት ቦታ አልነበረኝም፡፡ያንን ደግሞ እኔን ጨምሮ ማንም መረዳት አይችልም ነበር፡፡

የፓኪስታን ባሕልም ሆነ የአሜሪካ ባሕል ውስጥ አልነበርኩም፡፡ ሦስተኛ ባሕል ነበረኝ ነገር ግን በዚያ ክልል ውስጥ ገብቶ ከእኔ ጋር ሊገጥም የሚችል ማንም ሰው አልተገኘም፡፡

ምዕራፍ አሥራ ሁለት

# በምዕራብ የሚኖሩ ሙስሊሞች

ድምፄን በማጥፋት በሆዴ ለጥ ብዬ ተኝቼ የታችኛው ክፍል ውስጥ እየተደረገ የነበረውን ምስጢራዊ ስብሰባ እየተከታተልኩ ነበር፡፡ በዚያን ዕለት ማለዳ ቤተሰቤ የወንድ አያቴን የቀብር ስርአት ለማስፈፀም ተሰብስቦ የነበረ ሲሆን ሁሉም ሰው በስሜት ተውጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በቃላት ያልተገለፀ ውጥረት ነግሦ ነበር፡፡ አዋቂዎቹ እኔና በዕድሜ አነስ ያለውን አጎቴን ወደ መኝታችን የላኩን ቢሆንም እኔ ግን መልስ ፍለጋ ቀስ ብዬ ወጥቻለሁ፡፡

በዕድሜ ጠና ያለችው የአጎቴ ልጅ በክፍሉ ጥግ ላይ ተቀምጣለች፡፡ ፊቷ በመዳፎቿ ላይ ተደፍቷል፤ አዛውንቶቹ በግማሽ ክብ ቅርፅ በዙርያዋ ተቀምጠዋል፡፡ አካባቢው ጭንቀትና ስጋት ነግሦበታል፡፡ ሁሉም ሰው በዝምታ ተውጧል፡፡

በመጨረሻም ሴት አያቴ ለስለስ ባለ ድምፅ ዝምታውን ሰበረችው፡፡ “አሁንም ድረስ ንፁህ ነሽ?”

እናቷ ከመቅፅበት ጣልቃ በመግባት መልስ ሰጠች፤ “አዎ ንፁህ ናት!” ነገር ግን ሁሉም ዓይኖች በአጎቴ ልጅ ላይ ነበሩ፡፡ ጭንቅላቷን ከመዳፎቿ ላይ ሳታነሳ በዝግታ ነቀነቀች፡፡

እማ ጠንከር ባለ ድምፅ መናገር ጀመረች፡፡ “ንፁህ ከሆንሽ በቃ እርሺው! ስማችን የበለጠ ከመጥፋቱ በፊት ፈጠን ብለሽ ጥሩ የአሕመዲ ሙስሊም ማግባት ይኖርብሻል፡፡

ቢያንስ አሕመዲ ያልሆነ ሙስሊም ማግባት ኖርብሻል፡፡ ሒንዱ እንዴት ተብሎ? አስቶጉፉሩላህ!”

የአጎቴ ልጅ ፊቷ በእጆቿ እንደተሸፈነ እያነባች በሚርገበገብ ድምፅ “ግን እኮእወደዋለሁ” አለች፡፡

አክስቴ ትንፋሿ እየተቆራረጠ “አእምሮዋ መስራት ማቆሙን ማመን አልችልም” በማለት ካጉተመተመች በኋላ ወደ ልጅቷ በመዞር በቁጣ ድምፅ “ፍቅር ማለት ምን ማለት እንደሆነ አታውቂም! በአሜሪካዊነት አስተሳሰብ አትጠመቂ፡፡ ታላላቆችሽን ስሚ!” በማለት አንባረቀች፡፡

ከንግግሩ በኋላ ሌላ ፀጥታ ነገሠ፡፡ በክፍሉ ውስጥ የነበሩት ወንዶች ምንም ሳይተነፍሱ ያዳምጡ ነበር፡፡ በቦታው መገኘታቸው ለንግግሩ ክብደት የመስጠትና የሴቶቹን ስሜት የማረጋጋት ሚና ነበረው፡፡

ከቆይታ በኋላ እናቷ ቀጠለች “ወንድ አያትሽሚስዮናዊ ነበሩ፡፡ የአጥንቱ ፍላጭ የሥጋው ቁራጭ ውርሳችንን፣ እስልምናን ማንቋሸሿን ቢሰማ ምን ሊሰማው እንደሚችል አስበሻል?”

“ምንም ማሰብ አያስፈልገንም” አያቴ ዓይኖቿን አተኩራ እያየች ንግግሯን ቀጠለች “አንቺ ከሠራሽው ሥራ የተነሳ ነው ሕይወቱ ያለፈው፡፡”

አያቴ ሰዎችን በቀጥታ ስትወቅስ የሰማሁበት ብቸኛ ጊዜ ቢኖር ይህ ነበር፡፡ ከምስራቅ ሰዎች ፅኑ የፍቅር ባሕል የመነጨ ንግግር ቢሆንም ነገር ግን የአጎቴ ልጅ ንግግሩን ባሰበች ቁጥር እስከ ዛሬ ድረስ ጭንቀት ይሰማታል፡፡[14] ከቤተሰብ ጋር በዚህ መልኩ ግጭት ውስጥ ለመግባት እርሷ ብቸኛ ሰው አይደለችም፡፡ ስደተኛ ወላጆች በምዕራብ እያሉ የሚወልዷቸው ልጆች በወጣትነት ዘመናቸው ግጭት ውስጥ መግባታቸው የተለመደ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ሙስሊም ስደተኞች በምዕራብ እያሉከሚወልዷቸውልጆችበእጅጉ የተለየ አመለካከት እንዳላቸው ያስገነዝበናል፡፡

ከምስራቅ ባሕል የሚመጡ ሰዎች እውነትን የሚመዝኑት በሥልጣን ተዋረድ እንጂ የግል ምዘና በማድረግ አይደለም።[15] በርግጥ ምስራቃውያን ነገሮችን በጥልቀት ይመረምራሉ ነገር ግን በምዕራብ እንደሆነው ያን ያህል ግምትና ቦታ የሚሰጠው አይደለም። መሪዎች በጥልቀት የማጤኑን ሥራ ይሠራሉ። ከሁሉ የተሻለ እንደሚያውቁም ይታመናል። መረጃዎችን ከተለያዩ ምንጮች በመሰብሰብ እውነትን አንጥሮ ለማውጣት የሚደረግ ጥልቅ ምርመራ የሊቃውንት እንጂ የሁሉም ሰው ተግባር አይደለም።

ይህ ሁኔታ በነዚህ ባሕሎች ውስጥ የሚድጉትን ሙስሊሞች አስቸጋሪ አጣብቂኝ ውስጥ እንዲገቡ ያደርጋቸዋል። አንድ ሰው ወይም ተቋም የበላይ ነው ወይንም የበላይ አይደለም። ተኣማኒ ነው ወይም ተኣማኒ አይደለም። ጥሩ ወይም መጥፎ ነው። በሥልጣን ተዋረድ በሚያምኑ ባሕሎች ውስጥ ነጭና ጥቁር እንጂ በሁለቱ ድንበር ላይ የሚገኘው ግራጫ ቀለም የሚባል ነገር አይታወቅም።

ምስራቃውያን መምህራን ምዕራባውያን ሁሉ ክርስቲያኖች እንደሆኑና ባሕላቸውም የተበላሸ መሆኑን እስልምናንም እንደሚቃወሙ ያስተምራሉ። ስለዚህ አብዛኛው ሙስሊም ስደተኛ ምዕራባውያን ጋጣ ወጥ ክርስቲያኖችና የእስላም ጠላቶች ይመስሏቸዋል።

ወደ አሜሪካ ሲመጡ የባሕል ልዩነትና ቅድመ ግንዛቤያቸው ከምዕራባውያን ራሳቸውን እንዲነጥሉ ያደርጋቸዋል። ልክ እንደ እናቴ ሁሉ ብዙዎቹ ከራሳቸው አገራት ከመጡ ሰዎች ጋር ብቻ የሚግባቡ ሲሆን ይህ ደግሞ አመለካከታቸው እንዳይስተካከል ያደርጋል። ከዚህ በላይ ደግሞ አንዳንድ ሙስሊሞች በምዕራባውያንና በክርስቲያኖች ጉዳት ስለሚደርስባቸው ሁሉንም ምዕራባውያንና ክርስቲያኖች በአንድ መነፅር ለማየት ይገደዳሉ።

ሙስሊሞች ወደ ሌሎች ሰዎች ቤት የሚጋበዙት አልፎ አልፎ ብቻ ነው። የባሕልና የመስተንግዶ ልዩነቶች ሙስሊሙ ምቾት እንዳይሰማው ሊያደርጉ ይችላሉ። ልዩነቶቹን ለማስወገድ አስተናጋጁ አስቀድሞ ለመጠየቅ፣ መረጃ ለማግኘትና ነገሮችን ለማመቻቸት

ፍቃደኛ ቢሆን መልካም ነው፡፡ አንድ ሙስሊም ስደተኛ የክርስቲያኖችንና የምዕራባውያንን አውድ እንዳይረዳ የሚያደርጉ በርካታ እንቅፋቶች አሉ፡፡ የተለየ ፍቅር፣ ትህትና፣ እንግዳ ተቀባይነትና ልበ ሰፊነት ብቻ ናቸው እነዚህን እንቅፋቶች ለማሸነፍ የሚያስችሉት፡፡ ይህንን እያደረጉ የሚገኙት ደግሞ በጣት የሚቆጠሩ ሰዎች ብቻ ናቸው፡፡

ቤተሰቦቻችን "አሜሪካዊነት" እንዳያጠቃን የሞት ሽረት ትግል የሚያደርጉት በዚህ ምክንያት መሆኑ ግልፅ የሆነ ይመስለኛል፡፡ ቃሉ ከብሔርተኝነት ጋር የተያያዘ አይደለም፡፡ ነገር ግን ሰዎች ባሕሉን ከሚያዩበት መነፅር ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በአሜሪካዊነት አስተሳሰብ መጠመቅ ማለት ለታላላቆች አለመታዘዝ፣ በአለባበስ ገደብ ማጣትና ከቤተሰብ ይልቅ ከጓደኞች ጋር ጊዜን ማሳለፍ ተደርጎ ይተረጎማል፡፡ መሳደብ፣ መጠጣትና ከተቃራኒ ፆታ ጋር ማሳለፍ ፈፅሞ የማይታሰብ ነው፡፡

ከሁሉ ይልቅ አሳዛኙ ነገር ሙስሊም ስደተኞ የምዕራባውያንን ጋጣ ወጥነት ከክርስትና ጋር ማያያዛቸውና ሳያገናዝቡ ተጠራጣሪዎች መሆናቸው ነው፡፡ ምዕራባውያን ክርስቲያኖች ናቸው፣ ምዕራባውያን በአሜሪካዊነት አስተሳሰብ የተጠመቁ ናቸው፤ በዚህ አስተሳሰብ የተጠመቁበት ምክንያት ደግሞ ክርስቲያኖች በመሆናቸው ነው፡፡ በበርካታ ሙስሊሞች አስተሳሰብ ይህንን ስርኣት አልበኛ የሆነ ምዕራባዊ ባሕል የፈጠረው ክርስትና ነው፡፡ ስለዚህ ክርስትና ከእግዚአብሔር የሆነ ሃይማት አይደለም በማለት እንዲደመድሙ ምክንያት ሆኗቸዋል፡፡

ቅጥ ያጣ አለባበስ ለብሰው በቴሌቪዥን መስኮቶች ላይ የሚታዩት ሰዎች ክርስቲያን ላይሆኑ እንደሚችሉ እማና አባ እንዲረዱ ጥረት ማድረጌን አስታውሳለሁ፡፡ የእነርሱ መልስ ግን "ምን ማለትህ ነው? ራሳቸውን ‹ክርስቲያን› እያሉ ይጠሩ የለም እንዴ? ደግሞስ መስቀል ማድረጋቸው አይታይህም?" የሚል ነበር፡፡ አንዳንዶቻቸው የስም ክርስቲያኖች ብቻ መሆናቸውንና በእግዚአብሔር እንኳ የማያምኑ መሆናቸውን ሳስረዳ በእግዚአብሔር የማያምኑ ክርስቲያኖች ናቸው የሚል መልስ አገኛለሁ፡፡ ሃይማኖትን

ከእምነት ጋር ሳይሆን ከባሕል ጋር ነው የሚያያይዙት፡፡ አሳዛኙ ነገር ማንም ሰው ከዚህ የተለየ አስተሳሰብ እንዲኖራቸው ምክንያት አለመስጠቱ ነው፡፡ የተለየ አኗኗር ያለው አንድ ክርስቲያን እንኳ ቢያውቁ ኖሮ የተሳሳተ ግንዛቤያቸው ተስተካክሎ ክርስትናን መልካም በሆነ መነፅር ማየት በቻሉ ነበር፡፡

የምዕራባውያን ሙስሊሞች ካልኣይ ትውልድ የሆኑት ልጆቻቸው ግን ከዚህ የተለየ አመለካከት ነው ያላቸው፡፡ ሁለተኛው ትውልድ ልክ እንደ ጎረቤቶቻቸው ድብልቅ ናቸው፡፡ ስለ እነርሱ ሊነገር የሚችል አንድ ነገር ቢኖር ይህ ነው፤ ሙሉ በሙሉ ማለት ይቻላል ዓለምን የሚመለከቱት በምዕራባውያን መነፅር ሲሆን ነገር ግን ራሳቸውን ከእስልምና ወገን ያስሰልፋሉ፡፡

አንዳንዶች እንደ እኔ ነገሮችን በጥልቀት እንዲያጤኑ ተደርገው ያደጉና እስልምናን የሚወዱ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በጣም የተማሩ ነገር ግን *ቡርቃ* የተሰኘውን ዓይነ ርግብ የሚለብሱ፤ ምርጫቸውንም ምክንያዊ በሆነ መንገድ የሚያስረዱ የአክስቴና የአጎቴ ሴቶች ልጆች አሉ፡፡ ሌሎች እንደ አጎቴ ወንዶች ልጆች ያሉት ደግሞ ‹ሙስሊም› ከሚለው ስም ውጪ እስልምናን ሙሉ በሙሉ የተው ናቸው፡፡

ከባሕሉ ጋር የተቆራኘም ሆነ የስም ሙስሊም የሆነ ወጣት ከባሕል ግጭት ችግር ጋር መጋፈጡ የማይቀር ነው፡፡ እንደ እኔ በጣም ጠንካራ የሆኑ ወላጆች ያሉት ወጣት ባሕሉን አጥብቆ ለመያዝ የበለጠ ይጋደላል፡፡ ወላጆች ደግሞ የስም ሙስሊሞች ብቻ ከሆኑ ወጣቱም እንደዚያው ይሆናል፡፡

የልጁ ጓደኞች ስብዕና፣ አስተሳሰባቸውና በትምህርት ቤት የሚማረው ትምህርት ትልቅ ተፅዕኖ አላቸው፡፡ እህቴ ባጂ ለነገሮች ከእኔ የተለየ ዕይታ እንዲኖራት ተደርጋ ነው ያደገችው፡፡ እስካሁን ድረስ ቡርቃ ትለብሳለች፤ እስልምናንም ትወዳለች ነገር ግን እስልምናን ከምዕራባውያን የመቻቻል አስተሳሰብ ጋር ደባልቃለች፡፡ አላህ ሰዎችን ወደ ክርስትና፣ ሒንዱኢዝም፣ ይሁዲና ሌሎች ብዙ ሃይማኖቶች ሊመራ እደሚችል ታምናለች፡፡ ሁሉም መንገዶች ደግሞ ወደ አላህ ስለሚመሩ የዘላለምን ሕይወት ሊያገኙ

ይችላሉ ትላለች፡፡ ሁለታችንም በአንድ ቤት ያደግን ብንሆንም እምነቷ ግን ይህን የሚመስል ሆኗል፡፡ በውጪ ያጋጠሟት ነገሮች ከእኔ የተለየ አስተሳሰብ እንዲኖራት አድርጓል፡፡

የአጎቴ ልጅ ‹ወደ ልቦናዋ ተመልሳ› ሒንዱ የሆነውን ፍቅረኛዋን ባታገባም ነገር ግን ከዚያ ክስተት ሙሉ በሙሉ የምታገግም አትመስልም ነበር፡፡ ሌላኛው የአጎቴ ልጅ ፊሊፒናዊት ሴት ለማግባት መወሰኑ ተሰምቶ ከባድ የሆነ ተቃውሞ ገጥሞት የነበረ ቢሆንም ነገር ግን ‹ወደ ልቡ ተመልሶ› ሙሉ በሙሉ በማገገም ፓኪስታናዊት ልጅ አግብቷል፡፡ እንደገና ሌላ የአጎቴ ልጅ አሜሪካዊት ሴት ለማግባት በመወሰኑ ምክንያት የተለመደው ተቃውሞ አጋጥሞት የነበረ ቢሆንም እርሱ ግን በሐሳቡ በመፅናት አግብቷታል፡፡

የጠቀስኳቸው እነዚህ ሁለተኛ ትውልዶች በሙሉ የሥጋ ዘመዶቼ ናቸው፡፡ ሥር መሠረታቸው ፓኪስታን ውስጥ የምትገኝ አንዲት ከተማ ናት፤ በአንድ ጀማት ውስጥ ነበር ያደጉት፤ ሁሉም ደግሞ ከሞላ ጎደል በተመሳሳይ የዕድሜ ክልል የሚገኙ ናቸው፡፡ ሆኖም ሁላቸውም ራሳቸውን እንደ ሙስሊም የሚቆጥሩ ሲሆኑ የወላጆቻቸውን ሃይማኖት እንደወረሱ ይናገራሉ፡፡

ስለዚህ በምዕራብ አገር ውስጥ ሙስሊም መሆን ማለት ምን ማለት ነው? ብዙ ትርጉም ሊኖረው ይችላል፡፡ አንድ ሰው ምን እንደሚወድና ምን እንደሚያምን ለማወቅ ከፈለጋችሁ በግል መጠየቅ በእጅጉ አስፈላጊ ነው፡፡ ነገር ግን አንድን ሰው ቀርበን ከማወቃችን በፊት ልናደርገው የምንችለው ትልቁ ነገር ቢኖር ስደተኛ ወይንም ሁለተኛ ትውልድ ሙስሊም መሆን አለመሆኑን ማጣራት ነው፡፡ ይህ አንዱ ሁኔታ ብዙ ጊዜ ትልቅ ልዩነት ይፈጥራል፡፡

# ራስን መሳት እና መተካካት

ምስራቃዊ ሰው እንደ መሆኔ መጠን ከምዕራባውያን ጋር የነበረኝ ተግባቦት የተቃኘው በእስላማዊ ዓቀበተ እምነት ነበር፡፡ የኔን ትውልድ እስረኛ ካደረገው የድህረ ሥልጣኔ አንፅሮት ጋር ትግል ማድረግ እምብዛም አላስፈለገኝም ነበር፡፡ በኔ አመለካከት እውነት ፍንትው ብላ የምትታይ ናት፡፡ እውነት ከሌለች እውነት የለችም የሚለው አባባል ራሱ እውነት ይሆንና ለእውነት መኖር ምስክር ይሆናል፡፡ ምርጫ የለም፤ እውነት መኖሯ ግድ ነው፡፡በተለምዶ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ይህንን አስተሳሰብ ይጋሩታል፡፡ ሁለቱም በእውነት መኖር ያምናሉ፡፡ ቢያንስ ሃይማኖታቸው እውነት መሆኑን ያምናሉ፡፡ ነገር ግን የጋራ አስተሳሰቦቻቸው ከዚህ የላቀ ነው፡፡ አሃዳዊነትን፣ መንፈሳዊና ቁሳዊ አፅናፋትን፣ መላእክትንና አጋንንትን፣ መልካምና ክፉን፣ የመጨረሻውን ፍርድ፣ ገነትና ገሃነምን፣ የቅዱሳት መጻሕፍትን ግልጠተመለኮት እንዲሁም ሌሎች ጥቃቅን እሳቤዎችን በተመለከተ በግርድፉ ተመሳሳይ የሆነ እምነት ነው ያላቸው፡፡

እነዚህ የጋራ ጉዳዮች በሁለት ወገን እንደተሳለ ሰይፍ ናቸው፡፡ ሁለቱም ዓለምን ከተመሳሳይ የዕይታ ፅንፍ እንዲመለከቱ በማድረግ ለውይይትና ለመግባባት የጋራ መደላድልን ይፈጥራሉ፡፡ ነገር ግን እነዚህ የጋራ ነገሮች በሃይማኖታቱ ቁልፍ አስተምህሮዎች ላይ ያሉትን ልዩነቶች ማከረር ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ ያህል እስልምናና ክርስትና ስለ ኢየሱስና ስለ መሐመድ ያላቸውን ልዩነቶች ማየት ይቻላል፡፡

በክርስቲያኖች እምነት መሠረት ኢየሱስ የተሠገወ አምላክ ነው፡፡ ይህ እምነት ደግሞ ለታሪካዊው ክርስትና እጅግ ቁልፍ ነው፡፡[16] ሙስሊሞች ኢየሱስ ከነቢይ በላይ እንዳልሆነ

ያምናሉ፡፡ የተሠገወ አምላክ አድርጎ እርሱን መቁጠር በቁርአን መሠረት ክህደት ሲሆን ወደ ገሃነም ያወርዳል፡፡[17]

በሙስሊሞች እምነት መሠረት መሐመድ የአላህ መልእክተኛ ነው፡፡ ይህ እምነት ወሳኝ ከመሆኑ የተነሳ የሸሃዳ ግማሽ ክፍል ነው፡፡ በክርስቲያኖች እምነት መሠረት በኢየሱስ በኩል የሚገኘውን መዳን የሚያበስረውን ወንጌል የሚፃረር ትምህርት የሚያስተምሩ ሰዎች ሀሰተኛ መምህራን ናቸው፡፡[18]

በሙስሊሞችና በክርስቲያኖች መካከል የሚደረጉት ውይይቶች በኢየሱስና በመሐመድ ላይ የማተኮራቸው ምክንያት ይህ ልዩነት ነው፡፡ ሙስሊም ወጣት እንደመሆኔ መጠን የእስልምና ውጤታማ አምባሳደር ለመሆን ጥሩ ተቀባይነት ከማግኘት በዘለለ በነዚህ ልዩነቶች ላይ ጥልቅ ዕውቀት ሊኖረኝ እንደሚያስፈልግ አስብ ነበር፡፡መሐመድን በተመለከተ ምዕራባውያን ያላቸው ዕውቀት በእጅጉ አናሳ ነው፡፡ ስለ እርሱ የፈለኩትን ነገር ብናገር ሰዎች ያምኑኛል፡፡ ማንንም የማታለል ፍላጎት ባይኖረኝም ነገር ግን አብዛኞቹ ክርስቲያኖች ዕውቀት ስለሌላቸው ስለ መሐመድ ጥሩ ጥሩ ነገሮችን በመናገር ማሳመን ቀላል ነው፡፡ በልጅነቴ የተማርኳቸውን ነገሮች በተለይም ወደ መካ በተመለሰ ጊዜ ያሳየውን ደግነት በመናገር ሰዎች ለመሐመድና ለእስልምና ያላቸው አመለካከት ከቀድሞው የተሻለ እንዲሆን ያደረኩባቸው ጊዜያት ነበሩ፡፡

ኢየሱስን በተመለከተ ሙስሊሞች ከክርስቲያኖች ጋር የማይስማሙባቸው ሁለት ቁልፍ ጉዳዮች አሉ፡፡ እነርሱም ኢየሱስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ መሞቱና አምላክነቱን መናገሩ ናቸው፡፡ ቁርአን እነዚህን ሁለቱን እምነቶች ያስተባብላል፡፡[19] ጥሩ የእስልምና አምባሳደር ለመሆን እነዚህን ሁለቱን ጉዳዮች በጥልቀት ማጥናትና ኢየሱስ አምላክ መሆኑን አለመናገሩን እንዲሁም በመስቀል ላይ አለመሞቱን ሽንጤን ገትሬ መሟገት ያስፈልገኛል፡፡ ሁለተኛውን በተመለከተ የኛ ቤተ እምነት መስራች ጀማቱን ለማስታጠቅ አነስተኛ ክታብ ጽፏል፡፡ *«ኢየሱስ በሕንድ አገር»*የሚል ርዕስ ያላት ስትሆን ብዙ ጊዜ ደጋግሜ አንብቤያታለሁ፡፡[20]

የተማርኩትን በመያዝ ለመጀመርያ ጊዜ የተሚገትኩት በትምህርት ቤታችን በር ፊት ለፊት አውቶብስ ውስጥ ሆነን ወደ ቤት ለመሄድ ዝግጅት ላይ በነበርንበት ጊዜ ነበር፡፡ የፋሲካን መቃረብ ምክንያት በማድረግ ትምህርት ሲዘጋ ምን ለመሥራት እንዳቀድኩኝ ከጓደኛዬ ከክሪስተን ጋር እያወጋሁ ነበር፡፡ ግፍያ ሳይበዛ ከክፍላችን ቀደም ብለን በመውጣት መኪናው ላይ ተሳፈርን፡፡ በዕድሜ ከፍ ያልን ስለነበርን የኋላውን ወንበር ነበር የያዝነው፡፡አርብ የስቅለት ዕለት ምን ለማድረግ እንዳቀደች ከፊት ለፊቴ ተቀምጣ ትነግረኝ ጀመር፡፡

"ጉድ ፍራዴይ (መልካሚቱ አርብ) ስትዪ ምን ለማለት ፈልገሽ ነው?" በማለት ጠየኳት፡፡ ትርጉሙ አልገባኝም ነበር፡፡

"መልካሚቱ አርብ ኢየሱስ በመስቀል ላይ የተሰቀለባት ዕለት ናት፡፡"

"ታድያ እንዴት መልካም ልትሆን ቻለች?"

"በመስቀል ላይ በመሞት ኃጢአታችንን ስላስወገደልን ነው፡፡" መልሷ ቀጥተኛ ቢሆንም እኔ ግን ሳቅ አፍኖኝ ነበር፡፡ ክርስቲያኖች እንደዚያ እንደሚያምኑ ብሰማም ማንም ሰው ግን ስለ ሁኔታው በዚህ መልኩ በቀጥታ አውርቶኝ አያውቅም ነበር፡፡

"እርሱ በመስቀል ላይ መሞቱ የናንተን ኃጢአት ሊያስወግድ የሚችለው እንዴት ነው?"

"በቤተ ክርስቲያን የነገሩን እንደርሱ ነው፡፡ አላውቅም፡፡ ብዙ ጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን አንሄድም፡፡ ጠይቄ አላውቅም፡፡" ክሪስተን ራሷን እየተከላከለች አይደለም ነገር ግን በቅንነት እያወራችኝ ነበር፡፡ ለዚያ ነው ብዙ ጊዜ ከእርሷ ጋር ማውራት የሚያስደስተኝ፡፡ በጣም ቅንና አስተዋይ ልጅ ናት፡፡ ኋላ ላይ ከእርሷ ትንሽ የልጅነት ፍቅር ቢጤ ይዞኝ የነበረ ቢሆንም ቦታ ሰጥቼው ግን አላውቅም ነበር፡፡ ያንን ማድረግ ባህሌን ለድርድር ማቅረብ ስለሚሆንብኝ የማይታሰብ ነበር፡፡ አምባሳደርነቴ እንደተጠበቀ ሆኖ የወንድ ጓደኛዋ የመሆን መሻት ነበረኝ፡፡

ውይይቱን አቅጣጫ ለማስለወጥ ወሰንኩኝ፡፡ “ለማንኛውም በመስቀል ላይ ሞቷል የሚል እምነት የለኝም፡፡”

“ለምን?” በማለት ጠየቀች፡፡ እኔም የማሸነፍያ ካርዴን መዘዝኩኝ፡፡

“በመጽሐፍ ቅዱስ ምክንያት፡፡”

“ምን ማለትህ ነው?”

“እንግዲህ ሲጀመር ኢየሱስ በመስቀል ላይ የመሞት ፍላጎት እንዳልነበረው እናውቃለን፡፡ በጌቴ ሰማኒ በነበረበት ጊዜ ፈጣሪ መራራውን ፅዋ ከእርሱ እንዲወስድ ጸልዮ ነበር፡፡ መራራው ፅዋ የመስቀል ሞት መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ኢየሱስም ፈጣሪ እንዲታደገው የደም ላብ እስኪያልበው ድረስ ለሊቱን በሙሉ ሲጸልይ ነበር፡፡” ቆም ብዬ ማረጋገጫዋን ጠበኩኝ፡፡ እርሷም ራሷን ነቀነቀች፡፡

“ስለ አንቺ አላውቅም እኔ ግን ፈጣሪ ኢየሱስን እንደሚወደው አምናለሁ፡፡ ፈጣሪ የኢሱስን ጸሎት ሳይመልስ የሚቀርበት ምክንያት አይታየኝም፡፡ የዕብራውያን መጽሐፍ ያንን የሚያረጋግጥ ይመስለኛል፡፡ የሆነው ሆኖ ኢየሱስ በመስቀል ላይ የተሰቀለበትን ጊዜ ስናሰላው ሦስት ሰዓት ብቻ ነው የሚሆነው፡፡ ለሦስት ሰዓታት በመስቀል ላይ መቆየት ለሞት አይዳርግም፡፡ በወቅቱ ሰዎች በመስቀል ላይ ለቀናት ይቆዩ ነበር፡፡ በፍጥነት ነው ከመስቀል እንዲወርድ የተደረገው፡፡” የተናገርኩትን ሁሉ የምታሰላስል ነበር የምትመስለው፡፡ የተለመደውን ጥያቄ እንደምትጠይቅ በመገመት ቆም አልኩኝ፡፡ እርሷም ጠየቀች፡፡

“ለምንድነው ከመስቀል ላይ እንዲወርድ የተደረገው?”

“መጽሐፍ ቅዱስ ምክንያቱን በትክክል ይነግረናል! ጲላጦስ እንዲወርድ ስላዘዘ ነው፡፡ የጲላጦስ ሚስት ህልም በማየት ኢየሱስ እንዳይገደል ባሏን ለምናው ነበር፡፡ አይሁዶች መሰቀሉን ካረጋገጡ በኋላ እንዲወርድ ባሏን አሳምናው ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ

ጲላጦስ ከቀመስቀል አውርዶታል፡፡ ከዚያም በተጠረበው መቃብር ውስጥ እንዲሆን ተደረገ፡፡” ክሪስተን ተቃውሞ እንዳላት ስለገባኝ ቆም አልኩኝ፡፡

“ደቀ መዛሙርቱ ከዚያ በኋላ አይተውት ከሞት መነሳቱን መስክረዋል እኮ፡፡ ከመስቀል ላይ ካወረዱት እንዴት ያንን ሊያስቡ ይችላሉ?””

”ከመስቀል ላይ ያወረዱት ደቀ መዛሙርቱ ናቸው አላልኩም፡፡ የአርማቲያሱ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ነበሩ፡፡ ጲላጦስ ኢየሱስን እየረዳ ያለ ላለመምሰል ከደቀ መዛሙርቱ ጋር አልታየም፡፡ ስለዚህ ከአርማቲያሱ ዮሴፍና ከኒቆዲሞስ ጋር ነበር ሲሰራ የነበረው፡፡ የአርማቲያሱ ዮሴፍ የኢየሱስን አስከሬን ወስዶ መቃብሩ ውስጥ ካኖረ በኋላ ኢየሱስን ለማከም መቶ ፓውንድ የሚመዝን መድኃኒት ከተልባ እግር ጨርቅ ጋር ይዞ መጣ፡፡ ለሦስት ቀናት በመቃብር ውስጥ በነበረበት ጊዜ እግዚአብሔር ኢየሱስን ለማዳን መድኃኒቱን ተጠቀመ፡፡”

ክሪስተን እኔ ያላሰብኩትን ጥያቄ ጠየቀችኝ፡፡ “ነገር ግን እግዚአብሔር ኢየሱስን ለማዳን ለምን ይህንን ሁሉ ነገር ማድረግ አስፈለገው? ኢየሱስ በመስቀል ላይ እንዳይሞት ቢፈልግ ኖሮ ጥቂት ቀናት ቀደም ብሎ ኢየሱስን ወደ ሰማይ መውሰድ አይችልም ነበርን?” በጣም አስቸጋሪ ጥያቄ ነበር፡፡ ከዚያ አቅጣጫ አይቼው አላውቅም ነበር፡፡ ሆኖም ግን የኔ ጀማት አላህ ኢየሱስ በሕይወት እንዲኖር የፈለገበትን ምክንያት አስተምሮኛል፡፡

“ኢየሱስ ራሱ የተላከው ከእስራኤል ቤት ለጠፉት በጎች መሆኑን ተናግሯል፡፡ የጠፉት በጎች አይሁዶች በተሰደዱ ጊዜ በኢስያ ውስጥ የተበተኑት አይሁዶች ናቸው፡፡ በእስራኤል እንዳደረገው ሁሉ ወደዚያ በመሄድ ይሁዲን ማደስ እንዲችል ነው አላህ ያተረፈው፡፡”

ውይይቱ ሐሳባችንን ይዞት ስለነበር ተማሪዎች መኪናው ውስጥ መኮልኮል መጀመራቸውን አላስተዋልንም ነበር፡፡ ከፊታችን ባለው ወንበር ላይ የተቀመጠ ከኛ

በአንድ ክፍል የሚያንስ ልጅ ወደ እኛ ዞሮ በመቀመጥ ንግግራችንን ይከታተል ነበር፡፡ ከዚያ በቁጣ ፊቱን በማዞር “ያስጠላል” በማት አጉተመተመ፡፡

እኔም በልቤ “መልስ ቢኖረው ኖሮ ይናገር ነበር፡፡ እውነት ውሸትን ዝም ታሰኛለች” አልኩኝ፡፡

ክሪስተን አይታው ስለነበር ምናልባት ተቀይሜ እንዳይሆን ለማረጋገጥ አጤነችኝ፡፡ እኔ ምንም ቅሬታ አልገባኝም ነበር ነገር ግን ድምጿን ከፍ አድርጋ “ጥሩ ዕይታ ይመስለኛል፡፡ ስላካፈልከኝ አመሰግናለሁ” አለችኝ፡፡

ለክሪስተን ያካፈልኳት መከራከርያ “ራስን የመሳት መላ ምት” ይሰኛል፡፡ አሕመዲ ሙስሊሞችም ሆኑ ሌሎች ሙስሊሞች ያቀነቅኑታል፡፡ አሕመድ ዲዳትና ሻቢር አሊን የመሳሰሉት ሙስሊም ተሟጋቾች ይወዱታል፡፡ የተፈጠረው በዘመነ አብርሆት መገባደጃ በአስራ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን ውስጥ ሲሆን ያ ዘመን የኢየሱስን ትንሣኤ ለማስተባበል ሰዎች ተፈጥሯዊ ትንታኔዎችን ይጠቀሙ የነበሩበት ዘመን ነበር፡፡ ሚርዛ ጉለም አሕመድን የመሳሰሉት ሙስሊሞች ፈጣሪ የመኖሩን እሳቤ በማከል የኢየሱስን ከመስቀል ሞት መትረፍ ዕድል ለማስፋት ሞክረዋል፡፡ ክርክሩ እንዲህ የሚል ነው፡- “እግዚአብሔር ኢየሱስን ከሞት ማስነሳትን የሚያክል ትልቅ ተዓምር መስራት ከቻለ በመስቀል ላይ ሳለ እንዳይሞት በማድረግ አነስተኛውን ተዓምር እንዴት መስራት ይሳነዋል?”

ራስን የመሳት መላ ምት በሙስሊሞች የተፈጠረ አይደለም፡፡ የብዙሃኑም አመለካከት አይደለም፡፡ አብዛኞቹ ሙስሊሞች “የመተካካትን መላምት” ያቀነቅናሉ፡፡ የእስልምናን ቀደምት ታሪክ ስናጠና ሙስሊሞች ኢየሱስ ወደ መስቀል ከመሄዱ በፊት በሌላ ሰው እንደተተካ እናያለን፡፡ አላህ የኢየሱስን መልክ ለሌላ ሰው በመስጠቱ ሳብያ ኢየሱስ ተርፎ ያ ሰው ተሰቅሏል፡፡ “አልገደሉትም አልሰቀሉትምም ነገር ግን ተመሰለባቸው”[21] የሚለውን የቁርአን ጥቅስ በዚህ መልኩ ይተረጉሙታል፡፡በኢየሱስ ፋንታ የተገደለው ሰው ማን ነበር? የሚል ጥያቄ መነሳቱ የማይቀር ነው፡፡ የተለያዩ ሰዎች ይጠቀሳሉ፡፡

አንዳንዶች በኢየሱስ ፋንታ የመሞትን ክብር መውሰድ የፈለገ አንድ ወጣት ሰው መሆኑን ተናግረዋል፡፡ ሌሎች ደግሞ የኢየሱስን መስቀል የተሸከመው የቀሬናው ስምዖን ተሰቅሏል ይላሉ፡፡ አላህ ፍትሃዊ ፍርድ ለመፈፀም ሲል የኢየሱስን መልክ ለአስቆሮቱ ይሁዳ ሰጠው የሚሉም አሉ፡፡ በዚህ ዘመን ይህ የመጨረሻው መላ ምት በሙስሊሞች ዘንድ የበለጠ ተቀባይነት ያለው ይመስላል፡፡

የኢየሱስ እርገት በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት አለው፡፡ ቁርአን "አላህ ኢየሱስን ወደ ራሱ አነሳው" ይላል፡፡ ይህ ደግሞ ሙስሊሞች የኢየሱስን እርገትና ምፅዓት እንዲያምኑ ምክያት ሆኗቸዋል፡፡[22] ስለዚህ እንደ ክርስቲያኖች ሁሉ አብዛኞቹ ሙስሊሞች የመሲሁን ዳግም ምፅዓት ይጠባበቃሉ፡፡ አሕመድ መሲሁ መሆኑን በመናገሩ ምክያት የኛ ጀማት ይህንን አመለካከት አይቀበልም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን በመጥቀስ አይሁድ የኤልያስን ከሰማይ መምጣት መጠበቃቸው ስህተት ነው ብሏል፡፡ ኢየሱስ መጥምቁ ዮሐንስምፅዓተ ኤልያስ መሆኑን ተናግሯል፡፡ በተመሳሳይ መንገድ ዓለም የኢየሱስን መምጣት ቢጠብቅም እርሱ ግን በሚርዛ ጉለም አሕመድ በኩል ተመልሷል፡፡በእርግጥ የኛ ጀማት የሚያስተምረውን ሁሉ ዓይኔን ሳላሽ ስለምቀበል ኢየሱስ አርጓል ከሚለው አመለካት ይልቅ ወደ ሕንድ በመሄድ እዚያ ሞቷል የሚለውን አመለካከት በመደገፍ ነበር እከራከር የነበረው፡፡[23] አመለካከቴን ለሌሎች ባካፈልኩኝ ቁጥር እምነቴ እየጠነከረ ይመጣ ነበር፡፡ ሰዎች የኔን አመለካከት ውድቅ ለማድረግ የሚያስችል ምንም የረባ ነገር አለማቅረባቸውን ስመለከት ደግሞ የበለጠ ድፍረት በማግኘት እሰብክ ጀመር፡፡ የእስልምና አምባሳደር ለመሆን የሚያበቃኝን ግማሹን የክርክር ርዕስ በጥልቀት ያወቅሁት ሆኖ ተሰማኝ፡፡ የተቀረው ደግሞ ከዚያ እንደሚቀል አሰብኩኝ፡፡ ልክ ነበርኩኝ፡፡

ምዕራፍ አሥራ አራት

# አብ ከኢየሱስ ይበልጣል

አሥረኛ ክፍል ስደርስ የግል ሕይወቴ ጉልህ በሆነ ሁኔታ መለወጥ ጀመረ፡፡ ከጓደኞቼ ጋር በስልክ በመነጋገርም ሆነ በትምህርት ቤት ረዘም ያሉ ጊዜያትን የማሳለፍ ነፃነት ነበረኝ፡፡ ልብሶቼን እናቴ የምትመርጥልኝ ሲሆን ለአለባበስ እጨነቅ ነበር፡፡ “ቀለሜዋ” ላለመምሰል የንባብ መነፅር ከማድረግ ይልቅ በዓይን ብሌን ላይ የሚለጠፍ ሌንስ እንዳደርግ እንዲፈቀድልኝ እናቴን ብጠይቃትም ፍቃደኛ አልሆነችም፡፡

የምዕራባውያን ባሕል ተፅዕኖ ልቋቋመው የምችለው ዓይነት አልነበረም፡፡ አሁንም ድረስ ውጪ እንዳድርና የትምህርት ቤት የጭፈራ ዝግጅቶች ላይ እንድታደም አይፈቀድልኝም ነበር፡፡ ከጓደኞቼ ጋር የነበረኝ ቅርርብ ስለበረታ ከእነዚህ ዝግጅቶች መቅረት አስቸጋሪ ነበር፡፡

አንድ ቀን በላቲን ቋንቋ ክፍለ ጊዜ እንደሆነው እምነቴ በቀጥታ በሚጠቀስበት ወቅት በኩራት እስልምናን ለመወከል መቆሜን አላስተጓጎልኩም፡፡

በፐሪንሰስ ኣን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላቲን የሚያስተምሩ ሁለት መምህራን ነበሩ፡፡ ተማሪዎቻቸው በትምህርቱ ደስተኛ መሆናቸውን ሲገልፁ እነዚህ መምህራን በደስታ ይፈነድቁ ነበር፡፡ ላቲን ሁለትን ታስተምር የነበረችዋ መምህርት ኢርለስ ከሚገባው በላይ ትቀርበኝና ደግነትን ታሳየኝ ነበር፡፡ የላቲን ቋንቋንና የእርሷን ክፍለ ጊዜ በጣም ነበር የምወደው፡፡ የሚገስፀኝ ሰው ባለመኖሩ የተነሳ ከጊዜ ወደ ጊዜ ፀባዬ ተለውጦ ተንኮለኛ መሆን የጀመርኩበት ወቅት ነበር፡፡ የቤት ሥራዬን ብዙ ጊዜ የምረሳ

ዓይነት ተማሪ ስለሆንኩ ወደ ክፍል ከመግባቴ ከጥቂት ሰዓታት በፊት በማስታወስ በጥድፊያ ሞነጫጭሬ ለመጨረስ እሞክር ነበር፡፡ የመምህርት ኢርለስ ክፍለ ጊዜ ከእስፓኒሽ በፊት ስለነበረ ብዙ ጊዜ እርሷ ስታስተምር ክፍል ውስጥ ሆኜ የእስፓኒሽ የቤት ሥራ እሠራ ነበር፡፡ የእስፓኒሽ መጽሐፌን ከላቲን ስር በመደበቅ እርሷ ለመጻፍ ወደ ጥቁር ሰሌዳው ስትዞር እየፈፀምኩ ያለሁትን ነገር እንደማታውቅ በማሰብ የቤት ሥራዬን እሠራ ነበር፡፡ በዓመቱ አጋማሽ ላይ ግን የማደርገውን እያወቀች መጥፎ አመሌን መታገሷን ተረዳሁኝ፡፡

ከዕለታት በአንዱ ቀን የእስፓኒሽ የቤት ሥራዬን እየሠራሁ ሳለሁኝ አንዲት ልጅ ወደ እኔ በመዞር “ነቢል የሆነ ነገር ልጠይቅህ ፈልጌ ነበር” አለችኝ፡፡ ስሟ ቤስቲ ይሰኛል፡፡ በክፍላችን የምትገኝ የተመሰከረላት ክርስቲያን ነበረች፡፡ ሁሉም ሰው የወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን አባል መሆኗን ያውቃል፡፡ ብዙ ጊዜም ስለ እምነቷ ጥብቅና ትቆም ነበር፡፡ ከደግነቷና ሌሎችን ከመርዳት ፍላጎቷ ባሻገር ለስለስ ያለ ነገር ግን ሁላችንንም የሚስፈራ አቀራረብ ነበራት፡፡ ችግር እንዳለባት እናስብ ነበር፡፡

“ይቻላል” አልኳት፡፡ ምን ልትለኝ እንደሆነ ምንም የማውቀው ነገር አልነበረም፡፡ እርሳስ ፈልጋ ቢሆን ኖሮ በቀጥታ ትነግረኝ ነበር እንጂ የሆነ ነገር ልትጠይቀኝ እንደፈለገች መናገር አያስፈልጋትም ነበር፡፡ እኔ ደግሞ ሁል ጊዜ እርሳሴን ረስቼ እንደምመጣ ስለሚታወቅ እኔን መምረጥ አልነበረባትም፡፡

ትንሽ ፀጥ ብላ ከቆየች በኋላ “ስለ ኢየሱስ ታውቃለህ?” በማለት ጠየቀችኝ፡፡

‹ይህቺ ልጅ ጤና የላትም› አልኩኝ ለራሴ፡፡ በላቲን ክፍለ ጊዜ እንዴት እንዲህ ዓይነት ርዕስ ታነሳለች? በዚያው ቅፅበት ደግሞ ለእርሷ የአክብሮት ስሜት ተሰማኝ፡፡ ሌሎች ክርስቲያኖች ለምንድነው ይህንን ጥያቄ ያልጠየቁኝ? ወደ ገነት እንድሄድ ኢየሱስ እንደሚስፈልገኝ ያስቡ የለም እንዴ? ወደ ገሃነም እንድሄድ ስለሚፈልጉ ነው ወይንስ የሚናገሩትን ነገር ስለማያምኑ ነው?

በአሁኑ አውድ መልስ እንዴት መስጠት እንዳለብኝ ማሰብ ጀመርኩኝ፡፡ ሁኔታውን ለማጤን ከእስፓኒሽ የቤት ሥራዬ ላይ ቀና አልኩኝ፡፡ መምህርት ኢርለስ ወጣ በማለቷ በዙርያችን የነበሩት ተማሪዎች አፍ ለአፍ ገጥመው ማውራት ተያይዘዋል፡፡ ውይይቱ አጓጊ ስለሚሆንብኝ ጊዜዬን እዳይበላብኝ ስጋት አደረብኝ፡፡ መልሴን በተቻለ መጠን አጠር ለማድረግ ወሰንኩኝ፡፡

“አዎ” አልኳት፡፡

ዓይኖቿ ፈጠጡ፡፡ የጠበቀችው መልስ እንዳልሆነ ግልፅ ነው፡፡ “እውነትህን ነው? ስለ እርሱ የምታውቀው ምንድነው?”

“እንግዲህ እኔ ሙስሊም አይደለሁ? ሙስሊሞች ደግሞ ኢየሱስ ኃጢአት አልባ መሆኑንና ከድንግል መወለዱን ያምናሉ፡፡ ለምፃሞችን አንፅቷል፣ ዕውሮችን አብርቷል፣ ሙታንን አስነስቷል፡፡ ኢየሱስ መሲህና የአላህ ቃል ነው፡፡”[24]

ቤስቲ የመገረም ስሜት ታየባት፡፡ ከምታውቀው በላይ ሳልናገር አልቀርም፡፡ ከየት እንደምትጀምር ግራ የገባት ይመስላል፡፡ ስለዚህ እኔ ንግግሬን ቀጠልኩኝ፡፡

“ነገር ግን ኢየሱስ አምላክ አይደለም፡፡ ሰው ብቻ ነበር፡፡” አውደ ቀቲሉን አስምሬላት የመልስ ምቷን መጠባበቅ ጀመርኩኝ፡፡

“ይገርማል፣ ስለ ኢየሱስ ያለህ ዕውቀት ከገመትኩት በላይ ሆኖብኛል፡፡ ግሩም ነው! በብዙ ጉዳይ ላይ ካንተ ጋር እስማማለሁ፡፡ ደግሞም የማልስማማበት ነገር አለ፡፡ ብነግርህ ቅር ይልሃል?” መልሷ ለስለስ ያለ ቢሆንም ነገር ግን ግትር ባሕሪዋን ያንፀባርቅ ነበር፡፡

“ችግር የለውም ቀጥይ፡፡” ውይይቱ እኔ በምፈልገው መስመር እየሄደ ያለ ይመስላል፡፡

“ክርስቲያን መሆኔን ማወቅ አለማወቅህን እርግጠኛ አይደለሁም፡፡”

“ክርስቲያን እንደሆንሽ አስባለሁ፡፡” ፈገግ ብዬ ለራሴ እንዲህ አልኩት “አይ ቤስቲ ክርስቲያን መሆንሽንማ ዓለም ሁሉ ያውቃል፡፡” ክርስቲያን መሆኗን በማወቄ ደስተኛ መሆኗን የፊቷ ገፅታ ያሳብቃል፡፡

“ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እናምናለን፤ ያ ደግሞ ለኛ እጅግ ወሳኝ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነ ኃጢአት አልባ ነው፡፡ ስለዚህ የኛን ኃጢአት የመሸከም ብቃት አለው፡፡”

ከዚህ ንግግር ጋር አልስማማም ነገር ግን የፍልሚያ ሜዳውን ስላሰመርኩኝ በኢየሱስ አምለክነት ላይ አተኮርኩኝ፡፡ የጋራ መደላድል በመፍጠር መጀመር ፈለኩኝ፡፡

“ቤስቲ ዛሬ በእጃችን የሚገኘው መጽሐፍ ቅዱስ የፈጣሪ ቃል መሆኑን አላምንም፡፡ በዘመናት መካከል ብዙ ጊዜ ተለዋውጧል፡፡ ለአሁን ግን እስኪ የፈጣሪ ቃል ነው ብዬ ልቀበል፡፡ ኢየሱስ ‹እኔ አምላክነኝ› ብሎ የተናገረበት ቦታ አለ?”

ቤስቲ ለአፍታ አሰብ አደረገች፡፡ ብዙም የተጨነቀች አትመስልም ነገር ግን ኢየሱስ እንደርሱ ብሎ የተናገረበትን ቦታ ማስታወስ የቻለች አትመስልም፡፡ “በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ኢየሱስ ‹እኔና አብ አንድ ነን› ብሏል” በማለት መለሰች፡፡

ልትጠቅሰው የምትችለው ጥቅስ እርሱ ሊሆን እንደሚችል ገምቼ ነበር፡፡ መልስ ለመስጠት ደግሞ ዝግጁ ነበርኩኝ፡፡ “ልክ ነሽ ነገር ግን ደግሞ እዚያው የዮሐንስ ወንጌል ውስጥ እርሱና አብ አንድ እንደሆኑት ሁሉ ደቀ መዛሙርቱም አንድ እንዲሆኑ ጸልዮዋል፡፡ ‹አንድ› ሲል ምን ለማለት ፈልጎ እንደሆነ ግልፅ አድርጓል፡፡ የመንፈስና የዓላማ አንድነት ለማለት ፈልጎ ነው፡፡ አንድ ተፈጥሮ ለማለት ቢፈልግ ኖሮ ደቀ መዛሙርቱም እንደዚያው መሆን እንዲችሉ ይጸልይ ነበርን? ደቀ መዛሙርቱ አንድ ተፈጥሮ እንዲኖራቸው ነው እንዴ የጸለየው?”

በማስተዋል ሆና "ጥሩ ነጥብ ነው" በማለት መለሰች፡፡ ጥሩ መልስ? ንፅረተ ዓለሟን እያናጋሁ ነው፡፡ እንዴት ሆና ልትረጋጋ ቻለች? ይህች ልጅ እንደው በዘመኗ ድንጋጤ የሚባል ነገር ያውቃት ይሆን?

"በእርግጥ አሁን መልስ ልሰጥህ ባልችልም መልሱ ግን እዚያው የሚገኝ ይመስለኛል፡፡ አጥንቼ እመልስልሃለሁ፡፡"

"መልስ ብትሰጪኝ ደስ ይለኛል ቤስቲ፡፡ ነገር ግን መልስ እንደማታገኚለት እርግጠኛ ነኝ፡፡ ኢየሱስ አምላክ ነኝ አላለም፡፡" ክርክሬን ቀጠልኩኝ "ተቃራኒውን ግልፅ አድርጎልናል፡፡ ተርቧል፣ ተጠምቷል፣ ብቸኝነት ተሰምቶታል፣ ተፈትኗል፣ አልቅሷል ደግሞም ደምቷል፡፡ ‹የሰው ልጅ› እንጂ ‹የእግዚአብሔር ልጅ› ብሎ ራሱን ጠርቶ አያውቅም፡፡ ሰው መሆኑ በጣም ግልፅ ነው፡፡"

ቤስቲ ጭንቅላቷን በመነቅነቅ መስማማቷን ትገልፅ ነበር፡፡ "አዎ ልክ ነህ፡፡ ኢየሱስ ሰውም አምላክም ነው፡፡"

"አንድ አካል እንዴት ሰውም አምላክም ሊሆን ይችላል? ሰው ሟች ነው፤ አምላክ ኢ-ሟቲ ነው፡፡ ሰው ውሱን ነው፤ አምላክ አይወሰንም፡፡ ሰው ደካማ ነው፤ አምላክ ሁሉን ቻይ ነው፡፡ ሰው መሆን አምላክ አለመሆን ነው፡፡ አምላክ መሆን ደግሞ ሰው አለመሆን ነው፡፡"

ይህ ትንሽ ደንገጥ ያደረጋት ይመስላል፡፡ ከአቅሟ በላይ ቢሆንባትም የተወሰነ ያህል መግፋት እንዳለብኝ ወሰንኩኝ፡፡

"ኢየሱስ ወደ ገሊላ በሄደ ጊዜ የማርቆስ ወንጌል ተዓምራት ማድረግ አለመቻሉን ይነግረናል፡፡ ማድረግ ስላልፈለገ አይደለም ነገር ግን ስላልቻለ ነው፡፡ አምላክ ተዓምራት ማድረግ ይሳነዋል እንዴ? አንዲት ሴት በሕዝብ መካከል በነካችው ጊዜ ማንነቷን መለየት አልቻለም ነበር፡፡ አምላክ እንዲህ ቀላል የሆነውን ነገር ማወቅ እንዴት ይሳነዋል?" እንድታስብ ፋታ ከሰጠሁ በኋላ ቀጠልኩኝ፡፡

“አንድ ሰው ‹ቸር› ብሎ በጠየቀው ጊዜ ቸር አለመሆኑንና ፈጣሪ ብቻ ቸር መሆኑን ተናሯል፡፡[25] በእርሱና በፈጣሪ መካከል ያለውን ልዩነት በግልፅ አስቀምጧል፡፡ የዓለም ፍፃሜ መች እንደሆነ እንደማያውቅና ዕውቀቱ በፈጣሪ ዘንድ ብቻ እንደሚገኝ ተናግሯል፡፡ አምላክ አለመሆኑን ያለ ምንም መሸፋፈን ተናግሯል እኮ፡፡”

ቤስቲ አፏ የተለጎመ ይመስል ነበር፡፡ ስለዚህ ጉዳይ ከዚህ ቀደም አልተማረችም፡፡ የመጨረሻውን ግብኣተ መሬት ለመፈፀም ጊዜው እንደሆነ በማሰብ ንግግሬን ቀጠልኩኝ፡፡

“ቤስቲ ምንም ዓይነት ጥርጣሬ እንዳይኖረን ለማድረግ ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ‹ከእኔ አብ ይበልጣል› በማለት ተናሯል፡፡ ኢየሱስ ከተናገረው ጋር እስማማለሁ፡፡ ፈጣሪ ከኢየሱስ ይበልጣል፡፡ አንቺም መስማማት የሚኖርብሽ ይመስለኛል፡፡”

መልሷን ብጠባበቅም ቤስቲ ግን መልስ አልነበራትም፡፡

“ምን ማለት እንዳለብኝ አላውቅም፡፡” የተለመደው ግትርነቷ ይታይ ነበር፡፡ “እነዚህን ነገሮች አጥንቼ መልስ እሰጥሃለሁ፡፡ ወደ ቤተ ክርስቲያን መጥተህ እንድትጫወት ብጋብዝህ ትመጣለህ?”

“ምንም ችግር የለውም፡፡ ደስ ይለኛል፡፡ ነገር ግን መንጃ ፍቃድ የለኝም፡፡ አባቴ አብሮኝ ቢመጣ ችግር አለው?”

“ኧረ ችግር የለውም፡፡ የፈለከውን ያህል ሰው ማምጣት ትችላለህ፡፡ መረጃ የምታገኝበት ካርድ ይኸውልህ፡፡ የመምጣት ዕድል ስታገኝ የምትመጣበትን ቀን አስቀድመህ አሳውቀኝ፡፡” ቤስቲ መረጃ የያዘ ካርድ በፈገግታ አቀበለችኝ፡፡

ከፈገግታዋ በስተጀርባ ከዚህ ቀደም ያላየሁትን ነገር አስተዋልኩኝ፡፡ ደንግጣለች፡፡ የፈገግታዋን አፀፋ መለስኩላት፡፡

# የሰማይ ደጆችና የገሃነም ነበልባሎች

ወደ ቤተ ክርስቲያን በመጋበዜ በጣም ደስ ብሎኛል፡፡ ከዚያ ቀደም አንድ ቀን ወደ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መሄዴን አስታውሳለሁ፡፡ በላቲን የሚደረገው ቅዳሴ ለጆሮ ይጥማል፡፡ እውነቱን ለመናገር ለምን እንደተጋበዝኩኝ ግራ ገብቶኝ ነበር፡፡ ቤንና ቤተሰቡን ጨምሮ ካቶሊክ ያልነበሩ የተወሰኑ ጓደኞቼም በቦታው መገኘታቸውን አስታውሳለሁ፡፡ በመደዳ ቆመን እያለን ሰዎች ከቄሱ እጅ የሆነ ነገር ለመቀበል ወደ ፊት ሲሄዱ ተመለከትኩኝ፡፡ ምን ማድረግ እንዳለብኝ ስለማላውቅ አብሬያቸው ወደ ፊት ለመሄድ ተነሳሁ፡፡ የቤን እናት እጄን በመጎተት ወንበር ላይ አስቀመጠችኝ፡፡ ግራ ገብቶኝ ተመለከትኳት፡፡ ጭንቅላቷን በማወዛወዝ በፍፁም መሄድ እንደሌለብኝ ምልክት አሳየችኝ፡፡ እስከዚያች ደቂቃ ድረስ ፊቱን ቅጭም አድርጎ የነበረው ካህን ሳቅ አፍኖት ተመለከትኩኝ፡፡

የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን የተለየ መሆኑን ማንም ስላልነገረኝ ተመሳሳይ ነገር እንደሚኖር እጠብቅ ነበር፡፡ የኖርፎልክ ባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን ሕንፃ አዳራሽ መስሎ ታየኝ፡፡ የቤተ ክርስቲያን ሥርኣት የሚፈፀመው ሌላ ሕንፃ ውስጥ ሊሆን እንደሚችል በማሰብ ዙሪያ ገባውን ብማትር ምንም የሚታይ ነገር አልነበረም፡፡

ወደ መጨረሻ ጥግ ላይ ከአባቴ ጎን ነበር የተቀመጥኩት፡፡ ጫወታው ምን እንደሆነ ባናውቅም ግብዣውን በመቀበሌ አባቴ ደስተኛ ነበር፡፡ አለመቀበል ነውር መሆኑንና ከቤስቲ ጋር ውይይት ለመቀጠል ጥሩ በር እንደሆነ ተናግሮ ነበር፡፡ እምነቴን ለማካፈል

በመቻሌ ኩራት ተሰምቶት ነበር፡፡ በዚህ ቦታ የሚታየውን ድራማ መረዳት እንድችል ሊያግዘኝ ነበር አመጣጡ፡፡

የትዕይንቱ ርዕስ “የሰማይ ደጆችና የገሃነም ነበልባሎች” ይላል፡፡ የክርስትናን የደህንነት እሳቤ የሚገልፅ ነው፡፡ ክርስቲያኖች ይህንን መልዕክት “ወንጌል” በማለት እንደሚጠሩት ለመጀመርያ ጊዜ የሰማሁት በዚህ ድራማ ነበር፡፡ “ወንጌል” የሚለው ቃል ስለ ኢየሱስ የሚናገሩትን አራቱን የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ብቻ እንደሚያመለክት ነበር የማውቀው፡፡ ድራማው በቀጠለ ቁጥር መልዕክቱ እየጎላ ይሄድ ነበር፤ ኢየሱስን እንደ ጌታ ከተቀበላችሁ ወደ ሰማይ ትሄዳላችሁ አለበለዝያ ወደ ገሃነም ትወርዳላችሁ ይላል፡፡

እያንዳንዱ ክፍል የሚጠናቀቀው አንድ ሰው ወደ ሰማይ ወይም ወደ ገሃነም ሲሄድ በማሳየት ነበር፡፡ ይህ ደግሞ ኢየሱስን በመቀበል አለመቀበላቸው ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ የድራማው ምስል ጥርት ያለ አልነበረም፡፡ አንድ ሰው ወደ ሲኦል ሲወርድ ቀይና ቢጫ ቀለማት በክፍሉ ውስጥ ይበራሉ፡፡ ነጎድጓዳማ ድምፆች በማይክራፎን ያስተጋባሉ፡፡ ሰይጣንም  በመምጣት ኃጢአተኛውን ሰው እያሽካካ ከመድረክ ላይ ጎትቶ ይወስደዋል፡፡

አንድ ሰው ኢየሱስን ከተቀበለ ደግሞ  የሚያንፀባርቁ መላእክት በመምጣት ብርሃናማ ወደ ሆነ በር በደስታ ይመሩታል፡፡ በትዕይንቱ መጠናቀቂያ ላይ አንድ ሰው መኪና እየነዳ ተሳፋሪው ስለ ኢየሱስ ሲነግረው ይታያል፡፡ ሰውየው ብዙ መጥፎ ነገሮችን እንደሠራና በዘመኑ ሁሉ ከእግዚአብሔር ርቆ እንደኖረ ይናገራል፡፡ ተሳፋሪውም ኃጢአተኛ መሆኑንና ኢየሱስ እንደሚያስፈልገው ካሳመነው በኋላ የንስሐ ጸሎት አስጸለየው፡፡ ጸሎቱን ገና ከመጨረሱ አሳቃቂ አደጋ ደረሰ፡፡ መብራቱ ጭልምልም በማለቱ ሁለቱም ሰዎች መሞታቸው ታወቀ፡፡ መብራት ተመልሶ ሲበራ ደስ የሚል የሙዚቃ ድምፅ እየተሰማ ሾፌሩ ወደ ሰማይ ተወሰደ፡፡

ሆነ ተብሎ ታስቦ እንደሆን ባላውቅም ነገር ግን ሁላችንም ወደየ ቤቶቻችን ለመሄድ መኪናችን ውስጥ ከመግባታችን በፊት ድራማው በዚያ መልኩ ማለቁ ግሩም ሐሳብ

ነበር፡፡ እኔና አባቴ መኪናችን ውስጥ ገብተን ቀበቷችንን አጥብቀን ጉዞ እንደጀመርን አባዬ የውይይት ጥያቄ አቀረበ፡፡ "ነቢል ስለ ድራማው ምን ታስባለህ?"

"የማይረባ ሥራ ነው አባዬ፡፡ ሰዎችን ስሜታዊ በማድረግና በማስፈራራት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡"

"ልክ ነህ ካንተ ጋር እስማማለሁ ቤይታ ነገር ግን ያ ሁል ጊዜ መጥፎ ላይሆን ይችላል፡፡ ገሃነምንና የአላህን ቁጣ ልንፈራ ይገባናል፡፡"

ግራ ተጋብቼ "ስለዚህ ድራማው ጥሩ ነው ብለህ ታስባለህ ማለት ነው?" በማለት ጠየቅሁት፡፡

አባዬ ሳቅ አለ፡፡ "እንደርሱ ማለቴ አይደለም! ሰዎችን ለማስፈራራት ከመሞከራቸው ባሻገር የሆነ እውነታ አለ ማለቴ ነው፡፡"

"መልእክቱ ሙሉ በሙሉ ስህተት ነው" ሐሳቤን ለመሰብሰብ እየሞከርኩኝ መናገሬን ቀጠልኩ፡፡ "ሰዎች ዕድሜ ልካቸውን የፈለጉትን ነገር ካደረጉ በኋላ ጸሎት ብቻ በመጸለይ ወደ ገነት እንደሚሄዱ እያስተማሩ ናቸው፡፡"

"የሃይማኖት ዓላማ ጥሩ ሰዎችንና ጥሩ ማሕበረሰብ መፍጠር ነው፡፡ ሰዎች የፈለጉትን እንዲሠሩ ከተፈቀደ ኃጢአተኛ ባሕሪያቸውን ስለሚከተሉ ማሕበረሰብ ይፈራርሳል፡፡ ኃጢአት ለመሥራት የፍቃድ ወረቀት ተሰጥቷቸዋል፡፡ ሂትለር እራሱ ኢየሱስን በመቀበል ብቻ ወደ ገነት ይሄዳል ማለት ነው፡፡"

"ለዚያ ነው..." አባዬ ንግግሩን ከአፌ በመቀማት ቀጠለ

"ለዚያ ነው አሜሪካ አሁን ያለችበትን ሁኔታ የመሰለችው፡፡ ክርስቲያኖች ለተግባራቸው ተጠያቂነት እንደሌለባቸው ያስተምራሉ፡፡"

"ጥሩ፣ በጣም ጥሩ ነው ቤይታ፡፡ ስለዚህ ጓደኛህ ስለ ድራማው ከጠየቀችህ የተነጋገርነውን ማካፈልህን አትርሳ፡፡ ያንን ብቻ በመናገር መጨረስ የለብህም፡፡ ውሸትን በእውነት ማስወገድ ይኖርብሃል፡፡ ስለ ፍርድ እውነቱ ምንድነው?"

"አላህ በዚህች ምድር ላይ በምንመርጠው ምርጫ ላይ ተመስርቶ ነው በኛ የሚፈርደው፡፡ የምናደርገው ነገር ሁሉ በመላእክት ይመዘገባል፡፡ አንደኛው በቀኝ ትከሻችን ላይ ተቀምጦ ጥሩ ሥራችንን ሌላኛው ደግሞ በግራ ትከሻችን ላይ ተቀምጦ መጥፎ ሥራችንን ሁሉ ይመዘግባል፡፡ በአላህ ፊት ስንቆም ተግባራችን ሁሉ ከፍ ባለ ድምፅ ይነበባል፡፡ ቤተሰቦቻችን፣ ኢየሱስ፣ መሐመድ እንኳ ቢሆን ስለ እኛ ሊማልዱ አይችሉም፡፡ አላህ መልካምና ክፉ ሥራዎቻችንን በመመዝገብ መልካም ሥራችን በልጦ ከተገኘ ገነትን ይሸልመናል፡፡"

"ክርስቲያኖችስ ምን ይሆናሉ ቢሉ? ወደ ገነት መሄድ ይችላሉ?"

"አዎ፡፡ ክርስቲያኖች በአንድ አምላክ ቢያምኑና መልካም ሥራዎችን ቢሠሩ ወደ ገነት ሊገቡ ይችላሉ፡፡"[26]

ሙስሊሞችን እያከራከረ ስለሚገኝ የቁርአን ጥቅስ እየተናገርኩ ነበር፡፡ አንዳንድ ሙስሊሞች ይህ ጥቅስ እንዲህ በሚለው ሌላ የቁርአን ጥቅስ መሻሩን ይናገራሉ፡- "ከኢስላም ሌላ ሃይማኖትን የሚፈልግ ሰው ፈጽሞ ከርሱ ተቀባይ የለውም፡፡እርሱም በመጨረሻይቱ ዓለም ከከሳሪዎቹ ነው፡፡"[27] የኛ ጀማትን ጨምሮ ሌሎች ሙስሊሞች "ኢስላም" ተብሎ የተጠቀሰው የሃይማኖት ሥርኣቱ ሳይሆን *ሰላም* የሚለው የቃሉ ሰፋ ያለ ትርጉም እንደሆነ በመናገር ለማስታረቅ ይሞክራሉ፡፡

**በመሻሻር አስተምህሮ** ለሚያምን ሰው ሁለተኛው አተረጓጎም ደካማ እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡ ሱራ 2፡116 እና ሱራ 16፡101 አላህ የቀደሙትን የቁርአን ክፍሎች በኋለኞቹ እንደሚሽር በግልፅ ይናገራሉ፡፡ ሙስሊም

**የመሻሻር አስተምህሮ፡**የቁርአን ትምህርቶች ወይም ጥቅሶች ብዙ ጊዜ በኋለኞቹ እንደሚተኩ የሚያስተምህር አስተምህሮ ነው፡፡

ሊቃውንት “ሻሪና ተሻሪ” የሚል አስተምህሮ ያቀነባበሩ ሲሆን የተሻሩ ጥቅሶችን የሚያውቁበትን መስፈርት ለመወሰንና የጥቅሶቹን ታሪክ ለማወቅ ያገለግላል፡፡ በአንዳንድ ሙስሊሞች እምነት መሠረት እስከ አምስት መቶ የሚሆኑ የቁርአን ጥቅሶች በመሻራቸው ምክንያት አሁን አገልግሎት አይሰጡም፡፡ ሌሎች ደግሞ የተሻሩት  አምስት ብቻ መሆናቸውን ናገራሉ፡፡ በቁጥሩ ላይ ስምምነት ባይኖርም ነገር ግን አብዛኞቹ ሙስሊሞች የተሻሩ የቁርአን ጥቅሶች መኖራቸውን ያምናሉ፡፡ከዚህ ጋር የማይስማሙት ጥቂት ሙስሊሞች ሲሆኑ አሕመዲ ጀማት ከእነርሱ መካከል ይመደባሉ፡፡ በነዚህ ሙስሊሞች መሠረት የትኛውም የቁርአን ክፍል የሚሻር ከሆነ ዘላለማዊ የአላህ ቃል ሊሆን አይችልም፡፡ መሻራቸው ግልፅ የሆነውን የቁርአን ጥቅሶች ከላይ ባለው ዓይነት ደካማ ሥነ-ፍታቴ በመጠቀም ለማስታረቅ ይሞክራሉ፡፡ ይህ አመለካከት የማያስኬድበት ትልቁ ምክንያት ሐዲሳት ስለተሻሩ የቁርአን ክፍሎች በሚያወሱ ትርክቶች የተሞሉ መሆናቸው ነው፡፡እኔ በወቅቱ ስለ እነዚህ ጉዳዮች ምንም የማውቀው ነገር አልነበረኝም፡፡ ቢያንስ አንድ የቁርአን ጥቅስ በግልፅ እንደሚያመለክተው በአንድ አምላክ መኖር የሚያምኑ ሰዎች ይድናሉ፡፡ እኔም የኛ ጀማት ከሚያስተምረው ከዚህ የደህንነት ትምህርት ውጪ የማውቀው ነገር አልነበረኝም፡፡

“ቢሉ ክርስቲያኖች በስንት አማልክት ነው የሚያምኑት?”

“አንዳንዶች በአንድ ሌሎች ደግሞ በሦስት አማልክት፡፡”

“ልክ ነህ፣ ቁርአንም ደግሞ ‹ሦስት› ማለታቸውን ቢያቆሙ ለእነርሱ መልካም እንደሆነ ይናገራል፡፡[28] ለዚህ ነው ከጓደኞችህ ጋር እንደዚህ ዓይነት ውይይት ማድረግህ የሚያስደስተኝ፡፡ ቢያንስ አንድ አምላክ ብቻ መኖሩን መስማት ይኖርባቸዋል፡፡ ወደ እስልምናና ወደ አሕመዲያት ብታመጣቸው ደግሞ የበለጠ መልካም ይሆናል፡፡”

ስለ ደህንነት ያደረግነውን ውይይት ከመቋጨታን በፊት ፈጠን ብሎ አንድ ነገር አከለ፡- “ነገር ግን ከዚህች ልጅ ጋር ብዙ ጊዜ ማሳለፍ የለብህም! ሴቶች በተለይ በዚህ ዕድሜ ላንተ አደገኞች ናቸው፡፡ አንተ ልክ እንደ እሳት ስትሆን እነርሱ ደግሞ ልክ እንደ ነዳጅ

ናቸው፡፡ አንዳችሁ ስለ ሌላችሁ ምንም ስሜት ባይኖራችሁም ቅርርባችሁ በቀጠለ ቁጥር መንደድ ትጀምራላችሁ፡፡ ተፈጥሯችሁ እንደዚህ በመሆኑ ምንም ማድረግ አትችሉም፡፡”

“እሺ አባ፣ በቃ! ገብቶኛል፡፡ ስለ ሌላ ነገር እናውራ?”

እማና አባ “ስለ እሳትና ስለ ነዳጅ” ደጋግመው ያወሩኛል፡፡ ጊዜው ሲደርስ ደግሞ እንደ ቤተሰብ ተሰብስበን ማንን ማግባት እንዳለብኝ እንወያያለን፡፡ ያሰብኳት ሴት ካለች እነግራቸውና ወላጆቼ ያናግሯታል፤ ጋብቻም ይመቻችልኛል፡፡ ካልሆነ ደግሞ የምትስማማኝን ሴት በመፈለግ ያጋቡኛል፡፡ በራሴ ፍላጎት ምዕራባዊት ሴት ይቅርና ማንንም ማጨት አልችልም፡፡ ያንን ማድረግ ከባሕላችን ማፈንገጥ ነው፡፡

ምዕራፍ አሥራ ስድስት

# አንጡራ ትውፊት

ትውፊት የእስልምና ውጭያዊ ቅርፅ ሲሆን በውስጠኛው የእስልምና አስተምህሮ የተቃኘ ነው፡፡ በእስልምና የሕይወት ዘይቤ ውስጥ ጠልቀን ስንገባ በውስጣችን የሚሰርፅ ነገር ነው፡፡ እያንዳንዱ ቀን በትውፊት የተንቆጠቆጠ ነው፡፡ ሰላትን በቀን አምስት ጊዜ ለመስገድ፣ ብዙ ዝርዝር ዱኣዎችን ለመጸለይና የትጥበትን ሥርኣትን በጥንቃቄ ለመፈፀም እተጋ ነበር፡፡ የመሐመድንም ምሳሌነት ለመከተል መመርያዎችን ለማግኘት አጠና ነበር፡፡ ማንን ማግባት እንዳለባቸው ለመጸለይ፣ የጢማቸውን ርዝመት ለመወሰንም ሆነ ወርቅ ለማድረግ ትውፊቶችን የሚከተሉ እንደኔ ዓይነት ከአንድ ቢልዮን በላይ ሙስሊሞች አሉ፡፡

ነገር ግን እነዚህ ትውፊቶች ከቁርአን የተገኙ አይደሉም፡፡ በሐዲስ ውስጥ ነው የሚገኙት፡፡ ከጋብቻ ደንቦች ጀምሮ እስከ ጦርነት ድረስ፤ ከንግድ ሥርኣት ጀምሮ እስከ አለባበስ ድረስ የሸሪኣ ሕግጋት እና የእስልምና የሕይወት ዘይቤዎች ሁሉ የተቀዱት ከሐዲስ ነው፡፡

በእስልምናው ዓለም ውስጥ የሐዲስ አስፈላጊነት ተጋኗል ለማለት አያስደፍርም፡፡ ባጂና እኔ ዕድሜያችን ከፍ እያለ ሲመጣ እማና አባ ሐዲስን መማር እንደሚያስፈልገን ወሰኑ፡፡ ብዙ ጊዜ ከሐዲስ ስብስቦች ካነበቡ በኋላ አረብኛውን በመሸምደድ ትርጉሙን እንድንረዳ በጥብቅ ያሳስቡን ነበር፡፡ ለመጀመርያ ጊዜ ሐዲስን እንድንሸመድድ ማሳሰብያ የተሰጠንን ቀን አስታውሳለሁ፡፡ የመግሪብ ጸሎት ጸልየን አብቅተን ገና ከምንጣፉ ላይ አልወረድንም ነበር፡፡

"ቤይቲ፣ ቤይታ፣ ይህችን አጭር ሐዲስ እንድትሸመድዱት እንፈልጋለን፡፡ ሐዝራት ዑመር እንደዘገበው መሐመድ እንዲህ ብለዋል፡- ‹ምግባር በልብ ፍላጎት ይመዘናል›፡፡"[29]

አረብኛውን ለተወሰነ ጊዜ ከደጋገምነው በኋላ መሸምደድ በመቻላችን እማና አባ ደስ አላቸው፡፡ ጥያቄ ይኖረን እንደሆነ ጠየቁን፡፡

የተወሰኑ ጥያቄዎች ነበሩኝ፡፡ "አባ ይህ ሐዲስ ከየትኛው መጽሐፍ ነው የመጣው?"

"ይህኛው የመጣው **ከሳሂህ ቡኻሪ** ነው፡፡ ስለ ሳሂህ ቡኻሪ ልትነግረን ትችላለህ?"

**ሳሂህ ቡኻሪ፡**ቀደምት የሐዲስ ስብስብ ሲሆን ሱኒ ሙስሊሞች በጣም ተዓማኒ አድርገው ይቆጥሩታል፡፡

"በኢማም ቡኻሪ የተሰበሰበ ከሁሉ በላይ ተዓማኒ የሆነ ሐዲስ ነው፡፡ ሐዲሳት የተሰበሰቡት ከመሐመድ ሞት በኋላ ብዙ ዓመታትን በመዘግየት ነው፡፡ ብዙ የሐሰት ሐዲሳት ስለተፈጠሩ የትኞቹ ትክክል እንደሆኑ ለመወሰን አስቸጋሪ ነበር፡፡ ኢማም ቡኻሪ ወደ አምስት መቶ ሺህ የሚሆኑ ሐዲሳትን ከሰበሰበ በኋላ በጣም ተዓማኒ የሆኑትን አምስት ሺህ ሐዲሳት መረጠ፡፡"

"እንዴት ነበር የሰበሰበው?" እማ ጠየቀች፡፡

"ኢማም ቡኻሪ አንድን ሐዲስ ሲሰማ ዘጋቢው ታማኝ ሰው መሆን አለመሆኑን ያጠና ነበር፡፡ ጥሩ ተሰሚነት ያለው ሰው ካልሆነ፣ ከዚህ ቀደም ጥፋት ሰርቶ የሚያውቅ ከሆነ ወይንም ደግሞ እንስሳትን እንኳ በድሎ የሚያውቅ ሰው ከሆነ ኢማም ቡኻሪ ሐዲሱን ይጥለው ነበር፡፡ ሰውየው ታማኝ ሆኖ ከተገኘ ከማን እንደሰማ፣ ለእርሱ የነገረው ሰው ደግሞ ከማን እንደሰማ፣ ለዚያኛውም ሰው ማን እንደነገረው በመጠየቅ እስከ መሐመድ ድረስ ያለውን የዘገባ ሰንሰለት ያጠና ነበር፡፡ በዘገባ ሰንሰለቱ ውስጥ የሚገኝ እያንዳንዱ ዘጋቢ ምን ያህል ታማኝ እንደሆነ ካጠና በኋላ መስፈርቱን ካሟላ ኢማም ቡኻሪ ሐዲሱን ይመዘግበው ነበር፡፡"

የዘገባ ሰንሰለቱ **ኢስናድ** በመባል የሚታወቅ ሲሆን ለሙስሊም ሊቃውንት እንጅግ በጣም ወሳኝ ነው፡፡ እስልምና በሥልጣን ተዋረድ በሚያምን ማህበረሰብ ውስጥ የተፈጠረ ሃይማኖት ነው፡፡ "ይህ ሐዲስ ተዓማኒ ነውን?" በማለት ሲጠይቁ የአስተላላፊዎቹ ሥልጣን ምን ያህል እንደሆነ ይገለፅላቸዋል፡፡ ያለ ኢስናድ ሐዲሱ እርባና ቢስ እንደሆነ ይቆጠራል፡፡ ሲራ ኢስናድ ስለማይመዘግብ ሙስሊሞች ለሲራ የሚሰጡት ቦታ ከሐዲስ ያነሰ ነው፡፡

እማ ቀጠለች፡፡ "በጣም ጥሩ፡፡ ቤይቲ ሁለተኛው በጣም ተዓማኒ መጽሐፍ የትኛው ነው?"

"አላውቅም እማዬ፡፡" ባጂ በወቅቱ ዕድሜዋ 18 ሲሆን ኮሌጅ ገብታለች፡፡ እነዚህን ዝርዝር ጥያቄዎች እንደ በፊቱ ትኩረት የማትሰጣቸው ቢሆንም እማ ግን በቀላሉ ልትለቃት አልፈለገችም፡፡

"ታውቂያለሽ እንጂ፡፡ ቻሎ፣ ይህንን ጥያቄ መመለስ ከቻልሽ መልሱን አግኝተሻል ማለት ነው፡፡ ከሳሂህ ቡኻሪ ቀጥሎ የሚጠቀሰው የትኛው ሐዲስ ነው?"

"ሳሂህ ሙስሊም ይሆን?"

"ሻባሽ፡፡ ነቢል ሌላ የምታውቀው አለህ?"

"ሱናን አቡ ዳውድ የሚባል መኖሩንና ተዓማኒ ተደርገው የሚቆጠሩት ሐዲሳት ስድስት መሆናቸውን አውቃለሁ፡፡ የተቀሩት ተዓማኒ የሆኑና ያልሆኑ ሐዲሳት ድብልቅ ናቸው፡፡ ስድስቱ **ሳሂህ ሲታ** በመባል የሚታወቁ ሲሆን የመጀመርያዎቹ ሦስቱ ሳሂህ ቡኻሪ፣ ሳሂህ ሙስሊም እና ሱናን አቡ ዳውድ ናቸው፡፡"

> **ኢስናድ፡** የሐዲስ ዘገባ ሰንሰለት
> **ሳሂህ ሲታ፡**የሱኒ ሙስሊሞች በጣም ተዓማኒ አድርገው የሚቆጥሯቸው ስድስቱ ሐዲሳት

አባ ዝርዝሩን ቀጠለ “የተቀሩት ሦስቱ ሱናን ቲርሚዚ፣ ሱናን ኢብን ማጃህ እና ሱናን ናሳዒ ናቸው፡፡[30] እነዚህ ምርጥ የሐዲሳት መጻሕፍት ሲሆኑ ሳሂህ ቡኻሪና ሳሂህ ሙስሊም የበለጠ ተዓማኒነት ያላቸው ናቸው፡፡”

እማ ፈጠን ብላ አከለች “እነዚህ በጣም ትክክል የሆኑት ራሳቸው የአላህ ቃላት ሳይሆኑ የመሐመድ ﷺ ንግግሮች ናቸው፡፡ ሐዲሳትን ከቁርአን ጋር በእኩል ደረጃ ላይ ማስቀመጥ የለብንም፡፡”

የበለጠ ግልፅ እንዲሆንኝ ጥያቄ ጠየኩኝ፡፡ “ነገር ግን መሐመድ ﷺ ከተናገረ መታዘዝ የለብንም?”

አባዬ ጣልቃ ገባ፣ “አለብን እንጂ! ነገር ግን መሐመድ ﷺ ፈጣሪ አይደለም፡፡ ቁርአን በዓለም ላይ የሚገኝ ያልተበረዘ ፍፁም የሆነ ብቸኛ መጽሐፍ ነው፡፡ የሐዲስ መጻሕፍት እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ የሰው ሥራዎች ናቸው፡፡ መለኮታዊ እውነት በውስጣቸው ቢኖርም ነገር ግን ሊበረዙ ስለሚችሉ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልገናል፡፡ ከሌሎች ምንጮች ያገኘናቸውን መረጃዎች ከቁርአን እውነት ጋር ልናስተያይ ይገባል፡፡ ቻሎ፣ ለዛሬ ይህ ይበቃናል፡፡ ዛሬ የተማራችሁትን ሐዲስ እንዳትረሱ፡፡ ነገ በቃላችሁ እንድትደግሙት እንጠይቃችኋለን!”

የሐዲሳትን ይዘት ከማወቅ ይልቅ ስለ ታሪካቸውና ሙስሊም ሊቃውንት የሚያጠኑባቸውን መንገዶች ማወቅ ይበልጥ ያስደስተኝ ነበር፡፡ ተዓማኒነት ያላቸውን ሐዲሳት ተዓማኒነት ከሌላቸው እንዴት መለየት እንደምችል የመወቅ ጉጉት ነበረኝ፡፡ እማና አባ ሐዲሳትን የመመደቢያ መንገዶችን እንዲያስረዱኝ ጠይቁ በዚህ ጉዳይ ላይ ያላቸው እውቀት አናሳ መሆኑን ተገንዝቤያለሁ፡፡ ከዚያ በላይ ለማወቅ የሚያስችሉኝን የትኞቹን መጻሕፍ መግዛት እንዳለብን እንዲያሳውቁኝ ዕውቀት ያላቸውን ሰዎች ለመጠየቅ ቀጣዩን የጀማት ስብሰባ መጠበቅ ነበረብኝ፡፡

እማና አባ የጀማት ስብሰባ ለመካፈል ወደ እንግሊዝ አገር ተጉዘው ክረምቱን የማሳለፍ ዕቅድ ነበራቸው፡፡ እዚያ እያለን የተወሰነ ጥናት ለማድረግ ወሰንኩኝ፡፡ በዕቅዴ ውስጥ ያልነበረው አንድ ነገር ቢኖር ፈጣሪዬን በግል የማወቅ ጉዳይ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ሕይወቴን እስከ ወዲያኛው የለወጠ ተዓምራት ሊያደርግ በደጅ ነበር፡፡

# በሰማይ ውስጥ የሚታዩ ምልክቶች

ከስምንት ዓመታት በፊት ወደ ኮኔክቲከት ከተንቀሳቀስን ወዲህ እንግሊዝን ስጎበኝ የመጀመርያዬ ነበር፡፡ ደስታዬ ወደር አልነበረውም፡፡ ገና የሂዝሮው አየር ማረፍያ ከመድረሳችን የምወዳቸውን የእንግሊዝ ጭማቂና ብስኩቶች ገዛሁ፡፡

ከዘጠኝ ዓመታት በፊት ኢዮቤልዩ ለማክበር ወደተሰበሰብንባት ወደ ቲልፎርድ ገጠራማ አካባቢ ተጓዝን፡፡ የእንግሊዝ ትንንሽ ከተሞችን እያለፍን ስንሄድ የድሮ ትዝታዎቼ አንድ በአንድ መምጣት ጀመሩ፡፡ ጠባቦቹ መንገዶች፣ የተነባበሩት ሕንፃዎችና ትንንሾቹ መኪኖች ጣፋጭ ትዝታዎቼን እየጎተቱ ከፊቴ ማስቀመጥ ተያይዘዋል፡፡

ይህ የጀማት ስብሰባ ጀልሳ ይሰኛል፡፡  ቤተሰባችን የአሜሪካን ጀልሳ በየዓመቱ በዋሽንግተን ዲሲ ይካፈላል፡፡ የካናዳንም ጀልሳ እንዲሁ እንካፈላለን፡፡ ነገር ግን የእንግሊዙ ጀልሳ የተለየ ነው፡፡ የኛ ጀማት መሪ የሚኖረው እዚህ ሲሆን እርሱ ባለበት መገኘት ልዩ ስሜት ይሰጣል፡፡ ከእርሱ የተነሳ በአሥር ሺህዎች የሚቆጠሩ አሕመዲዎች የእንግሊዙን ጀልሳ ይካፈላሉ፡፡

እርሱን የማየት ጉጉቴ እንደተጠበቀ ሆኖ የእስኮትላንድ ጓደኞቼ የሆኑትን የማሊክ ቤተሰቦች እስካገኝ ድረስ በጣም ቸኩዬ ነበር፡፡ ሰባተኛ ክፍል እያለሁ ከትንሹ ልጅ ደብዳቤ ደርሶኝ ነበር፡፡ ከዚያ ውጪ ከእነርሱ ሰምቼ አላውቅም ነበር፡፡ በወቅቱ ኢ-ሜል መጠቀም ብዙም ያልተለመደ ሲሆን ዓለም አቀፍ የስልክ ጥሪ ማድረግ ደግሞ በጣም ውድ ነው፡፡

የጀልሳው ቦታ ስደርስ ጓደኞቼ እዚያ መገኘት አለመገኘታቸውን እርግጠኛ ልሆን እንደማልችል ገባኝ፡፡ ስብሰባው በጣም ወሳኝ ቢሆንም ነገር ግን እዚያ እንዳይገኙ ሊያደርጉ የሚችሉ ብዙ ምክንያች ነበሩ፡፡ ጀልሳው ውስጥ ወዲያ ወዲህ በመሄድ እነርሱን መፈለግም አስቸጋሪ ነበር፡፡ ብዙ ሕዝብ ከመሰብሰቡም በላይ ባለፉት ሰባት ዓመታት አድገን የቀድሞ መልካችን ተለውጧል፡፡ ባያቸው እንኳ ላውቃቸው መቻሌን እርግጠኛ አልነበርኩም፡፡ ላገኛቸው ብፈልግም ነገር ግን ከየት መጀመርእንዳለብኝ ግራ ገብቶኝ ነበር፡፡

ስለዚህ ወደ ፈጣሪዬ ፊቴን መለስኩኝ፡፡

በጣም ልጅ ሳለሁ ጀምሮ እናቴ በችግሬ ሰዓት እንድጸልይ አስተምራኛለች፡፡ ነገር ግን ሰዎችን ለማግኘት ምን ዓይነት ዱኣ ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም ነበር፡፡ ዕቃ ሲጠፋብን የሚጸለየውን ዱኣ አውቃለሁ፡፡ የአንድን ሰው ሞት ስንሰማ ተመሳሳይ ጸሎት ስለምንጸልይ ጓደኞቼን እያሰብኩኝ ያንን ጸሎት መጸለይ እንደሌለብኝ ተሰማኝ፡፡ ስለዚህ ራሴን ዝቅ አድርጌ ዓይኖቼን ገርበብ በማድረግ የግሌን ጸሎት ጸለይኩኝ፡፡

“አምላኬ ሆይ እባክህን ጓደኞቼን ማግኘት እንድችል እርዳኝ?” ምንም የምጨምረው ነገር ስላልነበረኝ ይህንኑ ብዬ ጨረስኩኝ፡፡

ዓይኖቼን ስከፍት የማይታመን ነገር ተመለከትኩኝ፡፡ ወርቃማና ብርማ ቀለሞች አየር ላይ በብሩሽ የተቀቡ ይመስል ከፊት ለፊቴ ታዩኝ፡፡ ወደ አንድ አቅጣጫ እየመሩኝ መንቀሳቀስ ጀመሩ፡፡

ከድንጋጤ የተነሳ የተናገርኳቸውን ቃላት እስከ ዛሬ ድረስ አልረሳቸውም፡ “ይሄ ነገር ቀልድ እንዳይሆን ብቻ፡፡ ተከትያቸው መሄድ ይኖርብኝ ይሆን?”

ለራሴ ልናገር ወይም ለፈጣሪዬ እርግጠኛ አልነበርኩም፡፡ በጣም እርግጠኛ ሆኜ የማውቀው ነገር ቢኖር ቀለማቱን ከኔ ውጪ ሌላ ሰው ሊያያቸው እንደማይችል ነው፡፡ ሰማይ ላይ ያሉ ቢመስሉም ሰማይ ላይ አልነበሩም፡፡ አንድ ማይል አይርቁም፡፡ አንድ

ጫማም የቀረቡ አልነበሩም፡፡ በነዚህ ርቀቶች መካከልም አልነበሩም፡፡ ብቻ ይታዩኛል፤ ደግሞም እየመሩኝ ነበር፡፡

ጀልሳው በጣም የተጨናነቀ ነበር፡፡ ንግግር እየተደረገ ስላልነበረ ሁሉም ሰው ውጪ ላይ ተኮልኩሏል፡፡ ልክ የፓኪስታን ባዛር ውስጥ እንዳለ ሰው በሰዎች መካከል እየተሽሎከሎኩኝ ቀለማቱን መከተል ጀመርኩኝ፡፡

ቀለማቱ ከዘጠኝ ዓመታት በፊት ባጀችን ለማየት ሲሄድ በነበረበት የገበያ ቦታ ላይ ቆሙ፡፡ በዚህ ጊዜ እንደ ሽማግሌው ጉዞዬን የገታ ሰው አልነበረም፡፡ በዚህ ፋንታ ቀለማቱ ወደ ታች በመውረድ የመልበሻ ድንኳን አናት ላይ ተረጭተው ጠፉ፡፡ ቀስ ብዬ ተጠግቼ ስመለከት ሁለት ሰዎች እያወጉ ኮፍያዎችን ለማጥለቅ ሲሞክሩ ተመለከትኩኝ፡፡ ትንሽ ድንግርግር ቢለኝም ነገር ግን አወኳቸው፡፡ ሁለቱ የማሊክ ተላላቅ ልጆች ነበሩ፡፡

ሮጬ ሄጄ እጃቸውን ያዝኳቸው፡፡ ማንነቴን ሲያውቁ ተቃቅፈን በደስታ ፈነደቅን፡፡ በርዝመቴ በመደነቅ “ምን በልተህ ነው እንደዚህ የተንቀዋለልከው!” እያሉ ይቀልዱ ጀመር፡፡ በጀልሳው ውስጥ ወዲያና ወዲህ እየሄድን ከዚያ ቀደም በግላስጎው ከማውቃቸው ሰዎች ጋር ከእንደገና አስተዋወቁኝ፡፡ ደስታችን ወደር አልነበረውም፡፡ በሰማይ ውስጥ ያየኋቸው ቀለማት ለጊዜውም ቢሆን ተረሱ፡፡

በዚያች ምሽት በአልጋዬ ላይ ጋደም ብዬ ውሎዬን ማሰብ ስጀምር ወርቃማና ብርማ ቀለማቱ ትዝ አሉኝ፡፡ ለኔ የፈጣሪን መኖር የሚያረጋግጡ ምልክቶች ነበሩ፡፡

የፈጣሪን መኖር ከዚያ ቀደምም ቢሆን አምን ነበር፡፡ የተመለሱ ጸሎቶችን፣ ትንቢታዊ ህልሞችንና የፈጣሪን ሐልዎት የሚያረጋግጡ ምክንያታዊ ሙግቶችን አውቃለሁ፡፡ ነገር ግን ደግሞ ሁል ጊዜ ትንሽም ቢሆን ጥርጣሬ አይጠፋም፡፡ ተመለሱ የተባሉት ጸሎቶች አጋጣሚዎች ብቻ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ሕልሞችም ደግሞ ከእውነታ ጋር እንዲመሳሰሉ በማሰብ ተጋነው ሊነገሩ ይችላሉ፡፡ አመክንዮአዊ ሙግቶችም ድክመት ሊኖርባቸው ይችላል፡፡ ፈጣሪ ስለመኖሩ 99 ከመቶ እርግጠኛ ነበርኩኝ ነገር ግን የጥርጣሬ ጥላ መቼም ቢሆን አይጠፋም፡፡

አሁን ግን መቶ በመቶ እርግጠኛ ሆኛለሁ፡፡ ዛሬ የተደረገውን ነገር በሌላ በምን መንገድ ላባራራ እችላለሁ? ጓደኞቼ የት ጋ ይሁኑ የማውቀው ነገር አልነበረኝ፡ ነግር ግን ስጸልይ ልዕለ ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ እነርሱ ወዳሉበት ቦታ ተመራሁ፡፡

አማራጭ ትንታኔዎችን ማሰብ ጀመርኩኝ፡፡ ምናልባት ቀለማቱን ራሴ በአእምሮዬ ውስጥ ፈጥሬ ይሆን? አይ ያ አያስኬድም፡፡ ጓደኞቼ ወደ ነበሩበት ቦታ እኮ በቀጥታ ነው የሄድኩት፡፡ ምናልባት ጓደኞቼ ያሉበትን ቦታ በደመነፍስ አውቄ ይሆን? በፍፁመ ያ ሊሆን የማይችል ነው፡፡ እንኳንስ በገበያ ቦታው ይቅርና በጀልሳው ቦታ ስለመኖራቸው እንኳ እርግጠኛ አልነበርኩም፡፡ ምናልባት በስኮትላንድ በነበርኩበት ጊዜ ከጓደኞቼ ጋር ጥልቅ የሆነ የስሜት መወራረስ ስላዳበርኩኝ ይሆን? ይህ ጥልቅ የስሜት ቁርኝት ደግሞ እስከዛሬ ድረስ ተሸሽጎ ቆይቶ ልክ ሳስታውሳቸው የተመለከትኩትን ምስል በመፍጠር እነርሱ ወዳሉበት ስቦኝ ይሆን? እውነቱን ለመናገር ስለ ክስተቱ ያገኘሁት ብቸኛ ተፈጥሯዊ ትንታኔ ቢኖር ይህ ነበር፤ ነገር ግን እርሱም ቢሆን ከተፈጥሯዊ ድንበር የወጣና የማይመስል ነው፡፡

"ሊሆን አይችልም" አልኩኝ ለራሴ፡፡ "ሌላ አማራጭ የለም፡፡ ፈጣሪ እውን ነው፡፡ እርሱ ጸሎቴን ይሰማል፡፡ ጓደኞቼ ያሉበትን ቦታ እንዲያሳውቀኝ የጠየቅሁትን ቀላል ጥያቄ እንኳ ሰምቶ የሚመልስ አምላክ ነው፡፡ በዚያን ዕለት ፈጣሪ እውን መሆኑን ከማመን በዘለለ እንደሚጠነቀቅልኝም ጭምር ለማወቅ ችያለሁ፡፡

ፐሪነሰስ ላን ትምህርት ቤት ስገባ ከተማርኳቸው ትምህርቶች መካከል አንዱ የዕውቀት ትወራ (ቲኦኬ) ይሰኛል፡፡ ያንን ትምህርት ለመማር ደግሞ ለኔ ትክክለኛ ጊዜ ያ ነበር፡፡ በማስከተል ለምወስዳቸው የፍልስፍናና የኢፒስቲሞሎጂ ትምህርቶች እንደ ቅድመ ሁኔታ የተቀመጠ ነበር፡፡ የመማርያ መጽሐፋችን ‹መለኪያው ሰው ነው› የሚል ርዕስ ነበረው፡፡ ለመጀመርያ ጊዜ ከተወያየንባቸው ርዕሶች መካከል አንዱ "ፈጣሪ መኖሩን

እንዴት ነው የምናውቀው?” የሚል ነበር፡፡ ውይይቱ ጥልቅና በአምላክ መኖር የሚያምኑ የብዙ ተማሪዎችን እምነት ያናወጠ ነበር፡፡

ውይይቱ ያተኮረው በቋሚ ሙግቶች ላይ ቢሆንም ግላዊ ዕውቀቶች የበለጠ ኃይል እንዳላቸው ተገንዝቤያለሁ፡፡ ቀለማቱን በሰማይ ውስጥ ማየቴንና ወደ ጓደኞቼ እንደመሩኝ ብናገር ማንም እንደማይቀበለኝ አውቃለሁ፡፡ ያንን ማድረግ ደግሞ አስፈላጊ አልነበረም፡፡ ምልክቱ ለግሌ የተሰጠ እንጂ ለሌላ ሰው አይደለም፡፡ አምላክ መኖሩን 99 ከመቶ ከማመን መቶ በመቶ ወደ ማመን አምጥቶኛል፡፡

ከአራት ዓመታት በኋላ የኔ ዓለም መፈራረስ ሲጀምር ያቺ አንድ ከመቶ የጎላ ሚና መጫወት ችላለች፡፡

ምዕራፍ አሥራ ስምንት

# ክብርና ሥልጣን

ቲኦኬ ከምርጥ ጓደኛዬ ከዴቪድ ጋር ከተማርኳቸው ትምህርቶች መካከል አንዱ ነበር፡፡ ቅርርባችን እያደገ ሄዶ የትምህርት ደረጃችን ሲጨምር መለያየት እስከማንችል ድረስ ደርሰናል፡፡ ከሰባቱ ትምህርቶቻችን መካከል ስድስቱን በጋራ የምንማር ሲሆን የኅበዝ ተማሪዎች ቡድን መሪዎች ሆነን የምርምር ቡድን ተቀላቅለን ነበር፡፡ ዴቪድና እኔ የመጀመርያ ዓመት ተማሪዎች ውድድርን ከእኛ ግዛት በአምስተኛነት ደረጃ በማጠናቀቅ ከፍተኛ አድናቆት አትርፈን ነበር፡፡ ሁለታችንም ገና ጀማሪዎች እንደመሆናችን መጠን ያንን ደረጃ ማግኘት የማይታሰብ ነበር፡፡ ሁለተኛ ዓመት ስንሆን ደግሞ ከግዛቱ አንደኛ በመውጣት ተሸልመናል፡፡

ዴቪድና እኔ ስለ ሃይማኖትና ስለ እግዚአብሔር መኖር የምንወያየው አልፎ አልፎ ብቻ ነበር፡፡ ብዙ ጊዜ የማይገጥሙ አመለካከቶችን የምናራምድ ሲሆን አስተዳደጋችን ተፅዕኖ አሳድሮብናል፡፡ እርሱ የፈጣሪን መኖር በጥርጣሬ ነበር የሚያየው፡፡ እኔ ደግሞ እንደ ሙስሊም ነው የማስበው፡፡ በቲኦኬ ክፍለ ጊዜ የነበረው ውይይት የእርሱን ጥርጣሬ ከፍ ያደረገ ሲሆን የኔን እምነት ግን ቅንጣት ታክል አልቀነሰም ነበር፡፡

ቤተሰቦቼ እምነቴን እንድመረምር ሲነግሩኝ ያስተማሩኝን ነገሮች እንዴት አድርጌ ከጥቃት መከላከል እንደምችል እንዳስብ ነበር ከእኔ የሚጠብቁት፡፡ በቲኦኬ ክፍለ ጊዜም ተመሳሳይ ነገር ነው የምንማረው፤ ማለትም እምነታችንን እንድንመረምር ነው የምንማረው ነገር ግን በተግባር ፍፁም የዚያ ተቃራኒ ነው፡፡ እምነታችንን በጥልቀት

በመመርመር እንገዳደረዋለን፣ ደካማ ጎኑን እናያለን፣ ከዘመኑ ጋር መሄድ አለመሄዱን እንፈትሻለን፡፡ አንዳንድ ተማሪዎች እንዲያውም እምነታቸውን እስከመለወጥ ደርሰዋል፡፡

ይህ በምዕራብና በምስራቅ መካከል የሚገኝ ልዩነት ሙስሊም ስደተኞችን ከልጆቻቸው ከሚለዩ ነገሮች መካከል አንዱ ነው፡፡ እስላማዊው ባሕል ከፍተኛ ደረጃ ላይ ያሉትን ሰዎች ሥልጣን የሚያጎናፅፍ ሲሆን በምዕራብ ባሕል ደግሞ ባለ ሥልጣኑ ምክንያታዊነት ነው፡፡ እነዚህ ሁለቱ የሥልጣን ባለቤቶች የአጠቃላዩን ማሕበረሰብ የሥነ ምግባር መለኪያ የሚወስኑ ናቸው፡፡

ሥልጣን ከምክንያታዊነት ይልቅ በሰዎች ደረጃ ላይ የተመሠረተ ከሆነ የሰዎችን የመሪነት ሚና መገዳደር አደጋ ያስከትላል ምክንያቱም ሥርኣቱን የማስቆጣት ሁኔታ ይኖረዋልና፡፡ አመፅ ቅጣትን ያስከትላል፤ መታዘዝ ደግሞ ሽልማትን ያስገኛል፡፡ ትክክለኛ የሆኑና ያልሆኑ ተግባራት በግል ደረጃ ሳይሆን በማሕበረሰብ ደረጃ ነው የሚወሰኑት፡፡ የአንድ ሰው ስብዕና የሚወሰነው ማሕበረሰቡ ከእርሱ የሚጠብቀውን በማሟላት አለማሟቱ እንጂ በግል ትክክልና ትክክል ያልሆነውን ለይቶ በመፈፀሙ አይደለም፡፡

ከዚህ የተነሳ በየበላይነት ላይ የተመሠረተ ሥልጣን ትክክልና ስህተትን በክብርና በውርደት ላይ ተመስርቶ የሚወስን ማሕበረሰብ ያፈራል፡፡

በሌላ ወገን ደግሞ ሥልጣን በምክንያታዊነት ላይ የተመሠረተ ከሆነ ጥያቄዎች የሥልጣንን መሠረት ስለሚያጠናክሩ በደስታ ይስተናገዳሉ፡፡ እያንዳንዱ ሰው የራሱን ተግባር በጥልቀት እንዲያጤን ይጠበቅበታል፡፡ ትክክል የሆኑና ያልሆኑ ተግባራት በግል ይመዘናሉ፡፡ የአንድ ሰው ስብዕና የሚወሰነው ሰውየው ትክክል እንደሆነ የሚያውቀውን ነገር በማድረግ አለማድረጉ ነው፡፡

ምክንታዊ የሆነ ሥልጣን ትክክልና ትክክል ያልሆነውን ነገር በንፅህናና በጥፋተኝነት ላይ ይመሰርታል፡፡

ምዕራባውያን ምስራቃውያንን የማይረዱበት ትልቁ ምክንያት በንፅህናና በጥፋተኝነት ላይ በተመሠረተው በራሳቸው ንፅረተ ዓለም መነፅር በክብርና በውርደት ላይ የተመሠረተውን የምስራቁን ንፅረተ ዓለም ለማየት መሞከራቸው ነው፡፡ በእርግጥ ይህ ጉዳይ እጅግ ውስብስብ ነው፡፡ የሁለቱም አመለካከቶች ቅንጣቶች በምዕራቡም በምስራቁም አንፅሮታት ውስጥ የሚገኙ ቢሆኑም ክብርና ውርደት ግን የምስራቁን አመለካከት የሚቃኝ ማዕከላዊ ጉዳይ ነው፡፡ ምዕራባውያን ደግሞ ይህንን ለመረዳት በእጅጉ ይቸገራሉ፡፡

ለብዙ ምዕራባውያን አስደንጋጭ የሆኑት በብዙ ሙስሊም አገራት የሚታዩት እንደ ክብር ግድያዎች፣ የስድስት ዓመትና ከዚያ የሚያንሱ ህፃናትን መዳር እና ደም መፋሰስ የዚያ ውጤቶች ናቸው፡፡ በነዚህ አገራት የሚገኘው መሕበረሰባዊ አደረጃጀት እነዚህን ተግባራት ተቀባይነት እንዲኖራቸው ከማድረግ አልፎ ተመራጭ ያደርጋቸዋል፡፡ ምንም ያህል ምክንያታዊነትም ሆነ የውጪ ተፅዕኖ እነዚህን ልማዶች ሊያስወግድ አይችልም፡፡ ለውጡ ከውስጥ የሚመነጭ፣ ማሕበራዊና አገር በቀል ሊሆን ይገባዋል፡፡

ነገር ግን ከላይ የተዘረዘሩት ችግሮች በምዕራብ ለሚወለዱት ሁለተኛ ትውልድ ሙስሊሞች በደምሳሳው ችግር የሚፈጥሩ አይደሉም፡፡ "እጅ ከፍንጅ ካልተያዛችሁ ችግር የለውም" ከሚለው የክብርና የውርደት መርህ ጋር ነው የምንታገለው፡፡ ውርደት የማያስከትል ከሆነ ችግር የለውም፡፡

ይህ መርህ ዕድሜዬ በጨመረ ቁጥር በጥሩ ሁኔታ ሲሰራ አስተውያለሁ፡፡ እኔና ብዙ ሙስሊም ጓደኞቼ ከሰዎች ዕይታ ተሰውረን ብዙ ጥሩ ያልሆኑ ነገሮችን እንፈፅም ነበር፡፡ ለምሳሌ ያህል የሚጠጣ ውኀ ከገዛን በኋላ አጭበርብረን ሶዳ እናስጨምር ነበር፡፡

ነገር ግን አንድ ቀን በቨርጂንያ በሚገኘው ታኮ ባሕር ዳርቻ ሳለን ከጓደኞቼ መካከል አንዱ ተመሳሳይ ነገር ሲፈፅም አስተናጋጁ እጅ ከፍንጅ ያዘው፡፡ "ውኀ ነው ያዘዝከው፡፡ ሶዳ ልትጨምርበት አትችልም!" ብሎ ጮኸበት፡፡ እዚያ የነበረ ሰው ሁሉ ጓደኛዬን ዞሮ ተመለከተው፡፡ ከእፍረት የተነሳ ፊቱ አሽቦ ሲመስል ይታይ ነበር፡፡

ጓደኛዬ እጅ ከፍንጅ ከመያዙ በፊት ሶዳ መስረቁ ለእርሱ ከጥፋት የሚቆጠር አልነበረም፡፡ ከተያዘም በኋላ ቢሆን ሶዳ መስረቅ ያን ያህል የሚያሸማቅቅ አይደለም፡፡ ለምዕራባውያን የሚዋጥላቸው ባይሆንም ሶዳ ከመስረቁ ይልቅ እጅግ ያሳፈረው በአንድ ባለ አነስተኛ ደሞዝ ተቀጣሪ እጅ ከፍንጅ መያዙ ነበር፡፡ ስለዚህ "ውኀ እየቀዳሁ ነው!" በማለት ተግባሩን ለመካድ ሞከረ፡፡ ከዚያም ብርጭቆውን በውኀ ሞልቶ ሄደ፡፡ የሶዳው ቅላትና አረፋ ግን በግልፅ ይታይ ነበር፡፡

በሌላ ጊዜ ደግሞ አንድ የአጎቴ ልጅ ኢንሹራንስ ሲያጭበረብር ተይዞ ከቤተሰቡ የነቀፌታ ውርጅብኝ ሲወርድበት ነበር፡፡ ነገር ግን እርሱ ትረካውን አስቂኝ ወደሆነ ገጠመኝ በመቀየር እፍረቱን ለመሸፈን ሞከረ፡፡

ብዙ ገንዘብ ማትረፍ እንዲችል ለኢንሹራንስ ኩባንያው ባለትዳር መሆኑን መናር አስፈላጊ መሆኑን እንዳመነ በመናገር ትረካውን ጀመረ፡፡ ስለዚህ ከሚስቱ ጋር እንዴት እንደተገናኙ፣ ሥራዋ ምን እንደሆነና የልደት ቀኗን የሚያስታውሰውን ገጠመኝ ሳይቀር ተናገረ፡፡ አሁንም ድረስ ፓኪስታን አገር እንደምትኖርና ከዚህ የተነሳ የምስክር ወረቀት እንደሌለው ለድርጅቱ ተወካይ አሳወቀ፡፡ የፈጠራ ታሪኩን እውነት በማስመሰል አውርቶ ኩባንያውን ካሳመነ በኋላ የመጨረሻ አነስተኛውን የክፍያ መጠን እንዲከፍል ተወሰነለት፡፡

በዚህ ተግባሩ የተቆጣነው እኔና አንድ ሌላ የቤተሰብ አባል ብቻ ነበርን፡፡ ሁለታችንም ደግሞ በአሜሪካ የተወለድን ነን፡፡ ነገር ግን ታላላቆቹ እየሳቁ ኩባንያው በቂ ገንዘብ ስላለው እንዳንጨነቅለት ነገሩን፡፡ የአጎቴ ልጅም በመስማማት ትረካውን ቀጠለ፡፡ ከአንድ ዓመት በኋላ በመንገድ ላይ ግጭት ስለደረሰበት የኢንሹራንስ ኩባንያው ክፍያ እንዲፈፅምለት ጥያቄ አቀረበ፡፡ ስልክ ደውሎ ስለ አደጋው በዝርዝር ሲያስረዳ ሳለ የኩባንያው ወኪል አደጋው በደረሰ ጊዜ ባለቤቱ አብራው መኖር አለመኖሯን ጠየቀው፡፡ እርሱ ግን ሚስት እንደሌለችው ተናገረ፡፡ አሁንም ወኪሉ ከዚህ ቀደም ሚስት አግብቶ

እንደሆን ጠየቀው፡፡ የአጎቴ ልጅም እንዳላገባ ተናገረ፡፡ ከዚያ በኋላ ለኩባንያው ሲከፍል ከነበረው የኢንሹራንስ ዋጋ እጥፉን ተቀበለ፡፡

ቤተሰቡ በመላ በሳቅ መፍረስ ጀመረ፡፡ ሲዋሽ የመያዙን አሳፋሪ ታሪክ ጎበዝ ተራኪ መሆኑን በማሳየት ከበሬታን አተረፈበት፡፡ መልካም ነገር መሥራትም ሆነ የጥፋተኝነት ስሜት በስሌቱ ውስጥ አልተካተቱም ነበር፡፡

በክብርና ውርደት ላይ የተመሠረተው የምስራቁ ባሕል በንፅህናና ጥፋተኝነት ላይ ከተመሠረተው የምዕራቡ ባሕል በተለየ ሁኔታ ነገሮችን እንዴት እንደሚያይ ለማስረዳት ያህል ነው እነዚህን ቀለል ያሉ ታሪኮች የጠቀስኩት፡፡ በእርግጥ በእስልምና ውስጥ ጥልቅ የሆነ የሥነ ምግባር መርህ ይገኛል፡፡ ስለዚህ ነገሩን በማቅለል ሙስሊሞች እጅ ከፍንጅ እስካልተያዙ ድረስ የፈለጉትን ነገር ያደርጋሉ የሚል የተሳሳተ አስተሳሰብ ውስጥ መግባት የለብንም፡፡ ሆኖም የጥፋተኝነት ስሜት በምስራቁ ባሕል ውስጥ ከውርደት ያነሰ ግምት እንደሚሰጠው መናገር ይቻላል፡፡

ወደ ሁለተኛ ትውልድ ምዕራባውያን ሙሰሊሞች ስንመጣ ደግሞ እነዚህን ሁለቱን ባሕሎች አብሮ ማስኬድ ምን ያህል ከባድ እንደሚሆን ማሰብ ይቻላል፡፡ በማሕበረሰቡ ዘንድ እምብዛም ተቀባይነት የሌለውን ተግባር ሲፈፅም ከተገኘ ወጣቱ ሙስሊም በውስጡ የጥፋተኝነት ስሜት ስለሚሰማው ለመደበቅ ይሞክራል፡፡ እፍረትን ለመሸፈን የሚደረገው የምስራቅ ልማድ የጥፋተኝነት ስሜት እንዲሰማው የሚያደርገውን የምዕራብ ባሕል ይሸፍነዋል፡፡

ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ስበቃ ለእኔም ይህ ጉዳይ ችግር ሆኖብኝ ነበር፡፡ ጓደኞቼ ሁሉ ሙስሊም መሆኔን ስለሚያውቁ በራሴ ምርጫ የፍቅር ጓደኛ መያዝ እንደማይፈቀድልኝ ያውቃሉ፡፡ በቤተሰብ ምርጫ ማግባት አስደሳችና ጥሩ መሆኑን ለማስረዳት በመሞከር ለባሕሌ አምባሳደር ለመሆን ጥረት አድርጌያለሁ፡፡ ሴቶችን የመቅረብ ፍላጎት እስካዳብር ድረስ ይህ ጉዳይ እምብዛም አላስጨነቀኝም ነበር፡፡

የሁለተኛ ዓመት ተማሪ ሳለሁኝ ፍቅር ቢጤ ጀማምሮኝ ነበር፡፡ ልጅቱም ደግሞ እንደምትወደኝ ትናገር ነበር፡፡ በምዕራባውያን ባሕል መሠረት እጅ ለእጅ ተያይዞ የፍቅር ወሬዎችን ማውራት ተቀባይነት ያለው ነገር ነው፡፡ ነገር ግን ከለመድኩት የምስራቅ ባሕል ጋር ስለሚጋጭብኝ ለማንም ሳልናገር ቆየሁኝ፡፡ ስሜቱ ባይለቀኝም ከአንድ ሳምንት በኋላ ጉዳዩን እርግፍ አድርጌ ተውኩት፡፡ ልጅቱ ትንሽ ቆይታ ከምርጥ ጓደኛዬ ከዴቪድ ጋር ጓደኝነት ጀመረች፡፡ ለእርሷ የነበረኝ ስሜት በቀላሉ ስላልተፋታኝ ከቆይታ በኋላ የምርጥ ጓደኛዬን የሴት ጓደኛ በመመኘቴ የጥፋተኝነት ስሜት ይሰማኝ ጀመር፡፡ ጓደኝነት ከመጀመራቸው በፊት ከእርሷ ጋር ምስጢራዊ ግንኙነት እንደነበረኝና አሁንም ድረስ ለእርሷ የሆነ ስሜት እንዳለኝ ለዴቪድ ተናዘዝኩኝ፡፡

ለምን ይህንን ጉዳይ እንደደበቅኳቸው ከጓደኞቼ መካከል ሊረዳልኝ የቻለ ማንም አልነበረም፡፡ ዴቪድ ጭራሹኑ እንቆቅልሽ ሆኖበታል፡፡ ጉዳዩን ከእርሱ መደበቄና የሴት ጓደኛውን ፍቅር በልቤ ውስጥ ማስተናገዴ ክህደት ሆኖ ነበር የታየው፡፡ ለምርቃት ጥቂት ጊዜ ሲቀረን በኔና በዴቪድ መካከል ክፍተት ተፈጥሮ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት ከምቀርባቸው ሰዎች ሁሉ ተነጥዬ ብቸኛ ሆኜ ነበር፡፡

አሁንም በድጋሜ ጓደኛ አልባ ሆኛለሁ ነገር ግን ልቤ በጣም ተሰብሮ ግራ መጋባት ውስጥ ገብቻለሁ፡፡ ምንድነው የተፈጠረው? ለምንድነው ሁል ጊዜ ብቻዬን የምቀረው? ጥፋት መሥራቴን አውቃለሁ ነገር ግን ጓደኞቼን ሁሉ ሊያሳጣኝ የሚችል ጥፋት ነው እንዴ የፈፀምኩት? የማይመረቁ ተማሪዎች በሚያዘጋጁቸው ድግሶች ላይ መሳተፍ ጀመርኩኝ፡፡ ቀደም ሲል በታቀዱት የቅድመ ኮሌጅ የጉብኝት መርሃ ግብሮች ላይ መሳተፍ አልቻልኩኝም፡፡ ጓደኞቼ ወደ ኮሌጅ ሲገቡ ልሰናበታቸው አልቻልኩኝም፡፡ ለእረፍትም ሲመለሱ ላገኛቸው አልቻልኩኝም፡፡

በወቅቱ ምን እየሠራሁ እንደነበር ቢገባኝ ኖሮ የተለየ ነገር ባደረኩ ነበር፡፡ እነርሱም ቢረዱኝ ኖሮ ግልፅነትን በማጣቴ ምክንያት የደረሰብኝ ጉዳት በቀነሰ ነበር፡፡ አንዳችን ሌላችንን መረዳት ብንችል ኖሮ የልጅነት ጓደኞቼ ዛሬም ድረስ ከጎኔ ይኖሩ ነበር፡፡

አንዳንዶች በምስራቅ እና ምዕራብ መካከል የባሕል ልዩነት እንደሌለና ሰዎች ዓለምን በተመሳሳይ መነፅር እንደሚመለከቱ ያስባሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ የምስራቅና የምዕራብ ባሕሎችን ምርምር ሊደረግባቸው እንደሚገባቸው የጥናት መስኮች ያያሉ፡፡ ለእኔና ለመሰሎቼ ግን በምስራቅና ምዕራብ ባሕሎች መካከል ያለው ልዩነት የሕይወታችንን አቅጣጫ ይቀይሳል፡፡ ከዚያ የተነሳ ነው የልጅነት ጓደኞቼን ያጣሁት፡፡ ከዚያ የተነሳ ነው የወጣትነት ዕድሜዬን ያለ ጓደኛ የጀመርኩት፡፡

ደስ በሚል ሁኔታ ጓደኞቼን የማጣት የህመም ስሜት የቆየው ያንን ክረምት ብቻ ነበር፡፡ ከጥቂት ወራት በኋላ ወርሃ ነሐሴ 2001 በአዲስ መንፈስና አዳዲስ ጓደኞችን በማፍራት ተስፋ ኮሌጅ ተቀላቀልኩኝ፡፡ ነገር ግን ኮሌጅ በገባሁ በሦስተኛው ሳምንት አገራችንን በእጅጉ የጎዳ እንግዳ የሆነ አደጋ ደረሰ፡፡ ከዚህ በኋላ ዓለም እንደቀድሞ አትሆንም፡፡

# የሰላም ሃይማኖት

በኦልድ ዶሚኒየን ዩኒቨርሲቲ ገና አራተኛ ሳምንቴን እየጀመርኩ ነበር፡፡ እኔና ባጂ ኦዲዩን የተቀላቀልነው ለተመሳሳይ ዓላማ ነበር፡፡ ለቤታችን የቀረበ ምርጡ ኮሌጅ ስለነበር እማና አባ ከቤት ርቀን እንዳንሄድ ስለፈለጉ ነበር፡፡ ብዙ ጊዜ ወደ ትምህርት ቤት አንድ ላይ ሆነን እንሄድ የነበረ ሲሆን ማክሰኞ ማክሰኞ ጠዋት ባጂ የትራፊክ መጨናነቁን በመፍራት አርፍዳ ከኔ ኋላ ትመጣ ነበር፡፡ ሁለት ሰዓት ላይ ለአናቶሚ ክፍለ ጊዜ መድረስ ይኖርብኛል፡፡

ያ የማክሰኞ ጠዋት እንደማንኛውም ቀን ነበር በሰላም የተጀመረው፡፡ የአናቶሚ ክፍለ ጊዜ አልቆ የኦዲዩ ተማሪዎች ሕብረት ወደ ሆነው ወደ ዌብ ማዕከል ሄድኩኝ፡፡ ከሰዓት በኋላ የምርምር ቡድን ለልምምድ እስኪሰበሰብ ድረስ ነፃ ነበርኩኝ፡፡ ያንን ቡድን የተቀላቀልኩት ኮሌጁን በተቀላቀልኩ በመጀመርያው ሳምንት ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ያስመዘገብኩትን ውጤት እስከ ኮሌጅ ማስቀጠል እችል እንደሆን አስብ ነበር፡፡

ወደ ተማሪዎች ሕበረት ቢሮ በር ስቀርብ የምርምር ቡድኑ መሪ በጥድፊያ እየተራመደች ስትወጣ ፊት ለፊት ተገጣጠምን፡፡ ምን እየሆነ እንዳለ ግራ ስለገባኝ “ምን ተፈጠረ?” ብዬ ጠየኳት፡፡

እርምጃዋን ሳትገታ “ሁለተኛው ሕንፃ አሁን ፈረሰ” አለችኝ፡፡ ግራ ገብቶኝ ቴሌቪዥን ፊት እጅብ ብሎ ወደቆመው ሕዝብ ሄድኩኝ፡፡

የቴሌቪዥን ጣቢያዎች የዓለም የንግድ ማዕከል የሰሜንና የደቡብ ሕንፃዎች ሲደረመሱ መልሰው መላልሰው ያሳዩ ነበር፡፡ አንድ አውሮፕላን የአንደኛው ሕንፃ ወገብ ላይ እንደ ሚሳኤል ሲሰካና ሁለቱም ሕንፃዎች ተከታትለው ሲደረመሱ  ደግመው ደጋግመው ያሳዩ ነበር፡፡ በፊልም የሚታይ ቅንብር ቢመስልም ነገር ግን እጅግ ዘግናኝና አስፈሪ ክስተት ነበር፡፡

ማንም አልተንቀሳቀሰም፡፡ መናገር የቻለም አልነበረም፡፡ ከአፍታ በኋላ ስልኬ ጮኸ፡፡ አባ ነበር፡፡ ድምፁ ይርገበገባል፡፡ “ነቢል የት ነው ያለኸው? ለምንድነው ስልክህን ያላነሳኸው?”

“ትምህርት ቤት ነው ያለሁት አባ፡፡ የአናቶሚ ክፍለ ጊዜ ስለነበር ዝግ ነበር፡፡”

“አሁኑኑ ወደ ቤት ና! ባጂ ካንተ ጋር ነች?”

“አይደለችም፣ ደህና ናት?”

“እርሷም ስልኳን አታነሳም፡፡ ፈልገህ አግኛትና በቀጥታ ወደ ቤት ኑ፡፡”

ድንጋጤው ሳይለቀኝ “አባ ምን ተፈጠረ? ለምንድነው ወደ ቤት መምጣት ያለብኝ?” ብዬ ጠየቅሁት፡፡

አባ ገርሞት “ምን እንደተፈጠረ አታውቅም? ጥቃት ተፈፅሟል እኮ” አለኝ፡፡

“አዎ ግን ለምንድነው ወደ ቤት መምጣት ያለብኝ?”

“ነቢል! ሙስሊሞች ናቸው የፈፀሙት እያሉ ነው! ሰዎች ስሜታዊ ሆነው አንተን ወይም ባጂን ሊጎዱ ይችላሉ፡፡ እርሷን ፈልጎ ማግኘት ያንተ ኀላፊነት ነው፡፡ ደህንነቷን አረጋግጠህ ወደ ቤት እንድትመጡ ይሁን፡፡”

“ነገር ግን አባ እኔ…”

አባ ጊዜ አላጠፋም፡፡ “ነቢል! እኔ ያልኩትን አድርግ! ለባጂ መደወል ይኖርብኛል፡፡ ስልክህ ካንተ ጋር ይቆይ፡፡” ያንን ብሎ ስልኩን ዘጋው፡፡

ቴሌቪዥን እያዩ የነበሩትን ሰዎች ተመለከትኳቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች ጠላቶቼ ይሆኑ እንዴ? ሊጎዱኝ ያስቡ ይሆን? ቀስ በቀስ አደጋው ከቴሌቪዥኑ ውስጥ በመውጣት በኔ ላይ አንዣበበ፡፡ የዚህ አስፈሪ ፊልም አካልና ተዋናይ ሆኛለሁ፡፡ በፍጥነት ወጥቼ ለባጂ ደወልኩላት፡፡

ስልኩን ስታነሳው ትልቅ እረፍት ተሰማኝ፡፡ “አሰላሙ አለይ ኩም?”

“ባጂ እየሆነ ያለውን አውቀሻል? የት ነው ያለሽው?”

“አዎ፣ መኪናዬ ውስጥ ነኝ፡፡ ወደ ቤት እየሄድኩ ነው፡፡”

“አባዬ ሲደውል ለምንድነው ስልክሽን የማታነሺው?”

“ሰቨን ኢለቨን ውስጥ ቴሌቪዥን እያየሁ እያለሁ ፖሊስ ጎትቶ ከሕዝቡ መሀል አውጥቶኝ ቡርቃ ስለለበስኩኝ እዚያ መቆየቴ አደጋ እንደሚኖረው ነገረኝ፡፡ አጅቦኝ ወደ መኪናዬ ስለወሰደኝ አሁን ወደ ቤት እየሄድኩ ነው፡፡”

“እውነትሽን ነው? በጣም ደግ ሰው ነው፡፡ እሺ ተጠንቅቀሽ ንጂ፡፡ ቤት እንገናኛለን፡፡”

የዚያን ዕለት ቴሌቪዥን ላይ አድፍጠን አመሸን፡፡ አባ ሳምንቱን ፍቃድ ጠይቆ ከሥራ ቀረ፡፡ እኛም እንደዚያው እንድናደርግ መከረን፡፡ መንገድ ዳር የሚሸጡትን የአሜሪካ ባንዲራዎች ለመግዛት ብቻ ነበር ከቤት የወጣነው፡፡ በመኪናዎቻችን ላይ፣ በግቢያችን ውስጥና በጋራዥ በር ላይ በግልፅ እንዲታዩ አድርገን የአሜሪካን ባንዲራዎች ሰቀልን፡፡

በዜና ማሰራጫዎች ምንም ይስሙ ምን እኛ ጠላቶቻቸው አለመሆናችንን ለህዝቡ ማሳወቅ ፈልገን ነበር ያንን ያደረግነው፡፡

አባቴ ይህንን ያደረገው ወዶ አልነበረም፡፡ በበረሃው ማዕበል ዘመቻ ወቅት የቤተሰቤ አባላት ጥቃት ተፈፅሞባቸው ነበር፡፡ ትልቋ እማዬ ደጓ አያቴ ቡርቃ በመልበሷ ምክንያት በኒውዮርክ በሚገኝ የነዳጅ ማደያ ውስጥ ሥራ እንዳትቀጠር ተከልክላ ነበር፡፡ ሌላ የሩቅ ዘመዳችን በገበያ አዳራሽ ውስጥ አካላዊ ጥቃት ደርሶባት ነበር፡፡ ሆዷ ቡጢ ቀምሳ ነበር፡፡ ከመስከረም ፲፩ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ኦዲዩ አካባቢ የነበረው መስጊድ ጥቃት ደርሶበት መስኮቶቹ ተሰባብረዋል፡፡ መስጊዱን ለማሳደስ ገንዘብ ያወጡ ሰዎችን አውቃለሁ፡፡ ጥሩና ታታሪ ሰዎች ነበሩ፡፡

ቀናት በሄዱ ቁጥር ይህንን ጥቃት በአገራችን ላይ የፈፀሙት በእርግጥም ሙስሞች መሆናቸውና ይህ ጥቃት በእስልምና ስም እደተፈፀመ ግልፅ እየሆነ መጣ፡፡ ነገር ግን እስላም እንዲህ ነው እዴ? እኔ የማውቀው እስልምና ይህ አልነበረም፡፡ በሩቅ አገራት የሚኖሩት ሙስሊሞች በአላህ ስም ክፉ ተግባራትን ሲፈፅሙ እሰማለሁ ነገር ግን ከሩቅ የሚሰሙ ወሬዎች እንደመሆናቸው መጣን በኔ ላይ ያመጡት ተፅዕኖ አልነበረም፡፡ ይህኛው ግን በቤታችን አቅራቢያ የተፈፀመ ነው፡፡ የገዛ ልባችንን የመታ ጥቃት ነበር፡፡

በተከታዮቹ ሳምንታት የዜና ማሰራጫ ጣቢያዎች ሕንፃዎቹ ሲፈራርሱ ደጋግመው ማሳየታቸውን ተያያዙ፡፡ ደግመው ደጋግመው ያሳዩታል፡፡ በአምላኬ ስም በሺህዎች የሚቆጠሩ ንፁሃን ሰዎች ሕይወት ሲቀጠፍ ተመለከትኩኝ፡፡ በመጨረሻም ከልክ አለፈ፡፡ ስለ እምነቴ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እውነቱን ማወቅ ይኖርብኛል፡፡ የሰላም ሃይማኖት የሆነውን የኔን እስልምናና የሽብር ሃይማኖት የሆነውን የቴሌቪዥን እስልምና የማስታርቅበትን መንገድ ማግኘት ሊያስፈልገኝ ነው፡፡

ከክስተቱ በኋላ አሥራ ሁለት ዓመታት ቢያልፉም ጥያቄው ፊት ለፊት ከሚታየው በላይ ውስብስብ መሆኑን ተረድቻለሁ፡፡ ከግምት ውስጥ ሊገባ የሚገባው ትልቁ ነገር *የእስላም* ትርጓሜ ነው፡፡ *እስላም* ስንል የሙስሊሞችን እምነት ማለታችን ከሆነ ሰዎች ስለ እምነቱ በሚያስተምሩበት መንገድ ላይ ተመስርቶ የሰላም ወይም የሽብር ሃይማኖት ሊሆን ይችላል፡፡

በምዕራብ የሚኖሩ ሙስሊሞች በጣም ውሱን የሆነን የእስልምና ዓይነት ነው የሚማሩት፡፡ ልክ እኔና ባጂ እንደተማርነው መሐመድ ራስን የመከላከል ጂሃድ ብቻ እንደፈፀመና በቁርአን ውስጥ የሚገኙት ነውጠኛ ጥቅሶች ውሱን የሆኑ ራስን የመከላከል አውዶችን ብቻ እንደሚያሳዩ ነው የሚማሩት፡፡ ጂሃድ ሰላማዊና ክፉ መሻቶቻችንን ለማሸነፍ በውስጣችን የሚደረግ ትግል ተደርጎ ነው የሚተረጎመው፡፡ ምዕራባውያን ሙስሊሞች ስለ እምነታቸው ሲጠየቁ በቅንነት የሰላም ሃይማኖት መሆኑን ይገልፃሉ፡፡

በምስራቅ ሚኖሩት ሙስሊሞች ደግሞ ስለ እስልምና የተለየ አመለካከት አላቸው፡፡ እስልምና ከሁሉም ሃይማኖቶችና የኑሮ ዘይቤዎች የላቀ እንደሆነና አላህ ይህ ሃይማኖት መላውን ዓለም ተቆጣጥሮ ማየት እንደሚፈልግ ነው የሚማሩት፡፡ ጂሃድን ብዙ ጊዜ የእስላምን ጠላቶች ለመታገል እንደሚደረግ አካላዊ ፍልሚያ ነው የሚያዩት፡፡ እነዚህ ሰዎች ስለ እምነታቸው ሲጠየቁ እስልምና ዓለምን ሁሉ እንደሚቆጣጠር በቅንነት ይናገራሉ፡፡

እስልምናን በተከታዮቹ አመለካከት መሠረት የምንተረጉም ከሆን የሰላም ሃይማኖት ሊሆንም ላይሆንም ይችላል፡፡ ነገር ግን እስልምናን መሐመድ እንዳስተረው የእምነቶችና የልማዶች ሥርኣት አድርገን ከተረጎምነው የትርጉሙ አከራካሪነት ይቀንሳል፡፡

ቀዳሚያን የሆኑ የታሪክ ድርሳናት እንደሚያስረዱት መሐመድ የማጥቃት ወታደራዊ ዘመቻዎችን ፈፅሟል[31] እንዲሁም ዓላማውን ከግብ ለማድረስ ነውጠኝነትን ተጠቅሟል፡፡[32] ጂሃድ የሚለውን ቃል መንፈሳዊና አካላዊ ትርጉም የሰጠው ቢሆንም በአካላዊ ገፅታው ላይ ይበልጥ አተኩሯል፡፡[33] ሰላማዊው የእስልምና ልምምድ ብዙ ጊዜ የተመሠረተው የቅርብ ጊዜና በተለይም በምዕራባውያን የመሐመድ ትምህርት አተረጓጎም ላይ ሲሆን የበለጠ ነውጠኛ የሆነው እስልምና ደግሞ በትክክለኛውና ታሪካዊው አተረጓጎም ላይ የተመሠረተ ነው፡፡[31]

በእርግጥ እንደማገኛውም ሰው በምዕራብና በምስራቅ የሚኖሩት ሙስሊሞች የተማሩትን ነው የሚያምኑት፡፡ ታሪካዊ ዳራዎችን የበለጠ በጥልቀት የማጥናት ጥረት

የሚያደርጉት የተወሰኑት ብቻ ናቸው፡፡ እነዚህ ጥቂት ሰዎች ደግሞ ልክ እኔ በቲኦኬ ክፍለ ጊዜ አደርግ እንደነበረው ቀደም ሲል ያመኑትን ነገር ለመከላከልና ከዚያ በተፃራሪ የሚያሳዩ መረጃዎችን ችላ ማለት ወይም አሳንሶ የማየት ጥረት ያደርጋሉ፡፡

እኔ እንደዚያ ነበርኩኝ፡፡ በውስጣዊው እኔነቴ የእስልምናን ትክክለኛ ገፅታ ለማወቅ እፈልግ ነበር ነገር ግን ምርመራዎችን በማድረግ የልጅነት እምነቴን መፈተሽ ከባድ ነበር፡፡ አስቸጋሪ የሆኑ እውነታዎችን ችላ የምልባቸውን መንገዶች እፈልግ ነበር፡፡ አድሎዬን ይዤ እንዳልቀጥል የሚያደርገኝ ነገር ያስፈልገኝ ነበር፡፡ ደካማ የሆኑ ሙግቶቼን ዳግመኛ ዞር ብዬ እስከማላያቸው ድረስ ደግሞ ደጋግሞ በፊቴ ድባቅ የሚመታ ማስረጃ ያስፈልገኝ ነበር፡፡

አመለካከቴን መገዳደር የሚችል የማያመቻምች አስተዋይ፣ ሙስሊም ያልሆነ ጓደኛ ያስፈልገኝ ነበር፡፡ በጣም ድፍረት ያለውና ግትር መሆን አይጠበቅበትም፤ ነገር ግን በሕይወቴ ውስጥ ትልቅ ቦታ የምሰጣቸውን ነገሮች ላወራው የምችለው ለእኔ የታመነና የተወደደ ሰው መሆን ያስፈልገዋል፡፡

እግዚአብሔር ከዚህ ሰው ጋር የመተዋወቅ ዕድል ለኔ መስጠቱና ሕይወቴን እስከወዲያኛው ሊለውጥ የሚችለውን መንገድ መጀመሬ አልገባኝም ነበር፡፡

*ማርክ ሚተልበርግየምርጥ መጻሕፍት ደራሲ ሲሆኑ ሁለገብ ክርስቲያን የሚለውን ወንጌልን የማድረስ ትምህርት ያዘጋጁ ናቸው፡፡ ስለ ምስራቅ እና ምዕራብ ባሕል የሚያወሳውን በኚህ ሰው የተዘጋጀውን የሊቅ አስተዋፅዖ ለማንበብ ተከታዩን ድረ-ገፅ ይጎብኙ፡፡contributions.NabeelQureshi.com*

## ክፍል ፫

# አዲስ ኪዳን ሲፈተሽ

*አላህ ሆይ መጽሐፍ ቅዱስ ትክክል ሊሆን አይችልም፣ ይችላል እንዴ?*

# ወንድማማች መሆን

የመንገድ ዳር ሰባኪያንን የማልሰማበት ግልፅ ምክንያት አለኝ፤ ስለ እኔ የሚጨነቁ አይመስሉም፡፡ እነዚህ ሰዎች አያበሳጩኝም፡፡ ቅንአታቸውን አደንቃለሁ፡፡ በእምነታቸው የማያፍሩትን ሰዎች አከብራለሁ፡፡ ነገር ግን የአጀንዳቸው መሣርያ አድርገው ስለሚቆጥሩኝ አልቀበላቸውም፡፡ መልዕክታቸው በሕይወቴ ላይ ምን ዓይነት ተፅዕኖ እንደሚኖረው ይገነዘቡ ይሆን? ምን ያህልስ ለእኔ ያስባሉ? ብዬ ራሴን እጠይቃለሁ፡፡

ሰዎችን በመልካም አቀራረብ በመቅረብ ሰላምታ እየሰጡ፣ ችግራቸውን ተካፍለው አብረው የሚጸልዩና መልዕክታቸውን የሚያስተላልፉ የመንገድ ዳር ሰባኪዎች መኖራቸውን አውቃለሁ ነገር ግን አንድም ቀን አላጋጠሙኝም፡፡ ያጋጠሙኝ ሰዎች ዝም ብለው መንገድ ዳር በመቆም ስለ እምነታቸው የሚናገሩ ናቸው፡፡ እንደዚህ ዓይነት ሰባኪዎች ጥቂቶችን እንደሚደርሱና ብዙዎችን ግን አሰናክለው ወደ ኋላ እንደሚመልሱ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡

እንዳለመታደል ሆኖ ብዙ ክርስቲያኖች ወንጌልን ስለማድረስ ተመሳሳይ አመለካከት አላቸው፡፡ ከአድማጫቸው ጋር ሳይግባቡና ሐሳቡን ሳይሰሙ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ስለ ክርስትና እምነት ይናገራሉ፡፡ ወንጌል መሠረታዊ የሆነ የኑሮ ለውጥን የሚፈልግ ነው፡፡ ነገር ግን ብዙዎች የማይግባቧቸው ሰዎች ሕይወታቸውን እንዲለውጡ ቢነግሯቸው ለመስማት ስለማይፈልጉ የጥድፊያ ወንጌል ስርጭት አያዋጣም፡፡ ስለዚያ ሰው ሕይወት ምንም የሚያውቁት ነገር አይኖራቸውምና፡፡

በሌላ ወገን ደግሞ እውነተኛ ጓደኛ ከልብ በመነጨ ቅንነት የጓደኛውን ሁኔታና የሕይወት ትግል በማጤን ተመሳሳይ መልዕክት ቢናገር መልዕክቱ ግልፅ ሆኖ ጎላ ብሎ ይደመጣል፡፡

ውጤታማ የወንጌል ስርጭት በመግባባት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ጥቂት የሆኑ ልዩ ሁኔታዎች ግን ይኖራሉ፡፡

የኔን ሁኔታ ብነግራችሁ ስለ ግል ሕይወቴ ከልቡ የሚያስብ አንድም ክርስቲያን አልገጠመኝም ነበር፡፡ በከፍታም ሆነ በዝቅታ የሕይወቴን ሸክሞች የተካፈለ አንድም አልነበረም፡፡ ከብዙ ክርስቲያኖች ጋር ተዋውቄያለሁ፡፡ እርግጠኛ ነኝ ክርስቲያን ብሆን ኖሮ ጓደኞች ይሆኑኝ ነበር፤ ነገር ግን ያ ዓይነት ጓደኝነት በሁኔታ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ስለ ሕይወት ግድ የሚላቸው ክርስቲያኖች አላጋጠሙኝም፡፡ ማንም ስለ እኔ ግድ የሚለው ክርስቲያን ስላልነበረ እኔም ስለ መልዕክታቸው ግድ አልነበረኝም፡፡

ነገር ግን ያ ሁኔታ የሚለወጥበት ጊዜ ቀርቦ ነበር፡፡

ከ 9/11 በኋላ ሕይወት የቀድሞ መልኳን ለመያዝ ጥቂት ሳምንታት ማለፍ ነበረባቸው፡፡ ባጂና እኔ ትምህርታችንን ከእንደገና ቀጥለናል፡፡ አባ ወደ ሥራ ተመልሷል፡፡ እማም ገበያ ለመሄድ የነበራት ፍርሃት እየረገበላት ነው፡፡ አሁንም ድረስ ሙስሊሞችን በጥርጣሬ የማየቱ ሁኔታ እንደቀጠለ ቢሆንም፤ እስልምናም በዜና ማሰራጫዎች ቢብጠለጠልም በስሜታዊነት ተነሳስቶ ጥቃት የመፈፀም ሁኔታ የፈራነውን ያህል አልነበረም፡፡ መስጊዳችን መጠቃቱና በተደጋጋሚ ፀረ ሙስሊም ንግግሮች መሰማታቸው እውነት ቢሆንም በሙስሊሞች ላይ የደረሰ አካላዊ ጥቃት መኖሩን አልሰማንም፡፡ ፈራ ተባ እያልንም ቢሆን ወደ ቀድሞ ሕይወታችን እየተመለስን ነው፡፡

የምርምር ቡድናችን በውድድር ላይ የሚሳተፍበት ጊዜ ቀርቦ ነበር፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከሚደረጉት ውድድሮች በተለየ ሁኔታ የኮሌጅ የምርምር ውድድሮች ለብዙ ቀናት የሚደረጉ ናቸው፡፡ ብዙ ጊዜ ደግሞ በሌሎች ግዛቶች ነበር የሚደረጉት፡፡

የኛ ቡድን ለመጀመርያ ውድድሩ ወደ ቸስተር ፔንሲልቬንያ ነበር ያቀናው፡፡በጉዟችን ዕለት እማ እስከ ኦዲዮ ድረስ ሸኘችኝ፡፡ *ቤተን አርትስ ኤንድ ሌተርስ* የተሰኘው ሕንፃ ጋር ስንደርስ ለውድድሩ ከሚጓዙት ተማሪዎች መካከል አንዱ ሊቀበለን መጣ፡፡ ከዚህ ቀደም በልምምድ ቦታ ላይ አንድ ሁለት ጊዜ አውርተናል፤ ነገር ግን ብዙም አንተዋወቅም ነበር፡፡ ወደኛ በፈጣን እርምጃ በመምጣት ሻንጣዬን እያገዛኝ ለእማ ራሱን አስተዋወቀ፡፡

"ሰላም እመቤት ቁሬሺ፡፡ ዴቪድ (ዳዊት) እባላለሁ፡፡"

እማ ወደማታውቀው ቦታ እኔን ከመሸኘቷ በፊት ከቡድኑ አባላት መካከል አንድ ሰው በመተዋወቋ በጣም ደስ ብሏታል፡፡ "ሰላም ዳዊት ስላገኘሁህ በጣም ደስ ብሎኛል፡፡ ከነቢል ጋር ትጓዛለህ?"

"አዎ፡፡ ስለ እርሱ እንደምትጨነቁ ነግሮኛል ነገር ግን በጥሩ ሁኔታ ስለምንንከባከበው መጨነቅ የለባችሁም፡፡"

እማ ከዳዊት አንደበት ያንን ከመስማት የበለጠ ሊያስደስታት የሚችል ነገር አልነበረም፡፡

"ነቢል ይህ ልጅ ጥሩ መሆኑን መናገር እችላለሁ፡፡ እንዳትለየው እሺ?"

"*አቻ፣* እማ፣ አልለየውም፡፡"

"ስልክህን እንዳትዘጋው እሺ ነቢልዬ? ሆቴል ስትደርሱ ደውለህ ያረፍክበትን ሆቴል ቁጥር ንገረኝ፡፡ ደህና መሆንህን እርግጠኛ መሆን እፈልጋለሁ፡፡"

"አቻ፣ እማ፣ እንዳልሽኝ አደርጋለሁ፡፡ ምንም ችግር አይደርስብኝም አትጨነቂ፡፡"

እማ እንዳትጨነቅ መንገር ማለት እንዳትተነፍስ የመንገር ያህል ስለሆነ ምክሬን አልተቀበለችም፡፡ "ለአባትህም ደውለህ ደህና መሆንህን ማሳወቅ እንዳትዘነጋ፡፡"

"አቻ፣ እማ!"

"ዳዊት፣ ነቢል እንዲደውልልን አሳስበው፡፡ በጣም ዝንጉ ልጅ ነው፡፡"

ዳዊት ፈገግታውን መሸሽግ አልቻለም፡፡ "እሺ አሳስበዋለሁ፡፡"

እማ በመጨረሻ እፎይታ ተሰማት፡፡ "አመሰግናለሁ ዳዊት፡፡ ከነቢል ጓደኞች መካከል አንዱን በመተዋወቄ በጣም ደስ ብሎኛል፡፡ ከጉዞው በኋላ ወደ ቤታችን መጥታችሁ ግብዣ ይደረግላችኋል፡፡ ቆንጆ የፓኪስታን ምግብ አዘጋጅላችኋለሁ፡፡"

በዳዊት ድምፅ ውስጥ ምንም የመግደርደር ሁኔታ አይስተዋልም፡፡ "ግብዣውን በአንድ አፍ ተቀብያለሁ፡፡ አመሰግናለሁ እመቤት ቁሬሺ!"

"እሺ የኔ ጎረምሶች መልካም ጊዜ ይሁንላችሁ፡፡ ደህና ሁኑ! ነቢል፣ ደውልልኝ፡፡ ሰላት መስገድህንም አትርሳ!"

እማ ልክ አራት ዓመት እያለሁ ታደርግ እንደነበረው ፊቴን በእጆቿ ይዛ ሁለቱንም ጉንጮቼን ሳመችኝ፡፡ አሁን ግን እርሷ ሳትሆን እኔ ነበርኩኝ ጎንበስ ማለት የነበረብኝ፡፡ ዳዊት እማ እንደ ልጅ ስትስመኝ ሲያይ የማፍር መስሎት ምላሱን ነክሷል፡፡ ነገር ግን ይህ ለኛ ቤተሰብ የተለመደ ነበር፡፡ ይህን ያህል በእርሷ በመወደዴ ደስተኛ ነበርኩኝ፡፡

ወደ መኪናዋ ውስጥ ተመልሳ እየገባች የተለመደውን የፓኪስታን ምርቃት መረቀችኝ፡፡ *"ኹዳ ሐፊዝ፣* ቤይታ፡፡" እግዚአብሔር ይጠብቅህ ማለቷ ነበር፡፡

"ኹዳ ሐፊዝ እማ፡፡ እወድሻለሁ፡፡"

ከመኪና ማቆሚያው ወጥታ መንዳት ስትጀምር ዳዊት የተንኮል ፈገግታ እያሳየ ትክ ብሎ ተመለከተኝ፡፡

"ምን ተፈጠረ?"

"አይ ምንም አልተፈጠረም፡፡ ለሦስት ቀን ብቻ እንደምትሄድ ታውቃለች አይደል?"

"አዎ ግን ብዙ ጊዜ ከቤት ርቄ ስለማልሄድ ነው፡፡" የተወሰኑ ቦርሳዎችን አንጠልጥዬ ቡድናችንን ለመቀላቀል ወደ ሕንፃው ማዘገም ጀመርኩኝ፡፡

ዳዊት የተቀሩትን ቦርሳዎች በማንጠልጠል ተከተለኝ፡፡ የተንኮል ፈገግታው ግን ከፊቱ ላይ አልጠፋም ነበር፡፡ “ስማ እንጂ፣ ላስታውስህ፡፡ እናትህን ካወራህት ብዙ ጊዜ ሆነ እኮ፡፡ በእውነት ልትደውልልላት ይገባል፡፡”

ቆም ቢዬ ዳዊትን ተመለከትኩት፣ ከዚያ ፊቴን መለስ አድርጌ መንገዱን አየሁት፡፡ እማ ወደ ግራ ለመታጠፍ ቀዩን መብራት እየጠበቀች እዚያው ቆማለች፡፡ ወደ ሕንፃው ውስጥ ስንገባ በዓኖቿ ሸኘችን፡፡ቀልዱን በቀልድ ለመመለስ ወደ ዳዊት ዘወር ብዬ “ዳዊት ስላስታወስከኝ አመሰግናለሁ፡፡ ከእናቴ ጋር ስላለኝ ቁርኝት በመጨነቅህ ደስ ብሎኛል፡፡ አሁኑኑ እደውልልላታለሁ” አልኩት፡፡ ስልኬን አውጥቼ ለእማ ደወልኩላት፡፡ ዳዊት ከገዛ ሳቁ ጋር መታገል ጀመረ፡፡

እንዲህ እንዲህ እያለ ጓደኝነታችን ከጅምር አልፎ በቅፅበት ወደ ወንድማማችነት ተሸጋገረ፡፡ በቀጣዮቹ ቀናት እኔና ዳዊትን የተመለከቱ ሰዎች ሁሉ አንዳችን የሌላችን ግልባጭ መሆናችንን መናገር ጀመሩ፡፡ ሁለታችንም ቁመታችን እኩል ነበር - ስድስት ጫማ ከሦስት ኢንች - ነገር ግን እኔ ጠየም ያለ ቆዳና ጥቁር ፀጉር ነው ያለኝ፡፡ ዳዊት ደግሞ ነጣ ያለ ቆዳና ብርማ ፀጉር ነው ያለው፡፡ እኔ ሶላላ ቁመት ያለኝ ሲሆን 175 ፓውንድ ነበር የምመዝነው፡፡ ዳዊት ደግሞ ከኔ አርባ ፓውንድ የሚመዝን ፈርጣማ ጡንቻ ነበረው፡፡ እኔ ለአለባበሴና ለገፅታዬ የምጨነቅ ዓይነት ሰው ስሆን ዳዊት ደግሞ ብዙ ጊዜ ቀለል ያለ አለባበስ ነበር የሚመርጠው፡፡ የኔ አስተዳደግ በከፍተኛ የወላጆች እንክብካቤ ሲሆን ዳዊት ግን አስቸጋሪ ሕይወት ያሳለፈ ሰው ነበር፡፡ነገር ግን ስለ ዳዊት ያላወቅሁት አንድ አስገራሚ ገፅታ ነበር፡፡ ዳዊት ያለፉትን አምስት ዓመታት መጽሐፍ ቅዱስን በማጥናትና ክርስቶስን ለመከተል በመማር ያሳለፈ ጠንካራና ፅኑ ክርስቲያን ነበር፡፡ የወንጌል ሸክም ቢኖረውም ነገር ግን በቀጥታ ስለ እምነቱ የሚያውቀውን በኔ ላይ ማዝነብ አልጀመረም፡፡ ውይይቱ ጓደኝነታችን ስር ከሰደደ በኋላ ነበር ሳይታሰብ የተጀመረው፡፡ በእርግጥ ጉዳዩን ቀድሜ ያነሳሁት እኔ ነበርኩኝ፡፡

# ዓይኖቼ ተከፈቱ

እስከ ዌስት ቸስተር የነበረው ጉዞ አስደናቂ ነበር፡፡ ሁሉም የቡድኑ አባላት አንዳችን ከሌላችን ጋር እየተዋቅን፣ የምርምር ወረቀታችንን እየተለማመድን፣ የግል ሕይወት ታሪካችንን እያወራንና በጋራ እየሳቅን ነበር ስንጓዝ የነበረው፡፡ የተለያየ የሕይወት ዘይቤና አስተሳሰብ ካላቸው ሰዎች ጋር በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሳሳልፍ የመጀመርያ ጊዜዬ ስለነበር ለኔ ዓይን ከፋች አጋጣሚ ነበር፡፡ ከቡድኑ አባላት መካከል አንዲት ልጅ አደንዛዥ እፆችን ሕጋዊ ማድረግ እንደሚገባ ትናገር ነበር፡፡ አንዱ ልጅ ከሴት የፍቅር ጓደኛው ጋር ነበር የሚኖረው፡፡ ሌላ ልጅ ደግሞ ከወንድ የፍቅር ጓደኛው ጋር ነበር የሚኖረው፡፡

“ወደ ኮሌጅ እንኳን በደህና መጣህ” አልኩት ራሴን፡፡

እራታችንን ለመብላት ሜሪላንድ ወደሚገኝ የጣልያን ሬስቱራንት ጎራ አልን፡፡ ለሁላችንም የሚበቃ ትልቅ ጠረጴዛ ካዘጋጁልን በኋላ ምግብ ሲበስል ማየት በሚያስችል ሁኔታ በማዕድ ቤቱትይዩ አስቀመጡን፡፡ ዳዊትና እኔ ያለፉትን ሰዓታት እርስ በርሳችን በመተዋወቅ ነበር ያሳለፍነው፡፡ በእራት ሰዓት ፒዛ ለመካፈል እንዲያመቸን ጎን ለጎን ተቀመጥን፡፡

ዳዊት የሰዎችን ስሜት በቀላሉ ማንበብ ይችላል፡፡ በጫወታ መካከል የሚነገሩት የተረብ ቀልዶች እንደማያስከፉኝ አውቋል፡፡ ሰዎች ተዝናንተው የልባቸውን ከእኔ ጋር

ሲያወጉያስደስተኛል፡፡ ቁጥብ የሆነ ጫወታ ለማይተዋወቁ ሰዎች እንጂ ለጓደኛሞች አይደለም የሚል እምነት ነበረኝ፡፡

የምግብ ዝርዝሩን እያገላበጥን ሳለን በስላቅ መልክ ወደ እኔ ዞሮ "ነቢል ከቤት ወጥተህ ስለማታውቅ ላንተ የሚሆን ፒዛ እየፈለኩ ነበር ነገር ግን የሜድትራንያን ፒዛ ብቻ ነው ያላቸው፡፡ የመካከለኛው ምስራቅ ፒዛ የላቸውም፡፡"

እኔም የዋዛ አልነበርኩም፡፡ "ነገር ግን ደስ በሚል ሁኔታ ላንተ የሚሆን ነጭ ፒዛ አላቸው፡፡ ሆኖም የሚጣፍጥ አይመስለኝም፡፡"

ዳዊት ሳቁን መቆጣጠር ተሳነው፡፡ "አልተሳሳትክም፡፡ ይህ ትክክለኛ ቦታ ይመስለኛል፡፡ ያንን መፈተሽ የሚቻልበት መንገድ መኖሩን ታውቃለህ?" (ቤቱ የነጮች ቤት መሆኑን)

"አልገባኝም?"

"ቆይ ይህንን ተመልከትማ፡፡" ከዚያ ዳዊት ወደ ኩሽናው በመዞር "ስማ ቶኒ!" ብሎ ተጣራ፡፡

ወዲያውኑ ከምግብ አብሳዮቹ መካከል ሦስቱ ወደኛ ተመለከቱ፡፡ ሁለታችንም ሳቅን፡፡ "ስማ ዳዊት ሌላ ጊዜ እንዲህ ዓይነት ነገር መፈፀም ስትፈልግ ምግባችንን አብስለው እስኪጨርሱ ድረስ ጠብቅ!"

ምሽቱ እንዲህ እያለ ሞቆና ደምቆ ቀጠለ፡፡ በመጨረሻም ወደ ሆቴላችን ስንመለስ አራቱ የቡድናችን ወንድ አባላት ሊጋሯቸው የሚችሉ ሁለት ክፍሎች መኖራቸውን አሰልጣኛችን ነገረን፡፡ እኔና ዳዊት ብዙም አላሳሰበንም ነበር፡፡ ሁለታችን አንደኛውን ክፍል ለመጋራት ወስነን ሄድን፡፡

የተቀሩት የቡድኑ አባላት ወደ ውጪ በመውጣት ለመዝናናት ሄዱ፡፡ አብዛኞቹ አባላት ለመጠጣትና ለጭፈራ በአቅራቢያው ወደሚገኝ መሸታ ቤት ነበር ያቀኑት፡፡ ሌሎቹ ደግሞ የተለያዩ ነገሮችን ለማጨስ አመቺ ቦታ ፍለጋ ተበተኑ፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ነገሮች

ውስጥ ተሳትፌ አላውቅም ነበር፡፡ ወደፊትም እንዲህ ዓይነት ልምምድ ውስጥ የመግባት ሐሳብ አልነበረኝም፡፡ ዳዊትም አብሯቸው ላለመሄድ መወሰኑ አስገርሞኛል፡፡ ከተቀሩት የቡድኑ አባላት የተለየ እንዲሆንና ከእኔ ጋር እንዲመሳሰል ያደረገው ምን እንደሆነ ግራ ገብቶኝ ነበር፡፡

ምክንያቱን ለማወቅ ግን ብዙ መጠበቅ አልነበረብኝም፡፡

ሻንጣዎቼን ስከፋፍት ሳለሁኝ ዳዊት እግሮቹን አጣምሮ ጥግ ላይ በሚገኘው ወንበር ላይ ተቀመጠ፡፡ ከዚያም መጽሐፍ ቅዱሱን በመምዘዝ ማንበብ ጀመረ፡፡

ይህንን ስመለከት የተሰማኝን መገረም ቃላት አይገልፁትም፡፡ ማንም ሰው በትርፍ ጊዜው መጽሐፍ ቅዱስን ሲያነብ አይቼም ሰምቼም አላውቅም ነበር፡፡ ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስን እንደሚያከብሩ አውቃለሁ ነገር ግን በጊዜ ሂደት መበረዙንና እርሱን ማንበብ ጥቅም እንደሌለው ልባቸው እንደሚያውቅ አስብ ነበር፡፡

ዳዊት ክርስቲያን መሆኑን ባወቅሁበት ቅፅበት በተለየ ሁኔታ እንደተታለለ አሰብኩኝ፡፡ በመካከላችን መፈራራት ባለመኖሩ ጥያቄ ጠየቅሁት፡፡

“ስማ ዳዊት” ልብሶቼን ከሻንጣ ውስጥ እያወጣሁ ንግግር ጀመርኩኝ “የወጣለት ክርስቲያን ነህ እንዴ?”

ዳዊት የተገረመ ይመስላል፡፡ “አዎ እንደርሱ ነኝ ብዬ አስባለሁ፡፡”

“መጽሐፍ ቅዱስ መበረዙን ታውቃለህ አይደል?”

“ምን እያልክ ነው?”

“አዎ፡፡ በጊዜ ሂደት ተለውጧል፡፡ ሁሉም ሰው ያንን ያውቃል፡፡”

ዳዊት የተናገርኩት ነገር የተዋጠለት አይመስልም ነገር ግን የበለጠ ለመስማት ጓግቷል፡፡ “እንዴት?”

“ይህ እኮ ግልፅ ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል እስኪ ስንት መጽሐፍ ቅዱሶች እንዳሉ ተመልከት፡፡ ኪንግ ጀምስ ቨርዥን፣ ኒው ኢንተርናሽናል ቨርዥን፣ ዘ ሪቫይዝድ ስታንዳርድ ቨርዥን፣ ዘ ኒው አሜሪካን ስታንዳርድ ባይብል፣ ዘ ኢንግልሽ ስታንዳርድ ቨርዥን፣ የተቀሩት ስንት እንደሆኑ ማን ያውቃል? እግዚአብሔር ምን እንደተናገረ ማወቅ ብፈልግ የትኛውን መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ እንዳለብኝ በምንድነው የማውቀው? ሁሉም የተለያዩ ናቸው፡፡”

“እሺ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ተዓማኒ እንዳልሆነ የምታስበው በዚያ ምክንያት ብቻ ነው?” የዳዊት የተረጋጋ ምላሽ አስደናቂ ነበር፡፡ ሰዎች ብዙ ጊዜ እንዲህ ዓይነት ጥያቄ ሲቀርብላቸው ስሜታዊ ይሆናሉ፡፡

“አይ ሌሎች ብዙ ምክንያቶች አሉኝ፡፡”

“እስኪ ልስማቸው፡፡”

ሻንጣዬን በመዝጋት ሐሳቤን ለመሰብሰብ ሞከርኩኝ፡፡ “ክርስቲያኖች የማይፈልጓቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አውጥተው የጣሉባቸው ጊዜያት ነበሩ፡፡ ደስ ያሰኛቸውንም ነገር ሲጨምሩበት ነበር፡፡”

“ለምሳሌ ያህል ምን ዓይነት ነገር?”

“ትክክለኛውን ጥቅስ አላውቅም ነገር ግን ስለ ሥላሴ መጨመራቸውን አውቃለሁ፡፡ ኋላ ላይ ተቃውሞ ሲገጥማቸው መልሰው አስወገዱት፡፡”

“አ፣ ስለምን እንደምታወራ ገብቶኛል፡፡ ስለ አንደኛ ዮሐንስ አምስት ነው እያወራህ ያለኸው፡፡”

“አንደኛ ዮሐንስ አምስት” ማለት ምን ማለት እንደሆነ ባይገባኝም ቅጥፈት በውስጡ መኖሩን በማመኑ ደስ አለኝ፡፡ “ይህንን ጉዳይ ታውቃለህ ማለት ነው!”

“ስለምን እንደምታወራ ገብቶኛል ነገር ግን በትክክል ያየኸው አይመስለኝም፡፡”

“እንዴት ነው በትክክል ያላየሁት?”

“የመጽሐፍ ቅዱስን ጽሑፎች የሚቆጣጠሩና ስውር ሴራ የሚሸርቡ ሰዎች ያሉ ይመስል ክርስቲያኖች ዝም ብለው የሆነ ነገር እየጨመሩና እየቀነሱ አይደለም፡፡ እስኪ አንድ ሰው የሆነ ነገር መጨመር ፈለገ እንበል፡፡ በዓለም ላይ የሚገኙትን መጽሐፍ ቅዱሶች ሁሉ በአንድ ጊዜ መቀየር የሚችል ይመስልሃል?”

“ሁሉንም መቀየር የሚችል አይመስለኝም፡፡ ነገር ግን በበቂ ሁኔታ መለወጥ የሚችል ይመስለኛል፡፡” ወደ አልጋዬ ሄጄ በዳዊት ትይዩ እየተቀመጥኩኝ የእምነት ቃሌን ሰጠሁ፡፡

“በበቂ ሁኔታ ምን ዓይነት ለውጥ?”

“ጽሑፉን በበቂ ሁኔታ መለወጥ የሚችል ይመስለኛል፡፡”

የተዋጠለት አይመስልም፡፡ “ነቢል በመላው ዓለም የሚገኙት ክርስቲያኖች አንድ ሰው ቅዱስ መጽሐፋቸውን ሲለውጥ ዝም ብለው ይመለከታሉ... ይህ ታላቅ ለውጥ ደግሞ በታሪክ ሳይመዘገብ ዝም ብሎ ይታለፋል  እያልከኝ ነው? ተው እንጂ፡፡”

“በመላው ዓለም ሳይሆን በተወሰነ አካባቢ አንድ ሰው ያንን በተሳካ ሁኔታ መፈፀም እንደሚችል አስባለሁ፡፡”

“ስለዚህ በአንድ አካባቢ መጽሐፍ ቅዱስን የመበረዝ ጥፋት ቢፈፀም በሌላ የዓለም ክፍል ደግሞ ያልተበረዙ መጽሐፍ ቅዱሶችን ማግኘት እንደምንችል አምነሀል ማለት ነው?”

“እንደርሱ ይመስለኛል፡፡”

“በቃ ገብቶሃል” አለ ነገሩን በመጨረስ ስሜት፡፡ “ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎች የመኖራቸውንና የአንደኛዮሐንስ አምስትን ጉዳይ በዚያ መልኩ መረዳት ትችላለህ፡፡”

“እምምም ምን አልክ?” ከዳዊት ጋር የቼዝ ጫወታ እየተጫወትኩ እንዳለሁና በድንገት ወጥመድ ውስጥ አስገብቶኝ “ተበላህ ጓዴ” ያለኝ መሰለኝ፡፡

“በዓለም ላይ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ **የእጅ ጽሑፎች**መኖራቸው እንድናስተያያቸውና ለውጦች የት ጋር እንደተደረጉ እንድናይ ይረዳናል፡፡ ይህ ‹የንባብ ሒስ› የተሰኘ የመጽሐፍ ቅዱስ የጥናት ዘርፍ ነው፡፡ ስለ ሥላሴ የሚናገረው የአንደኛ ዮሐንስ አምስት ዓይነት ለውጥ የሚደረግ ከሆን በቀላሉ ከሌሎች የእጅ ጽሑፎች ጋር በማነጻፀር ለውጡ የት ጋ እንደተደረገ ማወቅ እንችላለን፡፡ በተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎች መካከል የሚገኙትን ዋና ዋና ልዩነቶች በዚህ መልኩ መረዳት ይቻላል፡፡ ነገር ግን የተሳሳተ መረዳት እንዳይኖርህ፡፡ ዋና ሊባሉ የሚችሉት ልዩነቶች በጣም ጥቂት ናቸው፡፡”

**የእጅ ጽሑፎች፡** በእጅ የተጻፉ ጽሑፎች፡፡ ከፊል ወይም ሙሉ ጽሑፎች ሊሆኑ ይችላሉ

“ሌሎች አነስተኛ ልዩነቶችስ?”

“እነዚህ አብዛኞቹ የአተረጓጎም ልዩነቶች ብቻ ናቸው፡፡ የተለያዩ የቁርአን ትርጉሞች አሉ አይደል እንዴ?”

“አዎ ግን ሁሉም የሚጠቀሙት የአረብኛውን ዋና ጽሑፍ ነው፡፡ በእንግዳ ቋንቋዎች የተጻፉ ጽሑፎችን አይደለም የሚጠቀሙት፡፡”

“መጽሐፍ ቅዱስም እደዚያው ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎች መካከል ያሉት ልዩነቶች በአብዛኘው የትርጉም እንጂ በዋናው እብራይስጥና ግሪክ ውስጥ የሚገኙ አይደሉም፡፡”

እነዚህን አዳዲስ መረጃዎች ውጬ ዳዊትን በአዲስ ዕይታ ማየት ጀመርኩኝ፡፡ ይህንን ሁሉ መረጃ ከየት ነው ያገኘው? ከዚህ በፊት ለምን አልሰማኋቸውም? ማመን ተስኖኝ ነበር፡፡

ጥርጣሬዬ አሸንፎ ወጣ፡፡ “ዳዊት አላምንህም፡፡ ይህንን ለራሴ ማየት መቻል አለብኝ፡፡”

ዳዊት ሳቀ፡፡ “መልካም ነው! ይህንን ጉዳይ በጥልቀት ካላየኸው ለኔ ጥሩ ግምት አልሰጠኸኝም ማለት ነው፡፡ ጊዜ ሳታጠፋ መረጃዎችን ማገላበጥ መጀመር ይኖርብሃል፡፡”

ተነስቼ ወደ ሻንጣዬ እየሄድኩኝ “አታስብ፡፡ ከአሁን ጀምሮ ተጀምሯል” አልኩት፡፡

ልብሶቼን አውጥቼ ስጨርስ ለውድድሩ የመጨረሻውን ዝግጅት ማድረግ ጀመርን፡፡ ከአፍታ በኋላ ስለ ውይይታችን ማሰብ ጀመርኩኝ፡፡ አሁንም ድረስ መጽሐፍ ቅዱስ መበረዙን እርግጠኛ ነበርኩኝ ነገር ግን ከዚህ ቀደም ከሰማኋቸው ይልቅ ጠንከር ላሉ ሙግቶች መልስ መስጠት ነበረብኝ፡፡ ወደ ቤት ተመልሼ እነዚህን ነገሮች በጥልቀት ማጥናት እንዳለብኝ ወሰንኩኝ፡፡

ምዕራፍ ሃያ ሁለት

# የጽሑፎች ዝግመተ ለውጥ

ከጥቂት ቀናት በኋላ ወደ ትምህርት ቤት ተመልሰን ትምህርታችንን ቀጠልን፡፡ ዳዊት ሥነ-ሕይወትና ፍልስፍናን ደርቦ የሚያጠና ሲሆን እኔ ደግሞ የቅድመ ሜዲካል ተማሪ ነበርኩኝ፡፡ ከዚህም የተነሳ የኬሚስትሪና የዝግመተ ለውጥ ሥነ-ሕይወት (ኢቮሉሽን ባዮሎጂ) ትምህርቶችን በጋራ እንወስድ ነበር፡፡

አንዳንድ ጊዜ በአንድ ክፍል ውስጥ አብሮ መማር እንዴት ጥሩ ነው፡፡ ዳዊትና እኔ በመረዳዳት መንፈስ ኬሚስትሪን በጋራ እናጠና ነበር፡፡ ነገር ግን በመካከላችን ፉክክር ነበር፡፡ ከፈተና በኋላ መምህራኖቻችን የፈተና ውጤቶችን ሲለጥፉ እኔና ዳዊት ውጤታችንን ለማየት እርስ በርሳችን እንጋፋ ነበር፡፡ ከጓደኝነት ፉክክራችን የተነሳ እኔና ዳዊት ሁል ጊዜ ከክፍሉ ከፍተኛ ውጤት እናስመዘግብ ነበር፡፡

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በአንድ ክፍል ውስጥ አብሮ መማር ጥሩ አይደለም፡፡ በዝግመተ ለውጥ ሥነ-ሕይወት ክፍለ ጊዜ እኔና ዳዊት ትኩረት ሰጥቶ ለመማር እንቸገር ነበር፡፡ አስተማሪዋ በፈጣሪ መኖር እንደማታምን በግልፅ ትናገር ስለነበር አንዳንዴ ጣል በምታደርጋቸው አስተያየቶች ሐሳባችን ከዋናው ትምህርት ላይ ይሰረቅ ነበር፡፡ ጠንካራ አማኞች እንደመሆናችን መጠን አብዛኞቹ የአምላክ የለሾች አስተያየቶች ደካማ ሆነው ይታዩን ነበር፡፡ አስተማሪያችን ለአምላክ የለሽነት ያደላ አስተያየት በሰጠች ቁጥር አንዳችን ወደ ሌላችን ዞረን በተናገረችው ነገር መነሻ ወይም በእርሷ ሁኔታ እንቀልድ ነበር፡፡ መቸስ የኮሌጅ ልጆች እንደመሆናችን መጠን አይፈረድብንም፡፡

አንድ ቀን አምላክ የለሽነትን የሚሰብክ አጭር ንግግር ካደረገች በኋላ ስለ ታክሶኖሚ ማለትም እንስሳትን በዝርያቸው ስለመከፋፈል ማስተማር ጀመረች፡፡ ከዚያ ወደ ዳዊት ጠጋ ብዬ "ከብዙ ጊዜ ጥናት በኋላ የዚህች ሴትዮ ፀጉር የራሱ ሕይወት አለው ብዬ ደምድሜያለሁ፡፡ በየትኛው የሕይወት ቤተሰብ መመደብ እንዳለብኝ እያሰብኩ ነው፡፡"

"ግሩም ሐሳብ ነው ነቢል፡፡ ከጊንጦች ጋር የሚመሳሰል ራስን የመከላለል ዘዴ በዝግመተ ለውጥ ያዳበረ ይመስላል፡፡ ምን ታስባለህ?" የዳዊት አነጋገር ከልቡ ይመስል ነበር፡፡

"ግሩም ዕይታ ነው ዳዊት፡፡ እኔ ሳየው የሆነ የእንጨት ሽበት ዓይነት መስሎ ነበር የታየኝ፡፡ አሁን ስትናገር ግን የሆነ ሕይወት ያለው የሚንቀሳቀስ እንስሳ መሆኑ ገብቶኛል፡፡"

ሁለታችንንም ከገዛ ሳቃችን ጋር ትግል ገጠምን፡፡ እንዲህ ዓይነቶቹ ዋዛ ጫወታዎች ትምህርታችን ላይ እንዳናተኩር ስላደረጉን በመጨረሻ የዝግመተ ለውጥ ትምህርቶችን መውሰድ አቆምኩኝ፡፡

በኮሌጅ ውስጥ በቆየሁ መጠን የዝግመተ ለውጥ መላ ምት በብዙ የትምህርት መስኮች ውስጥ መግባቱን አስተዋልኩኝ፡፡ ባዮሎጂ፣ ሶሲዮሎጂ፣ አንትሮፖሎጂ፣ ተግባቦት፣ ሥነ ልቦናና አልፎ ተርፎ የሃማኖት ጥናቶች የዝግመተ ለውጥ አስተሳሰብ ተፅዕኖ አሳድሮባቸዋል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በተጠቀምኳቸው የሙግት ሐሳቦች ውስጥ እንኳ የዝግመተ ለውጥ ትወራ ይታይ ነበር፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ በጊዜ ሂደት መለወጡንና ሥልጣን ባላቸው ሰዎች ፍላጎት መሠረት መበረዙን እናገር ነበር፡፡ ኋላ ላይ ወንጌላት እንኳ በዝግመተ ለውጥ ሂደት ውስጥ በማለፋቸው ሳብያ የኢየሱስ አምላክነት ከመጀመርያው ወንጌል ጀምሮ እስከ መጨረሻው ወንጌል ድረስ በሂደት እያደገ መምጣቱን መከራከር ጀምሬ ነበር፡፡ በኔ ዕይታ ቀዳሚ የሆነው የማርቆስ ወንጌል ከሌሎች ወንጌላት በላቀ ሁኔታ የኢየሱስን ሰብዓዊነት ያጎላል፡፡አሁን ግን እኔና ዳዊት በመጀመርያው ነጥብ፣ ማለትም በመጽሐፍ ቅዱስ በተለይም በአዲስ ኪዳን ጽሑፍ ወጥነት ላይ አተኩረናል፡፡ እንደ አብዛኞቹ ሙስሊሞች ሁሉ የብሉይ ኪዳን ሁኔታ

የአዲስ ኪዳንን ያህል አያሳስበኝም ነበር፡፡ በኔ ዕይታ ብሉይ ኪዳን በአመዛኙ ከቁርአን ጋር ይስማማል፡፡ ቁርአን የጠቀሳቸውን ብዙ ነቢያት ይጠቅሳል፣ ነቢያት ጣዖታውያንን ለመዋጋት ጦር እንዳዘመቱ ይናገራል፣ ስለ ሥላሴ ደግሞ ምንም ነገር አይጠቅስም፡፡ የሙስሊሞችን እምነት የሚፃረረው አዲስ ኪዳን በመሆኑ በእርሱ ላይ ነበር ትኩረታችን፡፡

አንድ ቀን ከኬሚስትሪ ክፍለ ጊዜ በኋላ ስለ አዲስ ኪዳን የጀመርነውን ውይይታችንን ቀጠልን፡፡ “እሺ ዳዊት፣ ስለ ንባብ ሒስ መረጃዎችን ሳገላብጥ ነበር፡፡ የተወሰኑ ችግሮችንም አግኝቻለሁ፡፡”

“ምን አገኘህ?”

“ሰፋ ያሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ብረዛዎች መሆናቸውን መናገሬ ትክክል ይመስለኛል፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት እንደሚናገሩት የማርቆስ ወንጌል መጨረሻ በዋናው ጽሑፍ ውስጥ የለም፡፡ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የሚገኘውም በምንዝር ስለተያዘች ሴት የሚናገረው ታሪክ በመጀመርያው ጽሑፍ ውስጥ አይገኝም፡፡[35] ኢየሱስ ‹ከናንተ ኃጢአት የሌለበት አስቀድሞ በድንጋይ ይውገራት› ብሎ የተናገረበትን ክፍል ታውቃለህ አይደል?”

“አዎ፣ ያንን ታሪክ አውቃለሁ፡፡ ትክክል ነህ፡፡ በዋናው ጽሑፍ ውስጥ አይገኙም፡፡ ለማለት የፈለከው ምንድነው?”

ይህንን ነጥብ በማመኑ መገረም ያዘኝ፡፡ “ይህ ችግር ሆኖ አይታይህም? የእግዚአብሔር ቃል ያልሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ፡፡”

“ምን ለማለት እንደፈለክ ገብቶኛል ነገር ግን ይህ ችግር ተብሎ የሚወራ አይደለም፡፡ አይታይህም? እነዚህን ጭማሬዎች መለየት መቻላችን በራሱ ለውጦችን ማወቅ መቻላችንን ያሳያል፡፡”

“እውነት ነው ግን መለየት ቻላችሁም አልቻላችሁም መጽሐፍ ቅዱስ ግን መለወጡን ያሳያል፡፡”

“የኋለኞቹን የእጅ ጽሑፎች ለማለት ፈልገህ ከሆነልክ ነህ፡፡ ነገር ግን የኋለኞቹ የእጅ ጽሑፎች ለውጥ ቢገኝባቸው ችግሩ ምንድነው? ሰዎች የኋለኛውን ግልበጣ ከፊተኛው የበለጠ ተዓማኒ አድርገው አይቆጥሩም፡፡ አስፈላጊዎቹ ቀዳሚያን የእጅ ጽሑፎች ናቸው፡፡ እነዚህን ለውጦች ያላካተቱ በርካታ የአዲስ ኪዳን ጽሑፎች ደግሞ በእጃችን ይገኛሉ፡፡”

የተናገረውን ነገር በጥንቃቄ ሰማሁት፡፡ “ቁጥራቸው ስንት ይሆናል? ዕድሜያቸውስ?”

“ከሁለተኛው ክፍለዘመን የሆኑ ብዙ የግሪክ የእጅ ጽሑፎች አሉን፡፡ ከሦስተኛው ክፍለ ዘመንም እንደዛው፡፡ ከአራተኛው ክፍለ ዘመን የመጀመርያ ዓመታት የተገኙ ሁለት ሙሉ አዲስ ኪዳኖች ዛሬ በእጃችን ይገኛሉ፡፡[36] መጽሐፍ ቅዱስ ከአራተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ እስከ ሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ምን ያህል እንደተለወጠ ማወቅ ከፈለክ የእጅ ጽሑፎችን አምጥተህ ማነፃፀር ብቻ ነው የሚጠበቅብህ፡፡”

ይህ ሁሉንም ግራ መጋባት ከክርክሩ ውስጥ ያስወገደ ግሩም መረጃ ነበር፡፡ በትክክል መስማቴን ማረጋገጥ ነበረብኝ፡፡ “ከሦስት መቶዎቹ መጀመርያ የመጡ ሙሉ መጽሐፍ ቅዱሶች አሉን እያልከኝ ነው?”

“አዎ፡፡”

“ዛሬ ከሚገኘው መጽሐፍ ቅዱስ ምን ያህል ይለያሉ?”

ዳዊት ዓይኖቼ ውስጥ አተኩሮ ተመለከተኝ፡፡ “ነቢል በዚህ ዘመን የሚገኙት የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች በነዚህ የእጅ ጽሑፎች ላይ የተመሠረቱ ናቸው፡፡”[37]

የተናገረውን ተቀበልኩት ነገር ግን የተለያዩ ቅጂዎች የመኖራቸው እውነታ ግን አሳሰበኝ፡፡ ይህ ማለት የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት ከስምምነት አልተደረሰባቸውም ማለት

ነው፡፡ “ዳዊት፣ ቀጥተኞቹ ቃላት አስፈላጊ አይደሉም ትላለህ? እንደ ሙስሊም ቁርአን ልክ ለመሐመድ በወረደለት ሁኔታ ተጠብቆ መቆየቱን አምናለሁ፡፡ አንድ ቃል እንኳ አልተለወጠም፡፡[38] አንተ እየነገርከኝ ካለው ነገር የተረዳሁት ቀጥተኞቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት ብዙም አስፈላጊ አይደሉም፡፡”

“ቃላቱ አስፈላጊዎች ናቸው ነገር ግን አስፈላጊ እንዲሆኑ ያደረጋቸው መልዕክት መሸከማቸው ነው፡፡ ዋናው ነገር መልዕክቱ ነው፡፡ ለዚህ ነው መጽሐፍ ቅዱስ ሊተረጎም የሚችለው፡፡ ግልጠተ መለኮቱ ከመልዕክት ይልቅ ከቃላት ጋር የተቆራኘ ቢሆን ኖሮ መጽሐፍ ቅዱስን መተርጎም ባልቻልን ነበር፡፡ መተርጎም ካልቻልን ደግሞ እንዴት ሆኖ ነው ለሁሉም ሰው የሚሆን መጽሐፍ መሆን የሚችለው?”

ዳዊት የኔን የቁርአን ዕይታ እየተገዳደረ መሆን አለመሆኑን እርግጠኛ አይደለሁም ነገር ግን የተናገረው ነገር በጣም ትርጉም ይሰጣል፡፡

የተናገረውን እያሰላሰልኩ ሳለሁ ንግግሩን ቀጠለ፡፡ “ነቢል ትንሽ ወደ ኋላ መለስ ብለን ይህንን ጉዳይ ሰፋ አድርገን መመልከት ያለብን ይመስለኛል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ተመልሶ ሊገኝ በማይችልበት ሁኔታ መበረዙን ነው እየነገርከኝ ያለኸው፡፡ ነገር ግን መጀመርያ ትክክለኛውን ቦታ መናገር መቻል ይኖርብሃል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስድሳ ስድስት መጻሕፍት አሉ፡፡ ስለ የትኛው ክፍል ነው እያወራህ ያለኸው? መቼ ነው የተለወጠው? እንዴት ነው የተለወጠው? ልዩነት ሊያመጣ በሚችልበት ሁኔታ ተለውጧልን?”

በዝምታ ተውጬ ተቀመጥኩኝ፡፡ መምህራኖቼ  ትክክለኛው ቦታ ይህ ነው ብለው አላስተማሩኝም፡፡ ዝም ብለው ብቻ በመደጋገም መጽሐፍ ቅዱስ ተለውጧል እያሉ ነው የሚናገሩት፡፡ መልስ መስጠት አልቻልኩኝም፡፡

“ልዩነት የሚያመጣ ለውጥ እንዳለ የምታስብ ከሆነ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርብሃል፡፡ ግምት ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ ማረጋገጫ ያስፈልግሃል፡፡”

ዳዊት የሚናገረው ነገር ትክክል ቢሆንም ነገር ግን አጣብቂኝ ውስጥ መግባት አልፈለኩም፡፡ “የማርቆስ መጨረሻ፣ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የሚገኘው ታሪክና በአንደኛዮሐንስ አምስት ውስጥ የሚገኘው ስለ ሥላሴ የተጨመረው ክፍል መጽሐፍ ቅዱስ መለወጡን የሚያሳዩ ምሳሌዎች መሆናቸውን ነግሬሃለሁ፡፡”

“በዚህ ዘመን የሚገኝ የትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቅ እነዚህን ክፍሎች እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እንደማይቆጥር ነግሬሃለው፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እንደሆነ በምናስበው ክፍል ውስጥ የሚገኝ ትልቅ ለውጥ የምትለው ነገር ካለ ልታሳየኝ ይገባል፡፡”

ፍልምያዬን ቀጥያለሁ፡- “እስካሁን ድረስ ያላገኘናቸው ልክ እንደነዚህ ያሉ ክፍሎች ቢኖሩስ?”

“ነቢል ይሄ አሁንም ግምት ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ አነጋገር ውኀ የሚቋጥር ሙግት ሊሆን አይችልም፡፡ ማስረጃው የት አለ? በትክክል መናገር ካልተቻለ ባዶ ሙግት ነው፡፡”

እየተረታሁ መሆኔ ግልፅ ነበር፡፡ ዳዊት ዘና ብሎ የመጨረሻ አስተያየቱን ሰነዘረ፡፡ “የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ልክ እንደተጻፉ ነበር መሰራጨት የጀመሩት፡፡ ተደጋግመው በመገልበጥ መጻሕፍቱ በሩቅ ላሉት ክርስቲያኖች ይላኩ ነበር፡፡ ቁጭ ብሎ የሚቆጣጠር አካል በሌለበት እንዴት ሆነው ነው ተመሳሳይ በሆነ ሁኔታ ሳይታወቅ ሊበረዙ የሚችሉት? እንዴት ነው አንድ ሰው ዝም ብሎ ተነስቶ ቃላቱን መበረዝ የሚችለው? ከክርስቶስ በኋላ ብዙ ክፍለ ዘመናት እስኪያልፉ ድረስ በቤተ ክርስቲያን ላይ የበላይነትና ቁጥጥር የነበረው ማንም አልነበረም፡፡ ከዚያ ዘመን በፊት የተጻፉ ብዙ የእጅ ጽሑፎች አሉን፡፡ በዚህ ዘመን ከሚገኘው መጽሐፍ ቅዱስ ጋር ደግሞ ፍፁም ተመሳሳይ ናቸው፡፡ አዲስ ኪዳን እዚህ ግባ ሊባል በሚችልበት ሁኔት መለወጡን የሚያሳይ ምንም ዓነት ሞዴል የለም፡፡ ከታሪክ እውነታዎች ጋር አብሮ ሊሄድ የሚችል ያንን የማሳየት አቅም ያለው ምንም ዓይነት ሞዴል የለም፡፡”

ለጊዜውም ቢሆን እዚህ ጋ እንዲበቃኝ ፈለኩ፡፡ “መልካም፡፡ እስኪ እዚህ ጋ ይቁምና ላሰላስለው፡፡” የዳዊት ንግግር አመለካከቴን አልቀየረውም ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ መለወጡን በፅኑ አምኛለሁና፡፡ ነገር ግን ለኔ ግልፅ ባልሆነልኝ ምክንያት እንዴት እንደሆነ ምንም የማውቀው ነገር አልነበረም፡፡ ጉዳዩን ከእንደገና በጥልቀት ማጥናት ጀመርኩኝ፡፡በመጨረሻም የተለየ መንገድ ለመሞከር ወሰንኩኝ፤ አዲሱ ሙግት መጽሐፍ ቅዱስ ገና ከመሠረቱ ተዓማኒ አልነበረም የሚል ነበር፡፡

# ተዓማኒነትን እንደገና መፈተሽ

ብዙም ሳይቆይ ዳዊት በእማ ግብዣ መሠረት ወደ ቤታችን መጣ፡፡ በሩን ስከፍትለት የመጀመርያ ያደረገው ወደ ሪፍሪጀሬተሩ መሄድ ነበር፡፡ ይህ ደግሞ እናቴን በጣም አሳቃት፡፡ ነፃነቱን በጣም ነበር የወደደችው፡፡

ነገር ግን አፍንጫውን ተጠቅሞ ቢሆን ኖሮ ወደ ሪፍሪጀሬተር መሄድ አያስፈልገውም ነበር፡፡ እማ ለእንግዳ ምግብ ማብሰል በጣም ያስደስታታል፡፡ እንደ ልማዷ ጠረጴዛውን በምግብ ሞልታ አዘጋጅታልን ነበር፡፡ የፍየል ቢርያኒ፣ የበግ ኩርማ፣ የዶሮ መኻኒ፣ የበሬ ኒሐሪ እና ሌላ ለቁጥር የሚያታክት የምግብ ዓይነት አዘጋጅታ ነበር፡፡ በጠረጴዛው ላይ አትክልት ቢኖርም በልቼ ግን አላውቅም ነበር፡፡ለመብላት ስንቀመጥ ዳዊት በደስታ ግራ የተጋባ ነበር የሚመስለው፡፡ ከኒሐሪ ነበር የጀመርነው፡፡ ነገር ግን መቁረጫ ቢላዋ ጠረጴዛው ላይ አልነበረም፡፡ ሮቲ ቂጣ እንዴት በጣት ተቆርሶ በምግብ ተጠቅልሎ እንደሚበላ አሳየሁት፡፡ ዳዊት ቀስ ብሎ መብላት ጀመረ፡፡ ምግቡን ሳያዝረከርክ ልክ እንደ ጥሩ ፓኪስታናዊ በልቶ መጨረሱ እጅግ አስደነቀኝ፡፡በልተን ከጨረስን በኋላ ወደ ሌላ ክፍል ሄደን ሶፋ ላይ ተንጋለን ማውራት ጀመርን፡፡ ዳዊት በወገቡ ተኝቶ ጣርያው ላይ አፍጥጧል፡፡ ኬሚስትሪ አብረን እንድናጠና የመጣ ቢሆንም ነገር ግን ሳይዘጋጅ ድንገት ላጠምደው ፈልጌ ስለ አዲስ ኪዳን ተዓማኒነት እጠይቀው ጀመር፡፡

“እስኪ ለውይይታችን ስል አዲስ ኪዳን አለመለወጡን ልቀበል” በማለት ውይይቱን ከፈትኩት፡፡

ምንም ሳይንቀሳቀስ “ሃሌሉያ” አለ፡፡

“ባይለወጥ እንኳ ያ ተዓማኒ እንዲሆን አያደርገውም፡፡ በሌላ አባባል በውስጡ የተጻፈው ነገር ትክክል መሆኑን እንዴት ነው ማወቅ የምችለው?”

ዳዊት ፈጠን ብሎ ወደኔ ዞረ፡፡ “ነቢል! እንዴት እንዲህ ዓይነት ጥያቄ ትጠይቃለህ? ቁርአን ***ኢንጂል*** የአላህ ቃል መሆኑን ይናገር የለም እንዴ?” ዳዊት የበለጠ እኔን ለመረዳት በመፈለግ እስልምናን ሲያጠና እንደቆየ ግልፅ ነው፡፡ ደግሞም ትክክል ነበር፡፡ የኔ አመለካከት የአዲስ ኪዳን ወንጌላት ኢንጂል መሆናቸውን በሚቀበሉ ብዙ ሙስሊሞች ዘንድ የተለመደ አይደለም፡፡

“ቁርአን በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስለሚገኙት ወንጌላት ስለመናገሩ እርግጠኛ አይደለሁም፡፡ ምናልባት ለኢየሱስ ስለተሰጠና አሁን ግን ስለጠፉ መጽሐፍ ሊናገር ይችላል፡፡” በሙስሊም ተከራካሪዎች ሲነገር የሰማሁትን አመለካከት ነበር ሳስተጋባ የነበረው፡፡

**ኢንጂል፡** ሙስሊሞች ከአለህ ዘንድለኢየሱስ እንደወረደለት የሚያምኑት መጽሐፍ ሲሆን ብዙ ጊዜ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የሚገኙት ወንጌላት እንደሆነ ይታሰባል፡፡

ዳዊት ትኩረት ሰጥቶ ሰማኝ፡፡ “ጥያቄህን እመልሳለሁ ነገር ግን አዲስ ኪዳንን ለመጠራጠር መንገድ እየፈለክ ያለህ ይመስለኛል፡፡ ወደ ኢየሱስ ዘመን የቀረቡት ብቸኛ ወንጌላት በአዲስ ኪዳን ውስጥ የሚገኙት ወንጌላት ናቸው፡፡”

“ቆይ እስኪ፣” ጣልቃ ገባሁ፡፡ ዳዊት ከባድ ነገር ነው በድፍረት እየተናገረ ያለው ስለዚህ መግባባት ይኖርብናል፡፡ “በአዲስ ኪዳን ውሰጥ የሚገኙት ወንጌላት ስለ ኢየሱስ ከተጻፉት መረጃዎች ሁሉ ቀዳሚያን ናቸው እያልክ ነው?”

“አዎ፡፡ ስለ ኢየሱስ የተጻፉት ሌሎች ጽሑፎች ሁሉ በጣም ዘግይተው የመጡ ናቸው፡፡”

“ሌሎች ብዙ ወንጌላት መኖራቸውንና እነዚህ ክርስቲያኖች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለማካተት የመረጧቸው ብቻ መሆናቸውን ሰምቻለሁ፡፡”

“ሌሎች ወንጌላት ነበሩ ነገር ግን በጣም ዘግይተው ከሁለተኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ በኋላ የመጡ ናቸው፡፡ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የሚገኙት አራቱም ወንጌላት ከኢየሱስ በኋላ በአንደኛው ክፍለ ዘመን የተጻፉ ናቸው፡፡ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ከመረጠችባቸው ምክንያቶች መካከል አንዱ እርሱ ነው፡፡”

አሁንም ክርክሬን ቀጠልኩኝ፡፡ “ግን ኢንጂል ለኢየሱስ የተገለጠ ሌላ ወንጌል ቢሆንና ከእርሱ ሞት በኋላ ጠፍቶ ቢሆንስ?”

“ነቢል ይህ ሐሳብ ሁለት ትልልቅ ችግሮች አሉበት፡፡ መጀመርያ ተራ ጥርጣሬ ነው፡፡ ማስረጃ ከሌለ እንዲህና እንዲያ ቢሆንስ ማለት ሙግት አይደለም፡፡ ሁለተኛ እንደምታውቀው ቁርአን ክርስቲያኖች በወንጌል እንዲፈርዱ ይነግራቸዋል፡፡[39] ያ ማለት በመሐመድ ዘመን እንኳ በእጃቸው ይገኛል ማለት ነው፡፡ እንጂል የጠፋ መጽሐፍ አይደለም፡፡”

መልስ ለመስጠት ሞክሬያለሁ ነገር ግን ሙግቴን እንዴት ተቀባይነት እንዲኖረው ማድረግ እንደምችል ምንም አልታይህ አለኝ፡፡ የእርሱን ሙግት ባሰብኩኝ ቁጥር የበለጠ በአፌ ውስጥ እየጎመዘዘኝ መጣ፡፡ ቅድም የበላሁት ጣፋጭ ምግብ ጣዕም እንኳ ጠፍቶብኛል፡፡

ዳዊት ቀጠለ፡፡ “እንደ ምክንያታዊ ተመራማሪዎች ስለ ኢየሱስ ሕይወት ማወቅ የምንፈልግ ከሆነ ወደ ወንጌላት መሄድ ያስፈልገናል ምክንያቱም ትክክል ሊሆኑ የሚችሉት እነርሱ ናቸውና፡፡ ሌላ ምን አማራጭ ይኖረናል?”

ይህንን ነጥብ ይገፎ ተነሳሁ፡፡ “የተሻሉ ቢሆኑም እንኳን ጥሩ ናቸው ማለት ግን አይደለም፡፡”

“እውነት ነው ግን እነዚህ መጻሕፍት የተጻፉት ከኢየሱስ ስቅለት በኋላ ጥቂት ዘግይተው ነው፡፡ በወቅቱ ደቀ መዛሙርቱ በሕይወት ነበሩ፡፡ ይህ ደግሞ ከሌሎች ብዙ ግለ ታኮች የተሻሉ ያደርጋቸዋል፡፡ ለምሳሌ ያህል ዋና የሚባለው የታላቁ እስክንድር ግለ ታሪክ

የተጻፈው ከእርሱ ህልፈት በኋላ 400 ዓመታትን በመዘግየት ነበር፡፡[40] ስለ እስክንድር እንደምናውቅ በመተማመን መናገር ከቻልን ስለ ኢየሱስ ደግሞ እጅግ በጣም እንደምናውቅ መናገር እንችላለን፡፡"

"ልክ ነህ ግን ከሌሎች ግለ ታሪኮች የተሻለ መሆን ማለት ወንጌላት ተዓማኒዎች ናቸው ማለት አይደለም፡፡"

"ያልኩት ነገር አልገባህም፡፡ ወንጌላት ሌሎች ግለ ታሪኮች ለተተራኪዎቻቸው በዘመን ከቀረቡት በላይ ለኢየሱስ ዘመን የቀረቡ በመሆናቸው ብቻ አይደለም ከሌሎች ግለ ታሪኮች የተሻሉት ነገር ግን በጣም የቀረቡ ከመሆናቸው የተነሳ የዓይን ምስክሮች በወቅቱ በሕይወት ስለነበሩም ጭምር ነው፡፡ ወንጌላት በወቅቱ በክርስቲያን ማሕበረሰቦች መካከል እንደመዘዋወራቸው መጠን የዓይን ምስክሮች ይሰሟቸዋል፡፡ ምስክርነታቸውንም ያክሉባቸዋል፡፡"

ፈገግ አልኩኝ፡፡ "ዳዊት ያ ግምት ይመስለኛል፡፡ ማስረጃው የት አለ?"

"የቀደሙት የቤተ ክርስቲያን አባቶች አሁን የተናገርኩትን ዘግበውልናል፡፡ 100 ዓ.ም. አካባቢ ሲጽፍ የነበረው ፓፒያስ የተሰኘ ጸሐፊ የማርቆስ ወንጌል በጴጥሮስ የዓይን ምስክርነት ዘገባ ላይ የተመሠረተ መሆኑን ጽፎልናል፡፡[41] የዓይን ምስክሮች በወንጌላት ላይ የራሳቸውን አስተዋፅዖ ማከላቸው ከግምት ያለፈ ነው፡፡ በእነርሱ የተዘጋጁ መሆናቸው በታሪክ ሰፍሮልናል፡፡"

"ሉቃስስ?"

"ሉቃስ የጳውሎስ ወዳጅና አብሮ ተጓዥ ስለነበር ደቀ መዝሙር አልነበረም፡፡ ነገር ግን በወንጌሉ መግቢያ ላይ የዓይን ምስክሮችን መጠየቁን ነግሮናል፡፡ አብዛኛው እርሱ የጻፈው ነገር ደግሞ ከማርቆስና ከማቴዎስ ወንጌላት ጋር የሚስማማ መሆኑ ይህንን ያረጋግጥልናል፡፡"

ይህ ደካማ ሙግት ይመስላል፡፡ "አላውቅም፡፡ ሉቃስ የዓይን ምስክር አለመሆኑን አምነሃል፡፡ ይህ ደግሞ ችግር የሚያስከትል ይመስለኛል፡፡ በተጨማሪም በወንጌሉ ውስጥ ብዙ ታሪካዊ ስህተቶች መኖራቸውን ሰምቻለሁ፡፡"

ዳዊት መልስ አዘጋጅቶ ነበር፡፡ "ሉቃስ ብዙ ታሪካዊ ግብአቶችን ሰጥቶናል ይህ ማለት ሰዎች ትክክለኛነቱን እንዲመረምሩ ዕድል ሰጥቷል ማለት ነው፡፡ ነገር ግን የከርሰ ምድር ጥናቶችን የበለጠ ስንፈትሽ ትክክል መሆኑ ይበልጥ ይረጋገጣል፡፡ ለምሳሌ ያህል ሉቃስ 3፡1 ላይ ሊሳንዮስ  የሳቢላኒስ የአራተኛው ክፍል ገዥ እንደነበረ መጻፉስህተት እንደሆነ ብዙ የታሪክ ተመራማሪዎች ደምድመው ነበር፡፡ ሊሳንዮስ ከሃምሳ ዓመታት በፊት እንደኖረና ሉቃስ በስህተት በክርስቶስ ዘመን መኖሩን እንደጠቀሰ ተናግረው ነበር፡፡ ክርስቲያን ሊቃውንት ምናልባት ሁለተኛ ሊሳንዮስ ይኖር ይሆናል የሚል ግምት ቢያስቀምጡም ለዘብተኛ ሊቃውንት ግን ዓቃቤ እምነታዊ ግምት ብቻ እንደሆነ በመደምደም ውድቅ አድርገውት ነበር፡፡

"የከርሰ ምድር ተመራማሪዎች ሲቆፍሩ ሳሉ በክርስቶስ ዘመን የተጻፈ ዳግማዊ ሊሳንዮስ የሳቢላኒስ ገዥ እንደነበረ የሚናገር ጽሑፍ አገኙ፡፡ ይህ ደግሞ ሉቃስ ተዓማኒ የሆነ የጥንታዊ ታክ ምንጭና ለዘብተኛ ሊቃውንት ደግሞ እርሱን ለመተቸት በጣም ፈጣኖች መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡"

ይህ ለኔ አዲስ ዜና ነበር፡፡ ደግሞም በጣም አስደናቂ ነው፡፡ ነግር ግን ለራሴ እንኳ ቢሆን ወንጌላት ተዓማኒ መሆናቸውን ማመን አልፈለኩም ነበር፡፡ ዕድሜ ልኬን ሊታመኑ እንደማይችሉ ተምሬያለሁ ስለዚህ አስተማሪዎቼ መሳሳታቸውን ማመን ለኔ በጣም አሳፋሪ ነው፡፡ ስለዚህ መግፋቴን ቀጠልኩኝ፡፡ "ዳዊት ስለዚህ ሁሉ ነገር እርግጠኛ መሆን እንችላለን? ማለቴ እነዚህን ጽሑፎች አላየኋቸውም፡፡ ባያቸውን እንኳን ትክክለኛነታቸውን ማረጋገጥ አልችልም፡፡ በዚያ ላይ ደግሞ የቤተ ክርስቲያንን መረጃ ምን ያህል ማመን እንደምችል አላውቅም፡፡ ሚዛናዊ አይደሉም፡፡ እንድጠራጠር የሚያደርጉኝ ብዙ ምክንያች አሉ፡፡"

እንደዚህ ማለቴ ዳዊትን ያበሳጨው ይመስላል፡፡ “እየውልህ ነቢል፣ ኢፒስቲሞሎጂ ተምረሃል፡፡ መጠራጠር ከፈለክ ይህንን ውይይት ማድረጋችንን፤ ከነ ጭራሹምበሕይወት መኖራችንን እንኳ ልትጠራጠር ትችላለህ! እንደ *ማትሪክስ* ነው፡፡ በመስታወት ሳጥን ውስጥ የተቀመጥን በእብድ ሳይንቲስቶች የሚያነቃቁ ንጥረ ነገሮች እየተጨመሩልን ያለን አንጎሎች ልንሆን እንችላለን፡፡ ይህ እውነት አለመሆኑን ማረጋገጥ አትችልም፡፡

“ስለዚህ ተጠራጣሪ መሆን በምትፈልገው ልክ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ የፈለከውን ያህል ተጠራጣሪ ሁን ነገር ግን ሁለት ሚዛኖችን አትጠቀም፡፡ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን ያህል ተጠራጣሪ ከሆንክ ቁርአንን ስንመለከት የዚያኑ ያህል ተጠራጣሪ ስትሆን ማየት እፈልጋለሁ፡፡”

እምነቴ ተግዳሮት ሊገጥመው እንደሆነ ፍንጭ ሳይ ነቃ አልኩኝ፡፡ “ቁርአን ከፍተኛውን የጥርጣሬ ደረጃ ማስተናገድ ይችላል ዳዊት፡፡ ቁርአን አለመለወጡንና በቀጥታ ከአላህ ዘንድ በመሐመድ በኩል መምጣቱን በቀላሉ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡”

ዳዊት እንዲህ በማለት መለሰ፣ “ነቢል፣ ዛሬ ባሳየኸው የጥርጣሬ ጥልቀት የትኛውንም እምነት ለመያዝ መቻልህን እርግጠኛ አይደለሁም፡፡ እዚያ ስንደርስ የምናየው ይሆናል ነገር ግን አሁን ስለ ዕድል መጠን እያወራን እንዳለን ገብቶህ ይሆን? በእውኑ ዓለም ላይ እርግጠኛነት የሚባል ነገር የለም፡፡”

“አዎ እውነት ነው፡፡”

“መልካም፡፡ ስለዚህ ወንጌላት ከየትኛውም በእጃችን ከሚገኝ መረጃ ይልቅ ስለ ኢየሱስ ታሪክ የሚነግሩን ተዓማኒ ምንጮች መሆናቸውን ተስማምተናል ማለት ነው፡፡ ቢያንስ ከዚ ጋር መስማማት ትችላለህ?”

በልቤና በአእምሮዬ መካከል ገደል ሲፈጠር ተሰማኝ፡፡ እኔ ማመን የምፈልገው ከአዲስ ኪዳን ማስረጃዎች ጋር ጦርነት መግጠሜን ብቻ ነው፡፡ ጭንቀት ውስጥ ገባሁኝ፡፡

ትኩረት ለማስለወጥ አስቤ ወደ ኬሚስትሪ የቤት ሥራችን ዓይኔን ጣል አደረኩኝ፡፡ የቤት ሥራው ስለ ኤሌክትሮኔጌቲቪቲ እና መግነጢሳዊ ጉልበት ነበር፡፡ “ሃይማኖት እንደ ሳይንስ አለመሆኑ በጣም ያሳዝናል፡፡ እንደርሱ ቢሆን ኖሮ የትኛው መንገድ ትክክል መሆኑን በቤተ ሙከራ ውስጥ ማረጋገጥ በቻልን ነበር፡፡”

“እንጃ ብቻ ነቢል፡፡ ሳይንስ እንኳ ሳይቀር በምልከታና የተሻለ በሚባለው ማብራርያ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ሁል ጊዜ መቶ በመቶ እርግጠኛ መሆን አይቻልም፡፡ እየተወያየን ያለነው ርዕሰ ጉዳይ እንኳ የተለየ አይመስለኝም፡፡”

አፍጥጬ ተመለከትኩት፡፡ “ዝም ብለህ ለክርክር ስትል ነው ይህንን እያልክ ያለኸው! በእያንዳንዱ ነገር ላይ ከኔ የተለየ አቋም መያዝ ትፈልጋለህ አይደል?”

ዳዊት ሳቀ፡፡ “ባልነግርህ ደስ ይለኛል ግን ከዚህ አባባልህም ጋር ቢሆን አልስማማም! ለአሁን እስኪ ላለመስማማት እንስማማ፡፡” በአዎንታ ራሴን ነቅንቄ ወደ ኬምስትሪ የቤት ሥራችን አመራን፡፡

በእውነቱ ከሆነ በውስጠኛው አእምሮዬ ዳዊት ከተናገራቸው ነገሮች ጋር ተስማምቼ ነበር፡፡ መረጃዎቹ ትክክል ከሆኑ ሙግቶቹ ትርጉም ይሰጣሉ፡፡ ነገር ግን አልተቀበልኳቸውም ምክንያቱም ዋጋ ያስከፍሉኛልና፡፡ ወላጆቼና መምህራኖቼ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የነገሩኝ ነገሮች ሁሉ ስህተት መሆናቸውን ማመን ነበረብኝ ነገር ግን በጣም ቅኖችና አምላካቸውን ከልባቸው የሚፈልጉ ሰዎች ናቸው፡፡ ሊሳሳቱ ይችላሉን? ስለዚህ የዳዊት ሙግቶች ትርጉም እንደሚሰጡ አልነገርኩትም፡፡ እውነቱን ለመናገር ለራሴ እንኳን የማመን ፍላጎት አልነበረኝም፡፡

*ዳንኤል ቢ. ዋላስ በዳላስ ቲዎሎጂካል ሴሚነሪ የአዲስ ኪዳን ጥናቶች ፕሮፌሰርሲሆኑ የአምስት የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ዋና አርታኢ እና አማካሪ ናቸው፡፡በእሳቸው የተዘጋጀውን የሊቅ አስተዋፅዖ ለማንበብcontributions.NabeelQureshi.com ይጎብኙ፡፡*

ክፍል ፬

# ዋናው ነገር

*መብላት፣ መድከም፣ ማላብ፣ መድማት እና በመጨረሻም በመስቀል ላይ መቸንከር፡፡ ይህንን ማመን አልቻልም፡፡ አምላክ ከዚህ ጋር ሊነፃፀር የማይችል ክብር ነው የሚገባው፡፡*

ምዕራፍ ሃያ አራት

# የሊትመስ ወረቀት ፈተና

በሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት ውስጥ ከአዲዬ ጋር በጥልቀት መላመድ ችዬ ነበር፡፡ ብዙ ተቋማትንና የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን በመቀላቀል ጥሩ የኮሌጅ ልምድ ለመቅሰም ሞክሬያለሁ፡፡ በብዙ ክበባት ውስጥ ከመሳተፌም በላይ የምርምር ቡድን ፕሬዚዳንት በመሆን ከተማሪዎች መማክርት ቢሮ ጋር ሆኜ ልምምዶችን የመከታተልና የሕዝብ ግንኙነት ሥራዎችን እሠራ ነበር፡፡ በተማሪዎች ቅበላ ቢሮ ውስጥም *የፓወር ፖይንትጽሑፎችን* በማዘጋጀትና አስጎብኚዎች በሌሉበት የእነርሱን ቦታ በመሸፈን አገለግል ነበር፡፡ ከመደበኛ ትምህርት ውጪ ባሉት ተግባራት ላይ በስፋት ከመሳተፌ የተነሳ ብዙ ጥሩ ጓደኞችን ማፍራ የቻልኩ ሲሆን አንድም ቀን ብቸኝነት ተሰምቶኝ አያውቅም ነበር፡፡

ነገር ግን በኮሌጅ በነበርንባቸው ዓመታት ዳዊትና እኔ ምርጥ ጓደኛሞች መሆናችን ጥርጥር የለውም፡፡ ትምህርት በሌለበትና ሥራ በምፈታበት ሰዓት ወይንም ምሳ መብላት ስፈልግ ቀድሜ የምጠራው ሰው ቢኖር ዳዊትን ነበር፡፡ አብረውኝ ወዲያ ወዲህ የሚሉ ጥሩ ጥሩ ጓደኞች ቢኖሩኝም እንደ ዳዊት ግን በጥልቀት የተቆራኘሁት ሰው አልነበረም፡፡ ቅርርባችን ከጓደኝነት አልፎ ከቤተሰባዊነት እንኳ የጠለቀ ሆኖ ነበር፡፡

ቅርርባችን ዳዊትና እኔ አብዛኛውን ጊዜያችንን በሳይንስ ሕንፃ ውስጥ ወይንም ደግሞ በኪነ ጥበብ ሕንፃ ውስጥ እንድናሳልፍ ረድቶናል፡፡ በተደጋጋሚ የምንገናኝ ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ ጠዋት ጠዋት የሚሰጠው የሳንይንስ ክፍለ ጊዜ ሲያልቅ እንወጣና ወደ ሌሎች ክፍሎች ተጠባብቀን እንሄዳለን፡፡

ከእንዲህ ዓይነት አጋጣሚዎች መካከል አንዱ የኬሚስትሪ የቤተ ሙከራ ጊዜ ነበር፡፡ ዳዊትና እኔ ልምምዱን በተለያዩ ክፍሎች ውስጥ የምንሰራ ሲሆን የደረስንበትን ግኝት እንለዋወጣለን፡፡ የሠራነውን አጋነን በመናገር ጀምረን ኋላ ላይ አንዳችን ከሌላችን ጋር በመፎካከር መንፈስ የምንፈጥረው የጉረኝነት ትረካ ጥግ አልነበረውም፡፡

አንድ ቀን አሲድና ቤዝ እንዴት መለየት እንደሚቻል የሚያሳይ አስደናቂ ሙከራ ሰራሁኝ፡፡ ይህንን ርዕስ በጣም ነበር የምወደው፡፡ ምናልባት የምናሳየውን ለውጥ በየጊዜው ማየት ስለምንችል ሊሆን ይችላል፡፡ በመለየቱ ሂደት መካከል  ፈሳሹ አሲድ ይሁን ቤዝ መለየት ካልቻልን የሊትመስ ወረቀቶችን ውስጡ መንከር ብቻ ነው የሚጠበቅብን፡፡ ወረቀቱ ፒንክ ሆኖ የሚወጣ ከሆነ አሲድ ነው፡፡ ወረቀቱ ወይንጠጃማ ሆኖ ከወጣ ቤዝ ነው፡፡ የሊትመስ ወረቀቱ ሙከራችን በትክክል እየሄደ መሆን አለመሆኑን በቀላሉ ያሳውቀናል፡፡

ከቤተ ሙከራው ክፍለ ጊዜ በኋላ ከፊት ለፊት ከነበረው መናፈሻ ውስጥ ሆኜ ዳዊትን መጠበቅ ጀመርኩኝ፡፡ አርፍዷል፡፡ በመጨረሻም ከሕንፃው ወጥቶ ሲመጣ፤ ጊዜ ሳላጠፋ የሰራሁትን እነግረው ጀመር፡፡

“ሰውየው፣ ዛሬ ሙከራዬን ለማጠናቀቅ አሥራ አምስት ደቂቃ ብቻ ነበር የፈጀብኝ፡፡ የሊትመስ ወረቀት እንኳ አላስፈለገኝም ነበር፡፡ አየት አደረኩትና ብቻ *ቡም!* ጨረስኩት፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ይኸው እዚህ ተጎልቼ ስጠብቅህ ነበር፡፡”

“እውነትህን ነው? እኔ ደግሞ ወደ ቤተ ሙከራው ስገባ የአሲድና የቤዝ ጠርሙሶችን አገኘሁ ከዚያ ጎን ለጎን አስቀመጥኳቸውና እንዲቀላቀሉ በአፌ ብቻ አዘዝኳቸው፡፡ ከዚያ በፍርሃት እየተርበተበቱ ታዘዙኝ፡፡ ስለዚህ ለመጨረስ አንድ ደቂቃ ብቻ ነበር የፈጀብኝ፡፡”

“ሁ ሁ፡፡ ታዲያ ለምን አረፈድክ?”

“ለፕሮፌሰሮቹ በሙሉ ፊርማዬን ለማኖር ወደ አንድ ሰዓት ገደማ ፈጀብኝ፡፡”

“ለዚያ ነው ያረፈድከው?”

“አዎ፣ ለዚያ ነው ያረፈድኩት፡፡”

ቦርሳዬን አንጠልጥዬ ወደ ኪነ ጥበብ ሕንፃ መራመድ ጀመርን፡፡ የኬሚስትሪ ክህሎቱ የማን እንደሚበልጥ ለማሳየት የተጋነኑ ታሪኮችን ፈጥረን እያወራን የቤተ መጻሕፍት ትልልቅ የመስታዎት መስኮቶችንና በዜና ማሰራጫ ሕንፃው ስር በዝግታ የሚፈሱ ፏፏቴዎችን አልፈን አጭሯን መንገድ ጨረስናት፡፡

በቀልዱ መካከል ዝምታ ሲመጣ የዳዊት ፊት ቀስ በቀስ የቁምነገር መልዕክት ማስተላለፍ ጀመረ፡፡ አንድ ያሳሰበው ጉዳይ መኖሩን ተገነዘብኩ፡፡ የጓደኛዬ ሐሳብ የኔም ሐሳብ በመሆኑ ቀልዱን ትቼ ቁምነገር ለማውራት ራሴን አዘጋጀሁ፡፡

“ስማ ዴቭ፣ ምን እያሰብክ ነው?”

“የሆነ ነገር እያሰብኩ ነው፡፡ ሐሳብህን ማወቅ እፈልጋለሁ ግን በቅንነት እንድትመልስልኝ እፈልጋለሁ፡፡”

ዳዊት ብዙ ጊዜ እንደዚህ አያወራም ስለዚህ ትኩረት ሰጠሁት፡፡ “እሺ ሰውየው፡፡ ምንድነው እሱ?”

“አሁን በኬሚስትሪ ማን እንደሚበልጥ እየተፎካከርንና እየተቃለድን ነው፡፡ ምንም ትርጉም የሌለው ቀልድ ነው፡፡ በተሳሳተ መንገድ እንዳትረዳኝ፡፡ ራሳችንን ዘና እያደረግን ነው፡፡ ያ ደግሞ ጥሩ ነው፡፡ የምንፈልገው ሳቅ ሲሆን ክርክሩ ግን እርባና የለውም፡፡”

ራሴን በአዎንታ ነቀነኩ፡፡

“ስለ መጽሐፍ ቅዱስና ስለ ክርስትናም ስናወራ አስደሳች ነው ነገር ግን ዝም ብለን አንዳችን ሌላችንን ለመርታት እየተፎካከርን እንዳይሆን እሰጋለሁ፡፡ እያልኩ ያለሁት ገብቶሃል? ስለ እምነት እያደረግናቸው ያለናቸው ውይይቶች ከቀልድ የዘለሉ መሆን አለመሆናቸው ያሳስበኛል፡፡”

“ምን ማለትህ ነው? በእርግጥ ከቀልድ ያለፉ ናቸው፡፡”

“እንዲህ ብዬ ላስቀምጠው፡፡ እስኪ ክርስትና እውነት ነው እንበል፡፡ ለአፍታ ኢየሱስ አምላክ መሆኑን፣ በመስቀል ላይ ስለ ኃጢአትህ መሞቱንና ከሙታን መነሳቱን እውነት ነው ብለህ አስብ፡፡ ይወድሃል፣ በሕይወት ዘመንህም ሁሉ እርሱን እየተከተልክ ስለ እርሱ እየመሰከርክ እንድትኖር ይፈልጋል፡፡”

“እሺ እያሰብኩ ነው፡፡ ለኔ ከባድ ነው ግን እየሞከርኩ ነው፡፡”

“ጥሩ፡፡ ክርስትና እውነት ቢሆን ለማወቅ ዝግጁ ነህ?”

“ይቅርታ፣ ምን አልክ?” ምን እየጠየቀ እንደሆነ አልገባኝም ነበር፡፡

“ክርስትና እውነት ቢሆን ማወቅ ትፈልጋለህ?”

“ለምንድነው የማልፈልገው?”

“ብዙ ምክያቶች ይኖራሉ፡፡ ለምሳሌ ያህል ይህን ሁሉ ዓመታት ተሳስተህ እንደነበር መቀበል ይኖርብሃል፡፡ ያንን ማድረግ ደግሞ ቀላል አይሆንም፡፡ ሕይወትህን በሙሉ ወደ ኋላ መለስ ብለህ በመቃኘት ስለ እግዚአብሔርና ስለ ሃይማኖት እንደምታውቅ ስታስባቸው የነበሩትን ነገሮች ሁሉ ማጤን ያስፈልግሃል፡፡ ይህ ደግሞ ከባድ ነው፡፡ ያንን ማድረግ ለኔም ቢሆን ቀላል አይሆንም፡፡”

ወዲያውኑ መልስ አልሰጠሁም ግን ከዳዊት ጋር በቀስታ እርምጃ ማዝገሜን ቀጥያለሁ፡፡

ወደ ኪና ጥበብ ሕንፃ በተጠጋን ቁጥር እጅብ ብለው የነበሩት እፅዋት መጠናቸው እየሳሳ ይሄዳል፡፡ ከጥላዎቹ ውስጥ ስንወጣ ቦርሳዎቻችንን አስቀምጠን ፏፏቴው አጠገብ አረፍ አልን፡፡ በዳዊት ላይ አሻግሬ ውኃውን ተመለከትኩት፡፡

ዝምታ ከነገሰበት ቆይታ በኋላ “አዎን እና አይደለም” በማለት መልስ ሰጠሁ፡፡

ዳዊትን ተመለከትኩት፡፡ ማብራርያ እየጠበቀ ነበር፡፡

“አዎ ማወቅ እፈልጋለሁ ምክያቱም እውነትን ማወቅና ፈጣሪዬን መከተል እፈልጋለሁና፡፡ ደግሞም ማወቅ የማልፈልግበት ምክንያት ቤተሰቤን ስለሚያሳጣኝ ነው፡፡ በዓይነ ቁራኛ የሚጠብቁትን ልጃቸውን ያጣሉ፡፤ በማሕበረሰቡም መካከል ያላቸውን ከበሬታ ያጣሉ፡፡ ክርስቲያን ብሆን ቤተሰቤን ያጠፋል፡፡ ያንን ደግሞ ተቋቁሜ መኖር መቻሌን እርግጠኛ አይደለሁም፡፡ ይህንን ሁሉ ዋጋ ከከፈሉልኝ በኋላ? በፍፁም፡፡”

ከባድ ፀጥታ ሰፈነ፡፡ ከፏፏቴው ድምፅ በስተቀር የሚሰማ ነገር አልነበረም፡፡ በዝምታ እየተያየን ቆምን፡፡

በመጨረሻ ዳዊት ጥያቄ ጠየቀ፡፡ “ስለዚህ ማን የሚያሸንፍ ይመስልሃል? እግዚአብሔር ወይንስ ያንተ ቤተሰብ?” አስቸጋሪ ጥያቄ ቢሆንም መልስ ሰጠሁ፡፡

“እግዚአብሔር፡፡”

እየተናገርኩ እያለሁ የእምቢተኝነት ስሜት ሲወረኝ ተሰማኝ፡፡ እንደ መንቃት ብዬ ወደ ዳዊት ዞርኩኝ፡፡ “እነዚህ ሁሉ ነገሮች ምንም ትርጉም የላቸውም፡፡ ክርስትና እውነት አይደለም፡፡ እውነት እስልምና ነው፡፡ እውነት መሆኑ ሲገባህ ለመቀበል ዝግጁ ነህ ዳዊት?”

ዳዊት ትክ ብሎ ተመለከተኝ፡፡ “ነቢል፣ አሁን ደግመህ ያንኑ እየፈፀምክ ነው! ይቅርታ አድርግልኝና ስለ እምነቶቻችን ስንነጋገር በቅንነት እውነትን መፈለግ ሳይሆን ሙግቶችን በግትርነት የማሸነፍ ፍላጎት ይታይብሃል፡፡ ክርስትና ውሸት ነው ብለህ አስቀድምህ የወሰንክ ትመስላለህ፡፡”

ሌላ ሰው እንደዚህ ቢናገረኝ ኖሮ ውይይቱን አቋርጬ እሄድ ነበር፡፡ ነገር ግን አሁን እያወራሁ ያለሁት ከምርጥ ጓደኛዬ ጋር ነው፡፡ እርሱ ደግሞ እንደሚያስብልኝ አውቃለሁ፡፡ ንግግሩን በጥንቃቄ ሰማሁት፡፡

“ምናልባት ትክክል ልትሆን ትችላለህ፡፡ ክርስትና እውነት ሊሆን የሚችልበት ዕድል መኖሩን እንኳ አላምንም፡፡”

“ለምን ነቢል? በውይይቶቻችን ወቅት አቋምህን እንኳ መከላከል አልቻልክም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ በጊዜ ሂደት እንደተለወጠ ታምን ነበር ነገር ግን ያንን መከላከል አልቻልክም፡፡ ሲጀመር ተዓማኒ እንዳልሆነ ደግሞ ማመን ጀመርክ፡፡ እርሱንም መከላከል አልቻልክም፡፡”

“ምናልባት እነዚህን ጉዳች በሚገባ ስላልተማርኳቸው ሊሆን ይችላል፡፡ እኔ ሊቅ አይደለሁም፡፡ መልሶችን ሁሉ አላውቅም፡፡” ይህንን መናገሬ የተደበቀ እውነታን ገሃድ አውጥቷል፡፡ አስተዳደጌ እንደ ምዕራባዊ ቢሆንም በምስራቃውያን የሥልጣን መሠረት ላይ የተገነባ ነበር፡፡

ዳዊት አሁንም በማስተዋል ሆኖ መናገሩን ቀጥሏል፡፡ “ክርስትና እውነት ሊሆን እንደሚችል ማሰብ እንድትጀምር ምን መሆን አለበት?”

መልስ ከመስጠቴ በፊት በዚህ ጉዳይ ላይ ለአፍታ አሰብ አደረኩኝ፡፡ “ስለ ሃይማኖት ያስተማረኝ አባቴ ነው፡፡ ከኔ እጅግ የላቀ ዕውቀት አለው፡፡ እርሱ እንኳ ተቃውሞዎችን መመለስ እንደማይችል ካየሁኝ ነገሮችን የበለጠ በጥንቃቄ ማየት እጀምራለሁ፡፡”

“ከዝያ ክርስትና እውነት ሊሆን የሚችልበት ዕድል መኖሩን ማሰብ ትጀምራለህ ማለት ነው?”

“አዎ፣ እድል ብቻ፡፡”

ዳዊት በዚህ ጉዳይ ላይ አተኮረ፡፡ “አባትህ ለውይይት መምጣት የሚችል ይመስልሃል?”

“አዎ” ሳላቅማማ መለስኩኝ፡፡

“በወር አንድ ጊዜ በቤቱ ጉባኤ የሚያደርግ ማይክ የተባለ ጓደኛ አለኝ፡፡ የተለያየ አመለካከት ያላቸው ሰዎች ተሰብስበው ስለ እምነት ይወያያሉ፡፡ ጉባኤዎቹን

‹የራዕይቡድን ጉባኤዎች› ብለን ነው የምንጠራቸው፡፡ ከአባትህ ጋር ውይይት ለማድረግ ፍቃደኛ እንደሚሆን አውቃለሁ፡፡ የሚቻል ይመስልሃል?"

"አዎ በደንብ ይቻላል፡፡ አባቴን እጠይቀዋለሁ ግን ችግር ያለበት አይመስለኝም፡፡ በቃ ግብዣውን እንደተቀበለ ቁጠር፡፡"

"እሺ መልካም፡፡ ውይይታችን ፈር የለቀቀ እንዳይሆን ርዕስ እንምረጥ፡፡ ስለ ምን እንወያይ?"

"እንግዲህ በክርስትናና በእስልምና መካከል የሊትመስ ወረቀት ፈተና አለ ከተባለ የኢየሱስ በመስቀል ላይ መሞት አለመሞት ነው፡፡"

"መልካም፡፡ ስለ ኢየሱስ የመስቀል ላይ ሞት እንነጋገራለን፡፡ በቃ ጨረስን፡፡" እኔና ዳዊት የተነጋገርናቸው ነገሮች ያላቸውን ትርጉም እያሰብን ፏፏቴውን ለማየት ዞርን፡፡

ከዓመታት በኋላ ይህ ውይይት ለዳዊት ትልቅ የአቅጣጫ ለውጥ እንደነበረ ተረድቻለሁ፡፡ ክርስትና እውነት መሆኑን ማወቅ እንደማልፈልግ ብነግረው ኖሮ ዳዊት ውይይታችንን ከዚያ ወዲህ ለመቀጠል ፍላጎት አልነበረውም፡፡ ከእውነት የሚሸሹ ሰዎች ስኬታሞች እንደሚሆኑ ካወቀ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡

ለእኔም ትልቅ የአቅጣጫ ለውጥ ነበር፡፡ አባቴ የሚነሱትን ጥያቄዎች በሙሉ በብቃት መመለስ እንደሚችል ስላሰብኩኝ ውይይቱ ለሚያስከትለው ለውጥ ዝግጁ አልነበርኩም፡፡

# ራስን የመሳት መላምት በመስቀል ሲጠረቅ

ፏፏቴው አጠገብ ካደረግነው ውይይት በኋላ አባ ከማይክ ጋር ስለ ክርስቶስ ሞት ለመወያየት ፍቃደኛ መሆን አለመሆኑን ጠየኩት፡፡ እንደተጠበቀው አባ በደስታ መልስ ሰጠ፡፡ እንደ እኔ ሁሉ የእስልምናን እውነት መሆን በፅኑ ስላመነ ስለ ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ማውራት ያስደስተዋል፡፡ ስለ እምነታችን ከሰዎች ጋር ለመነጋገር ሚያገኛቸውን ዕድሎች በሙሉ ፈጣሪን እንደማክበርያ አጋጣሚዎች ይቆጥራቸዋል፡፡

ነገር ግን በመዝጊያ ፈተና፣ የቤተሰብ ጉዞና ሌሎች ምክያቶች ወደ ማይክ ስብሳባ በቅርቡ መሄድን የምንችል አይመስልም፡፡ እስከ ቀጣዩ የትምህርት ዓመት ድረስ ኮከባችን አልገጠመም ነበር፡፡

አንድ ቀን እኔና ዳዊት የጄኔቲክስ ትምህርት በአንድ ክፍል ውስጥ እየተከታተልን ሳለን ስለ **ታሪካዊው ኢየሱስ** ጥናትና ምርምር ያደረገ የማይክ ጓደኛ ወደ ከተማው እንደሚመጣ ነገረኝ፡፡ አምስታችን በሳምንቱ መጨረሻ ላይ መገናኘት እንችላለን፡፡ ጥሩ አጋጣሚ መስሎ ስለታየኝ እኔና አባ እንድንገኝ አመቻቸሁ፡፡ ከቀናት በኋላ ስንጠብቀው የነበረው ዕለት ደረሰ፡፡

> **ታሪካዊው ኢየሱስ፡** ኢየሱስበታሪካዊ መዛግብት አማካይነት እንደሚታወቀው

ጉባኤው የሚደረገው እዚያው እኛ ጎረቤት ነበር፡፡ ስብሰባውን የሚመራው ማይክ ሊኮና የተሰኘ የዳዊት ጓደኛ ነበር፡፡ በፊት የቴኳንዶ አሰልጣኝና የኢንሹራንስ ሽያጭ ባለሙያ

የነበረ ሲሆን ላለፉት ጥቂት ዓመታት አዲስ ኪዳንን ሲያጠና ነበር፡፡ በቅርቡ የማስተርስ ዲግሪውን ያጠናቀቀ ሲሆን ዶክተር የመሆን መንገድ ጀምሯል፡፡

እቤቱ ስንደርስ ሞቅ ያለ አቀባበል አደረገልን፡፡ ስድስት ጫማ ከአራት ኢንች የሚረዝም ሲሆን አስደናቂ ቁመና አለው፡፡ ከርዝመቱና የማርሻል አርት ችሎታው ባሻገር ደግነትን የሚፈነጥቁ ዓይኖችና ለስለስ ያለ ድምፅ አለው፡፡

ማይክ ከጓደኛው ከጌሪ ጋር አስተዋወቀን፡፡ ከአባ ወደ አምስት ዓመታት ገደማ በዕድሜ ከፍ የሚል ይመስላል፡፡ ጥርት ያሉ ሰማያዊ ዓይኖችና ተውቦ የተከረከመ ጢም ነበረው፡፡ የገና አባትና የአሜሪካ እግር ኳስ አጥቂ ድብልቅ ነበር የሚመስለው፡፡ ጌሪ እጁን ዘርግቶ ጨበጠኝ፡፡

"ሰላም፣ ጌሪ ሀበርማስ እባላለሁ፡፡ የማይክ ጓደኛና የቀድሞ ፕሮፌሰሩ ነኝ፡፡"

"ነቢል ቁሬሺ እባላለሁ፡፡ ስላገኘሁህ ደስ ብሎኛል፡፡ ወደ ጉባኤው ስለመጣህ አመሰግናለሁ፡፡ ስለ ታሪካዊው ኢየሱስ እንደምታውቅ ሰምቻለሁ ልበል?"

ጌሪ ሳቅ አለ፡፡ "እንደዚያ ማለት የምትችል ይመስለኛል፡፡ በርዕሱ ላይ የተወሰኑ መጻሕፍትን ጽፌያለሁ፡፡"

ይህ ለአባና ለእኔ በዚያን ምሽት ነገሮች በጥሩ ሁኔታ እንደማይሄዱ ማሳያ ነበር፡፡ ከማን ጋር ፊት ለፊት እንደተጋፈጥን ለማወቅ ጥቂት ጥቄዎችን ልጠይቀው ወሰንኩኝ፡፡ "ዳዊት ስለ ርዕሰ ጉዳዩ እንደምታውቅ ነግሮኛል ነገር ግን መጽሐፍት መጻፍህን አላውቅም ነበር፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ጥናት ማድረግ ከጀመርክ ስንት ጊዜ ሆነህ?"

"የዶክትሬት መመረቂያ ወረቀቴን የሠራሁት በኢየሱስ ትንሣኤ ታሪካዊነት ላይ ነው፡፡ ያንን የጻፍኩት በ 1976 ሲሆን ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ይኸው ለሃያ ስድስት ዓመታት ያህል ርዕሱን ሳጠና ነበር፡፡"

ፈገግ ብዬ ራሴን በአዎንታ በመነቅነቅ የምሽቱን አብዛኛውን ንግግር ለአባ ተውኩለት፡፡

አምስታችንም በማይክ ክፍል ውስጥ ሆነን እርስ በርሳችን መተዋወቃችንን ቀጥለናል፡፡ ማይክ ጀርባውን ለመስኮቱ ሰጥቶ ተቀምጧል፡፡ ጌሪ ደግሞ በስተግራው ነው፡፡ እኔ ደግሞ ከአባ በስተግራ በማይክ ትይዩ ተቀምጫለሁ፡፡ ዳዊት በክፍሉ ጥግ ላይ ፈንጠር ብሎ ወንበር ላይ ተቀምጧል፡፡ የውይይት መጀመርያ ሰዓት ሲደርስ እንድንጀምር አሳሰበን፡፡

"ፈጠን ብዬ የውይይቱን መነሻ ተናግሬ ለነቢልና ለአባቱ አስረከባለሁ፡፡ ስለ ኢየሱስ ስቅለት እንድንነጋገር ነው የተስማማነው፡፡ ነቢልና ጋሽ ቁሬሺ ኢየሱስ በመስቀል ላይ እንዳልሞተ ነው የሚያምኑት፡፡ የተቀረን ሁላችን ደግሞ ያ እውነት እንዳልሆ እናውቃለን፡፡"

ጌሪ እንደመደንገጥ አለ፡፡ እኔ ደግሞ ጭንቅላቴን አወዛወዝኩ፡፡ አባ ግን ዳዊትን ከዚህ ቀደም የተወሰነ ጊዜ አግኝቶት ስለነበር ቀልደኛ ቢጤ መሆኑን ያውቃል ስለዚህ ሳቅ አለ፡፡ ማይክ ደግሞ ትንሽ ቆጣ ብሎ "ዳዊት አሁን አስተካክለህ ጀምር!" አለው፡፡

"እሺ፣ እሺ፡፡ ግን እናንተ ሁለታችሁ ኢየሱስ መሰቀሉን ታምናላችሁ አይደል? ተሰቅሏል ግን በመስቀል ላይ አልሞተም ነው የምትሉት፡፡"

አባ መልስ ሰጠ፣ "አዎ ትክክል ነው፡፡"

ማይክ ጣልቃ ገባ፣ "መልካም፣ ለምን ከዚያ አንጀምርም? ለምን እንደርሱ እንደምታስቡ እስኪ ንገሩን፡፡"

እንደርሱ ብሎ ለኔና ለአባዬ መድረኩን ለቀቀልን፡፡ አባ *‹ኢየሱስ በሕንድ›* ከሚለው የሚርዛ ጉለም አሕመድ መጽሐፍ ያገኘውን ሙግት መካፈል ጀመረ፡፡ ንግግር የማድረጉን የአንበሳ ድርሻ የወሰደው እርሱ ሲሆን እኔ ግን ትንሽ ትንሽ ሐሳብ ብቻ ነበር ጣል የማደርገው፡፡ ከዓመታት በፊት በትምህርት ቤት መኪና ውስጥ ለጓደኛዬ ለክሪስተን

**የቱሪን ከፈን (መገነዣ ጨርቅ)፡** አከራካሪ ሲሆን ብዙ ጊዜ ኢየሱስ የተገነዘበት ጨርቅ እንደሆነና ልዕለ ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ ምስሉ በጨርቁ ላይ እንደቀረ ይታሰባል

ካካፈልኩት ሐሳብ ጋር ተመሳሳይ ነበር፡፡ ነግር ግን አባ ደጋፊ ሙግቶችን በማከል አጠናከሮታል፡፡

ማይክና ጌሪ ለግልፅነት ያህል ብቻ ጥያቄዎችን እየጠየቁ በትኩረት ያዳምጡ ነበር፡፡ ዳዊት ቅሬታ እስኪገባው ድረስ ጣልቃ ሳይገቡና መልስ ለመስጠት ሳይሞክሩ እስከ መጨረሳው ድረስ አዳመጡ፡፡ ከግማሽ ሰዓት በኋላ የክፍሉ መንፈስ ተቀየረ፡፡ ማይክና ጌሪ መልስ መስጠት ለመጀመር ዕድል ይጠብቁ ነበር፡፡

አባ **የቱሪን ከፈን** በመባል የሚታወቀውን ሲጠቅስ ጌሪ ጣልቃ ገባ፡፡ "ቆይ እስኪ፣ የቱሪን ከፈን እውነተኛ ነው ብለህ ታምናለህ? የኢየሱስ ምስል በዚያ ጨርቅ ላይ መኖሩን ታምናለህ?"

አባ ትንሽ ረጋ ብሎ የተናገረውን ነግር በጥንቃቄ ማጤን ጀመረ፡፡ "አዎ፡፡ ለምን፣ ማለቴ ምን አስበህ ነው?"

"አንተ ከተናገርከው ጋር ለመስማማት የሚያስችሉ ብዙ ጥሩ ምክንያቶች አሉ ነገር ግን ኢየሱስ እንደሆነ በማሰብህ በጣም ተደንቄያለሁ፡፡ በከፈኑ ላይ የሚታየው ሰው መሞቱ በጣም ግልፅ ነው፡፡"

የኛ ጀማት ኢማሞች የከፈኑን ትክክለኛነት የሚያውጁ ሲሆን ነገር ግን ከፈኑ ሲጠቀለልበት ኢየሱስ ሕያው እንደነበር ይሟገታሉ፡፡ አባ ሙግታቸውን ከሰማ በኋላ መልስ መስጠት ጀመረ፤ "አንድ ሰው ሲሞት ደሙ ይረጋል ነገር ግን በከፈኑ ላይ የሚታየው ሰው እየደማ ነበር፡፡"

"ትክክል ነህ ግን በጨርቁ ላይ የሚታየው ደም ውኃ መሰል ፈሳሽና የረጋ ደም መለያየቱን ያሳያል፡፡ ይህ ደግሞ ሊሆን የሚችለው አንድ ሰው ከሞተ በኋላ ነው፡፡ የጡንቻው መጨማደድ ሰውየው ስለመሞቱ ሌላ ማረጋገጫ ነው፡፡"

ስለ ከፈኑ በጥልቀት ስለማያውቅ አባ በወንጌላት ዝርዝር ዘገባ ላይ አተኮረ፡፡ "ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንኳ እንደተዘገበው የኢየሱስ ጎን በተወጋ ጊዜ ውኀና ደም

ፈስሷል፡፡ ያ ማለት ልቡ አሁንም ድረስ እየመታ ነው ማለት ነው፡፡ እንደርሱ ባይሆን ኖሮ ደም እንዴት ሊወጣ ይችል ነበር?"

ጌሪ ጭንቅላቱን አወዛወዘ፡፡ "ልቡ እስከዚያ ሰዓት ድረስ እየመታ የነበረ ቢሆን ኖሮ ውኃው ታድያ ምንድነው? የወንጌሉ ጸሐፊ ‹ውኃ› ብሎ የጠራው ነገር ደም ከረጋ በኋላ ተለይቶ የሚወጣ ውኃ መሰል ፈሳሽ ወይንም ደግሞ ልብ አካባቢ የሚገኝ ፈሳሽ መሆን አለበት፡፡ በዚህም ሆነ በዚያ ውኃና ደም ተለያይቶ ለመውጣት ኢየሱስ መሞት ያስፈልገዋል፡፡"

ማይክ አዲስ ኪዳንን በእጁ ይዞ ስለነበር እንዲህ በማለት አከለ፤ "‹ፈሰሰ› ብለህ የተረጎምከው የግሪክ ቃል ‹ዝም ብሎ መፍሰሱን› የሚሳይ ነው፡፡ ልብ እየመታ ነው ማለት አይደለም፡፡ በተጨማሪም ዮሐንስን የምትጠቅስ ከሆነ ትልቅ ችግር ውስጥ ትገባለህ፡፡ ዮሐንስ ኢየሱስ መሞቱን በግልፅ ነግሮናል፡፡ ይታይሃል? 19፡33፣ ‹ሞቶ ነበር› ይላል፡፡"

አባ ማይክ መጽሐፍ ቅዱሱን እንዲያሳየው ጠየቀው፡፡ ማይክ ጥቅሱን በጣቱ ጠቁሞ አሳየው፡፡ በግሪክ ስለተጻፈ ብዙ አልረዳውም ግን አባ የእርሱን ኪንግ ጀምስ መጽሐፍ ቅዱስና የማይክን የግሪክ አዲስ ኪዳን እያፈራረቀ ተመለከተ፡፡

ትንሽ ፋታ ከሰጠው በኋላ ጌሪ እንደገና መናገር ጀመረ፡፡ "አንድ ሰው በኢየሱስ ላይ የደረሰውን የጦር ውጋት መቋቋም የሚችል አይመስለኝም፡፡ ጎኑን የወጉበት ምክንያት መሞቱን ለማረጋገጥ ነው፡፡ ጦሩ የኢየሱስን ልብ በመውጋት ወዲያውኑ ሊገድለው ይችላል፡፡"

"ነገር ግን እኮ መጽሐፍ ቅዱስ ልቡን ወጋው አይልም፡፡" አባ ቀጠለ "ጎኑን እንደወጋው ብቻ ነው የሚናገረው፡፡ በተጨማሪም ደግሞ በመስቀል ላይ የነበረው ለጥቂት ሰዓታት ብቻ ነበር፡፡ በቀላሉ ከዚያ መትረፍ ይችላል፡፡"

“ስለ ስቅለት የሚናገር ሙሉ ታሪክ አለ፡፡ ስለዚህ ነገር እርግጠኛ ሆኜ ልነግርህ እችላለሁ፡፡ ለመትረፍ በሚያስችል ሁኔታ የሚፈፀም አይደለም፡፡ እኛ እስከምናውቀው ድረስ ሙሉ ከሆነው የሮማውያን የስቅለት ሂደት የተረፈ አንድም ሰው የለም፡፡[43] ሮማውያን አዋራጅ፣ እጅግ የሚያሰቃይና ገዳይ አድርገው ነው ያበጁት፡፡ ስለ ግርፋቱና ስለ ተቀረው የስቅለት ሂደት የምታውቀው ነገር አለ?”

አባ ጭንቅላቱን አወዛወዘ፡፡

“ቆዳን እየቦጨቀ በማንሳት እጅግ ደም እንዲፈስ የሚያደርግ ጉጠት ያለው መግረፊያ ነው የሚጠቀሙት፡፡ ከጥቂት ግርፋቶች በኋላ የሰለባው ቆዳ እየተቦጨቀ መነሳት ይጀምራል፡፡ ጡንጫዎችም መቆራረጥ ይጀምራሉ፡፡ የደም ቧንቧዎችም ይጋለጣሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ጉጠቶቹ ሆድ አካባቢ ያርፉና ሆድ ተቀዶ የሰለባዎቹ አንጀት ይዘረገፋል፡፡ ብዙ ሰዎችም በግርፋቱ ወቅት ይሞታሉ፡፡”[44]

ይህ ሁሉ ለኔ አዲስ ነበር፡፡ በጣም የመሳቀቅ ስሜትም ተሰማኝ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ መገረፉን ይናገራል ነገር ግን ዝርዝር ሁኔታዎችን አይናገርም፡፡ ኢየሱስ በእንዲህ ዓይነት ሂደት ውስጥ አልፎ ከሆነ ከመስቀል ሞት መትረፉን ደፍሬ መናገር አልችልም፡፡ ጌሪ ገና አልጨረሰም፡፡

“ከግርፋቱ በኋላ የሚሰቀሉት ሰዎች በእጃቸው ውስጥ ሚስማር ተሰክቶ ከእንጨት ጋር ይጣበቃሉ፡፡ ሚስማሮቹ በእጅ ነርቭ ውስጥ ስለሚያልፉ ከፍተኛ የህመም ስቃይ ያስከትላሉ፡፡ ወደ ሰባት ኢንች የሚሆን ሚስማር በሁለቱ እግሮቹ ላይ ይመታል፡፡ ከዚያም ተሰቃዩ ወደ ላይ ቀጥ ተደርጎ ይሰቀላል፡፡ ከዚህ የተነሳ መተንፈስ እጅግ ያስቸግረዋል፡፡ መተንፈስ ይችል ዘንድ የቀረችውን ትንሽ ጉልበት በመጠቀም በእግሩ ላይ በተሰካው ሚስማር ላይ ቆሞ ወደ ላይ መግፋት ይኖርበታል፡፡ ጉልበቱ ተሟጦ ወደ ላይ መግፋት ሲቸግረው የሳበውን አየር ማስወጣት ስለማይችል ታፍኖ ይሞታል፡፡”

ማይክ ፈጠን ብሎ አከለ፣ “ለዚያ ነበር ከኢየሱስ ጎን የተሰቀሉትን ወንበዴዎች እግሮች የሰበሩት፡፡ ጉልበታቸው ከተሰበረ ወደ ላይ በመግፋት መተንፈስ ስለማይችሉ ታፍነው ይሞታሉ፡፡”

ጌሪ ቀጠለ፤ “ጠባቂዎች አንድ ሰው መሞቱን በቀላሉ በዚያ ያውቃሉ፡፡ የተሰቀለው ሰው በእግሩ ወደ ላይ መግፋት ማቆሙን ማየት ብቻ ነው ከእነርሱ የሚጠበቀው፡፡ ነገር ግን ጠባቂዎቹ ተሰቃዩ መሞቱን የሚያረጋግጡበትን ዘዴ ፈጥረዋል፡፡ ጉልበትን ከመስበር ሌላ አንዳንዴ የተሰቃዩን የራስ ቅል ይሰብራሉ፤ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ አስከሬኑን ለውሾች ይመግባሉ፤ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በኢየሱስ እንዳደረጉት ልቡን ይወጉታል፡፡”

እያንዳንዱ ነጥብ በተጠቀሰ ቁጥር የኛ አቋም ችግር እንዳለበት ይገባኝ ነበር ነገር ግን አባ ገና አልተረታም፡፡ “ኢየሱስ መራራው ጽዋ ከእርሱ እንዲወሰድ በጌቴ ሰማኒ ጸልይዋል እኮ፡፡ መሞት እንዳልፈለገ ግልፅ ነው! እግዚአብሔር ያንን ጸሎት አልመለሰም ነው እያላችሁ ያላችሁት?”

ማይክ መልስ ሰጠ፣ “አዎ ጸልይዋል፤ ነገር ግን ‹ያንተ ፈቃድ እንጂ የኔ ፈቃድ አይሁን› ማለቱንም አንርሳ፡፡ ስለዚህ ሰው እንደመሆኑ መጠን ከደረሰበት ስቃይ የተነሳ በእርግጥ ኢየሱስ መሰቀል አልፈለገም፡፡ ነገር ግን በውስጣዊ ማንነቱ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲፈፀም ነበር ፍላጎቱ፤ ስለዚህም ለመሰቀል ፈቃደኛ ነበር፡፡ ይህንን ደግሞ ወደ ኢየሩሳሌም ሲመለስ ሳለ በአገልግሎቱ መጀመርያ ላይ ግልፅ አድርጎ ትንቢት ተናግሯል፤ በፈቃደኝነትና በፅናትም ገስግሦ ሄዷል፡፡”[45]

ጌሪ እንዲህ ሲል አከለ “ስላንተ አቋም በግልፅ መናገር የፈለኩት ያንን ነበር፡፡ አመለካከትህን የሚደግፉ ጥቅሶችን ብቻ እየመረጥክ ትጠቅስና ካንተ አመለካከት ጋር የሚጣረሱትን እንደዋዛ ትጥላቸዋለህ፡፡ ለምሳሌ ያህል የጲላጦስ ሚስት ያየችው ህልም አንድ ጊዜ ብቻ በአንዱ ወንጌል ውስጥ የተጠቀሰ ሆኖ ሳለ ተጠቅመህበታል፤[46]ኢየሱስ ስለ ሞቱ የተናገረው ትንቢት ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ በሁሉም ወንጌላት ውስጥ የሚገኝ ቢሆንም አልተቀበልከውም፡፡[47] ለምንድነው እንደርሱ የምታደርገው?”

አባ በቅንነት መልስ ሰጠ፤ "ምክንያቱም የኢየሱስ በመስቀል ላይ መሞት የማይቻል ነገር ስለሆነ ነው፡፡ እርሱ በፈጣሪ የተወደደ ነው፡፡ እንዲያድነውም ደግሞ በብርቱ ተማፅኗል፡፡ በመስቀል ላይ መሞቱን እንደተነበየ የሚናገሩ ጥቅሶች ካሉ በክርስቲያኖች የተጨመሩ መሆን አለባቸው፡፡"

የእፍረት ስሜት ተሰማኝ፡፡ ቀደም ሲል ከዳዊት ጋር ባደረኩት ውይይት የአዲስ ኪዳንን ጽሑፍ ተዓማኒነት መጠራጠር አዳጋች ነው፡፡ ነገር ግን አሳፋሪ ሆኖ ያገኘሁት እርሱን አይደለም፡፡ አባ የራሱን አቋም ለመደገፍ ጥቅሶችን በዘፈቀደ መውሰዱና መጣሉ ነው፡፡ መናገር እንዳለብኝ ስለተሰማኝ አንደበቴን ከፈትኩ፡፡

"አባዬ ጥቅሶችን የምንጥልበት በቂ የኾነ ምክንያት ከሌለን በስተቀር የፈለግነውን መጠቀምና ያልተመቸንን መጣል አቋማችን የሚዋዥቅ መሆኑን እንደሚያመለክት እየተናገሩ ያሉ ይመስለኛል፡፡"

አባ ሥልጣኑን በመገዳደሬ በመደመም ስሜት ዞሮ ተመለከተኝ፡፡ እንደተከዳ ስለተሰማው ያንን በመናገሬ የፀፀት ጅራፍ ህሊናዬን ይገርፈኝ ጀመር፡፡ ከዚያ በኋላ ብዙ መናገር አልፈለገም፡፡ በተቀረው አጭር የውይይት ጊዜ ተናጋሪው እኔ ሆንኩኝ፡፡

"እሺ ወገኖቼ ሙግታችሁን ሰምቻለሁ ነገር ግን ደግሞ ለጥርጣሬ ቦታ መኖሩንም አስተውያለሁ፡፡ ኢየሱስ በመስቀል ላይ አለመሞቱን በመደገፍ ከኔና ከአባ ጋር የሚስማሙ ሊቃውንት ይኖሩ ይሆን?"

ማይክ መልስ ሰጠ "በእርግጥ በአሥራ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን ውስጥ አንዳንድ ሊቃውንት ኢየሱስ በመስቀል ላይ አለመሞቱን እንደ ሐሳብ አቅርበው ነበር ነገር ግን ትወራው በአጭር ተቀጭቷል፡፡ ዴቪድ ስትራውስ የተሰኘ ክርስቲያን ያልሆነ ሊቅ ቁልፍ የሆነ ሙግት አቅርቧል፤ ኢየሱስ ከመስቀል መትረፉ ፈፅሞ የማይቻል ከመሆኑም በላይ የክርስትናን እንቅስቃሴ ገና ከጅምሩ የሚያኮላሽ ይሆን ነበር፡፡[48]

“አየህ ደቀ መዛሙርት በጌቴ ሰማኒ ከኢየሱስ ጋር ከመወገን ይልቅ ጥለውት ሸሽተዋል፡፡ ነገር ግን ኋላ ላይ ትንሣኤውን በማወጅ እስከ ሞት ድረስ ፀንተዋል፡፡ ኢየሱስ ከመስቀል ሞት ተርፎ ቢሆን ኖሮ በጣም ተጎሳቁሎና ለሞት የቀረበ እርዳታ ፈላጊ ሆኖ ወደ እነርሱ በመጣ ነበር፡፡ ያ ደግሞ ሰዎች ሙሉ በሙሉ ተለውጠው እስከ ሞት ድረስ ለመፅናት የሚያበቃ ክስተት አይሆንም፡፡ ድፍረትና ፅናት የክርስትና ኃይል ነበር፡፡ ይህ ባይሆን ኖሮ ክርስትና መቆም ባልቻለም ነበር፡፡”

ጌሪ አከለ “ለዚህ ነው ኢየሱስ በመስቀል ላይ መሞቱን የሚክድ አንድም ሊቅ የሌለው፡፡ እውነታው የዚያ ተቃራኒ ነው፡፡ ከኢየሱስ የሕይወት ታሪክ የትኛውም ክፍል ይልቅ በመስቀል ላይ መሞቱ የተረጋገጠ መሆኑን ብዙ ሊቃውንት ይስማሙበታል፡፡”

ጥያቄ አስከተልኩ “ስለ ክርስቲያን ሊቃውንት ነው የምታወራው አይደል?”

“ክርቲያኖች፣ ክርስቲያን ያልሆኑ፣ የፈለከውን መጥራት ትችላለህ፡፡ ቀደም ሲል እንዳልኩት ሌሎች አሳማኝ የሆኑ ምክንያቶች አሉ፡፡ ለምሳሌ ያህል ኢየሱስ በመስቀል ላይ መሞቱን የሚመሰክሩ ከኢየሱስ በኋላ በመጀመርያው ክፍለ ዘመን የተጻፉ ክርስቲያናዊ ያልሆኑ ምንጮች አሉ፡፡ ይህንን ደግሞ የሚያረጋግጡ ጉልቁ መሳፍርት የሌላቸው ክርስቲያናዊ ምንጮች አሉ፡፡ በተጨማሪም ለረጅም ዘመናት ይህንን የሚፃረር ትውፊት የለም፡፡ ነገር ግን ጥያቄህን ለመመለስ ስለ ሁሉም ነው እየተናገርኩ ያለሁት፡፡”

ማይክ የመጨረሻ ቃሉን አከለ፡፡ “ሊቃውንት በዚህ ላይ ሙሉ በሙሉ ይስማማሉ፡፡ ኢየሱስ በመስቀል ላይ መሞቱ በጣም ከተረጋገጡት የታሪክ እውነታዎች መካከል አንዱ ነው፡፡”

የተባለውን በጥሞና ሰምቼ ዋጥኩት፡፡ አባም ለመሄድ ጊዜው እንደሆነ ጠቆመ፡፡ ትንሽ ቆይቼ ለመወያየት ፈልጌ ነበር ነገር ግን አባ ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ወደ ቤት ስንሄድ የነበረው ፀጥታ የማይክን የመጨረሻ ቃላት የሚያስተጋባ ነበር፡፡

እስልምና ስለ ኢየሱስ ስቅለት የሚያቀርባቸውን ትወራዎች - የመተካካት ትወራ ወይንም ደግሞ ራስን የመሳት ትወራ - ይዤ መቀጠል የሚኖርብኝ ከሆነ ታሪክን መፃረር እንደሚኖርብኝ ይሰማኝ ጀመር፡፡ ቁርአን ግን ማስረጃዎችን በጭፍን በመካድ በእምነት ብቻ እንድቀበለው ይጠብቅብኛል፡፡

የሊትመስ ወረቀት ፈተናችን ይህ ነው፡፡ ምንም የሚያምታታ ነገር ደግሞ የለም፡፡ የክርስትና ሐሳብ ከማስረጃዎች ጋር ሙቶ በሙቶ ይስማማል፡፡

ከዚህ የከፋው ደግሞ አባ በሙግት ሲረታና እጅ ሲሰጥ ማየቴ ነው፡፡ በውይይታችን ወቅት በአንድም ሆነ በሌላ ምክንያት በግልፅ የተቀመጠውን ማስረጃ አይቼዋለሁ፡፡ ይህ ደግሞ በእጅጉ ምቾት ነስቶኛል፡፡ ወላጆቼ ያስተማሩኝን ሳልመረምር ዝም ብዬ ማመን እንደሌለብኝ ተገንዝቤያለሁ፡፡ ቅንነታቸውን፣ ትጋታቸውን ወይም ፍቅራቸውን አልጠራጠርም ነገር ግን እውነትን መረዳታቸውን መጠራጠር ጀምሬያለሁ፡፡

የእርግጠኛነት መጋረጃ የተገፈፈልኝ ይመስል ነገሮችን በተለየ ብርሃን ማየት ጀምሬያለሁ፡፡ ዕድሜ ልኬን ባለቀለም መነፅር ሳደርግ ኖሬ ለመጀመርያ ጊዜ የወለቀልኝ ያህል ተሰማኝ፡፡ ሁሉም ነገር ከበፊቱ የተለየ ሆኖ ታየኝ፡፡ ሁሉንም ደግሞ ከመሠረቱ በጥንቃቄ መመርመር እንዳለብኝ አመንኩኝ፡፡

ምናልባት ምናልባት የክርስትና መልዕክት እውነት የመሆን ጠባብ ዕድል ይኖረው ይሆናል፡፡

# በቤተ ክርስቲያን የተገኘ ሙስሊም

ቤት ስንደርስ እማ በር ላይ ተቀበለችን፡፡ ውይይቱ እንዴት እንደነበር ለማወቅ ጓጉታለች፡፡ ሐሳባችንን በተሳካ ሁኔታ ማቅረባችንን አፅንዖት በመስጠት ስለ ውይይቱ አጭር ዘገባ አቀረብኩላት፡፡ አባ አሁንም ድረስ አንደበቱ መቆለፉንና እኔም ክፍሉን ለቅቄ ለመውጣት መጣደፌን ካየች በኋላ የነገርኳትን ማመኗን እጠራጠራለሁ፡፡ ሰበብ ፈጥሬ በጥድፍያ ወደ ላይኛው ደረጃ ወጣሁ፡፡

ሁለተኛው ደረጃ ላይ የሚገኘው ሰፋ ያለ ክፍል መጀመርያ የታሰበው እቃ ማስቀመጫና ማጠብያ ክፍል እንዲሆን የነበረ ቢሆንም አባዬ ግን ሰፋ ያለ የመኝታ ክፍል እንዲሆን አድርጎ አስገነባው፡፡ ኋላ ላይም በመጽሐፍት የተጠቀጠቀ ቤተ መጻሕፍት አደረገው፡፡ ስለ ሃይማኖት ማንበብ ስፈልግ በመጽሐፍት ከተሞሉት መደርደርያዎች መካከል ወደ አንዱ በመሄድ የምፈልገውን መጽሐፍ መዝዤ በሆዴ ተኝቼ አነባለሁ፡፡ ብዙ ጊዜ ለመዝናናት የማደርገው ነገር ነው፡፡

ዛሬ ግን ስለ መዝናናት አይደለም እያሰብኩ ያለሁት፡፡ በልቤና በአእምሮዬ ውስጥ የነገሠውን ውጥረት የማርገብ ተልዕኮ ይዤ ነው የመጣሁት፡፡

ስለ ኢየሱስ የተጻፉትን በመደርደርያዎቹ ላይ ያሉትን መጻሕፍት በሙሉ አወጣኋቸው፡፡ ሁሉም በሙስሊም ምሑራን የተጻፉ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ቀደም ሲል ለሰማኋቸው ሙግቶች መልስ ፍለጋ ገፆቹን በርዕስ መግለጥ ተያያዝኩኝ፡፡

በዚህ ወቅት ነበር ለመጀመርያ ጊዜ አንድ ነገር ያስተዋልኩት፤ ስለ ኢየሱስ የሚያወሩት የአባዬ መጻሕፍት ሁሉ ክርስትናን ለማጥቃት ታልመው የተጻፉ ናቸው፡፡ ገና ከጅምራቸው የድምዳሜ ሐሳብ ያቀርባሉ፤ ከዚያም ያንን ድምዳሜ የሚደግፉ ሐሳቦችን ይለቃቅማሉ፤ ከዚያም ሙግታቸውን ያቀርባሉ፡፡ ጌሪ የአባን ሙግት በተመለከተ እንደተናገረው ሁሉ ጥናቶቹ በጥንቃቄ ወይም በገለልተኝነት የተደረጉ አይደሉም፡፡ ሙግታቸውን ውድቅ ለሚያደርጉ ማስረጃዎች መልስ አይሰጡም፡፡ ይህ ደግሞ ሙግታቸውን ያልተፈተነና ልፍስፍስ ያደርገዋል፡፡

ሙግታችን በተደጋጋሚ ውድቅ ሲሆን ብመለከትም ነገር ግን ይህ የሆነበት ምክንያት የጥናት አካሄዳችን ደካማ በመሆኑ ብቻ እንደሆነ አምኛለሁ፡፡ ምስራቃውያን ጸሐፍት በጥልቅ ስሜታዊነት ላይ የተመሠረቱና ልብን የሚመስጡ ሙግቶችን ማቅረብ ቢችሉም ምዕራባውያን ግን የበለጠ ሥልታዊ በሆነ መንገድ ማሰባቸውና ምላሽ የሚሆኑ ግሩም ሙግቶችን በማቅረብ የታጠቁ መሆናቸው የበላይነትን እንዲቀዳጁ ያደርጋቸዋል፡፡ የምዕራባውያኑን ሥልት ከምስራቃውያኑ ስሜት ጋር ባጣምር የበለጠ አሳማኝና ፈተናዎችን ማለፍ የሚችል ሙግት ማቅረብ እችል ይሆናል፡፡

በአካሄዴ ሥልታዊነትን ለመከተል ጊዜው እንደሆነ ተሰምቶኛል፤ ነገር ግን እንዴት መጀመር እንዳለብኝ ምንም የማውቀው ነገር አልነበረኝም፡፡ ብዙም ሳይቆይ ዳዊት ደወለ፡፡ ስልኬን አውጥቼ አየሁት፡፡

“ነቢል!” አለ ጫወታ በሚንፀባረቅበት ድምፀት፡፡ “ስለ ውይይቱ ምን ትላለህ?”

“እስካሁን እያሰላሰልኩት ነው፡፡ ሥልታዊ አጠናን መማር እንደሚያስፈልገኝ ይሰማኛል፡፡”

“እውነትህን ነው? እንዴት?”

“እንጃ ብቻ፡፡ ምናልባት ሐሳብ ይኖርህ ይሆን?”

“በርግጥ አዎ፡፡ መጨረሻ ላይ መሄድ እንዳልፈለክ አስተውያለሁ፡፡ ስለዚህ ማይክና ጌሪ ሌላ የውይይት ጊዜ ይኖራቸው እንደሆን ጠይቂያቸዋለሁ፡፡ ነገ ምሳ ላይ አብረው ይሆናሉ፡፡ ብንቀላቀላቸው ቅር እንደማይላቸው ነግረውኛል፡፡ ከቤተ ክርስቲያን ሰዓት በኋላ ነው፡፡ ተጋባዥ ተናጋሪው ጌሪ ነው፡፡ ከኛ ጋር መሄድ ትፈልጋለህ? ስለ ታሪካዊ የአጠናን ሥልት ልትጠይቃቸው ትችላለህ፤ ደግሞም…”

“ወይ ጉድ፤ ምን እያልክ ነው?” ያለውን ማመን አቅቶኛል፡፡ “ካንተ ጋር ወደ ቤተ ክርስቲያን እንድሄድ ትፈልጋለህ?”

“ፍቃድህ ከሆነ አዎ፡፡”

“ወላጆቼን ምን እላቸዋለሁ?”

“ለማለት የፈለከው አልገባኝም፡፡”

ላስረዳው ሞከርኩኝ፡፡ “ወደ ቤተ ክርስቲያን ካንተ ጋር እንድሄድ የሚለቁኝ ይመስልሃል? ከዚህ በኋላስ ከማይክና ከጌሪ ጋር እንድነጋገር የሚፈልጉ ይመስልሃል? የማይሆን ነገር ነው፡፡”

“አውራ ጣትህን መጥባት አቁመህ የደረት ፀጉር አብቅልና ንገራቸው፡፡ ጎረምሳ ነህ እኮ፡፡ እንደ ህፃን አትሁን፡፡”

ደንገጥ አልኩኝ፡፡ “አልገባህም፡፡ ነገሩ እንደምትለው ቀላል ሳይሆን ውስብስብ ነው፡፡”

ማይክና ጌሪን ለሁለተኛ ጊዜ ባገኛቸው ቤተሰቦቼ እንደተቀበልኳቸውና በእነርሱ ለመመራት ዝግጁ እንደሆንኩ ያስባሉ፡፡ በተለይም አባን ወደ ውይይቱ ካልጋበዝኩት ደግሞ ጉዳዩ ይጎላል፡፡ እርሱን መጋበዝ ደግሞ የማይመስል ነው፡፡ እርሱ ከእኔ ጋር የሚመጣ ከሆነ በነፃነት መናገር አልችልም፡፡

የሚጨነቁበትን ምክንያት ላቀብላቸው አልፈልግም፡፡ እውነቱን በመናገር ደግሞ እንዳልሄድ እንዲከለክሉኝ በር መክፈትም አልፈለኩም፡፡ ከዳዊት ጋር ለመዝናናት

እንደምሄድ ልነግራቸው ወሰንኩኝ፡፡ ይህ እውነት ቢሆንም ነገር ግን ግማሽ እውነት ነበር፡፡ በቀጣዮቹ ዓመታት ሙሉ በሆነ እውነትና በግማሽ እውነት መካከል ወዲያና ወዲህ በመቅዘፍ የግበረ ገብነት ልኬቴን መፈታተን ነበረብኝ፡፡ ይህንን ያደረኩት ደግሞ አስገዳጅ ሁኔታዎች ስለገጠሙኝና ለተሻለው መልካም ነገር ስል ነበር፡፡ ሁኔታው ባያስደስተኝም ከመራራና ከጎምዛዛ መምረጥ ስለነበረብኝ ይህንን ለማድረግ ተገድጃለሁ፡፡

በቀጣዩ ቀን ወደ ዳዊት ቤት ሄድኩኝ፤ እርሱም ወደ ቤተ ክርስቲያን ወሰደኝ፡፡ “ካምፓስ ኢምፓክት” የተሰኘ የኮሌጅ ቤተ ክርስቲያን ነበር፡፡ ለኔ ሙሉ በሙሉ እንግዳ የሆነ ሁኔታ ነበር፡፡ በመድረኩ ላይ “የአምልኮ ቡድን” ብለው የሰየሚቸው ሰዎች ነበሩ፤ ጊታር፣ ጃዝና ሌሎች የሙዚቃ መሣርያዎችን እየተጫወቱ ይዘምራሉ፤ ሕዝቡም እያጨበጨበ አብሯቸው ይዘምራል፡፡ አስቂኝ የሆኑ ማስታወቂያዎች ነበሩ፤ ሰዎች ደግሞ ሰላምታ የሚለዋወጡበት አጭር የእረፍት ጊዜ ነበር፤ የገንዘብ መሰብሰብያ ከረጢቶችም በጉባኤው ውስጥ ይዘዋወሩ ነበር፡፡

ከዚህ ቀደም እንዲህ ያሉ ነገሮችን አይቼ ስለማላውቅ ምንም አልጣመኝም ነበር፡፡ አምልኮ ማለት በሰውና በፈጣሪ መካከል የሚደረግ የግል ጉዳይ ነው፤ ነገር ግን እነዚህ ሰዎች ከበሮ ይደልቃሉ፤ ገንዘብም ደግሞ ይጠይቃሉ፡፡ በመስጊድ ሁሉም ሰው በፈጣሪው ላይ ብቻ እንዲያተኩር ተብሎ ማንም ሰው በአምልኮ ሰዓት ፊታችሁ ቆሞ አይጋርዳችሁም፡፡ ሴቶች ደግሞ በአምልኮ ሰዓት መድረክ ላይ መቆማቸው ገደብ የጣሰ ተግባር ነው፡፡

ስለዚህ የአምልኮ ጊዜው በጣም ረብሾኛል፤ ምኑም አልጣመኝም ነበር፡፡ “ለክርስቲያኖች እግዚአብሔርን ማምለክ ማለት ትርጉሙ ይህ ከሆነ ይቅርብኝ” ብዬ ለራሴ አሰብኩኝ፡፡

ለኔ ትልቁ ጉዳይ ስብከቱ ነበር፡፡ ጌሪ የመናገርያ ጊዜው ሲደርስ ግብረ ገብነት ስለማጣት ተናገረ፡፡ ከዚያም የኢየሱስ ትንሣኤ በታሪካዊ ማስረጃ ሊረጋገጥ የሚችልና ትልቅ ትርጉም ያለው መሆኑን አብራራ፡፡ ሞት የሕይወት ማከተሚያ እንዳልሆነና ሕልውናችን

እንደማይጠፉ ተናገረ፡፡ ይህ ደግሞ ከሞት በኋላ ሕይወታችን ምን እንደሚገጥመው በማሰብ እንድንደሰት ወይም እንድንጨነቅ የሚያደርገን ነገር ነው፡፡

ነገር ግን ጌሪ በተናገረው መሠረት የኢየሱስ ትንሣኤ ለዚህ ምላሽ ሰጥቷል፡፡ የክርስትና መልዕክት እውነት መሆኑንና ኢየሱስን እንደ ጌታና አዳኛችን ካመንነው ለዘለዓለም ከእግዚአብሔር ጋር በሰማይ እንደምንኖር ያረጋግጣል፡፡

በዚህ ጊዜ ነበር ሙስሊም የሆነው አእምሮዬ ከጌሪ ጋር መስማማት የቸገረው፡፡ እውነት ነው ፈጣሪያችን ኢ-ሟቲያን አድርጎናል፡፡ አካላችን ቢሞትም የነፍሳችን ህልውና ይቀጥላል፡፡ ነገር ግን ኢየሱስ ከዚህ ቀደም ከሞት ተነስቶ ቢሆን እንኳ ክርስትና የሚያስተምረው እያንዳንዱ ነገር እውነት እንዲሆን አያደርገውም፡፡

ከቤተ ክርስቲያን እንደወጣን “ዘማክስ” ወደ ተሰኘ ሬስቱራንት አቀናን፡፡ እኔም ሰላጣ እያላመጥኩ መናገር ጀመርኩኝ፡፡

“ጌሪ እስኪ የኢየሱስ ትንሣኤ እውነት ነው እንበል፡፡ ይህ ከመቅፅበት እንደ ጌታና አዳኝ ልንቀበለው ይገባል ማለት አይደለም፡፡ በቃ ሞቶ ነበረ ከሞት ተነሳ ማለት ነው፡፡”

“አዎ፣ ግን ‹ለምን?› የሚል ጥያቄ ማንሳት ይጠበቅብሃል፡፡ ለምን በመስቀል ላይ ሞተ ለምንስ ተነሳ?” ጌሪ ጉዳዩን እንዳሰላስል ፋታ ከሰጠኝ በኋላ ቀጠለ፡፡ “በተጨማሪም ይህ ሰው ስለ ራሱ የተናገራቸው ነገሮች እውነት መሆናቸውን ለማመን ትገደዳለህ፡፡”

“ምን ዓይነት እውነት?”

“አምላክ መሆኑን፡፡”

“ቆይ እስኪ፡፡ ይህ ሌላ ርዕስ ነው፡፡ ኢየሱስ አምላክ መሆኑን መናገሩን አላምንም፡፡”

ጌሪ ጭንቅላቱን ትንሽ ዘንበል አደረገ፡፡ “ይሁን፡፡ ነገር ግን ኢየሱስ ከሙታን ተነስቶ ከሆነ ቢያንስ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር መስማማቱን በማረጋገጫ ማህተም እንዳስታወቀ መቀበል ይኖርብሃል፡፡”

"አዎ፣ ነገር ግን ፈጣሪ ለኢየሱስ ማረጋገጫ መስጠቱን ከዚህ ቀደደምም ቢሆን አምናለሁ፡፡"

ዳዊት ጣልቃ ገባ፣ "ነቢል ትላንትና ሥልታዊ የጥናት ዘዴን የመማር ፍላጎት እንዳለህ ነግረኸኝ ነበር፡፡ ይህ ማለት በጥናትህና በአካሄድህ የበለጠ ምክንያታዊ መሆን ትፈልጋለህ ማለት ነው፤ አይደል?"

"ያለጥርጥር፡፡"

"ስለዚህ ‹የሆነ ነገር ከዚህ ቀደምም አምናለሁ› ብሎ ብቻ በዚያው እምነት መቀጠል ምክንያታዊ አይደለም፡፡ በጠንካራ መሠረት ላይ የቆሙ የተሻሉ ምክንያቶች ያስፈልጉሃል፡፡ ትንሣኤ ተከስቶ ከሆነ እግዚአብሔር ከኢየሱስ ጋር መስማማቱን ለማመን የሚያበቃ ጠንካራ ማስረጃ አለን ማለት ነው፡፡ ነጥቡ ይኼ ነው፡፡"

ወደ ጌሪ ፊቴን አዞርኩኝ፡፡ "እሺ ገብቶኛል፡፡ ስለዚህ ምን ይሁን? ይህ ለኔ የሚሰጠው ትርጉም ምንድነው?"

ጥያቄው ለጌሪ የቀረበ ቢሆንም ዳዊት ንግግሩን ቀጠለ፤ "ኢየሱስ አምላክ መሆኑን በእውነት ተናግሮ እንደሆን ማጣራት ያስፈልግሃል ማለት ነው፡፡"

"እሺ እንደርሱ ማድረግ እፈልጋለሁ፡፡ ነገር ግን እንዴት? ትልቁ ጥያቄዬ እርሱ ነው፡፡ ይህንን ጉዳይ በሚዛናዊነት መመርመር የምችለው እንዴት ነው? ሥልታዊ ጥናት ለማድረግ እንዴት ነው መጀመር ያለብኝ?"

እስካሁን ሲያዳምጠን የነበረው ማይክ መናገር ጀመረ፡፡ "እኔና ጌሪ በጋራ የምናሳትመውን

**ታሪካዊ አካሄድ፡** የታሪክ ምሑራን ያለፈውን ታሪክ ለመመርመር የሚጠቀሙባቸው መስፈርቶችና ዘዴዎች

**የብዝሃ ምስክርነት ማረጋገጫ፡** አንድ ታሪካዊ ክስተት በተለያዩ የተናጠል መዛግብት ውስጥ ሰፍሮ ከተገኘ እውነተኛ ክስተት የመሆኑ ሁኔታ ከፍ እንደሚል የሚናገር መርህ

**ቀዳሚ የምስክርነት መስፈርት፡** ከኋለኞቹ ዘገባዎች ይልቅ ቀዳሚያኑ የበለጠ ተዓማኒነት እንዳላቸው የሚያስቀምጥ መርህ

መጽሐፍ ስሠራ ነበር፡፡ ከኢየሱስ ትንሣኤ ጋር የተያያዘውን ይህንን ጥያቄ መልሰናል፡፡[49] የታሪክ ተመራማሪዎች ስላለፈው ነገር ሲያጠኑ በጥንቃቄ የሚጠቀሟቸው መስፈርቶችና ስልቶች አሉ፡፡ ሥልታዊ የሆነው የአጠናን ዘዴ **ታሪካዊ አካሄድ** ይሰኛል፡፡"

ማይክ የታሪክ ጥናት መሠረታዊ ዘዴዎች የሆኑትን **የብዝሃ ምስክርነት ማረጋገጫ**እና **ቀዳሚ የምስክርነት መስፈርቶችን**የመሳሰሉትን ነጥቦች ዘረዘረ፡፡ የተረዳሁት አንድ ነገር ቢኖር የታሪካዊ ጥናት ሥልት በአመዛኙ ታማኝና ጠንቃቃ መሆንና መሠረታዊ ግንዛቤያችንን መጠቀም መሆኑን ነው፡፡[50]

ውይይቱ ሲጠቀለልም ማይክ አንድ የመጨረሻ ነጥብ ነበረው፡፡ "ነቢል ጥናትህን ስታደርግ ሚዛናዊ መሆን በእጅጉ ወሳኝ ነው፡፡ ሁለቱንም ሙግቶች አንብብ፡፡ ሌሎቹን ከማጣራትህ በፊት አንድን ትወራ ዝም ብለህ አትቀበል፡፡ የትኛው ሙግት አብላጫውን እውነታ ያገናበዘ እንደሆነ፣ ምን ያህል አጥጋቢ በሆነ ሁኔታ እንዳገናዘበው፣ ለአጠቃላዩ ሙግት እነዚህ እውነታዎችና ርዕሰ ጉዳዮች ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆኑ ተመልከት፡፡ ላለፈው ታሪክ የላቀ ማብራርያ ማግኘት የምንችለው እንደርሱ ስናደርግ ነው፡፡"

ይህ አባባል ትኩረቴን ሳበው፡፡ "የላቀ ማብራርያ?" ብዬ ጠየቅሁ፡፡

"አዎ፣ ታሪክ የማጥናት ትርጉም ይኸው ነው፡፡ ሁል ጊዜም ቢሆን ተፎካካሪ ትወራዎች ይኖራሉ፡፡ ያለፈውን ሁኔታ በፍፁማዊነት የሚገልጥ ትወራ ደግሞ የለም፡፡ ነገር ግን ሁል ጊዜ የተሻለ ማብራርያ አለ፡፡ ይህ ማብራርያ ደግሞ ከሌሎቹ በእጅጉ ይልቃል፡፡ የኢየሱስን ሞት የከበቡትን ጉዳዮች በተመለከተ የላቀው ማብራርያ ከሞት ተነስቷል የሚል ነው፡፡ ይህ ደግሞ ከሌሎቹ ትወራዎች በእጅጉ የላቀ ነው፡፡"

ይህንን መረጃ እንዴት በተግባር ማዋል እንደምችል ማሰላሰል ተያይዣለሁ፡፡ "ነገሮች መስመር እየያዙ የመጡ ይመስለኛል፡፡ ማድረግ የምፈልገው ይህንን ነው፤ የእስልምናና የክርስትናን ዋና ዋና ጉዳዮች ለታሪክ ምርምር በሚያመቹ ቃላት አስቀምጣቸውና የትኛው የተሻለ እውነታን እንዳዘለ እወስናለሁ፡፡ እስኪ ኢየሱስ አምላክ መሆኑን

ከተናገረ፣ በመስቀል ላይ ሞቶ ከሞት ከተነሳ ክርስትና እውነት ለመሆኑ ትልቅ ማስረጃ ነው ከሚለው አባባል ጋር ትስማሙ እንደሆን ንገሩኝ፡፡"

ሦስቱም ጭንቅላታቸውን በአዎንታ ነቀነቁ፡፡ቀጠልኩኝ፤ "ኢየሱስ ካልሞተ ካልተነሣና አምላክ መሆኑን ካልተናገረ ክርስትና እውነት አለመሆኑን ለመናገር በቂ ምክንያት ይኖረኛል ማለት ነው፡፡ ትስማማላችሁ?"

ዳዊት የበለጠ ግልፅ እንዳደርግ ጠየቀ፡፡ "ክርስትናን ውድቅ ለማድረግ ሦስቱም ውሸት መሆን አለባቸው እያልክ ነው?"

ጭንቅላቴን አወዛወዝኩኝ፡፡ "አይደለም፣ ሦስቱ ሙግቶች አሳማኝ ካልሆኑ ሙግቱ ባጠቃላይ አሳማኝ አይሆንም፡፡ ለምሳሌ ኢየሱስ አምላክ መሆኑን ከተናገረና በመስቀል ላይ ከሞተ ምንድነው ትርጉሙ? አምላክ መሆናቸውን የተናገሩና የሞቱ ብዙ ሰዎች አሉ፡፡ ነገር ግን ከሙታን ከተነሳ ጉዳዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ማለት ነው፡፡"

ይህን ስል ጌሪ ጥያቄ አቀረበ፣ "መልካም፡፡ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ስለመሞቱ ትላንት ተነጋግረናል፡፡ ምን አስተያየት አለህ? ሙግቱ ጠንካራ ነው ትላለህ?"

"ጠንካራ ይመስለኛል፡፡ ስለዚህ እርሱን አልፌ አምላክነቱንና ትንሣኤውን እመረምራለሁ፡፡ በመስቀል ላይ ስለመሞቱ በኋላ መከለስ ያስፈልገኝ ይሆናል፡፡"

ማይክ ፈገግ አለ፣ "ስለ እምነትህ ጠንቃቃ ለመሆን አእምሮህን በመጠቀምህ በጣም ደስ ብሎኛል፡፡ ብዙ ሰዎች ወላጆቻቸው ያስተማሯቸውን ነገሮች የሙጥኝ ብለው በመያዝ ደረቅ ክርክር ይከራከራሉ፡፡ ነቢል አንተ ተስፋ ሰጥተኸኛል፡፡ ስላወኩህ ደስ ብሎኛል፡፡" እኔም በአፀፋው ፈገግ አልኩኝ፡፡ ማይክና ጌሪ በጣም ጥሩ ሰዎች ናቸው፡፡ የሆነ ነገር እንዳምን ጫና አላደረጉብኝም፡፡ "ሙስሊም ልጅ ነው" በሚል ዓይነት ዕይታ ከራሳቸው አርቀው አላዩኝም፡፡ እኔም ልክ እንደ እነርሱ እግዚአብሔርንና እውነትን ከልቤ የምፈልግ ሰው መሆኔን ተቀብለዋል፡፡

እንግዲህ አሁን የፍሊጋውን ፍኖት ተያይዣለሁ፤ ስለ ኢየሱስ ሞት፣ አምላክነትና ትንሣኤ መመርመር የምችልበትን መንገድ አውቄያለሁ፡፡ እነዚህ ሦስቱ ሙግቶች በጠንካራ ማስረጃ ከተረጋገጡ ለክርትና ጠንካራ ሙግት አለ ማለት ነው፡፡ ካልሆነ ግን ሙግቱ ደካማ ነው የሚሆነው፡፡ የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ሥርአትን የመሳሰሉት የግል አመለካከቶቼ ቦታ የላቸውም፡፡

ምሳችንን ጨርሰን ተሰነባበትን፡፡ከአንድ ዓመት በኋላ አንድ ታላቅ ሙስሊም ተሟጋች ወደ ከተማይቱ እስኪመጣ ድረስ ጌሪና ማይክን አላገኘኋቸውም ነበር፡፡ የሰውየው ዓላማ ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ በመቶዎች በሚቆጠሩ ሰዎች ፊት መከራከር ነበር፡፡ክርክር የሚገጥመው ደግሞ ከአዲሱ ወዳጄ ከማይክ ጋር ነበር፡፡

# ሙግት ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ

ክርክሩ የተዘጋጀው በሙስሊም ድርጅት ጥያቄ በመሆኑ በኖርፎልክ መስጊድ ከፍተኛ ማስታወቂያዎች ይደረጉ ነበር፡፡ ፖስተሮች ከሳምንታት በፊት ተለጣጥፈዋል፣ በራሪ ወረቀቶች ተሰራጭተዋል፣ በሰዎች ዘንድ የተፈጠረው ጉጉት ውይይቶች እንዲጋጋሉ አድርጓል፡፡ ሙስሊም ሊቅ፣ **ሼኽ** የክርስትናን ሙግት ሲገዳደር ለማየት ጥሩ አጋጣሚ ነበር፡፡ ማይክ ደግሞ የክርክሩ ተሳታፊ በመሆኑ ጉጉቴን ይበልጥ ጨምሮታል፡፡ የክርስቶስን ሞት በተመለከተ ለኔና ለአባ ያቀረበው ሙግት በሙስሊም ሊቅ ፈተና ውስጥ አልፎ መቆም ይችል ይሆን?

**ሼኽ፡** ብዙ ጊዜ በእስልምና ሥነ መለኮት የተመረቀ ሙስሊም መሪ

ሙስሊሙ ተሟጋች ሻቢር አሊ ከቶሮንቶ የመጣ እጅግ ዕውቅ የሆነ ሰው ነበር፡፡ መድረክ የመያዝ ብቃቱ ከፍተኛ ስለነበር አድናቂው ነበርኩኝ፡፡ አስተውሎት የተሞላበት አቀራረቡ ከ 9/11 የሽብር ጥቃት ወዲህ በሙስሊሞች ላይ የተፈጠረውን አሉታዊ አመለካከት ለመዋጋት መልካም አስተዋፅዖ አበርክቶ ነበር፡፡ ዘወትር የሙስሊም ኮፍያውን ያለ ምንም መሽማቀቅ አጥልቆ ይታይ ነበር፡፡ ረጅም ጥቁር ጢምና በሙስሊሞች ባሕል ውስጥ የተለመደው ሰፊ ቀሚስ መለያው ነበር፡፡ አሕመዲ ባይሆንም የተወሰኑ የአሕመዲ ሙግቶችን ስለሚጠቀም በኔ ዕይታ የተዋጣለት ተሟጋች ነው፡፡

ክርክሩ ከመጀመሩ በፊት ዳዊት ሻቢርን ከተማው የማስጎብኘት ዕድል ገጥሞት ነበር፡፡ *“ዘ ፓሽን ኦፍ ዘክራይስት”* የተሰኘውን የሜል ጊብሰን ፊልም እንዲያሳየው ሻቢር ዳዊትን

ስለጠየቀው በሬጀንት ዩኒቨርሲቲ ወደሚገኘው የክርክሩ አዳራሽ ከመሄዳቸው በፊት በጋራ አይተውት ነበር፡፡

ሻቢር ጥቂት ማረፍ ስለነበረበት ዳዊት ቀደም ብሎ በመምጣት በአዳራሹ ውስጥ የሚገኘውን የተሻለ ወንበር ያዘ፡፡ ጌሪ ክርክሩን ለመታደም ወደ ከተማይቱ ተመልሶ ስለመጣ ወደ አዳራሹ ከመግባታችን በፊት ጥቂት አብረን ቆይተናል፡፡ ከአፍታ በኋላ በጌሪና በዳዊት መካከል ተቀምጬ በሰባት መቶ ሰዎች በታጨቀው አዳራሽ ውስጥ የሚደረገውን ክርክር መከታተል ጀመርኩኝ፡፡

ማይክ ለውይይት የሚጋብዝ አቀራረብ ያለው ሰው ነው፡፡ እምነቱን የፈተሸበት ጊዜ እንደነበረና ወላጆቹ የነገሩትን ነገር በጭፍን ከመቀበል ይልቅ ስለ ሕይወትና ስለ እግዚአብሔር እውነቱን ለማወቅ ፍለጋ እንዳደረገ በመናገር ነበር የጀመረው፡፡ የሚያካፍለው መረጃ ክርስትና እውነት መሆኑን እንዳሳመነው ተናገረ፡፡ እኔም በተመሳሳይ የሕይወት አጋጣሚ ላይ ስለነበርኩኝ ይህ ንግግሩ በእጅጉ ቀልቤን ገዛው፡፡

በትንሣኤ አስፈላጊነት ላይ አፅንዖት በመስጠት ንግግሩን ቀጠለ፡፡ "የኢየሱስ ትንሣኤ በእጅጉ ወሳኝ የሆነበት ምክንያት የክርስትና እውነት በዚህ ክስተት ላይ የተንጠለጠለ በመሆኑ ነው፡፡ የኢየሱስ የቤዛነት ሞት ከታወቀበት ጊዜ ጀምሮ የክርስትና መሠረት ሆኖ ቀጥሏል፡፡ ስለዚህ ኢየሱስ ከሙታን ካልተነሣ መሠረቱ ስለሚናጋ ክርስትና ውሸት ይሆናል፡፡ በሌላ ወገን ደግሞ ኢየሱስ በእውነት ከሙታን ከተነሣ ክርስትና እውነት መሆኑን ለማመን የሚያስችል በቂ ምክንያት አለ፡፡ ለዚህ ነው የዛሬው ክርክር ከትምህርታዊ ርዕሰ ጉዳይ ውይይት በእጅጉ የላቀ የሚሆነው፡፡"

ለራሴ እንዲህ ብዬ አሰብኩኝ "እውነትህን ነው ማይክ፡፡ ክርስትና የተመሠረተው በትንሣኤ ላይ ነው፡፡ እውነቱን ማወቅ የሚፈልጉ ነፍሶች አሉ፡፡ ሙግትህ አሳማኝ መሆን አለበት!"

ስለ ማይክ ሙግት ሁለት ሊካዱ የማይችሉ ጉዳዮች አሉ፤ ታሪካዊ መሠረት አለው እንዲሁም ግልፅ ነው፡፡ ሙግቱን በግልፅ አስቀምጦታል፡፡ "በዚህ ምሽት ጠንካራ ማስረጃ

ያላቸውንና በአብዛኞቹ ምሑራን ዘንድ ተቀባይነት ያላቸውን ሦስት እውነታዎች አቀርብላችኋለሁ፡፡ ለእነዚህ ሦስት እውነታዎች የተሻለው ማብራርያ ደግሞ ኢየሱስ ከሞት ተነስቷል የሚል ነው፡፡

“የመጀመርያው እውነታ የኢየሱስ በመስቀል ላይ መሞት ነው፡፡ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ መሞቱ ጉዳዩን በሚያጠኑ ሊቃውንት ሁሉ ዘንድ መቶ በመቶ የሚታመን ነው፡፡”

እያንዳንዱን እውነታ በጠቀሰ ቁጥር ማይክ ማስረጃ ያቀርብ ነበር፡፡ ኢየሱስ በመስቀል ላይ መሞቱን በተመለከተ እርሱና ጌሪ ከአስራ ስምንት ወራት በፊት ያቀረቡልኝን ማስረጃዎች ነበር ያቀረበው፡፡ ይህም አሳቃቂ የሆነውን ግርፋትና ኢየሱስ በመስቀል ላይ መሞቱ በብዙ ምንጮች ውስጥ መጠቀሱን ያጠቃልላል፡፡ የመስቀል ሞትን በተመለከተ ያለው ታሪካዊ ማስረጃ ከግምት ውስጥ ሲገባ በዚህ ዘመን የሚገኙት የኅክምና ባለሙያዎች ኢየሱስ መሞቱን እንደማይጠራጠሩም አከለ፡፡

የመጀመርያውን እውነታ በበቂ ማስረጃ ካረጋገጠ በኋላ ማይክ ወደ ሁለተኛው አለፈ፡፡ “እውነታ ሁለት፡፡ መቃብሩ ባዶ ነበር፡፡ በሚያስገርም ሁኔታ ጉዳዩን ካጠኑት ሊቃውንት መካከል ሰባ አምስት ከመቶ የሚሆኑት መቃብሩ ባዶ መሆኑን ይቀበላሉ፡፡”

ከስቅለቱ ከጥቂት ቀናት በኋላ መቃብሩ ባዶ እንደነበረ የሚያሳምኑ ብዙ ምክንያቶች መኖራቸውን ማይክ አስረዳ፡፡ የመጀመርያው ምክንያት የክርስትና እንቅስቃሴ የተመሠረተው ኢየሱስ በመነሣቱና ሕያው በመሆኑ ላይ ነው፡፡ ክርስትና የተጀመረው በኢየሩሳሌም በመሆኑ የኢየሱስ አስከሬን መቃብር ውስጥ ቢሆን ኖሮ የአይሁድ መሪዎች አስከሬኑን በከተማይቱ ውስጥ እየጎተቱ በማሳየት የክርስትናን እንቅስቃሴ መቅጨት በቻሉ ነበር፡፡ ይህንን አለማድረጋቸው የኢየሱስ መቃብር ባዶ ስለመሆኑ ጠንካራ ማሳያ ነው፡፡

መቃብሩ ባዶ ስለመሆኑ ሌላው ማሳያ አይሁድ ስለ ትንሣኤ ያላቸው አመለካከት ነው፡፡ አብዛኞቹ አይሁድ በአካላዊ ትንሣኤ ያምናሉ፡፡ የሞተው ያው አካል ተነስቶ ኢ-ሟቲ

ወደ ሆነ አካል እንደሚለወጥ ነው የሚያምኑት፡፡ ደቀ መዛሙርቱ የኢየሱስን ትንሣኤ ሲናገሩ አካሉ እንደገና ሕይወት መዝራቱን መናገራቸው በመሆኑ በተዘዋዋሪ መቃብሩ ባዶ መሆኑን ያሳያል፡፡

ሦስተኛው ምክንያት ከአይሁድ መሪዎች ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ስለ ኢየሱስ ሲጠየቁ ደቀ መዛሙርቱ አስከሬኑን እንደሰረቁ በመናገር በተዘዋዋሪ መቃብሩ ባዶ መሆኑን አምነዋል፡፡

ይህንን ነጥብ ሲያጠቃልል ማይክ የኦክስፎርድ ፕሮፌሰር የሆነውን ዊልያም ዋንድ የተሰኘ ምሑር ጠቀሰ፤ "ያሉን ጠንካራ የሆኑ ታሪካዊ ማስረጃዎች ሁሉ መቃብሩ ባዶ መሆኑን ያሳያሉ፡፡ ይህንን የማይቀበሉ ምሑራን ሳይንሳዊ በሆነው የታሪክ ምርምር ላይ በመመሥረት ሳይሆን በሌላ ምክንያት መሆኑ መታወቅ አለበት፡፡"[51]

ይህንን ብሎ ማይክ የመጨረሻ ማስረጃውን አቀረበ፤ "እውነታ ሦስት፤ የኢየሱስ ትንሣኤ ምስክሮች፡፡ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ከሞት መነሳቱንና ለእነርሱ መታየቱን በተደጋጋሚ ሲናገሩ እናያለን፡፡ ይህንን የመሰከሩት ደቀ መዛሙርቱ ብቻ ሳይሆኑ ተቃዋሚዎቹም ጭምር ነበሩ፡፡"

ማይክ ሙግቱን ለማስረዳት ቀዳሚያን የሆኑ ብዝኀ ምንጮችን ጠቀሰ፡፡ የመጀመርያዋ ቤተ ክርስቲያን ኢየሱስ ከሞት ተነስቷል በሚለው ትምህርት ላይ መመሥረትዋንና ደቀ መዛሙርትም ለዚሁ እምነታቸው ሲሉ ለመሞት ፈቃደኛ መሆናቸውን አስረዳ፡፡ ለዚህ እምነት ለመሞት ፈቃደኛ የሆኑት ደቀ መዛሙርት ብቻ ሳይሆኑ ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ተቃዋሚዎቹ የነበሩት ጳውሎስና ያዕቆብም ጭምር ነበሩ፡፡

ይህ ነጥብ ችግር እንዳለበት ታየኝ፡፡ ኢየሱስ እንደታያቸው በማመን ለመሞት ፈቃደኛ የሆኑ ሰዎች መኖራቸው ምን ልዩነት ያመጣል? ይህ ማለት ከሞት ተነስቷል የሚል ድምዳሜ ላይ አያደርስም፡፡ ነገር ግን እንደታያቸው በእውነት ማመናቸውንና ቢያንስ አለመዋሸታቸውን እንደሚያመለክት በማስረዳት ማይክ ይህንን ተቃውሞ

አከሸፈው፡፡ነጥቡ በአጭሩ “ውሸታሞች ለሚናገሩት ነገር ሰማዕት የመሆን ፍላጎታቸው አናሳ ነው” የሚል ነበር፡፡

በመጨረሻም ሦስቱን እውነታዎች ካቀረበ በኋላ ማይክ ሙግቱን በግልፅ አስቀመጠ፤ “እስኪ በሦስቱ እውነታዎች ላይ ተመስርተን የሙግት ሐሳብ እናቅርብ፡፡ እነዚህ እውነታዎች በታሪካዊ ማስረጃዎች የተረጋገጡ መሆናቸውንና አስገራሚ በሆነ ሁኔታ በአብዛኞቹ ምሑራን ዘንድ ተቀባይነት እንዳላቸው ተመልክተናል፡፡ ተጠራጣሪዎችን ጨምሮ ይህንን ርዕሰ ጉዳይ ያጠኑ ምሑራን ሁሉ ማለት ይቻላል እነዚህን እውነታዎች ይቀበላሉ፡፡ የኢየሱስ ትንሣኤ ያለምንም ችግር እነዚህን እውነታዎች ማብራራት እንደሚችል ማየት አያዳግትም፡፡ እነዚህን እውነታዎች ማብራራት የሚችል አማራጭ ትወራ እስካልተገኘ ድረስ  የኢየሱስ ትንሣኤ ታሪካዊነት አጠራጣሪ ባልሆነ ሁኔታ ተቀባይነት ማግኘት ይችላል፡፡”

በሌላ አባባል የኢየሱስ ትንሣኤ የሚታወቁትን እውነታዎች በተሻለ ሁኔታ ማብራራት እንደሚችል ነው ማይክ እየተሟገተ የሚገኘው፡፡ ሌሎች መላ ምቶች ተቀባይነት እንዲያገኙ ለማድረግ መጠምዘዝ፣ መለጠጥና እውነታዎችን መካድ ይጠይቃሉ፡፡

በተቀመጥኩበት ወንበር ላይ ወደ ኋላ ተለጥጬ በመቀመጥ ሙግቶቹን አሰላሰልኳቸው፡፡ የሆነ ችግር አለ፡፡ በቀላሉ የሚፈታ ይሆን?

አማራጭ ትንታኔዎችን ማሰብ ጀመርኩኝ፡፡ “ኢየሱስን ያዩ የመሰላቸው ሰዎች የቁም ቅዠት ውስጥ ገብተው ቢሆንስ?” እንደርሱ ከሆነ መቃብሩ ባዶ ሊሆን አይችልም፡፡ ይችላል እንዴ? ደግሞስ ብዙ ሰዎች በተለያዩ ጊዜያት ስለ አንድ ጉዳይ የቁም ቅዠት ሊቃዡ የሚችሉት እንዴት ሆኖ ነው? በክርክሩ ወቅት አምስት መቶ ሰዎች በአንድ ጊዜ ከሞት የተነሣውን ኢየሱስን እንዳዩት በ1ቆሮንቶስ 15 ላይ የተጻፈውን ቃል ማይክ ጠቅሶ ነበር፡፡ ሰዎች በጋራ ሆነው የሚቃዡበት ሁኔታ ይኖር ይሆን? በተጨማሪም ይህ ጉዳይ ጳውሎስን የመሳሰሉት ጠላቶች ከሞት የተነሣውን ኢየሱስን ሊያዩ የቻሉበትን ሁኔታ አያብራራም፡፡ የኢየሱስን ትንሣኤ በተመለከተ ሊቃዥ የሚችልበት ምክንያት የለም፡፡

“ኢየሱስን ሳይሆን ሌላ ሰው አይተው ቢሆንስ?” ይህንን አማራጭ ለጥቂት ጊዜ ባስበውም አለመሥራቱን ተረዳሁ፡፡ እንደቀደመው ሁሉ መቃብሩ ባዶ ሊሆን አይችልም፡፡ በተጨማሪም ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስን ከሌላ ሰው ጋር ማምታታቸው የሚመስል ነውን? ከኢየሱስ ጋር ከአንድ ሺህ በላይ ቀናት ያህል ቆይተዋል፡፡ ይህ ጥሩ ማብራርያ አይደለም፡፡

“ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሞቶ ባይሆንስ?” ይህ የአሕመዲ አቋም ሲሆን ማይክና ጌሪ በጥሩ ሁኔታ ምላሽ ሰጥተውታል፡፡ ነገር ግን ሻቢር የመክፈቻ ንግግሩን ባደረገ ጊዜ ይህንን ሐሳብ በመደገፍ ሊናገር እንደሆነ ግልፅ ሆኖ ነበር፡፡ ይህ የተወራለት ዕውቅ ሰው የኛን አቋም ማፅናት የሚችል ማስረጃ ያቀርብ ይሆን? በሚል ጆሮዬን አቁሜ መስማት ጀመርኩኝ፡፡

ሻቢር ገና መናገር ሲጀምር የመድረክ ልምድ እንዳለውና ስለ ጉዳዩ በቂ መረጃ እንዳለው ግልፅ ሆነልኝ፡፡ “ሙስሊም መሆኔ ለኢየሱስ ትንሣኤ የቀረቡትን ማስረጃዎች ትኩረት ሰጥቼ እንዳላይ ያግደኝ ይሆናል፡፡ አስቀድሜ ይህንን ከተናዘዝኩ ዘንዳ ወደ ጎን አድርጌው እውነታዎቹን በግልፅ ማየት እፈልጋለሁ፡፡ ስለ ትንሣኤ የተሰጡትን ማስረጃዎች አሳማኝ ሆነው አላገኘኋቸውም፡፡ አንድ ሰው ወደ እኔ መጥቶ አንድ ሰው ሞቶ እንደነበረና ከሦስት ቀናት በኋላ እንደታየ ቢነግረኝ ‹መጀመርያውኑ መሞቱን እርግጠኛ ነህን?› ብዬ እጠይቀዋለሁ፡፡”

“ወንጌላትን አበጥረው ያዩ ምሑራን ‹ኢየሱስ እንዲሞት ያደረገው ምንድነው?› የሚል ጥያቄ አንስተዋል፡፡ ጽሑፎቹን ያነበቡ ዶክተሮች ምን እንደገደለው ሊስማሙ አልቻሉም፡፡ ጽሑፎቹን ባሉበት ሁኔታ ወስደን ብናያቸው ኢየሱስ በመስቀል ላይ መሞቱን እርግጠኛ አያደርጉንም፡፡”

ሻቢር ብዙ የተናገራቸው ነገሮች ቢኖሩም የሙግቱ አንኳር ነጥብ ይህ ነበር፡፡ ነገር ግን ክርክሩ በተጋጋመ ቁጥር ሻቢር እውነትን በቅንነት የሚፈልግ ሰው ማድረግ ከሚገባው በላይ እውነታዎችን መካድ እንደሚያስፈልገው ግልፅ እየሆነ መጣ፡፡ የተለመደው

የስቅለት ሂደት በኢየሱስ ላይ መፈፀሙን ቢክድም ለዚህ የሚሆን ምንም ምክንያት አልሰጠም፡፡ የዮሐንስ የስቅለት ዘገባ ከታሪክ ጋር የበለጠ የሚጣጣም መሆኑን ቢያምንም ነገር ግን ትክክለኛነቱን ክዷል፡፡ ሙስሊም ያልሆኑ ሊቃውንት በሙሉ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ መሞቱን እንደሚቀበሉ ቢያምንም ድምዳሜያቸው ስቅለት ላይ የተመሠረተ መሆኑን በመካድ እርስ በርሱ የሚጠፋፋ ሐሳብ አቅርቧል፡፡ ኢየሱስ ስለመሞቱ በወንጌላት ሁሉ ውስጥ የተነገሩትን ግልፅ ንግግሮች በሙሉ ክዷል፡፡ ሙግቱን ለማቆም እያንዳንዱን ጥቃቅን መረጃ ሳይቀር አንድ በአንድ መካድ ነበረበት፡፡

በሻቢር የንግግር ችሎታና ጥዑመ ልሳን ብንመሰጥም ነገር ግን ሙግቶቹን ስንፈትሽ ወደ ሁለት ድምዳሜዎች የሚያመሩ ሆነው እናገኛቸዋለን፤ መረጃዎችን ዝም ብሎ ከመጠራጠር በዘለለ የሚያቀርበው ማስረጃ አልነበረውም እንዲሁም የራሱን እምነት በተመለከተ ተመሳሳይ ሚዛን በመጠቀም በጥርጣሬ ዓይን የማየት ምንም ፍላጎት አልነበረውም፡፡ ይህ አድሎአዊ አካሄዱ ከእርሱ ጋር የመስማማት አዝማምያ ያለው ሙስሊም ብሆንም እንኳ አልተሰወረብኝም ነበር፡፡

ክርክሩ ካበቃ በኋላ ማይክና ሻቢር ወደ ተለያዩ ክፍሎች በመሄድ የታዳሚዎችን ጥያቄዎች በግል ይመልሱ ነበር፡፡ የተነገሩትን ነገሮች በማሰላሰልና ትርጉማቸውን በመፈለግ በብስጭት መንፈስ ከወንበሩ ላይ ተነሳሁ፡፡ እኔ፣ ማይክ፣ ዳዊትና ጌሪ ወደ መኪና ማቆሚያው ከማምራታችን በፊት በክፍሉ ውስጥ ወዲያና ወዲህ በመዘዋወር ለአንድ ሰዓት ያህል ክርክሩን አሰላሰልኩት፡፡ ምሽቱ ጨለማና ቀዝቃዛ ስለነበር ስናወራ ሳለን ትንፋሻችን አየር ውስጥ ጠጥሮ ሲነጣ ማየት እንችል ነበር፡፡

ማይክ ወደ እኔ በመዞር እንዲህ አለኝ፤ “ነቢል ምን እንደምታስብ የማወቅ ጉጉት አድሮብኛል፡፡ በኔና በሻቢር መካከል አንድ መቶ ነጥቦችን እንድትሰጥ ብትጠየቅ ስንት ስንት ትሰጠናለህ?”

“ነጥቡን በምሰጥበት ምክንያት ላይ የተመሠረተ ነው” በማለት ጀመርኩኝ፡፡ “ስለ መድረክ አያያዝና የንግግር ችሎታ የምትጠይቀኝ ከሆነ ለሻቢር ሰማንያ ላንተ ደግሞ ሃያ ነው የምሰጥህ፡፡”

ማይክ ትከሻውን ናጥ በማድረግ እንዲህ አለ፤ “ስለ ግልፅነትህ አመሰግናለሁ፡፡ አንዳንድ ቃላትን ስናገር እደነቃቀፍ ነበር እንዲሁም ያዘጋጀሁት ስላይድ በትክክል አልሠራ ብሎኝ ነበር፡፡ ስለዚህ ያልከው ይገባኛል፡፡ ነገር ግን ከዚህ ይልቅ በሙግት ሐሳቦቹ ላይ ያተኮርኩ ይመስለኛል፡፡ አጠቃላይ ሙግቱን በተመለከተ ምን ታስባለህ?”

ለአፍታ አሰብ አደረኩኝ፡፡ “በዚያ ረገድ ያሸነፍክ ይመስለኛል፡፡ ላንተ ስድሳ አምስት ለሻቢር ደግሞ ሰላሳ አምስት ከመቶ እሰጣለሁ፡፡”

ጌሪ የደስታ ጩኸት አሰማ፡፡ “ይህ ድንቅ ነው ማይክ! ዕውቀት አለው ከተባለ ሙስሊም አኳያ ትንሣኤን የሚደግፍ ማስረጃ እጥፍ ያህል አሳማኝ ነው፡፡ ስለዚህ ነቢል ሙግቱ በጣም ጥሩ እንደሆነ ታስባለህ አይደል?”

ትከሻዬን ናጥ አደረኩት፡፡ “አሁንም ለጥርጣሬ ቦታ ቢኖርም እውነቱን እንነጋገር ከተባለ የተሻለው ማብራርያ እርሱ ይመስለኛል፡፡”

ዳዊት አጣብቂኝ ውስጥ ሊከተኝ የነበረውን ፍላጎት መቋቋም አልቻለም፡፡ “ስለዚህ ነቢል ክርስቲያን ሆነሃል ማለት ነው?”

“ሲያምርህ ይቅር!” ዳዊትን ትከሻው ላይ መታ አድርጌው ሳቅሁኝ፡፡ “ከዚህ በላይ ለኔ አስፈላጊ ጉዳይ የሆነውን ኢየሱስ ስለ አምላክነቱ የመናገሩን ጉዳይ መች አየንና፡፡ በተጨማሪም እስልምናን የመመርመርያ ጊዜው ሲደርስ ሙግቶቹ ምን ያህል ጠንካራ እንደሆኑ ታያለህ፡፡ ልትቋቋመው አትችልም፡፡ ሙግቶቹ ሲቀጥሉ ክርስትና በእስልምና ላይ የበላይነትን የሚጎናፀፈው በትንሣኤ ረገድ ብቻ ነው፡፡”

ጌሪ የሰማውን ማመን የቸገረው ይመስል ማይክን ተመለከተው፡፡ “ብቸኛው ትንሣኤ ነው? ወዳጄ የሚያስፈልገን እርሱ ብቻ ነው!”

አጥንት ውስጥ የሚገባው የምሽቱ ቅዝቃዜ እስኪረታን ድረስ ለተወሰኑ ደቂቃዎች አራታችንም ስለ ክርክሩ ተወያየን፡፡ ጌሪን መቼ በድጋሜ እንደማየው ባላውቅም በስንብት መንፈስ አቀፍኩት፡፡ ማይክ በየወሩ በቤቱ ወደሚደረገው የውይይት ስብሰባ ጋበዘኝ፡፡ እኔም ለመምጣት እንደምሞክር ነገርኩት፡፡ ዳዊትና እኔ ወደ መኪናዬ በመሄድ ሳይታወቀን ለሁለት ሰዓታት ያህል ስለ እስልምናና ስለ ክርስትና ተወያየን፡፡

በመጨረሻም ሬጀንት ዩኒቨርሲቲን ለቅቄ ወደ ቤቴ ስመለስ አንዳንድ ነጥቦች በልቦናዬ ውስጥ ግልፅ ሆነውልኝ ነበር፡፡ መጀመርያ ጠንካራ በሆነው ሙግታቸው እንደረቱኝ ገባኝ፡፡ ሙግቶቹ ደግሞ የእውነት ጠንካሮች ነበሩ፡፡ አጠቃላዩ ታሪካዊ ማስረጃ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ መሞቱን ያመለክታል፡፡ ሞቱን የከበቡትን ነገሮች ደግሞ በበለጠ ሁኔታ ማብራራት የሚችለው ትንሣኤው ነው፡፡

ነገር ግን አሁን የኔ ተራ ነው፡፡ ኢየሱስ አምላክ መሆኑን እንዳልተናገረ የሚያሳዩ ማስረጃዎቼን በሙሉ በማዋቀር የማቀርብበት ጊዜ ነው፡፡ ቀጣዩ ርዕሰ ጉዳይ ወሳኝ የሆነ ፍልሚያ መሆኑን በልቤ ተረድቻለሁ፤ ወደ ጦርነቱም ለመግባት ዝግጁ ነበርኩኝ፡፡

*በሁስተን ባፕቲስት ዩኒቨርሲቲ ተባባሪ ፕሮፌሰር በሆኑትና የኢየሱስ ትንሣኤ የሚል ርዕስ ያለው መጽሐፍ ደራሲ በሆኑት በዶ/ር ማይክ ሊኮና የተዘጋጀውን የሊቅ አስተዋፅዖ ለማንበብ contributions.NabeelQureshi.com ይጎብኙ፡፡*

# ክፍል ፰

# ኢየሱስ ማን ነው? መሲህ ወይንስ መለኮታዊ ወልደ እግዚአብሔር?

*ወደዚህ ዓለም ገብተሃልን? ሰው ሆነሃልን? ያ ሰው ደግሞ ኢየሱስ ይሆንን?*

# ዘረመልና ኢየሱስ

ኤም ጂ ቢ 101 ሃያ ሺህ ተማሪዎች በሚኖሩበት ካምፓስ ውስጥ ትልቁ ክፍል ሲሆን እንደ ትርዒት ማሳያ ክፍል ዓይነት ነበር፡፡ እኔና ዳዊት በአንድ ጥሩ ምክንያት የተቻለንን ያህል ከፕሮፌሰሩ ርቀን ወደ ኋላ አካባቢ ተቀምጠን ነበር፡፡ የፕሮፌሰሩ ንግግር አስቂኝ ሆኖ ስላገኘነው ሳይታወቀን ሳቃችን ይመጣ ነበር፡፡

ዶ/ር ኦስጉድ ጎበዝ መምህር ስለነበር እኔና ዳዊት ትምህርቱን ከክፍል ውጪ ጊዜ ሰጥተን ማጥናት እስከማያስፈልገን ድረስ በጥሩ ሁኔታ ያስተምር ነበር፡፡ ነገር ግን ያልተለመዱ ቃላትን ስለሚጠቀም ከጊዜ በኋላ የቃላት ምርጫው አስቂኝ እየሆነብን መጥቷል፡፡ በጣም ከተለመዱት ቃላት መካከል ካርቱን የሚለው አንዱ ሲሆን ከግራፍ ጀምሮ እስከ ቪድዮ ድረስ ያሉትን ሁሉ ለማመልከት ይገለገልበታል፡፡ እኛ ደግሞ ይህችን አጋጣሚ ጠብቀን መሳቃችን የተለመደ ነበር፡፡

በክፍሉ ፊት ለፊት ወዳለው ምስል በመጠቆም ንግግሩን ጀመረ፡፡ “ተማሪዎች በማስከተል በጥልቀት ማወቅ የሚገባችሁ ስለ ዘረመል (ዲ ኤን ኤ) መተካካት ነው፡፡ ሴሎች ወደማይቀረው ሞታቸው ሲሄዱ በሙቶዎች ወይም በሺዎች ለሚቆጠሩ ጊዜያት በመከፋፈል የዘረመል መረጃቸውን ወደ ቀጣዮቹ ሴሎች ያሸጋግራሉ፡፡ ይህ ነው እንግዲህ የዘረመል መተካካት የሚባለው፡፡ ሂደቱ ሙሉ በሙሉ እንከን የለሽ ባይሆን ኖሮ ዝርያዎች የመተካካታቸው ጉዳይ ፈፅሞ የማይቻል በሆነ ነበር፡፡

የመተካካቱንሂደትለመረዳት የዘረመል ሞሌኪዩሎችን ከእንደገና ማየት ያስፈልገናል፡፡ የዘረመል ካርቱን እዚህ ጋ አለላችሁ፡፡”

የተናነቀኝን ሳቅ ጎሮሮዬን በማጥራት አሳለፍኩት፡፡

“ዘረመል ከሁለት የስኳር-ፎስፌት ቅንጣቶች የተሰሩ በኑክሎታይድ የተጣመሩ ሁለት ጫፎች እንዳሉት ቀደም ሲል ተናግሬያለሁ፡፡ በያንዳንዱ የዘረመል ቅንጣት ውስጥ ያሉት ከካርበን እስከ ፎስፌት የሚገኙት ውሁዶች ከ 5’ እስከ 3’ እንደሚሄዱ ልብ በሉ፡፡ ይህ ነው የእያንዳንዱ ቅንጣት መሠረት በመሆን አቅጣጫዊነት እንዲኖረው የሚያደርገው፡፡”

ዳዊት ወደኔ ጠጋ ብሎ እንዲህ አለኝ፤ “አቅጣጫዊነት? አቅጣጫ የሚለው ቃል አልበቃ ብሎት ነው ቅጥያ የጨመረበት?” ሳቃችንን መቆጣጠር ተሳነን፡፡

ነገር ግን ዶ/ር አስጉድ ገና አልጨረሰም፡፡

“በኒኩሎታይድ ወለል አፈጣጠር ምክንያት እያንዳንዱ ጫፍ ወደ ተቃራኒ አቅጣጫ ነው የሚያመለክተው፡፡ ሁለቱ ጫፎች ከግምት ውስጥ ሲገቡ ዘረመል ፀረ-አቅጣጫዊነት ይንፀባረቅበታል፡፡”

እኔና ዳዊት የሰማነውን ማመን ተስኖን በፈጠጡ ዓይኖች ዞረን ተያየን፡፡ ጆሮዎቻችን የሰሙትን ማመን ተስኖናል፡፡ ሰውየው ‹ፀረ-አቅጣጫዊነት› የሚለውን ቃል ተናግሮታል፡፡ ዶ/ር አስጉድ የሳቅ ጋስ የረጨብን ይመስል ድምፃችንን አፍነን መንፈቅፈቅ ጀመርን፡፡ሳቃችንን ማቆም ተስኖን ለደቂቃዎች ያህል በተቀመጥንበት ተርገፈገፍን፡፡ ሎሎች ተማሪዎች ዞረው ወደኛ ማየት ሲጀምሩ ሳቃችንን ለመግታት ተገደድን፡፡ እኔ የቻልኩትን ያህል ጉንጬን ነክሼ ያዝኩት፡፡

ራሴን ወደመቆጣጠር ስመጣ *“ፀረ-አቅጣጫዊነት”(anti directionality)* የሚለውን ቃል ወረቀት ላይ ጽፌ ለዳዊት አቀበልኩት፡፡ እንደገና በሳቅ ከተንፈቀፈቀ በኋላ፤ ሌላ ነገር በወረቀት ላይ ጽፎ አቀበለኝ፡፡ *ምስለፀረአቅጣጫዊነት* ይላል፡፡ ወረቀቶችን እየተቀባበልን

ሆዳንች እስኪቆስል ድረስ ከሳቅን በኋላ መጨረሻ ላይ *quasipsuedoantidirectionalityeousnessificationism* የሚል ቃል ፈጥረን አረፍን፡፡

ሳቃችንን መቆጣጠር ስለተሳነን ትምህርት ገና መጀመሩ ቢሆንም ክፍሉን ለቀን ለመውጣት ተገደድን፡፡

የተማሪዎች ተወካይ አዳራሽ እስክንደርስ ድረስ እየተቃለድንና እየተሳሳቅን ሄድን፡፡ ትንፋሼን ለመሰብሰብ ቦርሳዬን አውርጄ ክፍሉ ፊት ተቀመጥኩኝ፡፡ ዳዊት የተለመደው ቦታው ላይ ተቀመጠ፡፡ ቀልዱን ትተን ይህንን ወርቃማ ጊዜ እንዴት መጠቀም እንዳለብን ሁለታችንም በየፊናችን ማሰብ ጀመርን፡፡

ትተን የወጣነውን የትምህርት ክፍለ ጊዜ ለማካካስ የጄኔቲክስ ትምህርቴን ለማጥናት ከመወሰኔ አንድ ሐሳብ ተከሰተልኝ፡፡ “ዳዊት ጄኔቲክስ ለክርስትና እምነት ትልቅ ችግር የሚፈጥር መሆኑን የምታውቅ ይመስለኛል፡፡”

ዳዊት የተገረመ በሚመስል አስተያየት እየተመለከጀተኝ “እንዴት እንዴት?” አለኝ፡፡

“እስኪ አስበው፡፡ ለምንድነው ልጅ የምንወልደው? ለምንድነው አንድ ዝርያ መተካካት የሚያስፈልገው?”

ዳዊት ምንም ሳይመልስ ጠበቀኝ፡፡ ጥያቄዎቼን በትክክል ለመመለስ የተሻለው መንገድ እንድናገር ቅድሚያ በመስጠት እስክጨርስ ድረስ መጠበቅ መሆኑን ተረድቷል፡፡

“መዋለድ ዘርን ለማስቀጠል ነው፡፡ ልክ አስጉድ እንዳለው ሴሎች ይሞታሉ፤ ስለዚህ ከመሞታቸው በፊት በተቻላቸው መጠን ራሳቸውን ይተካሉ፡፡ ችግሩ ግልፅ ነው፡፡ እግዚአብሔር ኢ-ሟቲ ከሆነ ልጅ ለምን ያስፈልገዋል?”

የዳዊትን ትኩረት ለማግኘት ጥቂት ዝም ካልኩኝ በኋላ ቀጠልኩኝ፡፡ “አይሁድ ይህ ስለሚገባቸው እግዚአብሔር ልጅ ወልዷል ብለው አያምኑም፡፡ ኢየሱስ ደግሞ አይሁዳዊ ነበር፡፡ እርሱ ከሄደ በኋላ የሮማውያን ባሕል ከቤተ ክርስቲያን ትምህርት ጋር ተደባልቆ

መሆን አለበት፡፡ ሮማውያን አማልክት ሴቶች እንዲፀንሱ በማድረግ የሰውና የአምላክ ድብልቅ የሆኑ ፍጥረታትን ስለመውለዳቸው የሚናገሩ ብዙ ታሪኮች አሏቸው፡፡”

ዳዊት ግልፅ እንዳደርግለት ጠየቀኝ፡፡ “ክርስቲያኖች እንዲህ ብለው እንደሚያስተምሩ ነው የምታስበው?”

“እንደርሱ አይደል የምትሉት? መንፈስ ቅዱስ ወደ ማርያም በመምጣት እንድትፀንስ አደረጋት ትላላችሁ፡፡ የክርስትናው ኢየሱስ ከሰውና ከአምላክ ስለተወደለ ግማሽ ሰው ግማሽ አምላክ መሆን አለበት፡፡ ነገር ግን እውነታውን ልንቀበል ያስፈልገናል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ ሰው ስለሆነው ኢየሱስ ነው የሚናገረው፡፡ መራቡ፣ መጠማቱ፣ መድማቱ፣ በዕውቀት መወሰኑና መሞቱ ያንን ያመለክታል፡፡”

ሙግቶቼን ለማሰባሰብ እየሞከርኩ ቢሆንም እነዚህ ነጥቦች አዲስ አይደሉም፡፡ እንዲያውም እኔ የፈጠርኳቸው አልነበሩም፡፡ ለሁለት አስርተ ዓመታት የተማርኳቸው እስላማዊ ትምህርቶች “አላህ አልወለደም አልተወለደም” የሚለውን የቁርአን ጥቅስ የሚደጋግሙ ናቸው፡፡[52]እኔም ይህንኑ የአባቶቼን ትምህርት ለማስፋፋት በዕውቀትና በመንፈሳዊ ቅንዓት የተጠቀለሉ ሙግቶችን ለማቅረብ እየሞከርኩ ነው፡፡ የኢየሱስን ጌትነት ለመቃወም እያደረኩ ያለሁት ፍልሚያ ከልጅነት እስከ ዕውቀት የተማርኳቸውን ትምህርቶች በሙሉ የሚወክል የማንነቴ መገለጫ ነበር፡፡ ፍልሚያውን ለማድረግ በፅናት ቆሜያለሁ፤ ወደ ኋላ ሊመልሰኝ የሚችል ምንም ዓይነት ኃይልም የለም፡፡

ዳዊት ደንግጦ ይሁን፣ ፈርቶ ይሁን፣ መንፈስ ቅዱስ መርቶት ይሁን፣ መልስ ስላልነበረው ይሁን ብቻ ምንነቱን በማላውቀው ምክንያት ምንም መልስ አልሰጠኝም ነበር፡፡ “ነቢል የኢየሱስን አምላክነት የተለመከቱ በክርስቲያኖች የተጻፉ መጻሕፍትን አንብበህ ታውቃለህ?”

“አላውቅም ነገር ግን ከብዙ ክርስቲያኖች ጋር አውርቻለሁ፡፡”

“መልካም፡፡ እስኪ እንደዚህ እናድርግ፡፡ ነገ መጽሐፍ እሰጥሃለሁ፡፡ ጊዜ ስታገኝ ታነበዋለህ፡፡ ከዚያ እንነጋገራለን፡፡”

ደስተኛ አልነበርኩም፡፡ ዳዊት ለማቀርበው ክርክር መልስ ሳይሰጥ አያልፍም ነበር፡፡ “ለምንድነው አሁን መነጋገር የማንችለው?”

“በጄኔቲክስ ክፍለ ጊዜ የዘለልነውን ክፍል ማጥናት ስለምፈልግ፡፡”

“ዳዊት፣ ለዚህ ተጠያቂው ማነው?”

“ካንተ በላይ ተጠያቂ ሊኖር አይችልም ወዳጄ፡፡”

“በቃላት ላይ ቅጥያ የመጨመሩን ቀልድ የጀመርከው እኮ አንተ ነህ!”

የዚያን ዕለት ከጄኔቲክስ ጥናታችንም ከሥነ መለኮት ውይይትም ሳንሆን ጊዜያችንን በከንቱ ጨረስን፡፡ ቢሆንም ግን ለበጎ ነበር፡፡ እስላማዊው ማንነቴ የክርስቶስን አምላክነት በመቃወም ላይ የተመሠረተ ስለነበር በዚህ ጊዜ ይህንን ርዕስ መወያየት ፍሬ አልባና የመቃቃር ምክንያት ይሆን ነበር፡፡

መጀመርያ የሚያስፈልገው የክርትቶስን አምላክነት የሚቃወመውን የተሳሳተውን እስላማዊ የአመለካከት ዳዋ የሚመነጥር መንገድ ከፋች ነገር ነበር፡፡ ዳዊት ሊሰጠኝ ያሰበው መጽሐፍ ትክክለኞቹን ጥያቄዎች እንዳነሳ ይረዳኛል እንዲሁም አቅጣጫ ይጠቁመኛል፡፡ መጽሐፉ አነስተኛ መሆኑ ደግሞ አንብቦ ለመጨረስና ለመገንዘብ ጠቃሚ ነበር፡፡

# ኢየሱስ የአናፂዎች ፈጣሪ

ዳዊት በጠረጴዛው ላይ ወደኔ ገፋ ያደረጋትን መጽሐፍ ተመለከትኳት፡፡ ምሳዬን በልቼ ስለነበር ትኩረቴን ለመሰብሰብ አልተቸገርኩም ነበር፡፡ አነስተኛ መጠን ያላት ስለነበረች በጉጉት ስሜት አንስቼ በፍጥነት ገፆቿን እያገላበጥኩኝ ማየት ጀመርኩኝ፡፡ ከዚያ መልሼ ወደ ዳዊት እየገፋኋት "ኢየሱስ ከአናፂዎች በላይ መሆኑን አውቃለሁ" አልኩት፡፡

ዳዊት ዘና የማለት ስሜት ውስጥ ነበር፡፡ መቸስ አርብ ለተማሪ አስደሳች ቀን መሆኑ ይታወቃል፡፡ "አዎ ግን እርሱ ከአናፂዎች በእጅጉ ይልቃል፡፡ አናፂዎችን የፈጠረው እርሱ ነው፡፡"

ፈገግ አልኩኝ፡፡ "እንደርሱ እንደምትል አውቃለሁ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ እንደርሱ አይልም፡፡"

"ይላል እንጂ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ አናፂዎች ሁሉ በእርሱ ተፈጠሩ ይላል፡፡"

"ዳዊት ባትቀልድ ይሻላል፡፡ እኔ ከምር ነው እየተናገርኩ ያለሁ፡፡" ፊቴን የማስመሰል ለማኮሳተር ሞከርኩኝ፡፡

የዳዊት ፈገግታ ጨመረ፡፡ "እኔም ከምሬ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ‹ሁሉም በኢየሱስ ሆነ› ሲል ምን ለማለት ፈልጎ ይመስልሃል?"

"እንደርሱ ይላል እንዴ?" የምሬን ተኮሳተርኩኝ፡፡

"አዎ፡፡"

“በወንጌላት ውስጥ ሊሆን አይችልም፡፡ በወንጌላት ውስጥ የተጻፈውን ነው ማየት የምፈልገው፡፡”

“እንግዲህ ለመጨረሻ ጊዜ ርዕሱን እንዳየሁት....” ጮክ ብሎ ከመናገሩ በፊት የውሸት ሳል አሳለ፣ **“የዮሐንስ ወንጌል”** እንደገና ሳለ “ወንጌል ነው ይላል፡፡”

“የእውነት በዮሐንስ ውስጥ ነው የሚገኘው?”

“አዎ፡፡” የቅንነት ፈገግታ አሳየኝ፡፡

ይህ ሙስሊም አስተማሪዎች ስለ ኢየሱስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደተነገረ ከሚያስተምሩት ትምህርት ሁሉ ጋር የሚፃረር ነው፡፡ ወንጌል ኢየሱስ ፈጣሪ መሆኑን ሊናገር ይችላልን? ካናገርኳቸው ክርስቲያኖች መካከል ማናቸውም ይህንን ክፍል አላሳዩኝም፡፡ ብዙዎቹ እንዲህ የሚል ነገር ካለ እንዲያሳዩኝ ጠይቄያቸዋለሁ፡፡ ከዳዊት ውጪ ሌላ ሰው ይህንን ቢነግረኝ ኖሮ ከራሱ ፈጥሮ እንተናገረ ስለማስብ አላምነውም ነበር፡፡ ነገር ግን ዳዊት እንደማያታልለኝ ጠንቅቄ አውቃለሁ፡፡ ዳዊት ምናልባት የሆነ ነገር አጣሞ እየነገረኝ ይሆን? አላውቅም ግን ግራ ገብቶኛል፡፡

ዳዊት የፊቴን ገፅታ ካስተዋለ በኋላ መጽሐፉን በቀስታ መልሶ ወደ እኔ ገፋው፡፡ ልወስደው እጄን ስዘረጋ በፍጥነት መልሶ በመውሰድ ፈገግ ብሎ “ግን እኮ ኢየሱስ ከአናፂዎች በላይ መሆኑን አውቀሃል አለኝ፡፡”

ወደ ፊት ተዘርግቼ መጽሐፉን ከዳዊት እጅ በመንጠቅ “ጉራ መንዛትህን አቁም ባክህ” አልኩት፡፡

በሳምንቱ የእረፍት ቀናት በአባ የጥናት ክፍል ውስጥ በሆዴ ተኝቼ ያቺን ከታብ በጥንቃቄ ማጥናት ጀመርኩኝ፡፡ “ከአናፂ በላይ” የሚል ርዕስ ያላት ይህች መጽሐፍ ከእጄ መዳፍ ብዙም የማትበልጥ ስትሆን አንድ መቶ ገፆች ብቻ ነበሯት፡፡[53]የደራሲው ስም ጆሽ ማክዱዌል ሲሆን ከዚህ ቀደም ስሙን አውቀዋለሁ፡፡ አባ “የእስላም ሙግት” የሚል ርዕስ ያለው መጽሐፍ ነበረው፡፡ መጽሐፉ በማክዱዌልና ሙስሊም ዓቃቤ እምነት

በነበረው በአሕመድ ዲዳት መካከል በ1981 የተደረገውን ክርክር በጽሑፍ የሚያቀርብ ነው፡፡ ተለቅ ያለ መጠን የነበረውና እስልምናን በመከላከል ላይ ያተኮረ ስለነበር አላነበብኩትም ነበር፡፡ የኔ ትኩረት እስልምናን መከላከል ሳይሆን ክርስትናን መርታት ነበር፡፡

ነገር ግን በጆሽ ማክዱዌል የተጻፈች አንብበኝ ብላ የምትለማመጠኝ አነስተኛ መጽሐፍ እጄ ገብታለች፡፡ የማክዱዌል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ሁሉ ትክክል መሆናቸውን ለማረጋገጥ እያየኋቸው ንበባቤን ቀጠልኩኝ፡፡ ለማመን ቢያስቸግርም አንድ ነገር ልናዘዝ፡፡ ክርስትናን ውድቅ ለማድረግ ብዙ ጥቅሶችን ብሸመድድም መጽሐፍ ቅዱስን ከፍቼ ሳነብ ይህ የመጀመርያ ጊዜዬ ነበር፡፡ ከዚህ ቀደም ያነበብኳቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ሁሉ የሚገኙት በሙስሊሞች መጻሕፍት ውስጥ ነበር፡፡

የማክዱዌልን መጽሐፍ በሰዓታት ውስጥ አንብቤ ጨረስኩኝ፡፡ አብዛኛው ክፍል ሰዎች ለእምነታቸውና ለኢየሱስ ትኩረት እንዲሰጡ የሚያበረታቱ ናቸው፡፡ እኔ ደግሞ ያንን አድርጌያለሁ፡፡ ትኩረቴን የበለጠ የሳበኝ ምዕራፍ ሁለተኛው ሲሆን “ኢየሱስን ልዩ የሚያደርገው ምንድነው?” ይላል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ማክዱዌል አዲስ ኪዳን ኢየሱስ አምላክ መሆኑን እንደሚያስተምር ያስረዳል፡፡ ንባቤን ከጨረስኩኝ በኋላ ያንን ክፍል ከእንደገና በአንክሮ ለማጤን ወሰንኩኝ፡፡

ብዙዎቹን የማክዱዌልን ሙግቶች በቂ ሆነው አላገኘኋቸውም፡፡ እርሱ ከግምት ያልከተታቸው ሌሎች አማራጭ ትንታኔዎች ነበሩ፡፡ ለምሳሌ ያህል ጴጥሮስ ኢየሱስን “የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ” ብሎ የጠራበትን ማቴዎስ 16፡16 የኢየሱስን አምላክነት ለማሳየት ይጠቅሳል፡፡ ነገር ግን ለዚህ ምላሽ የሚሆን ሙግት ገና ከልጅነቴ ተምሬያለሁ፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አዳም፣ ሰለሞንና ስማቸው ያልተጠቀሰ ግለሰቦች ሳይቀሩ ብዙ ሰዎች የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው ተጠርተዋል፡፡[54] መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጆች መሆን እንደምንችል ከመናገር አልፎ ሰዎችን አማልክት ብሎ የሚጠራባቸው ቦታዎች አሉ፡፡[55]

የሆነ ቦታ ላይ ደግሞ ኢየሱስ በሁሉ ቦታ መገኘትን የመሳሰሉት የአምላክ ባሕርያት እንዳሉት ለማስረዳት ማክዱዌል ማቴዎስና ሉቃስን ይጠቅሳል፡፡ ነገር ግን አንዳቸውም የሚያሳምኑኝ አልነበሩም፡፡[56]ሁሉም ክፍሎች የሚናገሩት ኢየሱስ ተዓምራትን ማድረጉን ነው፤ ነገር ግን ሙስሊሞች ለኢየሱስ ተዓምራት የሚሰጡት ማብራርያ በጣም ቀላል ነው፡፡ በኢየሱስ ኃይል ሳይሆን በአላህ ፈቃድ የተደረጉ ናቸው፡፡ ቁርአን የሚያስተምረው እርሱን ሲሆን[57] ኢየሱስ ያደረጋቸው ተዓምራት ከአብ መሆናቸውንና ከራሱ አንዳች ማድረግ እንደማይችል የተናገረባቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ገና ድሮ በቃል በመሸምደድ ይዣቸዋለሁ፡፡[58]ክርስትናን ለመቃወም እንደሰለጠነ ሙስሊም በማክዱዌል ንግግሮች ውስጥ ምንም አዲስ ነገር አላገኘሁም፡፡ እነዚህን ሙግቶች ደግሞ ወደ ክርስቲያኖች የመመለስ ስልጠናዎችን ወስጃለሁ፡፡

ነገር ግን በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የሚገኙ የኢየሱስን አምላክነት ለመቃወም መጠቀም የምችላቸው ጥቅሶች ቢኖሩም ኢየሱስ አምላክ መሆኑን በግልፅ የሚያሳዩ ሌሎች ጥቅሶች ደግሞ መኖራቸውን እንድቀበል በማድረግ ረገድ ማክዱዌል ተሳክቶለታል፡፡ለምሳሌ ያህል “ሰዎች ሁሉ አብን እንደሚያከብሩት ወልድን ያከብሩ ዘንድ” በማለት ኢየሱስ ተናግሯል፡፡[59] በተጨማሪም ኢየሱስን “አምላኬ” ብሎ የጠራው ደቀ መዝሙር በኢየሱስ አድናቆት ተችሯታል፡፡[60]እነዚህን ጥቅሶች ከዚህ ቀደም ያልሰማኋቸው ሲሆን ከእኔ አስተሳሰብ ጋር የሚሄዱ አልነበሩም፡፡ ሊሄዱም አይችሉም፡፡ ኢየሱስ እነዚህን ነገሮች የሚናገርበት ወይም የሚፈቅድበት ምንም ዓይነት መንገድ የለም፡፡ ቢያን እኔ የማውቀው ኢየሱስ ይህንን ሊያደርግ አይችልም፡፡

እነዚህን ጥቅሶች ልጅ ሆኜ ከሸመደድኳቸው ተቃራኒውን ከሚናገሩት ጥቅሶች ጋር ለማጣጣም በአእምሮዬ ውስጥ ማውጣትና ማውረድ ጀመርኩኝ፡፡ “እንዴት ነው አንድ ላይ ሊገጥሙ የሚችሉት? እርስ በርሳቸው የሚጣረሱ ጥቅሶች ቁርአን ውስጥ መኖራቸውን አውቃለሁ ነገር ግን እማና አባ በቀላሉ ያስታርቋቸዋል፡፡ ቁርአንን የሚያውቁትን ያህል መጽሐፍ ቅዱስን የሚያውቁ ሰዎች በጀማት ውስጥ ይኖሩ ይሆን?”

ማክዱዌልን ማንበብ ከጀመርኩበት ጊዜ አንስቶ በአእምሮዬ ውስጥ ሲብላላ የነበረ ሐሳብ ከመቅፅበት ገንፍሎ ወጣ፡፡ ውስብስብ የሆነ የጥበብ ሥራን ሲጠላልፍ ቆይቶ ለመጀመርያ ጊዜ ወደ ኋላ በመመለስ እንደተመለከተ ሰው ቆም ብዬ ሳስብ ትልቁን ምስል መዘንጋቴ ተከሰተልኝ፡፡

መጽሐፍ ቅዱስና ቁርአን አንድ ዓይነት መጻሕፍት አይደሉም፡፡ በፍፁም አንድ አይደሉም፡፡ ለምንድነው በአንድ ዓይነት መንገድ ልተረጉማቸው የምሞክረው?

መሐመድ ቁርአንን በሃያ ሦስት ዓመታት ውስጥ ለጸሐፍቱ እየነገረ እንዲጽፉለት ያደርግ ነበር፡፡ ቁርአን በአንድ ጥራዝ የተሰበሰበው ከእርሱ ሞት በኋላ ነበር፡፡ ከአሥርተ ዓመታት በኋላ የተነገሩ ጥቅሶች ብዙ ጊዜ በመካከላቸው ምንም መያያዝ በሌለበት ሁኔታ ተከታትለው ይቀመጣሉ፡፡ በዚህም ሳብያ ሙስሊሞች ቁርአንን ሲተረጉሙ በዙርያው ላሉ ሌሎች ጥቅሶች የሚሰጡት ትኩረት አናሳ ነው፡፡ አውዱን ለማወቅ **አስባብ-አን-ኑዙል** በመባል የሚታወቁ ማብራሪያዎችን ወይም ሐዲሶችን ይጠቀማሉ፡፡

የቁርአን ታሪኮች ቁርጥራጭ ከመሆናቸው የተነሳ መጀመርያ፣ መካከልና መደምደምያ ያለው አንድ ታሪክ ብቻ ነው - የዮሴፍ ታሪክ፡፡ የተቀሩት ሌሎች ትረካዎች ሁሉ ከመካከል ይጀምራሉ ወይም ጀምረው እስከ መጨረሻው ድረስ አይዘልቁም፡፡ ቁርአንን ለመረዳት ወደ አስተማሪዎቼ ለመሄድ መገደዴ የሚያስገርም አይደለም፡፡

ነገር ግን ከማክዱዌል መጽሐፍ ጋር አያይዤ መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ውስጥ በመግባት ሳነብ ወንጌላት ግልፅ የሆኑ አውዶች ያሏቸውና ወጥነት ያላቸው ታሪኮችን እንደሚያቀርቡ ተገነዘብኩኝ፡፡ ወንጌላትን ለመረዳት ምንም ዓይነት ማብራሪያዎች አያስፈልጉም፡፡ማንኛውም ሰው መጽሐፍ ቅዱስን አንብቦ መረዳ ይችላል፡፡

**አስባብ-አን-ኑዙል፡** የቁርአን አናቅፅ የወረዱበትን አውድ በጥልቀት የሚዘግብ የእስልምና ጽሑፍ ስብስብ

ቁርአንን ስናነብ እንደምናደርገው የሆነ ሐሳብ ለመግለፅ በአንድ የወንጌል ጥቅስ ላይ ብቻ አንንጠለጠልም፡፡ ወንጌሉን በሙሉ በማንበብ፣ የጸሐፊውን ዓላማና ግብ በመረዳት መጽሐፉ ለራሱ እንዲናገር መፍቀድ ይኖርብኛል፡፡

በዚህ አዲስ መረዳት ታጥቄ የዮሐንስን ወንጌል ለመተርጎም ከመሞከሬ በፊት እስከ መጨረሻው ማንበብ እንዳለብኝ ወሰንኩኝ፡፡ መሬት ላይ ተቀምጬ የአባን መጽሐፍ ቅዱስ ዮሐንስ አንድ ላይ ገልጬ ማንበብ ጀመርኩኝ፡፡

ያገኘሁት ነገር ምቾት የሚሰጠኝ አልነበረም፡፡

“በመጀመሪያው ቃል ነበረ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ፡፡ ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፡፡ ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም፡፡”[61]

በጣም ግልፅ ነው፡፡ አራት ነጥብ፡፡ እነዚህን ጥቅሶች ደግሜ ደጋግሜ በማንበብ አሰላሰልኳቸው፡፡ ሌላ ምንም ዓይት አማራጭ ትርጉም የለም፡፡ እነዚህ ጥቅሶች የሚናገሩት እግዚአብሔር ዓለምን በቃሉ እንደፈጠረ፣ ቃል ከእግዚአብሔር ጋር በዘላለማዊነት ይኖር እንደነበረ፣ ራሱ እግዚአብሔር እንደሆነና ነገር ግን ደግሞ በተወሰነ ሁኔታ ከእርሱ የተለየ እንደሆነ ነው፡፡

ቃል ኢየሱስ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ይህንን የተረዳሁት ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ እንደርሱ ስለሚል ብቻ ሳይሆን ቁርአን ራሱ “የአላህ ቃል”[62] ብሎ ስለሚጠራው ነው፡፡ ከዚህ በተጓዳኝ ቁጥር 14 ለጥርጣሬ የሚሆን ምንም ዓይነት ቦታ አይሰጥም፡፡ “ቃልም ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነው ክብሩን አየን፡፡” የግድ ኢየሱስ መሆን አለበት፡፡

ግራ ከመጋባቴ የተነሳ ቃሉን እያሰላሰልኩኝ መጽሐፍ ቅዱሱን አስቀምጬ በክፍሉ ውስጥ ወዲያ ወዲህ መንቀሳቀስ ጀመርኩኝ፡፡ ይህ የዮሐንስ የመጀመርያው ምዕራፍ ነው፡፡ የመጽሐፉ መግቢያ ነው፡፡ በዘመናዊ መጻሕፍት ውስጥ እንደሚገኙት

መግቢያዎች የተቀረውን የመጽሐፉን ክፍል የምናነብበትን መነፅር ይሰጠናል፡፡ዮሐንስ “መጽሐፉን ስታነቡ ሳላችሁ ኢየሱስ ከአብ ጋር አብሮ ዘላለማዊ የሆነና በመፍጠር ሂደትም ተባባሪው እንደነበር አስታውሱ” የሚል ይመስላል፡፡

በሌሎቹ የወንጌሉ ክፍል ውስጥ የሚገኙትን ውጥረቶች ለማስታረቅ የምችልበት አውድ ይህ ነው፡፡ ጥቅሶችን ሳስታርቅ ምንም ዓይነት ችግር ቢገጥመኝ የዮሐንስን የመግቢያ ቃል ማስታወስ ያስፈልገኛል፡፡ ኢየሱስ አምላክ ነው፡፡

ከዚህ እውነት ላመልጥ የምችልበት ምንም ዓይነት መንገድ አለመኖሩን ስገነዘብ ወዲያ ወዲህ መሄዴን አቁሜ የተገለጠውን መጽሐፍ ቅዱስ ፍጥጥ ብዬ ተመለከትኩት፡፡ አሁንም ዮሐንስ 1 ላይ ተከፍቷል፡፡ ማመን ተስኖኛል፡፡ እውነት ሊሆን አይችልም፡፡ ኢየሱስ አምላክ ሊሆን አይችልም፡፡ የሆነ ማብራርያ መኖር አለበት አለበለዚያ ተታልያለሁ፡፡ የሆነ ማብራርያ መኖር አለበት አለበለዚያ ቤተሰቤም ሆነ የምወዳቸው ወገኖቼ ሁሉ በውሸት ወጥመድ ውስጥ ገብተዋል፡፡

ኢየሱስ በእውነት አምላክ መሆኑን ከተናገረ ቁርአን ተሳስቷል፤ እስልምናም የውሸት ሃይማኖት ይሆናል፡፡

የሆነ ማብራርያ መኖር አለበት፡፡ ያ ማብራርያ ምን እንደሆነ አላውቅም ነገር ግን ብቻ መኖር አለበት፡፡ ስለመኖሩ ምንም ጥርጣሬ አልነበረኝም፤ አላህ ደግሞ እንደሚያሳየኝ ተስፋ ነበረኝ፡፡

የጋራ ጸሎት ወደምንጸልይበት ክፍላችን ፈጠን ብዬ ሄድኩኝ፡፡ ወደ መጸለያው ቦታ ከደረስኩኝ በኋላ እጆቼን ወደ ጆሮቹ አንስቼ “አላሁ አክበር” ካልኩኝ በኋላ **የነፍስል** ጸሎት ሁለት ረካዎችን ወደ አላህ ጸለይኩኝ፡፡

ለዚህ ፍልሚያ ዳግመኛ ራሴን እያዘጋጀሁ ሲሆን የአላህን እርዳታ እየተለማመንኩ ነበር፡፡

**ነፍስል፡** አማራጭ ጸሎት ሲሆን የአላህን እርዳታ የምንለማመንበትና ወደ እርሱ የምንጠጋበት ነው፡፡

# መለኮታዊ የሰው ልጅ

“ዮሐንስ ከቁጥር ሊገባ አይችልም፡፡”

“እንደዛ ልትል እንደምትችል አስቤ ነበር፡፡”

ወደ ቄብ ማዕከል ተመልሰን ዳዊት *ከአናፂ በላይ* የሚለውን መጽሐፍ ባቀበለኝ ጠረጴዛ ዙርያ ተቀምጠናል፡፡ የእረፍት ቀናቱን የዮሐንስን ወንጌል በኢንተርኔት ላይ ሳጠናና ስጸልይ ነበር ያሳለፍኩት፡፡

ሐሳብ ስለገባኝ አልነበረም፡፡ እነዚህን ጉዳዮች ማጥናቴ በእስልምና ላይ ያለኝን መተማመን ዳግመኛ በማረጋገጥ የበለጠ የተሰጠሁ እንድሆን ምክንያት ሆኖኛል፡፡ በተጨማሪም አላህ ጸሎቴን በመመለስ ለእምነቴ አፀፋ እየሰጠና የዳዊትን አመለካከት መፋለም እንድችል እያስታጠቀኝ እንደሆነ እርግጠኛ ሆኛለሁ፡፡ የዮሐንስን ወንጌል ተዓማኒነት በተመለከተ በጣም ብዙ የሙግት ሐሳቦችን አግኝቻለሁ፡፡ ያለፉትን ጥቂት ቀናት ዝግጅት ሳደርግ ከቆየሁ በኋላ አውደ ቀቲሉን ለማስመር ዝግጁ ነበርኩኝ፡፡ አሁን እንግዲህ ትልልቆቹን ጠብመንጃዎች መምዘዝ ጀምሬያለሁ፡፡

“ለምንድነው ከቁጥር የማይገባው?” ዳዊት ጠየቀ፡፡

“ኢየሱስ ካረገ ከሰባ ዓመታት በኋላ የተጻፈ የመጨረሻው ወንጌል ነው፡፡ ከእርሱ በጣም የሚቀድሙ ከሚመስሉት ከሌሎቹ ወንጌላት ጋር ምንም አይመሳሰልም፡፡”

“ነቢል ነገር ግን ይህንን ተመልክተናል እኮ፡፡ የዮሐንስ ወንጌል የተጻፈው በደቀ መዝሙር ነው፡፡ ቢያንስ ደቀ መዛሙርት በነበሩበት ዘመን ነበር የተጻፈው፡፡ መልዕክቱ ተዓማኒ ነው፡፡”

“ዳዊት ስለዚያ እርግጠኛ መሆን አልችልም፡፡ ከኢየሱስ በኋላ ሰባ ዓመት ማለት ረጅም ጊዜ ነው፡፡ ደቀ መዛሙርት እስከዚያ ዘመን ድረስ በሕይወት ስለመኖራቸው እርግጠኞች መሆን አንችልም፡፡ ነገር ግን ከዚህ የከፋ ሌላ ጉዳይ አለ፤ ለምንድነው ከሌሎቹ ወንጌላት በጣም የተለየ የሚመስለው? በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ኢየሱስ ምንም ዓይነት ምሳሌ አይጠቀምም፡፡ በተመሳሳዮቹ ወንጌላት ውስጥ ከተናገረው በላይ ስለራሱ ደጋግሞ ይናገራል፡፡ በተጨማሪም ለአራቱ ወንጌላት የጋራ የሆነ አንድ ተዓምር ብቻ ነው በውስጡ የሚገኘው፡፡[63]ዮሐንስ ራሱ ስለፈጠረው ኢየሱስ እየነገረን ያለ ይመስላል፡፡ የተለየ ኢየሱስ፡፡”

**ተመሳሳዮቹ ወንጌላት (ሲኖፕቲክስ)፡** ማቴዎስ፣ ማርቆስና ሉቃስ በጋራ የሚጠሩበት ስያሜ፡፡

“ይህንን መረጃ ከየት ነው ያገኘኸው?” የዳዊት አጠያየቅ ትዕግስቱ መሟጠጡን ያሳብቃል፡፡ እንደዚህ ዓይነት ምላሽ የሚሰጠው አልፎ አልፎ ሲሆን እኔም እንዲህ የምሟገትበት የራሴ የሆነ ምክንያት ነበረኝ፡፡ ስለ ራሴ ክብር ብቻ ሳይሆን ስለ ቤተሰቤና ስለ እምነቴ ነበር ስፋለም የነበረው፡፡

“በቅርቡ ካወቅሁት ‹ጉግል› ከተሰኘ የኢንተርኔት የመፈለግያ መንገድ ነው፡፡”

“እንደርሱ ማለቴ አይደለም፡፡ በማን የተጻፈውን ጽሑፍ እንደጠቀስክ እየጠየኩ ነው፡፡” ዳዊት መልሴን በጉጉት ጠበቀ፡፡ “ይህንን ሐሳብ ከሙስሊም ያገኘህ አይመስለኝም፡፡”

“ሻቢር በክርክር ወቅት ከጠቀሰው ባርት ኤህርማን ከተሰኘ ክርስቲያን ምሑር ነው፡፡”[64]

የዳዊት ፊት ነገሩ የገባው መሆኑን የሚያሳይ ገፅታ ያዘ፡፡ “ባርት ኤህርማን ክርስቲያን አይደለም፡፡”

“እንዴ? ክርስቲያን መስሎኝ ነበር እኮ፡፡” ፈገግ አልኩኝ፡፡ “የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገብቶ ነበር፡፡”

“አዎ፣ ግን ኋላ ላይ እምነቱን ከዷል፡፡”

“ለምን እንደሆነ ይገባኛል!”በቀልድ መለስኩኝ፡፡ ነገር ግን ቀልዱ ከፊል ነበር፡፡

“እሺ ወደ ክርስቶስ አምላክነት ጉዳይ እንመለስ፡፡ በማክዱዌል መጽሐፍ ውስጥ አሳማኝ የሆነ ምንም ነገር አላገኘህም?”

“ከዮሐንስ ወንጌል ውጪ ምንም አላገኘሁም፡፡” የዮሐንስ ወንጌል ላይ የጀመርነውን ክርክር በቀላሉ መተው አልፈለኩም፡፡

“መልካም፡፡ እንዲህ ብናደርግስ? የዮሐንስን ወንጌል አጥንቼ ልምጣ፡፡ ነገር ግን ሌላ መጽሐፍ እስጥህና አስተያየትህን ትነግረኛለህ፡፡”

“ጥሩ ይመስላል፡፡ ነገር ግን *ከአናፂ በላይ* ከሚለው መጽሐፍ የተሻለ *ሥራ* ይጠበቅብሃል ዳዊት፡፡ በሚቀጥለው ጊዜ ተለቅ ያለ መጽሐፍ ብታመጣልኝስ?”

ዳዊት ሳቀ፡፡ “እንደጠየከው ይሆንልሃል!”

ከጥቂት ቀናት በኋላ መጠኑ ትልቅ የሆነ መጽሐፍ ይዤ በአባ ክፍል ውስጥ በሆዴ ተኝቻለሁ፡፡ የመጽሐፉ ርዕስ *ፍርድ የሚሻ ማስረጃ* ይላል፡፡ በጆሽ ማክዱዌል የተጻፈ ቢሆንም ነገር ግን ደረጃው ከፍ ያለ ነበር፡፡ ጆሽ ማክዱዌል ስለ ክርስትና ምንጮች ባጠናባቸው ረጅም ዓመታት ውስጥ ያሰባሰባቸው ማስታወሻዎች የተጠራቀሙበት ወደ ስምንት መቶ ገፅ የሚረዝም ጥራዝ ነበር፡፡

ምንም የስጋት ስሜት አላደረብኝም ነበር፡፡ የዮሐንስንወንጌል በተመለከተ በቅርቡ በዳዊት ላይ ያገኘሁት ድል ድፍረትን አጎናፅፎኛል፡፡ አላህ ከጎኔ መሆኑ ከመቸውም ጊዜ በላይ ይሰማኛል፡፡ በእርሱ ላይ የሚነገር የትኛውም ተቃውሞ ሊፀና እንደማይችልና

የኢየሱስ አምላክነት በኋለኛው ዘመን ወደ ክርስትና የተጨመረ ስለመሆኑ በጣም እርግጠኛ ነበርኩኝ፡፡

ኢየሱስ አምላክ መሆኑን ተናግሮ ከሆነ ግልፅ የሆነውን ንግግሩን በኋለኛው ወንጌል ውስጥ ብቻ ሳይሆን በቀደሙት ወንጌላትም ውስጥ ማግኘት ይኖርብናል፡፡ ኢየሱስ አምላክ መሆኑን ስለመናገሩ በማርቆስ ወንጌል ውስጥ ተጽፎ ማየት ያስፈልገኛል፡፡ ሳላቅማማ ስለ ኢየሱስ አምላክነት የሚናገረውን ክፍል ፈጠን ብዬ በመክፈት ንባቤን ጀመርኩኝ፡፡

ማክዱዌል አእምሮዬን ያነበበው ይመስል ከጅምሩ "በማርቆስ ወንጌል ውስጥ የሚገኝ ኢየሱስ ስለ ራሱ የሰጠው ሕጋዊ ምስክርነት" ብሎ ጽፏል፡፡ እርሱ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ስለመሆኑ ሊቃ ካህኑ በጠየቀው ጊዜ፤ "እኔ ነኝ፤ የሰው ልጅም በኃይል ቀኝ ሲቀመጥ በሰማይም ደመና ሲመጣ ታያላችሁ" በማለት ነበር የመለሰው፡፡[65]

"እኔ ነኝ" ከሚለው ውጪ ይህ ንግግር ብዙም ግልፅ አልሆነልኝም ነበር፡፡ ማክዱዌል ለምን እንደ ዋና የሙግት ሐሳብ እንዳቀረበውም ቶሎ አልተከሰተልኝም ነበር፡፡ ኢየሱስ ይህንን ሲል ምን ለማለት ፈልጎ ይሆን?

ምንም ይሁን ምን አንድ ነገር ግን ግልፅ ነው፡፡ በሸንጎው ውስጥ የነበሩት ካህናት ስለ ራሱ የተናገረው ይህ ንግግር ለሞት የሚያበቃ ከሃዲነት እንደሆነ ገብቷቸዋል፡፡ አንድ ሰው ለእንደዚህ ዓይነት የከፋ ቅጣት ሊዳረግ የሚችለው ስለ ማንነቱ አንድ ነገር የተናገረ እንደሆነ ብቻ ነው፤ እርሱም እግዚአብሔር መሆኑን መናገር ነው፡፡ መሲሁ መሆኑን መናገሩ ብቻውን በቂ አይደለም፡፡[66] ነገር ግን ኢየሱስ አምላክ መሆኑን እንደተናገረ እንዲያስቡ ያደረጋቸው በምላሹ ውስጥ የሚገኘው ሐሳብ ምን ይሆን?

ይህንን ለማብራራት ማክዱዌል የአዲስ ኪዳን ሊቅ የሆነውን ክሬግ ብሉምበርግን ይጠቅሳል፡- "ይህ ምላሽ ዳንኤል 7፡13 እና መዝሙር 110፡1 ላይ የሚገኘውን ሐሳብ የሚጠቁም ነው፡፡ በዚህ አውድ መሠረት ‹የሰው ልጅ› ማለት ከአንድ ተራ ሰው በእጅጉ የላቀ ነው፡፡ ኢየሱስ ‹የሰው ልጅ የሚመስለው፣ ከሰማይ ደመናት ጋር የሚመጣው፣

በዘመናት ወደ ሸመገለው የተወሰደው፣ በሰው ልጆች ሁሉ ላይ ሥልጣንና ኃይል የተሰጠው፣ ዓለም አቀፋዊ አምልኮና ዘላለማዊ ግዛት የተገባው አካል› እንደሆነ እየተናገረ ነው፡፡ የአይሁድ ከፍተኛ ችሎት የሞት ፍርድ ያስተላለፈው ኢየሱስ ሟች ከሆነው የሰው ልጅ እጅግ የላቀውን ይህንን ማዕርግ የራሱ ስላደረገ ነበር፡፡”

ግራ ተጋባሁ፡፡ ብሉምበርግ “የሰው ልጅ” የሚለው ማዕርግ ‹አምላክ ነኝ› ከማለት ጋር አንድ ነው እያለ ነውን? ይህ የማይቻል ነው፡፡

በዋሽንግተን ዲሲ መስጊድ ሳለሁ የተደረገውን **ኹጥባ** አስታወስኩኝ፡፡ ኢማሙ በጸሎቱ አዳራሽ ውስጥ በመቆም እንዲህ አለ፡- “ኢየሱስ አምላክ መሆኑን በተደጋጋሚ አስተባብሏል፡፡ ጉዳዩን ግልፅ ለማድረግ ሁል ጊዜ የሰው ልጅ በማለት ራሱን ይገልፅ ነበር! ‹የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ› ብሎ ራሱን ጠርቶ አያውቅም፡፡ አልፎ አልፎ በሌሎች ሰዎች ‹የእግዚአብሔር ልጅ› ተብሎ ቢጠራም ቃል በቃል የእግዚአብሔር ልጅ ነው ማለት አይደለም፡፡ ኢየሱስ የሰው ልጅ ነው፡፡ ሰው ነው፡፡”

**ኹጥባ፡** ብዙ ጊዜ በሙስሊሞች ዕለተ ሰንበት ማለትም አርብ ቀን የሚደረግ ስብከት

“የሰው ልጅ” የሚለው ሐረግ ከዚህ የላቀ የተለየ ትርጉም ይኖረው ይሆን?

ዳንኤል ሰባትን ለራሴ አውጥቼ ማንበብ ይኖርብኛል፡፡ የአባን መጽሐፍ ቅዱስ ከመደርደርያው ላይ አውርጄ “ዳንኤል” የሚለውን ከማውጫው ካየሁ በኋላ ገፁን ከፈትኩት፡፡ ብሉምበርግ እንዳለው ከሁሉም ነገድና ቋንቋ በሆኑ ሰዎች ሁሉ ለዘላለም ስለሚመለክ የሰው ልጅ የተነገረ ትንቢታዊ ራዕይ አለ፡፡ ይህ የሰው ልጅ ሥልጣንና ሉኣላዊ ኃይል በዘላለማዊ መንግሥት ላይ ተሰጥቶታል፡፡

አእምሮዬ በሐሳብ ባሕር ውስጥ መዋኘት ጀመረ፡፡ የዚህ ትርጉም ምን ይሆን? የኢየሱስ ምላሽ መዝሙር 110 ላይ የሚገኘውንም እንደሚጠቅስ ብሉምበርግ መናገሩ ትዝ አለኝ፡፡ ምናልባት እርሱ ነገሮችን ግልፅ ያደርግልኝ ሆን? መዝሙር 110ን በማውጣት

የመጀመርያውን ቁጥር አነበብኩኝ፡ “ጌታ ጌታዬን ጠላቶችህን የእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው” ይላል፡፡

ነገር ግን ምን ማለት ነው? ጌታ እንዴት ነው ለጌታ የሆነ ነገር ሊል የሚችለው? እግዚአብሔር በቀኙ እንዲቀመጥ እየጠየቀ ያለው ማንን ነው?

ኢንተርኔት ላይ በመግባት ስለ ዳንኤል 7 እና ስለ መዝሙር 110 የቻልኩትን ያህል ማጥናት ጀመርኩኝ፡፡ ከጥቂት ሰዓታት በኋላ ሁሉም ነገር ግልፅ ሆነልኝ፡፡ ዳንኤል 7 የሚያወራው ከእግዚአብሔር ጋር በሰማይ የሉኣላዊነቱ ተካፋይ ስለሆነ አካል ነው፡፡ ይህ አካል ለእግዚአብሔር ብቻ የሚገባውን ክብርና አምልኮ ይቀበላል፡፡ መዝሙር 110 ከእግዚአብሔር ጋር በዙፋኑ ላይ አብሮት መቀመጥ ስለሚገባውና የእርሱ ወራሽ ስለሆነው ጌታ ነው የሚናገረው፡፡

ማርቆስ 14፡62 ላይ ኢየሱስ መለኮታዊው የሰው ልጅ መሆኑንና የአብ ዙፋን ወራሽ መሆኑን እንዲሁም ሉኣላዊ ሥልጣን እንዳለው ግልፅ አድርጓል፡፡[68]

ነገር ግን ይህ ሊሆን የሚችለው እንዴት ሆኖ ነው? ምናልባት እንደ ዮሐንስ ወንጌል ሁሉ ይህ የማርቆስ ወንጌል ክፍልም ኢየሱስ የተናገረውን በትክክል አላስቀመጠም ይሆን? የማምለጫ መንገድ ፍለጋ ኢንተርኔትን አሰስኩት ነገር ግን አንዳች ላገኝ አልቻልኩኝም፡፡ በአራቱ ወንጌላት ውስጥ ኢየሱስ ከስምንት ጊዜ በላይ የሰው ልጅ በማለት ራሱን ጠርቷል፡፡ ቃሉን ለራሱ መጠቀሙ ሊካድ የማይችል ሃቅ ነው፡፡ “በኃይል ቀኝ ይቀመጣል” የሚለው እምነት ከጥንት ጀምሮ በቤተ ክርስቲያን አስተምሕሮ ውስጥ ስር ሰዶ የተተከለ ነው፡፡[69] እነዚህ አባባሎች አምላክ መሆኑን እንደተናገረ የሚገልፁ ከሆነ የኢየሱስ አምላክነት በወንጌላትና በቀዳሚው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ በግልፅ ተቀምጧል ማለት ነው፡፡

አመሻሽ አካባቢ ኮምፒውተሩን ዘግቼው የማክዱዌልን መጽሐፍ አስቀምጬ ይህንን አዲስ መረጃ ማመንዠግ ተያያዝኩ፡፡ አጣብቂኝ ውስጥ ገብቻለሁ፡፡ ቀዳሚው ወንጌልና የተቀሩት ወንጌላት ሁሉ መልዕክታቸው በኢየሱስ አምላክነት ዙርያ የተገነባ መሆኑን

መቀበል ተስኖኛል፡፡ ነገር ግን ደግሞ መካድም አልቻልኩም፡፡ በአንድ ወገን የሚያስከፍለው ዋጋ እጅግ አየለብኝ፤ በሌላ ወገን ደግሞ ማስረጃው እጅግ በረታብኝ፡፡

አስደሳቹ ነገር ከርዕሱ በተፃራሪ ማስረጃው ፍርድ የሚሻ አልነበረም፡፡ ቢያንስ አፋጣኝ በሆነ ሁኔታ ፍርዱን ለማስተላለፍ የሚያስገድድ አልነበረም፡፡ በማስረጃውና በእምነቴ መካከል ባለው ሁኔታ ላይ ፍርድ ለማስተላለፍ ግዴታ ውስጥ አልገባሁም፡፡ ነገር ግን ሳይታወቀኝ ጭንቀቱና ውጥረቱ ለእስልምና ያለኝን መሰጠት የበለጠ በማበርታት መተንፈሻ አገኘ፡፡ ለሰላት የነበረኝ ቅንዓት ታደሰ፣ ሐዲሳትን በማጥናት ብዙ ጊዜ አሳልፍ ነበር፣ በየዕለት ንግግሬም ውስጥም እስላማዊ ቃላትን ማብዛት ጀመርኩኝ፡፡ ከማስረጃው ለማምለጥ የምችለውን ሁሉ ባደርግም ነገር ግን እስከ ወዲያኛው መዝለቅ ተሳነኝ፡፡ ከወራት በኋላ ውጥረቱ ሲበረታ ከዳዊት ጋር የነበረኝ ወዳጅነት ለፈተና ተጋለጠ፡፡

# አስተምህሮተ ጳውሎስና ቀዳሚው ኢየሱስ

ዕለቱ ዝናባማ ሲሆን ከመኪናዬ አናት በላይ የነጎድጓድ ድምፅ ይሰማል፡፡ ከአፍታ በፊት ለስለስ ያለ የማለዳ ነጠብጣብ የነበረው ካፍያ አሁን ወደ ዶፍ ተቀይሮ ፀሐይዋን ጋርዷታል፡፡ የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ክፍል ኃላፊዎች በሮሊን አዳራሽ ውስጥ ተሰብስበው ስለነበር ዳዊት ወደዚያ መሄድ ያስፈልገዋል፡፡ በዝናብ እንዳይበሰብስ እኔ በመኪናዬ ባደርሰውም ከመኪናው ውስጥ ወጥቶ አንድ እርምጃ መራመድ በቦርሳው ውስጥ የያዛቸውን መጻሕፍቱንም ሆነ የኤሌክትሮኒክስ መሳርያዎቹን ለአደጋ ያጋልጣል፡፡ ስለዚህ እየወረደ የነበረው ዶፍ እስኪያባራ እዚያው የኔ መኪና ውስጥ ቆየን፡፡

ከባድ የሆነውን ርዕስ በዚያን ሰዓት አንስተን ለምን እንደተነጋገርን እስከዛሬ ሊገባኝ አልቻለም፡፡ ከመኪናው ውጪ የነበረው ማዕበል በውስጧ ከነበረው ጋር ሲነፃፀር ከቁብ የሚቆጠር አልነበረም፡፡

"የዮሐንስን ወንጌል አጥንቼዋለሁ" በማለት ጀመረ ዳዊት፡፡

"ግሩም ነው! ምን አገኘህ ታድያ?" በተመሳሳዮቹ ወንጌላት ውስጥ የላቀ **ትምህርተ ክርስቶስ** ካገኘሁ ወዲህ በዮሐንስ ወንጌል ላይ የነበረኝ ጥያቄ

**ትምህርተ ክርስቶስ፡** ስለ ኢየሱስ ባሕርይ፣ ማንነት ወይም ድርሻ የሚሰጥ አንድምታ፤ ለምሳሌ ያህል የቁርአን ትምህርተ ክርስቶስ ከዮሐንስ ወንጌል ያነሰ ነው፡፡ ይህም የሆነው በመጀመርያው ውስጥ ኢየሱስ ሰው ብቻ ሲሆን በሁለተኛው ውስጥ አምላክ በመሆኑ ነው፡፡

ተመልሶልኛል፡፡ ነገር ግን ይህንን ለዳዊት አላመንኩለትም፡፡

“በመጀመርያ ዮሐንስ ከተቀሩት ወንጌላት የተለየ እንደሚመስል የሰጠኸው አስተያየት ትክክል ነው፡፡ ነገር ግን ያ የሆነው የራሱ የሆነ ዕይታ በነበረው ሌላ ደቀ መዝሙር የተጻፈ በመሆኑ ነው፡፡ ሁለት ሰዎች ስለ አንድ ታሪክ ቢናገሩ በየራሳቸው መንገድ እንደሚያቀርቡ ይታወቃል፡፡ ይህ ማለት ግን ከሁለቱ አንዱ ተሳስቷል ማለት አይደለም፡፡”

ልቤ ባይፈልግም ልጋፈጠው ወሰንኩኝ፡፡ “ነገር ግን ዮሐንስ ከተመሳሳዮቹ ወንጌላት ጋር ያለው አለመመሳሰል ትንሽ ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡”

“አዎ ግን አብሮ ሊሄድ በማይችል መልኩ የተለየ አይደለም፡፡” ዳዊት ምላሽ እንድሰጠው ቢጠብቀኝም ምንም የምለው ነገር ስላልነበረኝ ንግግሩን ቀጠለ፡፡ “ሁለተኛው ዮሐንስ ከ90-100 ዓ.ም. መካከል የተጻፈ ስለመሆኑ እርግጠኞች መሆን አንችልም፡፡”

“ለምን?”

“ሊቃውንት የዮሐንስን ወንጌል ዕድሜ የለኩበት መንገድ ግብታዊ ነው፡፡ ብዙዎቹ ዕድሜው ያን ያህል የዘገየ እንደሆነ የገመቱት ስለ ኢየሱስ ከሚያስተምረው ነገር የተነሳ ነው፡፡ ከፍተኛ ትምህርተ ክርስቶስ ማለት የኋለኛው ዘመን ነው የሚል ግምት ስለያዙ ነው፡፡”

“ታድያ እንደርሱ አይደል እንዴ?” ጉዳዩን ለማክረር በመፈለግ ስሜት ጠየኩኝ፡፡ “ተመሳሳዮቹ ወንጌላት በተጻፉበት ዘመን ክርስቲያኖች ከፍተኛ ትምህርተ ክርስቶስ አላዳበሩም ነበር፡፡”

“በተመሳሳዮቹ ወንጌላት ውስጥ የሚገኘው ትምህርተ ክርስቶስ ከፍተኛ እንደሆነ አምናለሁ ነገር ግን እስኪ ለሙግቱ ስንል እንደርሱ አይደለም እንበል፡፡ አሁንም የማትፈታው ችግር አለ፡፡ ክርስቲያኖች ኢየሱስን እንደ አምላክ እንደሚቀበሉት የሚናገሩ ከወንጌላት በፊት የተጻፉ ጽሑፎች አሉ፡፡”

ዳዊት ውይይቱን ወደ ተለየ አቅጣጫ እየወሰደው ነበር፡፡ የኔም ጉጉት ከፍ ብሏል፡፡ “ምን ዓይነት ጽሑፎች?”

“የጳውሎስ መልዕክቶች፡፡”

ይህንን በማለቱ ዳዊት ሳይታወቀው በውስጤ ታፍኖ ለቆየው የተቃውሞ ነበልባል መተንፈሻ አበጀ፡፡ ሙስሊሞች ብዙ ጊዜ ጳውሎስን እንዲያብጠለጥሉ ተደርገው ይሰለጥናሉ፡፡ የክርስትናን ትክክለኛ ትምህርት በመጥለፍ በራሱ ትምህርት እንደበረዘ ሰው ይቆጥሩታል፡፡ በኛ ጀማት ውስጥ ከሚገኘው ትልቁ ኢማም ጀምሮ ታች እናቴና አባቴ ድረስ እስካሉት ሙስሊሞች ድረስ ያሉት ወገኖች ጳውሎስ የኢየሱስን ትምህርት በመበረዝ ቢሊዮኖችን ሟች የሆነ መሲህ እንዲያመልኩ ያሳተ ሰው ስለመሆኑ በተደጋጋሚ ሲናገሩ ሰምቻለሁ፡፡ ቁርአንና ሐዲስ ከሚናገሩት ነገር የተነሳ ሙስሊሞች ኢየሱስንና ደቀ መዛሙርቱን ማክበር ይኖርባቸዋል፡፡ ኢየሱስ ሰው መሆኑን ጨምሮ ትክክለኛውን የአላህ መልዕክት እንዲያሰራጩ የተመረጡ ሰዎች ናቸው፡፡ ነገር ግን በክርስትና ታሪክ ጅማሬ አካባቢ ኢየሱስመመለክጀመረ፡፡ ይህ ደግሞ ወንጀልና ክህደት ነው፡፡ ሙስሊሞች ከደቀ መዛሙርት ክበብ ውጪ በሆነ ተፅዕኖ ፈጣሪ የቀደመ ክርስቲያን ላይ ወንጀሉን ማላከክ አስፈልጓቸዋል፡፡ ያ ክርስቲያን ደግሞ ጳውሎስ ነው፡፡

ዳዊት ንግግሩን ቀጠለ፤ “የጳውሎስ ጽሑፎች የቀደሙት ክርስቲያኖች ኢየሱስን እንደ አምላክ እንደሚቀበሉት ያስረዳሉ፡፡ ጳውሎስ መጻፍ የጀመረው ከአርባዎቹ በፊት ሲሆን ከማርቆስ በአሥርተ ዓመታት ይቀድማል፡፡ ለምሳሌ ያህል በጣም ቀዳሚ ከሆኑት ጽሑፎቹ መካከል አንዱ ኢየሱስ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር እንደነበረና ራሱን ባዶ አድርጎ ሰው እንደሆነ ይናገራል፡፡[70]በሌሎች ቀዳሚያን ጽሑፎቹ ውስጥ የያሕዌን ባሕርይ በኢየሱስና በአብ መካከል ያካፍላል፡፡”[71]

“እና ምን ይሁን?” በተሰላቸ ስሜት መልስ ሰጠሁ፡፡

“ማሕበረሰቡ ኢየሱስ በሥጋ የተገለጠ አምላክ መሆኑን ቀደም ሲል የሚያስተምር ከሆነ በዚያ ማሕበረሰብ የተጻፈው ወንጌል ያንን አስተምህሮ የሚያንፀባርቅ ሆኖ

እንደምናገኘው ግልፅ ነው፡፡ ወንጌላትን ማንበብ ያለብን በጳውሎስ መልዕክታት ውስጥ በሚታየው የቀደሙት ክርስቲያኖች እምነት መሠረት ነው፡፡"

እዚህ ነጥብ ጋር ሲደርስ አንገሸገሸኝ፡፡ በማላገጥ አነጋገር ዳዊት የተናገረውን ደገምኩት፡፡

"የማርቆስ ወንጌል ውስጥ እንደዚያ ያለ ነገር እንደሌለ ግልፅ ነው፡፡ የኢየሱስን አምላክነት አስተምሕሮ የፈጠረው ጳውሎስ መሆን አለበት፡፡ የክርስትናን መልዕክት የበረዘው እርሱ ነው፡፡"

ዳዊት ግራ ተጋባ፡፡ "ምንድነው እያወራህ ያለኸው?"

በኹጥባዎችና በሃይማኖት መጻሕፍት ውስጥ ያነበብኳቸውን ተቃውሞዎች በጳውሎስ ላይ አዥጎደጎድኳቸው፡፡ "ኢየሱስ ሕግን ለመፈፀም እንጂ ለመሻር እንዳልመጣ ተናግሯል፡፡[72] ጳውሎስ ግን ኋላ ላይ በመምጣት ኢየሱስ ሕግን እንደሻረ አስተማረ፡፡ ኢየሱስ ሕዝቡን ‹አምላኬንና አምላካችሁን አምልኩ› በማለት ተናግሮ ነበር፡፡ ጳውሎስ ግን ኢየሱስ ራሱ አምላክ መሆኑን አስተማረ፡፡[73] ጳውሎስ ኢየሱስ ያስተማረውን ሃይማኖት በመቀየር ሃይማኖቱን ስለ ኢየሱስ የሚያስተምር አደረገው፡፡"

ዳዊት ስሜቱ ጥሩ እንዳልሆነ ያስታውቃል፡፡ "ለምን ብሎ ነው የኢየሱስን አምላክነት ከራሱ ፈጥሮ የሚያስተምረው? አይሁዳዊ ነበር እኮ፡፡ የገማልያ ግንባር ቀደም ተማሪ ነበር፡፡ ከአይሁድም አይሁዳዊ ነበር፡፡ ኢየሱስ አምላክ ነው የሚለውን ሐሳብ በመፍጠር ምን ያተርፋል?"

"ዳዊት፣ ይህ ግልፅ አይደል እንዴ? ጳውሎስ የሥልጣን ክፍተት መኖሩን ተመልክቷል፡፡ ኢየሱስ መሄዱንና ደቀ መዛሙርቱ ደግሞ ያለውን ሁኔታ የመቆጣጠር አቅም የሌላቸው የተበታተኑ ቡድኖች መሆናቸውን አስተውሏል፡፡ የሥልጣን ጥመኛ ነበር፡፡ ስለዚህ ኢየሱስን ባያየው እንኳ ራሱን ደቀ መዝሙር አድርጎ በመሾም በማደግ ላይ የነበረችዋን ቤተ ክርስቲያን ተቆጣጠረ፡፡ ከዚያ ቀደም ከነበሩት ወንጌላት ይልቅ ራሱ የፈጠረውንም ወንጌል አስፋፋ፡፡ የኢየሱስን ወንጌል በራሱ ወንጌል ለወጠ፡፡"[74]

ዳዊት ከልቡ ሳቀ፡፡ “ከምርህ ነው ግን? የመጀመርያው ነገር አሁን የተናገርከው እውነተኛ የሆነ አይሁዳዊ ለምን ኢየሱስን ወደ አምላክነት እንደሚለውጥ አያስረዳም፡፡ የሆነ የሥልጣን ጥመኛ ዓይነት ሰው እንኳ ቢሆን ሥልጣን ለማግኘት ያንን ማድረግ አያስፈልገውም፡፡ ለወንጌል ብሎ ብዙ ጊዜ ሕይወቱን ለአደጋ እንደማጋለጡ መጠን የሥልጣን ጥመኛ እንዳልሆነ ደግሞ እናውቃለን፡፡”[75] የዳዊት ድምፅ እየጠነከረና እየተለወጠ መጣ፡፡

አቋረጥኩት፡፡ “ዳዊት አንዳንድ ጊዜ ሰዎች መዋሸት ከጀመሩ ወደ ኋላ መመለስ ይቸግራቸዋል፡፡ ምናልባት በዚያን ጊዜ መመለስ እስከማይችል ድረስ ጠልቆ ገብቶ ይሆናል፡፡”

“ከውሸቱ ውስጥ መውጣት አቃተው ነው የምትለው? ጳውሎስ የውሸት ቀበኛ እንደሆነ ለመናገር የሚያስችል ምን ማስረጃ አለህ?”

“ሥልጣን ፈላጊ እንደነበረ ነግሬሃለሁ፡፡”

ዳዊት ንዴት ይስተዋልበታል፡፡ “ሥልጣን?! ሥልጣን ፈላጊ ቢሆንማ የቀድሞ ቦታውን መልቀቅ ባላስፈለገው ነበር፡፡ በዘመኑ የነበረው ታላቅ ረቢ ግንባር ቀደም ተማሪ ነበር፡፡ ሥልጣን በመንገድ ላይ ይጠብቀው ነበር፡፡ እርሱ ግን ተቃራኒውን መንገድ በመሄድ የድህነትና የውርደትን ሕይወት መረጠ፡፡ የቀደሙት ክርስቲያኖች ሕልውናቸው ለመቀጠሉ ጳውሎስና እርሱ የከፈለውን መስዋዕትነት ማመስገን ያስፈልጋቸዋል!”

“አዎ እያንዳንዱ ክርስቲያን ለፍርድ በፈጣሪ ፊት ሲቀርብ ከእርሱ ይልቅ ፍጡር የሆነውን ሰው በማምለኩ ጳውሎስን ማመስገን ያስፈልገዋል!” እነዚህ ቃላት ከአንደበቴ አፈትልከው በወጡበት ቅፅበት ድንበር መጣሴ ታወቀኝ፡፡ ነገር ግን አንዴ ሆኗል፡፡ ይቅርታ ለመጠየቅ የሚያስችል ትህትና የነበረኝ ሰው አልነበርኩም፡፡ የዳዊትን ምላሽ በመጠባበቅ አፍጥጬ ተመለከትኩት፡፡

ዳዊት በዝምታ ተዋጠ፡፡ ለደቂቃዎች ምንም ቃል አልተነፈሰም፡፡ በመጨረሻም ተናገረ፡፡ የተናገራቸው ቃላት በማጣርያ ውስጥ ያለፉ ይመስል በእርጋታ የተሞሉ፣ የተሰሉና የተመጠኑ ነበሩ፡፡ "ነቢል፣ እኔ ጳውሎስን ከኢየሱስ ቀጥሎ ቅዱስ ሰው እንደሆነ አድርጌ ነው የምቆጥረው፡፡ የገዛ መላምቶችህ ትርጉም እንዲሰጡልህ ለምታደርገው ጥረት ብለህ እርሱን ስታብጠለጥል እዚህ ቁጭ ብዬ ልሰማህ አልችልም፡፡ ለጓደኝነታችን ትልቅ ዋጋ ስለምሰጥ ዳግመኛ እነዚህን ነገሮች ባንነጋገር እመርጣለሁ፡፡" ንግግሩን ገታ አደረገ፡፡ "ትስማማለህ?"

"እስማማለሁ፡፡"

"መልካም፣በኋላ አገኝኻለሁ፡፡" ይህንን ብሎ ዳዊት በሩን በኃይል በመክፈት የዝናቡ ዶፍ ሳይበግረው ወጥቶ ሄደ፡፡"

*ጂ ኢድ ኮምስዜውስኪ በኖርዝ ዌስተርን የሥነ መለኮት ኮሌጅ የመጽሐፍ ቅዱስና የነገረ መለኮት ትምህርቶች ፕሮፌሴር ሲሆኑ ኢየሱስን መልሶ ማግኘትና ኢየሱስን በተገቢ ቦታው መመለስ የሚሉ ሁለት መጻሕፍትን በተባባሪነት አሳትመዋል፡፡ የክርስቶስን አምላክነት በተመለከተ የጻፉትን የሊቅ አስተዋፅዖ ለማንበብ contributions.NabeelQureshi.com ይጎብኙ፡፡*

# ክፍል ፮

# ስለወንጌል የቀረበ ሙግት

*ነገር ግን ግርማው የልጆቹን ያህል ለእርሱ አስፈላጊ ባይሆንስ?*

# ሥላሴ

የጳውሎስ ጉዳይ እኔና ዳዊትን ያጋጨ ብቸኛው ርዕስ አልነበረም፡፡ ዋና ዋና ስለሆኑት እምነቶቻችን ስንነጋገር ብዙ ጊዜ ስሜታውያን እንሆን ነበር፡፡ የምንነጋገርበት ርዕስ በጠነከረ መጣን ከአንዳችን አንደበት ኮምጣጣ ቃላት ይወጡ ነበር፡፡ መለያየታችን በከፋ መጠን ስሜታችንም ገንፍሎ ይወጣ ነበር፡፡ነገር ግን ሕይወትን በጋራ እንኖራት ስለነበር ልዩነታችን የቱንም ያህል ቢከፋ እስከ ወዲያኛው አልተለያየንም፡፡ መቃቃራችን ከፍቶ አንዳችን ሌላችንን ደግመን ላለማናገር የምንወስንባቸው ጊዜያት ቢኖሩም በተማሪዎች ተወካዮች ስብሰባ ወቅት ወይም በትምህርት ክፍል ስለምንገናኝ ነገሮችን ለማስተካከል እንገደድ ነበር፡፡ ስለ ጳውሎስ በተከራከርንበት ወቅት ዳዊት በመኪና እንድወስደው ስለፈለገ ከሃያ ደቂቃ በኋላ ነበር ታርቀን ወደ ቀድሞ ወዳጅነታችን የተመለስነው፡፡

ጠንካራ ወዳጅነት በጣም ወሳኝ እንደሆነ ከሚያሳዩ ምክንያቶች መካከል ይህ አንዱ ነው፡፡ የይስሙላ ወዳጅነት የመረረ አለመግባባት ሲፈጠር ሊበላሽ ይችላል፡፡ ነገር ግን ሕይወትን በጋራ የምንኖራት ከሆነ ተመልሰን ለመታረቅ እንገደዳለን፡፡በእርግጥ አንዳችን በሌላችን ላይ ጥገኛ ከመሆን በዘለለ እጅግ እንዋደድና አንዳችን ለሌላችን እንጠነቀቅ ነበር፡፡ ልክ እንደ እውነተኛ ወንድማማች የከፋ ጭቅጭቅ ውስጥ ከገባን በኋላም ቢሆን ወንድማማችነታችን አይቀርም ነበር፡፡ ፍቅር የኃጢአትን ብዛት ትሸፍናለች ይል የለ ቃሉ?

የሚገርመው ነገር መከራከራችን ደግሞ ጥቅም ነበረው፡፡ የከረሩ መለያየቶች ተለባብሰው የተቀበሩበትን ቦታዎችእንድለይና በእነርሱ ላይ አተኩረን እንድንወያይ አድርገውናል፡፡

ከእንደዚህ ዓይት ርዕሶች መካከል አንዱ ሥላሴ ነበር፡፡ እንደ ኢየሱስ አምላክነት ሁሉ ሙስሊም የሆነው ማንነቴ የሥላሴንም አስተምህሮ እንዳልረዳና እንድቃወም አድርጎኛል፡፡

የእስልምና ማዕከላዊ እምነት **ተውሂድ** ይሰኛል፡፡ አንድ ሙሉ የሆነ የእስልምና የጥናት ዘርፍ ለዚህ ርዕስ የተሰጠ በመሆኑ በቀላሉ ለማስረዳት አዳጋች ነው፡፡ ነገር ግን ተውሂድ እስልምና ስለ አላህ አንድነት የሚያስተምረው ትምህርት ነው፡፡ ይህ ዝም ብሎ ብቻ የአሃዳዊነትን እምነት መቀበል ሳይሆን እጅግ በፀና ሁኔታ የፈጣሪን አንድነት መመስከር ነው፡፡ የፈጣሪ አንድነት ወይም ፈጣሪ እንዲሆን ያደረገው ያ ነገር በራሱ አንድነቱ ነው፡፡ እርሱ የተለየ፣ በማንም ላይ ጥገኛ ያልሆነ፣ ሉኣላዊ፣ ከማንም የተነጠለና ፍፁም አንድ ነው፡፡ በእርሱ ውስጥ ምንም ዓይነት መከፋፈል የለም፡፡

ይህንን አስተምህሮ ወደ ሙስሊም-ክርስቲያን የውይይት ጠረጴዛ ያመጣነው እንደሆነ የእስልምና መሠረታዊ መርህ የሆነው ተውሂድ ከአስተምህሮተ ሥላሴ በተፃራሪ የቆመ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡በክርስቲያን አገር እንዳደገ ሰው ሙስሊም የሆኑት ታላላቆቼ የሥላሴን ትምህርት እንድቃወም አድርገው አሰልጥነውኛል፡፡ ትምህርተ ሥላሴን በማስተባበል ላይ ያተኮሩ የጁማ ኹጥባዎ፣ የወጣት ሥልጠናዎች፣ የሃይማኖት ማስተማርያ መጻሕፍትና የቁርአን ጥናት ክፍለ ጊዜያት እንደነበሩ አስታውሳለሁ፡፡ ሁሉም የሚያስተምሩት አንድ ነገር ነው፤ ሥላሴ በስሱ የተሸፈነ መድብለ አማልክታዊነት ነው፡፡

በግርድፉ ሥላሴን በሚከተለው መልኩ እንድመለከት ነው ያስተማሩኝ፤ ክርስቲያኖች አንድ አምላክ ብቻ እንዳለ ቢያውቁም ነገር ግን ኢየሱስን በእግዚአብሔር ላይ በመደበል የማምለክ ፍላጎት አደረባቸው፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔርን በአንድ ጊዜ አንድም ሦስትም ነው በማለት ሥላሴ የሚል ስያሜ ሰጡት፡፡ ይህ ትርጉም የሚሰጥ ባይሆንም ክርስቲያኖች በጭፍን ይቀበሉታል፡፡ ሥላሴን እንዲያብራሩ ሲጠየቁ ምስጢር በመሆኑ በእምነት ልንቀበለው እንደሚገባ ይነግሩናል፡፡

በምዕራብ እንዳደገ ሙስሊም ይህንን አባባል ለመመርመር ተነሳሁ፡፡ ከአንድ ክርስቲያን ጋር የመወያየት ዕድል በሚያጋጥመኝ ጊዜ ሁሉ የመጀመርያው የምጠይቀው ጥያቄ “ሥላሴ ላንተ አስፈላጊ ነውን?” የሚል ነው፡፡ በአዎንታ ሲመልሱ “አስፈላጊነቱ ምን ያህል ነው?” የሚል ጥያቄ አስከትላለሁ፡፡ ይህንንም በማድረግ ሥላሴን መካድ ኑፋቄ ነው የሚል መልስ እንዲሰጡኝ እገፋፋቸዋለሁ፡፡ ከዚያም ሦስተኛውን ወሳኝ ጥያቄ አቀርባለሁ፡- “ሥላሴ ማለት ምን ማለት ነው?” በእግዚአብሔር አንድነት ውስጥ ሦስትነት እንዳለ ይነገረኛል፡፡ ከዚያም “ምን ማለት ነው?” የሚል ጥያቄ አቀርባለሁ፡፡ ብዙ ጊዜ መልስ አልባ የፈጠጡ ዓይኖች ያጋጥሙኛል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ስለ እንቁላልና ስለ ውኀ ያወራሉ ነገር ግን ትምህርተ ሥላሴን ሊያብራራልኝ የሚችል ሰው አላጋጠመኝም፡፡ ሦስት ምን በአንድ ምን ውስጥ? ይህ ራሱን የሚጣረስ የማይሆነው እንዴት ነው? ጥያቄዎቼ የዳር ዳር በሁኑ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ አልነበሩም፡፡ ዋና በሚባለው የክርስትና አስተምህሮ ላይ የተኮሩ ነበሩ፤ ነገር ግን ማንም ክርስቲያን ሊመልስልኝ አልቻለም፡፡ ይህ ማለት ያገኘሁት እያንዳንዱ ክርስቲያን ስለ ሥላሴ ከቁርአን የተማርኩት ሁሉ እውነት መሆኑን ያረጋግጥልኛል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ መለኮታዊ ግሳፄን ያስከተለ ትርጉም አልባ አስተምህሮ እንደሆነ ደምድሜያለሁ፡፡[76]

የተከበሩት ኢማሞች፣ የተማሩት መሪዎች፣ የገዛ ወላጆቼና አያቶቼ ሥላሴን በዚህ መነፅር እንድመለከት አስተምረውኛል፡፡ የምወዳቸውና የማከብራቸው ሰዎች ሁሉ ሥላሴን እንዳልቀበል አስተምረውኛል፡፡ ክርስቲያኖች ማብራራት አለመቻላቸው ሲታከልበት ደግሞ ሥላሴን በፅኑ መቃወም የእስላማዊ ማንነቴ አካል ለምን እንደሆነ ግልፅ ይሆናል፡፡ በሁሉም እውነተኛ ሙስሊሞች ዘንድ ያለ ሁኔታ ተመሳሳይ ነው፡፡ዳዊትና እኔ ስለ ሥላሴ ጥቂት ውይይቶችን አድርገናል፡፡ ከብዙ ክርስቲያኖች በተሻለ ሁኔታ በግልፅና በጥልቀት ምላሽ ቢሰጠኝም ሥላሴ ትክክል ሊሆን እንደማይችል ቅድመ ግንዛቤ ስለያዝኩኝ አልተቀበልኩትም ነበር፡፡ ርዕሱ እያጋጨ ስላስቸገረን ጳውሎስን በተመለከተ እዳደረግነው ሁሉ ይህንንም ላለመነጋገር ወሰንን፡፡ብዙዎቻችሁ በማትገምቱት ቦታ ከዳዊት ጎን ተቀምጬ ሳለሁ ነበር በአጋጣሚ መፍትሄውን ያገኘሁት፡፡

# ሥላሴን ማሰላሰል

የሁለተኛ ዓመት የዩኒቨርሲቲ ትምህርቴን ካገባደድኩኝ በኋላ በነበረው የክረምት እረፍት ወቅት ጁላይ 2003 ትልልቅ ለውጦች በሕይወቴ ውስጥ ተከሰቱ፡፡ ከትክክለኛው የመመረቂያ ጊዜዬ አንድ ዓመት ያህል ቀደም ብዬ ለመመረቅ ወሰንኩኝ፡፡ ይህ ማለት ቀጣዩን የሕይወት እርምጃዬን በአንክሮ ማጤን ያሻኛል ማለት ነው፡፡ ውሳኔዬ ሌላ ከባድ ሥራ ያስከትልብኛል፡፡ የኅክምና ትምህርቴን መከታተል እችል ዘንድ የሚሰጠውን ቅድመ ፈተና ለማለፍ የኦርጋኒክ ኬሚስትሪ ትምህርት ቁጭ ብዬ መማር ሊኖርብኝ ነው፡፡ ስለዚህ የክረምት እረፍቴን በመሰዋት በሳምንት አምስት ቀን የሚሰጠውን ትምህርት መማር ተያያዝኩኝ፡፡ ዳዊትም ከእኔ ላለመለየት ትምህርቱን አብሮኝ መውሰድ ጀመረ፡፡

ነገር ግን ትልቅ የሕይወት ለውጥ ያስተናገድኩት እኔ ብቻ አልነበርኩም፡፡ ወደ ውድድር ቦታ ለመሄድ በረራ ከመጀመራችን በፊት እኔና ዳዊት ስለ ትንሣኤ እናወራ ነበር፡፡ “ራስን የመሳት ትወራ” ስለተሰኘው መላምት እናገር ነበር፡፡ ዳዊት እንዲህ አለኝ፡- “ስማ ሰውየው፤ ያ ደካማ ግምታዊ ወሬ በኔ ላይ አይሰራም፡፡ ጥሩ ንቃተ ኅሊና ያላቸው ሰዎች ከሚኖሩበት አካባቢ ነው የመጣሁት!”

አንዷት የውድድር ቡድኑ አባል የሆች ሴት ጆሮዋን ጣል አድርጋ ክርክራችን ታደምጥ ነበር፡፡ በክርክራችን መካከል ጣልቃ ገባች፡፡ “ከምራችሁ ነው ግን? እኔ የመጣሁት ከነጠላ ሴል እንስሳ ነው፡፡” እኔና ዳዊት ሐሳባችንን ወደ እርሷ መለስን፡፡ ይህች ልጅ ማን እንደሆነች አናውቅም ነገር ግን ከኛ ጋር የመወያየት ፍላጎት ነበራት፡፡ እኔና ዳዊትን

የሚያስማማን አንድ ነገር ቢኖር የታወረ ዝግመተ ለውጥ ፈፅሞ የማይመስል መሆኑ ነው፡፡ ሙግቷን ተባብረን ብናከሽፍም አልሞት ባይ ተጋዳይ ሆነች፡፡ በሳምንቱ መጨረሻ ቀናት ስለ እውነት፣ ስለ አንፃራዊነት፣ ስለ እግዚአብሔር፣ ስለ ዝግመተ ለውጥና ስለ ሳይንስ ከእርሷ ጋር ተከራከርን፡፡ ጥሩ የንግግር ክህሎት ያላት ስለነበረች በቀላሉ የምትረታ አልነበረችም፡፡

ከሦስት ቀናት በኋላ ሜሪ የእግዚአብሔርን መኖር አምና ተቀበለች፤ ዳዊት ደግሞ በፍቅር ወደቀ፡፡ ይህ ከሆነ ከሁለት ሳምንታት በኋላ ሁለቱም ተጫጩ፡፡ በ2003 ክረምት ላይ ዳዊትና ሜሪ ከተጋቡ ዓመት የሞላቸው ሲሆን የመጀመርያ ልጃቸውን በጉጉት እንጠብቅ ነበር፡፡ እኔና ዳዊት ወደ ሆስፒታል ፈጥነን እንድንመጣ የሚል የስልክ ጥሪ መች እንደሚደርሰን ስለማናውቅ ሁል ጊዜ በተጠንቀቅ እንጠብቅ ነበር፡፡

ድንገተኛው የስልክ ጥሪ መች እንደሚደርሰን ባናውቅም እንደልማዳችን አስቂኝ ቃላትን እየጻፍን ብጣሽ ወረቀቶችን መቀባበላችንን ቀጥለናል፡፡ ነገር ግን ከመምህርት አዳምስኪ ሦስት ጫማ ባልበለጠ ርቀት ላይ ከፊት ለፊት ተቀምጠናል፡፡ ሥላሴ ለሚለው ፅንሰ ሐሳብ ልቤ የተከፈተበት ቅፅበት በመሆኑ የተቀመጥኩበት ቦታና በወቅቱ የነበረው ሁኔታ ሁሉ የትላንት ያህል ይታወሰኛል፡፡

ከፊት ለፊት ባለው ግድጊዳ ላይ ሦስት የናይትሬት ምስሎች ጎላ ብለው ይታያሉ፡፡ በተወሰኑ ሞሌኪዩሎች ውስጥ የኤሌክትሮን ቅንጣቶች በምን መልኩ እንደተቀመጡ እየተማርን ነበር፡፡ የዚህ ትምህርት መሠረታዊ ፅንሰ ሐሳብ የኬሚስትሪ ዕውቀት ባይኖረን እንኳ ለመረዳት ቀላል ነው፡፡ የትኛውም ቁሳዊ አካል ከአተም የተገነባ ነው፡፡ አተም ፖዘቲቭ ቻርጅ ያለው አስኳል ሲኖረው ይህንን አስኳል የሚዞሩ ነጌቲቭ ቻርጅ ያላቸው የኤሌክትሮን ቅንጣቶች አሉት፡፡ አተሞች አንዳቸው ከሌላቸው ጋር ኤሌክትሮኖቻቸውን በማስተሳሰር ሞሌክዩል ይፈጥራሉ፡፡ በአንድ ሞሌክዩል ውስጥ የሚገኙት የኤሌክትሮኖች አደራደር “የረዞናንስ ድርደራ” በመባል ይታወቃል፡፡ እንደ

ውኃ ያሉ አንዳንድ ሞሌክዩሎች ምንም ረዞናንስ የሌላቸው ሲሆን ሌሎች ደግሞ ሦስትና ከዚያ በላይ ያላቸው አሉ፡፡ ከፊታችን ስሌዳው ላይ የሚታየው ናይትሬት አንዱ ነው፡፡

ፅንሰ ሐሳቡ ለመረዳት ቀላል ቢሆንም ከበስተጀርባው ያለው ዕውነታ ግን አስደማሚ ነው፡፡ መምህርት አዳምስኪ እንዲህ በማለት ክፍለ ጊዜውን ቋጨች፡- “እነዚህ ሦስቱ ስዕሎች የረዞናንስን አደራደር በሰሌዳ ላይ ለማሳየት ጥሩ መንገድ ናቸው ነገር ግን ጉዳዩ ከዚህ እጅግ ውስብስብ ነው፡፡ ረዞናንስ ያለው ሞሌክዩል አደራደሮቹ ምን ጊዜም ከሁለንተናው ጋር አንድ ሲሆኑ ነገር ግን ደግሞ በየትኛውም የጊዜ ነጥብ ላይ ከየትኛውም አደራደሩ ጋር አንድ አይደለም፡፡”

መምህርት አዳምስ የተናገረችውን በመድገም ስላፀናችው በክፍሉ ውስጥ የነበሩት ተማሪዎች እኔ ካሳየሁት ገፅታ ጋር ተመሳሳይ የሆነ የፊት ገፅታ ማሳየታቸው አልቀረም፡፡ “ሁል ጊዜ ከአደራደሮቹ ጋር አንድ ሲሆን ነገር ግን ደግሞ በየትኛውም የጊዜ ነጥብ ላይ ከአደራደሮቹ መካከል አንዱንም አይደለም፡፡” ለአፍታ ያህል ዝም ካለች በኋላ አንድ መተማመኛ ሰጠችን፡፡ “ነገር ግን ስለዚያ አትጨነቁ፡፡ በስዕል መግለፅ ስለምንችለው አደራደር ብቻ ነው የምትፈተኑት፡፡” ይህንን በማለቷ ተማሪዎቹ የእፎይታ ድምፅ አሰሙ፡፡

ነገር ግን እኔ ምንም የእፎይታ ስሜት አልተሰማኝም፡፡ መምህርት አዳምስኪ የተናገረችውን በቀላሉ ማለፍ ባለመቻሌ ዳዊትን ዘወር ብዬ አየሁት፡፡ ዳዊት ትከሻውን ሰብቆ ትኩረቱን ወደ መምህርቷ መለሰ፡፡ እርሷም ወደ ሌላ ርዕስ አለፈች፡፡ በጣለችው የሐሳብ ቦምብ ላይ ትኩረቱ የቀረው ብቸኛው ሰው እኔ ሳልሆን አልቀርም፡፡

አንድ ነገር በአንድ ጊዜ ብዙ የተለያዩ ነገሮችን ሊሆን የሚችለው እንዴት ነው? በአንድ ጊዜ ሞቃት፣ ዝልግልግ፣ ወፈር ያለና ተጣባቂ ሊሆን ስለሚችል የተፈጨ ሥጋ አይደለም እያወራን ያለነው፡፡ በጊዜ ገደብ ውስጥ ስለሚገኙ የኤሌክትሮኖች አደራደር ነው እያወራን ያለነው፡፡ በፕሮፌሰሯ የተባለው ነገር ነቢል ቴክሳስ ውስጥ ተቀምጦ ምግብ እየበላ ሳለ በዚያው ቅፅበት ደግሞ በካሪብያን ደሴት ላይ ተመቻችቶ እንቅልፍ

አሸልቦታል የማለት ያህል ነው፡፡ ሁለቱንም ነገሮች በአንድ ጊዜ ማድረግ ትርጉም የሚሰጥ አይደለም፡፡

ከሁሉ ያስደነቀኝ ደግሞ ሁሉም ሰው በጉዳዩ ምንም አለመጨነቁ ነው፡፡ በጭፍን መቀበላቸው በእጅጉ አስደምሞኝ በክፍሉ ውስጥ የነበሩትን ተማሪዎች ገረመምኳቸው፡፡

ነገር ግን ይህ ጭፍን እምነት ነውን? መምህርቷ ስለ ታህታይ የአተም ቅንጣቶች የሚያወራውን የተረጋገጠ ሳይንስ ነው እያስተማረችን ያለችው፡፡ በዚያ ደረጃ የሚገኙ ቅንጣቶች እኛ በሰውኛ ከምንረዳው ዓለም የተለዩና ትርጉም የማይሰጡ ነገሮችን መሆን ይችላሉ፡፡ ስለ አተም በጣም ቀላልና መሠረታዊ የሆነው እውነታ በራሱ ስናውጠነጥነው በእጅጉ የማይታመን ነው፡፡ የተቀመጥኩበት ወንበር ዝም ብሎ ተሸክሞኝ የተቀመጠ ጠጣር ቁስ አይደለም ማለት ነው፡፡ እጅግ ፈጣን በሆነ ሁኔታ በሚሽከረከሩ ቅንጣቶች የተሞላ ከሞላ ጎደል ባዶ የሆነ ስፍራ ነው፡፡ ስናስበው ስህተት መስሎ ሊታየን ይችላል ነገር ግን ነገሮች በምንኖርበት አፅናፈ ዓለም ውስጥ የሚገኙበት ሁኔታ ነው፡፡ ይህ የተረጋገጠ እውነታ ሲሆን በፍፁም የሚያከራክር ጉዳይ አይደለም፡፡

ተማሪዎቹ ትርጉም አልባ የሆነ ነገር በጭፍን እንዳልተቀበሉ ደመደምኩኝ፡፡ አዕምሯችን በቀላሉ ሊቀበላቸው የማይችላቸው እውነታዎች በምንኖርበት አፅናፈ ዓለም ውስጥ መኖራቸውን ከኔ ቀድመው እንደተቀበሉ ገብቶኛል፡፡

ዓይኖቼ በሰሌዳው ላይ በሚታዩት ሦስቱ የናይትሬት ቅንጣቶች ላይ አረፉ፡፡ በአእምሮዬ ውስጥ ሦስቱን ክፍልፋዮች ለማያያዝ ሞከርኩ፡፡ አንዱ የናይትሬት ሞሌክዩል ሁል ጊዜ ሦስቱንም ረዞናንሶች ነው ነገር ግን ከእነርሱ መካከል አንዱንም አይደለም፡፡ ሦስቱም የተለያዩ ናቸው ነገር ግን ተመሳሳይና አንድ ናቸው፡፡ ሦስት በአንድ ናቸው፡፡

ይህንን እያሰብኩ ሳለሁ ነበር ነገሩ የተከሰተልኝ፡፡ የሰው ልጆች ሊደርሱባቸው የሚችሉ ሦስትነት በአንድነት ያላቸው ነገሮች በዚህች ዓለም ላይ የሚገኙ ከሆነ እግዚአብሔር በዚህ ሁኔታ መኖር እንዴት ነው የማይቻለው?

ልክ እንደዚሁ ሥላሴ እውነት መሆን መቻሉን ልቤ አመነ፡፡ ዳዊትን ተመለከትኩት ነገር ግን ምንም ነገር መናገር አልፈለኩም፡፡

ኋላ ላይ አስተምህሮተ ሥላሴን አዲስ ከሆነ የዕይታ ፅንፍ እንደገና አጠናሁት፡፡ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር አሐዱ ሥሉስ ነው ሲሉ ምን ማለታቸው ነው? በጀምስ ኋይት ‹የተረሳው ሥላሴ›በሚል ርዕስ የተጻፈውን መጽሐፍ አነበብኩት፡፡ ሥላሴያዊ ባሕሪ ያለው አካል እንዳይኖር ምክንያት ሊሆን የሚችል ምንም ነገር እንደሌለ አስተዋልኩኝ፡፡

በአስተምህሮተ ሥላሴ መሠረት እግዚአብሔር በሦስት አካላት የሚኖር አንድ ማንነት ነው፡፡ "አካል" እና "ማንነት" አንድ አይደሉም፡፡ ይህ ማለት ሥላሴ እርስ በርሱ የሚጣረስ አይደለም ማለት ነው፡፡ እስኪ አንድ ምሳሌ ልስጥ፤ እኔ አንድ ማንነት ነው ያለኝ፣ ሰው የሆነ ማንነት፡፡ ደግሞም አንድ አካል ነኝ፣ ነቢል ቁሬሺ፡፡ ስለዚህ እኔ አንድ ማንነትና አንድ አካል ነኝ፡፡ ነቢል ቁሬሺ የተሰኘሁ ሰው ነኝ፡፡ በአስተምህሮተ ሥላሴ መሠረት እግዚአብሔር ሦስት አካላት ያለው አንድ ማንነት ነው፡፡ እነዚህ አካላት አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ይሰኛሉ፡፡

ከዳዊት ጋር ፍሬያማ ውይይት ሳላደርግ የሥላሴን አስተምህሮ በራሴ ጊዜ ተረዳሁኝ፡፡ የእግዚአብሔር ባሕርይ ትክክለኛ ሞዴል ሊሆን መቻሉን ተገነዘብኩኝ፡፡ ከተውሂድ ጋር ስለሚጣረስ እውነተኛ ሞዴል መሆኑን ገና አልተቀበልኩም ነገር ግን ሊሆን መቻሉን ተቀብያለሁ፡፡ ይህንን ሳደርግ ስለ እግዚአብሔር የነበረኝ ግንዛቤ ይበልጥ ዳበረ፡፡

ነገር ግን ወንጌልን እንዳልቀበል እንቅፋት የሆነብኝ አንድ ያልገባኝ ክርስቲያናዊ አስተምህሮ ነበር፡፡ እንዴት ነው የኢየሱስ ሞት የኃጢአቴን ዕዳ ሊከፍል የሚችለው? ዳዊትና እኔ ይህንን ጥያቄ መመለስ ስንጀምር ሦስተኛ ጓደኛ አክለን ነበር፡፡

ምዕራፍ ሠላሳ አራት

# ደህንነት በሚዛን ላይ

በኡዲዩ ያሳለፍኩት ሦስተኛ ዓመት አስደሳች ነበር፡፡ የሦስተኛ ዓመት ተማሪ ብሆንም ካምፓስ ውስጥ ጠቅልዬ ስኖር የመጀመርያዬ ነበር፡፡ እስከዚያች ዓመድ ድረስ ተቃውሞ ባሰማም እማና አባ ካምፓስ ውስጥ መኖር ለጥፋት እንደሚዳርገኝ ስላሰቡ ፍቃደኞች አልነበሩም፡፡ ሦስተኛ ዓመት ሲሆነኝ ነበር ብዙ ሥራ ስላለብኝ ካምፓስ ውስጥ ለመኖር እንደምገደድ ያሳመንኳቸው፡፡

ከኃላፊነቶቼ መካከል አንዱ የተማሪዎች ፐሬዚዳንት መሆን ስለነበር ወላጆቼን አስፈቅጄ የመኖርያ ክፍል መረጥኩኝ፡፡ የመረጥኩት የመኖርያ ክፍል በኋይትሀርት ደቡብ ምዕራብ ሕንፃ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን የፎቁ ጫፍ ነበር፡፡ የክፍሌ አቀማመጥ የኤልሳቤጥን ወንዝ ወደ ታች ማየት የሚያስችል የካምፓሱ ሁለተኛ ማራኪ ዕይታ ነበር፡፡ ቀጥሎ የሚገኘው ክፍል የተሻለ ዕይታ ቢኖረውም ያልተመጣጠነ ሙቀት ስለነበረው አልፈለኩትም፡፡

**ዳዋ፡** ሰዎችን ወደ እስልምና የመጥራት ተግባር

ያ ክፍል ብዙም ሳይቆይ ዛከ በተሰኘ የቡድሃ እምነት ተከታይ ተያዘ፡፡ እኔና ዛከ ኋላ ላይ ተወዳጀን፡፡ ዛከ የፍልስፍና ተማሪ ሲሆን ንግግሩ ለስለስ ያለና በአስተሳሰቡም በሳል ስለሆነ ምሑራዊ በሆነ መንገድ ለመነጋገር ምቹ የሆነ ሰው ነበር፡፡ ሴሚስተሩ በተጀመረ በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ጥሩ ተግባቦት ፈጥረን ስለነበር አንድ ሁለት ጊዜ **የዳዋ** ሥራ ሠርቼበት ነበር፡፡

እንደ አጋጣሚ ሆኖ ዛክ በዳዊት የሚመራ የፍልስፍና ክበብ አባል ሆኖ ስለነበር የተጋጋመ ውይይት ማድረጋቸው አልቀረም፡፡ ስለዚህ እኔና ዳዊት በየፊናችን የዛክ ጥሩ ወዳጆች ሆንን፡፡ ሦስታችንም ወዳጆች መሆናችንን ካረጋገጥን በኋላ አብረን ጊዜ ማሳለፍ ጀመርን፡፡ ሠልስቱ ደቂቃን የቀልድና የሳቅ ማሕበር መሠረትን፡፡

> **የቤዛነት አስተምህሮ፡** ኢየሱስ የሰው ልጆችን የኃጢአት ዕዳ መክፈል መቻሉን የሚናገር አስተምህሮ፡፡

አንድ ቀን ሙስሊም፣ ክርስቲያንና ቡዲህስት ጓደኛሞች ተቀምጣው ለስላሳ መጠጥ እየተጎነጩ ሳሉ ግራ የተጋባሁበትን አንድ የመጨረሻ የክርስትና ርዕሰ ጉዳይ አነሳሁ፡፡ **የቤዛነት አስተምህሮ** ይሰኛል፡፡ እግረ መንገዴን ዛክን የኔ ዳዋ ዒላማ ውስጥ ለማስገባት አስቤ ነበር ያነሳሁት፡፡ ለሁለታችንም ወንጌልን እያካፈለ የነበረውን ዳዊትን በመተቸት ዛክን ወደ እስልምና የማምጣት ፍላጎት ነበረኝ፡፡ ምንም ዓይነት ፍላጎት ያልነበረው ዛክ በመካከላችን አጣብቂኝ ውስጥ ገብቷል፡፡ እንደ ቡዲህስት የነበረው ፍላጎት ምንም ፍላጎት የማጣት ደረጃ ላይ መድረስ ነበር፡፡

ሌባ ጣቴን ወደ እርሱ ጠቁሜ “ዛክ ታውቃለህ እስልምና ፍትሃዊ ሃይማኖት ነው፡፡ አንድ የማይታወቅ ሰው ስለ አንተ ኃጢአት መሰቃየት እንዳለበት አያስተምርም፡፡” አልኩት፡፡

“ቆይ ቆይ እስኪ!” አለ ዳዊት ጣልቃ ገብቶ፡፡ እኔም ፊቴን በፍጥነት ወደ እርሱ በማዞር “ራስህ ቆይ ገና መች ጨረስኩና!” አልኩት፡፡ “ቀደም ሲል እንዳልኩት በእስልምና መሠረት እያንዳንዳችን ለገዛ ኃጢአታችን ተጠያቂዎች ሆነን በፈጣሪ ፊት እንቆማለን፡፡ ስለ እኛ መማለድ የሚችል ማንም የለም፡፡ መንፈሳዊ ሕይወታችን የግል ኃላፊነታችን ነው፡፡ መልካም ሥራችን ከኃጢአታችን ይልቅ ከመዘነ ወደ ገነት እንገባለን፡፡ ኃጢአታችን ከመልካም ሥራችን ይልቅ ከመዘነ ወደ ገሃነም እንኼዳለን፡፡ ይህ ትክክለኛና ፍትሃዊ ነው፡፡ የምለው ገብቶሃል?”

ዛክ “አዎ” በማለት መልስ ሰጠ፡፡

“በእርግጥ ፈጣሪ ፀጋውን ሊለግሰን ከፈለገ ይችላል፡፡ እርሱ ፈጣሪ ነው፡፡ ነገር ግን ኃጢአታችንን በመውሰድ በንፁህ ሰው ላይ ማስቀመጥ የማይታሰብ ነው፡፡ እርሱ ተቀጥቶ እኛ ነፃ መውጣት አንችልም፡፡ እንደርሱ የሚሆን ከሆን ይህ ምን ዓይነት ፍትህ ነው?”

ዳዊት ፈገግ ብሏል፤ ነገር ግን ከተቀመጠበት ተስፈንጥሮ ወደ ጠረጴዛው ወዲህ ጫፍ ለመዝለል የተዘጋጀ ይመስል አቆብቁቧል፡፡ “ፍትሃዊ በሆነ መንገድ አላቀረብከውም” አለ፡፡

“ሰዎች ፍትሃዊነት ሲጎድላቸው ይሰነፍጣል፣ አይደለም እንዴ? አሁን ትንሽ ረጋ በልና አድምጠኝ፡፡ አንድ የምነግርህ ነገር አለ፡፡”

ሁላችንም እየሳቅን ነበር፡፡ ርዕሱ በጣም ከባድ ቢሆንም የመዝናናት ስሜት ተሰምቶን ነበር፡፡ ዳዊት ብዙ የሚናገረው ነገር እንዳለው ያስታውቃል፡፡ መድረኩን ለእርሱ ከመልቀቄ በፊት እንደ መጨረሻ ጥይት የቆጠብኩትን አንድ ምሳሌ ተኮስኩኝ፡፡

“በአሁኑ ወቅት የኛ ብሔራዊ ዕዳ ወደ ሰባት ትሪሊየን ዶላር ደርሷል ልበል? ወደ ፕሬዚዳንት ቡሽ ዘንድ ሄጄ፣ ‹ይስሙኝ ቡሽ፣ የኛ ዕዳ ሰባት ትሪሊየን እንደሆነ አውቃለሁ፣ ነገር ግን እኔ መክፈል እችላለሁ፡፡ ክፍያውን የሚሸፍን አንድ ዶላር ይኸውና ይቀበሉኝ› ብላቸው ቡሽ ምን የሚሉ ይመስላችኋል?”

ዛክ ጊዜ ሳያጠፋ “ጅል ነህ ይልሃል” በማለት መለሰ፡፡

ጣቴን ወደ ዳዊት በመጠቆም “በ-ትክ-ክል ተ-መል-ሷል!” አልኩኝ፡፡

“ለማለት የፈለከው አልገባኝም” አለ ዛክ፡፡

“ሒሳቡ ትክክል አይመጣም እያልኩ ነው፡፡ አንድ ዶላር የትሪሊዮኖችን እዳ መክፈል እንደማይችል ሁሉ ኢየሱስ በመስቀል ላይ መሞቱ የእያንዳንዱን ሰው ዕዳ መክፈል አይችልም፡፡ አንድ ሰው ለሌላው መክፈል ይችላል ብንል እንኳ አንድ ግለሰብ በቢሊየኖች ለሚቆጠሩት ኃጢአተኞች መክፈል አይችልም፡፡ የክርስትና የቤዛነት

አስተምህሮ ኢ-ፍትሃዊ ከመሆኑም በላይ ትክክለኛ ስሌት አይደለም፡፡ እስልምናስ? ውስብስብ ያልሆነ፣ ለመረዳት ቀላልና ሙሉ በሙሉ ፍትሃዊ ነው፡፡" ይህንን ብዬ ሸክሙን እንዳወረደ ሰው ለስላሰዬን ወደመጎንጨት ተመለስኩኝ፡፡

ዛክ ማዶ ማዶ እያየ፣ "መልካም፣ ይህ ትርጉም የሚሰጥ ንግግር እንደሆነ እገምታለሁ" አለ፡፡

ዳዊት ማብራርያዬን አልተቀበለም፡፡ "ጨረስክ?" አለኝ ፈገግ ብሎ፡፡ ጉዳዩ አስቂኝ እንደሆነበት ያሳብቃል፡፡

"አይ ገና መጠጣት መጀመሬ ነው፡፡"

"ማለቴ መንጣጣቱን ጨረስክ?"

"መድረኩ ያንተ ነው፡፡" ከልጅነቴ ጀምሮ የማውቀውን ሙግት በድጋሜ በክርስትና ላይ አቅርቤያለሁ፡፡ ጠንካራ በመሆናቸው ላይ ደግሞ ሙሉ መተማመን ነበረኝ፡፡ ደግሞም ኩራት ተሰምቶኛል፡፡

"ነቢል ሙግትህን ለማቅረብ የክርስትናን አስተምህሮዎች ተገቢ ባልሆነ መንገድ አጣመህ አቅርበሃል፡፡"

ምን እያለ እንደሆነ ስላልገባኝ ዝም ብዬ አየሁት፡፡

"ቀጥል እስኪ፡፡"

"ክርስትና ኢየሱስ አምላክ መሆኑን እንደሚያስተምር በሚገባ ታውቃለህ፡፡ ነገር ግን አስተምህሮውን ስትተች ይህንን እውነታ ከስሌቱ ውጪ አድርገሃል፡፡ እግዚአብሔር ማንነቱ የማይታወቅ መንገደኛ ስለ እኛ እንዲሞት አላስገደደም፡፡ ራሱ ነው የኃጢአት ዕዳችንን የከፈለው፡፡ የተሻለ ምሳሌ የሚሆነው የገዛ አባቱን ንብረት የሰረቀ ልጅ ነው፡፡ ንብረቱን ካወደመ በኋላ ወደ አባቱ ተመልሶ ይቅርታ ቢጠይቅ አባትየው ይቅር የማለት ሙሉ መብት አለው፡፡ ነገር ግን ይህ በቂ አይደለም፡፡ የተዛባው ሒሳብ መስተካከል

ይኖርበታል፡፡ የተሰረቀውን ንብረት የሚተካ ሰው ያስፈልጋል፡፡ ልጁ ከገዛ መዝገቡ ያጎደለውን አባትየው በፍቃደኝነት መክፈል ይችላል፡፡ ይህ ፍትሃዊ ነው፡፡”

ግራ ተጋባሁ፡፡ “ልጅየው ማን ነው?”

“እኛ ነን፡፡ እግዚአብሔር ደግሞ አባታችን ነው፡፡ የእግዚአብሔር ባለ ዕዳዎች ሆነናል ነገር ግን ልንከፍለው አንችልም፡፡ ስለዚህ በምሕረቱ ብዛት የኃጢአታችንን ዕዳ ከፈለልን፡፡ የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው፡፡ እርሱ ስለ እኛ በመሞት ሒሳቡን አስተካከለ፡፡”

ለስላሳዬን እየተጎነጨሁ ዝም ብዬ ተቀመጥኩኝ፡፡ ዛክ ጣልቃ ገባ፡፡ “እሺ ዳዊት፣ እያልክ ያለኸው የገባኝ ይመስለኛል፡፡ ኃጢአት የሠራነው በእግዚአብሔር ላይ በመሆኑ እግዚአብሔር ይቅር ሊለን ይችላል፡፡ ኢየሱስ ደግሞ አምላክ ከሆነ የኃጢአታችንን ዕዳ መክፈል ይችላል፡፡”

ዳዊት አሰብ አደረገ፡፡ “አዎ፣ እንደርሱ ማለት የምትችል ይመስለኛል፡፡” እኔ ግን አልተዋጠልኝም፡- “ነገር ግን አሁንም ይህ ማብራርያ አንድ ሰው ስለ ሰው ልጆች ሁሉ ኃጢአት መክፈል እንደሚችል አያረጋግጥም፡፡”

“ነቢል አሁንም ከፋዩ አንድ ተራ ሰው አለመሆኑን ከግንዛቤ አላስገባህም፡፡ ይህ እግዚአብሔር ነው፡፡ ይህ የትሪሊዮን ዶላሮችን ዕዳ በአንድ ዶላር እንደ መክፈል አይደለም፡፡ ይህ የትሪሊዮን ዶላሮችን ዕዳ ከቁጥር በላይ በሆነ የባንክ መዝገብ እንደ መክፈል ነው፡፡ የእግዚአብሔር ሕይወት በአፅናፈ ዓለም ውስጥ ከሚገኙት ሕይወቶች ሁሉ ድምር ይልቅ ዋጋ አለው፡፡ የእርሱ ሞት እኛ ሁላችን ልንሞት ከተገባን በላይ የሞት ዕዳችንን ይከፍላል፡፡”

ድጋፍ እንደሚሰጠኝ ተስፋ በማድረግ ዛክን ዞር ብዬ ተመለከትኩት፡፡ “የመመለስ ኃላፊነት ያንተ ነው” እንደማለት ዕይታዬን በዕይታ መለሰው፡፡ ሐሳቤን ከእንደገና ሰደርኩ፡፡

“መልካም ዳዊት፣ ሌላ አንድ ችግር አለ፡፡ ይህንን ሁሉ ስትናገር አንድ ሰው ኃጢአት በሥራ ቁጥር መሞት አለበት የሚል ቅድመ ግንዛቤ በመያዝ ነው፡፡ ይህን መቼም ልቀበለው የምችለው አይደለም፡፡”

“ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ነው፡፡ ሮሜ 6፡23፡፡” ዳዊት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ሲጠቅስ ሁል ጊዜ ያስደንቀኛል ደግሞም ያበሳጨኛል፡፡ እስላማዊ አስተምህሮዎችን የሚደግፉ ጥቅሶን መጥቀስ የምችለው አልፎ አልፎ ብቻ ነው ምክንያቱም አብዛኛውን ነገር የተማርኩት ከአስተማሪዎቼ ነውና፡፡ እነርሱ ራሳቸውም ቢሆኑ ጥቅሶቹን አያውቋቸውም፡፡ በዚህ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስን መጥቀሱ ልዩነታችንን አከረረው፡፡

“እውነቱን ለመናገር መጽሐፍ ቅዱስ እንደርሱ ማለቱ ምንም ግድ አይሰጠኝም፡፡ ምንም ትርጉም የሚሰጥ አይደለም፡፡ ትንሹን ስህተት ከትልቁ ወንጀል እኩል የሚቀጣ ምን ዓይነት ዳኛ ነው? እስኪ አስበው፡፡ መንገድ ያለ አግባብ በማቋረጥህ ወደ ዳኛ ተወሰድክ እንበል፡፡ ካንተ በፊት የነበረው ሰው አስገድዶ በመድፈርና በግድያ ተከሶ ሞት ተፈርዶበታል፡፡ አንተም መንገድ ያለ አግባብ በማቋረጥህ ሞት ተፈረደብህ፡፡ ኢ-ፍትሃዊ መሆንን እርሳው፡፡ ያ ዳኛ ጨካኝና አረመኔ ነው!”

ይህ ሙግት በልቤ ውስጥ ጠልቆ የተመሠረተ ነበር፡፡ ኃጢአተኛ መሆኔን በሚገባ አውቃለሁ፡፡ በእግዚአብሔር ትዕዛዛት ላይ በማመፅ ከመንገዱ ይልቅ የገዛ መንገዴን የመረጥኩባቸው ብዙ ጊዜያት ነበሩ፡፡ ነገር ግን በሙስሊሞች እምነት መሠረት ደህንነት ከክፉ ሥራዎች ይልቅ የበዙ መልካም ሥራዎችን መሥራት በመሆኑ እኔ ደግሞ በመልካሙ የሚዛን ጎን ላይ መቀመጤን አምን ስለነበር በኃጢአቴ ምክንያት የከፋ ኀዘን ተሰምቶኝ አያውቅም፡፡ ለእኔ ኃጢአት መጥፎ ነገር ነው፤ ነገር ግን በጣም ከፉ ነው የምለው አይደለም፡፡

ነገር ግን ኃጢአቶች ሁሉ ወደ ገሃነም የሚወስዱ አጥፊ ነገሮች ከሆኑ እኔ ያለኝ የመዳን ተስፋ ምንድነው? በእርግጥ አላህ ምህረት ማድረግ ይችላል፤ ነገር ግን ቁርአን አላህ

ኃጢአተኞችን እንደማይወድ ይናገራል፡፡ የማይወደኝ ከሆነ እኔን ለመማር ምን ምክንያት አለው?

ዳዊት ከዚህ ቀደም ግንዛቤ ያለው ይመስል የጉዳዩን አስኳል በመንካት ተናገረ፡፡ ጭንቅላቱን በማወዛወዝ ረጋ ባለ ድምፅ እንዲህ አለ፡- "ነቢል አሁንም ክርስቲያናዊ አስተምህሮዎችን በእስልምና መነፅር እየተመለከትክ ነው፡፡ ኃጢአት ነፍሶችን የሚያጠፋ፣ ዓለማትን የሚያፈራርስ አውዳሚ ነገር እንደሆነ ክርስትና ያስተምራል፡፡ ሁሉንም ነገር ቀስ በቀስ እንደሚበላ ካንሰር ነው፡፡ ለዚህ ነው ይህ ዓለም ቀድሞ ከነበረው የኤደን ገነት መልክ እጅግ አስጨናቂና አሳቃቂ ወደሆነ ቦታ የተለወጠው፡፡ እግዚአብሔር ይህንን የሚመስል ነገር በሰማይ እንዲፈፀም የሚፈቅድ ይመስልሃል? በእርግጠኝነት አያደርገውም፡፡ ሰማይ ፍፁም የሆነ ቦታ መሆን ካለበት ምንም ዓይነት ኃጢአተኛ በውስጡ መገኘት የለበትም፡፡ አንድ እንኳ እዚያ መኖር የለበትም፡፡"

መጨረሻ ላይ የተናገረው ቃል አየር ላይ ተንጠልጥሎ ቀረ፡፡ ቀስ በቀስ ክብደቱ እየጨመረ ወደ ውስጤ ጠልቆ ገባ፡፡

ከጥቂት የዝምታ ጊዜ በኋላ ተናገርኩ፡፡ "ታድያ ተስፋችን ምንድነው ዳዊት?"

ዳዊት በእርግጠኝነት መንፈስ ፈገግ አለ፡፡ "የእግዚአብሔር ፀጋ ብቻ፡፡"

"ነገር ግን ለምንድነው ፀጋውን የሚሰጠኝ?"

"ስለሚወድህ፡፡"

"እኔን ኃጢአተኛውን ለምንድነው የሚወደኝ?"

"ምክንያቱም እርሱ አባትህ ስለሆነ ነው፡፡"

ዳዊት የተናገረው ቃል ኃይል በእጅጉ መታኝ፡፡ ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን "አባት" ብለው ሲጠሩት ሰምቻለሁ ነገር ግን ትርጉም ሰጥቶኝ አያውቅም ነበር፡፡ እግዚአብሔር ምህረቱንና ፀጋውን ለምን እንደሚሰጠኝ ሳስብ ነበር ጉዳዩ የተከሰተልኝ፡፡

መናገር ተሳነኝ፡፡ ሁሉም ነገር እየተገጣጠመ ነበር፡፡ አባቴ ለምን እንደሚወደኝ ጥያቄ እጠይቅ ይሆን? ከመወለዴ ጀምሮ ወዶኛል፡፡ አዛንን ጆሮዬ ላይ ከተናገረበት ዕለት ጀምሮ ወዶኛል፡፡ ምንም ነገር ስላደረኩለት አይደለም ነገር ግን አባቴ ስለሆነ ነው፡፡ ለእኔ ያለውን ፍቅርና በጎነት ተጠራጥሬ አላውቅም፡፡ ምንም ነገር ሰርቼ ስላስደሰትኩት አይደለም፤ ነገር ግን ልጁ በመሆኔ ብቻ ነው፡፡

የእውነት እግዚአብሔር የወደደኝ በዚህ መልኩ ነውን? እግዚአብሔር ያን ያህል አፍቃሪ ሊሆን ይችላልን? ይህን ያህል ግሩም አምላክ ሊሆን ይችላልን?

የሰማዩ አባቴን ለመጀመርያ ጊዜ ፊት ለፊት የተገናኘሁት ያህል ነበር የተሰማኝ፡፡ የኃጢአቴን ጥልቀት ከተረዳሁ በኋላ የፍቅሩ ብዛት ጥፍጥና ደግሞ ይበልጥ አስደነቀኝ፡፡ ይህ አምላክ፣ በወንጌል ውስጥ ራሱን የገለጠው አምላክ እጅግ አስደናቂ ነው፡፡

ልቤና አእምሮዬ አብዮታዊ ለውጥ ማድረግ እየጀመሩ ነበር፡፡

ምዕራፍ ሠላሳ አምስት

# ወንጌል ሲፈተሽ

ሦስታችንም ከካፌው በመውጣት በኔ መኪና ወደ ካምፓስ ጉዞ ጀመርን፡፡ እየነዳሁ ቅድም የሰማኋቸውን ሐሳቦች አመነዥግ ነበር፡፡ ልክ የመጨረሻው ብሎን ቦታውን ያገኘ ያህል ነበር የተሰማኝ፡፡ ጥያቄዬ ተመልሶልኛል፡፡

ዳዊትም ጉዳዩን እያውጠነጠንኩኝ እንደነበር ስለገባው ከዛክ ጋር ወሬ በመጀመር እንዳሰላስል ነፃነት ሰጠኝ፡፡ "እሺ ዛክ፡፡ ስለ ክርስትና የቀረበውን ሙግት ስለ ቡድሂዝም ከሚነገረው ጋር ስታነፃፅር እንዴት ታየዋለህ?"

ዛክ ከዚህ ቀደም የማይክን የውይይት ቡድን ከዳዊት ጋር በተደጋጋሚ ተካፍሎ ስለነበር ለእንደነዚህ ዓይነት ጥያቄዎች አዲስ አልነበረም፡፡ ከኋላ ወንበር ላይ እንዲህ ብሎ መለሰ፡- "እውነቱን ለመናገር ቡዲሂዝም ምንም ዓይነት ሙግት የለውም፡፡ ለመከተል ልትመርጠው የምትችለው መንገድ ነው፡፡ እኔ የተከተልኩት በተመስጦው ምክንያት ነው፤ ነገር ግን ሌላ ሰው እንዲከተለው ወይም እውነት መሆኑን ለማንም መንገር አልችልም፡፡ ክርስትና በዚህ ረገድ ይለያል፡፡ በክርስትና መሠረት ኢየሱስ ሞቶ ከሞት ተነስቷል የሚለው አባባል ወይ እውነት ነው ወይም ደግሞ ውሸት ነው፡፡ ለእንዲህ ዓይነቱ ነገር ሙግት ልታቀርብለት ትችላለህ፡፡"

ይህ ንግግር ትኩረቴን ስለሳበው ዝም ልል አልቻልኩም፡፡ "ዛክ ስለ አንድ ጉዳይ ትክክል እንደሆንክ አስባለሁ፡፡ ለክርስትና ሙግት ማቅረብ ትችላለህ ነገር ግን ደግሞ ለእስልምናም እንደዚያው ማድረግ ትችላለህ፡፡"

ዳዊት ሲጠብቀው የነበረው ክፍተት ይህ ነበር፡፡ “መልካም ነቢል፣ ሃቀኝነትህን ለማሳየት ጊዜው ነው፡፡ የክርስትና ሙግት በሦስት ነገሮች ላይ እንደተመሠረተ ተናግረሃል፤ ኢየሱስ አምላክ መሆኑን መናገሩ፣ መስቀል ላይ መሞቱና ከሙታን መነሳቱ፡፡ እነዚህን ሁሉ ጉዳዮች አጥንተናል፡፡ እነዚህ ጉዳዮች ታሪካዊ መሆናቸውን በተመለከተ ከዜሮ እስከ አንድ መቶ ባሉት የመለኪያ ቁጥሮች መካከል ስንት ነጥብ ትሰጣቸዋለህ? ዜሮ ማለት ምንም ታሪካዊ መሠረት የላቸውም የሚለውን ይወክላል፡፡ መቶ ደግሞ የተረጋገጡ ታሪካዊ እውነታዎች መሆናቸውን ያመለክታል፡፡ በል እስኪ ንገረኝ?”

ያቺ ቅፅበት የእውነት ቅፅበት ነበረች፡፡ ለስላሳ እየጠጣን ያደረግነው ውይይት ጋሻዬን አሳስቶት ስለነበር በመከላከል ቦታ ላይ አልነበርኩም፡፡ ከመመለሴ በፊት ጥያቄውን በሚገባ አብላላሁት፡፡ “ከሰማንያ እስከ ሰማንያ አምስት በመቶ እሰጣቸዋለሁ፡፡ በጣም ጠንካራ ናቸው፡፡”

ዳዊት መደመሙን ለመናገር ወደ ተሳፋሪ ወንበር ዞር ብዬ ማየት አላስፈለገኝም፡፡ “እስልምናንስ የት ታስቀምጠዋለህ?”

ከመ ቅፅበት ራሴን በተከላካይ ቦታ ላይ አገኘሁት፡፡ ሃይማኖቴን ማስደፈር የለብኝም የሚል ስሜት አየለብኝ፡፡ “ምን ጥያቄ አለው ዳዊት፤ መቶ ከመቶ ነዋ፡፡ የእስልምና ሙግት ምንም ሽንቁር የለውም፡፡ የመሐመድን ሕይወት ያጠና ማንኛውም ሰው የአላህ ነቢይ መሆኑን ይደመድማል፡፡ ሚዛናዊ በሆነ አስተሳሰብ ቁርአንን ያጠና ሰው ደግሞ በሳይንሳዊ ይዘቱና ውብ በሆኑት ትምህርቶቹ ይደመማል፡፡”

እስልምናን የክርስትና ያህል በጥልቀት አለመመርመሬን ዳዊትና ዛክ እንደሚያውቁት ሁሉ እኔም አውቃለሁ፡፡ ነገር ግን እስምናን ሙሉ በሙሉ ሳይመረምሩ እንዲያው በጭፍን እውነት መሆኑን ማመንና በራስ በመተማመን መናገር የእኔም ሆነ የአብዛኞቹ ሙስሊሞች ልማድ ነው፡፡ ሙስሊሞች የሚናገሩትን ቋንቋ ያህል የእስልምና ባሕልና ውርስ አካል ሆኗል፡፡ ሁሉም ሙስሊም በዚያ መልኩ ነው የሚያስበው፡፡ ስለዚህ

ለዳዊት የሰጠሁት ጠንካራ ምላሽ በዘፈቀደ የተነገረ አልነበረም፡፡ ዓለምን የማይበት መነፅር ነበር፡፡

ዳዊት በሰጠሁት  የተኮፈሰ መልስ ላይ ጊዜውን አላጠፋም፡፡ “መሐመድና ቁርአን የሚሉት ያንተ መለኪያዎች ናቸው?”

“አዎ፣ እንደርሱ ይመስለኛል፡፡ መሐመድ እውነተኛ የፈጣሪ መልዕክተኛ መሆኑን የሚያመለክት ጠንካራ ማስረጃ ማቅረብ ከቻልኩኝ እርሱ ያመጣውም መልዕክት ከፈጣሪ መሆኑን ልደመድም እችላለሁ፡፡ ወይም ደግሞ ቁርአን ግልጠተ መለኮት መሆኑን ማረጋገጥ ከቻልኩኝ  የሚያስተምረው መልዕክት እውነት መሆኑን መናገር እችላለሁ፡፡”

የተናገርኩትን ነገር ዳዊት በአዎንታ የተቀበለ ቢሆንም ዛክ ግን በዝምታ ሊያልፈኝ አልቻለም፡፡ ከልቡ ስቆ ካሽማቀቀኝ በኋላ እንዲህ አለ፡- “የምር ግን ለእስልምና የሚቀርበው ሙግት ሙቶ በሙቶ አስተማማኝ እንደሆነ ታምናለህ? ማለቴ እውነቱን እንነጋገር እንጂ፡፡ ያን ያህል ጠንካራ ሊሆን የሚችል ምንም ነገር የለም!”

“ዛክ፣ እስልምና እንደርሱ እንደሆነ አስባለሁ፡፡ ለማመን እንደሚከብድ አውቃለሁ፡፡ ነገር ግን እስኪ ለማየት ጊዜ ውሰድ፣ ያኔ የምለው ይገባሃል፡፡”

ዛክ አሁንም ሊለቀኝ አልቻለም፡፡ “ታድያ እንደርሱ የምታስብ ከሆነ ለምን በማይክ ቤት በሚደረገው ስብሰባ ላይ በሚቀጥለው ቀን ተገኝተህ ሙግትህን አታቀርብም?”

“ሙግት ለእስልምና?”

“በመሐመድ ወይም በቁርአን ልትጀምር ትችላለህ፡፡ ከዚያ ቀጣዩ ነገር ምን እንደሚሆን አብረን እናያለን፡፡ ማይክ ቅር እንደማይለው እርግጠኛ ነኝ፡፡ ስለ ቡዲሂዝም ተነጋግረን ስለጨረስን አዲስ ርዕስ እየፈለግን ነው፡፡”

ስለ ጉዳዩ ባሰብኩኝ ቁጥር እየወደድኩት መጣሁ፡፡ ለዳዋ እንደሚሆን አጋጣሚ ነበር የቆጠርኩት፡፡ ስለ ክርስትና ስለማናወራ ከአባቴ ጋር ስለ ክርስቶስ ስቅለት ስንነጋገር ከነበረው ሁኔታ በተፃራሪ ውይይቱን እኔ እንደምቆጣጠረው አሰብኩኝ፡፡ “በእርግጠኝነት

እንደርሱ አደርጋለሁ፡፡ በሚቀጥለው ጊዜ ስለ መሐመድ በመነጋገር እንጀምርና ከዚያ ወደ ቁርአን አልፋለሁ፡፡” ዳዊት የቀን መቁጠርያውን ከተመለከተ በኋላ ቀጣዩ የስብሰባ ጊዜ ከሁለት ሳምንታት በኋላ መሆኑን አረጋገጠ፡፡ እቅዳችንን መልክ ካስያዝን በኋላ ያቺን ዕለት መጠባበቅ ጀመርን፡፡ ነገር ግን ሁላችንም የየራሳችን ፍላጎት ነበረን፡፡

ለዚያች እለት ዝግጅት ሳደርግ ከአንዱ የሕይወት ምዕራፍ ወደ ሌላው ለማለፍ ጫፍ ላይ መድረሴ አልታወቀኝም ነበር፡፡ በወላጆቼ የተገነባልኝን ዓለም በፀጋ ተቀበዬ ነበር፡፡ ይህ ዓለም እስልምና ላይ ምንም ዓይነት ጥያቄ የማይቀርብበት ዓለም ቢሆንም ከፊቴ የነበረው ጊዜ የቆምኩበት መሠረት በሚገባ ተፈትሾ የሚፈራርስበት ነበር፡፡

*ሮበርት ኤም ቦው ማን ጁንየር በግራንድ ራፒድስ ሚችጋን የሃይማኖታዊ ጥናትና ምርምሮች ዳይሬክተር ሲሆኑ የበርካታ መጻሕፍትና መጣጥፎች ደራሲ ናቸው፡፡ እሳቸው የጻፉትን የሊቅ አስተዋፅዖ ለማንበብ contributions.NabeelQureshi.com ይጎብኙ፡፡*

# ክፍል ፯

# ስለ መሐመድ እውነተኛው ነገር

*መሐመድ ያንተ መልዕክተኛ መሆኑን የምመሰክረው እንዴት ነው?*

# መሐመድን በአጉሊ መነፅር

የእስልምና መልዕክት ከመልዕክተኛው ጋር የተቆራኘ ነው፡፡ ለአንዱ መታመን ለሌላው መታመን ነው፡፡ አንዱ በሌላው ይተረጎማል፡፡ ይህንን ጉዳይ አስገራሚ የሚያደርገው ደግሞ ስለ አላህ ያለው እውነታ ተመሳሳይ አለመሆኑ ነው፡፡ የሙስሊሙ ማሕበረሰብ በአላህ ላይ ጥያቄ የሚያነሱትን ሙስሊሞች ብዙ ጊዜ ይታገሳቸዋል፡፡ ነገር ግን በመሐመድ ላይ ጥያቄ ማንሳት ከማሕበረሰቡ መገለልን ያስከትላል፡፡ የከፋ ነገርም ሊከተል ይችላል፡፡

መሐመድ ሰው መሆኑንና እንደማንኛውም ሰው ስህተት የሚሠራ መሆኑን እያንዳንዱ ሙስሊም ያለማቅማማት ቢቀበልም ነገር ግን እንከን አልባ እንደሆነ ሰው የመቁጠር ሁኔታም ይታያል፡፡ እስላማዊ *ሥነ መለኮት* ለመሐመድ *አል-ኢንሳን አል-ከሚል* “ፍፅምና ላይ የደረሰ ሰው” የሚል መዕርግ እስከማጎናፀፍ የተለጠጠ ነው፡፡

ነገር ግን ወደ ሙስሊሞች ልብ እጅግ ከመቅረብ አልፎ መሐመድ እስልምናን በሁለንተናው የሚገልፅ ነው፡፡ የመላው እስላማዊ ሥልጣኔ ሰንደቅ ነው፡፡ በሐዲስና ትውፊቶች ምክንያት የሙስሊም ሃይማኖት፣ ባሕል፣ቅርሶችና መለያዎች ሁሉ ምሉዕ የሚሆኑት በመሐመድ ነው፡፡ ለዚህ ነው ሙስሊሞች በእርሱ ላይ የሚሰነዘሩትን ጥቃቶች ሁሉ በእነርሱና የእነርሱ በሆነው ነገር ሁሉ ላይ እንደተሰነዘሩ ጥቃቶች የሚቆጥሩት፡፡

ለዚህ ነው በደምሳሳው ስንናገር ሙስሊሞች በትዕግስት ስለ መሐመድ መወያየት የሚሳናቸው፡፡ ከርዕሱ ጋር ያልተገናኙ ዝባዝንኬ ነገሮችን ወደ ውይይቱ ያመጣሉ፡፡ ስለ መሐመድ ከተነሳ ለዘመዶቻችን ታማኞች ስለመሆንና የእስራኤልና ፍልስጥኤም ግጭቶችን የመሳሰሉ ወቅታዊ ጉዳዮችን እንኳ ወደ ውይይቱ ሊያመጡ ይችላሉ፡፡

ከዚህ የተነሳ በማይክ መኖርያ ቤት ውስጥ ስለ መሐመድ ውይይት ባደረግንበት ወቅት ፍላጎቴን በጥልቀት መረዳት የቻለ ሰው አልነበረም፡፡ መሐመድን በጥሩ ሁኔታ አሳምሮ በማቅረብ እስልምናን ከፍ ከፍ የማድረግ ተስፋ ስለነበረኝ በጉጉት ተሞልቼ ነበር፡፡ ሌሎች ታዳሚያን ደግሞ ለመማርና እኔ የምናገረውን ነገር በአንክሮ ለማጤን ነበር በቦታው የተገኙት፡፡

ጥያቄዎቻቸው በእኔ ላይ የሚፈጥሩትን ተፅዕኖ ቢያስተውሉ ኖሮ የበለጠ የተለሳለሰ ንግግር በተጠቀሙ ነበር፡፡ ስሜቴን ማወቅ ባለመቻላቸው ደስተኛ ነበርኩኝ፡፡

የስብሰቡ ስብጥር ካሰብኩት በላይ ነበር፡፡ ማይክ፣ ዳዊትና ጥቂት ክርስቲያኖች ነበሩ፡፡ ዛክ ቡድሂዝምን በመወከል ተገኝቷል፡፡ ነገር ግን ደግሞ አምላክ የለሾችና ስለ አምላክ መኖር እርግጠኞች መሆን እንደማይችሉ የሚያምኑ ወገኖችም በቦታው ተገኝተዋል፡፡ እነዚህ ወገኖች አንዱ መርማሪ ፖሊስ፣ ሌላው አስትሮ ፊዚሲስትና ሁለቱ መምህራን ነበሩ፡፡

የመግቢያ ንግግሮች ከተደረጉ በኋላ መድረኩ ተለቀቀልኝ፡፡ ስለ መሐመድ ለመሟገት ገላጭ ምስሎችንና ቻርቶችን የተጠቀምኩ ሲሆን ከልጅነቴ ጀምሮ የተማርኳቸውን መረጃዎች ነበር ያካፈልኩት፡፡ በምዕራብ የሚኖሩት ሙስሊሞች ድልድይ ለማበጀትና ወደ እስልምና የሚመጡትን ሰዎች ለማጥመድ የሚጠቀሙትን ዘዴ በመጠቀም እስልምናንና እስላማዊ ታሪኮችን የማቅረብ ሙከራ አደረኩኝ፡፡

ከ 9/11 የሽብር ጥቃት ወዲህ ከነውጠኛ እስላማዊ ገፅታ በተቻለ መጠን ራስን ማራቅ በምዕራብ የሚኖሩት ሙስሊሞች ጭንቀት ሆኗል፡፡ እኔ ደግሞ የአሕመዲ ሙስሊም እንደመሆኔ መጠን ይህ ለኔ እጅግ አስፈላጊ ነበር፡፡ እስልምና ሰላማዊ ሃይማኖት

መሆኑንና መሐመድም ደግሞ በሰው ልጆች ታሪክ ከተነሱት ሰዎች ሁሉ እጅግ ርህሩህና ደግ ሰው መሆኑን በመናገር ሙግቴን ጀመርኩኝ፡፡ በዓለም የንግድ ማዕከልና በፔንታገን ላይ የተፈፀሙት ጥቃቶች እስልምናን እንደማይወክሉ ለሁሉም ሰው በአፅንዖት አረጋገጥኩኝ፡፡ "መስከረም 11 አውሮፕላኖቹን የጠለፉት ሽብርተኞች እስልምናንም ጭምር ጠልፈዋል" የሚል አባባል ጠቀስኩኝ፡፡ ይህ አባባል የራሴ ሳይሆን አንድ የመስጊድ ኢማም ሲናገር የሰማሁት ነበር፡፡

ኢስላም የሚለው የአረብኛ ቃል "ሰላም" ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ከሆነ ሥረወ ቃል የመጣ መሆኑንና የመሐመድም ሕይወት ይህንኑ እንደሚያንፀባርቅ አብራራሁኝ፡፡ መካውያውን ሙስሊሞች ላይ ካደረሱት በደል በተፃራሪ መሐመድ መካን ባሸነፈበት ዕለት ያሳየውን ምህረት የሚያወሳውን ታሪክ ጠቀስኩኝ፡፡ መሐመድ የተሳተፈባቸውን ሌሎች ሰልፎች ሁሉ በመጥቀስ ሁሉም የመከላከል ጦርነቶች እንደነበሩ፣ አላህ ደግሞ ተዓምራዊ በሆነ መንገድ ጣልቃ በመግባት ማፅደቁን በአፅንዖት ተናገርኩኝ፡፡

ከዚህ በተጓዳኝ መሐመድ ስለ ሳይንስ የነበረውን የጠለቀ ግንዛቤ አስረዳሁኝ፡፡ በሙስሊም ዓቃቤያነ እምነት ዘንድ ይህ የተለመደ ነው፡፡ መሐመድ ስለ ሽል ዕድገት፣ ስለ ሥነ ፈለክና ስለ ጂኦሎጂ ዕውቀት እንደነበረውና አላህ ካልገለጠለት በስተቀር ይህንን ዕውቀት ማግኘት እንደማይችል ተሟገትኩኝ፡፡ ይህም ደግሞ መሐመድ በአላህ የተባረከ እውነተኛ ነቢይ መሆኑን እንደሚያመለክት ተናገርኩኝ፡፡

ሌላው ሙስሊም ዓቃቤ እምነታውያን የሚጠቀሙት ስልት ለእስላማዊ ሙግቶቻቸው ድጋፍ ለማግኘት መጽሐፍ ቅዱስን መጥቀስና እስልምና የአዲስ ኪዳን እንዲሁም የብሉይ ኪዳን ምልዓት መሆኑን ማስረዳት ነው፡፡ ይህንን ለማድረግ ስለ መሐመድ የተነገሩ ትንቢቶች እንደሆኑ ያሰብኳቸውን ሁለት ጥቅሶች አንዱን ከብሉይ ሌላውን ከአዲስ ኪዳን ጠቀስኩኝ፡፡ የመጀመርያው ዘጸአት 18፡18 ሲሆን እንደ ሙሴ ያለ ነቢይ እንደሚነሳ ይናገራል፡፡ ኢየሱስ በሁሉም ረገድ እንደ ሙሴ ባለመሆኑ ይህ የግድ መሐመድ መሆን እንዳለበት ተሟገትኩኝ፡፡ ከዚያም ዮሐንስ 16፡12-13 በመጥቀስ ኢየሱስ

ሰዎችን ወደ እውነት የሚመራ አፅናኝ ከእርሱ በኋላ እንደሚመጣ መናገሩን አስገነዘብኩኝ፡፡ ከኢየሱስ በኋላ ትልቅ የሚባል የሃይማኖት መሪ ከመሐመድ ሌላ ስላልተነሳ ይህ ሰው መሐመድ መሆን አለበት አልኩኝ፡፡

እስልምና የመጨረሻ መልዕክት መሆኑን፣ መሐመድም አይሁዳዊነትንና ክርስትናን ለመሻር ሳይሆን ለማፅናትና ወደ አንዱ እውነተኛው አምላክ ከእንደገና ለመመለስ መምጣቱን በመናገር ሙግቴን አጠናከርኩኝ፡፡ የመሐመድ መልዕክት “ዓይን ስለ ዓይን” የሚለውን የሙሴን ፍትሃዊ ሕግና “ሌላኛውን ጉንጭህን አዙረህ ስጠው” የሚለውን የኢየሱስ የምህረት መልዕክት በማጣመር ዋና መመርያ ያደረገ መሆኑን እንዲሁም እስልምና ለሰው ልጆች የተላከ የመጨረሻው መልዕክት መሆኑን አፀናሁኝ፡፡ ይህንን የመደምደምያ መልዕክቴን ስናገር ሙስሊሞች የሚያመልኩት አምላክና አይሁዶች እንዲሁም ክርስቲያኖች የሚያመልኩት አምላክ አንድ ዓይነት መሆኑን በማረጋገጥ ነበር፡፡

ለአርባ አምስት ደቂቃዎች ያህል የተናገርኩኝ ሲሆን እስልምናን በትክክል ማሳየቴንና የመሐመድን ነቢይነት የሚያረጋግጥ ሙግት በመንፈሳዊ ቅንዓት በተሞላ ሁኔታ ማቅረቤን እርግጠኛ ነበርኩኝ፡፡

ነገር ግን ጥያቄዎች መነሳት ጀመሩ፡፡

ክርስቲያኖችን ስለ ሥላሴ እጠይቅ እንደነበሩት ዓይነት ጥያቄዎች ሁሉ ከቅንነት የመነጩ የማብራርያ ጥያቄዎች ነበሩ፡፡ ነገር ግን ለመጀመርያ ጊዜ ጥያቄ ተቀባይ ሆኜ ራሴን አገኘሁት፡፡

ማይክ ጀመረ፡፡ “ነቢል ጥያቄ አለኝ፡፡ እስልምና በሰይፍ መስፋፋቱን ሰምቻለሁ፡፡ አንተ ግን መሐመድ ራስን በመከላከል ጦርነቶች ብቻ እንደተሳተፈ ነው የነገርከን፡፡ ያንተ አመለካከት ትክክል መሆኑን በማስረጃ ልታረጋግጥልኝ ትችላለህ?”

ይህ ጥያቄ የተለመደ ስለነበር በፍጥነት መልስ ሰጠሁኝ፡፡ "ቁርአን *ላ-ኢቅራሀ ፊ-ዲን* ይላል፡፡"[77] ኢማሞች ብዙ ጊዜ ንግግራቸው የበለጠ ክብደት እንዲኖረው በአረብኛ ይናገራሉ ስለዚህ እኔም እንደዚያው አደረኩኝ፡፡ "ይህ ጥቅስ በሃይማኖት ማስገደድ የለም ተብሎ ነው የሚተረጎመው፡፡ መሐመድ ደግሞ ቁርአንን አጥብቆ ከመከተሉ የተነሳ ሙሉ በሙሉ በኑሮው ገልጦታል፡፡ ስለዚህ በሃይማኖት ማስገደድ እንደሌለ ያስተማረው መሐመድ እስልምናን በሰይፍ አስፋፍቶታል ብሎ መናገር ትርጉም የሚሰጥ አይደለም፡፡"

ከዚያ ቀደም ስለ እስልምና ስናገር ሰዎች የምሰጠውን ምላሽ በቂ እንደሆነ በመቁጠር ይቀበላሉ፡፡ ነገር ግን ማይክ ከሻቢር ጋር ለክርክር ከመቅረቡ በፊት ስለ እስልምና የተወሰነ ነገር አንብቦ ተዘጋጅቶ ኖሮ ተያያዥ ጥያቄ አስከተለ፡፡ "ነገር ግን ነቢል ሌሎች ጥቅሶች ደግሞ በቁርአን ውስጥ ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ ‹ አጋሪዎችን ባገኛችኋቸው ቦታዎች ሁሉ ግደሏቸው›[78] የሚል፡፡ አንተ የጠቀስከው ጥቅስ ቅድሚያ እንደሚሰጠው በምን እናውቃለን?"

እንደ አጋጣሚ ሆኖ ይህ ጥያቄ በቅርቡ በተደረገ ኹጥባ ሲብራራ በመስማቴ መልሱ አልከበደኝም፡፡ "ያ ጥቅስ የመካ መድብለ አማልክታውያን ከሙስሊሞች ጋር የሰላም ውል ባፈረሱበት ወቅት የተነገረውን ሁኔታ ብቻ የተመለከተ ነው፡፡ አጠቃላይ መርህ አይደለም፡፡ አጠቃላዩ መርህ ሰላም የሚል ነው፡፡"

ከዝያ ማይክ እጅግ ቀላል ነገር ግን ደግሞ እጅግ አውዳሚ የሆነውን ጥያቄ አቀረበ፡፡

"ያንን እንዴት ነው ልታውቅ የቻልከው?"

"ይቅርታ ምን አልከኝ?"

"የቁርአንን ታሪካዊ ዳራ እንዴት ነው ያወከው?"

"የመሐመድን ትውፊቶች መዝግበው ከያዙት የሐዲስ መጻሕፍት ነው፡፡"

"ነገር ግን እነሱ ተዓማኒ መሆናቸውን እንዴት ነው ማወቅ የምትችለው? እኔ የታሪክ ተመራማሪ መሆኔን አትረሳ ነቢል፡፡ ክርስትናን እንኳ በጥልቀት ስፈትሽ የታሪክ

መዛግብትን የምመረምረው በዚህ መልኩ ነው፡፡  አራቱ ወንጌላት ከኢየሱስ በኋላ ብዙም ሳይቆዩ የዓይን ምስክሮች ባሉበት ማሕበረሰብ ውስጥ ስለተጻፉ ልተማመንባቸው እችላለሁ፡፡ የሐዲስ መጻሕፍት ተዓማኒ መሆናቸውን እንዴት እናውቃለን? ቀደም ብለው የተጻፉ ናቸውን? በዓይን ምስክሮች የተጻፉ ናቸውን?”

እኔው ራሴ ስጠይቃቸው የነበርኳቸው ጥያቄዎች ወደኔ ሲዞሩ መግብያ ጠፋኝ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን ዘውትር በምንተችበት መንገድ እስላማዊ ትውፊቶችን የሚተች ሰው አጋጥሞኝ አያውቅም፡፡ በክፍሉ ውስጥ የነበሩት ሰዎች ይህ ጥያቄና መልስ ወዴት እንደሚያመራ ለማወቅ በመጓጓት አንገቶቻቸውን አስግገዋል፡፡ በሕይወት ዘመኔ የተማርኳቸውን መረጃዎች ሁሉ አንድ ላይ አሰባስቤ አሰለፍኳቸው፡፡

“ማይክ በመሐመድ ዘመን የነበሩት የዓይን ምስክሮች ታሪኮቹ በጽሑፍ እስከሰፈሩበት ጊዜ ድረስ በአፈ ታሪክ ነበር ሲያቀባብሉ የነበሩት፡፡ በጽሑፍ ያሰፈሯቸው ሰዎች እጅግ የተከበሩ ሲሆኑ የየታሪኮቹ የዘገባ ሰንሰለቶች ጠንካራ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ከፍተኛ ጥንቃቄ አድርገዋል፡፡ ለዚህ ነው ሐዲሳትን ለማመን የምንችለው፡፡”

ያለኝ የመጨረሻ ጥሩ መልስ እርሱ ቢሆንም ማይክ ግን አልተዋጠለትም፡፡ “ምን እያልክ እንደሆነ ገብቶኛል፡፡ ነገር ግን ነቢል ያንን ማወቅ የምንችለው እንዴት ነው? መች ነው ለመጨረሻ ጊዜ የተሰበሰቡት?”

ሊመጣ ያለውን ትችት ልቤ እያወቀ እንዲህ ብዬ መለስኩኝ፡- “መሐመድ ካለፈ ከሁለት መቶ እስከ ሁለት መቶ ሃምሳ ዓመታት ያህል በመዘግየት ነው፡፡”

ጉዳዩ ያለቀ ይመስል ክፍሉ ውስጥ የነበሩት ሰዎች ሁሉ በአንድ ጊዜ ጀርባዎቻቸውን ወንበሮቻቸው ላይ አሳረፉ፡፡ በክፍሉ ውስጥ የነበሩት ሰዎች ሁሉ የኔን ሙግት ውድቅ እንዳደረጉት ይሰማኝ ጀመር፡፡

ማይክ እኔን ለማስጨነቅ እየሞከረ እንደሆነ እንዳይመስል ድምፁን የተቻለውን ያህል ለስለስ በማድረግ ተናገረ፡፡ “ነቢል ሁለት መቶ ሃምሳ ዓመት ታሪኮችን ለመጻፍ በእጅጉ

የሰፋ ጊዜ ነው፡፡ ይህን ያህል በሚረዝም ጊዜ ውስጥ የፈጠራ ታሪኮች ከቁጥጥር ውጪ በሆነ ሁኔታ ሰርገው ይገባሉ፡፡ ፈሪዎች እንደ ጀግና ይቆጠራሉ፡፡ ጀግኖች የበለጠ ይጀግናሉ፡፡ የፈጠጡ እውነታዎች ይረሳሉ፡፡ ብዙ ያልተከሰቱ ታሪኮች በየቦታው ይጣፋሉ፡፡”

ማይክ እየተናገረ የነበረው ቢገባኝም በኛ ባሕል ውስጥ ሥልጣን ያለውን ቦታ እያንኳሰሰ ነበር፡፡ ይህንን ደግሞ እያደረገ የነበረው ቅሬታን ሊያስከትል በሚችል መልኩ ነው፡፡ ኢማም ቡኻሪና ኢማም ሙስሊምን የመሳሰሉትን ጥንታውያን ሊቃውንት ሥልጣን ለመገዳደር ማይክ ምን መብት አለው? ወይም ትውፊቶቹን ያስተላለፉት ሀዝራት አይሻና ሀዝራት ዐሊ ታማኞች አይደሉም እያለ ነውን?

ማይክ የቀደሙትን ሙስሊሞች ተዓማኒነት ነው አጣያያቂ እያደረገ የነበረው፡፡ ይህ ደግሞ ሙስሊሞች ለውይይት እንኳ የማያቀርቡት አስደንጋጭ ነገር ነው፡፡ ጥያቄዎቹ በብዙ መልኩ አደናቃፊ ነው የሆኑብኝ፡፡

“ማይክ ለጥያቄ እያቀረብካቸው ያለሃቸውን ሰዎች በፍፁም አታውቃቸውም፡፡ እነዚህ የሰላ ዕውቀትና ንፁህ ልብ የነበራቸው ታላላቅ ስብዕናዎች ናቸው፡፡ ሐዲሳቱ ተዓማኒ የሚሆኑት በግብረ ገብነታቸው ደረጃ ምክንያት ነው፡፡”

“ትክክል ነህ ነቢል” አለ ዳዊት ጣልቃ ገብቶ፡፡ “ማይክ እነዚህን ሰዎች አያውቃቸውም፡፡ ነገር ግን አንተም እንደማታውቃቸው እየነገረህ ነው፡፡ ምንጮቹ በጣም የዘገዩ በመሆናቸው ታሪኮቹን ያስተላለፉ ሰዎች የነበራቸውን የሥነ ምግባር ደረጃ ልንፈትሽ የምንችልበት መንገድ የለም፡፡”

ማይክ ጭንቅላቱን በማወዛወዝ እንዲህ አለ፡- “አይደለም፡፡ የተናገርከው ትክክል ቢሆንም የኔ ነጥብ እርሱ አይደልም፡፡ እኔ እያልኩ ያለሁት በጣም የተከበሩ መልካም ሰዎች ትውፊቶቹን ጽፈውት ቢሆን እንኳ አሁንም ሰዎች ናቸው፡፡ ታሪኮች በተለይም በብዙ ትውልዶች ከምንጮቻቸው ከራቁ በየጊዜው አዳዲስ ነገሮች ይታከሉባቸዋል፡፡ ይህ ደግሞ የታሪኮቹ ባለቤቶች መሐመድ ለቀደሙት ሙስሊሞች እንደነበረው ሁሉ

ከባሕሉ መለያ ጋር የተቆራኙ ስብዕናዎች ከሆኑ የበለጠ እውን ይሆናል፡፡ እነዚህ ታሪኮች ምን ያህል እውነት እንደሆኑ በፍፁም እርግጠኞች መሆን አንችልም፡፡”

ዳዊትና ማይክ ምልልሳቸውን ቀጠሉ፡፡ ከአፍታ በኋላ እኔ የተናገርኳቸውን የተለያዩ ነገሮች እየጠቀሱ አስተያየት የሚሰጡ ድምፆች እየበዙ መጡ፡፡ በክፍሉ ውስጥ የነበሩት ክርስቲያኖች የበለጠ በውይይቱ ውስጥ በንቃት የሚሳተፉ ይመስላል፡፡ በተለይም ስለ መሐመድ የተነገሩ ትንቢቶች ናቸው ብዬ ያነሳኋቸውን ነጥቦች የተገዳደሩት እነርሱ ነበሩ፡፡ በጣም ወሳኝ የሆኑትን የንባብ ክፍሎች ችላ ማለቴን ነገሩኝ፡፡ ለምሳሌ ያህል በዘጸአት ላይ እንደሚመጣ የተነገረው ነቢይ እስራኤላዊ መሆኑን፣ በዮሐንስ ውስጥ የተጠቀሰው አፅናኙ መንፈስ ቅዱስ መባሉን ወዘተ.፡፡

በሌላ ወገን ደግሞ አምላክ የለሾችና ዛክ ከመናገር ይልቅ ሁኔታውን ይታዘቡ ነበር፡፡ ነገር ግን መሐመድና ሳይንስን በተመለከተ ጥያቄዎችን አንስተዋል፡፡ ኢምብሪዮሎጂ ወይም አስትሮኖሚ በመሐመድ ዘመን አይታወቅም የሚሉትን የመሳሰሉ አባባሎች አልተቀበሉም፡፡ እውነቱን ለመናገር ለማለት የፈለጉትን ነገር መረዳት ተስኖኝ ነበር፡፡ የመጀመርያው ጥያቄ አእምሮዬን አስጨንቆት ስለነበር በተከላካይ ቦታ ላይ ነበርኩኝ፤ እናም የተባሉትን ነገሮች ሁሉ በትክክል ማዋሃድ አልቻልኩም ነበር፡፡

በእርግጥ በዚያች ምሽት ስለ ምንም ጉዳይ አመለካከቴን አልለወጥኩም ነበር፡፡ አንድ ነገር ብቻ ነበር ያሳሰበኝ፡፡ እጅግ አሳሳቢ ሆኖብኛል፡፡ የአንድንም ሰው ልብ ወደ እስልምና መሳብ የተሳነኝ ሰው ነኝ፡፡ ዝግጅቴ፣ ጉጉቴም ሆነ ጸሎቴ ከንቱ ሆኖ ቀርቷል፡፡ ዓላማዬን ከግብ ማድረስ አልሆንልህ ብሎኝ በተሸናፊነት ስሜት ወጥቻለሁ፡፡ ተከላካይ የማያስፈልገውን መሐመድን መከላከል ስለምን አስቸጋሪ ሆነብኝ? ያቀረብኳቸው መረጃዎች ስለምን አሳማኝ ሳይሆኑ ቀሩ?

ስለ መሐመድ እውነቱን ለማወቅ የበለጠ ጥናት ማድረግ እንዳለብኝ በዚያች ምሽት ጓደኞቼ አሳምነውኛል፡፡ ይህንን ያደረጉት ደግሞ ስለ መሐመድ ጠባይም ሆነ ተግባር

ቀጥተኛ ነገር በመናገር አልነበረም፡፡ በተከላካይ ቦታ ላይ እንድሆን የሚያስገድደኝን ምንም አሉታዊ ነገር ስለ መሐመድ አልተናገሩም፡፡

“እውነቱን ማወቅ የምንችለው እንዴት ነው?” የሚለውን ጥያቄ መነሻ አድርጌ የመሐመድን ሕይወት ከመጀመርያ ጀምሮ በጥልቀት ለመፈተሽ ወሰንኩኝ፡፡ ወደ ቁርአን ከማለፋችን በፊት ስለ መሐመድ እንደገና እንደምንወያይ በመስማማት ተለያየን፡፡

ነገር ግን በተባባልነው መሠረት ውይይት አላደረግንም፡፡ በግሌ ጥናቶችን በማድረግ ስለ መሐመድ ያወቅሁት እውነታ መርሃ ግብራችንን አዛብቶት ነበር፡፡

ምዕራፍ ሠላሳ ሰባት

# እንከን አልባው ነቢይ

ሙስሊሞች ስለ መሐመድ የሚያውቁት ነገር ከሞላ ጎደል በአፈ ታሪክ የሰሙት ነው፡፡ ከዋናዎቹ ምንጮች እምብዛም የሚገናኝ አይደለም፡፡ ክርስቲያኖች ስለ ክርስቶስ የሚማሩት ከመጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ ቁርአን ግን ስለ መሐመድ የሚናገረው በጣም በጥቂቱ ነው፡፡ በምዕራብም ሆነ በምስራቅ የሚኖሩት ሙስሊሞች ስለ መሐመድ በአፈ ታሪክ የሚነገረውን ነው የሚሰሙት፡፡ በማወቅ ወይም ባለማወቅ የሚጨመሩትን የተዛቡ ታሪኮች መለየት አይችሉም፡፡ ቀዳሚያን የሆኑት የመሐመድ ታሪኮች ሆነ ተብለው እንዲዛቡ መደረጋቸውን ከራሳቸው ከእነዚህ ታሪኮች ሲያዩ በመገረም ይሞላሉ፡፡ እኔንም ያጋጠመኝ ተመሳሳይ ነገር ነበር፡፡

*ሲራት ረሱል አላህ* በሚል ርዕስ በኢብን ኢስሐቅ የተጻፈው የመሐመድ የመጀመርያው ግለ ታሪክ ኢብን ሒሻም በተሰኘ ሌላ ጸሐፊ የታረመ በመሆኑ የመጀመርያው ቅጂ የለንም፡፡ በመቅድሙ ላይ ኢብን ሒሻም የመሐመድን ታሪክ ሆነ ብሎ መቀየሩን ይናገራል፡፡ “ለመነጋገር አሳፋሪ የሆኑ ነገሮች፣ አንዳንድ ሰዎችን ሊያስጨንቁ የሚችሉ ጉዳዮች እና በመምህሬ ተዓማኒ ተደርገው እንደማይቆጠሩ የተነገሩኝ ጉዳዮች እንዲወገዱ አድርጌያለሁ፡፡”[79]

ስለዚህ የመሐመድ ቀዳሚያን ግለ ታሪኮች ከእነርሱ በፊት የነበሩትን ታሪኮች በመቀየር የተዘጋጁ ሲሆኑ የመጀመርያዎቹ ምንጮች ራሳቸው የተቀየሩ ናቸው ማለት ነው፡፡

ኢብን ሒሻም ቀና የሆነ ዓላማ እንደነበረው አልጠራጠርም፤ ነገር ግን የመሐመድን ታሪኮች የበለጠ ተቀባይነት እንዲኖራቸው የማድረግና ተቀባይነት እንደሌላቸው ያሰባቸውን ጉዳዮች የማስወገድ ዓላማ ይዞ ታሪኮቹን መቀየሩ ሊስተባበል አይችልም፡፡ ወላጆቻችንና መምህራኖቻችንም የመሐመድን ታሪኮች ሲነግሩን ተመሳሳይ ነገሮችን ይፈፅማሉ፡፡

ወጣት ሙስሊሞች ስለ መሐመድ የሚማሯቸው ታሪኮች በጥሩ ሁኔታ የተበጠሩ ናቸው፡፡ አጓጊ ገፅታ እንዲኖረው መጥፎ ነገሮች ይወገዳሉ ጥሩ ነገሮች ደግሞ ይጋነናሉ፡፡ ታሪኮቹ ተመራርጠው ስለሚነገሩ መሐመድ እንከን አልባ ነቢይ ሆኖ ይታያል፡፡

የሐዲስና የሲራ አብዛኛው ክፍል ይህንን ለማድረግ ያገለግላል፡፡ ምዕራባዊ ሙስሊም ሰላማዊ የሆነውን የመሐመድን ገፅታ መሳል ቢፈልግ ነውጠኛ የሆኑትን በመተው ሰላማዊ የሆኑትን የሐዲስና የቁርአን ጥቅሶች ይጠቅሳል፡፡ አክራሪ ሙስሊም ተከታዮቹን ለሽብር ማነሳሳት ከፈለገ ሰላማውያኑን በመተው ነውጠኖቹን ይጠቅሳል፡፡[80]

ይህ ዓይነቱ ጥቅሶችን በመምረጥ የመጥቀስ አካሄድ በእጅጉ የተለመደ ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል እስልምና ሰላማዊ መሆኑን ለማሳየት በተደጋጋሚ የሚጠቀሰው ጥቅስ ሱራ 5፡32 ነው፡፡ ቁርአን መግደልን እንደማያበረታታ ለማሳየት ሲ ኤን ኤን፣ ኤም ኤስ ኤን ቢሲ፣ ኤ ቢ ሲን በመሳሰሉት የመገናኛ አውታሮችና ለቁጥር በሚያታክቱ የዳዋ ጽሑፎች ላይ ይጠቀሳል፡፡ ነገር ግን ሰዎች መገደል የለባቸውም የሚለው ትዕዛዝ የተሰጠው ለአይሁዶች መሆኑን የሚናገረው የጥቅሱ ቀዳሚ ክፍል ተቆርጦ እንዲቀር ይደረጋል፡፡ ጥቅሱ ለሙስሊሞች የተነገረ ትምህርት አይደለም፡፡ እስልምናና ሙስሊሞችን የሚመለከተው ጥቅስ ከእርሱ ቀጥሎ የሚገኘው ነው፡፡

*"የእነዚያ አላህንና መልክተኛውን የሚዋጉ በምድርም ላይ ለማጥፋት የሚተጉ ሰዎች ቅጣት መገደል ወይም መሰቀል ወይም እጆቻቸውንና እግሮቻቸውን በማፈራረቅ መቆረጥ ወይም ከአገር መባረር ነው፡፡ ይህ በነሱ በቅርቢቱ ዓለም ውርደት ነው፡፡ በመጨረሻይቱም ለእነርሱ ከባድ ቅጣት አላቸው፡፡" ሱራ 5፡35*

እንዳለመታደል ሆኖ ከአውድ ውጪ በመጥቀስ ሂደት ውስጥ ይህም አንቀፅ ችላ ተብሏል፡፡

እውነቱን ለማግኘት በግሌ ፍለጋ ማድረግ እስከጀመርኩበት ጊዜ ድረስ ይህንን ሁሉ አላውቅም ነበር፡፡ ያሉኝን መረጃዎች ሁሉ ተጠቅሜ የመሐመድን ሕይወት ለማጥናት ወሰንኩኝ፡፡ ጽሑፎቹን አንዴ ካገኘሁ መጠቀም የሚገባኝን የታሪክ ጥናት ሂደት አውቃለሁ፡፡

ዳዊት እንዲረዳኝ ስጠይቀው በደስታ የትብብር እጁን ዘረጋልኝ፡፡ መሐመድ ታላቅ መሪ እንደነበር የሚገልፅ ንግግር እንዲያዘጋጅ ከዚህ ቀደም በኮሌጅ ተጠይቆ ነበር፡፡ ከዚህ በፊት የነበረውን ዕውቀቱን የበለጠ መርማሪ በሆነ ዓይን የማየት ጉጉት አድሮበታል፡፡ ያገኛቸውን መረጃዎች በቅርቡ እንደሚያቀብለኝ ቃል ገባልኝ፡፡

እጄ የገቡትን የሐዲስ መጻሕፍት በሙሉ በማንበብ መጀመር እንዳለብኝ ወሰንኩኝ፡፡ የአባ ቤተ መጻሕፍት ውስጥ ዘጠኙም የሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅፆች ስለሚገኙ እንደተለመደው በሆዴ ተኝቼ ማንበብ ጀመርኩኝ፡፡ ከሞላ ጎደል ሁሉም ሙስሊሞች የታሪክ ይዘቱ ተዓማኒነት ከሁሉም የተሻለ እንደሆነ የሚያምኑበት ስብስብ ነው፡፡ከዚህ በፊት የማውቀውን የመሐመድን ምስል ይሰጠኛል የሚል ግምትነበረኝ፡፡

ከዚህ ቀደም ከሐዲስ ሲጠቀሱ ከመስማት በዘለለ በራሴ አንብቤ አላውቅም ነበር፡፡ አሁን ግን በሕይወቴ ለመጀመርያ ጊዜ በገዛ ራሴ እያነበብኳቸው ነው፡፡ ከዚህ ቀደም የማውቀው የመሐመድ ታሪክ የተጣራ ታሪክ መሆኑን ለማወቅ ብዙ ጊዜ አልወሰደብኝም፡፡ እውነቱን ለመናገር ከሰላሳ ሰከንድ በላይ አልወሰደብኝም ነበር፡፡

የመጀመርያው ቅፅ ሦስተኛው ሐዲስ ላይ መሐመድ በሒራ ዋሻ ውስጥ መገለጥን የተቀበለበትን የተለመደ ሁኔታ ይተርካል፡፡ በልጅነቴ የተማርኳቸውን ነገሮች የሚናገር ቢሆንም ሌሎች ያልሰማኋቸው ነገሮችም ነበሩ፡፡ መሐመድ እንዲያነበንብ መልአኩ ነገረው ከሚለው በተጨማሪ "መልአኩ በኃይል ይዞኝ መቋቋም እስኪያቅተኝ ድረስ ጨመቀኝ" ይላል፡፡ እንዲያነበንብ መልአኩ በጠየቀው ቁጥር መሐመድ መቋቋም

እስኪያቅተው ድረስ “ይጨምቀው” ነበር፡፡ መልአኩን ካገኘው በኋላ መሐመድ “ልቡ በኃይል እየመታ” በፍርሃት ውስጥ ሆኖ ወደ ሚስቱ ተመለሰ፡፡ ከዚህ በኋላ መልአኩ ተመልሶ አልመጣም “መለኮታዊ መገለጡም ለተወሰነ ጊዜ ቆመ፡፡”

የማውቀው የመሐመድ ምስል ይህ አልነበረም፡፡ በጣም ግርድፍ ሲሆን በኩራት ለመናገር የሚያስደፍር አይደለም፡፡ አሁን እንግዲህ ትክክለኛውን የመሐመድን ታሪክ እያነበብኩ ነው፡፡ ያለሁበት ገፅ ታሪኩን የበለጠ ወደሚያብራራ ሌላ ክፍል ያጣቅሳል፡፡ ይህም ቅፅ 9.ιι ነው፡፡ ከአባ የመጽሐፍት መደርደርያ ላይ ቅፅ ዘጠኝን አውርጄ ሐዲስ መቶ አሥራ አንድን ማንበብ ጀመርኩኝ፡፡

ያነበብኩት ሐዲስ ስለ መሐመድ አውቃለሁ ብዬ ያሰብኩትን ቅዠት ከመቅፅበት አስወገደው፡፡ ገብርኤል ሲጎበኘው “የአንገቱ ስሮች በፍርሃትና በሽብር ይገታተሩ ነበር” ይላል፡፡ ገብርኤል ትቶት ለጥቂት ጊዜ በተሰወረ ጊዜ ነቢዩ “በተደጋጋሚ ራሱን ከተራራ ላይ ወርውሮ ለመግደል ሙከራ አድርጎ ነበር፡፡ ራሱን ወርውሮ ለመግደል ወደ ተራራ በወጣ ቁጥር ገብርኤል ተገልጦለት ‹መሐመድ ሆይ! አንተ እውነተኛው የአላህ መልእክተኛ ነህ› ይለው ነበር፡፡ በዚህ ጊዜም ልቡ ይረጋጋ ነበር፡፡”

ከድንጋጤ የተነሳ መላወስ አቃተኝ፡፡ ይህ የሳሂህ ቡኻሪ ሐዲስ መሐመድ ራሱን የመግደል ሙከራ እንዳደረገ እየተናገረ ነውን?

ሐዲሱ አፅንዖት ለመስጠት ይመስል መገለጥ በዘገየ ቁጥር “እንደ ቀድሞ ያደርግ ነበር፤ ነገር ግን የተራራው ጫፍ ላይ ሲደርስ ገብርኤል ይገለጥለት ነበር” ይላል፡፡

የማነበውን ማመን አቅቶኝ መጽሐፉ ላይ አፈጠጥኩኝ፡፡ ጨዋ በሆነ መንገድ ወደ ነቢይነት ከመጠራት በተፃራሪ መሐመድ በአንድ መንፈሳዊ ኃይል ጥቃት ደርሶበት ተሸብሯል፡፡ በዚህም ምክንያት በተደጋጋሚ ራስን የማጥፋት ሙከራ አድርጓል፡፡ ይህ መረጃ የሚገኘው ደግሞ በአንድ ተራ መጽሐፍ ውስጥ ሳይሆን እጅግ ተዓማኒ በሆነው የሳሂህ ቡኻሪ ሐዲስ ውስጥ ነው፡፡

በዚህ ጊዜ ነበር ስለ መሐመድ የነበረኝ መረጃ ጥራዝ ነጠቅ መሆኑ የገባኝ፡፡በእርግጥ እውነተኛው መሐመድ ምናብ አይደለም፡፡ ተጨባች የሆነ ታሪክ ያለው ሰው ነበር፡፡ እንግዲህ ይህ መሐመድ በታሪክ ገፆች ውስጥ የሚገኝ ከሆነ እርሱን ለማወቅ እየጣርኩ ነው፡፡ ነገር ግን ታሪኮቹን አንድ ላይ አቀናጅቼ ለመረዳት በሞከርኩኝ ቁጥር ትልቅ ቦምብ የወደቀብኝ ያህል ይሰማኝ ነበር፡፡

# ከመጋረጃው በስተጀርባ የሚገኝ ሽብር

ከቅፅ አንድ ጀምሬ እስከ ሦስት ድረስ ንባቤን በቀጠልኩኝ ቁጥር ከዚህ ቀደም የማውቃቸውን መልካም ትምህርቶች አገኘሁ፡፡ ሙስሊሞች ሌሎችን መጉዳት የለባቸውም (1.10)፣ ድኾችን መመገብና ለእንግዶች በመልካም ሁኔታ ሰላምታ ማቅረብ ይኖርባቸዋል (1.11)፣ ወርቃማውን ትዕዛዝ እንኳ መከተል እንደሚገባቸው ተጽፏል (1.12)፡፡ ይህ እኔ የማውቀው አፍቃሪና ሰላማዊ እስልምና ለመሆኑ ጥርጥር የለውም፡፡

ነገር ግን ሐዲስ 1.24 ላይ ስደርስ በድንጋጤ አፍ የሚያስከፍት ነገር አየሁኝ፡፡

በሐዲሱ ውስጥ መሐመድ እንዲህ ይላል፡- “ሰዎች ከአላህ በስተቀር ሊመለክ የሚገባው እንደሌለና መሐመድም መልእክተኛው መሆኑን እስኪመሰክሩ ድረስ እንዲሁም ሰላትን በትክክል እስኪሰግዱ ድረስና ግዴታ ምፅዋትንም እስኪሰጡ ድረስ እንድዋጋቸው ታዝዣለሁ… ይህንን ካደረጉ ሕይወታቸውንና ንብረታቸውን ከእኔ ይታደጋሉ፡፡”

ከዓይኔ ነው ወይስ እውነት ነው? መሐመድ ሰዎች እስኪሰልሙ ድረስ እንደሚዋጋቸውና ካልሰለሙ እነርሱን በመግደል ንብረታቸውን እንደሚዘርፍ ነው እየተናገረ ያለው፡፡ ይህ የማይሆን ነገር ነው! ስለ መሐመድ የማውቀውን ነገር ሁሉ ይፃረራ እንዲሁም “በሃይማኖት ማስገደድ የለም” ከሚለው የቁርአን ቃል ጋር ይጣረሳል፡፡

ማመን ስለተሳነኝ ወደሚቀጥለው ሐዲስ በፍጥነት ተሸጋገርኩኝ፡፡ ነገር ግን ሐዲስ 1.25 አንድ ሰው ሙስሊም ከሆነ በኋላ ሊፈፅመው የሚችለው ትልቁ ነገር ቢኖር ጂሃድ

እንደሆነ ይናገራል፡፡ ምን ዓይነት ጂሃድ እንደሆነ ግልፅ ለማድረግ ሳሂህ ቡኻሪ "ሃይማኖታዊ ጦርነት ነው" ይላል፡፡

ይህ ጉዳይ መሸከም ከምችለው በላይ አእምሮዬን አስጨንቆታል፡፡ እጅግ ግራ ገብቶኛል፡፡መላወስ እንኳ ተስኖኛል፡፡ የአባቴ ቤተ መጻሕፍት ውስጥ ሆኜ በሆዴ ከተኛሁበት ሳልንቀሳቀስ የአባቴን እርዳታ ተጣራሁ፡- "አባዬ እፈልግሃለሁ!" አልኩት፡፡ በኛ ባሕል ልጆች አባቶቻቸውን በዚያ ሁኔታ አይጣሩም፤ ነገር ግን አባቴ ድምፄን ሰምቶ እየተጣደፈ መጣ፡፡

ባልተረጋጋ እርምጃ ወደኔ እየመጣ *"ክያ ባት ሃይ፣ ቤይታ?"* ብሎ ጠየቀኝ፡፡ በድምፁ ውስጥ የስጋት ስሜት ይንፀባረቃል፡፡

"ተመልከት፡፡ እነዚህን ምን እንደማደርጋቸው አላውቅም፡፡" መሐመድ ራሱን የመግደል ሙከራ ማድረጉንና ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎች ካልሰለሙ ሊገድላቸው መዛቱን የሚናገሩትን ሁለቱን ሐዲሳት እየጠቆምኩት የተከፈቱትን ሁለቱን መጻሕፍት ሰጠሁት፡፡ አባ ለአፍታ ያህል በፅሞና አጤናቸው፡፡ ድንጋጤውን ለመሸፈን ቢሞክርም ስሜቱን በሚገባ አንብቤያለሁ፡፡ የሳሂህ አል ቡኻሪ መጻሕፍት መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሽፋን ገፆቻቸውን አየት ማድረጉ ለዚህ ሌላው ማረጋገጫ ነበር፡፡

መበጨረሻም ምክር ቢጤ ጣል ሲያደርግ ስጋት ውስጥ መግባቱን ሳይሸሽግ ነበር፡፡ "ነቢል፣ ሊቃውንት ባለመሆናችን ምክንያት የማንረዳቸው አንዳንድ ነገሮች አሉ፡፡ የሊቃውንትን መጽሐፍት ብታነብ በደንብ ይገባሃል፡፡"

አባ አንድ መጽሐፍ ፈልጎ ከመደርደርያው ላይ አወረደ፡፡ ምዕራባዊ ስም ባለው ማርቲን ሊንግስ በተባለ ሰው የተጻፈ ሲሆን ርዕሱ ጎላ ብሎ ይታያል፡፡ *‹መሐመድ፤ በቀዳሚያን ምንጮች ላይ የተመሠረተው ታሪኩ›* ይሰኛል፡፡ አባ ትክክል ይመስላል፤ እኔ ስፈልገው የነበረው በቀዳሚያን ምንጮች ላይ የተመሠረተውን የመሐመድን ታሪክ ነበር፡፡

አባን አመስግኜው መጽሐፉን ከማንበቤ በፊት ስለ ደራሲው ማንነት በድረ ገፅ ላይ ፍለጋ አደረኩኝ፡፡ ማርቲን ሊንግስ እንግሊዛዊ ሲሆን በኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ነበር የተማረው፡፡ የሲ. ኤስ. ሌዊስ ተማሪና የቅርብ ወዳጅም ነበር፡፡ ነገር ግን በእንግሊዝ የፕሮቴስታንት ባሕል ያደገ ቢሆንም የሱፊ እስልምናን ተቀበለ፡፡

ሊንግስ እስልምናን መቀበሉና መጽሐፍ መጻፉ በእስልምናው ዓለም ውስጥ ከፍተኛ ደስታን ያስከተለ ሲሆን በተማሩት ሙስሊሞች ዘንድ ስሙ በተደጋጋሚ የሚነሳ ሆኗል፡፡ እርሱ የጻፈው ሲራህ በምሑራዊ አቀራረቡ ዕውቅና የተሰጠው ሲሆን ለመሐመድ ወደር የለሽ ባሕርይ እንደ ምሳሌ የሚጠቀስ ለመሆን በቅቷል፡፡ እስልምናን በቅንነት ያጠና አስተዋይ ምዕራባዊ እውነትን ለመቀበሉ ማረጋገጫ ሆኖልኝ ነበር፡፡

አዲስ በተፈጠረብኝ የደስታ ስሜት ውስጥ ሆኜ በቀጥታ ስለ መሐመድ የመጀመርያው መገለጥ የሚናገረውን ቦታ ከፈትኩኝ፡፡ ነገር ግን የተሰማኝ የደስታ ስሜት ከመቅፅበት ቀዘቀዘ፡፡ በዚህም መጽሐፍ ውስጥ በድጋሜ ያልተሟላ ምስል አገኘሁ፡፡ ሊንግስ መሐመድ መፍራቱን ጠቅሷል ነገር ግን ራሱን ለመግደል ማሰቡን አልጠቀሰም፡፡ ምንም ነገር አላለም፡፡ ለምን እንዳልጠቀሰም ምክንያት አልሰጠም፡፡ ሊንግስ ጉዳዩን የሚያውቅ አይመስልም፤ ወይም ደግሞ ይህ ሁኔታ መኖሩን እንድናውቅ የፈለገ አይመስልም፡፡ ሙስሊም ያልሆኑትን እንዲያሰልም ወይም እንዲገድል በአላህ ለመሐመድ የሰጠውን ትዕዛዝ አገኝ እንደሆን ፈለኩኝ፤ ነገር ግን እርሱም ተዘሏል፡፡

ሊንግስ ያለጥርጥር ቀዳሚያን የሆኑ ምንጮችን በመጠቀም ነበር ግለ ታሪኩን የጻፈው፤ ነገር ግን እየመረጠ ነበር የጻፈው፡፡ ችግር የሚያስከትሉትን ታሪኮች ከማብራራት ይልቅ በቸልታ አልፏቸዋል፡፡ ይህ በስፋት ተቀባይነት እንዳገኘ የተነገረለት ምሑራዊ የሆነ የመሐመድ ግለ ታሪክ በዚህ ረገድ ወላጆቼ ከነገሩኝ ታሪክ በምንም አይለይም፡፡ እውነቱ ያለው የቱ ጋር ነው? ስለ መሐመድ ሕይወት የተነገሩትን አጠራጣሪ ነገሮች የሚያብራራ ሰው ለምን ጠፋ?

የሊንግስን መጽሐፍ ሳነብ ሳለሁ ስለ እስልምና የማውቀውን ነገር የሚገዳደር ሌላ ነገር አገኘሁ፡፡ ርዕሱ “የጦርነት ወርድና ስፋት” ይላል፡፡ መሐመድ ወደ መዲና ከተሰደደ በኋላ የመካ ነዋሪዎችን አስቀድመው ያጠቁት ሙስሊሞች እንደሆኑ የሚናገር ይመስላል፡፡ በቅዱሱ ወር የመካን ነጋዴዎች ሸምቀው እንዲጠብቁ መሐመድ ስምንት ሰዎችን ላከ፡፡ ወሩ አረቦች እርስ በርሳቸው የማይዋጉበት የተከበረ ወር ቢሆንም ሙስሊሞች አንድ ሰው በመግደል ሁለት ማረኩ፤ ንብረታቸውንም ዘረፉ፡፡

ሊንግስ የሙስሊሞችን ተግባር ለማፅደቅ ብርቱ ጥረት ቢያደርግም የኔን ጭንቀት የሚያረግብ ምክንያት አላቀረበም፡፡ አስተማሪዎቼ በተደጋጋሚ የነገሩኝ ምን ጊዜም ሙስሊሞች ንፁኀን እንደነበሩ ነው፡፡ ከመካውያን ዘንድ ስደት ሲደርስባቸው የነበሩ ተጠቂዎች እንደነበሩ ነው የተማርኩት፡፡ ለዚያ ነበር ወደ መዲና የተሰደዱት፡፡ መሐመድና ሙስሊሞች በነፃነት መኖር ከጀመሩ በኋላ ደም ለማፍሰስ ቀዳሚዎች ሊሆኑ ይችላሉን?

በአዲሱ ጥናቴ መሠረት የተማርኩት ነገር ቢኖር ሙሉውን ታሪክ እንደማላውቅና ከዓላማቸው ጋር ካልሄደ ዘመንኛ ጸሐፊያን ሊነግሩኝ እንደማይፈልጉ ነው፡፡ ሊንግስ የሆነ ነገር ቆርጦ እየተወ ይሆን?

በቀጣዮቹ ጥቂት ሳምንታት እነዚህን ነገሮች በበይነ መረብ ላይ ማጥናት ተያያዝኩኝ፡፡ ጥናቱ ውስጤን እየሸረሸረው ነበር፡፡ ስለ መሐመድ የማላውቃቸውን ብዙ ታሪኮች አገኘሁኝ፡፡ እያንዳንዱ ጉዳይ መሐመድን በሚመረምሩ ወይም በሚከላከሉ ያልታወቁ ሰዎች አጉሊ መነፅር ስር ገብቶ ታየኝ፡፡ ከሁለቱም ወገን የሚወረወሩት የድረ ገፆች ክርክሮች በተቀመሙ ንግግሮች የታጀቡ ነበሩ፡፡

በአንድ ወገን ያሉት ሙስሊም ያልሆኑ ወገኖች ስለ መሐመድ የተጻፉትን የነውጠኝነት ታሪኮች ያብጠለጥላሉ፤ አልፎ አልፎ ለዘብ ያለ አቀራረብ ቢኖራቸውም ድምዳሜያቸው ነቢያችንን ዝቅ የሚያደርግ ነበር፡፡ በምላሹ ደግሞ ሙስሊሞች ታሪኮቹን ውድቅ

በማድረግ ወይም በማብራራት በቅንዓት በተቀጣጠለ ስሜት ሆነው መሐመድን ይከላከላሉ፡፡

የታሪኮችን ሐቀኝነት የሚከዱ ምሳሌዎች ስፍር ቁጥር የላቸውም፡፡ ከእነዚህ መካከል አንዱ መሐመድ የአምስት ልጆች እናት የነበረችውን አስማ ቢንት ማርዋን የተሰኘች ሴት እንዲገድሉ ተዋጊዎቹን እንደላከ የሚናገረው ነው፡፡ ስትገደል ልጇን ጡት እያጠባች ነበር፡፡ ደሟ በልጆቿ ላይ ተረጭቶ ሞተች፡፡ ባደረገው ነገር ህሊናው መወቀሱን ገዳዩ ለመሐመድ በነገረው ጊዜ መሐመድ ምንም ዓይነት ፀፀት አላሳየም ነበር፡፡[81]

ይህ ታሪክ ቀዳሚያን በሆኑት ድርሳናት ውስጥ ቢገኝም በድረ ገፆች ላይ መልስ የሚሰጡት ሙስሊሞች በሳሂህ አል ቡኻሪ ወይም በሌሎች ተዓማኒ ሐዲሳት ውስጥ እንደማይገኙ ይናገራሉ፡፡ ስለዚህ በደፈናው ይክዱታል፡፡ ወሰን በሌለው የመሐመድ ርህራሄ እንደሚያምን ሙስሊም እነዚህ ሰዎች ትክክል እንዲሆኑ ከልቤ ተመኘሁ፡፡

ነገር ግን አልፎ አልፎ ሙስሊሞቹ አንዳንድ አሳቃቂ ታሪኮችን ለማብራራት ቢሞክሩም ልቀበላቸው አልቻልኩም፡፡ ለምሳሌ ያህል ከምሽጎች ጦርነት በኋላ መሐመድ ከአምስት መቶ በላይ የሚሆኑ ጎልማሶችንና ዕድሜያቸው በአሥራዎቹ ውስጥ የሚገኙትን ወንዶች አንገታቸውን አስቀልቶ ነበር፡፡ እነዚህ የበኒ ቁረይዛ አይሁዶች ነበሩ፡፡ ሙስሊሞች ወንዶቹን ከገደሉ በኋላ ሴቶቹንና ህፃናትን ለባርነት ሸጧቸው፤ ንብረታቸውንም ተከፋፈሉ፡፡[82]

ይህ ታሪክ በሐዲስና በሲራ ውስጥ ስለሚገኝ በድረ ገፆች ላይ የሚሟገቱት ሙስሊሞች ሃቀኝነቱን መካድ አልቻሉም፡፡ ከዚህ ይልቅ የመሐመድን ተግባር የሚያፀድቁበትን መንገድ ነበር የሚፈልጉት፡፡ ሙስሊሞች ቃል ኪዳን አፍራሾች በመሆናቸው የሚገባቸውን ቅጣት እንዳገኙ ይናገራሉ፡፡

ነገር ግን እነዚህ ማብራርያዎች አልተዋጡልኝም፡፡ የኔ ነብይ አድርጌ የተቀበልኩት እኔ የማውቀው መሃሪውና ደጉ መሐመድ ጎልማሶችና ወንድ ልጆች እንዲታረዱ አያዝም፡፡ እርሱ የሰላምና የምህረት ነቢይ ነው፡፡ ሴቶችንና ህፃናትንም ለባርነት አይሸጥም፡፡ እርሱ

የሴቶችና የህፃናት መብት ተሟጋች ነው፡፡ ስለ መሐመድ የሚያወሩ ብዙ የነውጠኝነት ታሪኮችን አገኘሁ፡፡ የኢንተርኔት ሙስሊሞች ሲያደርጉት እንደነበረው እኔም ሆነ ብዬ ታሪኮቹን ለመካድ ሞከርኩኝ ነገር ግን ህሊናዬ ይወቅሰኝ ነበር፡፡ ስንቱን ክጄ ስንቱን እጨርሰዋለሁ? በዚህ ሁኔታ እስከ መቼ ድረስ ነው መቀጠል የምችለው?

# መሐመድ ረሱል አላህ?

ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ዳዊት ስለ መሐመድ ያደረገውን ጥናት ይዞልኝ መጣ፡፡ ጥናቱ እጅግ ጥልቅ ነበር፡፡

“መሐመድ የፈጣሪ ነቢይ ነውን?” የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ተነሳን፡፡ *ሲራት ረሱል አላህ፣* ሳሂህ አል ቡኻሪና ሳሂህ ሙስሊም የተሰኙ ድርሳናትን በመዳሰስ ያገኛቸው ብዙ መረጃዎች የመሐመድን ነቢይነት እንደሚፃረሩ ሙግት አቀረበ፡፡ ያዘጋጃንም ጽሑፍ በአንድ ጠርዞ ሰጠኝ፡፡ የጥናቱ ርዕስ “በቅንነት እውነትን የሚፈልግ ሰው ከመሐመድ ሕይወትና ባሕርይ በመነሳት እውነተኛ የፈጣሪ ነቢይ መሆኑን ሊደመድም ይችላልን?” የሚል ነበር፡፡

እርሱ ባዘጋጀው ጥራዝ ውስጥ ከዚህ በፊት ያላየኋቸው ብዙ ነገሮች ነበሩ፡፡ አንዳንዶቹ እኔን ካሳሰቡኝ በላይ ነበር ያሳሰቡት፡፡ ለምሳሌ ያህል በእስልምና አንድ ሙስሊም ወንድ እስከ አራት ሚስቶች ብቻ እንዲኖረው የተፈቀደ ሲሆን መሐመድ በአንድ ወቅት እስከ ሰባት ሚስቶች ነበሩት፡፡ ነገር ግን አላህ ለመሐመድ የፈለገውን ያህል እንዲያገባ በቁርአን ውስጥ ስለፈቀደለት ችግር እንደሌለው ነገርኩት፡፡[83] እርሱም “ይህ ትንሽም ቢሆን ጥርጣሬን የሚያጭር መስሎ አይሰማህም?” በማለት ጠየቀኝ፡፡ ጥርጣሬን እንደማያጭር በደፈናው መለስኩለት፡፡

መሐመድ ከአይሻ ጋር የፈፀመውን ጋብቻ በተመለከተ እንዲሁ ዳዊት ተቃውሞውን አቀረበ፡፡ በብዙ ሐዲሳት መሠረት መሐመድ ሲያገባት ስድስት ዓመቷ ነበር፡፡ ጋብቻውን

ደግሞ ሲያሟላ ዘጠኝ ዓመቷ ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ ዕድሜው ሃምሳ ሁለት ነበር፡፡[84] በእርሱ ምሳሌነት ምክንያት በሙስሊሙ ዓለም ውስጥ የሚገኙ ሴቶች ለደህንነታቸው አደገኛ በሆነ ዕድሜ ላይ ለማግባት እየተገደዱ መሆናቸውን ገለፀ፡፡[85] ነገር ግን የኔ ጀማት እነዚህ ሐዲሳት ትክክል እንዳልሆኑ ስለሚያስተምር ጉዳዩ እምብዛም አላስጨነቀኝም፡፡

ዳዊት የመሐመድን ነቢይነት የሚቃወሙ ትውፊቶችን አንድ በአንድ አቀረበልኝ፡፡ ክብደታቸው ደግሞ ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚጨምር ነበር፡፡ መሐመድ በመርዝ ጉዳት ደርሶበታል፤[86] በሞቱ አልጋ ላይ ሆኖ እያጣጣረ በመርዙ ምክንያት እየሞተ እንደሆነ ተሰምቶት ነበር፤[87] አስማት ተደርጎበት ነበር፤[88] ኋላ ላይ ከሰይጣን እንደሆኑ የተናገራቸውን መገለጦች አምጥቶ ነበር፤[89] ለገንዘብ ብሎ ሰዎችን አሰቃይቷል፤[90] ባልታጠቁ አይሁዶች ላይ ጥቃት ፈፅሟል፤[91] የማደጎ ልጁ ሚስት የሆነችውን ዘይነብን ለማግባት ሲል ትዳሯን አፍርሷል፤[92] ሰዎች የግመል ሽንት እንዲጠጡ አዟል፤[93] ይህ ዝርዝር ማቆምያ የለውም፡፡

መጀመርያ ለእነዚህ ሐዲሳት አንድ በአንድ መልስ ለመስጠት ሞክሬ ነበር፤ ነገር ግን እንደርሱ ማድረጌን በቀጠልኩኝ ቁጥር ሚዛናዊ አለመሆኔ እየገባኝ መጣ፡፡ የምወደውን ነቢይ የመሐመድን ታሪክ የሚያጎድፉ ሐዲሳትን እንዴት ማጣጣል እንደምችልና ስብዕናውን የሚያልቁ ሐዲሳትን እንዴት ማፅደቅ እንደምችል ለማወቅ ዕውቅ በሆኑ ሊቃውንት ስለ ሐዲስ ሥነ-ጥናት የሚያስተምሩ መጻሕፍትን ማጥናት፤ ምሑራዊ የሆኑ ትምህርቶችን መስማት፤ የተለያዩ ማብራርያዎችን ማንበብ ጀመርኩኝ፡፡ ነገርግን ሁለቱን የማላቅቅበትን መቁረጫ ማግኘት ተሳነኝ፡፡ “መሐመድ የግድ ነቢይ መሆን ስላለበት እነዚህ ታሪኮች ውሸት መሆን አለባቸው” ከሚለው ጭፍን አስተሳሰብ ውጪ ምንም ነገር ላገኝ አልቻልኩኝም፡፡

ነገር ግን ከተከበሩ ምንጮች የተገኙ ጉልቁ መሣፍርት የሌላቸው ታሪኮች ነበሩ፡፡

ጊዜ በሄደ ቁጥር ትክክለኛነታቸውን የካድኳቸው ሐዲሳት ከልክ አለፉ፡፡ ማድረግ የምችለው እርሱን ነበር፡፡ እንደርሱ ካላደረኩኝ እሰጥማለሁ፡፡ የግለ ታሪክ ጸሐፍትና አስተማሪዎቼ ለምን እንደዚህ ዓይነት ነገር እንደሚፈፅሙ እየገባኝ መጣ፡፡

ወደ መቶ የሚጠጉ እንደዚህ ዓይነት ታሪኮችን መካዴን ስረዳ መራራውን ሃቅ ለመቀበል ተገደድኩኝ፤ እነዚህ ታሪኮች የተገኙት የእስልምናን ታሪካዊ መሠረት ከገነቡት ምንጮች ነው፡፡ መሠረቱ ሳይናጋ ስንቱን መካድ እችል ይሆን?

በሌላ አነጋገር፤ የትውፊቶቹን ትክክለኛነት መካዴን ከቀጠልኩኝ ሲጀመር እርሱን ነቢይ ብዬ የምጠራበት መሠረት የለኝም ማለት ነው፡፡ መሐመድን ሊዋጅ የሚችል አንድ ነገር ከሌለ፤ ከታሪክ ያለፈ አንድ ነገር ከሌለ በስተቀር ሸሃዳን የምመሰክርበት ምንም ዓይነት መንገድ አይኖረኝም፡፡

ከዚህ አጣብቂኝ ለመውጣት መንገዱ አንድ ብቻ ነው፤ ቁርአን፡፡

*ዶ/ር ዴቪድ ውድ ከፎርድሃም ዩኒቨርሲቲ በፍልስፍና ፒ ኤች ዲ ያላቸው ሲሆን የአክትስ 17 ዓቀበተ እምነት ዳይሬክተርና ‹የኢየሱስ ወይስ መሐመድ› የቴሌቪዥን ፕሮግራም አዘጋጅ ናቸው፡፡ ስለ ታሪካዊው መሐመድ የጻፉትን የሊቅ አስተዋፅዖ ለማንበብ contributions.NabeelQureshi.com ይጎብኙ፡፡*

ክፍል ፫

# የቁርአን ቅድስና

*ስለ ቁርአን እንደማውቃቸው ያሰብኳቸው ነገሮች ብዙዎቹ እውነት አይደሉም፡፡ እውን ያንተ መጽሐፍ ነውን?*

# የቁርአን ሙግት

እስኪ ስለ ፈጣሪ ሚስጢርና ጥበብ፣ ስለ ኃይሉ ታላቅነት፣ ስለ ፍፅምናው፣ ስለ መለኮታዊ ተስፋዎቹና ትንቢቶቹ ለማሰብ ሞክሩ፡፡ እነዚህ ሁሉ ቁሳዊ በሆነ መጽሐፍ ገፆች ውስጥ ሰፍረው መጽሐፉን የፈጣሪ ባሕሪ ተካፋይ ማድረጋቸውን ስታስቡ ሙስሊሞች ለምን ለቁርአን ከፍተኛ ክብር እንደሚሰጡ ትረዳላችሁ፡፡

ቁርአን ለእስልምና ልክ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሆነ መታሰብ የለበትም፡፡ እንደርሱ አይደለም፡፡ ለሙስሊሞች ቁርአን ወደ አላህ ተሠግዎ የቀረበ ነገር ነው፡፡ የእስልምናንም እውነተኛነት ለመግለጥ የሚያቀርቡት ማስረጃ ነው፡፡ በክርስትና ውስጥ የሚገኝ የተሻለ ንፅፅር የኢየሱስ ተሠግዎና ትንሣኤ ነው፡፡ ቁርአን ለእስልምና ሥነ መለኮት የዚያን ያህል ማዕከላዊ ነገር ነው፡፡[94]

የእምነቴ መሠረት ይህ ነው፡፡ እንደ ሁለተኛ የዕምነቴ አዕማድ የምቆጥረው መሐመድ የትክክለኛነቱ ማረጋገጫ በቁርአን ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ይህንን ቅዱስ መጽሐፍ መመርመር ስጀመር በፍርሃትና በአክብሮት ነበር፡፡

የእስልምና እውነተኛነት፣ መሐመድ የቆመለት ዓላማ ሁሉና የኔም ሕይወት ጭምር የተመሠረተው በቁርአን መለኮታዊ መገለጥ ላይ ነው፡፡

የመሐመድን ሕይወት መመርመር ስጀምር እንደነበረው ሁሉ ቁርአንም ምርመራውን ማለፍ ይችላል የሚል ግምት ነበረኝ፡፡ ከኡማ አባላት መካከል አንድም ሰው መለኮታዊ መገለጥ መሆኑን የሚጠራጠር የለም፡፡ ቁርአን ፍፁምና ተዓምራዊ መሆኑን

ምዕራባውያን ሊቃውንትን ጨምሮ ማንም አጠያያቂ ማድረግ እንደማይችል እርግጠኞች ነን፡፡ ሙግታችን እጅግ ጠንካራ መሆኑን እናምናለን፡፡

ስለ ቁርአን መለኮታዊነት ጎልቶ የሚነገረው ሙግት ማንም እርሱን የሚመስል ጽሑፍ መፍጠር አለመቻሉ፣ ማለትም አስደናቂ አጻጻፉ ነው፡፡ “ማንም የእርሱን ጥዑመ ልሳን መፍጠር አይችልም” እንላለን፡፡ ሙግታችን ከራሱ ከቁርአን የተገኘ ነው፡፡ በመሐመድ ዘመን የነበሩት ሰዎች ቁርአን የራሱ ፈጠራ መሆኑን በመናገር ሲከሱት ተጠራጣሪዎች እርሱን የሚመስል ጽሑፍ እንዲፈጥሩ በተደጋጋሚ ሲጠይቃቸው እናያለን፡፡[95] ከሰዎችም ከጂኒዎችም ጋር በማበር ቢሞክሩ እንኳ አይሳካላቸውም፡፡

የቁርአን ግድድር ይህንን ይመስላል፤ ማንም ሰው ከእርሱ ጋር ሊፎካከር የሚችል ጽሑፍ መጻፍ አይችልም፡፡

ከልጅነታችን ጀምሮ እነዚህን ተግዳሮቶች በቁርአን ውስጥ እያነበብን እንደ ማደጋችን መጠን እንዲሁም የምንከተለው ንፅረተ ዓለም ቁርአን እጅግ ውብ መሆኑን በሚሰብኩ መምህራን የተቃኘ እንደመሆኑ መጠን እኔና እኔን መሰል ሙስሊሞች ቁርአን ተፎካካሪ ሊፈጠርለት እንደማይችል ከልክ በላይ በራስ በመተማመን እንናገራለን፡፡

ለቁርአን ግድድር መልስ የሚሰጥ *አል ፉርቃን አል ሀቅ* በሚል ርዕስ የተጻፈውን መጽሐፍ ሳገኝ ያደረብኝን መደመም ማሰብ ትችላላችሁ፡፡ “እውነተኛ መለኪያ” ተብሎ የተተረጎመው ይህ መጽሐፍ በቁርአናዊ አጻጻፍ የክርስትናን ትምህርት የሚያቀርብ ነው፡፡[96] ይህ መጽሐፍ የቁርአንን አጻጻፍ ተከትሎ የተጻፈ ከመሆኑ የተነሳ አንዳንዶች በአደባባይ ሲያነቡት ቁርአንን እራሱን በማንበባቸው ምክንያት አረብ ሙስሊሞች እንኳ ሲያመሰግኗቸው ተሰምቷል፡፡

ቁርአን ስለ ራሱ ያቀረበው ሙግት ማንም እርሱን የሚመስል መጽሐፍ መፍጠር አለመቻሉን ነው፡፡ ነገር ግን ይህንን ተግዳሮት የሚመልስ መጽሐፍ ተገኝቷል፡፡ ይህ ዜና ለኔ አስደንጋጭ ነበር፡፡

*አል ፉርቃን አል ሀቅ* የሚለው መጽሐፍ አደገኛ መሆኑን ለመናገር እኔ ብቸኛ ሰው አይደለሁም፡፡ ቢያንስ አንዲት አገር ያንን አድርጋለች "ለደህንነታችን ስንል .... ይህንን መጽሐፍ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት የተከለከለ ነው .. ይህ ደግሞ የትኛውንም የመጽሐፉን ክፍል፣ ዳግም ህትመት ወይም ትርጉም እንዲሁም በውስጡ የሚገኘውን የትኛውንም ክፍል ያካተተ የትኛውንም ጽሑፍ ያጠቃልላል፡፡"[97]

በኔ አመለካከት ማንም ይህንን የቁርአን ተግዳሮት መመለስ አይችልም ነበር፡፡ ይህንን ካየሁ በኋላ ግን ይህ ተግዳሮት እኔ ካሰብኩት የተለየ ትርጉም እንዳለሁ ደመደምኩኝ፡፡ አስቸጋሪውን ሁኔታ በማለፍ ሌሎች ሙግቶችን ማሰባሰብ ጀመርኩኝ፡፡

ሙስሊም ዓቃቤ እምነታውያን ቁርአን ስለ ራሱ መለኮታዊነት ባቀረበው መከላከያ ብቻ አይወሰኑም፡፡ በተደጋጋሚ እንደ ማስረጃ የሚጠቅሷቸው አራቱ ሙግቶች የሚከተሉት ናቸው፡- የተፈፀሙ ትንቢቶች፣ የሒሳብ ቁጥር ድግግሞሾች፣ ሳይንሳዊ እውነታዎችና የጽሑፉ አለመለወጥ፡፡ እያንዳንዱን በየተራ ለመፈተሽ ተነሳሁኝ፡፡ ዓላማዬ ተዓማኒነታቸውን መፈተሽ ሳይሆን ለእስልምና አዎንታዊ የሆነ ማስረጃ በማቅረብ የእስልምና እውነትነት እኔን ጨምሮ ለኡማ በሙሉ ግልፅ የሆነውን ያህል ለጠያቂም ግልፅ እንዲሆን ማድረግ ነበር፡፡

የመጀመርያዎቹ ሁለቱ ሙግቶች ፈጥነው ወደቁ፡፡ በቁርአን ውስጥ አሳማኝ ትንቢት የለም፡፡ አንዳንድ ትንቢት የሚመስሉ ጥቅሶች ቢኖሩም ቁርአን ግን እንደ ትንቢት አያቀርባቸውም፡፡ ዝርዝር ጉዳዮችን ስለማያቀርቡ ጠንካራና ተጨባጭ የሆነ ሙግት ሊፈጥሩልኝ አይችሉም፡፡

በተመሳሳይ በቁርአን ውስጥ የሚገኙት የሒሳብ ስሌቶች መለኮታዊ መሆኑን ያሳያሉ የሚል እምነት የለኝም፡፡ አብዛኞቹ መረጃዎች ትርጉማቸው የተዛባና ከልክ በላይ የተለጠጡ ናቸው፡፡ ሌሎቹ ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲሁም በኤድጋር አለን ፖ ልበወለድ ውስጥና አልፎ ተርፎም በድረ ገፆች ላይ ልናገኛቸው የምንችላቸው ዓይነት ናቸው፡፡

አስደሳቹ ነገር እነዚህ ሁለቱ ሙግቶች የኔ ንፅረተ ዓለም መሠረታዊ ሙግቶች እንደሆኑ በመማር አለማደጌ ነው፡፡ የተቀሩት ሁለቱ ሙግቶች መሠረታውያን ናቸው፡፡ ያለ መለኮታዊ መገለጥ መሐመድ ሊያውቃቸው የማይችላቸው ዘመን ተሻጋሪ ሳይንሳዊ እውነታዎች በቁርአን ውስጥ መኖራቸውን ከልጅነቴ ጀምሮ ስማር ነበር፡፡ እነዚህ ሳይንሳዊ እውነታዎች የቁርአን ደራሲ ራሱ አላህ መሆኑን ያረጋግጣሉ፡፡

ከሳይንሳዊ ሙግቱም በላይ ሙስሊሞች ቁርአን ሳይለዋወጥ ተጠብቆ መቆየቱን በፅኑ ያምናሉ፡፡ ሙስሊሞች አንድ ነቁጥ እንኳን እንዳልተለወጠ ያምናሉ፡፡ አላህ ሱራ 15፡9 ላይ ቁርአንን እንደሚጠብቅ ቃል ገብቷል፡፡ ተጠብቆ መቆየቱ አላህ ለቃል ኪዳኑ ታማኝ መሆኑን እንደሚያሳይ ሙስሊሞች ያምናሉ፡፡

የሳይንስ ሙግት በተለይም ደግሞ ቁርአን ያለምንም እንከን ተጠብቆ መቆየቱ የእምነቴ የማዕዘን ድንጋይ ነው፡፡ የእምነቴ መሠረት  ለሆነው የእስልምና ሙግት ጠንካራ ማረጋገጫ የሚሆኑ ፍሬዎችን ማፍራት እንደሚችሉ ተስፋ በማድረግ እነዚህን የማዕዘን ድንጋዮች ለመፈተሽ በአጭር ታጥቄ ተነሳሁኝ፡፡

“እነዚህ የማዕዘን ድንጋዮች ውድቅ ከሆኑ ምን ይፈጠር ይሆን?” የሚለው ጥያቄ እንዳያስጨንቀኝ የተቻለኝን ጥረት አድርጌያለሁ፡፡ ጥያቄዎቹ ሲበረቱ ከመጨነቅ ይልቅ በአላህ ፊት ተንበርክኬ ለእስልምና ታማኝ እንድሆን እንዲረዳኝ እጸልይ ነበር፡፡ የአርብ ስብከቶችን በመምራትና የአቂዳ ትምህርቶችን በማስተማር ይበልጡኑ ወደ እስልምና እምነቴ ተጠጋሁ፡፡ ይህንን በማድረግም በሙስሊሞች መካከል የተሻለ ሆኖ በመገኘት በውስጤ የተፈጠረብኝን ግጭት ለመሸፈን እሞክር ነበር፡፡

መሠረቱ ከተናጋ ሁሉም ነገር ይፈረካከሳል፡፡ በውስጤ ሲደረግ የነበረው ትግል ያንን አመላካች ነበር፡፡

# ቁርአን፣ ሳይንስና አስተምህሮተ ቡካይሌ

ከመሐመድ ዘመን ጀምሮ ዳዋ ሙስሊሞችን ወደ ፊት የሚያራምድ ኃይል ሆኖ የቆየ ቢሆንም ሃያኛው ክፍለ ዘመን ውስጥ የእስልምናን የማሳመን አቅም ያቀጣጠለ አንድ ነዳጅ ተገኘ፡፡ እርሱም ዘመናዊው ሳይንስ ነበር፡፡ ይበልጥ አስገራሚ የሆነው ነገር ደግሞ ይህ አከራካሪ ግኝት የተፈጠረው ሃይማኖተኛ ባልሆነ የፈረንሳይ ሰው መሆኑ ነው፡፡

መውሪስ ቡካይሌ በሙያው ኃኪም ሲሆን የሳውዲ አረብያ ንጉሥ የግል ኃኪም ነበር፡፡ ይህ ሰው በ1976 ዓ.ም.*መጽሐፍ ቅዱስ፣ ቁርአን እና ሳይንስ* በሚል ርዕስ መጽሐፍ በማሳተም እድገቱ እየጨመረ ለመጣ እስላማዊ ዓቀበተ እምነት መሠረት ጣለ፡፡ ይህ ከታብ መጽሐፍ ቅደስ በሳይንሳዊ ስህተቶች የተሞላና ቁርአን ደግሞ በተፃራሪው ተዓምራዊ በሆነ ሁኔታ ቅድመ ዕውቀቶችን በውስጡ የያዘ እንዲሁም ከስህተት የጸዳ መሆኑን ይሞግታል፡፡ ቁርአን ሳይንሳዊ ትንቢያዎችን በውስጡ የያዘ በመሆኑ ምክንያት የፈጣሪ ቃል መሆን አለበት በማለት ይደመድማል፡፡

ይህ ጅምር ሥራ ሙስሊሞችን በከፍተኛ ሁኔታ ለስብከተ እስልምና አነቃቅቷቸዋል፡፡ እንደ ማርቲን ሊንግስ ሁሉ ምዕራባዊ ምሑር ማስረጃዎችን ካጤነ በኋላ ከእስልምና ጋር መወገኑን የዳዋ ቅንዓት ያላቸው ሙስሊሞች በከፍተኛ ሁኔታ አራግበውታል፡፡ በሂደቱ ውስጥ ቡካይሌ ደጋግሞ መጽሐፍ ቅደስን በማጣጣሉ የተነሳ እነዚህ ወገኖች ከፍተኛ እርካታ እንዲሰማቸው አድርጓል፡፡

ቁርአን ተዓምራዊ በሆነ ሁኔታ ሳይንሳዊ ግኝቶችን አስቀድሞ ተንብዮዋል የሚለው ስብከት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ከመድረሱ የተነሳ ለዘርፉ**ቡካይሌኢዝም** የሚል ስም ተበጅቶለታል፡፡

ከእንደነዚህ ዓይነት ሙግቶች መካከል አንዱ የሰዎችን ሥነ ተዋልዶ የሚመለከት ነው፡፡ ቡካይሌ እንዲህ ይላል፡- "ቁርአን በሽል እድገት ውስጥ የሚገኙትን ደረጃዎች ያስቀመጠበት መንገድ ዛሬ ከምናውቀው ጋር በትክክል ይገጥማል፡፡ ቁርአን ከዘመናዊ ሳይንስ ትችትን የሚያስከትል ምንም ነገር በውስጡ አይገኝም፡፡"[98] የዚህ ንግግር ምልከታ ግልፅ ነው፡፡ ቁርአን በተገለጠ ጊዜ ስለ ሽል የሚያውቀው ፈጣሪ ብቻ ነበር፡፡ ስለዚህ የቁርአን ደራሲ ራሱ ፈጣሪ መሆን አለበት፡፡

**ቢካይሌኢዝም፡** ቁርአን በውስጡ ተዓምራዊ የሳይንስ ትንቢያዎች እንደሚገኙ በማሳየት መለኮታዊ መሆኑን የማስረዳት ሥልት

መጽሐፉ በታተመ በጥቂት ዓመታት ውስጥ የቡካይሌ ሙግት ራስን በመከላከል አስተሳሰብ ውስጥ በሚኖረው እኔ በተወለድኩበት የሙስሊሙ ዓለም ውስጥ ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ ናኘ፡፡ ምግብ ስንበላ፣ እንግዳ ሲመጣብንም ይሁን በጀማት መሪ የተጻፈ መጽሐፍ ስናነብ የቡካይሌ ሙግቶች የሃይማኖታዊ ውይይቶቻችን ማጣፈጫዎች ሆኑ፡፡ በሙግቶቹ ጥፍጥናና ጥልቀት እንመሰጥ ነበር፡፡ እንደ ሌሎቹ እስላማዊ ትምህርቶች ሁሉ ቡካይሌኢዝም ያለ ምንም ጥያቄ በሙስሊሞች ሁሉ ዘንድ ተቀባይነት ማግኘቱ የባሕላችንን ባሕርይ ያሳያል፡፡

ሳይንስ ቁርአን ምንጩ ከመለኮት መሆኑን እንደሚያረጋግጥ እርግጠኞች ሆነናል፡፡ ይህ ሙስሊሞች በኩራት የሚናገሩት ቢሆንም የመረመረ ሰው ግን የለም፡፡

በመጨረሻም እኔ ስፈትሸው ሌላኛው የኔ ንፅረተ ዓለም መሠረት ተናጋ፡፡ የሃይማኖትና የሕክምና ተማሪ እንደመሆኔ መጠን የቡካይሌን ትምህርት መፈተሽ ጀመርኩኝ፡፡ በሥነ ፍታቴው፣ በአመክንዮውና በምሑራዊ ጥናቱ ውስጥም ብዙ ችግሮችን አገኘሁበት፡፡ የሰዎችን ሥነ ተዋልዶ የተመለከተውን ጥናቱን እንኳን ብንመለከት አብዛኞቹ ምሑራን

ቢያንስ ከምዕራባውያን ዕይታ አኳያ ለቡካይሌ ከልክ ያለፈ ውዳሴ ቅንጣት ቦታ አይሰጡም፡፡ ቅጥ አልባ ከሆነው ውዳሴው ባሻገር ቡካይሌ እንደ ተዓምራት በቆጠረው የቁርአን ጥቅስ ውስጥ ሳይንሳዊ ችግሮች ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ችግሮች አንዳንዶቹ ለጤና ባለሙያዎች ግልፅ ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ ለማንኛውም ሰው በግልፅ የሚታዩ ናቸው፡፡

ለምሰሌ ያህል 23፡13-14 እንዲህ ይነበባል፡- "ከዚያም በተጠበቀ መርጊያ ውስጥ የፍቶት ጠብታ አደረግነው፡፡ ከዚያም ጠብታዋን (በአርባ ቀን) የረጋ ደም አድርገን ፈጠርን፤ የረጋውን ደም ቁራጭ ሥጋ አድርገን ፈጠርን፤ ቁራጭዋንም ሥጋ አጥንቶች አድርገን ፈጠርን፤ አጥንቶቹቹም ሥጋን አለበስናቸው፤ ከዚያም (ነፍስን በመዝራት) ሌላ ፍጥረት አድርገን አስገኘነው፡፡"

ሥነ ሕይወትን የሚያጠና ሰው ይህንን ጥቅስ ሚዛን የሚደፋ ሆኖ አያገኘውም፡፡ ቡካይሌ እንኳ ትንተናውን ሲጀምር ይህንን ሃቅ በመረዳት እንዲህ በማለት ይናዘዛል፡- "ይህ ዘርፉን በሚያጠኑ ሊቃውንት ዘንድ ፈፅሞ ተቀባይነት የለውም፡፡"[99] ነገር ግን ችግሩ ቁርአን በሰባተኛው ክፍለዘመን ለመጠቀም የተገደደው ቃል መሆኑን ይናገራል፡፡ ነገር ግን "ዩተረስ" የሚለውን የዘመናዊ ሳይንስ ቃል "በተጠበቀ መርጊያ" በሚለው ቦተ ብንተካ ችግሩ ይወገዳል፡፡[100] ቁርአንን አመቺ በሆነ መንገድ ሁሉ እየተረጎመ እንዳደገ ሙስሊም የቡካይሌን ሐሳብ እጋራለሁ፡፡ እንደ ኅክምና ተማሪ ግን ቃላትን የፈለገ ያህል ብንተካ የዚህ ጥቅስ አንዱ ችግር ፈፅሞ ሊቀረፍ እንደማይችል ተገንዝቤያለሁ፡፡ ጥቅሱ የሽልን የዕድገት ቅደም ተከተል የሚናገር ቢሆንም ቅደም ተከተሉ ግን ትክክል አይደለም፡፡ ሽል መጀመርያ አጥንት ሆኖ ከዚያ በሥጋ አይሸፈንም፡፡ ሜሶደርም የተሰኘው የሽል ክፍል ነው በአንድ ጊዜ ሥጋም አጥንትም ወደመሆን የሚያድገው፡፡

ለዚህ የተሰጡትን ምላሾች መርመሬያለሁ፡፡ ብዙዎቹ ደካማ የሆነ ተቃውሞ መሆኑን ቢናገሩም ሙስሊም እያለሁ እንኳ ምላሹን አልተቀበልከትም ነበር፡፡ ቡካይሌ በጥቅሱ ውስጥ የሚገኙት ቅደም ተከተሎች ተዓምራዊ በሆነ ሁኔታ ትክክል መሆናቸውን ለማስረዳት ቢሞክርም ቅደም ተከተሉ ግን ትክክል አይደለም፡፡ ይህ እንደ ቀላል

የሚታይ አይደለም፡፡ ቡካይሌ ጥቅሱን በስፋት ለመተንተን ቢሞክርም ነገር ግን ችግሩን አለባብሶ አልፎታል፡፡

ግልፅ በሆነው የጥቅሱ ክፍል ውስጥ የሚገኘውን ስህተት መረዳት ቀላል ነው፤ ነገር ግን ብቸኛው ችግር አይደለም፡፡ የጥቅሱ የመጀመርያው ክፍል የአረብኛውን የተሳሳተ ቃል በሳይንሳዊ ቃል እንድንተካ ያስገድደናል፡፡ ስለዚህ የመጀመርያውን ችግር ብቻ በመፍታት ሁለተኛውን በቸልታ የምናልፈው ከሆነ ሳይንሳዊ ተዓምር ሊባል የሚችል ምን ነገር ይኖራል?ይህ ጥቅስ ቁርአን ግልጠተ መለኮት መሆኑን እንደማያስረዳ ተገንዝቤያለሁ፡፡ ከዚህ በተፃራሪ ይህንን ጥቅስ ለማስረዳት መጀመርያ ቁርአን ግልጠተ መለኮት መሆኑን መቀበል ሊያስፈልገን ነው፡፡

ከዚሁ ከሥነ ተዋልዶ ጋር በተያያዘ ቁርአንን ሳጠና ተጨማሪ ችግሮችን አግኝቼአለሁ፡፡ ሱራ 86፡6-7 የወንድ ዘር “ከጀርባና ከእርግብግብቶች” መካከል እንደሚወጣ ይናገራል፡፡

እንዲህ ያለ ግልፅ ቅጥፈት በቁረአን ውስጥ ይገኛል የሚል እምነት ስላልነበረኝ መልሶችን በኢንተርኔት ላይ መፈለግ ጀመርኩኝ፡፡ አሁንም ጥቅሱን ለማብራራት ተመሳሳይ ዘዴ አጋጠመኝ፤ ቃላትን ከእንደገና መተርጎምና ችግሮችን አለባብሶ ማለፍ፡፡የቁርአንን ሳይንሳዊ ተዓምራት ለማወጅም ሆነ ሳይንሳዊ ስህተቶችን ለማብራራት ግልፅ የሆኑትን የቁርአን ቃላት እንደገና በመተርጎም የማይሉትን ነገር ማስባልና ችግሮችን አለባብሶ ማለፍ መደበኛ አካሄድ መሆኑ ተከሰተልኝ፡፡

ይህ አካሄድ ከተገለፀልኝ በኋላ ቡካይሌኢዝም ልክ የመሐመድን ሕይወት እንደማጥናት መሆኑ ገባኝ፡፡ እንደ አንድ ሙስሊም ቃላትን በአዲስ መንገድ በመተርጎምና አቋሜን የሚደግፉ ጉዳዮችን በማጉላት እስላማዊ እምነቴን መከላከል እችል ነበር፡፡ ነገር ግን ነፃ እንደሆነ መርማሪ ጽሑፉን እንዳለ በማንበብ ትርጉም ያለው የሙግት ሐሳብ ባቀርብ በቁርአን ውስጥ ምንም ዓይነት ሳይንሳዊ ተዓምር የሆነ ዕውቀት አይገኝም፡፡

እዚህ ነጥብ ላይ ስደርስ በቁርአን ውስጥ ሳይንሳዊ ዕውቀት የመኖሩን ዕድል አልዘጋሁም ነገር ግን መለኮታዊ መገለጥ መሆኑን የሚያስረዳ የበለጠ ጠንካራ የሆነ የሙግት ሐሳብ ያስፈልጋል የሚል ድምዳሜ ላይ ነው የደረስኩት፡፡ ያለኝ በራስ የመተማመን ስሜት እየተሸረሸረ ቢመጣም ነገር ግን እምነቴ ጠልቆ የተመሠረተበትን ሥር ማለትም የቁርአንን እንከን አልባ በሆነ መንገድ ተጠብቆ መቆየት ለመመርመር ተሰናዳሁኝ፡፡

# ሐዲስ እና የቁርአን ታሪክ

ቁርአን እንከን አልባ በሆነ ሁኔታ ተጠብቆ መቆየቱን ሙስሊሞች በራስ በመተማመን መናገር እንዲችሉ የሚያደርጓቸው ሁለት ጠንካራ ኃይላት ይገኛሉ፡፡

በአንድ ወገን እንደሌሎቹ የእስልምና ኩራት የሆኑ አቋሞች ሁሉ በሙስሊሞች ሥነ ልቦና ውስጥ ጠልቆ የተተከለው ጭፍንነት ነው፡፡ “በቁርአን ውስጥ የሚገኝ ምንም ነገር በየትኛውም ቅፅበት ተለውጦ አያውቅም፡፡ መሐመድ ልክ ከገብርኤል በተቀበለበት ሁኔታ ነው ወደ እኛ የደረሰው፡፡” ይህ በመሆኑም እንዲህ የሚለው የቁርአን ትንቢት ተፈፃሚነትን አግኝቷል፡ “እኛ ቁርአንን እኛው አወረድነው እኛም ለርሱ ጠባቂዎች ነን፡፡”

በሌላ ወገን የቁርአን ጽሑፍ ፍፁም በሆነ ሁኔታ ተጠብቋል የሚለው እምነት ይሁዲና ክርስትናን ለመቃወም መሠረት ሆኗል፡፡ በአሜሪካ ውስጥ ግምባር ቀደም የሆነ “እስልምናን ለምን ይመርጣሉ?” የሚል መጠርያ ያለው የዳዋ ንቅናቄ ይህንን ጉዳይ በጥሩ ሁኔታ አስቀምጦታል፡- “በእስልምና መሠረት መዝሙራት፣ ቶራና ወንጌል የቀደመውን መልካቸውን ይዘው አይገኙም፡፡ ተጨምሮባቸዋል፣ ከነቢያቶቻቸው ጋር ቀጥተኛ ተያያዥነት የላቸውም ወይም ደግሞ ተቀይረዋል፡፡ የቀደመውን መልኩን ይዞ የሚገኘው ቁርአን ብቻ ነው፡፡ ልክ ለነቢዩ መሐመድ በተገለጠለት መልኩ ዛሬም ድረስ ተጠብቋል፡፡”[101]

ቁርአን እስስ ዛሬ ድረስ ተጠብቆ መቆየቱ ሌሎች እምነቶችን ለማጣጣልና እስለምናን ለመቀበል እንደ መሠረታዊ ጉዳይ የሚያገለግል እንደመሆኑ መጠን ለእስልምና

ዓቅዕበተእምነት በእጅጉ ወሳኝ ነው፡፡ ከዚህ በላይ ደግሞ ለእስልምና ነገረ መለኮ በእጅጉ አስፈላጊ ነው፡፡ ቁርአን የእስልምና ንፅረተ ዓለም የማዕዘን ድንጋይ ነው፡፡ ሸሪኣ የተመሠረተበት መሠረት፣ የዘወትር ጸሎት የሚጸለይበትና የእስልምና አርማ ነው፡፡ በብዙ ሙስሊሞች አስተሳሰብ መሠረት ቁርአን በትክክል ተጠብቆ ባይቆይ ኖሮ ሁሉም ነገራቸው ትረጉም አልባ በሆነ ነበር፡፡ ነገር ግን ያ ባለመሆኑ በእምነታቸው ላይ ያላቸው መተማመን በእጅጉ ከፍ ያለ ነው፡፡

የቁርአን ተጠብቆ መቆየት በዚህ ዘመን የሚገኙት ሙስሊሞች ከየትኛውም የእምነት ቡድኖች ይልቅ በራሳቸው እምነት እንዲተማመኑ አድርጓቸዋል፡፡ በዚህ ዘመን የሚገኘው ቁርአን በመሐመድ ዘመን ከነበረው በምንም መልኩ መለየቱን ማሰብ ለየትኛውም ሙስሊም የሚዋጥ አይደለም፡፡

ነገር ግን ብዙ ሙስሊሞች ሐዲሳትን ለራሳቸው አያነቡም፡፡ አሁንም እምነቴን ቆም ብዬ እንድመረምር ያደረጉኝ በጣም ተዓማኒ የሚባሉት እስላማዊ ትውፊቶች ናቸው፡፡ አሁን እንግዲህ በቁርአን ላይ ያለኝን እምነት ለመመርመር ተገድጃለሁ፡፡

ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅፅ 6 የቁርአንን አሰባሰብ የሚተርክ ነው፡፡[102] በዚህ መጽሐፍ ውስጥ መሐመድ ቁርአንን ለተከታዮቹ በአፉ ያስተምር እንደነበርና መጀመርያ እንዲጻፍ እንዳላደረገ እናነባለን፡፡ በአንድ ጊዜ ጥቂት ቁጥሮችን ብቻ የሚያስተምራቸው ሲሆን አንዱን አንቀፅ ለተለያዩ ሙስሞች እርስ በርሳቸው በማይጣጣሙ መንገዶች ይነግር ነበር፡፡

ከዚህ የተነሳ በመሐመድ ዘመን እንኳ በነበሩት ጥሩ ሙስሊሞች መካከል ትክክለኛው ቁርአን የትኛው ነው? በሚል የመረረ ክርክር ተደርጎ ነበር፡፡ በወቅቱ መሐመድ እዚያው ስለነበር “ሁለታችሁም በትክክለኛው መንገድ እያነበነባችሁ ነው” በማለት አረጋግቷቸዋል፡፡ “ከእናንተ በፊት የነበሩት ሕዝቦች የጠፉት በልዩነቶቻቸው ምክንያት ነው” በማለት እርስ በርቸው እንዳይለያዩ ምክር ለግሷቸዋል፡፡

መሐመድ ከሞተ በኋላ ብዙ ሰዎች ሙስሊሞች ሆነው የመኖር ፍላጎት አልነበራቸውም፡፡ አቡበከር ሙስሊሞች ከሓዲያኑን በመዋጋት እስላማዊ ግዴታቸውን እንዲወጡ ሰደዳቸው፡፡[103] ሙስሊሞች የቀድሞ ሙስሊሞችን ሲዋጉ ሳሉ ቁርአንን በቃላቸው ያጠኑትን ጨምሮ ብዙዎቹ በጦርነቱ አለቁ፡፡ ጦርነቱ የሚቀጥል ከሆነ አቡበከር አብዛኛው የቁርአን ክፍል እንዳይጠፋ ስለሰጋ ዘይድ ኢብን ጣቢት በተሰኘ ሰው የበላይ ተቆጣጣሪነት ቁርአን በአንድ ጥራዝ እንዲሰበሰብ አዘዘ፡፡

ሳሂህ አልቡኻሪ ሙስሊሞች የቁርአን አንቀፆችን በቀላሉ እንደሚረሱ በአፅንዖት ይናገራል፡፡ ከዚህ የተነሳ ቁርአንን የመሰብሰብ ኃላፊነቱ ዘይድን በእጅጉ አድክሞት ነበር፡፡ አንቀፆቹን ከግለሰቦች ትውስታና ከተለያዩ ቁርጥራጭ መጻፍያዎች ላይ ነበር የሰበሰበው፡፡ ከአንድ በላይ በሆኑ አጋጣሚዎች የተወሰኑ የቁርአን አንቀፆችን ማስታወስ የቻለው አንድ ሰው ብቻ ነበር፡፡ ዘይድ ሥራውን ካጠናቀቀ በኋላ የቁርአን ጥራስ ከመሐመድ መበለቶች መካከል በአንዷ ቤት እንዲቀመጥ ተደርጎ ነበር፡፡

የማሰባሰብ ተግባሩ ዋነኛ ዓላማ አንድም የቁርአን ጥቅስ እንዳይጠፋ የነበረ ቢሆንም ነገር ግን ዘይድ በስህተት የዘለላቸው የቁርአን ጥቅሶች መኖራቸው ተደርሶበታል፡፡ ከዚህም አልፎ በተለያዩ የሙስሊም ግዛቶች ውስጥ የሚኖሩት ብዙ ሙስሊሞች ቁርአንን በተለያዩ መንገዶች ያነበንቡ ስለነበር “ይህ ሕዝብ በቁርአን ላይ ካለው ልዩነት የተነሳ ከመጥፋቱ በፊት የትድግና ተግባር እንዲከናወን” ሙስሊም መሪዎች ጠይቀው ነበር፡፡

በልዩነቶች ላይ እንዳያተኩሩ የሚገልፀውን የመሐመድን ምክር ችላ በማለት ኸሊፋ ዑስማን ቁርአን አንድ ወጥ መልክ እንዲኖረው ትዕዛዝ ሰጠ፡፡ በመሐመድ መበለት ዘንድ የነበረውን ቅጂ በመውሰድ የዕርማት ሥራ ከሰሩለት በኋላ በመገልበጥ ወደ እያንዳንዱ የሙስሊም ግዛት አሰራጩት፡፡

ከዚያም በቁርአን ላይ የነበረውን ክረክር ለማብረድ ዑስማን “በቁርጥራጮች ላይ የተጻፉትም ሆኑ ሙሉ ቁርአኖች እንዲቃጠሉ አዘዘ፡፡”

ይህ እንግዲህ በሳሂህ አል-ቡኻሪ ውስጥ የሚገኘው የቁርአን አሰባሰብ ታሪክ ነው፡፡ ሙስሊሞች አንዳቸው ለሌላቸው ከሚነግሩት በተፃራሪ ሳሂህ አል-ቡኻሪ ያቀረበው ታሪክ እንደ መሐመድ ታሪክ ሁሉ የበለጠ ወደ እውነት የተጠጋ ግርድፍ ታሪክ ነው፡፡ እኔ በተማርኩት ታሪክ መሠረት መሐመድ ቁርአንን ለጸሐፊያን ይነግራቸዋል፣ እነርሱም ይጽፋሉ፣ ሙስሊሞችም ደግሞ ይሸመድዱታል፡፡ መሐመድ ሲሞት ብዙ ሰዎች ቁርአንን በጽሑፍና በሽምደዳ ይዘው ነበር፡፡ ዘይድ ኢብን ጣቢት ቁርአንን ኦፊሴላዊ በሆነ ሁኔታ ለመጻፍ የመጀመርያው ሰው ሲሆን በቃሉ ሸምድዶት ስለነበር ብዙም አልከበደወም ነበር፡፡ የእርሱ ቁርአን በቃላቸው በሸመደዱት ሌሎች ዋና ዋና ሙስሊሞች ማረጋገጫ የተሰጠው ነው፡፡

እኔ የተማርኩት ይህንን ነበር፡፡ በስፋት ተቀባይነት ባገኘው መረጃ መሠረት በይዘቱ ላይ ምንም ክርክር አልነበረም፣ ደካማ ትውስታ የሚባል ነገር አልነበረም፣ ይጠፊሉ ተብለው የተሰጉ ምንባቦች አልነበሩም፣ ነጠላ ምስክሮች አልነበሩም፣ የተረሱ ጥቅሶች አልነበሩም፣ በእርግጠኝነት ደግሞ ልዩነቶችን በማስወገድ ለመደበቅ የተደረገ አዋጅ አልነበረም፡፡ በሳሂህ ቡኻሪ ውስጥ የተዘገበው የቁርአን አሰባሰብ ታሪክ የቁርአን ጥቅሶች እንዲጠፉ ሰፊ የሆነ በር የሚከፍት ጥንቃቄ የጎደለው ሥራ ነው፡፡ በእርግጥ ሳሂህ ቡኻሪ ይህንን በግልፅ አስቀምጧል፡፡

ዘይድ ቁርአንን አንድ ወጥ መልክ ባስያዘ ጊዜ ኡበይ ቢን ካእብ የተሰኘ ሰው ያነበንባቸው የነበረውን የተወሰኑ ክፍሎች አስወግዶ ነበር፡፡ ኡበይ ዘይድ ያዘጋጀውን ቁርአን ችላ በማለት እነዚህን ጥቅሶች ማነብነብ እንደማይተውና የዚህ ምክንያቱ ደግሞ ከመሐመድ ስለሰማቸው መሆኑን ተናግሮ ነበር፡፡

በሳሂህ ቡኻሪ ኑዛዜ እጅግ ደነገጥኩኝ፡፡ ለምንድነው አስተማሪዎቹ ሁሉንም ታሪክ ያልነገሩኝ? ሌላ ያላወቅሁት ጉዳይ ምን ይሆን?

ሌሎች የሐዲስ መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙትን ታሪኮች ማንበብ ጀመርኩኝ፡፡ ቀጣዩ ተኣማኒ ምንጭ ሳሂህ ሙስሊም እንደዚሁ የከፉ ችግሮችን መዝገቧል፡፡ አንድ ሙሉ

ምዕራፍ በቁርአን ውስጥ እንደማይገኝና ቢያንስ አንድ ቁጥር በመሐመድ ሞት አካባቢ መጥፋቱን አስፍሯል፡፡[104] ሱናን ኢብን ማጃህ የተሰኘ ሦስተኛው ተአማኒ መጽሐፍ ደግሞ ጥቅሱ የተጻፈበት ወረቀት በፍየል በመበላቱ ምክንያት ሊጠፋ መቻሉን መዝግቧል፡፡[105]

ጥናቴን በቀጠልኩኝ ቁጥር የቁርአንን በትክክል ተጠብቆ መቆየት የሚገዳደሩ ብዙ ትውፊቶች አጋጠሙኝ፡፡ የመሐመድን ታሪኮች ሳጠና አደርገው እንደነበረው ሁሉ እነዚህን ማስረጃዎች ከመቀበል ይልቅ በአእምሮዬ ወደብ ላይ በማስቀመጥ በሙስሊም ዓቃቤ እምነታውያን የተፈጠሩትን ደካማማብራርያዎች እንደመፍትሄ አቀርብ ነበር፤ የራሴንም ማብራርያዎች እፈጥር ነበር፡፡ በመጨረሻ ሐሳቤን እንድቀይር ያስገደደኝ በበሳሂህ ቡኻሪ ውስጥ የሚገኘውን አንድ ታሪክ ደግሜ ማንበቤ ነው፡፡

በሐዲስ መሠረት መሐመድ የቁርአን ምርጥ መምህራን እንደሆኑ የጠቆማቸው አራት ሰዎች ነበሩ፡፡ የመጀመርያው መሐመድ ከሁሉም የላቀ የቁርአን ሊቅ እንደሆነ የመሰከረለት አብዱላህ ኢብን መስዑድ ነበር፡፡ የመጨረሻው ደግሞ ሳሂህ ቡኻሪ ምርጥ የቁርአን አነብናቢ መሆኑን ያሰፈረለት ኡበይ ቢን ካእብ ነው፡፡

እነዚህ መሐመድ እንደ ምርጥ የቁርአን አስተማሪዎች የመረጣቸው ሲሆኑ ነገር ግን ቀዳሚያን ምንጮችን ሳጠና ዛሬ በእጃችን የሚገኘውን የመጨረሻውን የቁርአን ቅጂ እንደማይቀበሉ ደርሼበታለሁ፡፡ እርስ በርሳቸው እንኳ አይስማሙም ነበር፡፡

የተወሰኑ ጥቅሶችን ማነብነብቡን እንደማይተው ከገለጸባቸው ቀደም ሲል ከተጠቀሱት ሐዲሳት በተጨማሪ የኡበይ ቢን ካእብ ቁርአን 116 ምዕራፎች ነበሩት፡፡ ይህ ደግሞ ከዘይድ ቅጂ በሁለት ምዕራፎች ይበልጣል፡፡ ኢብን መስዑድ ደግሞ 111 ምዕራፎች ብቻ ያሉት ሲሆን በዘይድ እና በኡበይ ቁርአኖች ውስጥ የሚገኙት ተጨማሪ ምዕራፎች ጸሎት ብቻ እንደሆኑና የቁርአን ምዕራፎች እንዳልሆኑ ተናግሮ ነበር፡፡[106]

ቁጥራቸው የበዛ ቀዳሚያን የሙስሊም ሰነዶች በጥንቱ እስላማዊው ዓለም ውስጥ በሚገኙት ብዙ ቁርአኖች መካከል የሚገኙትን ልዩነቶች በተመለከተ ብዙ ታሪኮችን አስፍረዋል፡፡ እነዚህ ሁሉ ሰነዶች እንደወደሙ ቢታሰብም አንዱ እስከ ሃያኛው

ክፍለዘመን መጀመርያ ድረስ ሊዘልቅ ችሏል፡፡[107] በብዙ ቦታዎች የአብደላህ ኢብን መስዑድና የኡበይ ቢን ካእብ ቁርአኖች የሚስማሙ ሲሆን የዘይድ ግን እንደሚለይ ያሳያል፡፡

በአእምሮዬ ውስጥ የተጠራቀሙትን እነዚህን ልዩ ልዩ መረጃዎች አንድ ላይ ገጣጥሜ ገመገምኳቸው፡፡ አንዱን ጥቅስ በተለያዩ መንገዶች ማንበብ፣ የጠፉ ጥቅሶች፣ የጠፉ ምዕራፎች፣ በቀኖና ላይ የነበረው አለመግባባት፣ ሁሉንም ልዩነቶች ተከታትሎ ማውደም… እውነቱ ይህ ሆኖ ሳለ ቁርአን በትክክል ተጠብቆ እንደቆየ ልንሟገት የምንችለው እንዴት ነው?

በበይነ መረብ ላይ የሚገኙትን ምላሾችና በሊቃውንት የተጻፉ መጻሕፍትን አንብቤያለሁ፡፡ እንደተለመደው መረጃዎችን በተቻላቸው መጠን ገሸሽ የማድረግ አካሄድ ይስተዋልባቸዋል፡፡ እንዲህም ሆኖ ሁሉንም ዓይነት ምክንያታዊ ማብራርያ ከሰጡ በኋላ ሙስሊም ሊቃውንት አስደንጋጭ የሆነ ምክንያት ለመስጠት ይሞክራሉ፡፡ የጠፉት ክፍሎች እንዲጠፉ አላህ አቅዷል፣ የንባብ ልዩነቶች እንዲወድሙ ፈቅዷል፣ የዘይድ ቅጂ የመጨረሻው ቁርአን እንዲሆን ወስኗል ይላሉ፡፡

ስለዚህ በእውነቱ ከሆነ ሊቃውንቱ ቁርአን ሳይቀየር እንደኖረ እየተሟገቱ አይደለም፡፡ ሙግታቸው በውስጡ የተፈፀሙት ለውጦች ሁሉ በአላህ የታቀዱ ናቸው የሚል ነው፡፡ ይህ ራሱን የቻለ የመከላከያ ሙግት ነው ቢባልም ነገር ግን ቁርአን አልተለወጠም የሚለውን አጠቃላዩን እስላማዊ ክርክር ያገናዘበ አይደለም፡፡

አሁንም በድጋሚ ቀዳሚያን እስላማዊ ምንጮች ዘመናዊው እስልምና ያስተማረኝን ትምህርት እንደተገዳደረ ለማመን ተገደድኩኝ፡፡ ቁርአን ተጠብቆ ኖሯል የሚለው አስተምህሮ እምነትን ለመከላከል የሚበቃ አይደለም፤ ነገር ግን እርሱ ራሱ በጭፍን እምነት ላይ የተመሠረተ ሌላ መከላከያ የሚሻ ነው፡፡

ይህንን የመጨረሻ ምርመራ ካደረኩኝ በኋላ የእምነቴ የመጨረሻው የማዕዘን ድንጋይ ተፈረካከሰ፡፡ አጠቃላዩ ሕንፃ መሠረት አልባ ከሆነ ትንሽ ነገር ሲነካው እንደ እምቧይ ካብ መፈራረሱ የማይቀር ነው፡፡

በማስከተል የሆነው ነገር እንደዚሁ ተራራን የሚያፈርስ ፍንዳታ ነበር፡፡

# ቀኝ እጆቻቸው የያዙትን ሁሉ

ቃላቱን ከልጅነቴ ጀምሬ በተደጋጋሚ ባነባቸውም ምንም ማለት እንደሆኑ ለማሰብ ግን ቆም ብዬ አላውቅም፡፡ ነገር ግን ዳዊት በማስታወሻው ውስጥ ስላካተተው እንደገና ለማጥናት ተገደድኩኝ፡፡

“ቀኝ እጆቻችሁ የያዟቸው” የሚለው ሐረግ በብዙ የቁርአን ጥቅሶች ውስጥ ይገኛል፡፡ ዳዊት የጠቆመኝ የመጀመርያዎቹ ሦስቱ 4፡24፣ 23፡6 እና 70፡30 ላይ የሚገኙት ሲሆኑ በመጀመርያ ዕይታ ብዙም ትርጉም የሚሰጡ አይደሉም፡፡

> 4፡24 “ከሴቶችም (በባል) ጥብቆቹ እጆቻችሁ (በምርኮ) የያዙዋቸው ሲቀሩ በእናንተ ላይ እርም ናቸው፡፡ (ይህን) አላህ በናንተ ላይ ጻፈ፡፡”
>
> 23፡6“በሚስቶቻቸው ወይም እጆቻቸው በያዟቸው (ባሪያዎች) ላይ ሲቀር፡፡ እነርሱ (በነዚህ) የማይወቀሱ ናቸውና፡፡”
>
> 70፡30 “በሚስቶቻቸው ወይም እጆቻቸው በያዙዋቸው (ባሪያዎች) ላይ ሲቀር፡፡ እነርሱ (በእነዚህ) የማይወቀሱ ናቸውና፡፡”

ጥቅሶቹን ወደ እማ በመውሰድ የሐረጉን ትርጉም እንድትነግረኝ ስጠይቃት ሙስሊም ወንዶች ስለሚያገቧቸው ሴት ባርያዎች እንደሚናገሩ ነገረችኝ፡፡ ያ ግን የሚያስኬድ አይደለም፡፡ በጥቅሶቹ ውስጥ ሚስቶች ቀኝ እጅ ከያዛቸው በግልፅ ተለይተዋል፡፡ አተረጓጎሟን ሳልቀበል ስቀር በጀማት ውስጥ ወደሚገኙት ሊቃውንት መራችኝ፡፡ በሚቀጥለው ዕድል ሳገኝ ለመጠየቅ በመወሰን እማን ትቻት ሄድኩኝ፡፡

በመጨረሻም ይህንን ጉዳይ በግሌ ማጥናት እንዳለብኝ ተሰማኝ፡፡ ከዚህ ቀደም ሊቃውንቱ በቂ ምላሽ ስላልሰጡኝ አሁን ሊሰጡኝ እንደሚችሉ ለማሰብ ምክንያት አልነበረኝም፡፡

በእርግጥ ዳዊት የራሱን ትርጉም ቢሰጠኝም ነገር ግን የተሳሳተ እንደሆነ አውቅ ነበር፡፡ ስህተት መሆን አለበት፡፡ የእርሱ ክርክር "ቀኝ እጅ የያዛቸው" የተባሉት በሙስሊም ወራሪዎች የተያዙት ሴት ባርያዎች ናቸው የሚል ነበር፡፡ እርሱ እንደሚለው ከሆነ ሱራ 23፡6 እና 70፡30 እንደ ጦር ምርኮኞች ከተያዙት ሴቶች ጋር ሙስሊም ወንዶች ፍትወት መፈፀም እንደሚችሉ ነው የሚናገሩት፡፡ በዚህ ሳያበቃ 4፡24 ሙስሊም ወንዶች ከምርኮኛ ሴቶች ጋር ባሎቻቸው በሕይወት ቢኖሩም እንኳን ፍትወት መፈፀም እንደሚችሉ ሞገተኝ፡፡

ይህን መናገር በራሱ እጅግ የሚያስቆጣ ነው፡፡ በተዘዋዋሪ ቁርአን አስገድዶ መድፈርን እንደ ሕግ ማስቀመጡን ነው እየተናገረ ያለው፡፡ ሌላ ምን ሊባል ይችላል? አንዲት ሴት በጦርነት ተያዘች ማለት አባቷ፣ ባሏ፣ ወንድሟ ወይም ልጇ እርሷን ከጥቃት ለመከላከል ሲሉ ሞተው ሊሆን ይችላል፡፡ እንዲህ ዓይነት ሴት ከአፍታ በፊት የምትወዳቸውን ወንዶች ከገደለ ተዋጊ ጋር የመተኛት ፍላጎት ይኖራታል ብሎ እንዴት ማሰብ ይቻላል?

ይህ እኔ የማውቀው እስልምና አይደለም፡፡ አስቶግፍሩላህ!የኔ መሐመድ የባርያዎች ነፃ አውጪና የቅዱሳን ሰዎች መሪ እንጂ የአስገድዶ ደፋሪዎችን ሰራዊት የሚመራ ወረሪ ባርያ ፈንጋይ አልነበረም፡፡ እስልምና እንዲህ ዓይነቱን ከፋት የሚፈቅድ እምነት አይደለም፡፡ ይህ የማይመስል ነው፡፡ ባለፉት ጥቂት ወራት እኔ የማውቃቸውን ሁሉ የሚገዳደሩ እውነታዎችን ብማርም ይኸኛው ግን እጅግ ተለየብኝ፡፡ ዳዊት መሐመድ ምግባረ ብልሹ ሰው ነው የሚል ክስ እያቀረበ ነው፡፡ እስልምና በማይታመን ሁኔታ የጭካኔ ሃይማኖት መሆኑን እየተናገረ ነው፡፡

በውይይታችን መካከል ዳዊት የኔን ነቢይ ስም ለማጉደፍ ጥረት በማድረጉ ምክንያት ከፉኛ በመቃወም ገሰፅኩት፡፡ ይህ ከሚታሰበው በላይ አዋራጅ ጉዳይ ነው፡፡ መጀመርያ

እስላማዊ ትውፊቶችን በመጥቀስ ሊሚገት ቢሞክርም ነገር ግን እርሱ የሚያቀርባቸው መከላከያዎች ሁሉ የበለጠውን እያስቆጡኝ እንደሆኑ ሲረዳ ትንሽ አፈገፈገ፡፡ ለምን እንደዚያ እንደተበሳጨሁና ቁርአን ምን እያለ እንደሆነ እንዳስብ ብቻ በመጠየቅ ጉዳዩን ተወው፡፡

እምነቴንና ነቢዬን መከላከል በማያስፈልገኝ ሁኔታ ለብቻዬ ስሆን ነበር ጉዳዩን እንደገና አንስቼ ለህሊናዬ በመታመን ማስረጃዎቹን እንደ አዲስ መመርመር የጀመርኩት፡፡

ሳሂህ ሙስሊም ሱራ 4፡24 ላይ ለሚገኘው መገለጥ ታሪካዊ ዳራ ይሰጣል፡፡ “በሁናይን ዘመቻ ወቅት የአላህ መልእክተኛ የጠላትን ሰራዊት እንዲዋጉ ወታደሮችን ላከ፡፡ ካሸነፏቸውና ከማረኳቸው በኋላ የአላህ መልእክተኛ አጃቢዎች ከጣዖታውያን ባሎቻቸው የተነሳ ከምርኮኛ ሴቶች ጋር ፍትወት መፈፀም አልፈለጉም ነበር፡፡ ከዚያም ታላቁ አላህ እንዲህ የሚለውን ጥቅስ አወረደ፡- “ከሴቶችም በባል ጥብቆቹ እጆቻችሁ (በምርኮ) የያዙዋቸው ሲቀሩ በናንተ ላይ እርም ናቸው፡፡” (ሱራ 4፡24)”[108]

ሐዲሱን ደግሜ ደጋግሜ አነበብኩት፡፡ ይህ ሐዲስ የዳዊትን ሙግት የሚደግፍ ስለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ እንዲያውም ዳዊት ጉዳዩን አክርሮ ያልጠየቀ ያስመስለዋል፡፡ በዚህ ሐዲስ መሠረት ጥቅሱ ወታደሮቹ በቅርቡ ከማረኳቸው ሴቶች ጋር ፍትወት እንዲፈፅሙ ከመፍቀድም አልፎ እነርሱ ማድረግ ባይፈልጉ እንኳን ተግባሩን እንዲፈፅሙ ያበረታታቸዋል፡፡

የማነበውን ነገር ማመን ተሳነኝ፡፡ የቆምኩበት ዓለም ከእግሬ ስር ሲንሸራተት ተሰማኝ፡፡ ወዲያውኑ ሼኾችና ኢማሞች ሲያደርጉት ያየሁትን ነገር አደረኩኝ፡፡ ሐዲሱ ደካማ መሆን አለበት ብዬ ደመደምኩኝ፡፡ በሳሂህ ሙስሊም ውስጥ የሚገኝ ቢሆን እንኳን አንዱን ሐዲስ ወደ ጎን ማድረግ ቀላል ነው፡፡

ነገር ግን የበለጠ ዝርዝር ታከሎበት በሱናን አቡ ዳውድ ውስጥ ሰፍሯል፡፡ ሙስሊም ወታደሮቹ የሴቶቹ ባሎች በሕይወት ስላሉና እዚያው በአጠገባቸው ስለነበሩ ከሴቶቹ ጋር ለመተኛት አልፈለጉም ነበር፡፡[109] አንድ ነባር ሐቲት እንዳብራራው ከሆነ ሱራ 4፡24

በተገለጠ ጊዜ ባሎቻቸው እዚያው ቢኖሩም ወንዶቹ ከሴቶቹ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈፅመዋል፡፡[110]

ሳሂህ ቡኻሪ ውስጥ ተመሳሳይ ሐዲስ ይገኛል፡፡ ከሴት ምርኮኞቻቸው ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከማድረግ ስለተቆጠቡ ተዋጊዎች እናነባለን፤ ነገር ግን ምክንያታቸው የተለየ ነበር፡፡ ተዋጊዎቹ ሴቶቹ ይፀንሳሉ የሚል ፍርሃት ነበረባቸው፡፡ መሐመድም የሴቶቹ ማርገዝ አለማርገዝ በአላህ ፍቃድ ላይ የተመሠረተ መሆኑን በመንገር ስጋታቸውን አረገበላቸው፡፡[111] ሳሂህ ሙስሊም ተዋጊዎቹ ሴቶቹ እንዳያረግዙ የፈለጉበት ምክንያት ሊሸጧቸው ስለፈለጉ እንደሆነ በመግለፅ ታሪኩ ላይ ያክላል፡፡[112]

ይህ በቂ ነበረ፡፡ ዳዊት “ቀኝ እጆቻችሁ የያዟቸው” የሚለወን ሐረግ የተረጎመበት መንገድ ትክክል ከመሆኑም አልፎ ሊያመልጡት የማይቻለውን ሃቅ አዝለዋል፡፡ በቁርአን ውስጥ፣ በሳሂህ ቡኻሪ ውስጥ፣ በሳሂህ ሙስሊም ውስጥ፣ በሱናን አቡ ዳውድ ውስጥ፣ በሐተታዎች ውስጥ፣ ባጠቃላይ በሁሉም ቦታዎች ይገኛል፡፡

ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? ሕይወታቸው ከተበላሸባቸው ሴቶች ጋር ባሎቻቸው ባሉበት ቦታ እንዲተኙ ቁርአን ለወንዶች እንዴት ፈቀደ? አላህና መሐመድ ሴቶቹ ስለማርገዛቸውም ሆነ በኋላ ላይ ለባርነት ስለመሸጣቸው እንዴት ግድ አላላቸውም? ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?

በሙስሊሞች የተወረሩት የገዛ ሕዝቦቼ ቢሆኑስ? ቤተሰቦቼን እየተከላከልኩ ሳለሁኝ አባቴ ሲገደል ብመለከትስ? ባጂና እማ ላይ የሚደርሰውን ዓይኔ ቢያይስ...

ይህ ከልክ አልፏል፡፡ በቅቶኛል፡፡ ከዚህ በላይ ማሰብ ተስኖኛል፡፡ እንዲህ ማሰብ አመፅ መስሎ ተሰማኝ፡፡ ነቢዬንና እምነቴንም እንድክድ እንዳያደርገኝ ሰጋሁኝ፡፡

ልክዳቸው ባልፈልግም ነገር ግን በቸልታ ላልፋቸው የምችልበት መንገድ አልነበረኝም፡፡ ስለዚህ አንገሸገሸኝ፡፡ ትግሉ አሰለቸኝ፡፡ በመጨረሻም ተስፋ ቆረጥኩኝ፡፡

*በኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ የሚገኘው የቦድሌን ቤተ መጻሕፍት የቁርአን የእጅ ጽሑፎች ሊቅ እንዲሁም የንባብ ሒስና የቁርአን እጅ ጽሑፎች የሚለውን መጽሐፍ የደረሱትን የዶ/ር ኪዝ እስሞልን አስተዋፅዖ ለማንበብ contributions.NabeelQureshi.com የሚለውን ድረገፅ ይጎብኙ፡፡*

ክፍል ፱

# እምነት በጥርጣሬ ሲተካ

*አንተ ማን እንደሆንክ አላውቅም ነገር ግን አንተን ሳያውቁ መኖር ትርጉም እንደሌለው ገብቶኛል፡፡*

# አመክንዮና መገለጥ

ለሦስት ዓመታት ያህል ምሑራዊ ፍልሚያዎችን አድርገናል፡፡ የመጀመርያ ዓመት ተማሪ ሳለሁኝ በመጀመርያው ወር የተጀመረው ክርክር እስከ ምርቃት ዋዜማ ድረስ ቀጥሏል፡፡ ተስፋ እየቆረጥኩ ነበር፡፡

ነገር ግን በእስልምና ላይ አልነበረም ተስፋ የቆረጥኩት፡፡ ገና ነበርኩኝ፡፡ በምክንያታዊነት ላይ ተስፋ እየቆረጥኩኝ ነበር፡፡

ከሽልማት ሥነ ሥርዓት መልስ በመኪናዬ የፊት ወንበር ላይ ተቀምጠናል፡፡ በሺዎች ከሚቆጠሩ ተመራቂ ተማሪዎች መካከል *የካውፍማን* ሽልማት የተሰኘውን የኦዲዩ ከፍተኛ ሽልማት ለመቀበል ስድስት ተማሪዎች ተመርጠው የነበረ ሲሆን ምርጫው በውጤት፣ በመሪነትና በማሕበራዊ አገልግሎት ተሳትፎ ላይ የተመሠረተ ነበር፡፡ ዳዊትና እኔ ከሰድስቱ መካከል ነበርን፡፡ ይህ ሽልማት በኮሌጅ ውስጥ ሳለሁ የወጣሁበትን የስኬት ማማ አመላካች ነበር፡፡

ነገር ግን ሽልማቱን እንደ ተራ ነገር ነበር የኋላ ወንበር ላይ የወረወርኩት፡፡ ለእርሱ ግድ አልነበረኝም፡፡ ለምንም ነገር ትኩረት መስጠት አቁሜያለሁ፡፡ ሕይወቴን በሙሉ የኖርኩት በጠንከራ የራስ መተማመን ነበር፡፡ እስልምናዬ፣ አስተሳሰቤ፣ ቤተሰቤ፣ ቃሌና ተግባሬ ሁሉ የማንነቴ መገለጫዎች ነበሩ፡፡ ግልፅና ያልተሸቃቀጠ ማንነት ነበረኝ፡፡ ያሰብኩትን ነገር ከመናገር ሳልቆጠብ ባመነኩት ነገር በነፃነትና ያለመሸማቀቅ ኖሬያለሁ፡፡

አሁን ግን ውጪዬ እስልምናን አጥብቄ የያዝኩ ቢያስመስለኝም ውስጤ ግን ተሸርሽሮ ግራ በመጋባት ተሞልቷል፡፡ ስለ ክበርና ውርደት ያለው እስላማዊ አመለካከት በውስጤ እየሆነ ያለውን ትርምስ ለሌላ ሰው እንዳላካፍል እንቅፋት ሆኖብኛል፡፡ ስለዚህ ሕይወቴ ሳይመሰቃቀል የውስጤን ችግር አውጥቼ ለጓደኞቼም ሆነ ለቤተሰቤ ልነግር የምችልበት መንገድ አልነበረኝም፡፡

ፈጣሪዬ ማን እንደሆነ ማውቅ ተስኖኛል፡፡ ዓለም ምን እነደሆነች ማወቅ ተስኖኛል፡፡ እኔ ራሴ ማን እንደሆንኩኝ ማወቅ ተሰኖኛል፡፡ ምን ማድረግ እንዳለብኝ ምንም የማውቀው ነገር አልነበረኝም፡፡ ልክ በከባድ ማዕበል እየናወዘ ነፍሱን ለማትረፍ የሚጨብጠውን ነገር እንደሚፈልግ ሰው ሆኛለሁ፡፡ ከዚህ ቀደም ስኖረው የነበረውን ሕይወት ለመቀጠል አንድ የመጨረሻ ተስፋ የመቁረጥ ሙከራ አደረኩኝ፡፡

“ስማኝ ዳዊት የክርስትናን መልዕክት የምቀበልበት ምንም ዓይነት መንገድ አይኖርም፡፡”

እኔ ዓይኖቼን መንገዱ ላይ አደድርጌያለሁ፤ ዳዊት ደግሞ በመስኮቱ አሻገሮ እየተመለከተ ነው፤ የሚታይ አዲስ ነገር ባይኖርም፡፡ እንድናገር ዕድል እየሰጠኝ ነበር፡፡

እኔም ንግግሬን ቀጠልኩኝ “የክርስቲያን አምላክ አንድን እውነታ እንደቀበል ከእኔ ይፈልጋል፡፡ ኢየሱስ ጌታ መሆኑን እንዳምን ይጠብቅብኛል፡፡ ነገር ግን እኔ በወቅቱ እዚያ ስላልነበርኩኝ አምላክ መሆኑን መናገሩን እንኳ አላውቅም፡፡ እኔ ሙስሊም ነኝ፡፡ ምን ጊዜም ዓለምን በእስልምና መነፅር ስመለከት ነበር፡፡ ኢየሱስ አምላክ ቢሆን እንኳን የማውቅበት ምንም መንገድ የለም፡፡ ላውቀው የማልችለውን እውነታ ባለማወቄ የተነሳ እግዚአብሔር በተጠያቂነት እንዴት ሊይዘኝ ይችላል? ሲጀመር እኮ ማወቅ የምችልበት መንገድ የለም፡፡”

የእስልምና እምነቴን ይገኔ ለመቀጠል የሞከርኩት የመጨረሻ የሙግት ሐሳብ ነበር፡፡ እርግጠኛ የሆነ እውነት ላይ መድረስ መቻሌን መካድ፡፡

ዳዊት ንግግሬን እያሰላሰለ ማዶ ማዶ ይመለከት ነበር፡፡ በመጨረሻም የተናገረው ንግግር ምንም መፈናፈኛ የሚሰጥ አልነበረም፡፡ “ነቢል ያ እውነት እንዳልሆነ ታውቃለህ፡፡ ወላጆችህ ህልም ያልማሉ፡፡ አንተንም ደግሞ እግዘአብሔር በሰማይ ውስጥ በሚታይ ልዕለ ተፈጥሯሚ ምልክት መርቶሃል፡፡ እውነቱን እንዲገልጥልህ ብትጠይቀው እንደሚገልጥልህ በሚገባ ታውቃለህ፡፡”

ዳዊት በተናገረበት በዚያው ቅፅበት ትክክል መሆኑን አውቄያለሁ፡፡ ንግግሩ ከዚህ በፊት ያላሰብኩትን የእፎይታ መንገድ የሚጠቁም ነበር፡፡ እግዚአብሔር እንዳለ የማምን ከሆን ለምን ማንነቱን እንዲገልፅልኝ አልጠይቀውም? ይህንን እውነት ለኔ ለማብራት ይሳነዋል እንዴ?

የዓቀበተ እምነትን ዋጋና እነዚህ ክርክሮች ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆኑ የተረዳሁበት ወቅት ነበር፡፡ ትሁት በሆነ መንፈስ እግዚአብሔር ማንነቱን እንዲገልፅለኝ እንዳልጠይቀው እንደ ዕውቀት የያዝኳቸው እነዚህ ነገሮች እንቅፋት ሆነውብኝ ነበር፡፡ ሙግቶቹና ዓቀበተ እምነት እነዚህን ጋሬጣዎች በመናድ እግዚአብሔርን ለመፈለግ እንድወስን አረድተውኛል፡፡

እውነትን በዕውቀት ለማግኘት ያደረኩት ጥረት እዚህ ጋ አብቅቷል፡፡ ወደ መሰዊያው የሚያደርሰኝን መንገድ ከፍቶልኛል ነገር ግን በዚያ መንገድ ላይ የመሄድና ያለመሄድ ውሳኔ ማድረግ ነበረብኝ፡፡ ያንን መንገድ ለመሄድ ከወሰንኩኝና እግዚአብሔርን ለማወቅ ከፈለኩኝ በምህረቱና በፍቅሩ እጅ ላይ ራሴን በመጣል ራሱን እንዲገልጥልኝ ሙሉ በሙሉ በእርሱና በፈቃዱ ላይ መደገፍ ይኖርብኛል፡፡

ነገር ግን ይህ ውሳኔ ምን ያህል ዋጋ ይጠይቀኝ ይሆን?

# መስቀሉን መከተል የሚያስከፍለው ዋጋ

አንድ ሙስሊም ወንጌልን ቢቀበል የሚከፍለው ዋጋ እጅግ ከባድ ነው፡፡ በእርግጥ ኢየሱስን ለመከተል ብመርጥ ወዲያውኑ ከማሕበረሰቡ የመገለል እጣ ይገጥመኛል፡፡ ይህ ለሁሉም ሙስሊሞች ከልጅነታቸው ጀምሮ የገነቡትን ጓደኝነትና ማሕበራዊ ትስስር መስዋዕት ማድረግን የሚጠይቅ ነው፡፡ በወላጆች፣ በወንድሞችና እህቶች፣ በትዳር አጋር እንዲሁም በአብራክ ክፋዮች መጠላትን ያስከትላል፡፡

ሙስሊሙ ኢየሱስን ለመከተል ከወሰነ በኋላ ሊቀርበው የሚችል ክርስቲያን ካላገኘ ይህ ችግር በእጅጉ ይከፋል፡፡ ኢየሱስን መከተል የሚፈልጉ ነገር ግን ባሎቻቸው ቢለዩዋቸው መሄጃ የሌላቸውን ብዙ ሙስሊም ሴቶች አውቃለሁ፡፡ ልጆቻቸውን ለማግኘት በፍርድ ቤት መሟገት ይቅርና የሚቀጥለውን ቀን መዋል የሚችሉበት ገንዘብ የላቸውም፡፡ ከቅርብ ዘመዶቻቸው ከሚመጣባቸው ነቀፋ የተነሳ ከሚደርስባቸው የስሜት መጎት ጋር እየታገሉ ይህንን ሁሉ ችግር መቋቋም ያስፈልጋቸዋል፡፡

ብዙዎች የማያስተውሉት - እኔ ራሴ ይህንን ውሳኔ ስወስን ያላስተዋልኩት ነገር ቢኖር እነዚህ ዋጋዎች ንቁ በሆነው ህሊናችን ውስጥ መሰወራቸውን ነው፡፡ ወንጌልን ላለመቀበል እውነተኛዎቹ ምክንያቶች ሆነው ሳሉ ሌሎች ሰበብ አስባቦችን እንድንፈጥር ያደርጉናል፡፡ “ኢየሱስን መከተል ቤተሰቤን ስለሚያሳጣኝ ሙስሊም ሆኜ እቀጥላለሁ” ብዬ አላውቅም ነበር፡፡ ነገር ግን እነዚህን ዋጋዎች ላለመክፈል ወንጌልን ላለመቀበል ሳይታወቀኝ ሰበብ አስባቦችን እፈጥር ነበር፡፡

በውሳኔዬ ምክንያት ዋጋ የምከፍለው እኔ ብቻ አይደለሁም፡፡ የኔ ቤተሰብ በደስተኛነቱ፣ ባለን መቀራረብና እስልምናን በታማኝነት በመከተል በሙስሊሙ ማሕበረሰብ መካከል ከበሬታን አትርፏል፡፡

ውሳኔዬ ቤተሰቤን ትልቅ ውርደት ውስጥ በመጣል እንዲያፍሩ ያደርጋል፡፡ ኢየሱስን በትክክል ባውቀው እንኳን እንዲህ ዓይነቱን አስደንጋጭ ነገር በቤተሰቤ ላይ ለመፈፀም እችል ይሆን? ይህንን ሁሉ ነገር ካደረጉልኝ በኋላ እንዲህ ያለውን ነገር በእነርሱ ላይ ለመፈፀም እንዴት ነው የምደፍረው?

በመካከለኛው ምስራቅ የሚገኙ ብዙ ሰዎች ለክብራቸው ሲሉ ዘመዶቻቸውን የሚገድሉት በዚህ ምክንያት ነው፡፡ በቁርአን ወይም በሐዲስ ውስጥ ለክብር ሲሉ መግደልን የሚያዝ ነገር ባይጻፍም ነገር ግን ሥርአት የሚያፈርሱትን ሰዎች ስለመግደል የተሰጠ ቁርአናዊ ትዕዛዝ አለ፡፡[113] ከእስልምና የሚወጡትንም ሰዎች ስለመግደል የተሰጡ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ትዕዛዛት በሐዲሳት ውስጥ ይገኛሉ፡፡[114]

እንደዚህ ዓይነት ግድያዎች በመካከለኛው ምስራቅ የተወሰኑ አይደሉም፡፡ ከምርቃት ጥቂት ሳምንታት በኋላ ማይክ ስልክ ደውሎ ከመካከለኛው ምስራቅ የመጡ በኒው ጀርሲ ይኖሩ የነበሩ የአንድ ቤተሰብ አባላት በሙሉ እስልምናን አዋርደዋል በሚል መገደላቸውን ከነገረኝ በኋላ ኢየሱስን ብከተል ደህንነቴ የተጠበቀ መሆን አለመሆኑን ጠይቆኝ ነበር፡፡ ለኔ በማሰቡ አመስግኜው ነገር ግን ያ ብዙም እንደማያሳስበኝ ነገርኩት፡፡ የኔ ቤተሰብ እንዲህ ያለውን ተግባር አይፈፅምም፡፡ ግድያውም ደግሞ አንዳንዶች የሚፈሩትን ያህል የሚደጋገም አይደለም፡፡ ከዚህም በላይ ሰማዕትነት ክብር ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡

ለኔ ትልቁ ስጋት የነበረው ኢየሱስን መከተል ስህተት ሆኖ እንዳይገኝ ነው፡፡ ኢየሱስ አምላክ ባይሆንስ? ሰው አምላኪ ልሆን ነው፡፡ ያ ደግሞ የአላህን ቁጣ ያስከትላል፤ ከምንም በላይ ደግሞ ወደ ገሃነም እንድወርድ ምክንያት ይሆናል፡፡

በእርግጥ ይህ ቁርአን የሚያስተምረው ሃቅ ነው፡፡ በእስልምና ይቅርታ የሌለው አንድ ኃጢአት ቢኖር **ሽርክ** ነው፡፡ ሽርክ ከአለህ ጋር ሌላ ነገር አምላክ መሆኑን ማመን ነው፡፡ ሽርክ በሱራ 5፡72 ላይ ኢየሱስን ባማከለ ሁኔታ ተብራርቷል፡፡ ኢየሱስ አምላክ መሆኑን የሚያምን ሰው "አላህ ገነትን በእርሱ ላይ እርም አድርጓል፡፡ መኖርያውም የገሃነም እሳት ነው፡፡"

**ሽርክ፡** በእስልምና መሰረት ምህረት የሌለው ኃጢአት ነው፡፡ ከጣዖት አምልኮ ጋር እኩል ሲሆን ለአላህ የሚገባውን ክብር ለሌላ አካል መስጠት ነው፡፡

ሙስሊሞች ወንጌልን ለመቀበል ሲወስኑ ሊያሰሏቸው የሚገቧቸው ዋጋዎች እነዚህ ናቸው፡፡ በዚህ ምድር ላይ የገነቧቸውን ማሕበራዊ መስተጋብሮች የማጣት፣ ሕይወታቸውን ጭምር የማጣትና ከተሳሳቱ ደግሞ ከሞት በኋላ ያለውን ሕይወታቸውን የማጣት እጣ ይገጥማቸዋል፡፡ ሙስሊሞች መስቀሉን ለመከተል ሲወስኑ ሁሉን ነገር የማጣት አደጋ ከፊታቸው ይጋረጣል ብንል ማጋነን አይሆንም፡፡

ይህ የመስቀል ባሕርይ ነው፡፡ ኢየሱስ እንዲህ ብሎ መናገሩ ያለምክንያት አልነበረም፡- "በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር፥ ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ፡፡ ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታልና፥ ስለ እኔና ስለ ወንጌል ነፍሱን የሚያጠፋ ሁሉ ግን ያድናታል" (ማርቆስ 8፡34-35)፡፡

መስቀሌን ተሸክሜ ከኢየሱስ ጎን መሰቀል ተገቢ ይሆንን? አምላክ ካልሆነ ተገቢ አይደለም፡፡ ሁሉን ነገር አጥቼ የተሳሳተ አምላክ ላመልክ? አይደረግም!

ነገር ግን አምላክ ከሆነ አዎን፡፡ ለዘላለም ከጌታዬ ጋር ተጣብቄ ከእርሱ ጋር መከራን ልቀበል? አንድ ሚሊዮን ጊዜ አዎን የሚል መልስ እሰጣለሁ!

አሁን ከየትኛውም ጊዜ በላቀ ሁኔታ ነገሮች እየጠሩ ስለመጡ የእርሱን ማንነት ማወቅ አስፈልጎኛል፡፡ ሁሉም ነገር በእርሱ ማንነት ላይ የተንጠለጠለ ነው፡፡ ስቆም፣ ስራመድ፣ ስጸልይም ሆነ ስተኛ ማንነቱን እንዲገልፅልኝ መወትወትን ተያይዠለሁ፡፡ ከዚህ ቀደም

ልዕለ ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ ስለመራኝ አሁንም ደግሞ እንደሚመራኝ ሙሉ እምነት ነበረኝ፡፡

ነገር ግን የሽግግር ጊዜው በእጅጉ መራራ ነበር፡፡ ከመስጊድ ወደ መስጊድ በመንከራተት ኢማሞችና ሊቃውንት በውስጤ እየሆነ ለነበረው ትግል መፍትሄ እንዲሰጡኝ እጠይቅ ነበር፡፡ መሐመድም ሆነ ቁርአን ትክክል መሆናቸውን ሊያሳየኝ የቻለ ማንም አልነበረም፡፡ ሁላቸውም ችግር ሊያስከትሉ የሚችሉ ትውፊቶችን እየመረጡ ተዓማኒነታቸውን በመካድ የእነርሱን አመለካከት የሚደግፉ ትውፊቶችን ብቻ ይመርጡ ነበር፡፡ መፍትሄ በእነርሱ ዘንድ አልነበረም፡፡

ከእነርሱ ጋር ለመነጋገር ስጠብቅ ሳለሁኝ ስለ ሐዲሳት አሰባሰብ፣ ስለ ሲራና የቁርአን ታሪክ የሚናገሩ በሙስሊም ሊቃውንት የተጻፉ መጻሕፍትን ዓይኖቼ እስኪቀሉ ድረስ አነብ ነበር፡፡ በሰላት ሰዓት ደግሞ የአምላኬን ምሕረት ስማፀን እነዚሁ ዓይኖቼ እንባ ያዘንቡ ነበር፡፡

# እኔ ቅርብ ነኝ፣ ፈልጉ ታገኛላችሁ

በተሰበረ ልብ ሆኜ ሰፊ በሆነው የሙስሊሞች የጸሎት አዳራሽ ውስጥ በአምላኬ ፊት ተደፋሁ፡፡ ባለፉት ጥቂት ዓመታት የኔ ንፅረተ ዓለም፣ የማውቀው ነገር ሁሉ ቀስ በቀስ ተፈረካክሷል፡፡ በፍርስራሹ ውስጥ ተቀምጬ አላህን መማፀን ጀመርኩኝ፡፡ ዓይኖቼ እንባ አቅርረው ዕይታዬ ተጋርዷል፡፡ የተለመደው ጸሎት ተጠናቋል አሁን ደግሞ የልቤን ጸሎትየምጸልይበት ጊዜ ነው፡፡

“አምላኬ ሆይ ሰላምህን እሻለሁ፡፡ እባክህን እዘንልኝና አንተን በማወቅ የሚገኘውን ሰላም ስጠኝ፡፡ አንተ ማን እንደሆንክ አላውቅም ነገር ግን አንተን ሳያውቁ መኖር ትርጉም እንደሌለው ገብቶኛል፡፡ አንተ ይህንን ዓለም ፈጥረሃል፡፡ ትርጉም የምትሰጠውም አንተ ነህ፡፡ አንተ በዓላማ ሰርተኸው ባይሆን ኖሮ ትርጉም የለሽ በሆነ ነበር፡፡

“እባክህን ሁሉን ቻዩ አምላክ ሆይ ማን እንደሆንክ ንገረኝ! አንተንና አንተን ብቻ እሻለሁ፡፡ ልትታደገኝ የምትችለው አንተ ብቻ ነህ፡፡ የተማርኳቸውን ነገሮች ሁሉ በእግሮችህ ስር አስቀምጣለሁ፡፡ ሕይወቴንም በሞላ ላንተ እሰጣለሁ፡፡ ፈቃድህ ከሆነ ደስታዬን፣ ጓደኞቼን፣ ቤተሰቤን ወይም ደግሞ ሕይወቴን እንኳ ቢሆን ውሰዳቸው፡፡ ነገር ግን እባክህን አምላኬ ሆይ አንተን ላግኝህ፡፡

የምሄድበትን ጎዳና አብራልኝ፡፡ ምንም ያህል እንቅፋቶች በፊቴ ቢኖሩ፣ ምንም ያህል ጉድጓዶችን መዝለል ቢኖርብኝ ወይም ገብቼ መውጣት ቢኖርብኝ፣ በምንም ዓይነት

እሾኽና አሜኬላ መካከል ማለፍ ቢኖርብኝ ግድ የለኝም፡፡ በቀናው ጎዳና ላይ ምራኝ፡፡ እስልምና ከሆነ እንዴት እውነት ሊሆን እንደሚችል አሳየኝ! ክርስትና ከሆነ ማየት እችል ዘንድ ዓይኖቼን ክፈትልኝ! ውዱ አምላኬ ሆይ እሄድበት ዘንድ መንገድህ የትኛው እንደሆነ አመልክተኝ፡፡"

ፈጣሪዬ ጸሎቴን እንደሰማና እኔን ለማዳን ቁልፉን እንደጨበጠ እርግጠኛ ነበርኩኝ፡፡ በየትኛውም ደቂቃ የእውነቱን በር ሊከፍትልኝ ይችላል፡፡ የክርስትና ሙግት ጠንካራ መሆኑ ገብቶኛል፤ ኢየሱስ አምላክ መሆኑን መናገሩና ይህንንም ደግሞ በሞቱና በትንሣኤው ማረጋገጡ ሃቅ ነው፡፡ እውነተኛው አላህ የመጽሐፍ ቅዱሱ እግዚአብሔር መሆኑን ከገለጠልኝ እርሱን፣ ማለትም ኢየሱስን እንደ ጌታዬ አድርጌ ለመቀበል ዝግጁ ነበርኩኝ፡፡ ነገር ግን በጭንቀትና ተስፋ በመቁረጥ ውስጥ ሆኜ አላህ የእስልምና አምላክ እንደሆነ ይገለጥልኝ ዘንድ እመኝ ነበር፡፡ ያ ካልሆነ ግን የምከፍለው ዋጋ እጅግ የከበደና ልሸከመው ከምችለው በላይ ይሆንብኛል፡፡

በየዕለቱ በጸሎቴ መካከል ሁለት ጥቅሶችን አስታውስ ነበር

- ሱራ 2፡186 "እኔ ቅርብ ነኝ፡፡ የለማኝን ጸሎት በለመነኝ ጊዜ እቀበለዋለሁ፡፡"
- ማቴዎስ 7፡7-8 "ለምኑ፥ ይሰጣችሁማል፤ ፈልጉ፥ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያን አንኳኩ፥ ይከፈትላችሁማል፡፡ የሚለምነው ሁሉ ይቀበላልና፥ የሚፈልገውም ያገኛል፥ መዝጊያንም ለሚያንኳኳ ይከፈትለታል፡፡"

ከነዚህ ከሁለቱ ጥቅሶች የተነሳ አላህ ይሁን ኢየሱስ፣ የቁርአኑ አምላክ ይሁን የመጽሐፍ ቅዱሱ - ብቻ እውነተኛው አምላክ ጸሎቴን እንደሚመልስ ሙሉ እምነት ነበረኝ፡፡ ጥያቄው ግን እስከዚያው ድረስ ማዕበሉን ተቋቁሜ መፅናት መቻል ያለመቻሌ ጉዳይ ነበር፡፡

ከአምስት ወራት በኋላ መልስ ሰጠኝ፡፡

# በመስቀሎች የተሞላው መስክ

ዲሴምበር 19፣ 2004 እኔና አባ በኦርላንዶ ፍሎሪዳ ነበርን፡፡ የኅክምና ትምህርቴን የመጀመርያ መንፈቀ ዓመት ትምህር ያጠናቀቅሁኝ ሲሆን ከቤተሰቤ እንዳልርቅ በድጋሜ የመረጥኩት በአቅራቢያው የሚገኘውን ትምህርት ቤት ነበር፡፡ እማና አባ ሴሚስተሩን በሙሉ በትኩረት ሳጠና ስላዩኝ ሊሸልሙኝ ፈልገዋል፤ ስለዚህ በክረምት እረፍት ወቅት አባ ለስብሰባ ወደ ፍሎሪዳ ሲሄድ አብሬው እንድሄድ ጋበዘኝ፡፡ ፍሎሪዳን ለመጀመርያ ጊዜ የማየት ዕድል በማግኘቴ ብቻ ሳይሆን አባና እኔ ብቻችንን ለሽርሽር ስንሄድ የመጀመርያችን በመሆኑ ምክንያት ደስተኛ ነበርኩኝ፡፡

ቀልዶችን እየፈጠርንና ታሪኮችን እየተጨዋወትን ወደ ኦርላንዶ ያደረግነው ጉዞ በእጅጉ አስደሳች ነበር፡፡ በአናቶሚ ክፍለ ጊዜ የነበረውን አስቂኝ ገጠመኝ አጫወትኩት፡፡ እርሱም ደግሞ በባሕር ኃይል ውስጥ የጤና ባለሙያ ሆኖ ሲሰራ በነበረባቸው የመጀመርያዎቹ ዓመታት ያጋጠሙትን አስቂኝ ገጠመኞች ይነግረኝ ነበር፡፡ ከመስከረም አስራ አንዱ የሽብር ጥቃት ወዲህ በነበረው ጥብቅ ቁጥጥር ምክንያት በአየር ማረፍያ ጣብያ ከነበረው ጥብቅ ቁጥጥር ውጪ ፍሎሪዳ እስክንደርስ ድረስ የገጠመን ችግር አልነበረም፡፡ እንደ አባትና ልጅ ከነበረን መቀራረብ በዘለለ የጓደኝነት መንፈስም አዳብረን ነበር፡፡

በዚያን ምሽት በሆቴል ክፍል ውስጥ ሆነን የኢሻ ሰላት በጋራ ከጸለይን በኋላ ወደ መኝታችን ከመሄዳችን በፊት የቀጣዩን ቀን መርሃ ግብራችንን ተነጋገርን፡፡

"ቢሉ ነገ እስከ ረፋድ ድረስ ተኝተህ ከዚያ ሆቴሉ ውስጥ መዝናናት ትችላለህ፡፡ እኔ በጠዋት ወደ ስብሰባ መሄድ ይኖርብኛል፡፡ ከሰዓት በኋላ ጨርሼ ስመለስ አብረን ወደ *ኢፕኮት* ሄደን መዝናናት እንችላለን፡፡"

"አባ አንድ ሐሳብ አለኝ፡፡ እስከ ስብሰባው ቦታ ድረስ ወስጄህ የኪራዩን መኪና ይዤ ብመለስስ? እንደርሱ ከሆነ ኢፕኮት ሲከፈት እሄድና አንተ ደግሞ እዚያው ትመጣለህ፡፡"

"እሺ፣ ነገር ግን እንድታደርሰኝ በጠዋት መነሳት ይኖርብሃል፡፡"

"ችግር የለውም አባ፡፡"

"ቻሎ ቤይታ፡፡ እንዲህ ብለህ ጸልይ፡ *ላላሁማ ቢስሚከ ላሙቱ ወአህያ፡፡"* [115]

ይህ የሦስት ዓመት ልጅ ሳለሁ ጀምሮ አባ ወደ መኝታዬ ሲልከኝ እንድጸልይ ያስተማረኝ ጸሎት ነበር፡፡ ልጆች ለወላጆቻቸው ምን ጊዜም ልጆች ናቸው፡፡

ከጸለይኩኝ በኋላ አንገቱ ስር ሳምኩት፡፡ "አባ እወድሃለሁ፡፡"

"እውነት ነው ትወደኛለህ፤ ልጄ እኮ ነህ፡፡" አባ "እኔም እወድሃለሁ" የሚልበት የተለመደ መንገድ ነበር፡፡ ከዚያ መብራቱን አጠፋ፡፡

ክፍሉ ጭልምልም ብሏል ነገር ግን በመስኩት በኩል የሚገባው አነስተኛ ብርሃን በክፍሉ ውስጥ የሚገኙትን ቁሳቁሶች ለመለየት ያስችል ነበር፡፡ ቀኑን ያሳለፍኩት በደስታና በሳቅ ቢሆንም ልቤ ግን እንዳዘነ ነው፡፡ በቨርጂንያ እንደነበረው ሁሉ በፍሎሪዳም መብራት ሲጠፋ ልቤ እውነተኛውን አምላክ በመፈለግ ሐሳብ መዋተት ጀምሯል፡፡

አባዬ እንቅልፍ እንደወሰደው ካረጋገጥኩኝ በኋላ ከብርድልብሱ ስር በመውጣት ወደ አልጋው ጠርዝ ሸርተት ብዬ በመንበርከክ ማንነቱን እንዲገልጥልኝ በእንባ መማፀን ጀመርኩኝ፡፡ ብዙ ነገር እንደማውቅ አስብ የነበረ ቢሆንም ነገር ግን ምንም እንደማላውቅ ተረድቻለሁ፡፡ እግዚአብሔር እውነቱን እንዲገልጥልኝ ያስፈልገኛል፡፡ ያለ እርሱ እርዳታ ምንም ማድረግ አልችልም፡፡ በግራ መጋባት ውስጥ ሆኜም መቀጠል አልፈልግም፡፡

በሕይወቴ ውስጥ በተዋረደ መንፈስ ሆኜ በፊቱ የቀረብኩበት ጊዜ ቢኖር ያ ጊዜ ነበር፡፡ ህልም ወይም ራዕይ እንዲያሳየኝ አጥበቄ ለመንኩት፡፡

በዚያው ቅፅበት ክፍሉ በጨለማ ተዋጠ፡፡ በፊቴ ባለው ጥቁር ጨለማ ላይ አፈጠጥኩኝ፡፡ ከፊቴ ጥቂት ስንዝሮች ላይ ግድግዳ ቢኖርም ነገር ግን አሁን የለም፡፡ በዚህ ምትክ ያየሁት ነገር ቢኖር በመቶዎች በሚቆጠሩ መስቀሎች የተሞላ መስክ ነበር፡፡ በዙርያቸው ከሚገኘው ድንግዝግዝታ በተፃራሪ የብርሃን ጨረሮችን ይፈነጥቁ ነበር፡፡

እምባዬ ቆመ፡፡ ሰውነቴ ተዝለፈለፈ፡፡ ጊዜም የቆመ ይመስል ነበር፡፡ መስቀሎቹን ለመቁጠር ሞከርኩኝ ነገር ግን ከቁጥር በላይ ነበሩ፡፡ ራዕዩ ፈጥኖ እንደመጣ ሁሉ ፈጥኖ ተሰወረ፡፡ ወደ ሆቴሉ ክፍል ተመልሼ የአልጋው ጠርዝ ላይ ነበርኩኝ፡፡

በዝምታ ተውጬ የያሁትን ነገር ማሰላሰል ጀመርኩኝ፡፡ ከአፍታ በኋላ ወደ ሰማይ ተመልክቼ "እግዚአብሔር ሆይ ያ ከቁጥር የሚገባ አይደለም!" አልኩኝ፡፡

የልቤ ግማሽ ክፍል እንዲህ እያለ ይጠይቃል "እግዚአብሔር ራሱን ገልጦልኝ ይሆንን? ለጸሎቴ መልስ ሰጥቶኝ ይሆንን? በመስቀሎች የተሞላ መስክ ነው የታየኝ፡፡ ይህ ማለት ወንጌልን እንድቀበል እየነገረኝ ነው ማለት ነው፡፡"

ሌላው የልቤ ግማሽ ደግሞ የሰይጣንን ድርሻ በመውሰድ እንዲህ እያለ ይሞግተኛል "ነቢል በዚህ ጉዳይ ላይ ስህተት የምትሰራ ከሆነ አላህ ለዘላለም ወደ ገሃነም ይልክሃል፡፡ ከክርስትና ሽርክ፣ መድብለ አማልክታዊነት ጋር እየተጫወትክ ስለሆነ ሰይጣን ግራ ሊያጋባህ ይህንን እያደረገ ይሆናል፡፡"

የበለጠ ምክንያታዊ የሆነው የአእምሮዬ ክፍል ደግሞ እንዲህ እያለ ይነግረኛል "ምናልባት የታየህ ምስል ከድካም የተነሳ አእምሮህ የፈጠረው ሊሆን ይችላል፡፡ የሕይወትህን ትልቁ ውሳኔ በአንድ ቅዠት በሚመስል አጋጣሚ ላይ መመስረት ትፈልጋለህን? ለዚህ ነገር ብለህ ሁሉንም ነገር መስዋዕት ለማድረግ ዝግጁ ነህ?"

የክፍሉ ጥግ ላይ ባለው አልጋ ላይ ተኝቶ በስሱ የሚያንኮራፋውን አባን ተመለከትኩት፡፡ በመጨረሻ እንዲህ ብዬ ወሰንኩኝ "አይሆንም፣ በዚህ ላይ ብቻ ተመስርቼ ከእርሱ መለየት አልችልም፡፡ እግዚአብሔር ይህንን ይረዳልኛል፡፡ የተሻለ ማስረጃ ያስፈልገኛል፡፡"

እፍረት ቢሰማኝም ነገር ግን ወደ እግዚአብሔር እንዲህ ብዬ ጸለይኩኝ፤ "እግዚአብሔር ሆይ ያ ከቁጥር የሚገባ አይደለም! ያየሁት ነገር እውነት ይሁን አይሁን አላውቅም፡፡ ሳይታወቀኝ ክርስቲያን የመሆን ፍላጎት አድሮብኝ አእምሮዬ ያንን ምስል ፈጥሮ ይሆናል፡፡ ራዕይ እንድታሳየኝ በመጠየቄ ይቅር በለኝ ነገር ግን ህልም ስጠኝ፡፡ ህልሙ ራዕዩን የሚያረጋግጥ ከሆነ ክርስቲያን እሆናለሁ፡፡"

በእርግጥ ሳይታወቀኝ ሊቀር የማይችለውን ጉዳይ እየተጋፋሁ ነበር ነገር ግን እግዚአብሔር ያ እንዲሆን አልፈቀደም፡፡ በዚያኑ ዕለት ህልም ሰጠኝ፡፡

*በሊበርቲ ዩኒቨርሲቲ የጥናትና ምርምር ፕሮፌሰር በሆኑት በዶ/ር ጌሪ ሀበርማስ ስለ እመነትና ጥርጣሬ የተጻፈውን የሊቅ አስተዋፅዖ ለማንበብ contributions.NabeelQureshi.com ይጎብኙ፡፡*

ክፍል ፲

# በእግዚአብሔር እጅ መመራት

*ማየት እችል ዘንድ ዓይኖቼን ክፈትልኝ፡፡ ውዱ አምላኬ ሆይ እሄድበት ዘንድ መንገድህ የትኛው እንደሆነ አመልክተኝ፡፡*

# ህልሞችን መተርጎም

አባዬን የስብሰባው ቦታ ሳደርሰው ገና ጎህ አልቀደደም ነበር፡፡ ኢፐከት ከመከፈቱ በፊት ትንሽ ጊዜ ስለሚቀር ወደ ሆቴል ክፍላችን ተመልሼ ለማረፍ ወሰንኩኝ፡፡ ከጥቂት ሰዓታት በኋላ ዓይኖቼ በድንጋጤ ተከፈቱ፤ ልቤም በፍጥነት ይመታ ነበር፡፡

እግዚአብሔር ህልም አሳየኝ፡፡ ነገር ግን ትርጉሙ ምን እንደሆነ አላውቅም ነበር፡፡

የዚህ ህልም ጥራት ከዚህ ቀደም ካየኋቸው ሁሉ የተለየ ነበር፡፡ በህልሙ ውስጥ ሆኜ እንኳን ከእግዚአብሔር የሆነ መልዕክት መሆኑ ይታወቀኝ ነበር፡፡ እንዴት እንደሆነ ባይገባኝም ዝም ብሎ ብቻ ይታወቀኝ ነበር፡፡ ነገር ግን ህልሙ ለየት ያለና በማላውቃቸው ትዕምርቶች የተሞላ ነበር፡፡

ከነቃሁ በኋላ የህልሙን እያንዳንዱን ዝርዝር በግልፅ አስታውስ ነበር፡፡ እንደ ሌሎቹ ህልሞች በብዥታዎች የታጠረ አልነበረም፡፡

በአእምሮዬ የትውስታ መዝገብ የተመዘገበ መሆኑን ባውቅም ነገር ግን እንዳይረሳኝ በሚል እያንዳንዱን ዝርዝር በማስታወሻዬ ላይ አሰፈርኩት፡፡ የሚከተለው በዕለቱ የጻፍኩት ነበር፡-

> በህልሙ መጀመርያ ላይ መርዛማ የሆነ ቀይ እባብ ታየኝ፡፡ ቀዩ ቀለም በቀጫጭን ነጫጭ ሸንተረሮች የተከፋፈለ ነበር፡፡ ሰዎች አጥሩ ውስጥ ለመግባት ሲሞክሩ የማፏጨት ድምፅ ያሰማ ነበር፡፡ በርቀት ላይ ስለሚገኝና በዓለት ምሰሶ ላይ ስለተጠመጠመ በአጥሩ ወስጥ የነበሩት ሰዎች ሊያዩት

አይችሉም ነበር፡፡ ይህ ምሰሶ መተላለፍያ አካባቢ ነበር የሚገኘው፡፡ እስከ ህልሙ አጋማሽ ድረስ የዓለቱ መወጣጫ ላይ ሆኜ ነበር ዙርያ ገባውን ስመለከት የነበረው፡፡

ኮረብቶች፣ አረንጓዴ ሳርና ዛፎች በሚገኙበት ጓሮ መሳይ ውስጥ አስፈሪ ኢጉዋና (ግዙፍ እንሽላሊት) ይታያል፡፡ በዝምታ በማድፈጥና ኮረብታ በመምሰል ተቀምጧል፡፡ ሲረማመዱበት የነበሩ ሰዎች እንሽላሊት መሆኑን አላወቁም ነበር፡፡ እንሽላሊት መሆኑን ቢያውቁ ኖሮ በደነገጡ ነበር ነገር ግን እንሽላሊቱ ማንም ሊያስተውለው ባለመቻሉ ደስተኛ ነበር፡፡ ከዚያ አንድ ዕድሜው ትንሽ ሰውነቱ ግን ግዙፍ የሆነ ብላቴና ሲመጣ አየሁኝ፡፡ ይህ ብላቴና የእንሽላሊቱን ምንነት ያውቅ ነበር፤ ከዚያ እየተረማመደበት እንሽላሊት መሆኑን ይናገር ነበር፡፡ እንስሳውም በመቆጣት ጭራው ላይ ቆሞ የነበረውን ብላቴና ለመንከስ አፉን ከፈተ፡፡

ሊነክሰው ጥቂት ሲቀረው ከብላቴናው ጎን ክሪኬት (አንበጣ መሳይ እንስሳ) ብቅ አለ፡፡ አሁን ያለሁበት ቦታ ተለውጦ ከግዙፉ እንሽላሊት በታች በመሆን ጭንቅላቱን እመለከት ጀመር፡፡ እንሽላሊቱ የአንበጣውን የፍልሚያ ግብዣ ተቀብሎ ወደ ፍልሚያው ሜዳ ሲሄድ ሳለ ወደ እኔ በመዞር አፉን ከፍቶ ሊገድለኝ ፈለገ፡፡ ነገር ግን ሊውጠኝ ሲል አንበጣው ጭንቅላቱን ነክሶ ቆረጠው፡፡

በዚያን ዕለት እስከ ረፋድ ድረስ ህልሙን ሳሰላስል ቆየሁኝ፡፡ ትርጉሙ ምን ይሆን? ትዕምርቶቹ ምንድናቸው? እንዴት ነው አብረው የሚሄዱት?

ምስሎቹን ለማገጣጠም ሞከርኩኝ፡፡

በድንጋይ ምሰሶ ላይ የነበረው እባብ የክፋት ምሳሌ ነው፡፡ ሌላ ምን ሊሆን ይችላል? ግቢው ደግሞ ዓለም ነው፡፡ ዓለምን ከእባቡ ዕይታ አቅጣጫ ማየቴ ከፍጥረቴ የሆነ የተደበቀ ክፋት በውስጤ መኖሩን ያሳያል፡፡ ይህ ደግሞ

ከክርስትና የውርስ ኃጢአት ፅንሰ ሐሳብ ጋር እንደሚገጥም ተከሰተልኝ፡፡ በሌላ ወገን ደግሞ ከመጀመርያው ጀምሮ በውስጤ የነበረው እስልምና ክፉት ነው ማለት ይሆን? እርግጠኛ አይደለሁም ነገር ግን ሁለቱም ወደ ክርስትና የሚጠቁሙ ነው የሚመስሉት፡፡

ዓለምን ስመለከት ሳለሁ ተፈጥሯዊ የመሬት አካል የመሰለው ሌላ ተሳቢ እንስሳ ነው፡፡ የእባቡ አምሳያ ቢሆንም ነገር ግን እጅግ ግዙፍ ከመሆኑ የተነሳ ሰዎች ኮረብታ መስሏቸው ይረማመዱበታል፡፡ ከዚያ አንድ ብላቴና በመምጣት ትክክለኛ ምንነቱን አጋለጠ፡፡ እነዚህ ትዕምርቶች አንድ ማብራርያ ብቻ ነው ያላቸው፤ ብላቴናው ዳዊት ነው፡፡ ኮረብታ የመሰለው ተሳቢ እንስሳ እስልምና ሲሆን ሀሰት መሆኑን አጋልጧል፡፡ በተሳቢ እንስሳው የተመሰለው እስልምና በማታለልና በማጭበርበር ሰዎች የዓለም ተፈጥሯዊ አካል እንደሆነ እንዲያስቡ አድርጓል፡፡

ከብላቴናው ጎን ብቅ ያለው አንበጣ መሳይ እንስሳ እስልምናን የተገዳደረው ክርስትና መሆን አለበት፡፡ አንበጣው መናገር መቻሉና ግዙፉ እንሽላሊት መናገር ያለመቻሉ ክርስትና ስለ ራሱ ማስረጃ ማቅረብ መቻሉን ያመለክታል፡፡ በሌላ አባባል ክርስትና ጠንካራ ማስረጃ አለው ማለት ነው፡፡ ግዙፉ እንሽላሊት መናገር አለመቻሉ ማስረጃ እንደሌለው ያሳያል፡፡ አንበጣው እንሽላሊቱን ለግጥሚያ ሲጋብዘው ከመግጠም ይልቅ እኔን ለመግደል መፈለጉ ይህንን ይጠቁማል፡፡

ግዙፉ እንሽላሊት ሊገድለኝ ሲሞክር አንበጣው አተረፈኝ፡፡ ይህ በራሴ ጥረት የማላገኘውን ደህንነት እንደሚያመለክት ተከሰተልኝ፡፡ ይህ ደግሞ ሌላ የክርስትና ፅንሰ ሐሳብ ነው፡፡

ህልሙ ሌላ ትርጉም ይኖረው እንደሆን ብዬ ደግሜ ደጋግሜ አሰላሰልኩት ነገር ግን ከዚህ የተሻለ ማብራርያ ላገኝ አልቻልኩኝም፡፡ ነገር ግን ይህ አተረጓጎም ለክርስትና ያደላ

በመሆኑ ያን ያህል አልተማመንኩበትም፡፡ በውስጤ የነበረውን ትግል ሳልገልጥ የህልሙን ትርጉም የማገኝበትን መንገድ ማሰብ ጀመርኩኝ፡፡

ሰዎችን ለማማከር ወሰንኩኝ፡፡ ወደ ኢፒከት ገብቼ በአየር ላይ የሚንሳፈፈውን ሉል እየተመለከትኩኝ ለዳዊት ደወልኩለት፡፡

“ነቢል፣ ስጠብቅህ ተከስተሃል! ምን አዲስ ነገር አለ? ፍሎሪዳ እንዴት ናት?”

ይህ ስለ እንቶ ፈንቶ የሚወራበት ጊዜ አይደለም፡፡ “መጥፎ አይደለችም፡፡ እየተዝናናሁ ነው፡፡ አደዋወሌ ጥያቄ ልጠይቅህ ነበር፡፡ ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር ዘንድ ህልም ይሰጣቸዋል?”

ዳዊት ፈጣን አእምሮ አለው፡፡ “ምነው? የሆነ ነገር አይተሃል እንዴ?”

“የሆነ ነገር አይቻለሁ አልወጣኝም፡፡ ዝም ብለህ ጥያቄውን መልስ፡፡”

ዳዊት መልስ ከመስጠቱ በፊት አሰብ አደረገ፡፡ “መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች ከእግዚአብሔር ዘንድ ህልም እንደተሰጣቸው በሚናገሩ ታሪኮች የተሞላ ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል ዮሴፍ፡፡”

“ነቢዩ ዮሴፍ ወይስ የኢየሱስ አሳዳጊ አባት ዮሴፍ?”

እንደመሳቅ አለ፡፡ “ሁለቱም ናቸው፡፡ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የኢየሱስ አሳዳጊ አባት ዮሴፍ ከእግዚአብሔር ዘንድ ግልፅ ትዕዛዛትን ያዘሉ ወደ አምስት ህልሞችን አግኝቷል፡፡ ነገር ግን እኔ እየተናገርኩ ያለሁት ትዕምርታዊ የሆኑ ህልሞችን መፍታት ስለቻለው ስለ ብሉይ ኪዳኑ ዮሴፍ ነው፡፡ እግዚአብሔር ከእስር ቤት የታደገው በዚያ መንገድ ነበር፡፡”

መጽሐፍ ቅዱስ ትዕምርታዊ ህልሞችን ስለመተርጎም ይናራል ማለት ነው? እኔ የምፈልገው ምን ሆነና! “ስለዚህ ዮሴፍ ህልሞችን ይተረጉም የነበረው እንዴት ነበር? ዛሬ ክርስቲያኖች ህልሞችን የሚተረጉሙት እንዴት ነው?”

“ዮሴፍ ከእግዚአብሔር የተሰጠው የመተርጎም ስጦታ ነበረው፡፡ ዛሬ ህልም የሚተረጉሙ ክርስቲያኖች ስለመኖራቸው ምንም የማውቀው ነገር የለኝም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር

ለሰዎች ትርጉም የሚያስፈልገውን ህልም የሚሰጥ ከሆነ የሚተረጎምበትንም መንገድ እንደሚያዘጋጅ አምናለሁ፡፡”

እርሱ የተናገራቸው የመጨረሻዎቹ ቃላት የረሳሁትን ነገር አስታወሱኝ፡፡ እማ አንዳንድ ጊዜ ኢብን ሲሪን በተሰኘ ጥንታዊ የህልም ተርጓሚ የተጻፈውን መጽሐፍ እንደ ማጣቀሻ ትጠቀማለች፡፡ ምናልባት እግዚአብሔር በእርሱ በኩል ይመራኝ ይሆን?

ለእማ ለመደወል በመቻኮል ዳዊትን ፈጥኜ ተሰናበተኩት፡፡

“መልካም፣ አመሰግናለሁ ወዳጄ፡፡ በኋላ እደውልልሃለሁ፡፡”

“የያኸውን ህልም ትነግረኛለህ ወይስ እንዴት ነው?”

“ህልም አይቻለሁ አላልኩም እኮ፡፡”

“አይቻለሁ ብለሃል አላልኩም፡፡ ትነግረኛለህ አትነግረኝም?”

“አዎ እነግርሃለሁ ግን እስኪ አሁን ላስብበት፡፡”

ስልኩን ዘግቼ ፈጠን ብዬ ለእማ ደወልኩላት፡፡ ግራ የሚገባ ነገር ነው፡፡ በህልሙ ውስጥ የሚገኙትን ትዕምርቶች ብቻ ልነግራት ነገር ግን ሙሉውን ታሪክ ላልነግራት ወሰኛለሁ፡፡

“ሄሎ?”

“አሰላሙ አለይኩም እማ፡፡”

“ወአለይኩም አሰላም፡፡ ከአባትህ ጋር ነህ?”

“ኢፐከት ነው ያለሁት፡፡ አባ ከስብሰባ በኋላ ይመጣና ያገኘኛል፡፡ አሁን ብዙ ማውራት አልፈልግም፤ በፓርኩ ውስጥ ዞር ዞር ማለት እፈልጋለሁ፡፡ ነገር ግን ዛሬ ህልም አይቼ ነበር፡፡ የኢብን ሲሪን መጽሐፍ በአቅራብያሽ አለ?”

“የላይኛው ክፍል ነው ያለው፡፡ ህልሙ ምን ነበር?” የእማ ድምፅ ስጋት ይታይበታል፡፡ ይህ ደግሞ እንድረበሽ አድርጎኛል፡፡ ሰዎች ውስጤን ማንበብ መቻላቸው ለምን ይሆን?

“እማ ረጅምና ውስብስብ ነው፤ ነገር ግን የሚያስጨንቅ ነገር የለውም፡፡ እቤት ስመጣ ዝርዝሩን እነግርሻለሁ፡፡ አሁን እንዳስብበት የአንዳንድ ምልክቶችን ትርጉም ማወቅ እፈልጋለሁ፡፡”

“እንደርሱ አይሆንም ቢሉ፡፡ መተርጎም እንድችል ሙሉውን ልትነግረኝ ያስፈልጋል፡፡”

“እማ መጽሐፉ የሚለውን ብቻ ልታነቢልኝ አትችይም? ለራሴ መተርጎም እፈልጋለሁ፡፡”

“ቤይታ መጽሐፉ ብዙ ነገር ነው የሚያወራው፡፡ ትዕምርቶቹ በአውድ ላይ የተመሠረቱ ናቸው፡፡ ቻሎ፣ የመጀመርያውን ምልክት ንገረኝ፡፡”

“እባብ፡፡”

“አስቶጉፍሩላህ!” ደነገጠች፡፡ “ምን ዓይነት ህልም ነው ይሄ?!”

“እማ!”

“እሺ ይሁን፡፡ እባቡ ውኀ ውስጥ ነበር? ተኝቶ ነበር? እየበላ ነበር? ምን እያደረገ ነበር?”

“ለምንድነው እርሱን ማወቅ ያስፈለገው?”

“መጽሐፉ የተለያዩ ነገሮችን ስለሚናገር ነው፡፡ እባብ ማለት አታላይ ወይም መሰሪ ጠላት ማለት ነው፡፡ ነገር ግን እባቡ ሰው ከበላ ወይም አንድ ሰው ወደ እባብነት ከተለወጠ ትርጉሙ ሌላ ነው የሚሆነው፡፡”

የመጨረሻ ንግግሯ ትኩረቴን ሳበው፡፡ እባቡን ካየሁት በኋላ እርሱ ከነበረበት ቦታ ሆኜ ማየት ጀምሬ ነበር፡፡ እኔ ወደ እባብነት ተቀይሬ ይሆን? የቻልኩትን ያህል ጉዳዩን ለማውጠንጠን ሞከርኩኝ፡፡

“ከጠላት ብዙም የተለየ ትርጉም አይኖረውም አይደል? አንድ ሰው ወደ እባብነት ቢቀየር ትርጉሙ ምንድነው?”

እማ መለሰች “ያ ሰው ኃይማኖቱን በመጠራጠር ውስጥ ነው ማለት ነው፡፡”

ልቤ ቀጥ ያለ መሰለኝ፡፡ የሰማሁትን ነገር ማመን ተሳነኝ፡፡የበለጠ ለማወቅ ጥያቄ አስከተልኩኝ "እባቡ ምሰሶ ላይ ነበር፡፡ ምን ማለት ነው?"

ከዝያ ቦታውን ፈልጋ በማውጣት እንዲህ ብላ አነበበችልኝ፡- "ምሰሶ የአንድ ሰው ሃይማኖት ነው፡፡" ነገሩ ከጠበኩት በላይ ሆኖብኛል፡፡ አእምሮዬን እያነበበችው ይሆን? ቀጠለች፡- "ምሰሶው ከምን እንደተሰራ ታስታውሳለህ?"

"ከድንጋይ ነው፡፡"

ለአፍታ ዝም አለች፡፡ "ይህ የተለየ ነው… የጠበኩት አይደለም፡፡ መጽሐፉ እንደሚለው ከሆነ የድንጋይ ምሰሶ ማለት የአንድ ሰው ሃይማኖት ነው ወይም ደግሞ ዓለምን የሚመለከቱበት መንገድ በፍጥነት እየተለወጠ ነው ማለት ነው፡፡"

የምሰማውን ነገር ማመን ተሳነኝ፡፡ እያንዳንዱ ምልክት እኔ ያለሁበትን ሁኔታ የሚናገር ነው የመሰለኝ፡፡ ትዕምርቶቹን በዚህ መጽሐፍ ላይ ተመስርቼ እንድፈታ እግዚአብሔር እንደፈለገ እርግጠኛ ሆኛለሁ፡፡

"እሺ እማ ይህ በቂ ነው፡፡ ኢጉዋናስ ምንድነው?"

"ምንድነው እሱ?"

"ትልቅ እንሽላሊት መሳይ ተሳቢ እንስሳ ነው፡፡"

የመጽሐፉን ገፆች ካገላበጠችና ምልክቶቹን ካጣራች በኋላ *ትልቅ እንሽላሊት* በሚል ርዕስ ስር የሚከተለውን አገኘች፡- "ግዙፍና አስፈሪ የሚመስል ጨካኝና የተደበቀ ጠላት ማለት ሲሆን ነገር ግን ፊት ለፊት ከተጋፈጡት ማስረጃ ማቅረብ ስለማይችል በቀላሉ ይሸነፋል፡፡"

መደመም ያዘኝ፡፡ እውነት ይህ ሁሉ በመጽሐፉ ላይ ተጽፏል? ስለ እስልምና የነበረኝ ስጋት ተመሳሳይ ሲሆን ያንን ምልክት የተረጎምኩት በዚያው መንገድ ነበር፡፡

በተጨማሪም በህልሙ ውስጥ ኢጉዋናው በማታለል ራሱን የሰወረ ሲሆን ስለ ራሱ ምንም መናገር አልቻለም ነበር፡፡ "ብላቴናስ ምን የሆን?"

"ምን ዓይነት ልጅ? አዲስ የተወለደ? ትንሽ ልጅ? ወጣት?"

"ትንሽ ልጅ" አልኩኝ ፈጠን ብዬ፡፡ እግዚአብሔር እየነገረኝ ያለውን ነገር አንድ ላይ ለመገጣጠም ቸኩዬ ነበር፡፡ "በሰውነት ግዝፈት ሳይሆን በዕድሜ ትንሽ የሆነ ልጅ፡፡"

"በህልም ትንሽ ልጅ ማለት ጠላትህን እንድታሸንፍ የሚረዳህ ጓደኛ ማለት ነው፡፡ መልካሙን የምሥራች የያዘ ነው፡፡"

የምስራች? ይህ ወንጌል የሚለው ቃል ቀጥተኛ ትርጉም ነው! ዳዊት ወንጌሉን ይዞ ወደ እኔ የመጣ ጓደኛዬ ነው፡፡ ጠላትን ማሸነፍ? በህልሜ ብላቴናው እንሽላሊቱን እንዳሸንፍ እረድቶኛል፡፡ አእምሮዬ መታመስ ጀመረ፡፡

"ቆይ እስኪ" እማ ቀጠለች፡፡ "ልጁ መልከ መልካም ነበር?"

"አዎ፣ በጣም ቆንጆ ነበር፡፡"

"ይህ ጓደኛህ ጠላቶችህን እንድታሸንፍ ብቻ አይደለም የሚረዳህ፤ የምትፈልገውን ነገር ይሰጥሃል፡፡ የተትረፈረፈ ሕይወት እንድትኖር የሚያስችልህን ነገር ይሰጥሃል፡፡"

እዚህ ጋ ስደርስ መናገር እየተሰነኘ መጣ፡፡ "እማ የመጨረሻ፡፡ ክሪኬት፡፡"

"የክሪኬት በትር ወይስ የክሪኬት ኳስ?"

"ጫወታውን አይደለም እያልኩ ያለሁት፡፡ ክሪኬት፣ አንበጣ መሳዩን እንስሳ ለማለት ነው፡፡"

እንደ ኢጉዋና ሁሉ ምልክቱ በመጽሐፉ ውስጥ አልተጠቀሰም ነገር ግን ተቀራራቢ የሆነ ነገር *አንበጣ* በሚል ርዕስ ስር አገኘች፡፡ "አንበጣ ወታደር የሚል ርዕስ አለ"፡፡ አሁንም ትርጉሙ ከህልሙ ጋር በትክክል ይገጥማል፡፡ "ጎድቶሃል?"

“አይ አልጎዳኝም ነገር ግን ጠላቴን ነው የጎዳው፡፡”

“አንተን ካልጎዳህ ደስታን የሚሰጥህ ተዋጊ ነው ማለት ነው፡፡ ደግሞም ጠላቶችህን እንድታሸንፍ ይረዳሃል ማለት ነው፡፡ ቤይታ ያየኸው ህልም ምን እንደሆነ ባላውቅም ትዕምርቶቹ ተያያዥ ናቸው፡፡ ይህ ህልም ከአላህ ዘንድ ይመስለኛል፡፡”

“እቻ፣ እማ፡፡ ጽፌዋለሁ፡፡ እቤት ስመጣ ያንቺን ትርጉም ትነግሪኛለሽ፡፡ በቃ እማ ፓርኩ ከመጨናነቁ በፊት መሄድ ይኖርብኛል!”

“እሺ ቤይታ ዘና በል፡፡ አባ ሲመጣ ደውልልኝ፡፡

“እቻ፡፡”

“ወይም ደግሞ በጣም የሚቆይ ከሆነ ደውልልኝ፡፡”

“እቻ፡፡”

“በቃ ዝም ብለህ ብቻ ደውልልኝ፡፡”

“እቻ እማ፡፡ እወድሻለሁ፡፡ ኹዳ ሐፊዝ፡፡”

ስልኩን ከዘጋሁት በኋላ የሰማኋቸውን ነገሮች ሳስብ ከአእምሮዬ በላይ ሆነብኝ፡፡ እያንዳንዱ ምስል አንድ ላይ የሚገጥም ሲሆን ህልሙን ካየሁ ከአፍታ በኋላ ከሰጠሁት ፍቺ ጋር በማይታመን ሁኔታ በእጅጉ ይገጥማል፡፡ነገር ግን የሰይጣን ወገን ማንሾካሾክ ጀመረ፡፡ በትክክል ባልገጠሙት ሁለቱ ትዕምርቶች ላይ አተኮርኩኝ፡፡ እንሽላሊት አልነበረም ነገር ግን ኢጉዋና የተሰኘ እንሽላሊት መሳይ ተሳቢ ነው፡፡ አንበጣ አልነበረም ነገር ግን ክሪኬት የተሰኘ አንበጣ መሳይ እንስሳ ነው፡፡ ሁሉም ምስሎች በትክክል ሲገጥሙ እነዚህ ለምንድነው በትክክል ከመግጠም ይልቅ የተጠጋጉት?

በአእምሮዬ ውስጥ ቃላቱን ቀያይሬ ለማንበብ ሞከርኩኝ፡፡ ኢጉዋና፡፡ ክሪኬት፡፡ ኢጉዋና፡፡ ክር... ኢ..... ክር... ኢ.... ክርስቲያኒቲ፡፡ ኢስላም፡፡አይ ሊሆን አይችልም፡፡ በጣም ተለጥጧል፡፡ ይህንን ጉዳይ ተረጋግቼ ማሰላሰል ይኖርብኛል፡፡

# ጠባቡ በር

ህልሙን እያሰላሰልኩኝ ሁለት ወራት ያህል አለፉ፡፡ በእያንዳንዱ ቀን የዲያብሎስ ወገን ድምፅ በአእምሮዬ ውስጥ እየጎላ ይመጣ ነበር፡፡ ሕይወቴንና የዘላለም እጣ ፋንታዬን በህልም ላይ ብቻ ተመስርቼ መወሰን ይኖርብኛለን? በአንድ ህልም ላይ ብቻ? ያ ህልም ደግሞ በምልክቶች ከመሞላቱ የተነሳ ኢብን ሲሪንና ዮሴፍ እንዲፈቱልኝ አስፈለገ እኮ፡፡

ምናልባት ህልሙን ለክርስትና በማድላት የተረጎምኩት ሳይታወቀኝ ክርስትና እውነት እንዲሆን ጉጉት አድሮብኝ ይሆንን? ምናልባት ደግሞ እስልምና ትክክል እንዲሆን መመኘቴን አይቶ ሰይጣን ወደ ዘላለም ጥፋት ሊወስደኝ እያታለለኝ ይሆንን? በሆቴሉ ክፍል ውስጥ እንደነበረው ራዕይ ሁሉ ህልሙም አወዛጋቢ ከመሆኑ የተነሳ በተለያዩ መንገዶች ላብራራው እችላለሁ፡፡

ህልሙን ለእማ ነገርኳት፡፡ እርሷም ምልክቶቹ እንዴት አብረው ሊሄዱ እንደሚችሉ እንዳልገባት ነገር ግን አላህ በእስልምና ላይ ያለኝን መተማመን ከፍ ለማድረግ ህልሙን እንዳሳየኝ ነገረችኝ፡፡ ራዕዩንና ህልሙን ለዳዊት ስነግረው ደግሞ ወደ ክርስትና የሚመሩኝ ስለመሆናቸው ጥርጥር እንደሌለው ነገረኝ፡፡

እነዚህ ሁሉ ሐሳቦች በአእምሮዬ ውስጥ ተደበላልቀው ስላወኩኝ እግዚአብሔር ሌላ ህልምም ሆነ ራዕይ እንዲሰጠኝ ለመጠየቅ ድፍረት አልነበረኝም፡፡ ከሁለቱም ወገን አንዳንድ እንደሰጠኝ በልቤ ውስጥ ባውቅም ነገር ግን ትርጉማቸው ምን እንደሆነ እርግጠኛ ለመሆን የምችልበት ሁኔታ ውስጥ አልነበርኩም፡፡ በውስጤ ያሉት ተቃራኒ

ኃይላት፣ እርግጠኝነት ማጣትና ልከፍለው ያለሁት ዋጋ እየተፈራረቁ በእጅጉ አድክመውኝ ነበር፡፡

ሽባ ልሆን ምንም አልቀረኝም ነበር፡፡

ዳዊት በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስለተጠቀሰው ዮሴፍ የተናገረው ነገር ትዝ አለኝ፡፡ እግዚአብሔር "ግልፅ የሆኑ መመርያዎችን" በህልሞች በኩል ሰጥቶት ነበር፡፡ እኔ የምፈልገው እንደርሱ ዓይነቱን መመርያ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ሊመራኝ ከፈለገ ለእንደ እኔ ዓይነቱ የተሰበረ ተጠራጣሪ የበለጠ ግልፅ የሆነ መመርያ እንደሚያስፈልገው ያውቃል፡፡

"ሦስት" አልኩኝ ለራሴ፡፡ "አላህ ጎደሎ ቁጥሮችን ይወዳል፡፡ የክርስቲያኖች አምላክ ደግሞ ሥሉስ ነው፡፡[116] ለምን ሦስት ህልሞችን አልጠይቅም?" ስለዚህ ግልፅ ጥያቄ በመያዝ ወደ አላህ ጸለይኩኝ፡፡

"ከአንድ ህልም ይልቅ እባክህን ሦስት ህልሞችን ስጠኝ፡፡ ሁሉም ወደ ክርስትና የሚጠቁሙኝ ከሆነ ክርስቲያን እሆናለሁ፡፡ እባክህን ጌታ ሆይ እራራልኝ፡፡ ቀጣዩን ህልም ትርጉም የማይሻ ቀላል ህልም አድርግልኝ፡፡"

ማርች 11፣ 2005 ማለዳ ላይ በወረቀት ላይ ላሰፍረው የምችለውን ህልም አገኘሁኝ፡፡

> ከጡብ በተሰራ ጊድጊዳ ላይ በሚገኝ ጠባብ በር ፊት ቆሜያለሁ፡፡ ወደ ውስጥ አልገባሁም ነገር ግን ከፊቱ ቆሜያለሁ፡፡ የበሩ መዝጊያ ሳንቃ ነገር ነው፡፡ መግቢያው ሰባት ተኩል ጫማ ያህል ከፍ ያለ እንደሆነ እገምታለሁ፡፡ ስድስት ተኩል ጫማ ያህል ደግሞ ከመሬት ወደላይ ከፍ ብሏል፡፡ አንድ ጫማ ያህል የሚሆን ቆልመም ያለ መቃን ዓይነት ከላይ በኩል አለው፡፡ ስፋቱ ከሦስት ጫማ በጥቂት ያነሰ ሲሆን ወርዱ ደግሞ ሦስት ወይም አራት ጫማ ያህል ይሆናል፡፡ ዙርያው ሙሉ በሙሉ በጡብ የተከበበ ነው፡፡ ብዙ ሰዎች በሚያዩጉ ምግቦች በተሞላ ጠረጴዛ ዙርያ ተሰብስበው ወዳሉበት ክፍል የሚያስገባ በር

ነው፡፡ ሰላጣዎች መኖራቸውን የማስታውስ ይመስለኛል ነገር ግን እርግጠኛ ሆኜ መናገር አልችልም፡፡ እየበሉ አይደለም ነገር ግን ከግብዣው በፊት የክብር እንግዳ የሚጠብቁ ይመስል ከእኔ በስተግራ በኩል ይመለከታሉ፡፡ በክፍሉ ውስጥ ከሚገኙ ሰዎች መካከል አንዱ ዴቪድ ውድ (ዳዊት) ነው፡፡ ዳዊት በሩ ላይ ተቀምጦ መንገድ መተላለፍያውን ስለዘጋው መግባት አልቻልኩኝም፡፡ በጠረጴዛው አጠገብ ተቀምጧል ነገር ግን ወደ እኔ ግራ አቅጣጫ እየተመለከተ ነው፡፡ “አንድ ላይ የምንበላ መስሎኝ ነበር?” ብዬ ጠየቅሁት፡፡ ዓይኖቹን ከበሩ ላይ ሳይነቅል “ምላሽ ለመስጠት ፍቃደኛ አልሆንኩም” አለኝ፡፡

ህልሙን ጨርሼ ስነቃ ትርጉሙ ወዲያውኑ ተከሰተለኝ፡፡ ክፍሉ ሰማይ ነው፡፡ ድግሱ በመንግሥተ ሰማያት የተደረገ ሲሆን ሰርግ ዓይነት ነው፡፡ ወደ ክፍሉ መግባት እችል ዘንድ የዳዊትን ግብዣ መቀበል ይኖርብኛል፡፡

ስለ ህልሙ ያልገባኝ አንድ ነገር ቢኖር በሩ ነው፡፡ በህልሙ ውስጥ ከሚገኙት ትዕይንቶች ሁሉ ቀልብ የሚስበው እርሱ ነው ነገር ግን ትርጉሙ ምን ይሆን? ለምንድነው እርሱ ከሁሉም በላይ ግልፅ የሆነው? ደግሞስ ለምንድነው ጠባብ የሆነው?

አሁን ደርሳ እማ ስለ ህልሞች በምጠይቀው ጥያቄ ጥርጣሬ አድሮባታል፡፡ ይኸኛው ደግሞ ዳዊትን ስላካተተ ትርጉሙ ምን ሊሆን እንደሚችል ልጠይቃት አልችልም፡፡ ዳዊት ምን እንደሚል ለማወቅ ደወልኩለት፡፡

“ነቢል ይህ ህልም ግልፅ ከመሆኑ የተነሳ ምንም ትርጉም አያሻውም፡፡” የተናገራቸው ቃላት ከጥቂት ቀናት በፊት ወደ እግዚአብሔር የጸይኩትን ጸሎት አስታወሰኝ፡፡ ምን ለማለት እንደፈለገ ግልፅ እንዲያደርግልኝ ስጠይቀው ሉቃስ 13፡22ን እንዳነብ ነገረኝ፡፡

በአባዬ ኪንግ ጀምስ ቅጂ ፋንታ ባለፈው ዓመት ዳዊት እንደ ስጦታ ያበረከተልኝን ባለ ማጥኛ መጽሐፍ ቅዱስ ገለጥኩኝ፡፡ እስከዚያች ቀን ድረስ ከፍቼው አላውቅም ነበር፡፡ የዞንደርቫን ኤን አይ ቪ መጽሐፍ ቅዱስ ነበር፡፡ ክፍሉን ስገልጠው ጎላ ባሉ ፊደላት የተጻፈ “ጠባቡ በር” የሚል ርዕስ ተመለከትኩኝ፡፡

ልቤ አንድ ምት ወደፊት ዘለለች፡፡ ከዚህ ቀደም ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አይቼ አላውቅም ነበር፡፡ በጥንቃቄ ደግሜ ደጋግሜ አነበብኩት፡፡

> ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄድ ከተማዎችንና መንደሮችን እያስተማረ ያልፍ ነበር፡፡አንድ ሰውም፡- ጌታ ሆይ፥ የሚድኑ ጥቂቶች ናቸውን? አለው፡፡ እርሱም እንዲህ አላቸው፡- በጠበበው በር ለመግባት ተጋደሉ፤ እላችኋለሁና፥ ብዙዎች ሊገቡ ይፈልጋሉ አይችሉምም፡፡ ባለቤቱ ተነሥቶ በሩን ከቈለፈ በኋላ፥ እናንተ በውጭ ቆማችሁ፡- ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ ክፈትልን እያላችሁ በሩን ልታንኳኩ ትጀምራላችሁ እርሱም መልሶ፡- ከወዴት እንደ ሆናችሁ አላውቃችሁም ይላችኋል...
>
> አብርሃምንና ይስሐቅን ያዕቆብንም ነቢያትንም ሁሉ በእግዚአብሔር መንግሥት ባያችሁ ጊዜ፥ እናንተ ግን ወደ ውጭ ተጥላችሁ ስትቀሩ፥ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል፡፡ ከምሥራቅና ከምዕራብም ከሰሜንና ከደቡብም ይመጣሉ፥ በእግዚአብሔርም መንግሥት በማዕድ ይቀመጣሉ፡፡”[117]

ማንበብ አቁሜ መጽሐፉን አስቀመጥኩት፡፡ መደመም ይዞኛል፡፡ እግዚአብሔር ትርጉም የማያስፈልገውን ግልፅ ህልም አሳይቶኛል፡፡ ይህ ትርጉም ለሁለት ሺህ ዓመታት ያህል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰፍሯል፡፡ጠባቡ በር ወደ ደህንነት የሚያስገባ በር ነው፡፡ ወደ እርሱ ለመግባት የተቻለኝን ሁሉ እንዳደርግ ኢየሱስ እየነገረኝ ነው፡፡ በመንግሥተ ሰማያት ማዕድ ተቀምጬ መካፈል እንድችል ለዳዊት ግብዣ ምላሽ መስጠት እንዳለብኝ ከህልሙ ተረድቻለሁ፡፡ ምላሽ ካልሰጠሁ በውጪ ቆሜ ወደ ውስጥ ለመግባት ብለምን መግባት አይቻለኝም፡፡

በደህንነት ጠባብ በር ላይ ቆሜ ወደ ውስጥ ለመግባት ለምን እንዳልተፈቀደልኝ ግራ ገብቶኛል፡፡ ደስ የሚለው ነገር የቤቱ ጌታ በመምጣት በሩን አልዘጋብኝም፡፡

አሁን ያልተመለሰልኝ ጥያቄ የለም፡፡ ምን ማድረግ እንዳለብኝ አውቄያለሁ፡፡ ግብዣውን መቀበል ይኖርብኛል፡፡

# ከመስጊድ የሚያስወጣው ቀጥተኛ መንገድ

ሦስት ህልሞችን የጠየኩ ሲሆን እግዚአብሔር ከመታመን የሚያልፈውን ቸርነቱን አሳየኝ፡፡ ኤፕሪል 24፣ 2005 ረፋድ ላይ ሦስተኛውን ህልም አገኘሁኝ፡፡

> ነጫጭ ደረጃዎች ባሉት መስጊድ ውስጥ በመጀመርያው ደረጃ ላይ ተቀምጫለሁ፡፡ ደረጃዎቹ ማስጌጫዎች ያሏቸው ሲሆን ወደ ግራ አቅጣጫ የተጠመዘዙ የእጅ መያዣዎች አሏቸው፡፡ ደረጃዎቹ የተሠሩበትን ቁስ አላስታውስም ነገር ግን ከእብነ በረድ ወይም ከእንጨት የተሰሩ እንደሆኑ እገምታለሁ፡፡ የደረጃው ጫፍ ላይ ፊቴን አዙሬ ተቀምጫለሁ፡፡ በዚህ ህልም ውስጥ ሆኜ ከእኔ በስተቀኝ ካለው አቅጣጫ ራሴውኑ መልሼ እመለከት ነበር፡፡ በደረጃው ላይ ተቀምጬ ከእንጨት ወደተሰራው ቡናማ ምስባክ እየተመለከትኩኝ የሆነ ሰው ንግግር እንዲያደርግ እየተጠባበኩ ያለሁ ይመስለኛል፡፡ ክፍሉ አረንጓዴ ምንጣፍ ያለው ሲሆን ሰዎች እዚያ ላይ እንዲቀመጡ ይጠበቅባቸዋል፡፡ እኔ ግን ደረጃው ላይ መቀመጤ ምንም ችግር እንደሌለው ይሰማኝ ነበር፡፡ እኔ ከተቀመጥኩበት ደረጃ በስተግራ ባለው ክፍት ቦታ ሰዎች መጥተው እንዲቀመጡ እጠባበቅ ነበር፡፡ በክፍሉ በስተቀኝ በኩል ምንም እንቅስቃሴ አልነበረም፡፡
>
> ክፍሉ ቀስ በቀስ እየሞላ ሲመጣ ኢማሙ በስተግረዬ በኩል ወደ ኋላ ትንሽ ፈንጠር ብሎ ወለሉ ላይ ተቀምጧል፡፡ ነጭ ልብስ ለብሶ እንደ ሌሎቹ ሰዎቸ ሁሉ እርሱም ተናጋሪውን ይጠባበቅ ነበር፡፡ እኔ ስጠባበቅ የነበረው እርሱን

ሲሆን ቅዱስ ሰው ሆኖ እንደማንኛውም ሰው ከእኔ ኋላ በወለል ላይ መቀመጡ አስገርሞኛል ደግሞም ግራ ገብቶኛል፡፡ አክብሮቴን ለማሳየት ከደረጃው ላይ ወርጄ ከእርሱ በስተ ጀርባ ወለሉ ላይ ልቀመጥ ብፈልግም ነገር ግን ካለሁበት መነሳት አልቻልኩኝም፡፡ በሆነ በማይታይ መግነጢሳዊ ኃይል ከተቀመጥኩበት ቦታ ጋር የተሰፋሁ መስሎ ይሰማኝ ነበር፡፡ ይህ ኃይል ምቾት በመንሳት ጨምቆ የሚይዝ ዓይነት ባይሆንም ነገር ግን እንደ ፈለኩ እንድሆን የሚፈቀድ ዓይነት አልነበረም፡፡ ወለሉ ላይ አጣብቆ ይዞኛል፡፡

ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም ነበር፡፡ ክፍሉ ውስጥ የነበሩት ሰዎች ምን እንደሚጠባበቁ አላውቅም ነበር፡፡ ተናጋሪው ማን ሊሆን እንደሚችል ምንም የማውቀው ነገር አልነበረኝም፡፡ በእንደህ ዓይነት ግራ መጋባት ውስጥ ሆኜ ህልሙ ተጠናቀቀ፡፡

ለእኔ ህልሙ ግልፅ መልዕክት ያለው ነው፡፡ ከመስጊድ በሚያስወጣው ደረጃ ላይ ተቀምጫለሁ፡፡ ከዚህ ቀደም የማከብራቸው ሙስሊሞች ከእኔ በታችና ከእኔ ኋላ ተቀምጠዋል፡፡ አክብሮት ላሳያቸው ብሞክርም ከእነርሱ ኋላ ባለው የቀድሞ ቦታዬ ላይ ሄጄ መቀመጥ ተስኖኛል፡፡ ከኋላዬ የተውኳቸው ሲሆን ከመስጊድ በሚያስወጣው መንገድ ላይ ነኝ፡፡ ይህ እንዲሆን ውሳኔው የእግዚአብሔር ነው፡፡

ከዚህም በላይ ደግሞ የምንጠባበቀው ሰው ኢማሙ አይደለም፡፡ ምናልባት ከእርሱ የላቀ ሥልጣን ያለውን ሰው እየተጠባበቅን ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ሰው ደግሞ ምናልባት ጭራሹኑ ወደ መስጊዱ ላይመጣ ይችላል፡፡ ይህኛውም ህልም እንደ ሁለተኛው ህልም ሁሉ ያለሁበትን ቦታ እንጂ ምን ማድረግ እንዳለብኝ አልነገረኝም፡፡ የሚመጣውን እየተጠባበኩ ነበር ነገር ግን እርሱ ሊመጣበት በሚችለው ትክክለኛ ቦታ ላይ ባለመሆኔ ግራ ተጋብቻለሁ፡፡

በዚህ ህልም ውስጥ መስጊድና ኢማም ስለሚገኙ እማ እንድትተረጉምልኝ ነገርኳት፡፡ የኢብን ሲሪንን መጽሐፍ በመጠቀም ትተረጉምልኝ ጀመር፡፡ ደረጃዎቹ በዚህም ሆነ

በመጪው ዓለም ደረጃዬ ከፍ ማለቱን እንደሚያመለክት፤ በመጀመርያው ደረጃ ላይ መቀመጤ ጉዞዬን ገና መጀመሬን እንደሚያመለክት፤ በህልሙ መጀመርያ ላይ መስጊዱ ባዶ መሆኑ የሃይማኖት ትምህርት ልማር እንደሆነ እንደሚያመለክት፤ ወደ መጨረሻ አካባቢ መስጊዱ መሙላቱ አስተዋይ የሆነ የሃይማኖት መምህርና ውጤታማ አማካሪ እንደምሆን እንደሚያመለክት፤ ኢማሙ ሙስሊውን ኡማ በሙሉ እንደሚወክልና ነጭ ልብስ መልበሱ ልባቸው ቀና መሆኑን እንደሚያመለክት ነገረችኝ፡፡

ከእኔ ኋላና ከእኔ በታች የመቀመጡን ሚስጥር ልትፈታ አልቻለችም፡፡ በምንጣፍ ላይ የመቀመጡንም ትርጉም ልትነግረኝ አልቻለችም፡፡ አንድ ሰው በምንጣፍ ላይ ተቀመጦ ማየት ያ ሰው መሳሳቱንና ሀሰተኛ የሆኑ መረጃዎችን ሊሰጥ እንደሚችል ያሳያል፡፡ የህልሙ ትክክለኛ ትርጉም እንደተሰወረባት ብትደመድምም ነገር ግን ጥሩ ዜና ያዘለ መሆኑን ተረድታች፡፡

ህልሙን ለዳዊት ስነግረው የሰጠኝ ምላሽ ይበልጥ ትርጉም የሚሰጥ ነበር፡፡ “ከመስጊድ የሚያስወጣ ደረጃ? ነቢል ምን ነካህ? ክርስቲያን ከመሆንህ በፊት እግዚአብሔር የሆነ ከባድ ብረት ነገር ከሰማይ ጭንቅላትህ ላይ እንዲወረውርብህ ትጠብቃለህ እንዴ?”

እውነቱን ነው፡፡ ምንድነው እየጠበኩ ያለሁት? ሦስት ህልሞችና አንድ ራዕይ አይቻለሁ፡፡ የመጨረሻዎቹ ሁለቱ ግልፅ ሲሆኑ አራቱም ግን ጠንካሮች ናቸው፡፡ አንድ ላይ ሲደመሩ ለጥያቄ የሚቀርቡ አይደሉም፡፡

እውነቱን አውቄያለሁ፤ ወንጌሉን እንድቀበል እግዚአብሔር እየጠራኝ ነው፡፡

እውነቱን በግሌ አምኛለሁ ነገር ግን ለማንም አልነገርኩም፤ ለእግዚአብሔር እንኳ ገና እጅ አልሰጠሁም፡፡ ምናልባት በወቅቱ ያሳየሁት ጠባይ ያልተገባ እንዲያውም ይቅርታን የማያሰጥ መሆኑን የሚናገር ሰው ሊኖር ይችላል፡፡ ምናልባት ትክክል ሊሆን ይችላል፡፡ ሦስተኛው ህልም የክርስትና ሕይወት ጅማሬ ባይሆንልኝም ነገር ግን የኀዘን ጊዜ እንድጀምር ምክንያት ሆኗል፡፡ ከዚህ በኋላ የነበረው የሕይወቴ ክፍል የሰቆቃ ነበር፡፡

# የኀዘን ጊዜ

2005 ክረምቱን በሙሉ ወንጌልን ሳልቀበል አሳለፍኩኝ፡፡ ወደ ብዙ መስጊዶች በመሄድና ብዙ ኢማሞችን በማናገር መልስ ስፈልግ ብቆይም ጥረቴ ሁሉ መና ሆኖ ቀርቷል፡፡ ከአባቴ ጋር እንኳ ወደ አውሮፓ መስጊዶች ሳይቀር ጉዞዎችን በማድረግ ባለፉት አራት ዓመታት የተማርኳቸውን ትምህርቶች ለመቀልበስ ብሞክርም ነገር ግን ምንም ውጤት አልነበረውም፡፡ እግዚአብሔር ሌሎች ህልሞችን እንዲሰጠኝ ብለምነውም ነገር ግን ምንም አልሰጠኝም፡፡ የሚያስፈልገኝን ሁሉ አግኝቻለሁ፡፡

ህመሙ ቀላል አልነበረም፡፡ ዋጋ ልከፍል እንደሆነ አውቃለሁ ነገር ግን ምን ሊሆን እንደሚችል አላውቅም ነበር፡፡ እማና አባ ይጠሉኝ ይሆን? ከቤተሰባቸው ክበብ ያስወጡኝ ይሆን? በልብ ድካም ምክንያት ይሞቱ ይሆን? ይህ የመጨረሻው ከሁሉም ጎልቶ ታየኝ፡፡

እውነቱን ለመናገር ሊሆን ያለውን አላውቅም ነበር፡፡ የማውቀው ነገር ቢኖር ሕይወት እንደ ቀድሞው እንደማትሆን ብቻ ነው፡፡

ወቅቱ የክረምት መገባደጃ ሲሆን ለሚቀጥለው ዓመት የኅክምና ትምህርት ዝግጁ ሆኛለሁ፡፡ ከክፍል ጓደኛዬ ጋር ለመሄድ ተዘጋጅቼ ስለነበር የጉዞው ዋዜማ ለቤተሰቤ የሸኘት ጊዜ ነበር፡፡ በሌላ ወገን ደግሞ የሃያ አምስት ደቂቃ ርቀት ወዳለው ቦታ ስለነበር የምሄደው ያን ያህል አክብደው አላዩትም፡፡ እኔ በበኩሌ እንደ ቤተሰብ ሊኖረን

የሚችለው የመጨረሻው የፍቅርና የቅርርብ ጊዜ መሆኑን አውቅ ነበር፡፡ እያንዳንዱን የሳቅ አጋጣሚ ተደሰትኩበት፤ እያንዳንዱን የመተቃቀፍ ጊዜ አጣጣምኩት፡፡

እማና አባ ምን ላደርግባቸው እንደሆነ ምንም የሚያውቁት ነገር አልነበራቸውም፡፡ ምን እያሰብኩ እንደሆነ ምንም አልገባቸውም፡፡ ውስጤ በጥፋተኝነት ስሜት መታመስ ጀምሯል፡፡ ይህንን ቤተሰብ እንዴት ብዬ ነው የማጠፋው? ምን እየሆንኩ ነው ግን?

በሚቀጥለው ቀን ወደ ትምህርት ቤት ነድቼ መሄድ በእጅጉ ከብዶኝ ነበር፡፡ እንባዬን መቆጣጠር ተስኖኛል፡፡ ቤቱን እንደምንም ለቅቄ ለመውጣት ራሴን እያደፋፈርኩኝ ይህ ቀን ምን ያህል አስፈላጊና ወሳኝ እንደሆነ ራሴን በማስታወስ ላበላሸው እንደማይገባኝ አስብ ነበር፡፡ ለጎክምና ተማሪ ሁለተኛው የትምህርት ዘመን ፈታኝ መሆኑና የመጀመርያዋ ቀን ወሳኝ መሆኗ ይታወቃል፡፡ ራሴን ማረጋጋት ይኖርብኛል፡፡

ያንን ማድረግ አልቻልኩኝም፡፡ ድምፄን ከፍ አድርጌ ወደ አምላኬ መጮኽ ጀመርኩኝ፡፡ “ያ አላህ! አምላኬ ሆይ! እባክህን እርሜን እንዳወጣ ጊዜ ስጠኝ! ቤተሰቦቼን ላጣቸው ስለሆነ የምወደውን ሕይወት ላጣ ስለሆነ እባክህን የኀዘን ጊዜ ስጠኝ፡፡”

ወደ ትምህርት ቤቱ ስቀርብ ወደ ውስጥ ለመግባት ዝግጁ እንዳልሆንኩኝ ገባኝ፡፡ መኪናዬን አዙሬ ከትምህርት ቤቱ ፊት ለፊት ማዶ ላይ ወደሚገኘው የመኖርያ አፓርትመንቴ ነዳሁ፡፡ ከጥቂት ቀናት በፊት እኔና አባ ቁሳቁሶቼን ወደዚያ አምጥተን ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ከእግዚአብሔር ዘንድ መፅናናትን ሊሰጡኝ የሚችሉ ሁለት መጻሕፍትን እያሰብኩኝ ነበር፡፡

ወደ አፓርትመንቱ ከመግባቴ አሮጌውን ቁርአኔንና የጥናት መጽሐፍ ቅዱሴን አወጣሁ፡፡ ሶፋው ላይ ቁጭ ብዬ መጀመርያ ቁርአንን ገለጥኩት፡፡ ስለ መፅናናት የሚናገሩ ጥቅሶችን ፍለጋ ገፆቹን ማገላበጥ ጀመርኩኝ፡፡ መጀመርያ እያንዳንዱን ገፅ በጥንቃቄ በማንበብ ማሰስ ተያያዝኩኝ ከዚያ በኋላ ወደ ቃላት ማውጫው በመሄድ ፈጠን እያልኩኝ ሊያፅናኑኝ የሚችሉ ጥቅሶችን ለማግኘት ከገፅ ገፅ መዝለል ጀመርኩኝ፡፡

ምንም ነገር ላገኝ አልቻልኩኝም፡፡ በሁኔታዎች ላይ ተመስርቶ የሚወድና የሚጠላ፣ እርሱን ለማስደሰት ከፍተኛ ጥረት ካላደረኩኝ በስተቀር የማይወደኝና ጠላቶቹን ወደ ገሃነመ እሳት በመላክ የሚደሰት አምላክ ምስል ተከሰተልኝ፡፡ እንኳንስ የእግዚአብሔርን ፍቅር ለሚሻ የተጎዳ ሰው ይቅርና ለተጎዳው የሰው ተፈጥሮ እንኳ የሚሆን መልዕክት የለውም፡፡ ለሰባተኛው ክፍለ ዘመን የተጻፈ በብዙ ስህተቶች የተሞላ መጽሐፍ ነው፡፡

ሕያው የሆነውን ቃል ፍለጋ ቁርአንን በማስቀመጥ መጽሐፍ ቅዱስን አነሳሁ፡፡

ከዚህ ቀደም መጽሐፍ ቅዱስን ለግል ምሪት አንብቤ አላውቅም ነበር፡፡ ከየት መጀመር እንዳለብኝ እንኳ አላውቅም ነበር፡፡ ከአዲስ ኪዳን መጀመር ጥሩ መሆኑን ስላሰብኩኝ የማቴዎስን ወንጌል አወጣሁ፡፡ በደቂቃዎች ውስጥ እነዚህን ቃላት አገኘሁ፡-

“የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው፥ መፅናናትን ያገኛሉና፡፡”

ቃላቱ ልክ በሙት ልቤ ውስጥ እንደተለቀቀ የኤሌክትሪክ ንዝረት ነበሩ፡፡ የምፈልገው ይህንን ነበር፡፡ እግዚአብሔር ስለ እኔ አስቦ ከዛሬ ሁለት ሺህ ዓመታት በፊት እነዚህን ቃላት በዚህ ቦታ ያስቀመጣቸው መስሎ ተሰማኝ፡፡

ከመገረሜ የተነሳ ማመን እንኳ ተስኖኛል፡፡ ዓለምን በሙስሊም መነፅር ሲያይ ለኖረ ሰው መልዕክቱ ከአእምሮ በላይ ነው፡፡ “ኀዘንተኛ በመሆኔ ብፁዕ ነኝ? ለምን? እንዴት? እኔ ፍፅምና የለኝም፡፡ የእርሱን መስፈርት ማሟላት አልችልም፡፡ ለምንድነው የሚባርከኝ? ስላዘንኩ ብቻ ነው፡፡ ለምን?”

በጉጉት ውስጥ ሆኜ ማንበቤን ቀጠልኩኝ፡፡ “ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው? ጻድቃን ብፁዓን ናቸው አይልም ነገር ግን ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ? እኔ ጽድቅን እራባለሁ እጠማለሁ ነገር ግን በራሴ ጥረት ላገኘው አልችልም፡፡ ይህም ሆኖ ሳለ እግዚአብሔር ይባርከኛል? በውድቀቴ ውስጥ እንኳ ሆኜ የሚወደኝ ይህ አምላክ ማነው?”

በድጋሜ ዓይኖቼ እንባ አፈሰሱ ነገር ግን አሁን የደስታ እንባ ነበር፡፡ አሁን በእጄ ይዤ ያለሁት ሕይወትን እራሱን መሆኑ ገብቶኛል፡፡ ይህ እውነተኛ የእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡ ለመጀመርያ ጊዜ ፊት ለፊት እንዳገኘሁት ይሰማኝ ጀመር፡፡

በጥማት የደረቀችው ነፍሴ፤ ከሕይወት ምንጭ ጠጥታ የማታውቀው ነፍሴ ከቅዱሱ መጽሐፍ በሚመነጨው የሕይወት ቃል ውኀ እስክትረሰርስ ድረስ ንባቤን ቀጠልኩኝ፡፡ የእያንዳንዱን ጥቅስ ሙሉ ትርጉም አገኝ ዘንድ በግርጌ ማስታወሻው የተቀመጠውን ማጥኛ እየተመለከትኩኝ ማጣቀሻዎቹን አነብ ነበር፡፡ በአእምሮዬ ውስጥ ጥያቄዎች ሲፈጠሩ ከአፍታ በኋላ ጥቅሱ ራሱ ወይም ደግሞ የግርጌ ማስታወሻዎቹ ወደ መልሱ ይመሩኝ ነበር፡፡ መቁጠር ከምችለው ጊዜ በላይ በተደጋጋሚ ይህ ሆኗል፡፡

መጽሐፍ ቅዱሱን መልሼ ማስቀመጥ ተስኖኛል፡፡ ይህን ስል ማጋነን አይምሰላችሁ፤ የእውነት ማስቀመጥ ተስኖኛል፡፡ መልሼ ባስቀምጠው ልቤ ምቷን የምታቆም ነበር የመሰለኝ፡፡ የዚያን ዕለት ትምህርት ቤት ሳልሄድ ብቀርም ሌላ ምርጫ አልነበረኝም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የሕይወቴ ደምስር እንደሆነ ተሰምቶኝ ነበር፡፡

# ቃሉ ይናገራል

በቀጣዮቹ ጥቂት ቀናት ውስጥ ልቤ እግዚአብሔርን በማግኘት አዲስ ደስታ ተሞልቶ ነበር፡፡ ሕይወቴን በሙሉ ያወቅሁት መስሎ ሲሰማኝ የነበረ ቢሆንም አሁን ግን ከዚህ ቀደም ከነበረኝ ዕውቀት ጋር ፈፅሞ ሊነፃፀር በማይችልበት ሁኔታ የእውነት አውቄዋለሁ፡፡ ከእውነተኛው አምላክ ጋር ሊነፃፀር የሚችል ምንም ነገር የለም፡፡

ምናልባት ለምን በማስከተል አዲስ አማኝ የሚጸልየውን የንስሐ ጸሎት እንዳልጸለይኩ የሚጠይቅ ሰው ሊኖር ይችላል፡፡ መልሱ ቀላል ነው፤ አዲስ አማኝ ስለሚጸልየው የንስሐ ጸሎት ሰምቼ አላውቅም ነበር፡፡ የማውቀው ነገር ቢኖር የመጽሐፍ ቅዱሱን እግዚአብሔርን መውደዴንና እርሱን ለማወቅ በየዕለቱ ማንበቤን ነው፡፡

የጥናት መጽሐፍ ቅዱሴን ሳላቋርጥ ማንበቤን ቀጠልኩኝ፡፡ እያንዳንዱን ቃል እያሰላሰልኩኝ፣ እያንዳንዱን የግርጌ ማስታወሻና ማጣቀሻ እያነበብከኝ፣ ወደ ሌላ ቦታ የሚመራኝን ማጣቀሻ ካላገኘሁ ብቻ ወደ ማቴዎስ እየተመለስኩኝ ቀናት አለፉ፡፡ ከማቴዎስ 5 እስከ ማቴዎስ 10 ለማንበብ ብቻ አንድ ሳምንት ፈጀብኝ፡፡

ከዕለታት በአንዱ ቀን ከእኩለ ሌሊት በኋላ በዚህ አዲስ ግኝት ተመስጬ እያነበብኩኝ ሳለሁኝ እንዲህ የሚል ቃል በማቴዎስ 10፡32-33 ላይ አገኘሁ፡- “በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ፤ በሰው ፊትም የሚክደኝን ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እክደዋለሁ፡፡”

ልቤ ደነገጠ፡፡ ስለ ኢየሱስ በሰዎች ፊት ልመሰክር ይቅርና በኢየሱስ በራሱ ፊት እንኳ መስክሬ አላውቅም ነበር፡፡ ነገር ግን ስለ እርሱ መመስከር ማለት ቤተሰቤን ማጥፋት ማለት ነው፡፡ እውነት እንዲህ ዓይነቱን ነገር እንድፈፅም ይጠብቅብኛልን?

ሕያው የሆነው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ከልቤ ጋር ንግግር እያደረገ ያለ ይመስል በእያንዳንዱ ጥቅስ ውስጥ ኢየሱስ ለልቤ ምላሽ መስጠት ጀመረ፡፡ "በምድር ላይ ሰላምን ለማምጣት የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ሰይፍን እንጂ ሰላምን ለማምጣት አልመጣሁም፡፡ ሰውን ከአባቱ፥ ሴት ልጅንም ከእናትዋ፥ ምራትንም ከአማትዋ እለያይ ዘንድ መጥቻለሁና፤ ለሰውም ቤተ ሰዎቹ ጠላቶች ይሆኑበታል፡፡"

ነገር ግን ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? ኢየሱስ እንዴት በእማና በአባ ላይ ፊቴን እንዳዞር ሊጠይቀኝ ይችላል? በጣም ግሩም ሰዎች ናቸው፡፡ ለምንድነው እግዚአብሔር እንዲህ ዓይነቱን ነገር የሚፈፅመው?

ኢየሱስ በቀጣዩ ጥቅስ ውስጥ ምላሽ ሰጠኝ፡- "ከእኔ ይልቅ አባቱን ወይም እናቱን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም፤ ከእኔ ይልቅም ወንድ ልጁን ወይም ሴት ልጁን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም፡፡"

ኢየሱስ ራሱ አይደለም ፊቴን በእነርሱ ላይ እንዳዞር የሚያደርገኝ፡፡ ነገር ግን ቤተሰቦቼ እግዚአብሔርን ለመከተል ፍቃደኞች ካልሆኑ ከሁለቱ አንዱን መምረጥ ግድ ይለኛል፡፡ በቤተሰቤ ላይ ፊቴን አዞሬ እርሱን ብመርጠው እንኳ እግዚአብሔርን መምረጥ ትክክል ነው፡፡ ነገር ግን እንዴት? ህመሙን ልሸከም የምችለው እንዴት ነው?

ያ ከባድ ህመምና ማሕበራዊ መገለል የክርስትና ሕይወት አንዱ አካል መሆኑን አረጋገጠልኝ፡- "መስቀሉንም የማይዝ በኋላዬም የማይከተለኝ ለእኔ ሊሆን አይገባውም፡፡" ክርስቲያን መሆን ማለት ለእግዚአብሔር ሲሉ ትክክለኛውን ህመም ማስተናገድ ማለት ነው፡፡ አንድ ሙስሊም አላህ ስላዘዘው ለአምላኩ የሚሰቃየውን ዓይነት ስቃይ ማለት አይደለም ነገር ግን እግዚአብሔር አስቀድሞ መከራን እንደተቀበለለት አመስጋኝ ልጅ የምንከፍለው ዋጋ ነው፡፡

እንዲህ ብዬ ተማፀንኩት፡- "ነገር ግን ጌታ ሆይ ባንተ ላይ ያለኝን እምነት በሰዎች ፊት መመስከር ማለት የሕይወቴ ፍፃሜ ነው፡፡ ከሚደርስብኝ የስሜት ስብራት ስቃይ የተነሳ አካላዊ ሞት ባልሞት ወይም አንድ ቀናዒ ሙስሊም ባይገድለኝ እንኳ ቢያንስ ከዚህ ቀደም የማውቀው ሕይወቴ ያከትምለታል፡፡"

"ልጄ ነቢል" ብሎ የጠራኝ ያህል ተሰማኝ፤ "ነፍሱን የሚያገኝ ያጠፉታል፥ ነፍሱንም ስለ እኔ የሚያጠፋ ያገኛታል፡፡"

የእርሱን ሕይወት መቀበል እንድችል የኔን መተው ይኖርብኛል፡፡ ይህ የሆነ ዓይነት ድግግሞሽ አይደለም፡፡ ወንጌል እንድሞት ነው እየጠራኝ ያለው፡፡

በዝያን ምሽት እነዚህ ቃላት ሸክም ሆነውብኝ የመተኛት ፍላጎቴ ጠፍቶ ጋደም ብዬ ማሰላሰል ጀመርኩኝ፡፡ ማረፍ ባልፈግም ነገር ግን ከተሰማኝ ሰለም የተነሳ እንቅልፍ ወዲያውኑ ይዞኝ ነጎደ፡፡ ለብዙ ጊዜ እግዚአብሔርን ክጄዋለሁ፡፡ ኦገስት 24፣ 2005 ከሌሊቱ 9 ሰዓት ላይ በአልጋዬ ግርጌ ላይ በግንባሬ ተደፍቼ ጸለይኩኝ፡፡

"ራሴን ሰጥቻለሁ፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰማይና የምድር ጌታ መሆኑን በመቀበል እገዛለታለሁ፡፡ ኃጢአቴን ለማንፃት ሲል ወደዚህ ምድር መምጣቱንና ጌትነቱን ከሙታን በመነሳት ማረጋገጡን እቀበላለሁ፡፡ እኔ ኃጢአተኛ ነኝ ስለዚህ ከኃጢአቴ ለመንፃት እርሱ ያስፈልገኛል፡፡ ጌታዬ ክርስቶስ ሆይ በሕይወቴ ውስጥ እቀበልሃለሁ፡፡"

ትልቅ ሸክም የተንከባለለልኝ ያህል ሰላም ስለተሰማኝ ወዲያውኑ እንቅልፍ ወሰደኝ፡፡ በመጨረሻ የወንጌልን እውነት ተቀብያለሁ፡፡ አሁን አማኝ ሆኛለሁ፡፡

አማኝ ብሆንም ነገር ግን የወንጌልን ኃይል አላውቅም ነበር፡፡ ይህንን ያስተምረኝ ዘንድ እግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ ሊሰብረኝ ተዘጋጅቷል፡፡

# ኢየሱስን ማግኘት

እግዚአብሔርን እየተማፀንኩት መሬት ላይ ተደፍቻለሁ፡፡ ጌታዬን ከተቀበልኩት ከሁለት ሳምንታት በኋላ ከንፈሮቼ እየተንቀጠቀጡና መላው ሰውነቴ ወባ እንደያዘው ሰው እየተርገፈገፈ ተማፅኖዬን በፊቱ እያቀረብኩ ነው፡፡ “እግዚአብሔር ሆይ ለምን...?” የምናገራቸውን ቃላት በትክክል አስተካክዬ መናገር አልቻልኩም ነበር፡፡ መንቀጥቀጡን መቆጣጠር ተስኖኛል፡፡

ከዚያ በፊት በነበረው ምሽት የአባ ዓይኖች እንባ አቅርረው ነበር ያየኋቸው፡፡ በጆሮዬ ላይ አዛን ከተናገረበት ዕለት ጀምሮ ለኔ ሲጠነቀቁልኝ የነበሩት እነዚያ ዓይኖች፤ በየምሽቱ የፈጣሪውን ጥበቃ ሲለማመን በስሱ የሚከደኑት እነዚያ ዓይኖች፤ አገሩንና ቤተሰቡን ለማገልገል በየማለዳው ወደ ባሕር ሲሄድ በፍቅር ዞረው የሚመለከቱት እነዚያ ዓይኖች እያነቡ ነበር፡፡ እነዚህ ዓይኖች ሲያነቡ ያየሁት ለመጀመርያ ጊዜ ነበር፡፡ ምክንያቱ ደግሞ እኔ በመሆኔ መቋቋም ተስኖኛል፡፡

“እግዚአብሔር ሆይ ለምን...?”

እማ ከአባ ይልቅ ጥቂት ቃላትን ብትናገርም ዓይኖቿ ከዚያ በላይ ነበር የሚናገሩት፡፡ “ብቸኛ ወንድ ልጄ ነህ፡፡ ከማህፀኔ ነው የወጣኸው፡፡ ከተወለድክበት ቀን ጀምሮ የኔ *ጀን ካይ ቱክረይ፣* የሕይወቴና የልቤ ቁራጭ እያልኩ ነበር የምጠራህ፡፡ በጆርባዬ አዝዬሃለሁ፣ ዘምሬልሃለሁ የአምላክን መንገድ ደግሞ አስተምሬሃለሁ፡፡ ወደዚህ ዓለም ከመጣህበት ጊዜ ጀምሮ በየዕለቱ ማንንም ባልወደድኩበት መንገድ በሁለንተናዬ ወድጄሃለሁ፡፡

“ቢሉ፣ ለምንድነው የከዳኸኝ?”

ዓይኖቿ ነፍሴን ሰንጥቀው በመግባት በትውስታዬ ላይ ታተሙ፡፡ አባ እማን በጥድፍያ ከኔ ክፍል በማስወጣት ወደ ሆስፒታል ከመብረሩ በፊት ያየሁት የመጨረሻው ምስል ነበር፡፡ ሌሊቱን ማደሯን ማናችንም እርግጠኞች አልነበርንም፡፡

ተርፋለች፤ ነገር ግን ከዚያን ዕለት ጀምሮ ዓይኖቿ እንደቀድሞው ብሩህ ሊሆኑ አልቻሉም፡፡ ብርሃናቸውን ያጠፋሁት እኔ ነኝ፡፡

በእግዚአብሔር ፊት ተዘርሬ ዓይኖቼ እንባ እየረጩ፣ አፍንጫዬና አፌ የጎዘኑን ምሬት መቋቋም ተስኗቸው በመጨረሻ በእንባና ከአፍንጫ በሚወጣ ፈሳሽ የታጀቡ ቃላትን መናገር ቻልኩኝ፡- “ለምን እግዚአብሔር ሆይ፣ ባመንኩበት ቅፅበት ለምን አልገደልከኝም? ለምን እዚህ ምድር ላይ ተውከኝ? ቤተሰቦቼ ከዚህ ቀደም ተጎድተው በማያውቁበት ሁኔታ እንዲጎዱ እንዳደርግ ለምን ተውከኝ? ይህ አይገባቸውም ነበር! አጥፍቻቸዋለሁ! ምንም የቀረ ነገር የለም!”

“ለምን አልገደልከኝም?” ተስፋ በመቁረጥ ውስጥ ሆኜ ከእግዚአብሔር ጋር ሙግት ገጠምኩኝ፡፡ “ቤተሰቦቼ የመከዳት ስሜት እንዳያድርባቸው ባመንኩበት በዚያው ቅፅበት ብትገድለኝ ይሻለኝ ነበር፡፡ ከሞቴ ይልቅ ይህ ለእነርሱ እጅግ የከፋ ነው፡፡ ቢያንስ ፍቅራችን ይቀጥል ነበር፡፡ ቢያንስ ቤተሰባችን አንድ ሆኖ ይኖር ነበር፡፡”

“እግዚአብሔር ሆይ ለምን?”

የሕይወቴ ከባድ የሰቆቃ ጊዜ በነበረው በዚያው ሰዓት ከእኔ ሥነ-መለኮትና አስተሳሰብ የወጣ አንድ ነገር ተከሰተ፡፡ እግዚአብሔር ሜጋፎን አንስቶ በህሊናዬ ውስጥ የተናገረ ይመስል እንዲህ የሚል ድምፅ በመላው እኔነቴ ውስጥ ሲሰራጭ ሰማሁ፡-

“ምክንያቱም ይህ ስለ አንተ ጉዳይ ባለመሆኑ ነው፡፡”

አፌን ከፍቼ ቀረሁ፡፡ እንባው፣ መንፋረቁ፣ መንቀጥቀጡ በሙሉ በአንድ ጊዜ ቀጥ አለ፡፡ በኤሌክትሪክ ንዝረት እንደተመታና ራሱን እንደሳተ ሰው ሆኜ መሬቱ ላይ ተዘርሬ ቀረሁ፡፡ ለአሥር ደቂቃዎች ያህል መንቀሳቀስም ሆኔ አፌን መክደን ተስኖኝ ቆየሁ፡፡

ውስጤን እያደሰው ነበር፡፡

መንቀሳቀስ ስችል ኅዘኔ በሙሉ ጠፋ፡፡ በሰቆቃ ውስጥ ሆኜ የተናገርኳቸው የጸሎት ቃላት ባለፈው ሕይወቴ ውስጥ የተነገሩ ዓይነት ሆነዋል፡፡ ከመሬት ተነስቼ ዙርያ ገባውን ማየት ጀመርኩኝ - ዛፎቹን፣ ሰማዩን፣ የቆምኩባቸውን ደረጃዎች አጤንኳቸው፡፡

ነገር ግን ዓለምን በተለየ መንገድ ማየት ጀምሬያለሁ፡፡ ከዚህ ቀደም ባለቀለም መነፅሮችን ነበር ሳደርግ የነበረው አሁን ግን ሁሉም ወልቀዋል፡፡ ሁሉም ነገር የተለየ ሆኖ ታየኝ፡፡ አንድ በአንድ የመመርመር ፍላጎት አደረብኝ፡፡

ከዚህ ቀደም ደግሜ ደጋግሜ ያየሁትን አንድ ነገር አስተዋልኩኝ፡፡ ወደ ኅክምና ትምህርት ቤት እየሄደ ያለ ሰው፡፡

ነገር ግን ያየሁት እርሱን ብቻ አልነበረም፡፡ ይህ ሰው ማን እንደሆነ ባላውቅም ነገር ግን ከራስ ጋር በሚደረግ ትግል የተሞላ ሕይወት እንዳለው፣ የተበላሸ የፍቅር ግንኙነት እንዳስጨነቀውና ለራስ ዝቅተኛ የሆነ አመለካከት በመስጠት የታሰረ ሕይወት እንዳለው ተረዳሁ፡፡ ዕውር በሆነ ዝግመተ ለውጥ የመጣ መሆኑን በማመኑ ምክንያት ሳያውቀው ለራሱ የሰጠው ግምት ዝቅተኛ ሆኗል፡፡ የተራ ዕድል ውጤት እንደሆነ ያምናል፡፡ ደስታን አሳዳጅ በመሆን የበለጠ የጥፋተኝነት ስሜት እንዲያድርበት ካደረገው የሕይወተ ዘይቤ የዘለለ ዓላማ፣ ተስፋና ትርጉም የለውም፡፡ እነዚህን ደስታዎች ማሳደድ የጥፈተኝነት ስሜት እንዲያድርበትና ታማሚ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ይህንን ችግሩን ለማሸነፍ የሚያሳድደው ሌላ አዲስ ደስታ ለበለጠ የህሊና ቁስልና ህመም ዳርጎታል፡፡ እነዚህን ችግሮች ችላ በማለትና አዙሪቱን የሚሰብርበትን መንገድ ባለማወቅ ቀኑን ለመኖር ከቤቱ ወጥቷል፡፡

የተመለከትኩት ሰው እግዚአብሔር ነፃ ሊያወጣው እንደሚችል ማወቅ የነበረበትን ሰው ነው፡፡ ይህ ሰው ስለ እግዚአብሔርና ስለ ኃይሉ ችሎት ማወቅ ይኖርበታል፡፡

ያውቅ ይሆን?

እግዚአብሔር ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ጀምሮ እንደወደደው ያውቅ ይሆን? በአፅናፈ ዓለም ውስጥ የሚገኘው ኃይል ሁሉ ሊመጥነው በማይችለው ሁኔታ ያንን ሰው ወደ መፍጠር ሐሳቡን ከመለሰ በኋላ፣ “አንተ ልጄ ነህ፡፡ እወድሃለሁ” ብሎታል፡፡ እግዚአብሔር በሚፈልገው ሁኔታ እንደፈጠረውና የራስ ፀጉሩን ሳይቀር በቁጥር እንደሚያውቅ፤ የዘመኑንም ቁጥር እንደወሰነ ያውቅ ይሆን? ለዚህ ሰው የሰጣቸው እጆች በእርሱ ላይ ኃጢአትን እንደሚሰሩና የፈጠረለትን እግሮች እርሱን ትቶ ለመሄድ እንሚጠቀምባቸው እግዚአብሔር አስቀድሞ ያውቅ ነበር፡፡ ነገር ግን እነዚህን ስጦታዎች ከመከልከል ይልቅ ከሁሉ የላቀውን ውድ ስጦታ ጨምሮ ሰጥቶታል፤ የገዛ ልጁን፡፡

ፈጣሪው ስለ እርሱ መከራን ለመቀበል ወደ ዓለም መምጣቱን ያውቅ ይሆን? መጀመርያ ሊያድናቸው በመጣላቸው ሕዝቦች በጥፊ መመታቱን፣ ቆዳው እስኪተለተል ድረስ መገረፉን፣ ከዚያም ሁሉም ሰው እያየ እስኪያላግጥበት ድረስ እጆቹና እግሮቹ ተቸንክረው እርቃኑን በእንጨት ላይ መሰቀሉን ያውቅ ይሆን? ትንፋሽ ለመስወጣትና ለማሰገባት ወደላይና ወደታች ሲል ቆዳው የተገፈፈውን ጀርባውን ደረቅ እንጨት ይፈቀፍቀው ነበር፡፡ የመጨረሻው እስትንፋሱ እኛን ነፃ በማውጣት ዘላለማችን ከእርሱ ጋር መሆኑን አረጋግጧል፡፡

ይህ ሰው ያውቅ ይሆን?

አያውቅም፡፡ ልንነግረው ይገባል፡፡ እኔ በግል ጉዳዮቼ ተወጥሬ ስባዝን በቢሊዮኖች የሚቆጠሩ እግዚአብሔር ማን መሆኑን የማያውቁ፣ አስደናቂ ፍቅሩን ያልቀመሱ፣ ያደረገልንን ድንቅ ሥራ ያልተገነዘቡ ሰዎች በዓለም ዙርያ ይገኛሉ፡፡ በትክክል በሥቃይ ውስጥ እያለፉ የሚገኙት እነርሱ ናቸው፡፡ እርሱ የሰጠንን ተስፋ፣ ሰላምና ከመታወቅ የሚያልፈውን ፍቅሩን አያውቁትም፡፡ የወንጌሉን መልዕክት አያውቁትም፡፡

ኢየሱስ ለእኛ ያለውን ፍቅር እጅግ የተዋረደ ሕይወት በመኖርና እጅግ አሣቃቂ አሟሟት በመሞት ካሳየ በኋላ “እኔ እንደወደድኳችሁ እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ” በማለት አዞናል፡፡ እርሱ እንደኖረው ለመኖር፣ እርሱ እንደሞተው ለመሞት፣ መወደድ የማይገባቸውን እንደወደደው ለመውደድና ተስፋ ለሌላቸው ተስፋን እንደሰጠው ለመስጠት የማልፈልግ ከሆነ የኢየሱስ ተከታይ መሆኔን መናገር የምችለው እንዴት ነው?

ይህ ስለ እኔ ጉዳይ አይደለም፡፡ ስለ እርሱና እርሱ ለልጆቹ ስላለው ፍቅር ነው፡፡

አሁን እግዚአብሔርን የመከተል ትርጉም ገብቶኛል፡፡ በልጁ በኩል በተሰጠን ሕይወት፣ አብን በማክበር ዘላለማዊ ዓላማ፣ በፀጋውና በፍቅሩ መንፈስ በድፍረት መመላለስ ነው፡፡

አሁን ኢየሱስን አግኝቼዋለሁ፡፡

*ስለ ህልሞችና ስለ ራዕዮች ዓለም አቀፍ ወንጌላዊና ከ130 በላይ መጻሕፍት ደራሲ*

*በሆኑት በጆሽ ማክዱዌል የተጻፈውን የሊቅ አስተዋፅዖ ለማንበብ*

*contributions.NabeelQureshi.com ይጎብኙ፡፡*

# የነገሩ ፍፃሜ

ውድ ወዳጆቼ

የኔን ታሪክ ስላነበባችሁ በጣም አመሰግናለሁ፡፡ ጌታ በዚህ ታሪክ ተጠቅሞ ስለ እስልምና ዕውቀት እንድትጨብጡ እንዲረዳችሁና ኢየሱስን እንዲሁም ፍቅሩን የበለጠ በመረዳት እንዲባርካችሁ ጸሎቴ ነው፡፡ የሕይወት ታሪኬን ሳካፍል ሰዎች በተደጋጋሚ የሚጠይቋቸው ጥያቄዎች አሉ፡፡ የመጨረሻውን መልዕክቴን ከማስተላለፌ በፊት የናንተም ጥያቄዎች እንደሆኑ የምገምታቸውን ጥቂቶቹን እመልሳለሁ፡፡

ኢየሱስን ከተቀበልኩ ከጥቂት ቀናት በኋላ ዳዊት የፒ ኤች ዲ ትምህርቱን ለመከታተል ወደ ኒው ዮርክ ተንቀሳቀሰ፡፡ እንዳለመታደል ሆኖ ቤተ ክርስቲያኒቱን እንደ መጋቢ ያገለግል የነበረው እርሱ በመሆኑ አካባቢውን ለቆ ሲሄድ አባላቱ ተበተኑ፤ እኔም ብቻዬን ቀረሁ፡፡ በዚህ ጊዜ የነበረኝ ብቸኛ ክርስቲያን ጓደኛ ቢኖር ከእኔ ጥቂት ወራት በመቅደም የጌታ ኢየሱስ ተከታይ የሆነው ዛክ ነበር፡፡ ሁለታችን ከሌሎች ሁለት አዳዲስ አማኞች ጋር በመሆን በየሳምንቱ ረቡዕ እንሰበሰብ ነበር፡፡ ለአንድ ሰዓት ያህል ‹ክርስቶስን ለመምሰልትሻለህን?›የሚለውን የቻርለስ ዝዊንዶልን መጽሐፍ ካነበብን በኋላ ቀሪዎቹን ጥቂት ሰዓታት መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ እናሳልፍ ነበር፡፡ አንዳንድ ጊዜ ለእግዚአብሔርና ለቃሉ ካለን ጥማት የተነሳ ሌሎች ሥራዎቻችንን በመርሳት እስከ ሌሊቱ አሥር ሰዓት መጽሐፍ ቅዱስን እናጠና ነበር፡፡ በጋራ እንጸልይ ነበር፣ እንፆም ነበር፣ ጥቅሶችን እንሸመድድ ነበር እንዲሁም የጌታን ፊት በፅኑ እንፈልግ ነበር፡፡ በነዚህ ጊዜያት ተዓምራትን አይተናል፣ ትንቢቶችንና ራዕዮችን ተቀብለናል፣ አጋንንት እንኳ ሲወጡ ተመልክተናል፡፡

ከክርስቶስ ጋር በነበረኝ ጉዞ ጅማሬ አካባቢ የኖርኩት ወርቃማ ጊዜ ከሰባት ወራት በኋላ አከተመ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን ከጨረስኩኝ በኋላ የበለጠ ጊዜ ለትምህርት በመስጠት

የቃሉን ጥናት ቀነስኩኝ፡፡ ቤተ ክርስቲያንን ስለተቀላቀልን የረቡዕ ምሽት መርሃ ግብራችን እየቀነሰ መጣ፡፡ በዙርያዬ በነበረው የየዕለት ኑሮ ተመልሼ ስለተጠመድኩኝ ልዕለ ተፈጥሯዊ ተዓምራቱ ተገቱ፡፡

ዳዊት ለክረምት እረፍት ተመልሶ ሲመጣ አገልግሎት አብረን ጀመርን፡፡ እኔና ዳዊት ሜይ 21፣ 2006 ላይ በወቅቱ አዲስ ርዕስ ለነበረው የዳን ብራውን *ዳቪንቺ ኮድ* መጽሐፍ መልስ የሚሆን ትምህርት በኖርፎልክ፣ ቨርጂንያ ሴንትራል ባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን እሁድ አምልኮ ላይ አስተማርን፡፡ በአገልግሎቱ መጨረሻ ላይ ሁለት አምላክ የለሾች ወደ ፊት በመምጣት ክርስቶስን ተቀበሉ፡፡ ለአገልግሎት መጠራታችንም ተረጋገጠ፡፡ ሚኒስትሪያችንን *አናስታሲስ ዓቃቤ እምነት* በማለት የሰየምነው ሲሆን የመልዕክታችን ማዕከል የሆነውን የክርስቶስን ትንሣኤ የሚያመለክት የግሪክ ቃል ነው፡፡ አናስታሲስ ዓቀበተ እምነት የሚለው ስም ለመጥራት ትንሽ የሚያስቸግር እንደሆነ ስለተሰማን *አክትስ 17* (የሐዋርያት *ሥራ* 17) ወደሚል ቀየርነው፡፡

ቤተሰቤን በተመለከተ ደግሞ ከድንጋጤው ካገገሙ በኋላ እኔን በተመለከተ ሁለት ነገሮችን ግልፅ አደረጉ፤ እንደተከዱ ቢሰማቸውም ነገር ግን ፍቅራቸው አልቀነሰም ነበር፡፡ ቁጣ ቢነድም፣ መጥፎ ቃላት ቢነገሩም፣ ክርክር ቢጦፍም ነገር ግን ከቤተሰብ አባልነት አልሰረዙኝም ነበር፡፡ በአንድ ወገን ይህ ትልቅ በረከት ነው፤ ምክንያቱም የቤተሰቤ አባል ሆኜ ቀጥያለሁና፡፡ በሌላ ወገን ደግሞ በየጊዜው የስሜት ማዕበላትን ማስተናገድ ስለነበረብኝ በጣም ከባድ ነበር፡፡ እማ የቤተሰቡን ደስታ በማደፍረሴ ምክንያት ለተከታታይ ሁለት ዓመታት በምሬት ታለቅስ ነበር፡፡ በነዚያ ጊዜያት ፊልጵስዩስ 4፡6-7፣ ሉቃስ 18፡1-8 እና ማቴዎስ 6፡25-34 የመሳሰሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በማንበብ እፅናና ነበር፡፡

ከውድ ባለቤቴ ጋር የተዋወቅሁት በ2007 ሲሆን ከአንድ ዓመት በኋላ ጥያቄ አቅርቤላት ከአራት ወራት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ጋብቻ ፈፀምን፡፡ ከአምስት ተወዳጅ የአጎቴ ልጆችና ከአንድ አጎቴ በስተቀር ከቤተሰቤ የእኔ ሰርግ ላይ የተገኘ ማንም አልነበረም፡፡ እንደርሱ

መሆኑ በእጅጉ ያሳዘነኝ ሲሆን አሁንም ድረስ ሳስበው ህመም ይሰማኛል፡፡ በ2009 ከኅክምና ትምህርት ቤት ስመረቅ የኅክምና ሥራ ከመሥራት ይልቅ ሙሉ ጊዜዬን ለአገልግሎት ለመስጠት ወሰንኩኝ፡፡ ቤተሰቦቼ ይህንን ውሳኔዬን ሲሰሙ ከእኔ ጋር የነበራቸውን ግንኙነት ሁሉ አቋረጡ፡፡ ከዓመት በኋላ መነጋገር የጀመርን ሲሆን ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ግንኙነታችን በየመሃሉ ይረባበሻል፡፡

ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ ከተከሰቱት ያልታሰቡ ነገሮች የተነሳ ከጁን 2011 ጀምሮ አክትስ 17 ዓቀበተ እምነት በንግግር ነፃነት፣ ሸሪኣ በምዕራብ አገራትና እስልምና ላይ ማተኮር ጀመረ፡፡ ወንጌልን በማሰራጨት ብቻ ላይ ያተኮረ ምኒስትሪ መጀመር እንዳለብኝ ስለተሰማኝ ከአክትስ 17 በመለየት *ክሪድ 2፡6* የተሰኘ ምኒስትሪ ጀመርኩኝ፡፡ ከራቪ ዘካርያስ ጋር በ2011 መጨረሻ ላይ ተዋውቄ ጁላይ 2013 ላይ ምኒስትሪውን ተቀላቀልኩኝ፡፡

በመጨረሻም ክርስቶስን ለመከተል ሊወስኑ ላሉቱ፤ በተለይም ደግሞ ይህንን በመወሰናቸው ብዙ መስዋዕትነት እንደሚከፍሉ ለሚያውቁቱ መልዕክቴን ለማስተላለፍ እፈልጋለሁ፡፡ እውነቱን ለመናገር እንደ ክርስቲያን ያሳለፍኩት የመጀመርያው ዓመት ከሚታሰበው በላይ አስቸጋሪ ነበር፡፡ በሕይወቴ ውስጥ እጅግ የተሰቃየሁበት ጊዜ ነበር፡፡ እያንዳንዷ ቀን በትግል የምታልፍ ሲሆን ከዚያ ቀደም ያላየሁትን ጥልቅ የስሜት መረበሽ አስተናግጃለሁ፡፡ነገር ግን ደግሞ ከስምንት ዓመታት በኋላ ዞር ብዬ ሳየው የሕይወቴ ጠንካራ ጊዜ እንደነበር ልናገር እችላለሁ፡፡ የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ወደመሆን በመቅረፅና በማስተካከል ለውጦኛል፡፡ መንፈስ ቅዱስ አፅናኜ ነበር፣ ቃሉ ደጋፊዬ ነበር፣ ያንን ጊዜ በምንም ነገር ልለውጠው አልችልም፡፡ እውነተኛ የኢየሱስ ተከታይ ያደረገኝ ያሳለፍኩት መከራ ነበር፡፡ ከጌታ ጋር ያለኝን ጉዞና ከውዷ ባለቤቴ ጋር ያለኝን ትስስር ጨምሮ አሁን ያለኝ ሕይወት ሙስሊም ሆኜ አስብ ከነበረው በላይ እጅግ ግሩም ነው፡፡

በየትኛውም መከራ ውስጥ ብናልፍ እንኳን ኢየሱስን መከተል አዋጭ የሆነ ምርጫ ነው፡፡ እርሱ እጅግ ድንቅ ነው፡፡ ውድ ወዳጆቼ አንድ ቀን ተገናኝተን ስለ ደስታችንና ስላሳለፍነው መከራ እግዚአብሔርን በጋራ ማመስገን እንችል ዘንድ ጸሎቴ ነው፡፡

በክርስቶስ የናንተው፣

ነቢል ቁሬሺ

# ማስታወሻዎች

1. ይህ ምልክት በአረብኛ *ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም* የሚለውን የሚወክል ሲሆን “የአላህ ሰላምና በረከት በእርሱ ላይ ይሁን” ማለት ነው፡፡ ሙስሊሞች የመሐመድን ስም ከጠቀሱ በኋላ የሚናገሩት ነው፡፡
2. *ሱብሃነ ወታዓላ* የሚለው ይህ አነጋገር የአላህ ስም ከተጠራ በኋላ የሚደጋገም ነው፡፡ ትርጉሙም “የተከበረና ከፍ ያለ” ማለት ነው፡፡
3. “በአላህ እጠጋለሁ” የሚል ትርጉም ያለው የተለመደ የሙስሊሞች ንግር ሲሆን አንድ ጥሩ ያልሆነ፣ የክህደት ወይም አሉታዊ የሆነ ቃ ሲነገር የሚባል ነው፡፡
4. በእስልምና አላህ 99 ስሞች እንዳሉት ይታመናል፡፡ ሁለቱ “ይቅር ባይ” እና “አዛኝ” የሚሉ ናቸው፡፡
5. “ክብር ለአላህ ይሁን” የሚል እጅግ የተለመደ የሙስሊሞች ንግር ሲሆን መልካም ዜና ወይም ደስ የሚያሰኝ ነገር ሲነገር ብዙ ጊዜ በአንክሮ ይነገራል፡፡
6. ሙስሊሞችን የሚያመለክት “ማሕበረሰብ” የሚል ትርጉም ያለው የአረብኛ ቃል ነው፡፡
7. Sahih Bukhari 6.61.508: “መለኮታዊ መገለጥ በእርሱ ላይ መጣ… የነቢዩ ፊት ቀላ፣ ቁና ቁና ይተነፍሱ ነበር ከዚያም እፎይታ ተሰማቸው፡፡” በተጨማሪም Sahih Muslim 30.5763: “የአላህ ነቢይ መገለጥ ሲመጣላቸው በቀዝቃዛ ቀን እንኳ ያልባቸው ነበር፡፡”
8. የተለመደ የንስሐ ንግግር ሲሆን “ከአላህ ምህረትን እሻለሁ” ማለት ነው፡፡
9. Sahih Muslim 1.311.
10. ሙስሊም ዓቃቤ እምነታውያን ዘዳግም 33፡2 መሐመድ ወደ መካ በድል ስለገባበት ሁኔታ የተተነበየ ትንቢት እንደሆነ ይናገራሉ፡፡
11. የቁርአን ንባብ ብቸኛ አማራጭ የሆነ፡፡
12. Sunan Abu Daud 14.2526.
13. Sahih Bukhari 9.87.116.
14. ይህ ዘገባ ከብዙ ንግግሮች የተሰበሰበ ሲሆን አንዳንዶቹ በተደጋጋሚ የሰማኋቸው ሌሎቹ ደግሞ የተሳተፍኩባቸው ናቸው፡፡
15. ይህ ምናልባት የቀደመው እስልምና በስልጣናዊ አገዛዝ የሚያምን ከመሆኑ ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል፡፡ ወይም ደግሞ በዚህ ዘመን ያሉት ሙስሊሞች በአንፃራዊነት ፊደል የመቁጠራቸው

ሁኔታ አናሳ በመሆኑ ምክንያት በአፍ ከአንዱ ወደ ሌላው የሚሸጋገር ታሪክ አስፈላጊ በመሆኑ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

16. ሮሜ 10:9.
17. 5:72.
18. ገላቲያ 1:6 – 9.
19. 4:157; 5:116.
20. Mirza Ghulam Ahmad, *Jesus in India*. (Surrey: Islam International Publications, 2003). Originally published in India. ይህ የተሻሻለ ህትመት ነው፡፡
21. 4:157.
22. 4:158.
23. አሕመዲ ጀማት ሱራ 4:158 መንፈሳዊ እርገትን እንጂ ሥጋዊ እርገትን እንደማያመለክት ያስተምራሉ፡፡
24. 3:49; 3:45.
25. ይህ በርግጥ ማርቆስ 10:18 እና ሉቃስ 18:19 በተሳሳተ መንገድ ማቅረብ ሲሆን በሙስሊሞች ሙግት ውስጥ በብዛት ይስተዋላል፡፡ በሁለቱም ቦታዎች ላይ ኢየሱስ ቸር መሆኑን አላስተባበለም፡፡
26. 5:69.
27. 3:85.
28. 5:73.
29. Sahih Bukhari 1.1.1.
30. ሱኒዎች አንዳንዴ በሙዋታ ኢማም ማሊክ የመጨረሻዎቹ ሦስቱ ላይ አይግባቡም፡፡
31. የመጀመርያው ታላቁ ጦርነት በመባል በእስላማዊ ታሪኮች ውስጥ የሚታወቀው የበድር ጦርነት እንኳ መሐመድ በመካ የሲራራ ነጋዴዎች ላይ በፈፀሙት ጥቃት ምክንያት የተደረገ ነበር፡፡ የመኸላ ዘመቻ በመባል ይታወቃል፡፡ Sahih Bukhari 5.59.287; A. Guillaume, trans., *The Lifeof Muhammad: A Translation of Ibn Ishaq's Sirat Rasul Allah* (New York: Oxford University Press, 2002), 289 ይመልከቱ፡፡
32. Sahih Bukhari 1.2.24: የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- ‹ሰዎች ከአላህ በስተቀር ሊመለክ የሚገባው እንደሌለና መሐመድ የእርሱ መልዕክተኛ መሆኑን እስኪመሰክሩ ድረስ

እንዲሁም ሰላትን ደንቡን ጠብቀው እስኪሰግዱ ድረስ እንድዋጋቸው ታዝዣለሁ፡፡ ይህንን ካደረጉ በእስልምና በተወሰነው ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ነፍሳቸውንና ንብረታቸውን ከእኔ ይታደጋሉ፡፡ ድርሻቸውም በአላህ ይታሰብላቸዋል፡፡›” Sahih Muslim 19.4366: “ኡመር እንዳስተላለፈው የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- ‹አይሁድና ክርስቲያኖችን ከአረብያ ባሕረ ሰላጤ አስወጣቸዋለሁ፡፡ ከሙስሊም በስተቀር አንዱንም አልተውም፡፡›” *The Battles of the Prophet*, and the Qur’an, 9:5, 9:29, and 9:111.

33. በአል ቡኻሪ ውስጥ በጂሃድ ርዕስ ስር የሰፈረውን ማንበብ ብቻ ይህንን ግልፅ ያደርጋል፡፡ vol. 4, book 52.
34. “የቀደሙትንም ሆነ የአሁኖቹን እስላማዊ ጽሑፎች ስናነብ መንፈሳዊ ጂሃድን የተመለከቱ መረጃዎች በጣም ጥቂት ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ዛሬ ምዕራባዊ ባልሆኑ ቋንቋዎች (አረብኛ፣ ፋርስ፣ ኡርዱ በመሳሰሉት) የሚጽፉ ሙስሊሞች ጂሃድ በዋናነት ነውጠኛ አለመሆኑን ወይም መንፈሳዊ ትግል መሆኑን በፍፁም አይገልፁም፡፡ እንዲህ ያሉ ብሂሎች በብቸኝነት በምዕራባውያን ምሑራን፣ በሱፊዎች፣ በሃይማኖት ውይይቶች ላይ በሚሳተፉ ወይም እስልምናን በተቻለ መጠን ተቀባይነት ባለው መንገድ ለማቅረብ በሚሞክሩ ዓቃቤ እምነታውያን የሚነገሩ ናቸው፡፡” (David Cook, *Understanding Jihad* [London: University of California Press, 2005], 165 – 66).
35. ማርቆስ 16:9 – 20; ዮሐንስ 7:53 – 8:11.
36. ኮዴክስ ሲናይቲከስእና ኮዴክስ ቫቲካነስ
37. የንጉሥ ጀምስ መጽሐፍ ቅዱስ የዚህ ዘመን ትርጉም ካልሆኑት ትርጉሞች መካከል እንደ ምሳሌ ይጠቀሳል፡፡ ወሳኝ ከሆኑት ኋላ ላይ ከተገኙት የግሪክ አዲስ ኪዳን የሚቀድሙትን የእጅ ጽሑፎች ይጠቀማል፡፡ እንዲያም ሆኖ ዘመናዊዎቹ ትርጉሞችና የቆዩት ትርጉሞች የአስተምህሮ ልዩነት አያስከትሉም፡፡
38. ይህ በሙስሊሞች መካከል የሚነገር ሌላኛው የግንዛቤ እጥረት ነው፡፡ምዕራ 42, “ሐዲሳት እና የቁርአን ታሪክ” የሚለውን ይመልከቱ፡፡
39. 5:46 – 47; 5:66 – 68.
40. የአሪያን እና የፐሉታርክ
41. ኢዮስቢዮስ፣ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ 3.39.15 – 16.
42. ዝኒ ከማሁ, 3.39.4.

43. የዮሴፍ ወልደ ኮርዮን አንድ ወዳጅ ከመስቀል ወርዶ ሳይሞት ቀርቷል፡፡ ነገር ግን የስቅለት ሂደቱ ከመጠናቀቁ በፊት ነበር፡፡ እንዲገደል አልተወሰነም ነበር፡፡ ደግሞም በሕይወት እንዲተርፍ ጥረት ተደርጓል፡፡ከሌሎች ሁለት ሰዎች ጋር እንዲወርድ የተደረገ ሲሆን ሦስቱም ሕክምና ቢደረግላቸውም ሁለቱ ሞተዋል፡፡*Life of Flavius Josephus* (trans. Mason), §420 – 21.

44. ለበለጠ መረጃ read Martin Hengel, *Crucifixion* (Philadelphia: Fortress, 1977) ያንብቡ፡፡

45. ማርቆስ 8:31.

46. ማቴዎስ 27:19.

47. ማቴዎስ 16:21; 17:23; 20:18; ማርቆስ 8:31; 10:34; ሉቃስ 9:22; 18:33; ዮሐንስ 12:33; 18:32.

48. David Strauss, *A New Life of Jesus* (London: Williams and Norgate: 1879), 1:408 – 12.

49. Gary R. Habermas and Michael R. Licona, *The Case for the Resurrectionof Jesus* (Grand Rapids, MI: Kregel, 2004).

50. ስለ ታሪካዊ አካሄዶች በክርስቶስ ትንሣኤ አውድ ሰፊ ትንተና ለማግኘት Michael R. Licona, *The Resurrection of Jesus: ANew Historiographical Approach* (Downers Grove, IL: InterVarsity, 2010) ይመልከቱ፡፡

51. William Wand, *Christianity: A Historical Religion?* (Valley Forge, PA: Judson, 1972), 93 – 94.

52. 112:3.

53. Josh McDowell, *More Than a Carpenter* (Carol Stream, IL: Tyndale, 1977).

54. ሉቃስ 3:38; 1 ዜና 28:6; ዘፍጥረት 6:2; ኢዮብ 1:6.

55. ሮሜ 8:14; ገላቲያ 3:26; መዝሙር 82:6.

56. ማቴዎስ 8:26 – 27; ሉቃስ 4:38 – 41; 7:14 – 15; 8:24 – 25.

57. 3:49.

58. ዮሐንስ 10:32 እና 5:19 በተከታታይ.

59. ዮሐንስ 5:23.

60. ዮሐንስ 20:28.

61. ዮሐንስ 1:1 – 3.

62. በትክክል ለማስቀመጥ "ከአላህ የሆነ ቃል" ይላል፡፡ ሙስሊሞች ባጠቃላይ የትኛውንም ማዕርግ አይቃወሙም፡፡ 3:45.

63. አምስት ሺህዎቹን መመገብ፡፡

64. ይህንን ሙግት የበለጠ ለማወቅ Bart Ehrman, *The New Testament: AHistorical Introduction to the Early Christian Writings*, 5th ed. (New York: Oxford University Press, 2011) ይመልከቱ፡፡

65. ማርቆስ 14:62.

66. ኢየሱስ "አዎን እኔ መሲሁ ነኝ" ብሎ መናገሩ ስድብ አይደለም፡፡ ራሳችሁን የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ነኝ ወይም የአንዲት ቤተ ክርስቲያን ፕሬዚዳንት ነኝ ብላችሁ ብትጠሩ ስድብ እንደማይሆን ሁሉ መሲሁ ብላችሁ መጥራትም እንደ ስድብ ሊቆጠር አይችልም፡፡ላትሆኑ ትችላላችሁ ነገር ግን እንደርሱ ብላችሁ ራሳችሁን መጥራታችሁ ብቻውን ከስድብ አይቆጠርም፡፡ ሕገ ወጥ የሚያደርገው ምንም ነገር የለም፡፡ ራሳቸውን መሲሁ ብለው የጠሩ ወይም በአይሁድ መሪዎች መሲሁ ተብለው የተጠሩ አይሁድ ነበሩ፡፡ መሲህ ማለት የሕዝቡ መሪ ማለት ነው፡፡ እንዲያ ማለት ስድብ አይደለም፡፡ (Bart Ehrman, *HistoricalJesus*, The Great Courses, course 643, lesson 21, 24:42 – 29:06, *http:// www.thegreatcourses.com/tgc/courses/course_detail.aspx?cid=643*).

67. Craig Blomberg, *Jesus and the Gospels* (Nashville: B&H Academic, 1997), 342 – 43.

68. በዚህ ማጠቃለያ ውስጥ እንደ ቅድመ ሁኔታ የተያዘው በአይሁድ ሃይማኖት ውስጥ ፈጣሪ አንድ የመሆኑ ሁኔታ ነው፡፡ አምላክ መሆኑን በመናገሩ ኢየሱስ የያሕዌ ማንነት አካል መሆኑን ተናግሯል፡፡ ለበለጠ መረጃ Richard Bauckham, *God Crucified: Monotheism and Christology in the New Testament* (Grand Rapids, MI: Eerdmans, 1999) ያንብቡ፡፡

69. መዝሙር 110:1 በአዲስ ኪዳን ውስጥ ወደ 20 ጊዜ የተጠቀሰ ሲሆን ከየትኛውም የብሉይ ኪዳን ክፍል ልቅ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተደጋገመ ነው፡፡ የቀደሙት ክርስቲያኖች ስለ

ኢየሱስ ባላቸው አመለካከት ላይ ጉልህ ተፅዕኖ እንዳሳደረ ያመለክታል፡፡

70. ፍሊጵስዩስ 2:6 – 7፡፡

71. 1 ቆሮንቶስ 8:6 እና ዘዳግም 6:4; ለበለጠ መረጃ Bauckham, *GodCrucified* ያንብቡ፡፡

72. ማቴዎስ 5:17.

73. በዮሐንስ 20:17 ላይ የሚገኘውን የኢየሱስን ንግግር ከአውድ በማውጣት ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ መጠቀም፡፡

74. ገላትያ ፤፡8 ላይ የሚገኘውን ቃል ጳውሎስ የራሱን ወንጌል እንደፈጠረ እንደሚናገር በማስመሰል በተሳሳተ መንገድ መተርጎም፡፡

75. 2 ቆሮንቶስ 11:23 – 27.

76. 5:73, 116; እንዲሁም 5:116 ሥላሴ ማለት አላህ፣ ልጁ ኢየሱስ እና እናቱ ማርያም እንደሆኑ በማስመሰል የሚያቀርብ ይመስላል፡፡

77. 2:256.

78. 9:5.

79. በኢብን ሒሻም ማስታወሻ ውስጥ ይገኛል፣ Guillaume, *Life of Muhammad*, 691.

80. ይህ ከመጽሐፍ ቅዱስ መርጦ ከመጥቀስ የተለየ ነው፡፡ክርስቲያኖች አጠቃላዩን መጽሐፍ ቅዱስን ትክክለኛ እንደሆነ ያምናሉ፡፡ ነገር ግን ብዙ ሙስሊሞች አብዛኛው ሐዲስ ትክክል እንዳልሆነ ያምናሉ፡፡ስለዚህ ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚጠቅስ ወጥ አቋም ያለው ሰው እርስ በርሳቸው የሚጣረሱትን ክፍሎች ማስታረቅ መቻል ያስፈልገዋል፡፡ ነገር ግን የሐዲስ ጽሑፎች እንዲያ አይደሉም፡፡በተጨማሪም የሐዲስ ጽሑፎች ሰፊና አሰልቺ ናቸው፡፡ አንዱ ስብስብ እንኳ ፱ ቅፆችና ከዚያ በላይ አሉት፡፡ስለዚህ ከሐዲስ መርጦ በተሳሳተ መንገድ መተርጎም ቀላል የሆነውን ያህል ከመጽሐፍ ቅዱስ እደርሱ ማድረግ ቀላል አይደለም፡፡

81. Guillaume, *Life of Muhammad*, 676. See also Ibn Sa'd, *Kitab al Tabaqat*

82. Guillaume, *Life of Muhammad*, 464.

83. 33:50.

84. Sahih Bukhari 7.62.64; 7.62.65; 7.62.88; Sahih Muslim 8.3310;

8.3311.

85. Nujood Ali, *I Am Nujood, Age 10 and Divorced* (New York: Three Rivers Press, 2010) ይመልከቱ፡፡

86. Sahih Bukhari 3.47.786.

87. Sahih Bukhari 5.59.713.

88. Sahih Bukhari 4.54.490.

89. Guillaume, *Life of Muhammad*, 165 – 66.

90. ዝኒ ከማሁ 515.

91. Sahih Bukhari 1.11.584.

92. ቁርአን 33:37; Sahih Muslim 8.3330; Tabari, vol. 8, pp. 2 – 3.

93. Sahih Bukhari 8.82.794; Sahih Muslim 16.4130.

94. ለዚህ ነው ይህ መጽሐፍ መጽሐፍ ቅዱስን በመጠቀም ለክርስትና የሙግት ሐሳቦችን ያላቀረበው፡፡ ለአንዳንዶች ከመጽሐፍ ቅዱስ ይልቅ በቁርአን ላይ ጥልቅ ምርመራ እንደተደረገ ሊመስላቸው የሚችለው ለዚህ ነው፡፡ሆኖም ይህ ሁለት ዓይነት ሚዛኖችን መጠቀም አይደለም፡፡ ንፅፅሩ መደረግ ያለበት በቁርአንና በኢየሱስ አምላክነት/ ትንሣኤ መካከል ነው፡፡ ሁለተኛው ርዕስ የመጀመርያውን ያህል በጥልቀት ተመርምሯል፡፡

95. 2:23; 10:38; 11:13; 17:88; 52:34.

96. የቁርአን ሌላኘው ስም “አል ፉርቃን” የሚል ነው፡፡ የመጽሐፉ ርዕስ *እውነተኛው ፉርቃን* መሰኘቱ በራሱ የቁርአንን የበላይነት የሚገዳደር ነው፡፡

97. Notification No. 78, September 7, 2005, from Anupam Prakash, Under

Secretary to the Government of India, accessed July 1, 2013, *http://www .cbec.gov.in/customs/cs-act/notifications/notfns-2k5/csnt78-2k5.htm*.

98. Maurice Bucaille, *The Bible, The Qur’an, and Science: The Holy ScripturesExamined in the Light of Modern Knowledge*, 7th rev. exp. ed. (Elmhurst, NY: Tahrike Tarsile Qur’an, 2003), 218.

99. Bucaille, *The Bible, The Qur’an, and Science*, 214.

100. Ibid., 215.

101. “Belief in Divine Books,” WhyIslam.org, accessed July 1, 2013, *http://*

*www.whyislam.org/submission/articles-of-faith/belief-in-divine-books*.

102. ቃል በቃል ያልተጠቀሱት በዚህ አንቀፅ ውስጥ የሚገኙት መረጃዎች ሁሉ ሳሂህ አል ቡኻሪ ውስጥ የሚገኙ ናቸው፡፡

103. Sahih Bukhari 9.84.59.

104. Sahih Muslim 5.2286.

105. Sunan ibn Majah 1944.

106. Suyuti, *Al Itqan fi Ulum al-Qur’an*; Ibn Abi Daud, Kitab al-Masahif.

107. Ibn Abi Daud, *Kitab al masahif*, found by Arthur Jeffery and catalogued in his work *Materials for the History of the Text of the Qur’an*.

108. Sahih Muslim 8.3432.

109. Sunan Abu Daud 11.2150.

110. Tafsir ibn Kathir.

111. Sahih Bukhari 5.59.459.

112. Sahih Muslim 8.3371.

113. 5:33; “በምድር ላይ የሚያበላሹ” የሚለው *ፍሳዳ* የሚለውን የአረብኛ ቃል ይወክላል፡፡ ትርጉሙም “ስርአት አልበኝነት” የሚል ነው፡፡

114. ለምሳሌ Sahih Bukhari 9.84.57 – 58, 64, 72 ይመልከቱ፡፡

115. “አላህ ሆይ በስምህ እኖራለሁ እሞታለሁም” የሚል ትርጉም ያለው ጸሎት ነው፡፡

116. Sahih Muslim 35.6475.

117. ሉቃስ 13:22 – 25, 28 – 29፡፡